ማኅደረ ሥዕላት ጥሪቱ

ኦቦቃ



ዓርትም ጀሚል ሀሰን ሁሴን

t.me/OLDBOOKSPDF

ለወ·ድ አባ·ቴ ለሀጅ ሱ·ልጣን ኢ·ሳ አል·ቃጥባሪ
ለ·ታ·ላቁ ·ተክለ–ሰው·ነ·ታ·ቸው·
መ·ታ·ሰቢ·ያ ይሁ·ን

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አንድ

ትናንት ማታ ማንደርሌይ ብቅ ብዬ ነበር ። መች በእውኔ ሆነና? — በህልሜ እንጂ ። የብረት መዝጊያውን ተጠግቼ የቆምኩ ይመስለኛል ። ተንጠልጣዩ ቁልፍ ያነሰ ይመስል መዝጊያው በሰንሰለት ጭምር ተከር ችሞ ወደ ውስጥ መዘለቅ አልቻልኩም ። ዋርዲያውን ብጣራ አቤት ባይ ስላጣሁ በዛጉት የመዝጊያው ዘንጎች መካከል አሻግሬ ሙሪያ ገባውን ቃኘሁ ። የሚላወስ ህያውት አልታይሽ አለኝ ።

ጢስ መውጫው ምንም አይተንበትም ። ትናንሾቹ ባለጌዋ መስኩ ዶች ሲያዛጉ ሳያቸው የአስታዋሽ ያለህ ብለው የሚያላዝኑ መሰሉኝ ። ማንኛውም አላሚ እንደሚገምመው ሁሉ አንዳች ልዕለ—ተፈጥሯዊ ሃይል አሽቀንጥሮ ከግቢው አስገባኝ ። ጥቂት እንደተራመድኩ መንገዱ ጠቦ ፡ አካባቢው ሁሉ እንክብካቤ ጎድሎት ታየኝ ። ይህኔ ነው ፡ ማን አማዶኝ ባይዋ ተፈጥሮ ውስጣዊ ተንኮሏን መሸረብ መጀመሯን የተገነዘብ ኩት ። እንዲያ እየተንከባከብናቸው እንኳ ወትሮውኑ ያስቸግሩን የነበሩት እፅዋት ዛሬ የሚቀነጣጥሳቸው በሉለበት ረጃጅምና ቆልማማ ጣዮቻቸ ውን እየዘረጋጉ መውጫ መግቢያውን ጭምር አጥረውታል ። ድሮ የማውቃቸው የዛፍ ዐይነቶች ከአዳዲሶቹ ጋር እጅ ለእጅ ተቆላልፈው አንዳሻቸው ተንሰራፍተዋል ።

ከሳር ቅጠሉና ከቁጥቋጦው ጋር እየታገልኩ እንደምንም ተፍጨር ጭሬ ከቤቱ ደረሰኩኝ ። ቆም ብዬ ስመለከት አይኖቼ ድንገት በእንባ ጭጋግ ተጋረዱ ። ልቤ ደረቴን ፈንቅሎ ለመውጣት ግብ ግቡን ተያያዘው።

ማንደርሌይ የትናንት ግርማ ሞገሱን እንደተነናፀፈ ከፊቴ ተደቀነ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደ እውኑ አለም ሁሉ በህልሙም አለም ቢሆን ልዩ ተአምራዊ ጥበብ የመሥራት ክህሎቱ ያላት ጨረቃ ብርሃኗን እቤቱ ላይ ፈንጥቃ አድምቃዋ ለች ። የሰገነቱንና የመስኩን ምስሎች በመስኩቱ መስተዋት ውስጥ ተንፀባርቀው ሳያቸው ማንደርሌያችን ወናውን የተገተረ ቀፎ መሆኑ ቀርቶ እንደ ቀድሞው ሁሉ ህያውት ህያውት ይሸተኝ ጀመር ።

መለስ ወደ ቀኝ ፡ ቀለስ ወደ ግራ! መስኩን አሻግሬ የወረወርኩት አይኔ የጨረቃዋ ብርሃን የነጠረ ብር የፈሰሰበት ካስመሰለው ባህር ላይ ተማርኮ ቀረ ። ከምርኮ አላቅቁ ወደ ሌላ አቅጣጫ ሳዞረው ያረፈበት አፀድ አረም ውጦት በማየቱ በእጅጉ አዘንኩ — በገንኩም ። ያን በመሰለ ውብ አፀድ ላይ ቅጥ የለሽ ቅጠላ ቅጠሎችና መልክ ቢስ ስራስሮች ገንውበት ያሸፉብኛል ።

ወደ ውስጥ ገባሁ ። መስኮቶቹን ዘልቆ ቀድሞኝ የገባው ብርሃን ቤቱን ሞልቶታል ። በንፋሱ የሚራገቡት መጋረጃዎች ዳንኪራ የሚለማመዱ ይመስላሉ ። የቤተ መፃህፍቱ በር እንደዚያው ፡ እኛ እንደተውነው ገርበብ እንዳለ ነው ። መሀረቡም ጠረጴዛው ላይ ነው ። መጽሀፍ ፡ የታይምስ ጋዜጣ ፡ መተርኮሻው…ሁሉም ነገር እንደነበር መኖሩ ቤቱን ጥለን ላለመሄዳችን ምስክርነት መቆሙ ይመስላል ።

የምንወደው ውሻችን ጀስፐርንም አየሁት ። ረጅሙን አገጩን ወለሉ ላይ አስደግፎ ፡ ውብ አይኖቹን ያተረጠርጣል ። የጌታውን ድምፅ ሲሰማ ጭራውን እየወዘወዘ ብድግ ሲል ታየኝ ።

ከባድ ደመና ከየት መጣ ሳይባል ጨረቃዋን አለበሳት ። ጨለማው ብርሃኑን ሲውጠው ደስታዬንም አንዳች ሰለቀጠው ። ሁሉም ነገር ወጥ እርጭ አለ ። ሹክሹክታ የለ ፡ ኮሽታ የለ ። ዙሪያዬ ድንገት ባዶ ሆነብኝ ። ውስጤንም ባዶነት ወረረው ። ህልሜም አከተመ ።

በህልሜ ማንደርሌይ ገብቼ ስሽከረከር በእውኔ ግን እጅግ በጣም ርቄ ከአንድ የባእድ አገር ነው ያለሁት — በአንዲት ትንሽ አልቤርጎ ውስጥ ተኮራምቼ ተኝቼ ።

የማለዳ ፀሐይ በህልሜ ካየሁት የጨረቃ ብርሃን በተለየ መልክ በጠራው ሰማይ ላይ መንጎማለል ስትጀምር ያንን አሰልቺና የማይገፋ ቀን ለመጋተር ተነስተን ደፋ ቀና ማለታችን አይቀርም ። ይሁን እንጂ ህልም ማየቴን እንኳን አልነግረውም ። ስለ ማንደርሌይ ማውራት ካቆምን ጊዜም የለው ። ማንደርሌይ የኛነቱ አክትሞለታልና ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ትዝታው ያየለው በኔ ላይ ነው እንጂ እርሱ እንኳን ጠንካራ ነው ። ታጋሽነቱና ፈፅሞ አለማማረሩ በጣም ይደንቀኛል ። ያለፈው ትዝታ ሳይዳስሰው ቀርቶ አይደለም ። ስሜቱን ለመቆጣጠር ከራሱ ጋር ብርቱ ፍልሚያ እያደረገ እንጂ ። አንዳንዴ በሀሳብ ጭልጥ ብሎ ሲነጉድ አየዋለሁ ። ሲጋራውን እላይ በላዩ ያቀጣጥለዋል ። በጨዋታ መሃል አንዱን ርእስ ይይዝና እልባት ሳያበጅለት ወደ ሌላው ይዘላል ። ይህን ጊዜ ነው በትዝታ ፈረስ ሽምጥ እየጋለበ መሆኑን የማውቅበት ።

ከሁሉም በላይ እንደ ውስጥ እግር እሳት የሚለበልበን የሀገር ናፍቆር ስሜት ነው — ናፍቆቱ ። ወንዝ ጅረቱ ይናፍቀናል ። ሜዳ ሸንተረሩ ይመጣብናል ። ሳር ቅጠሉ ድቅን ይልብናል ። ይበልጥ ደግሞ ወገን ፡ የወንዝ ልጅ ትንፋሹ ይሞቀናል ። ድምፁ ይጠራናል ፡ ጠረኑ ይሸተናል ። ሁሉም እረፍት ይነሱናል ። ይህን መሰሉን ሀያል ናፍቆት የምንወጣው የእንግሊዝ ጋዜጦችን በማንበብ ነው ። ጋዜጦች ለአንድ ቀን እንኳን ቢተኙሉብን ጭንቅ ጥብብ ይለናል ። ስለ ክሪኬት ጨዋታዎች ፡ ስለ ተማሪዎች ስፖርታዊ ውድድር ፡ በአጠቃላይ ስለ ጥቃቅን ጉዳዮች ሁሉ ስናነብ ልባችን ይሸፍታል ። የናፍቆት ጥማችንን አረካን ባልን ቁጥር እንደገና እያየለብን መታጠል ነው ። ይህ ነው እኔና ማክሲም በስፋት የምንጋራው ስሜት ።

የኔ ሀሳብ ደግሞ ብሄራዊ አድማሱን አጥብቦ ማንደርሌይ ሲገባ ይህን ይመስላል ። የግቢው አጠቃላይ መልክ ፡ የድኑና የአዐዲቹ ውበት ፡ የአእዋፍ ጣእመ—ዜማ ፡ ሌላ ሌላውም ውልብ እያለ ያስቸግረኛል ። እንበላው የነበረ ምግብ ሽታው አፍንጫዬን ሰርስሮ እየገባ ፡ የቅምሻ እጠዎቼን እየቀሰቀሰ የአፌን እልፍኝ በምራቅ የሚያጥለቀልቅበት ጊዜ ጥቂት አይደለም ። በየእለቱ ይቀርብልን የነበረው ምግብ ከአይነቱ የጥራቱ ነገር ይገርመኛል ። ይልስ ይቀምሰው አጥቶ ረሀብ ለቆላው ምስኪን ቤተሰብ ሳምንት መቀለብ የሚችል ያ ሁሉ የተትረፈረፈ ምግብ ለኛ ለሁለታችን ብቻ መቅረቡ የምን አባካኝነት ነው? ያስብለኝ ነበር ።

ይሁን እንጂ ከማእዱ የሚመለሰውን ምግብ ምን እንደሚያደርጉት ሚስዝ ዳንሸርስን ለመጠየቅ ድፍረቱ አልነበረኝም ። ጠይቂያቸው ቢሆን ኖሮ በንቀት እንዲት እንደሚመለከቱኝና ያንን አሽፈ ጥርሳቸውን ብልጭ አድርገው "ሚስዝ ደዊንተር እንዲህ አይነቱን ጥያቄ አንስታም

t.me/OLDBOOKSPDF

አታውቅ…” ይሉኝ እንደነበር በምናቤ ይታየኛል ። አሁን እኒያ አሮጊትና ያ ፌቭል ምን እየሰሩ ይሆን? መቼም አሮጊቷን ለመጀመሪያ ጊዜ ሳያቸው ነበር አስተያየታቸው ያስደነገጠኝ ። “ከርብቃ ጋር እያወዳደሩኝ ነው እንዴ?” የሚለው ሀሳብም ያደረብኝ ገና ከጅምሩ ነበር።

እድሉን ነፍገነው እንጂ እንዲህ አይነቱ ትዝታ ሰላማዊ ኑሯችንን ለማደፍረስ ዘወትር እንደተፈታተነን ነው ። ፍርሀት ምን እንደሆነ ሁለታችንም አብጠርጥረን እናውቀዋለን ። ብቸኝነት ሲያንገላታን ኖሯል። የመከራ ዘር በሙሉ ደቋቅሰናል ። የክፉ እድል እጣ ሁሉ በየመልኩ ተፈራርቆብናል — ጥንካሬያችን በእሳት እስኪፈተን ድረስ ። መከራን የቻለ አሸናፊ ነው የሚለውን ብሂል በገቢር ተርጉመነዋል ባይ ነኝ ።

ዛሬ ግን በጣም ደስተኞች ነን ። ደስታ በገንዘብ የሚሸመት ሳይሆን ከሰዎች አስተሳሰብ ፡ ከአመለካከታቸው የሚመነጭ የውስጣዊ ማንነታቸው ነፀብራቅ ነው ። ለዚህም ነው ዛሬ ባለን አቅም ተብቃቅተን ኑሯችንን በደስታ የምንገፋው ። ለዚህም ነው ከምንጊዜውም ይበልጥ በአካልም በሀሳብም በእጅጉ የተቀራረብነው ። ሀዘን ደስታውን በጋራ ስለምንወጣ አንዱ ከሌላው የሚሸሽገው ምስጢር የለም ።

ይህ የተያያዝነው አዲስ ህይወት በጣም ነው የቀየረኝ ። ልዩ ሰው እያደረገኝ ነው ። ፍራቻን ፡ መሸቆጥቆጥንና አይን አፋርነትን አውልቄ ጥዬአቸዋለሁ ። ከሁሉም በላይ ከፍተኛ ግምት የምሰጠው ከጊዜ በኋላ ላዳበርኩት በራስ የመተማመን ችሎታዬ ነው ። ይህንን ባህሪይ ያጎናፀፈኝና ልቤን በድፍረት የሞላው እርሱ የኔ ጥገኛ እየሆነ መሄዱ ይመስለኛል። ማንደርሌይ ለመጀመሪያ ጊዜ ስገባ የነበረኝና የዛሬው አስተሳሰቤም ሆነ ጥንካሬዬ ጭራሽ የተለየ ነው ። በዚህ ጤናማ ለውጥ በእጅጉ የመደሰቱን ያህል ያኔ በሚስገ ዳንሸርስና በብጤዎቻቸው ያስናቀኝና መዘባበቻ ያደረገኝ አንጉቱን መድፋቱ መሆኑ ሲታወሰኝ ብስጭትጭት ያደርገኛል።

የቀድሞ መልኬ ፡ አለባበሴና የወገር አሰራሬ ምን ይመስል ነበር? በአጭሩ የተከረከመ ወገሬን እንደ ነገሩ አበጥሬ ፡ የቅባት ዘር ንብኝቶት የማያውቀው ፊቴ አመድ የተነፋበት እንደመሰለ እላዬ ላይ የተጣበቀውን ትንሹን ኩቴን መናኛ ቀሚሴ ላይ ደርቤ እንደ ድንጉጥ ውርንጭላ የሚስገ ቫን ሀፐርን ጭራ ተከትዬ ሱክ ሱክ ማለቴ ምኔም አይረሳኝ ። እርሳቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

ደግሞ ተረከዘ ረጅሙ ጫማቸው ፡ አጠር ፈርጠም ያለውን ሰውነታቸውን መሸከም ተስኖት እንዴት ይወላገዱ እንደነበረ ትውስ ሲለኝ ሳቁ ይቀድማል ።

የሚስዝ ቫን ሁፐር ጉድ ተወርቶ የሚያበቃ አይደለም ። ሞንቴ ክርሎ በነበርንበት ወቅት ያደርጉት የነበረ ነገር ሁሉ ግርም ይለኛል ። ካረፍንበት ሆቴል ውስጥ ወጭ ወራጁን በደንብ ሊያጠኑ ከሚያስችላቸው ስትራቴጂያዊ ቦታ ይቀመጣሉ ። ከዚያ አጉልቶ የሚያሳይ መነፅራቸውን አውጥተው ምርምራቸውን መጀመር ነው ።

አንድ ቀን እዚሁ ኮት—ደአዙር ሆቴል እንደተቀመጥን በመነፅራቸው ግራ ቀኙን ሲማትሩ ቆዩና "ምን አይነት ጣጣ ነው? አንድም የጨዋ ልጅ የማይታይበት? ኧረ እኔ እቴ ፡ አስተዳደሩ ከሂሳቡ እንዴቀንስልኝ እነግረዋለሁ ። ንሺ እቴ ፡ እዚህ ድረስ የመጣሁት የእነርሱን ቆርፋዳ አሳላፊዎች ፊት ማየት ናፍቆኝ መሰላቸው እንዴ?" አሉ ብስጭትጭት ብለው ።

ይህን በተናገሩ በሦስተኛው ቀን ምግብ አዳራሽ ውስጥ ምሳችንን እየበላን ሳለ አንድ ሰው ጎናችን ከነበረው ወንበር ለመቀመጥ ሲዘጋጅ ያያሉ ። ሹካቸውን ጣል አድርገው መነፅራቸውን ፍለጋ ገቡ ። እንግዳውን አገላብጠው ሲያዩት ለእርሳቸው እኔ አፈርኩላቸው ። የበቃቸውን ያህል ካፈጠጡበት በኋላ ሞንቅላታቸውን ወደኔ አዘነበሉት ። አይናቸውን አቁለጨለጩት ። አፋቸውን አሞጠሞጡት ። "አታውቂውም እንዴ? ማክስ ደዊንተር እኮ ነው ። በመልክ ባታውቂውም ዝናውን እንኳን ሳትሰሚ አልቀረሽም ። የማንደርሌይ ባለቤት ማለት እኮ ነው ። ምን እንዲህ አገረጣው ልጄ? የሚስቱ ሀዘን ገና አልወጣለትም የሚባለው ለካስ…" አሉና ጅምራቸውን አንጠልጥለው አይናቸውን እንደገና ወደ ሰውዬው ላኩት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ ሁለት

ሚስዝ ቫን ሁፐርን መጀመሪያ ያወቅኋቸው ጊዜ ባህሪያቸውን መላመድ አቅቶኝ በጣም ተቸግሬ ነበር ። ሰዎች ከበስተጀርባ ሲስቁባቸው ፣ ገና ብቅ ሲሉ እየተጠቃቀሱ ሲንሽኳሽኩባቸው ሳይ ስቅጥጥ ይለኝ ነበር ። እርሳቸው እንደሆን ምኞታቸውን ለማሳካት ይሉኝታ የሚሉት ነገር ሲያልፍም አይነካቸው ። "የኛ" የሚሏቸውን መኳንንቱንና ወይዛዘርቱን ሲክቡ ለኛ ድሮ ነው ። ተራውን ሰው ሲያጥላሉና ሲዘረጥጡ ለነገ አይሉም ። ስመ ጥር የሆኑ ሰዎችን ለመተዋወቅ ልዩ ዜዴ አላቸው ። ስማቸውን ጋዜጣ ላይ ካይዋቸው ደራስያን ፣ ሠአሊያን ፣ ተዋንያንና መሰል እውቅ ሰዎች ጋር ለመገናኘት የማይበጥሱት ቅጠል የለም ።

የዚያን እለትም አለወትሮአቸው ምሳቸውን በጊዜ ቀማምሰው ወደ ሶፋቸው የተጣደፉት እንግዳውን ሰውዬ ለማጥመድ እንዲያመቻቸው መሆኑን ነቅቼባቸዋለሁ ። ወዲያውኑ "እስቲ ፊጠን በይና ያንን የእህቱ ልጅ የፃፈልኝን ደብዳቤ አምጪልኝ ። ታውቂው የለ? ያኔ በሰርጉ ሰሞን ከነሮቶግራፉ የላከልኝን ነው የምልሽ ።" አሉኝ ።

መጣቢያ ቀዳዳቸውን አያዘጋጁ መሆኑ ገባኝ ። ደብዳቤውን ለማምጣት በመሄድ ላይ ሳለሁ "እሁን ይህንን ሰው ባያስቸግሩት ምን አለ?" የሚል ሀሳብ አደረብኝ ። ለአጭር ጊዜም ቢሆን እንግዳውን ገበታ ላይ እንዳየሁት ይህን መሰሉን ግንኙነት የሚፈቅድ አልመሰለኝም ። ምንነቱ ለራሴ ለገባኝ ያልቻለ ስሜት ለሰውዬው እንዳዘንለት ገፋፋኝ ። በጓሮ በር ወደ ምግብ አዳራሹ ገብቼ ስለ ተዘረጋለት ወጥመድ እንድነግረውም ጻድቶኝ ነበር ። ከሥነ - ምግባር ውጭ እሆናለሁ የሚለው ሀሳብ ግን

t.me/OLDBOOKSPDF

በጣሙን ተጫነኝ ። ሁሉን ትቼ ፡ ድፍረቱን እንኳን ባገኝ ፡ በምን መልክ እንደማናግረው ግራ ግብት አለኝ ። ያለኝ አማራጭ እንደፈረደብኝ አሮጊቷ ጎን ቁጭ ብዬ እርሳቸው እንደ ኩሩ ሽረራት ያንን ሙዝዝ ያለ ድራቸውን በሰውዬው ላይ ሲያደሩ መታዘብ ብቻ ነው እያልኩኝ ደብዳቤውን ይዤ ተመለስኩ ።

አሮጊቷ ምናቸው ሞኝ! የደብዳቤውን መምጣት ሳይጠብቁ ሰውዬውን እጎናቸው አስቀምጠው ይነዘንዙታል ። ደብዳቤውን ሰጠኋቸው ። እንግዳው እኔን አክብሮ ብድግ ብሎ መቆሙ በጣም ደነቀኝ ። ሚስዝ ቫን ሁፐር ፍንድቅድቅ ማለታቸውን ሳይ ሴራቸው እንደሰመረላቸው ተረዳሁ። ስሜን ጠርተው ፡ "እስቲ ሄደሽ ለሚስተር ደዊንተር ቡና እዘገርለት" አሉኝ እኔን በሚያናንቅና እራሳቸውን ከፍ ከፍ በሚያደርግ አኳኋን ። የለመድኩት ጠባያቸው በመሆኑ እምብዛም ባይደንቀኝም የወቅቱ አብይ አላማቸው ጭውውታቸውን እንዳልሰማ ሆን ብለው ማባረራቸው እንደ ሆነ መገንዘቡ አላዳገተኝም ።

"ይቅርታ ያድርጉልኝና ቡናውን ከሁለታችሁም ጋር አብረን ብንጠጣው ደስ ይለኛል ።" አለ እንግዳው እዚያው እቆመበት ለአሳላፊው ምልክት እየሰጠው ። እንደቆመ መቅረቱ ሲገርመኝ ይባስ ብሎ ሰፋ-ውን ለቄ ለቄ ደረቅ ወንበሩ ላይ ተቀመጠ ።

ሚስዝ ቫን ሁፐር ሁኔታው ከመጠን በላይ እንዳናደዳቸው ከገፅታቸው ይነበብ ነበር ። እንዳይታወቅባቸው እንደምንም እራሳቸውን ተቆጣጠሩና ወደ እንግዳው ዘወር ብለው "ግና ወደ ምግብ አዳራሹ ብቅ ስትል እኮ ነው ያወቅኩህ" አሉት ። አያይዘውም "ይሄ የቢሊ ጓደኛ ሚስተር ደዊንተር አይደለም እንዴ? ቆይ የቢሊንና የሙሽራውን ፎቶግራፍ አሳየዋለሁ ብዬ አሰብኩ ። እኚው ልህ እኮ ፡ ዶራ ቆንጅዬ ልጅ አይደለችም? የሽንጢ ቅጥነት ፡ የአይኗ ጎላ ጎላ ማለት ፡ እጇን ታጥቦ የሰራት ናት ። አየሃቸው? ከባህሩ ዳርቻ ወሀይ እየሞቁ እኮ ነው ። መቼም ቢሊ እብድ ፡ ከንፍ እንዳለላት ከፎቶግራፉ ሳትረዳ የምትቀር አይመስለኝም ። ክላሪጅ ውስጥ ቢሊ ግብግ አድርጎ በነበረበት ወቅት እንኳን ከዶራ ጋር አይተዋወቁም ነበር ። አንተንም እኮ ያኔ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ ያያሁህ ። እኔ ይኸው ልህ ጭራሽ አልረሳም ። የስንት አመቱ ነገር ልክ ዛሬ እንደተደረገ ቁልጭ ብሎ ነው የሚታየኝ...አንተስ አስታወስከኝ? ግን የኔ

t.me/OLDBOOKSPDF

ብጤዋን አሮጊት ምን ልታደርግልህ ታስታውስና" በማለት ጥርሳቸውን ብልጭ አድርገው የጎንዮሽ አዩት ።

"እሪ በሚገባ አስታውሶታለሁ" አለና በነገሩ ይበልጥ እንዳይገፋበት የፈለገ ይመስል ፓኬቱን አንስቶ ሲጋራ ጋበዛቸው ። ቀና ብዬ ሳየው ፊቱ ልዩ የመሳብ ሀይል ያለው ፣ አንዴ — በየትኛው የስዕል አዳራሽ እንደሆነ እንኳን ረስቼዋለሁ — ያየሁትን "የማይታወቀው ሰው" የሚለውን ስዕል መስሎ ታየኝ ። በዚህ ሀሳብ ሰጥሚ ሳለ የጭውውታቸው ውሉ ቢጠፋኝም "አይ ፣ ከሀያ አመት በፊትም ቢሆን ለእንደዚህ አይነቱ ነገር ደንታም አልነበረኝ" ሲል ሰማሁት ።

ሚስዝ ቫን ሁፐር ሻካራ ሳቃቸውን ለቀቁትና "ቢሊ እኮ ማንደርሌይን የመሰለ ቤት ቢኖረው እዚያ ፖልም ቢች ውስጥ ባልተጨማለቀ ነበር። መቼም ሰው ማንደርሌይን ሲያደንቅ ለጉድ ነው ። የምድር ላይ ገነት ነው ይለዋል" አሉት ። ፈገግ ይልልኛል ብለው ሲጠብቁ ከነአካቴው ቸል ብሏቸው ሲጋራውን ሲምግ "በእርግጥ ፎቶግራፉን እንኳን አይቼዋለሁ ። እንደሚወራለትም ግሩም ፣ ድንቅ ቤት ነው ። ቢሊም ስለ ትልቅነቱና ስለ ውበቱ ያጫወተኝ ነበር ።" በማለት አሁንም አይኑን በአይናቸው ለማባበል ሞከሩ ።

እንደገና ዝም ማለቱ ውይይቱን ለመቀጠል አለመፈለጉን ግልፅ ቢያደርገውም ቅሉ አሮጊቷ በውትወታቸው መግፋታቸው እኔን አሳፈረኝ ። እንዲሁ የቆጥ የባጡን ሲዘባርቁ ፣ እንቶ ፍንቶውን ሁሉ እያነሱ ሲጥሉ ፣ በማያውቁት ገብተው ሲፈተፍቱ ብዙ ታገሳቸው ። የማይመስልና የማይሆን ነገር መቀባጠሩን ሲያበዙት "አይ..." በማለት በትህትና ስህተታቸውን ለማሳየት ሞከረ ። እርሳቸው ግን ምንም ሳይመስላቸው በመለፍለፉ ገፉ ። ሁኔታው እረፍት እንደነሳኝ ከመቁነጥነጤ ገባው መሰለኝ ወደ እኔ መለስ ብሎ ቡና መድገም እፈልግ እንደሆነ በለዘብታ ጠየቀኝ ። አለመፈለጌን በጭንቅላቴ ንቅናቄ ገልጨለት ቀና ስል አይኖቹ እኔ ላይ እንደተተከሉ መቅረታቸውን አየሁ ።

"ለመሆኑ ሞንቴ ካርሎን ወደድሽው?" ሲለኝ ክው አልኩ ። ያልጠበቅኩት በመሆኑ ምን ብዬ እንደምመልስ ግራ ቢገባኝ እንደመጣልኝ "አዎን ፣ ብቻ ስፍራው ሰው ሰራሽ ይመስላል..." ከማለቴ ሚስዝ ቫን ሁፐር አቋረጡኝና "ይቸውልህ ፣ እንዲህ ብልሽትሽት ያሉች ልጅ እኮ ናት ። ስንት ቆነጃጅት አይኖቻችንን መስዋእት አድርገን እንኳ አንዴ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሞንቴ ካርሎን ባየነው ይላሉ…” ሲሉ እንግዳው ፈገግ ብሎ “እንዴት ጥሩ አድርገው አዩት!” አላቸው ። አባባሉ ዘልቆ የገባቸው አልመሰለ ኝም። መለፍለፋቸውን አላቋረጡምና ።

በዚህ መሃል አንድ ተላላኪ መጥቶ ሚስዝ ቫንሁፐርን ልብስ ሰፊያቸው እንደምትጠብቃቸው ነገራቸው ። ለሚስተር ደዊንተር ታላቅ የምስራች ነበር—የእፎይታ ። ብድግ ብሎ “እንግዲህ ጊዜዎን ከምሽማ ብሄድ መልካም ነው ። የዘመኑ ፋሽን ደግሞ በየሰአቱ ሆኗል የሚቀያየ ረው። ምናልባት ፎቅ እስኪወጡ ድረስ ቅይርይር ብሎ ሊጠብቅዎት ይችላልና ፈጠን ይበሉ ፣ የኔ እመቤት” አላቸው ።

አሽሙሩ ጭራሹን አልተሰማቸውም ። እንዲያውም በደስታ ነው የተቀበሉት ። በማግስቱ እከፍላቸው ድረስ እንዲመጣ ቢጋብዙት እንደማይመቸው ነገራቸው ። ስለ መኝታ ክፍሉ ፣ ስለ ግል ተላላኪው ብዙ ጠያየቁት ። “የግል አገልጋይ እንኳን የለኝም ። እርስዎ በዚህ ሊተባበሩኝ ይችሉ እንደሆን?” ሲላቸው ፊታቸው ወዲያው ቅይርይር ብሎ አፋቸውን አጣመሙት—የግዳቸውን ፈገግ እንደ ማለት ብለው “እንዴ ፣ ይህ እንኳን …” አሉና ድንገት ፊታቸውን ወደኔ መልሰው “አንቺ ፣ ሚስተር ደዊንተር አንዳንድ ነገሮች ቢፈልግ እንድትረጂው” አሉኝ ።

“ለድንቅ ሀሳብዎ አመስግናለሁ ። ግን የዘመዶቼ መርህ ምን እንደሆነ ያውቃሉ? መንገድ የሚቀላጠፈው ሉብቻ ሲጓዙ ነው የሚል አባባል አላቸው ።” አሉና መልሳቸውን ሳይጠብቅ ሹልክ ብሎ ወጣ ።

“ጉድ እኮ ነው! ሳይሰናበተን እንዲህ ውልቅ ማለቱ ለቀልድ ያለው ይሆናል እንጂ ሆን ብሎ ያደረገው አይመስለኝም ። አንዳንድ ሰዎች እኮ እንዲህ ያለ ግር የሚያሰኝ ባህሪይ አላቸው ። ድሮ አንድ እውቅ ደራሲ ድንገት ፊት ለፊት የተጋጠምን እንደሆን መንገድ አሳብሮ ይሄድ ነበር ። እርሱ እንኳን ድፍረቱን አጥቶ እንጂ ፍቅር ብጤ ሳይዘው የቀረ አይመስለኝም ። ያኔ ደግሞ ገና ለግላጋ ወጣት ስለነበርኩ …” አሉኝ በአሳንስሩ ወደ ፎቅ እየወጣን ሳለን ።

ወደ ክፍላችን ስናመራ “በነገራችን ላይ ፣ ዛሬ ምንድን ነው የነካሽ በጨዋታችን መሃል ጣልቃ እየገባሽ እንዲያ ማወክሽ ግርም ነው ያለኝ ። እርሱም ቢሆን በደንብ ነው የታዘበሽ ። ወንዶች ደግሞ እንዲህ አይነቱን ነገር እንደማይወዱ ማወቅ አለብሽ” ሲሉኝ መልስም አልሰጠኋቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

“አይ እንግዲህ ፡ እኔ ለክፋት ያልኩት ሳይሆን ላንቺው ብዬ ነው ። ሊከፉሽ አይገባም” አሉኝና ትከሻቸውን ነቅንቀው ፈገግ አሉ ። “ደግሞም እኮ የእናትነት ምክሬን ልትቀበይ ይገባል ” ብለውኝ እያንጎራጎሩ ወደ መኝታ ክፍላቸው ገቡ ።

መኝታ ክፍሌ ውስጥ ሆኜ ሀሳብ በየመልኩ ሲመላለስብኝ ከቆየ በኋላ እርሳስና ወረቀቱን ይዤ ስዕሌን መሞነጫጨር ጀመርኩ ። በሩ ተንኳኩቶ ተላላኪው ብቅ ሲል አይኔ ያረፈው በያዘው ወረቀት ላይ ነበር ። “እሚቴ መኝታ ክፍላቸው ውስጥ ናቸው ።” ስለው መልእክቱ ለኔ መሆኑን ነግሮኝ ፖስታውን ሰጠኝ ። ስሜ እላዩ ላይ መኖሩን ሳረጋግጥ ከፍቼ አነበብኩት።

“ዛሬ ተገቢ ያልሆነ ባህሪይ በማሳየቱ በእጅጉ ተሰምቶኛልና ይቅርታሽን እጠይቃለሁ ።” ይላል የፀሀፊው ስም ያልሰፈረበት መልእክት ።

“መልስ ይኖርዎታልን?” ሲል ጠየቀኝ ልጁ

“አይ ፡ የለኝም” አልኩትና ማስታወሻውን አጣጥፌ ኪሴ ውስጥ አኖርኩት ።

ወደ ስዕሌ አይኔን ስመልስ የሳልኩት አላረካሽ አለኝ ። ዝጋታም... ህይወት አልባ...ጨጎጎት ፊት...

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ ሦስት

በሦስተኛው ቀን ሚስዝ ቫን ሁፐር እንፍሉዌንዛ ብጤ ያዛቸውና ከአልጋ ዋሉ ። ዶክተራቸው እረፍት እንዲያደርጉ ፣ ልምድ ያላት ነርስ በቅርብ እንድትከታተላቸው አዘዘ ። እንደኔ አመለካከት ሁኔታው ያን ያህል አሳሳቢ ባለመሆኑ የነርሷን መቀጠር አልደገፍኩትም ነበር ። አሮጊቷ ግን የመታመማቸው ዜና የሚፈጥረው የሰውን ግርግርና አዘኔታ ፣ የወዳጆቻቸው ጥየቃ ፣ የሚጎርፍላቸው አበባ ከወዲሁ እየታያቸው ነው መሰለኝ የዶክተሩን ሀሳብ ተቀበሉት ።

ሚስዝ ቫን ሁፐር በመታመማቸው ምክንያት ለዚያን እለት ምሽት አቅደውት የነበረ ግብዣ መሰረዙን ለወዳጆቻቸው ደውዬ ካስታወቅኩ በኋላ ነርሷ ስትመጣ ምሳዬን ለመብላት ወደ ምግብ አዳራሹ ወረድኩ ። ከወትሮው ልምዳችን ግማሽ ሰዓት ያህል ቀደም ብዬ ስለነበረ ሰው ይኖራል አላልኩም ነበር ። ሚስተር ደዊንተር ተቀምጦ ማየቱ ግን አስደነገጠኝ ። እርሱም ቀደም ብሎ መምጣቱ ሆን ብሎ ከኛ ጋር ላለመገናኘት አስቦ ይሆናል ብዬ ገመትኩ ።

አልመለስ ነገር የአዳራሹን ግማሽ አገባድጄው ነበርና እግሮቼ እየተላተሙ ወደ ጠረጴዛችን አመራሁ ። ለመቀመጥ ስዘጋጅ የአበባ ማስቀመጫውን ጣልኩት ። ተሰበረ ፤ ውሀው በላዬ ላይ ተከለበሰ ። አይኔ በድንጋጤ ሲቁለጨለጭ ሚስተር ደዊንተር መጣና "ተነሽ እንጂ ፣ መቀመጫሽ ሁሉ ረጥቦ የለም እንዴ ? ቅዝቃዜው የምግብ ፍላጎትሽን ይዘጋዋል" ብሎኝ የጠረጴዛ ጨርቁን ያደራርቅ ገባ ። "አይ ፣ ምንም አይለኝ ፣ ብቻዬን ስለሆንኩ ችግር የለም" አልኩት ።

ወዲያው አሳላፊው ከተፍ ብሎ የአበባ ማስቀመጫውን ሲያነሳ

t.me/OLDBOOKSPDF

“እርሱን ተወውና እኔ ገበታ ላይ ለወይዘሪት ስፍራ አዘጋጅላት ። ከኔ ጋር ትበላለች” አለ ሚስተር ደዊንተር

ያልጠበቅኩት በመሆኑ ልቤ ከዳኝና “አይ ፡ አልችልም” አልኩ

“ለምንድነው የማትችዪው ?”

“ግድ የለም ፡ እኔን ለማረጋጋት ሲሉ መቸገር የለብዎትም ። አሳላፊው ሲያዐዳልኝ እዚሁ ብሆን ነው የሚሻለኝ” በማለት እንዲተወኝ ለመንኩት ።

“አንቺን ለማረጋጋት ሳይሆን የአበባ ማስቀመጫውን ባትጥዪውም እንኳን ልጋብዝሽ አስቤ ነበር” ካለ በኋላ መጠራጠሬን ከግንባሬ አነበበ መሰለኝ “አላመንሽኝም ማለት ነው ? ግድ የለሽም ነይ ።” አለኝ ወደ መቀመጫው እየመራኝ ።

እንደምንም ግብግቡን ተቀበልኩ ። ምግባችን ቀርቦልን ስንበላ “ንደኛሽስ የት ጠፉ ?” ሲል ጠየቀኝ ። እንፍለቁንባ እንደያዛቸው ስነግረው “አዝናለሁ” ካለ በኋላ ለአፍታ ወጥ አለ ። “መልእክቱ የደረሰሽ ይመስለኛል ። የሰራሁት ብልግና በጣም ነው በራሴ እንዳፍር ያደረገኝ ። ይህ የብቸኝነት ኑሮዬ ነው መሰለኝ ጠባዬን በጣም የቀያየረብኝ ። ታዲያ ዛሬ ግብግቡን ተቀብለሽ ከብቸኝነት ስለገላገልሽኝ ምስጋናዬ ዳር ድንበር የለውም ።”

“የምን ብልግና ? ኧረ ምንም አይደለም ። እርሳቸውም ቢሆኑ ያን ያህል ያጤኑት አልመሰለኝም ። እንዲያ መወትወታቸው ደግሞ ለክፋት ያሉት ሳይሆን ትላልቅ ሰዎች ሲያገኙ ሁሌም እንዲሁ ናቸው.”

“ሞቅ ሊለኝ ይገባል በይኝ ። ለመሆኑ ለምንድነው ከትላልቆቹ ተርታ ያሰለፉኝ ?” ብሎ ሲጠይቀኝ እንደማመንታት ብዬ “የማንደርሌይ ባለቤት ስለሆኑ ይሆናላ” በማለት መለስኩለት ።

መልስ ካለመስጠቱም በላይ ማንደርሌይን ማንሳቱ እንዳስከፋው ይታወቅበት ነበር ። አገር ሁሉ በዝና ሰምቶ ብቻ እንደ ጉድ የሚያደንቀው ቤቱ እርሱን ይህን ያህል የሚያስፈልንቀው ለምን ይሆን ? የሚለው ጥያቄ አእምሮዬን እረፍት ነሳው ። በመካከላችን ዐጥቶ ነገሰ ።

በልጅነቱ በቀለሙ ድምቀት ተማርኬ ከአንድ የመንደር መደብር የገዛሁት ፖስት ካርድ ከፊቱ ድቅን አለና በሀሳብ ሰረገላ አሳፍሮ ከማንደርሌይ ጣለኝ ። ካርዱ ላይ የነበረው የቤት ምስል ምን እንደሆነ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስጠይቅ "አታውቂውም እንዴ? ማንደርሌይ ነዋ!" በማለት ባለ መደብሯ የሰጠችኝ መልስ ዛሬም በጆሮዬ ያቃጭላል ።

"ጓደኛሽ ግን ከአንቺ በዕድሜ በጣም ይበልጣሉ ። ዘመድሽ ናቸው ልበል ?" የሚለው የሚስተር ደዊንተር አነ ጋገር ከሀሳብ አለም መለሰኝ ።

"ጓደኛዬ እንኳን አይደሉም ።ቀጣሪዬ ናቸው ። በእመት ዘጠና ፓውንድ እየከፈሉኝ ባልደረባቸው እንድሆን እያሰለጠኑኝ ነው"

"ጉድ ! ጆሮ ኦይሰማው የለ ! ባልደረባ በግር ? ልክ እንደ ጥንቱ የምሥራቁ አለም የባሪያ ግር ?!" ብሎ ግርምታውን ከገለፀ በኋላ "ግን እኮ ሁለታችሁን የሚያመሳስል አንድም የጋራ ባህሪይ አይታየኝም" አለኝ ሳቅ ሳሩ እያሰ ። አያይዞም "ለመሆኑ ስራው ደስ ብሎሽ ነው የምትሰሪው ?" ሲል ጠየቀኝ ።

"ምን ላድርግ ? ዘጠና ፓውንድ ደግሞ ለእኔ ብዙ ነው"

"ቤተሰቦችሽስ ?"

"እነሱንማ ሞት ነጥቆኝ እንጂ..."

"እንዴት ያለ ግሩምና ልዩ ስም ነው ያለሽ ?" አለና ጨዋታውን ቀየረው

"አባቴም እንዲሁ ግሩምና ልዩ ሰው ነበር" አልኩት

"እስቲ ስለ አባትሽ አጫውቺኝ"

አባቴን መግለፅ በጣም ነበር የሚከብደኝ ። ደግሞ ስለ እርሱ አዘውትሬ ለሰው ተናግሬም አላውቅ ። ማንደርሌይ የሚስተር ደዊንተር የግል ንብረት እንደሆነው ሁሉ አባቴም የእኔ የግሉ ፣ የብቻዬ ምስጢር ነው ። እዚህ ሞንቴ ካርሎ ምግብ ቤት ውስጥ ድንገት በተፈጠረ ሁኔታ አባቴን ለማስተዋወቅ ፈፅሞ አልፈልግም ነበር ።

ይሁንና እንግዳው አሳዛኝ አይኖቹን እላዬ ላይ ሲያንከራትትብኝ አሻፈረኝ ማለቱ አልሆንልሽ አለኝ ። ምስጢር ብዬ ያቆየሁትን የአባቴን ፣ የቤተሰቤን ታሪክ አውጥቼ ዘከዘኩለት ። ጥቂት እንዳወራሁ ሀፍረቴን ከነሰንኮፉ ነቅዬ ጣልኩት ። ምላሴ መተሳሰሩ ቀርቶ ጭራሽ አንደበተ–ስል ሆንኩኝ ። ደስታና ሀዘን ስለተፈራረቀበት የልጅነት ህይወቴ ፣ ስለ አባቴ አስደናቂ ተክለ–ሰውነት ፣ እናቴ ለአባቴ ስለነበራት ፅኑ ፍቅር ፣ አባቴ በሳምባ ምች ህይወቱ ስታልፍ ሀዘን ክፉኛ ያኮራመታት እናቴም ከአምስት ሳምንታት በኋላ ተከትላው ስለመሄዷ ፣ በደፈናው ስለ ሁሉም

t.me/OLDBOOKSPDF

ነገር ዘርዝሬ አሜወትኩት ።

ጊዜው መግፋቱን የተረዳሁት የግድግዳው ሰአት ስምንት መሙላቱን ሲነግረኝ ነበር ። በአንድ ሰአት ተኩል ቆይታችን መድረኩን በአመዛኙ እኔ ይገርው እንዲያ ወግ ጠራቂ መሆኔ እራሴን እንድታዘበው አደረገኝ ። ይቅርታ ጠይቄው መሄድ እንዳለብኝ ስነግረው ሰምቶኝ እንዳልሰማ እንዲህ አለኝ ፦

"በጭውውታችን መግቢያ ፡ ድንቅና ልዩ ስም አለሽ ባልኩት ላይ እንዳክልበት የምትፈቅጅልኝ ከሆነ ስም አወጣጡ የአባትሽን ረቂቅ ባህሪይ የማሳየቱን ያህል ስያሜው ላንቺ የሚመጥን መሆኑን ላረጋግጥ ልሽ እወዳለሁ ። ካንቺ ጋር ያሳለፍኩት ይህ ወቅት ለረጅም ጊዜ ርቆኝ የነበረ ልዩ ደስታ እንዳጎናፀፈኝ ልትረጂልኝ ይገባል ። አንድ አመት ሙሉ ለብቸኝነት ዳርጎኝ በቀቢፀ—ተስፋ እንድውተረተር ካደረገኝ የሀሳብ አለም ነው መንጭቀሽ ያወጣሽኝ ።"

አነጋገሩ ፣ መላ አስተያየቱ ከበፊቱ ይበልጥ ፈጣዋነት የተመላበት ፡ ሰብአዊነት የሚንፀባረቅበት ሆኖ ሰላገኘሁት እምነት ጣልኩበት ። የነገረኝ ሁሉ ከአንጀቱ ነው ብዬ ከአንጀቴ ተቀበልኩት ። አያይዞም "እኔና አንቺን የሚያመሳስለን ነገር እንዳለ ታውቂያለሽ ? ሁለታችንም ከአለም የተገለልን ፣ አለም ያገለለን ብቸኞች ነን ። በእርግጥ አንዲት እህት ብትኖረኝም አዘውትረን አንገናኝም ። በአመት ሦስት ጊዜ የምጠይቃት አሮጊት አያት አለችኝ ። ዳሩ ግን ማናቸውም የልቤ ሊደርሱ አይችሉም ። ታዲያ ሚስዝ ቫን ሁፐር አንቺን የመሰለች ልጅ ለአመት በዘጠና ፓውንድ ማግኘታቸው እድለኛ ናቸው እላለሁ" አለኝ ።

"ሊሉ ይችላሉ ። ግን ደፈረችኝ አይበሉኝና አንድ ታላቅ ነጥብ የዘነጉ ይመስለኛል ። እርስዎ ከቤትም ቤት ፡ ልዩ ድንቅ ቤት አለዎት ። እኔ ግን...እኔ ግን አንተቴን የማስገባበት ደሳሳ ጎጆ የተነፈገ ባይተዋር መሆኔን ልብ ይበሉልኝ" አልኩ ። ፊቱ ልውጥውጥ ሲል ማየቴ ምነው ባልተናገርኩ አሰኘኝ ። መልስ ከመስጠቱ በፊት አንገቱን ደፍቶ ሲጋራውን ካቀጣጠለ በኋላ "ቤት አልሺኝ ? ቤት ብቻውን ምን ፋይዳ አለውና ? አንዳንዴ በህዝብ ተጨናንቆ ድብልቅልቅ ባለ ሆቴል ውስጥ ተቀምጦ ብቸኝነት እንደሚያጠቃ ሁሉ ወና ቤት ታቅፎ መኖርም የባሰ ነው" አለኝ ። እንደማመንታት ሲለው ስለ ማንደርሌይ ሊያወራ

t.me/OLDBOOKSPDF

መስሎኝ አይን አይኑን ስማዐነው ድፍረቱን ያጣ አይነት ሀሳቡን ቀይሮ ሌሎች ነገሮች ማንሳት ጀመረ ።

በመጨረሻም ስዕሌን ለመለማመድ በዘጠኝ ሰዓት ወደ ሞናኮ መሄድ እንዳለብኝ ስነግረው "በመኪናዬ አደርስሻለሁ" አለኝ ።

አብሬው ለመሄድ ይሁንኝ ብዬ የፈጠርኩት መላ መስሎ ይታየው እንደሁ በማለት ሀፍረት ተሰማኝ ። ለመቃወም እንኳን ፋታ ሳይሰጠኝ ብድግ አለ ። ከምግብ አዳራሹ ስንወጣ አሳላፊውና በረኛው ከወትሮው በተለየ መልክ አክብሮታቸውን ሲያሳዩኝ ሀፍረቱ ይበልጥ ተጫነኝ ።

የስዕል ደብተሬንና እርሳሴን ከመኝታ ክፍሌ አውጥቼ ባርኔጣዬን አድርጌ መኪናው ላይ ተሳፈርኩ ። በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ደጋግሞ ይሰነዝረው የነበረ ሀሳብ ከሚስዝ ቫን ሁፐር ጋር በፍፁም መግጠም እንዳልነበረብኝ ነበር ። "ስለ ወደፊቱ ህይወትሽ አስበሽ ታውቂያለሽ ?" ሲል ጠየቀኝ "ማለቴ ፡ ለምሳሌ ሚስዝ ቫን ሁፐር በቃሽኝ ቢሉ ፡ ምንድነው የምታደርጊው ?"

ወጣት በመሆኔ አፍላ ጉልበቱ ገና ስላልተበላና በራሴ ሙሉ እምነት ስላለኝ ምንም እንደማያስጨንቀኝ ፈገግ እያልኩ ነገርኩት ። እድሜዬን ጠየቀኝ ። ነገርኩት ። ከአንጀቱ እየሳቀ "እውነት አለሽ ፡ ይሄ እድሜ ፍፁም ግትርነት የሚገንበትና የተጋረጠው ቢጋረጥ ስለ ወደፊቱ ህይወት ቅንጣት ፍርሀት የማይሰማበት አፍላ የወጣትነት ጊዜ መሆኑን አሳምሬ አውቃለሁ ። እንዴ ካለፍነው ተመልሶ አለመምጣቱ ከፋ እንጂ" አለኝ ።

አሁን እንዲህ ሊቀለኝ ለካስ ይህን ሰው እንዲሁ ነው አክብጄ ያየሁት የሚል ሀሳብ አደረብኝ ። የረጅም ጊዜ ጓደኛዬ እንዲያውም ምነው በኖረኝ እያልኩ ስመኝ የነበረውን ወንድሜ መስሎ ታየኝ ። ሁለታችንም በደስታ ተውጠን ፡ አየተጫወትንና እየሳቅን ካለምነው ስፍራ ደረስን ። ንፋሱ በማየሉ ስእል መሳሉ የማይሞከር ሆነና ወደ መኪናው ተመልሰን ጉዟችንን አቀናን ። ወዴት እንደምናመራ ሳይገባኝ በጎማ የሚሽከረከር ሳይሆን በክንፍ የሚንሳፈፍ ይመስል አውቶሞቢሉ ሽቅብ ይዞን ከኮረብታው ጫፍ አሳረፈን ።

ከመኪናው ወርደን የተጓዝንበትን ጠመዝማዛ መንገድ ቁልቁል ሳስተውለው ቢሰቀጥጠኝም የኮረዳ ልቤ ግን አልተሸነፈም ። የተፈጥሮን

t.me/OLDBOOKSPDF

ውብ ገፅታ በተመለጠ ስናደንቅ ከቆየን በኋላ "ከዚህ ቀደም እዚህ መጥተው ያውቃሉ?" ብዬ ብጠይቀው ምላሹን ነፈገኝ ። ቀና ብዬ ሳየው በድኑ ብቻ እንጂ ስሜቱ ከኔ ጋር እንዳልነበር ተገነዘብኩ ። ጥቂት ቆይቼ እየመሸ በመሆኑ እንድንሄድ ጠየቅኩት ። እንደ መባነን አለና እኔን ትቶ በሀሳብ በመስጠሙ ይቅርታ ጠይቆኝ ወደ መኪናው ገባን ።

ተዳፋቱን ማሽቆልቆል እንደጀመርን ቀደም ብዬ ያቀረብኩትን ጥያቄ በድጋሚ ሰነዘርኩለት ። ስፍራውን በፊትም እንደሚያውቀውና የአሁኑም አመጣጡ ለውጥ እንዳለው ለማየት መሆኑን ነግሮኝ ጉዟችንን ቀጠልን ። ዝምታ አጥር ሆኖ እኔን ከእርሱ እርሱን ከኔ ከለለን ።

ከምእራባዊው አድማስ ጉያ ገብታ ለመሸሸግ በምታዘግመው ጀምበር ላይ የደመና ቁልል ያንጣባብባታል ። እይታዬን በርቀት ለቅቄው ይህንን ማራኪ ትእይንት ሳጣጥም ድንገት ስለ ማንደርሌይ ይነግረኝ ጀመር ። አጋጣሚውን እጠብቀው ነበርና ወሬውን መጀመሩ ይብሱን አጓጓኝ ። አእምሮዬን አንቅቼ ፡ ጆሮዬን ከፍቼ ብሰጠውም ይበልጥ ይሰማኝ ይመስል አይኔን ፊቱ ላይ ተክዬ አዳምጠው ገባሁ ። ገለፃው ማንደርሌይን በምናብ እንድጎበኝ ነው የጋበዘኝ ።

በፀደይ ወራት ፀሐይ በማንደርሌይ ምድር ስትጠልቅ ምንኛ ውብ እንደምትሆን ታየኝ ። የራሷን መልክ እየቀያየረች ከመሄዷም በላይ አካባቢውን ልብ በሚመስጡ ቀለማት ትሸልመዋለች ። ደረታቸውን ለፀሐይ ሰጥተው በኩራት የተኮፈሱት ኮረብቶች በሚንቀሳቀሱ የጭፍ ሰንሰለቶች የተቆላለፉ ይመስል ሞቅ ደመቅ ብለው ይታያሉ ። ማንደርሌይን አካሉ የተንጣለለው ባህር ፀጥ ረጋ ባለበት ወቅት የርቀት አይን ውሀ አይለውም—ሰማያዊ የድንጋይ ንጣፍ እንጂ ። ሞገድ በተፈታተነው ጊዜ ደግሞ የሚሸሸው ውሀ ከዳርቻው እየተላተመ የሚፈጥረው ድምፅ የራሱ የሆነ ሙዚቃዊ ቃና አለው ።

መሬቱን ዳር እስከ ዳር ያለበሱት ተክሎችና እፅዋት ማንደርሌይን በማስጌጡ ተጣባር ግንባር ቀደሙን ሚና የሚጫወቱት አይኖርም ። ዛፎቹ እንደ ተፈጥሯዊ ባህሪያቸው ፡ እንደ መልካቸውና እንደ ቁመታቸው በቅለዋል ። በተለይ እጅብ ስብስብ ብለው በበቀሉበት አካባቢ የፈጠሩት ደን ልዩ ግርማ ሞገስ አለው ። እንደየህብረ ቀለማቸው ሁሉ የተለያየ መአዛ ያላቸው አበቦች ልብ ይሰውራሉ—መንፈስን አድሰው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እዚህም እዚያም በእንክብካቤ በተያዙት መስኮች ላይ የተኛው አረንጓ ዴው የሳር ምንጣፍ ውብ የአይን መስህብ ነው ። በማንደርሌይ አፀዶች ውስጥ የሚንሸራሸር ማንኛውም ጎብኚ አይኑን ለአበቦች ፣ አፍንጫውን ለመአዛቸው ፣ ልቡን ለፍስሐ መዳረጉ የግድ ነው ።

እንዲህ እንዲህ እያለ ስለ ማንደርሌይ ሲያጫውተኝ እጅግ ከመመ ሰጤ የተነሣ ከሆቴላችን መድረሴ አልታወቀኝም ነበር ። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ማንደርሌይ ውስጥ እንዴት እንደሚኖር ከአሁን አሁን ይነግረኛል ብዬ ስጠብቅ ስለ ራሱ ቃልም ሳይተነፍስልኝ ጨዋታውን ደመደመው ።

ከመኪናው ኪስ ውስጥ ጓንቴን ስፈልግ አንድ መጽሀፍ አገኘሁና አነሳሁት ። ርእሱን ለማየት ስሞክር ወስጄ ማንበብ እንደምችል ነገረኝ ። ተሰናብቼው ከመኪናው ስወርድ ሁለመናው በፈገግታ ፈክቶ በድጋሚ አመሰገነኝ ።

ደረጃውን አቀርቅሬ ስወጣ አሻንጉሊቱን እንደ ተነጠቀ ህፃን ሀዘን ልቤ ውስጥ ገብቶ ተዘፈዘፈ ። ባሳለፍኩት ወርቃማ ጊዜ የሸመትኩትን ደስታ እኒያ ነትራካ አሮጊት በዚያ ሞዛዛ ጥያቄያቸው እንዳይበርዙብኝ ከወዲሁ ስጋት ስጋት አለኝ ። መሸት እስኪልልኝ ከሆቴሉ መዝናኛ ክፍል ለመቆየት ወሰንኩና ሻይ አዝዤ ተቀመጥኩ ። የያዝኩትን የግጥም መፅሐፍ ሳገላብጥ በቅድሚያ ያየኋቸው ስንኞች አንዳች ስሜት አጫሩ ብኝ ።

ሌት ዕልመት አልብሼው፡
የመዓልት ጅምበር ኩዬው፡
ግለ-ምናብ ገድሌን ካሰፈርኩበት የጊዜ ሰሌዳ፡
ቁልቁል ሸመጠጥኩኝ ፡ አመለጥኩት ትቼው እንደ ዘመድ ባዳ ።
ታቹን ሰርሳ-ሰርሰሩን ከዘመናት ስሌት ፡ ከአመታት ቅመራ፡
ሸሸሁ ካጠገቡ ቢከተለኝ ላይደርስ ፡ ላልሰማው ቢጣራ ።
ልለየው ሰርቀው፡
አይኔ በእንባ ሟጦማ እንደተጋረደ፡
ልደበቅ ሳመልጠው፡
አልከደን ብሎኝ ጥርሴ ሲንከተከት ፡ እግሬ ግን ነጎደ ።
ሸቅብ ስገሰግስ ፡ የትዝታን ዳገት ቧጥጬ ስወጣው፡
አስፈሪ አስደንጋጭ ፡ የተለየ አንዳች ድምፅ ፡ ጆሮዬን ጠለዘው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደ መብረቅ ፈጭሽ እንደ መይሳ፡ አንራ ፣
ከሠማይ ሸለቆ ተምዘግዝጎ ወረዶ ፣
የጭሬሃት ዘር ዘፋን በልዘ ሙሰጥ ዘራ ።
እጅ እግሬ ዛለ ፣ ልዘ ከንጎፉሱ በዛሙ ከዛኝ ፣
መፈት አሪድ ኮዝ እግር በእግር ገብዱ፣
እየተከተለ መቅኖ ቢያሳጣኝ ።

ግጥሙን አንብቤ እንዳበቃሁ መዕሀፉን መያ ሳን ብዬ ሀሳብን ተሳጣኝሁ ። ለምን እዚያ ኮረብታ ላይ ለመሄድ ፈለገ ? አእምሮውን እረፍት የሚነሳው የምን ኮዝ ይሆን ? ምን አይነት ትዝታ ይሆን የሚያብሰለሰለው ? እያልኩኝ አንዱን ጥያቄ አንስቼ እልባት ሳላገኝለት መያሴላው ሰዘምት ፣ አሳላፊው ሻዩን ይዞልኝ መጣ ። አሁንም ከሀሳብ ልነሳነል አልቻልኩም ። የነገረኝን እያስታወስኩ ማንያርሴያ በአይነ ሀሊናዬ ደቅን አለብኝ ። የአበባቸ መአላ አንድ አፍታ መጣና አወደኝ ። ነጫሬሙቸ የባህር ዳሩ ጠጠሮች አብረተረቱብኝ ። "ታዲያ" አልኩኝ እራሴ ለራሴ "ማንያርሴያን ይህን ያህል ከወደደው ፡ ለምን የትም የትም ይባዝናል ?"

መዕሀፉን እንደገና አንስቼ ስገልጠው ርእሱ በሰፈረበት ገፅ ላይ "ለማክሰ ክርብቃ ፡ ግንቦት 17" የሚለውን ማስታወሻ አየሁ ። ርብቃ የሚለው ቃል ጋደል ባለ የእጅ ዕሀፊት ጎልቶና ደምቆ ታየኝ ። ረዘም ቆል መም ብሎ የሰፈረው "ር" የሚለው ፊደል ይበልጥ አይኔን ሳበው ።

መዕሀፉን አላጥፌ አስቀምጬው አጠገቤ ያገኘሁትን አንድ የቆየ ጋዜጣ አነሳሁ ። አይኔ ጋዜጣው ላይ ያፍጥ እንጂ ምን እንደማነብም አይገባኝ ። ገፁ ላይ የሚታየኝን ስዕል አእምሮዬ ተያዥ የሚስዝ ሻን ሁፐርን ምስል ደቀነብኝ ። ከትናንት በስቲያ ምግብ ቤቱ ውስጥ ሆነው ስለ ሚስተር ደዊንተር ያጫወቱኝ ከአጠቃላይ ሁኔታቸው ጋር ብልጭ አለብኝ ።

"...የሚሰቀጥጥ አሳዛኝ ታሪክ ነው እባክሽ ። እዚያው ማንደርሌይ አካባቢ ባህር ውስጥ ሰጥማ ነው የሞተችው አሉ ። አንድ ሰሞን የጋዜጦች ሁሉ መረባረቢያ ዜና ነበር ። እርሱ ግን ስለ ሁኔታው ማውራት ቀርቶ ስሟንም ሹራሽ ማንሳት አይፈልግም ይባላል" ነበር ያሉኝ አሮጌቷ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አራት

ሰለ ሌላው ሰው አላውቅም እንጂ እኔ ግን የመጀመሪያ ፍቅር ትዝታ ፡ ከነትኩሳቱ ከነምናምኑ ዳግም ተመልሶ አለመምጣቱን መድፎዋለሁ ። ባለ ቅኔዎች ፍቅርን ባልመሰለ ነገር የለም ። በተለይ የመጀመሪያ ፍቅርን፡

ባሬ በጎልማሳነት ዘመኔ ወደ ኋላ መለስ ብዬ ያኔ በሀያ አንድ አመቴ እንደዬት እፈራ ፡ ምክንያት በሌለው ነገር ሁሉ እንደዬት እበረግግ ፡ በረባ ባልረባው እንደዬት እከፋ እንደነበር ሳስታውስ የያን ዘመን እኔነቴን ከፉኛ እታዘበዋለሁ ። አንዳንዴ ደግሞ እራሴን መታዘቤ ተገቢ አለመሆኑ ይሰማኛል ። ምክንያቱም ይህ ባህሪይ በዚህ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ መላዩችን በአመዛኙ የሚጠናወታቸው በሽታ ይመስለኛልና ።

ያኔ ሁኔታው አስገድዶኝ ልዋሽ ብል እንኳን ምላሴ እየተሳሰረ ሲያሳጣኝ ፡ ቃላት እርስ በእርስ እየተጠላለፉ ያጋልጡኝ ነበር ። በዚያ እድሜ ሽፍጥን ፡ ማጭበርበርን ፡ ውሸትን ፡ እንደ መሣሪያ መጠቀሙ የሚያዳግት ይመስለኛል ። በእድሜ ለበሰሉ ሰዎች ግን ችግር አለው አልልም ። ምን ይሉኝን ከጭንቅላታቸው ፍቀው እስካወጡ ፡ ህሊናቸውን በግል ጥቅም እስከለወጡ ፡ የሌላውን በደልና ስቃይ በማየት የሚረኩ እስከሆነ ድረስ እነዚህን እኩይ ባህሪያት ለመጠቀም አይናቸውን አያሹም።

“ለመሆኑ ፡ እስካሁን ምን ስትሰሪ ነው የቆየሽው ?” ብለው ጠየቁኝ አሮጊቷ ።

“ከአሰልጣኜ ጋር ቱኒስ ስለማመድ ነበር ።” አልኳቸው ። ውሸቴን ያወቁብኝ መስሎኝ እየተቁለጨለጭኩ አይን አይናቸውን አየኋቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

አሰልጣኜ ድንገት ቢመጣና በዚያን ሰሞን ልምምዴን አቋርጬ እንደነበር ቢነግርብኝስ ? ጉዴ ፈላ ማለት አልነበር ?

“ዳሩ አንቺ ምን ታደርጊ ? እኔ እዚህ ተጋድሜልሽ በየት ወጣሽ ? በየት ገባሽ ? የሚልሽ የለ ። ” አሉኝ ይዘውት የነበረውን ካርታ እየጣወዙ “ቀኑን ሙሉ ምን ስትሰሪ እንደምትውዪ እኔ እንጂልሽ ፡ ታምሚ ከተኛሁ ይኸው አስራ አምስት ቀኔ የሳልሻቸውን ስዕሎች አላየሁ ። እኔ እንጂ ፡ እንጂልሽ ። ደግሞም ልብሽን የሚሰውር ነገር መጥቶብሻል ። ገበያ ወጥተሽ የተላክሺውን ግማሹን ትተሽ መምጣት ጀምረሽ የለ ?” ሲሉ የተግሳፅ ከረጢታቸውን ፈተው ከሰሞኑ ያጠራቀሙትን ዘረገፉብኝ ።

‘ከሚስተር ደዊንተር ጋር እየተንሸራሸርኩ እኮ ነው’ ልላቸው አሰብኩና ዋጥ አደረግኩት ። ከእርሱ ጋር እንሸራሸር በነበረበት ወቅት ልቤ ምንኛ በደስታ ይዋኝ እንደነበር ሲታወሰኝ አሁን አሁን እያለኝ እንደ መፈንጠዝ ይዳዳኛል ። አንዴ ወደ ምስራቅ ስናቀና ፡ አንዴ ወደ ምዕራብ ስናሽቆለቁል ፡ ወደ ሰሜን ስንሽከረከር ፡ ወደ ደቡብ ስንበር መዋል ነበር ። የሜዲትራንያንን የባህር ዳርቻ የሙጥኝ ብለው ከተገጠገጡት መንደሮች ገብተን ያልወጣንበት አንድም አይገኝም ። ይህን ሁሉ በማለቴ ‘ያልፈሳን በት ሚዳ የለም’ ካለችው አህያ ጋር ደምራችሁኝ ትታዘቡኝ ይሆናል ። እንዲያው ለነገሩ ያህል አወሳሁት እንጂ በዚያን ወቅት ጉልበቴን ታቅፌ ከጎኑ መቀመጤ ብቻ ምንኛ ያረካኝ እንደነበረ እኔ ነኝ የማውቀው ። ከስፍራ ስፍራ መንሸራሸሩ ቀርቶብኝ መኪናው በአንድ ቦታ ዙሪያውን ሲሽከረከር ቢውል እንኳን ደንታዬም አልነበር ።

አንድ ቀን ልንንሸራሸር ስንዘጋጅ “ዛሬ በጣም ስለሚበርድ ኮቴን ላይሽ ላይ ደረብ አድርጊው” ሲለኝ የምሆነውን አሳጣኝ ። ሩንዳቅድቅ ከማለቴ የተነሣ ሪዉ ልረግጥ ምንም አልቀረኝም ። አንድ ትንሽ ልጅ የሚያደንቀውን ኳስ ተጫዋች ልብስ መያዙን ብቻ እንደ ታላቅ ዐጋ እንደሚቆጥረው ፡ ልብሱን በደረቱ ለጥፎ በደስታ ሲታ እንደሚታፈን ፡ በኩራት እንደሚወጣጠር አይነት ነው የተሰማኝ ። ለጥቂት ደቂቃዎችም ቢሆን ትከሻዬ ላይ ጣል ያደረግኩት ኮቴ አንድ ታላቅ ድል የተቀዳጀው ያህል በኩራት አስከፈሰኝ ።

“ትዝታን ፡ ሳይዝግ ሳይጠወልግ ጠርሙስ ውስጥ አፍኖ የሚያስቀ

t.me/OLDBOOKSPDF

ምጥ መጣሪያ ቢፈለሰፍ ምን ነበረበት? ባስፈለገ ጊዜ ጠርሙሱን ከፍቶ እንደ ማራኪ ሽቶ እያሸተቱ ባለፈ ትዝታ እንዳሻ መዋኘት ነበር" አልኩ ድንገት ከውስጤ ልዩ ስሜት ፈንቅሎኝ ።

ማክሲም አይኑን ከመንገዱ ሳይነቅል "የትኛውን የህይወት ዘመን ሽን ነው ከፍተሽ ዳግመኛ ለመኖር የምትፈልጊው?" ሲል ጠየቀኝ ።

ማሽሚጠጡ ይሁን አይሁን ባይገባኝም "እኔ እንጃ" ብዬ ጀመር ኩና እንደመጣልኝ "ይህንን ወቅት አፍኜ አስቀምጩው ፡ ዘላለም እንዳልረሳው ማድረግ ነው የምፈልገው" አልኩት ።

"ለዛሬው እለት የመታሰቢያ ሀውልት መቅረፅሽ ነው ወይስ በአነዳዴ ያደረብሽን አድናቆትና ከበሬታ ለመግለፅ?" ሲል እያፌዘ ጠየቀኝ ።

መልስ አልሰጠሁትም ። ሌላ ሀሣብ ገባኝ ። ይህን ጉዴን በምንም አይነት ለሚስዝ ቫንሁፐር መንገር እንደሌለብኝ ተገነዘብኩ ። "ሚስተር ደዊንተር እኮ ዘወትር በመኪናው ያንሸራሽረኛል" ብላቸው ፡ ከትከት ብለው እየሳቁብኝ "ወይ ጉዴ! ወግ ወጉ ተይዞልኛልሳ! እርሱ እንግዲህ በቅን ልቦና ደግ የዋለ መስሎት ይሆናል ። ምስኪን ፡ የዋሁ ። ታዲያ ካንቺ ጋር ሲንከረፈፍ ይሄኔ እንዴት ቂቅ ፡ ግፍግፍ ብሎት ይሆን? በይ እስቲ ፡ ወሬውን ተይውና የፀጉር ቅባቱን ገዝተሽልኝ ነይ ።" ብለው ትከሻዬን መታ መታ እያደረጉ ሲያባርሩኝ በምናብ መጣብኝና ዝግንን አለኝ ። ወጣትነቴን ረገምኩት — ይኸው ልጅነቴ ነው እንዲህ የሁሉ መዘባባቻ ያደረገኝ የሚል ሀሣብ ቢመጣብኝ ።

"ምነው ደማቅ ጥቁር ከፋይ የለበሰች ፡ በእንቁ የተንቆጠቆጠች የስልሳ ስድስት አመት ባልቴት በሆንኩኝ?" አልኩ በሀሣብ እንደሰጠ ምኩ ።

"እንዲህማ ብትሆኚ ኖሮ ከነአካቴው መኪናዬ ውስጥ ባላስገባሁሽ ነበር" አለኝና ዞር ብሎ አየኝ ። "ደግሞ ጣትሽን መጉረሱ ቢበቃሽ መልካም ነው ። እንዲያውም ከርከመሽ ከርከመሽ ጥፍርሽን እንዴት እንዳበላሸሽው አይታይሽም ?" አለ ኮስተር ብሎ ።

"መቼም ቅሌታምና ባለጌ አድርገው እንደሚገምቱኝ ባውቅም የሚከነክነኝን ነገር ማወቅ እሻለሁና አይፍረዱብኝ ። ለመሆኑ በየቀኑ

t.me/OLDBOOKSPDF

በመኪናዎ የሚያንሸራሽሩኝ ለምንድነው ? አድራጎትዎ ከርህራሄና ከቅንነት የመነጨ መሆኑን ብረዳም ይህንን መልካም ምግባርዎን ለምን ለእኔ ሊያውሉት ፈለጉ ማለቱ ነው?"

"እንግዲያውስ ያን ያህል ምክንያቱን የማወቅ ጉጉት ካደረብሽ እነግርሻለሁ ። የማንሸራሸርሽ ጥቂር ከፋይ ስለማትለብሽ ፡ የእንቁ ሀብል ስለማታንጠለጥይና በተጨማሪ ደግሞ የስልሳ ስድስት አመት ባልቴት ስላልሆንሽ ነው ።" አለኝ — ገፅታው ላይ አንዳችም የስሜት መለዋወጥ ሳይንፀባረቅ ። በውስጡ ስቆብኝ እንደሆነም ልቦናው ይፍረድ እንጂ እኔ እንደሁ የማውቅበት አንዳችም ምልክት አልነበረም ።

"ካሉም ደግ ፡ ይሁንልዎት ። እንደ እውነቱ ከሆነ እኔ ያን ያህል የሰፋ ታሪክ ባይኖረኝም ስለ እኔ ማወቅ የሚገባዎትን ሁሉ ጠንቅቀው ያውቃሉ ። እኔ ግን በመጀመሪያ ያየሁዎት እለት ስለ እርስዎ ከሰማሁት ሌላ ምንም የማውቀው ነገር የለም ።"

"ያኔስ ቢሆን ስለ እኔ ምንድነው ያወቅሽው?"

"ያው ነዋ ፡ የማንደርሌይ ባለቤት እንደሆኑና ደግሞ... ደግሞ ባለቤትዎ እንደሞቱ ።"

እንዲያ እንደ አንድ ነገር ይከብደኝ የነበረውን ቃል ምንም ሳይመስለኝ እንደ ዘበት አወጣሁት ። ባለቤትዎ ። ባለቤትዎ አልኩኝ አይደል! አሁንማ አንዴ ከአፌ ከወጣ መልሼ አልውጠው ። ቃሉን መጥራቱ በዚያ በግጥም መፅሃፍ ላይ ያየሁትን ስም ከነጥምዝምዙ 'ር' አምጥቶ አይኔን ሲጋርደው መንፈሴ ሁሉ ርብሽብሽ አለብኝ ።

ከእንግዲህ የእኔ ነገር አከተመ አልኩኝ ። ወዳጅነታችን አለቀለት ፡ በምንም አይነት ይቅርታ የሚያደርግልኝ መስሎ አልታየኝም ። ዐጥታ በመሃላችን ሰፍኖ ስንጓዝ መንገዱ አልቆረጥልሽ አለኝ ። ደቂቃው አመት ሆነብኝ ። ከሰው ጋር መሆኔንም የተገነዘብኩት "ቅድም ..." ብሎ መናገር ሲጀምር ነበር ።

"ቅድም ፡ ትዝታን አፍኖ የሚያቆይ መሣሪያ በፈለሰፍ መልካም ነበረ ነው ያልሽው? ያለፍሽውን ጊዜ እንደገና መኖሩ የሚያስደስትሽ መሆኑን ነበር መሰለኝ የነገርሽኝ? — ባልሳሳት ። አይግረምሽና የኔ ሀሣብ ደግሞ ከአንቺው ፍፁም የተለየና እንዲያውም ተቃራኒው ነው ። ለኔ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያለፉት ትዝታዎች ሁሉ ከፊት የሚመሩ የሚያንገፈግፉ ናቸው ። አንዳቸውም ቢሆኑ ትንሽ እንኳን ውል እንዲሉብኝ አልሻም ። ከአንድ አመት በፊት ጠቅላላ ሕይወቴን የለወጠ ነገር ነው የደረሰብኝ ። ለዚህም ነው ከዚያ በፊት የነበሩትን ነገሮች ሁሉ ከአእምሮዬ ፍቄ እንዳወጣቸው የምገደደው ። አለቀ ፡ ደቀቀ ። ያ ዘመን ተመልሶ ላይመጣ አልሯልና ከእንግዲህ ሰለ እርሱ የምጨነቅበት አንዳችም ምክንያት የለም። በአዲስ ተስፋ ፡ በአዲስ ስሜት አዲስ ህይወት መጀመር አለብኝ ብዬ ነው የማስበው ። መጀመሪያ የተገናኘን ቀን ሚስዝ ቫን ሁፐርሽ ሞንቴ ካርሎ ለምን እንደመጣሁ ያቀረቡልኝ ጥያቄ ያለፈውን ትዝታ ለመቀስቀስ ምንኛ እንደተፈታተነኝ ልነግርሽ አልችልም ።

“በመጀመሪያ ሽርሽራችን እዚያ ኮረብታ ላይ ስንወጣ የጠየቅሺኝን ጥያቄ የምትረሺው አይመስለኝም ። ስፍራው ከድሮው ተለውጠብኝ እንደሆነ አልነበር የጠየቅሺኝ? ይሽውልሽ ፡ ቦታውን አንዴ ከባለቤቴ ጋር አይተነው ነበር ። ታዲያ እኔና ባለቤቴ የተውነው አንድም አሻራ አልነበረምና ምንም ለውጥ አላየሁበትም ። ምናልባትም ያንቺ አብረሽኝ ከነኔ መሆን ይሆናል ልዩነቱን እንዳልገነዘብ ያደረገኝ ። ይህንን ስል ደግሞ ህሊናዬን አሳትሽኝ ፡ ግንዛቤዬን ገፈፍሽኝ ብዬ አንቺን መኮነኔ እንዳልሆነ እንድትረጅልኝ ያስፈልጋል ። ወቀሳ ከተባለ የምወቅስሽ ግን ከደማቁ ሞንቴ ካርሎ ይበልጥ ያለፈውን ህይወቴን እንድረሳ በማድረግሽ ብቻ ነው ። አንቺን ከነኔ ላኖረልኝ አጋጣሚ ምስጋና ይግባውና ይሄኔ በጣሊያንና በግሪክ ምድር እንከላወስ ነበር ። ላንቺ አይታወቅሽም እንጂ ከዚህ መሰለ መንከራተት ስላዳንሺኝ ብቻ የጣልሽብኝ ውለታ በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። ይህን በመልካም ቃላት ከሽነሽ ደግነትህ ፡ ርህራሄህ የምትይውን ከንቱ ማሞካሻ ወዲያ ጣይውና አብረሽኝ እንድትውይ የምጋብዝሽ ሰብእናሽ ስለገዛኝ ብቻ ነው ። ወዳጅነትሽን አጥብቄ ስለምሻ ብቻ ነው ። የማታምኚኝና አባባሌን የማትቀበይኝ ከሆነ አውኑኑ ከመኪናዬ ወርደሽ ወደፈለግሺበት መሄድ ትችያለሽ… ደህና ሁኚ ። በይ እንጂ… ምንድነው ዝምታው?… በሩን ክፈቺው … ሂጂ እንጂ …”

ክው አልኩኝ ። ከአንጀቱ ይሁን አይሁን መረዳት ተስኖኝ ፀጥ ብዬ እንደተቀመጥኩ “እና? በይ እንጂ ፡ ሀሳብሽ ምንድነው?” ሲል ጠየቀኝ ።

እንባ ዳዳኝ ፡ መላ ሰውነቴ ተረበሸ ። እየተንተባተብኩ “እቤቴ

t.me/OLDBOOKSPDF

መሄድ እፈልጋለሁ” ስለው ቃል ሳይተነፍስ መኪናውን ወደመጣንበት አቅጣጫ አዞረው ።

ቅድም እንዲያ ውበቱ እያማለለኝ ትዝታው ዘላለማዊ እንዲሆን የተመኘሁለት ተፈጥሮአዊ ገፅታ ሁሉ ለዛውን አጣ ። ውበቱ ከደስታዬ ጋር አብሮ ተነነ ። ቆራጥነቴ እንደከዳኝ የተረዳው እንባዬ እጢዎቹን ፈንቅሎ ጉንጮቼ ላይ ኮለል አለ ። መሀረቤን ከኪሴ እንዳላወጣ ማልቀሴን ያይብኛል ብዬ ስለፈራሁ እንባዬ እንዳሻው እንዲፈስ ተውኩት ። ፈሰሰም። በጉንጮቼ ወርዶ ፣ የከናፍሬን ጠርዞች አልፎ ፣ ከምላሴ ሲደርስ ጨውማ ጣእሙ እጅጉን መረረኝ — የሀፍረት ፅዋ የተጋትኩ ያህል ። በእንባ ጭጋግ የተጋረደውን አይኔን እመንገዱ ላይ እንደሰካሁ ድንገት እጁ እጄ ላይ ሲያርፍ ቀና ብዬ አየሁት ። እጄን ሳመው ። መሀረቡን ከኪሱ አውጥቶ እጭኔ ላይ ወረወረልኝ ።

አሁን ደግሞ ሀሣብ አሽቀንጥሮ ከሚስዝ ቫን ሁፐር ክፍል ውስጥ አስገባኝ ። ከአሁኑ መጥፎ አጋጣሚ ይልቅ ከዚህ ስሄድ ስለሚጠብቀኝ አሰልቺ ጊዜ እያሰብኩ እጨነቅ ገባሁ ። ‘ይሀን አምጪ ፣ ያን ውሰጂ ፣ ለዚህ ተፈለጪ ፣ ለዚያ ተቆረጪ’ ፣ የሚለው ሙገዝ ያለው ትዕዛዛቸው ብቻ ሳይሆን አይናቸውን ማየት አስጠላኝ ።

በሀሣብ መስጠሜን አይቶ ነው መሰለኝ “እኮ ይብቃሽ” አለኝ ። ድንገት የሰነዘራቸው ቃላት የጠብ ይሁኑ የሰላም ለመለየት ስታገል ትከሻዬ ላይ የጣለው እጁ ገላገለኝ ። ለጠቅ አደረገና “እንደማይሽ በእድሜ ልጅ ስለምትሆኚ እንደኤት እንደማስተናግድሽ ግራ ይገባኛል” አለ ። ይህ ሁሉ ሲሆን እኔ መልስ አልነበረኝም ። እጁን ከትከሻዬ ላይ ሳያወርድ በአንድ እጁ መሪውን እንደጨበጠ መኪናውን እያሽከረከረ ነበር ። ጠመዝማዛውን ፣ አባጣ ጎባጣውን መንገድ አልፈን ቀጥ ያለውን ጎዳና ስንይዝ “እስካሁን በተናገርኩት ቂም ልትይዢብኝ አይገባም ። ሁለታችንም እንዳለፈ ነገር ነው መቁጠር ያለብን ። አየሽ ደግሞ ፣ ቤተሰቦቼ ሁሉ እንደሚጠሩኝ ማክሲም ብለሽ እንድትጠሪኝ ። የእስካሁኑ ከበፊታና አንቱታ ይበቃኛልና ከእንግዲህ እንዳልሰማው” ብሎኝ ከራሴ ላይ ባርኔጣዬን አንስቶ ወደኋላ ወረወረው ። ሳብ አደረገኝ—ወደ እርሱ። አንገቴን መለስ አደረገው — ወደኔ ። ሳመኝ — ግንባሬ ላይ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

“ከእንግዲህ ጥቁር ከፋይ ላትለብሺ ቃል ግቢልኝ” ሲለኝ ፈገግ አልኩ። ከአንጀቱ ሲስቅልኝ ተጫጭኖኝ የነበረ ከባቢው አየር ጭምር የሳቀልኝ ያህል ሁለንተናዬ በደስታ ፈካ ።

ተለያይተን ወደ ማረፊያዬ ስገባ ቀደም ሲል እንዳሰብኩት ከሚስዝ ቫን ሁፐር ጋር መዋሉ ያን ያህል የሚያሸብረኝ ሆኖ አላገኘሁትም ። የእርሳቸው ባህሪይ ተለውጦ ግንኙነታችን አዲስ መልክ ይዞ ሳይሆን ነገ ከማክሲም ጋር ለመገናኘት የመቻሌ ሀሣብ ሁሉን ነገር እንድረሳው ስላደረገኝ ብቻ ነበር ።

ሚስዝ ቫን ሁፐር እንደ ምንም እየቆሰቆሱ ስለ ማክሲም ያጫውቱኝ ጀመር ። ስለ ርብቃ ዝና ፣ ስለ ውበቷ ፣ ስለ ስነ ምግባሯ የወሬ ወሬ የሰሙትን ሁሉ ዘከዘኩልኝ ። ይህን ማንሳታቸው ከማክሲም ጋር የጀመርኩትን ግንኙነት ቢሰሙ ይሆናል የሚል ጥርጣሬ አሳደረብኝ ።

እኔም በዚሁ ሀሣብ ተመስጬ የማላውቃትን ርብቃ በምናብ ቀርጬ እገመግማት ገባሁ ። ከቁመናዋ እስከ ቁንጅናዋ ፣ ከአረማመዷ እስከ አለባበሷ ፣ ከአነጋገሯ አስከ አሳሳቋ — ሁሉንም እያነሳሁ ስጥል ቆየሁ። ማክሲም የሰጠኝን መፅሀፍ — ያን ከትራሴ ስር ያስቀመጥኩትን መፅሀፍ — ሳስታውስ ደግሞ ‘ማክስ’ የሚለው ቃል ብልጭ አለብኝ ። ይህ ስያሜ የርብቃ የግሏ ምርጫ መሆን አለበት ብዬም ገመትኩ።

“እናም ፣ እኔም ከእንግዲህ ማክሲም ብዬ ልጠራው ነው ማለት ነው?” በማለት ለራሴ አንሾካሾኩ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አምስት

“ሄለን በሚመጣው ቅዳሜ ወደ ኒውዮርክ ልትሄድ ነው ። ልጇ ናንሲ ትርፍ አንጀት እያሰቃያት ነውና በፍጥነት እንድትደርሺ ብለው ደውለው ላታል ። እኛም አብረናት መሄድ አለብን ብዬ ወስኛለሁ ። መቼም ይሄ አውሮፓ ቋቅ ነው ያለኝ ፡ ትንሽ አረፍ ብለን እንመለሳለን ። አንቺም በአጋጣሚው ኒውዮርክን ማየትሽ ደስ ሳይልሽ የሚቀር አይመስለኝም?” አሉኝ ሚስዝ ቫን ሁፐር አንድ ቀን ጧት ።

መሄድ የሚለው ቃል ብቻውን ፡ ዘብጠያ የመወርወርን ያህል ነው የቀፈፈኝ ። ሀሣቡ እንዳላስደሰተኝ ከፊቴ ተረዱ መሰለኝ በግርምታ ሲያስተውሉኝ ቆይተው አንዴ አምባረቁብኝ ። “እኔ እኮ ፡ ምን አይነቷ ልጅ እንደሆንሽ ነው ጭራሽ አልገባ ያለኝ ። ያንቺ እኩዮች ይህንን እድል ቢያገኙ ኖሮ እንዴት እንደሚፈነጥዙ ባወቅሽ ። ጅሎ! እድሜ ልክሽን ያላየሽው ስንት አስደናቂ ነገር ነው የምታይው ። ምን ከመሳሰሉ ሎጋ ጎረምሶች ፡ ከበርካታ ብጤዎችሽ ጋር ወዳጅነት የምታፈሪበት ቦታ ነው ። ሞንቴ ካርሎን አልወደድኩትም ስትይ አልነበረም እንዴ?”

“አሁንማ ለምጄዋለሁ” አልኩኝ እምብዛም በመልሱ አላማኝነት ሳልጨነቅ ።

“እንግዲያውስ ኒውዮርክንም ትለምጂዋለሽ ። ይልቅ አሁን ወደ እንግዳ መቀበያው ሄደሽ ፀሀፊው ጉዟችን የሚታናበትን መንገድ እንዲያቀላጥፍልን ንገሪው ። በይ እንግዲህ ቀኑን ሙሉ የሚጠብቅሽ በርካታ ሥራ ስላለ ሞንቴን ትተሽ በመሄድሽ ለማሰቢያ ጊዜም የለሽ”

t.me/OLDBOOKSPDF

ብለው እያሾፉ ሲስቁብኝ እዚያው እንቂያቸው ፡ እንቂያቸው ነበር ያሰኘኝ።

ወደ ጽሕፈት ቤቱ መሄድ ትቼ ወደ መፀዳጃ ክፍል ገባሁና በሩን ዘጋሁት ። እትንሿ ምንጣፍ ላይ ቁጭ ብዬ ጭንቅላቱን ቀብሬ ሀጣብ እጎነጉን ገባሁ ። ነገ ማምሻውን በባቡር ስንሳፈር እኔ ገረድ እመስል የአሮጊቷን የጌጣጌጥ ሻንጣ ይዤ ኋላ ኋላቸው ሱክ ሱክ ስል ፡ እሳቸው እንደ እንዲት ልዕልት ተጀንነው ሲንጎማለሉ ታየኝ ። ከሁሉ በላይ የባሰብኝ ከማክሲም መለየቱና እንዴትስ ብዬ እንደምሰናበተው አለማ ወቄ ነበር ። ምነው ባላወቅሁት? ምነው ያን ያህል ቅንነት ፡ ያን የመሰለ ርህራሄ ባላሳየኝ? በህይወቱ አይቼ የማላውቀውን ያን አይነት መስተንግዶ ምነው ባላቀረበልኝ? እንኳን በእውኔ በህልሜ ያልገጠመኝን ያን ፍቅር የሚባለውን በሽታ አስይዞኝ ይሆን? እኔ እንጃ ። ብቻ ልቤ ሽብር ሽብር ፡ ድንግጥ ድንግጥ ይልብኛል — ስለ እርሱ ሳስብ ፡ ከእርሱ ስለመለየቱ ሲታወሰኝ ።

የነገውን ጉዟችን ከመሰናዶው ጀምሬ ፡ መነሻውን ይዤ ፡ መድረሻው ድረስ ሳጠናጥን ኒውዮርክ የሚጠብቀኝንም አልዘነጋሁትም ። የእናቷ ትክክለኛ ፎቶ ኮፒ የሆነችው የዚያች የሄለን ድምፅ በእዝነ—ልቦናዬ አቃጨለብኝ ። ይቺ ያልተቆነጠጠች ትንሿ ናንሲ ደግሞ ሙልቅቅ ስትል በአይነ—ህሊናዬ ቃኘኋት ። እኒያ ሚስዝ ቫን ሁፐር ብጤዎችሽ ካሉኝ የኮሌጅ ተማሪዎችና የባንክ ቤት ፀሀፊዎች መካከል አንዱ "ረቡዕ ማታ እራት ልጋብዝሽ?" ሲለኝ ፡ ሌላው ደግሞ መቀራረቢያ ያለውን "ለመሆኑ ሞቅ ያለ ሙዚቃ ትወጂያለሽ?" በማለት ጥያቄ ሲያቀርቡልኝ ሰማኋቸው። ምነው ሁሉም ለቀቅ አድርገውኝ እዚህቹ መፀዳጃ ክፍል ውስጥ ሆኜ…

ድንገት በሩ ተንኳኳ ። "ምን እያደረግሽ ነው?" የሚለውን የአሮጊቷን ድምፅ ሰማሁ ። "እሺ ፡ እሺ ፡ ይቅርታ … እየመጣሁ ነው" አልኩና ስታጠብ የቆየሁ ለማስመሰል ቧንቧውን ከፍቼ ወዲያ ወዲህ እየተንጐራደድኩ ድምፅ ለማሰማት ሞከርኩ ።

በሩን ከፍቼ ስወጣ "ምን ያህል እንደቆየሽ አልታወቀሽም? ገና ብዙ የምንሠራው ሥራ አለ እያልኩሽ ይህን ያህል እዚህ መወዘፍሽ ምን

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚሉት ፊሊጥ ነው?" ብለው ገረመሙኝ ።

ቀትር ላይ ከምግብ አዳራሹ ውስጥ ከሚስዝ ቫን ሁፐር ጋር ገበታ ላይ ቀርበን ሳለ አሳላፊው በአጠገባችን ባለፈ በአገደመ ቁጥር ከአሁን አሁን "የእኔ እመቤት ፡ ዛሬ ማታም እራት ከሚስተር ደዊንተር ጋር ነው የሚበሉት?" ብሎ ምስጢሬን ያወጣብኝ ይሆን ብዬ ልቤ ፈራ ።

ቀኑን ሙሉ እቃችንን ስናዘጋጅ ውለን ማምሻውን እራት ከበላን በኋላ ሚስዝ ቫን ሁፐር ሲተኙልኝ ምክንያት ፈጥሬ ወደ መዝናኛው አዳራሽ ወረድኩ ። በአይኔ ብማትርም ላገኘው አልቻልኩም ። ገና ከጅምሩ ውቃቢዬ ያልወደደው እንግዳ ተቀባይ ከሁኔታዬ ተጠራጠረ መሰለኝ "ሚስተር ደዊንተርን እንደሆነ የምትፈልጊው ከሄዱበት እስከ እኩለ ሌሊት እንደማይመለሱ መልእክት ትተዋል" ሲለኝ ይብስ ጠላሁት።

ወደ መኝታ ክፍሌ ሳመራ እያንደረደረ የወሰደኝ የብስጭት ፡ የተስፋ መቁረጥ ፡ የእልህ ፡ የብቸኝነት ጥምር ሀይል ነበር ። ጎኔን ለአልጋው ሰጥቼ በሀሳብ ሀዋውን ስቀዝፍ ፡ እንቅልፍ በአይኔ ሳይዞር እንዲሁ ነጋልኝ ። የዚያን ሌሊት ያለቀስኩትን አይነት መራር ለቅሶ በአሁኑ እድሜዬ ወይም ከዚህ በኋላ የማለቅሰው አይመስለኝም ። ያን ሌሊት ያነባሁት ፡ ትራሴን ዘልቆ ፍራሼን ያራሰው አይነት እንባ ከነግለቱ ከነስሜቱ የሀያ አንድ ዓመት እድሜን ሲያልፉ መምጣቱን እጠራጠራለሁ ።

ወርቸ ተንሳፈፉ ፡ ጎህ ቀደደ ። ጭንቅላቴ ከበደኝ ፡ አይኖቼ ቀልተዋል ፡ ፊቴ አባብጧል ፡ ጉሮሮዬ ተዘግቷል ። ሰው የሆንኩትን እንዳያውቅብኝ ፊቴን በቀዝቃዛ ውሀ ብታጠበው ፡ በኮሎኛ ባባብሰው ፡ በፓውደር ብዳብሰው አሻፈረኝ አለኝ ። አሮጊቷ ፊቴን በጥርጣሬ እያስተዋሉ "ጉንፋን ይዞሻል እንዴ?" ሲሉ ጠየቁኝ ።

"አይ ፡ አልያዘኝም" አልኳቸው

"አንዴ ዝዙ ከተዘጋጀ በኋላ ጊዜ ማባከን አልወድም" በማለት መመሳያቃቸውን ጀመሩና ጉዟችንን አሁኑኑ መጀመር እንዳለብን ፡ ይህንንም ለፀሀፊው እንድነግረው አዘዙኝ ። ይበልጥ ጠላኋቸው ። ይህችን ጠዋት እንኳን በሰላም እንዳሳሳልፋት ማድረጋቸው አይደል? ወይኔ

t.me/OLDBOOKSPDF

ልጅት! ግማሽ ሰአት ፡ ኧረ አስር ደቂቃ እንኳን ለመሰነባበቻ ላይኖረኝ ነው? ብዬ እየሮጥኩ ከመኝታ ክፍሉ ገባሁ ። እንደነገሩ ለባበስኩና ወጣሁ። ቁልቁል ወደ ፅሀፈት ቤቱ ከመሄድ ፈንታ ሽቅብ መውጣቱን መረጥኩ ። አሳንሰሩን ለመጠበቅ ትእግስቱን አጥቼ ደረጃውን ተያያዝኩት ሦስቱን በአንዴ እየተራመድኩ ። ልቤ እንደ ኳስ እየነጠረ ፡ ትንፋሼ ቁርጥ ቁርጥ እያለ የቁጥር 148ን በር አንኳኳሁ ።

"ይግቡ" የሚለውን ድምፅ ስሰማ ገባሁ ። ጸሙን እየተላፊኤ ነበር ። "ምነው? ደህና አይደለሽም እንዴ?" ሲል ጠየቀኝ ።

"መሄዳችን ስለሆነ ለመሰናበት ነው የመጣውት" አልኩት ።

በግርምታ ትክ ብሎ እያየኝ "እስቲ በሩን ዝጊው" አለኝ ። በሩን ዘግቼ እዚያው ፈዝዝ እንዳቆምኩ "ምንድነው የምታወሪው?" ሲል ጠየቀኝ ።

"እውነቱን እኮ ነው ። አሁን መሄዳችን ነው ። ማምሻውን እንሄዳለን ሲሉ ቆይተው ድንገት አመጣጣቸውና አሁኑኑ ካልሄድኩ ሞቼ እገኛለሁ አሉ ። ስለዚህ ከመሄዴ በፊት ቢያንስ ላመሰግንህ ነው የመጣውት"

"ለምን ቀድም ብለሽ አልነገርሺኝም ታዲያ?"

"እንዴት ብዬ? ለእኔ ለራሴ የነገሩኝ ትናንት ነው ። ልጆቹው ትዳሚ እለት ወደ ኒውዮርክ ስለምትሄድ ፓሪስ ተገናኝተን አብረን እንድንንዝ ድንገት የፈጠሩት ሀሣብ ነው ።"

"ኒውዮርክ ይዘውሽ ሊሄዱ ነዋ?"

"ነገር ነገሩማ እንደዚያ ነው ። እኔ ግን መሄዱን በሩቡም አልፈቀድኩትም?"

"ታዲያ ለምን ብለሽ ነው አብረሻቸው የምትሄጂው?"

"መች አጣኸውና? ለእንጀራ ስል እንደምንከራተት እያወቅ ኸው?"

መላጨቱን እያጣደፈ "ቁጭ በይ እስቲ ፡ በአምስት ደቂቃ ውስጥ ለባብሼ እመለሳለሁ" ብሎኝ ፡ ወደ መፀዳጃ ክፍሉ ገባ ።

አልጋው ላይ ቁጭ ብዬ የፈረደባቸው ጥፍሮቼን በጥርሴ እነከረክማ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቸው ጀመር ። ባላገባኝ ገብቼ በጫማዎቼና በክራባቶቼ ስደነቅ እንዳለው ቶሎ ተዘጋጅቶ ከተናፍ አለ ። "በይ ነይ ፡ ቱርስ እየበላን እንጫወታለን" ቢለኝ "አይ ፡ ጊዜ የለኝም ፡ ወደ ዕሕፈት ቤቱ ተልኬ እኮ ነው እግረ መንገዴን ጎራ ያልኩት" አልኩት ።

"ስለ እርሱ ግድ የለሽም ፡ የማዋይሽ ነገር ስላለኝ ነው ።"

ከምግብ አዳራሹ እንደተቀመጥን "ምን ትወስጃለሽ?" ሲል ጠየቀኝ ። ቱርሴን እንደበላሁና ከእንግዲህ ለመቆየት የምችለው አምስት ደቂቃ ብቻ መሆኑን ነግሬው አይን አይኑን ስመለከት ሀሣቤን ችላ ብሎት ለራሱ ቱርስ አዘዘ ። "ሚስዝ ቫንሁፐር የሞንቴ ካርሎ ኮንትራታቸውን ጨረሱ ነው የምትይኝ? መልካም ፡ እንግዲህ እርሳቸው ወደ ኒውዮርክ ሲጓዙ እኔም ወደ ማንደርሌይ ። አንቺስ እመቤት? የትኛውን ትመርጫለሽ ?"

"ሃ ነው ባታሾፍብኝ? ይልቅስ አሰናብተኝና የተላክሁትን ላድርስ"

"በቱርስ ሰአት መቀለድ የምወድ ሰው መስዬሽ ከሆነ ተሳስተሻል ። እንዲያውም ዒት ዒት ይከፋኛል ፡ ያነጫንጨኛል እንጂ ቀልድ ፈፅሞ አያምረኝም ። አሁንም የምሬን ነው የምነግርሽና ምርጫሽን አስተካክይ። ከሚስዝ ቫን ሁፐር ጋር ወደ አሜሪካ መሄድ? ወይስ ከኔ ጋር ማንደርሌይ መጣት? ምርጫው የግልሽ ነው ።"

"ገረድ ወይም ፀሀፊ ትፈልጋለህ ማለት ነው? ወይስ…? አልገባኝም።"

"አይ የኔ ጅል! የምን ገረድ? የምን ፀሀፊ? ሚስት ነው የምፈልገው ነው የምልሽ ።"

"እባክህን አትቀልድ"

"አንቺ ደግሞ ዝም ብለሽ ቀለድክብኝ ፡ አሾፍክብኝ ማለት ታበሳጭሽ"

"ታዲያ ይህ ቀልድ ሳይሆን ምንድነው?"

"የቱ ?"

"ይሄ ሚስት እፈልጋለሁ ፡ ምናምን የምትለው ጨዋታ"

"የኔ እህት ፡ ልብ ብለሽ ትሰሚኝ እንደሆነ እኔ እየቀለድኩ አያደለም። እፈልጋለሁ ማለት እፈልጋለሁ ነው ። አንቺንም ሚስት

t.me/OLDBOOKSPDF

እንድትሆኚኝ እየጠየኩሽ ነው ። በቃ ይሽው ነው ቃሌ ።”

“እረ እባክህን ተወኝ ፣ እኔ ያንተ ሚስት ልሆን ?”

“ለመሆኑ ምን ማለትሽ ነው? ለምን እትሆኚም?” ሲል አፈጠጠ ብኝ ።

“እንዴት ብዬ እንደማስረዳህ እኮ ነው የጨነቀኝ ። እኔ ላንተ ክብር የምገባ ሰው አይደለሁም ማለቴ ነው ።”

“የኔ ክብር ደግሞ ምኑ ይሆን ?”

“ምነው አውቀህ እንዳላወቀ ትሆንብኛለህ? ከማንደርሌይ የበለጠ ምን ክብር ሊመጣ?”

“እንቺም ከሚስዝ ቫን ሁፐር ያልተሻልሽ ጅል ነሽ ልበል? ስለ ማንደርሌይ ምን የምታውቂው ነገር አለና? ለማንደርሌይ የምትገቢ መሆን አለመሆንሽን የሚያውቅ ከኔ ሌላ ማንም እንደሌለ ልታውቂ ይገባል ። ይህንን የጠየቅኩሽ ደግሞ እንዲያው በግብታዊነት ተነሳስቼ ድንገት በተፈጠረው ሁኔታ ተገፋፍቼ ፣ ማለቴ ኒውዮርክ ለመሄድ አለመፈለግሽን ስለነገርሽኝ ይመስልሽ ይሆናል ። ምናልባትም ከዚህ ቀደም ያንሸራሸርኩሽ ፣ እራትም የጋበዝኩሽ ፣ ደግ ለመዋል ብቻ እንደመሰለሽ ሁሉ ዛሬም እንድታገቢኝ የጠየቅኩሽ በዚሁ ምክንያት ነው ብለሽ ታስቢ ይሆናል ። አይደለም እንዴ?”

“አዎና”

“መልካም ፣ ደግነት ብዙ የሚወራለት ባህሪዬ እንዳልሆነ አንድ ቀን ትገነዘቢ ይሆናል ። አሁን ግን ምንም ልትረጂልኝ አልቻልሽምና እዚሁ ላይ እንተወው… በነገራችን ላይ ፣ ጥያቄዬ አልተመለሰም ። ታገቢኛለሽ ወይስ አታገቢኝም ?”

እንዲህ አይነቱ የጋብቻ ጥያቄ በህልሜ እንኳን ሊመጣ ይችላል ብዬ ስላልገመትኩ በጣም ነው ያስደነገጠኝ ። አንድ ንጉሥ የጠየቁኝ ያህል ነው የቆጠርኩት ። ጥርጣሬ ገባኝ ። እኔ እንዲያ ተጨንቄ ድንብርብሬ ወጥቶ እርሱ ግን ምንም ያልተፈጠረ ይመስል ዐጥ ብሎ ቁርሱን ያጣጥማል ። ከመሃከት እንደማነበው ከሆነ ወንዶች ለሴቶች የሚንበረከኩት በሙሉ ጨረቃ እንጂ እንዲህ በማለዳ ለዚያውም ቁርስ ላይ አልነበረም ።

“በይ ተይው ። ጥያቄዬ ተገቢውን ምላሽ ባለማግኘቱ በጣም

t.me/OLDBOOKSPDF

አዝናለሁ ። እኔ የምትወጂኝ መስሎኝ እንጂ እንዲህ ስሜቴን የምታቆስ ይው መሆኑን ባውቅ መች አፈን አበላሽ ነበር?" አለኝ ቀዝቀዝ ብሎ ።

"እንዴ? እወድሃለሁ እንጂ ። ነፍሴ እስኪወጣ ነው የምወድህ ። ደግሞም የማንገናኝ መስሎ ቢታየኝ ሌሊቱን ሙሉ ስንፈቀፈቅ ያደርኩት ባልወድህ ነው እንዴ?" ስለው እየሳቀ እጁን ዘረጋልኝና

"እንዲህ ነው እንጂ የኔ ወለላ ። ያን የምትመኚውን ስልሳ አምስት አመት እድሜ ስትደርሺ ይህንን የዛሬውን ሁኔታ ሳስታውስሽ ምን እንደምትይ ከወዲሁ እየታየኝ ነው" አለኝ ።

መቼም በሀፍረት ቁንጫ አከልኩኝ ። ስለሳቀብኝም በጣም ተናደድሁ ። ሴቶች ለወንዶች እንዲህ ግልፅ ሆነው ስሜታቸውን ማውጣት እንደሌለባቸው የተረዳሁትም ያኔ ነው ።

"እንግዲህ ከስምምነት ላይ የደረስን ይመስለኛል ። የሚስዝ ቫን ሁፐር ባልደረባ መሆንሽ ቀርቶ የኔ ባልደረባ ትሆኛለሽ ማለት ነው ።" በማለት ስለ ሥራ ድርሻዬ እንደ ቀልድ እያደረገ ጠቃቀሰልኝ ።

አሁንም የሚቀልድብኝ መስሎኝ በሀሣብ ሰጥሜ ሳለ "ትንሽ ነገሩን እንዳከበድኩብሽ ይሰማኛል ። በወግ በማእረግ ታጭተሽ ፡ ለደመቀ የቀለበት በአል አለመታደልሽ ቅሬታ እንደሚያሳድርብሽም ይገባኛል ። ግን ምንም አይደለም ። ለዚህ ደስታ ባላበቃሽም የጫጉላ ጊዜያችንን ለማሳለፍ ግን ቬኒስ ይገርሽ እንደምሄድ ቃል እገባልሻለሁ ። ብዙም ሳንቆይ ግን ወደ ማንደርሌይ እንሄዳለን" ሲል አፅናናኝ ።

በየሁኔታው ጭልጥ እያለ የሚዋልለው መከረኛ ሀሣቤ እያንሳፈፈ ከማንደርሌይ ጣለኝ ። ግቢው ውስጥ ስንፈላሰስበት በመናፈሻው ውስጥ እየተዘዋወርኩ ማክሲም የሚወዳቸውን አበቦች እየቀጣጠፍኩ ሳዘጋጅ ፡ ሀገሩ ተሰብስቦ በአድናቆት ሲያስተውለኝ ፡ በአዲሱ ስሜ 'ማስዝ ደዊንተር' እያለ ሲጠራኝ ፡ በየጊዜው እንግዶች ለምሳ እየጋበዝኩ ግሩም ድንቅ የሚሰኙበትን መስተንግዶ ላቀርብላቸው ፡ ማክሲም በእኔ በእጅጉ ሲረካብኝ ፡ የአድናቆት ቃላቱን ሲቸረኝ …

እኔ ከምናቤ ጋር ስጫወት ማክሲም ቁርሱን አገባዶ ለመነሣት ይዘጋጅ ነበር ። "ለመሆኑ ለሚስዝ ቫን ሁፐር ዜናውን አንቺ ታበስሪላ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቸው እኔ?" ሲል ጠየቀኝ ።

"እረ ምን በወጣኝ ፡ ሆ! ደግሞ በዚያ ምላሳቸው ያንገብግቡኝ እንዴ! እንተው ትሻላለህ" አልኩትና ተነስተን ወጣን ። እጇን ለቀም አደረገና "የአርባ ሁለት አመት ሰው ፡ ሽማግሌ ይባላል ወይስ አይባልም?" ብሎ ጠየቀኝ ።

"በፍጹም ፡ እኔ እንዲያውም ልጅ እግር ወንድ አልወድም" ስል መለስኩለት ጥድፍ ፡ ችኩል ብዬ ።

"ስላላጋጠመሽ ነው ።" አለ ማክሲም

ከክፍላችን በር ላይ ስንደርስ "እንግዲህ እንዳልሺው ጉዳዩን እኔው ብቻዬን እጨርሰዋለሁ" አለና አያይዞም "በነገራችን ላይ ጋብቻችንን በአጭር ጊዜ ውስጥ ብናደርገው ምን ይመስልሻል የሙሽራ ልብስና ከዚሁ ጋር የተያያዙ ሌሎች ዝባዝንኬዎች የምትሺ አይመስለኝም ። ካስፈለገም በጥቂት ቀናት ሊዘጋጅ ይችላል ። ከዚያም ተፈራርመን የጋብቻ የምስክር ወረቀታችንን ይዘን ወደቪኒስ ወይም ደስ ወደሚልሽ ስፍራ መሄድ ነው" በማለት ሀሣቤን ጠየቅኝ ።

"በቤተክርስቲያን ፡ በተክሊል ላንጋባ ነው ማለት ነው? እንዴ ፡ ቬሎ ላይኖር? ሚዜዎች አጃቢዎች ሳይኖሩኝ? ዘፈን ፡ ጭፈራ በሌለበት ለቅሶ ይመስል እንተቲን ሰብሬ ልወጣ? እረ ደግሞስ የእኔ ቢተር ፡ ያንተ ወዳጅ ዘመዶች አይገኙም ማለትህ ነው?" በማለት በጥያቄ አጣደፍኩት ።

"ከዚህ ቀደም በዚህ አይነት ሥነ ሥርአት ማግባቱን ዘንጋሽው እንዴ?" አለችና ለአፍታ ፀጥ ካለ በኋላ "እና ፡ ምን ይመስልሻል?" ሲል ጠየቀኝ ።

"በእርግጥ ጋብቻችንን እቤታችን ውስጥ የምናከብር መስሎኝ ነበር እንጂ ቤተክርስቲያኑንም ሆነ የሰውን ግርግር አልፈትደውም" ብዬ መለስኩለት ።

ፈገግታ ተለዋወጥንና በሩን ከፍቶልኝ እኔ ቀድሚ ገባው ። "እንቺው ነሽ? እንዲህ ነዋ የኛ ኮረዳ" በማለት ሚስዝ ቫን ሁፐር በድንፋታ ተቀበሉኝ "ምን ውሎሽ ነበር እስካሁን በይ? ምን ቀረኝ? አገር ላገር ሳፈላልግ ? እቢሮ ሦስት ጊዜ ብደውል ከደጁም አልሠርሽ አሉኝ"

t.me/OLDBOOKSPDF

ድንገት አንዳች ስሜት ቢወረኝ መሳቅ ከጀለኝ ፣ ጩኺ ጩኺም አለኝ ። ምኑንም ሳልሞከረው ማክሲም ደረሰልኝ ። ‘‘ይቅርታ ፣ የኔው ነው ስሀተቱ ፣ እርሷ ምንም አላጠፋችም’’ ብሎ ወደነበሩበት ሲጠጋ መደናገጥ ቃጣቸው ።

ትቼአቸው ወደ መኝታ ክፍሌ ገብቼ ከተከፈተው መስኮት አጠገብ አረፍ አልኩ ። ለቀዶ ጥገና የገባ በሽተኛን የመጨረሻ ሁኔታ ለመስማት ቁሜ ብሎ በጭንቀት እንደሚጠባበቅ አስታማሚ ነው የሆንኩት ። ግድግዳው ደግሞ ከፋ ሲለው ያለ ቅጥ ወፈረና የሚሉትን መስማት አልቻልኩም ። ለምኑም ለምኑ ምንም የማይሳነው ሀኪቤ ግን ከተናገረ አለና ‘‘ይገርምዎታል ፣ ገና መጀመሪያ ያየኋት ቀን ነው በፍቅሯ የተነደፍኩት። ከዚያ በኋላማ በየቀኑ ስንገናኝ ቆየንና አሁን ለመጋባት ተስማምተናል እልዎታለሁ’’ የሚለውን የማክሲምን ድምፅ ከእዝነ ልቦናዬ ይለው ። አሮጊቷም ‘‘ምን አይሰማ ጆሮ! በህይወቱ ሰምቼው የማላውቀው አይነት ልዩ የፍቅር ታሪክ እኮ ነው የምትነግረኝ ሚስተር ደዊንተር’’ ሲሉ በሀሳብ ሰማኋቸው ።

የማፈቅረውን ሰው ፣ ማክሲምን ለማግባት መብቃቴ ምን ያህል ደስታ እንደሚያጎናፅፈኝ እየታሰበኝ ጉልበቴን እንደታቀፍኩ ፍንድቅ ድቅ አልኩ ። ወዲያው ደግሞ ሌላ ተግራሪ ስሜት መጣብኝ ። ምነው ማክሲም ግን አንዴም እንኳን ‘‘እወድሻለሁ’’ የሚል ቃሉን ያልሰጠኝ? አልኩ ። መላ ትኩረቴን ያዋለው በጋብቻው ጥያቄ ላይ ስለነበር እንዳገባው መጠየቁ በቂ ነው አልና ወዲያው ደግሞ ቢሆንስ? ምንም ቢሆን እንደሚያፈቅረኝ ለመንገር ይችል ነበር እላለሁ ። ቀደም ባሉት ቀናትስ ሊነግረኝ አይችልም ነበር እንዴ? አሁን ግን ይሙት ርብቃን ከማግባቱ በፊት እንደሚወዳት ሳይነግራት ቀርቶ ነው? ለሷማ ያውም አንዴ ብቻ? አንድ ሺህ ጊዜ ‘‘እወድሻለሁ ፣ እሞትልሻለሁ’’ ሳይላት ይቀራል? አይደረግም ። ታዲያ ምነው ለኔ ጊዜ? እንዲያው ሳት ብሎት እንኳ አንድ ጊዜ ብቻ ቢተነፍስልኝ ምን ነበረበት?

ይህንና መሰል መጥፎ ሀሳቦችን ላወጣና ላወርድ ቆይቼ ምን አይነት ሰይጣን ነው እንዲህ የሚያዘናጋኝ? በማለት እራሴን ታዝቤው ቀና ቀናውን አስብ ገባሁ ። ቢወደኝ እንጂ ባይወደኝማ እንዲያገባኝ ማን አስገደደውና? ቢያፈቅረኝ አይደለም እንዴ በሚስትነት ማንደርሌይ

t.me/OLDBOOKSPDF

ይዞኝ ሊሄድ ቃል የገባልኝ? ብዬ ብልሹ ሀሳቤን አደስኩት ።

እንዲያውም ሺህ ጊዜ ከሚደረደር አፍአዊ "እወድሻለሁ" የአንድ ጊዜ ልባዊ የጋብቻ ጥያቄው እንደበለጠብኝ የተገነዘብኩት ውሎ አድሮ ነው ። ሀልቆ—መሳፍርት የሌላቸው የዘመኑ አፈ—ጮማ ወንዶች ልቀንጠስ ፣ ልበጠስ በሚል ሽንገላ ሲደልሉ ቆይተው የልባቸው ሲደርስ ገሸሽ ማለታቸውን የምናየው አይደለም እንዴ? ለፍቅር ፣ በፍቅር ፣ ስለ ፍቅር ሞትን እያሉ ነገ በተግባር የማይተረጉሙትን ባዶ ተስፋ የሚሰጡ ፣ ምለው ተገዝተው የደረደሩትን ቃል ከነመተንፈሳቸው የሚዘነጉትን ቤታቸው ይቁጠራቸው ።

ሀሳብ ቡዝዝ ያደረገው አይኔ ሲንከራተት ማከሲም ካዋሰኝ የግጥም መፅሀፍ ላይ አረፈ ። 'አንቺው እንጂ ፣ ምን ትጠብቂያለሽ? የመጀመሪያውን ገፅ ግለጪው' የሚል ሰይጣናዊ ድምፅ በጆሮዬ አንሾካሾከ 'ወይድ እባክህ' ብዬ ትእዛዙን ላለማክበርና እራሴን ለማረጋጋት ብጥርም የኋላ ኋላ መረታቴ አልቀረም ። አዛጋሁ ፣ ተንጠራራሁ ። እያዘገምኩ ሄጄ መፅሀፉን ሳነሳው ተደናቀፍኩና ከእጄ ወደቀ—የመጀመሪያው ገፅ ተገለጠ ። "ለማክስ ፣ ክርብቃ" የሚለው ዕሁፍ ቦግ ብሎ ታየኝ ። ከዚህች ሙት ጋር መያያዙ ቢበቃኝስ ? አርፋ ብትተኛ ምን አለበት ? የሚል ቅን ሀሣብ ብልጭ ቢልብኝም አልፀናሁበትም ።

ፊደላቱ ነፍስ የዘሩ ይመስል በአይኔ ስር ውር ውር ሲሉብኝ ቀለሙ ፣ ሞቅ ደመቅ ብሎ ብርሃኔን ሲፈታተነው ትእግስቱ ተሟጠጠ ። መቀስ እንስቼ ገፁን ከርከሜ አወጣሁት ። ብጥስጥስ አድርጌ ቅርጫት ውስጥ ወረወርኩት ። ሀሳቤ ግን ከቁርጥራጮቹ ላይ አልነቀል ስላለኝ ቅርጫቱ ውስጥ አቀርቅሬ መመልከት ጀመርኩ ። እያንዳንዱ ፊደል ይበልጥ እየጎላ፣ ቀለሙ ይበልጥ እየደመቀ ስላስቸገረኝ ክብሪት ለኩሼ ቁርጥራጮቹን አመድ አደረግኳቸው ። በተለይ ጥምዝምዙ 'ር' በእሳቱ እየተጥመለመለ እስከመጨረሻው እስኪወድም ጠብቄ እጄን ታጠብኩ ። በዘመን መለወጫ ዋዜማ ያለሁ እየመሰለኝ ልዩ ደስታ ወረረኝ ፣ አዲስ የተስፋ ስሜት ከበበኝ ።

በዚህ የደስታ ስሜት ውስጥ እየዋኘሁ ሳለ በሩ ተንኳኳ ። ተከፈተ ። ማከሲም ብቅ አለና "ጨርሼ መጣሁ ። በመጀመሪያ ፣ ነገሩ እንግዳ ሆኖባቸው ተደናግጠው ነበር ። ድንጋጤው ሲተዋቸው ግን በጋብቻችን

t.me/OLDBOOKSPDF

ላይ የመገኘት ምኞት እንዳላቸው ዳር ዳር ሲሉብኝ ምንም እንደማያስፈልግ ጠንከር አልኩባቸው ። ሳይጥማቸው የግዳቸውን ተዉት ። በይ እስቲ እንግዲህ እቢሮ ወርጂ ባቡሩ እንዳያመልጣቸው እንዲያደርጉ ልንገርላቸው ። አንቺም ገብተሽ አነጋግሪያቸው'' ብሎኝ ፈገግ አለና እጁን አውለብልቦልኝ ወጣ ።

እየከበደኝ ሄድኩ ። ሚስዝ ቫን ሁፐር ጀርባቸውን ለበሩ ሰጥተው ከመስኮቱ አጠገብ ቁመው ሲጋራቸውን ሲምጉ አገኘኋቸው ''በጄ'' ብለው ጀመሩ ሽሙጣቸውን ''እንዲህ ነው የኛ ስልጡን ፡ ለካስ በእኔው ያመወዝ ለሁለት አሳዳሪ ስታገለግይ ከርመሻልና? አንተ መስበርሽን ላየ ምንም የማታውቂ እርግብ እኮ ነው የምትመስዪው ። እንዲህ እባብ መሆንሽን እኔስ የት አባቱ አውቂ? ሰውን ማመን ቀብሮ ነው አሉ ፡ እውነታቸውን ነው ። እንዴት ነው እንዲህ በአጭር ጊዜ የቀናሽ በይ?''

ምን ብዬ ልመልስ? እንደ ንግግራቸው ሁሉ ፈገግታቸውም አስጠላኝ ። ''እኔን በእንፍሉዌንዛ ለጣለልሽ አምላክ ምን እንደተሳልሽ ለት እንጃ! ውሎሽ የት እንደነበረ ፡ ልብሽን ምን ይሰውረው እንደነበረ አሁን ነው የገባኝ ። ግን እኮ ምነው ብትነግሪኝ ኖሮ?'' ሲሉ ጠየቁኝ ።

''ይቅርታ ያድርጉልኝ'' ብላቸው ከላይ እስከታች ገረመሙኝና ''ደግሞ ቶሎ ልንጋባ ነው ያለኝ መሰለኝ ። እሪ ታድለሻል ። ለምን? እንዴት? ብለው የሚጠይቁ ወላጆች የሉሽ ። ብቻ ፡ እኔ ምን አገባኝ? እንደፍጥርጥራችሁ ። እኔ ቫንሁፐር ከደሙ ንፁህ ነኝ ። ያንቺስ ይሁን ፡ እኔን ግርም የሚለኝ የእርሱ ጓደኞች ምን እንደሚሉት ነው ። በእድሜ ብዙ እንደሚበልጥሽ ግን ታውቂያለሽ?'' አሉኝ በንቀት ፡ በጥላቻ እያስተዋሉኝ ።

''እርባ ሁለት አመቱ ብቻ እኮ ነው ። እኔም ብሆን ከእንግዲህ ልጅ አይደለሁም ።'' አልኳቸው ።

ከትከት ብለው እየሳቁ ''እሪ እውነትም ልጅ አይደለሽም'' አሉኝና ውስጤን በሚመረምር አይነት ልዩ አስተያየት ቃኝተውኝ ሲያበቁ እንደ ልብ ወዳጅ ቀዝቀዝ ፡ ለዘብ ብለው ''ብቻ አንዳንድ አጓጉል ነገር አድርገሽ እንዳይሆን?'' በማለት ጠየቁኝ ።

''ምን ማለትዎ እንደሆነ አልገባኝም''

t.me/OLDBOOKSPDF

ትከሻቸውን እየነቀነቁና እየሳቁብኝ "ተዪው ፣ ተዪው ግድ የለም … ከድሮ ጀምሮ የእንግሊዝ ልጃገረዶች ቆዳ ሞኞች ናቸው እንዳልኩኝ ነው። እንግዲህ አንቺን ከእጮኛሽ ጋር ትቼሽ ብቻዬን ወደ ፓሪስ መጓዜ ነዋ። በሠርጋችሁ ላይ እንድገኝ የፈለገ አይመስለኝም" አሉኝ ።

"ማንንም ለመጋበዝ የሚፈልግ አይመስለኝም ። እርስዎ ደግሞ መሄድዎ አይደለም እንዴ?"

"እህህ" አሉና ፊታቸውን በፓውደር ማበስ ጀመሩ ። "አንቺ እቱ ፣ ሞኝ እየመሰልሽ የዋዛም አይደለሽ ። ብቻ ሰውዬው ቀላል ሰው እንዳይመስልሽ ። ባህሪዩን በደንብ ማጥናት ይኖርብሻል ። ከብዙ ነገር ተገልለሽ መኖርሽን ደግሞ አትዘንጊው ። እኔ በሥራ ወጥሬሽ ለዚህ እንዳላበቃሁሽ ሀሊናሽም ያውቀዋል ። ታዲያ የማንደርሌይ እመቤት ለመሆን የሚጠብቅሽ ሥራ ቀላል አይደለም ። እውነቱን ለመናገር ደግሞ ችግሩን ትወጪዋለሽ የሚል ቅንጣት እምነት የለኝም ። ልምዱ የለሽ ፣ አካባቢውን አታውቂው ። በእኔ እንግዶች ፊት አንድ ቃል ሉሞተንፈስ አንደበትሽ እስርስር የሚለው ሴትዮ በየጊዜው ለግብግ በሚሰባሰቡ በእርሱ ጓደኞች ፊት ምን ልታወሪ ነው? ምን ሊውጥሽ? ካሁኑ አስቢበት። እኔ ውርድ ከራሴ ብያለሁ ።"

አነጋገራቸው ከአንድ ሰአት በፊት በኔው ላይ ተቀርጾ የነበረውን ሀሣብ በሙሉ አካቶ የያዘ በመሆኑ በዕሞና ነበር የማዳምጣቸው ።

አሮጊቷ ንግግራቸውን ቀጥለው "እንደ እውነቱ ከሆነ ደስታሽን የማይመኝ የለም ። እጅግ በጣም መልከ መልካም ሰው እንደገጠመሽ ይታየኛል ። ሆኖም ይቅርታ አድርጊልኝና እንደኔ ከሆነ እድሚ ልክሽን የሚፀፅትሽ ሳህተት ውስጥ ነው የተዘፈቅሽው" አሉኝ ።

ምናልባትም የማታ ማታ ቅንነት ተጠማቷቸው ፣ የልባቸውን ሲነግሩኝ ይሆናል የሚል ግምት ቢያድርብኝም ልቦናዬ ግን ሊቀበላቸው አልፈቀደም ። ያሉት ሁሉ ሀቅ ቢሆንም ከእርሳቸው መስማቱን አልፈለግኩም ። ሆን ብለው ፣ በሴትነታቸው ባደረባቸው ልዩ ስሜት እንደሆነስ ጋብቻውን ያልፈለጉት ? በሚል ጥርጣሬ ሀሣባቸውን ሁሉ ውድቅ አደረግኩት ።

ያሉትን ቢሉም ከመውጣታቸው በፊት ግን የማበረታቻ ቃላቸውን

t.me/OLDBOOKSPDF

ለግሰውኝ ፣ መልካሙን ሁሉ ይመኙልኛል ብዬ አይን አይናቸውን ስማዐን እንደዚያው እየሳቁብኝ ‘‘መቼም የሚያገባኝ ስላፈቀረኝ ነው ብለሽ የምትኩራሪ አይመስለኝም ። ባዶ ቤት ውስጥ ብቻውን መኖሩ ናላውን ብጥብጥ እንዳደረገው አሁን ከመግባትሽ በፊት እንኳ እያጫወተኝ ነበር ። ወትሮውንስ ይህን ያህል የሚጃጃል ተራ ሰው መች ሆነና? የምትሆነውን መች አጥቶ? እርሱ እቴ ፣ ቤት ጠባቂ ነው የሚፈልገው እንጂ ሌላማ…’’ ብለውኝ ውልቅ አሉ ።

‘ቆሽቱን እንዳሳረሩት ቆሽትዎ ይረር’ ነበር የውስጣዊ ልሳኔ ርግማን ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ ስድስት

ማንዬት በባተ ሰሞን ነበር ማንደርሌያ የገባነው ። ሎንዶንን ለቀን ስንወጣ ዝናቡ እየረገጠው ነበር ። ማክሲም ''ማንደርሌይም እንዲህ ሞቃቃም እንዳይመስልሽ ። በብሩሁ ሰማይ ላይ ሯ የምትለዋ ወሀይ ናት የምታስተና ግደን'' እንዳለኝ ሁሉ እየተረብን በሄድን መጠን ዝናቡ እየቀለለ ፡ ደመናው እየገለጠ ፡ ሰማዩ እየፈካ ማየቱ በጣም አስደሰተኝ ።

''እይዞሽ ፡ ደርሰናል ። ሶስት ኪሎ ሜትር ያህል ቢቀረን ነው ። እዚያ ኮረብታ ላይ ችምችም ብሎው የሚታዩት ዛፎች ያሉበት ነው ማንደርሌይ ማለት'' ሲል ማክሲም ሊያፅናናኝ ሞከረ ። ጥርሴ የማይን ብልጭ ይበል እንጂ ውስጥ አካሌ ተናወጠ ። ማንደርሌይን ለማየት እንዳልጓጓሁ ሁሉ ፡ ምነው ባልመጣሁ አሰኘኝ ። ሚስዝ ደዊንተር ተብዬ የማንደርሌይ እመቤት ለመሆን እንዲያ እንዳልቸኮልኩ ፡ ወግ ማእረጉ ቀርቶብኝ ድህነቴንና ተራ ሰውነቴን እንደያዝኩ መኖሩ በስንት ጣእሙ የሚል ሀሣብ ተመላለሰኝ ። ከጋብቻችን በኋላ ባሳለፍናቸው ሰባት ሳምንታት ውስጥ የተላበስኩት ደስታ ፡ ያደረብኝ ኩራት ፡ የነበረኝ በራስ የመተማመን ስሜት ንፋስ ያየው ገለባ ሲሆን ተሰማኝ ። ለመጀመሪያ ጊዜ ት ቤት እንደገባች ሀዘን ልጅ ወይም ከቤቷ ወጥታ የማታውቅና ምንም ልምድ ሳይኖራት ለመጀመሪያ ጊዜ ማርድና እንደጀመረች ኮረዳ ነው የሆንኩት ። እጅግ ከመደናገጤ የተነሣ ማራው ቱኝ ፡ ቱኝ ማራ ሆነብኝ።

''እዚህ ሞራሽ አንድም ጠብታ አልሣለም እኮ ። እሬ ይዘንን የዝናብ ልብስ መዲያ ልሣለው ። እስቲ አንቺም የደረብሽውን ወፍራም ኮት አስተካክዪው ። ሎንዶን ውስጥ በርካታ ልብሶች መግዛት ስትችዪ እያጣደፍኩ አመጣሁሽ አይደል?'' አለኝ ማክሲም እጁን እይኔን እያየ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንተን እስካልተሰማህ ፡ እኔ ግድ የለኝም ።"

"የምትገርሚ ፍጡር እኮ ነሽ ። አብዛኞቹ ሴቶች ጢት ማታ ስለ ልብሳቸው ከመጨነቅ ሌላ ምን ሥራ አላቸው?" ብሎኝ ጥቂት ከተንዝን በኋላ ከአቋራጩ ስንደርስ ደግሞ "ይሽውልሽ እንግዲህ ፡ ማንደርሴይ ገባን" ሲለኝ የማደርገው ቢጠፋኝ የተቀመጥኩበትን ወንበር በሁለት እጆቼ ጥርቅም አድርጌ ያዝኩት ።

የብረት መዝጊያውን አልፈን ስንንዝ ሰው በየመስኩቱ እየተንጠራራ ሊያየኝ ሲሞክር ሽብር ልቤን አናጋው ። ሰዉ እኔን ለማየት የጓጓበትን ምክንያት ፡ ምን እያለ እንደሚንሽኳሸክብኝ ብቻዬን አወጣና አወርድ ገባው ። ማክሲም አወቀብኝ ። እንዳወቀብኝም አወቅኩበት ። ሊያረጋጋኝ ሞከረ ። "ሰዉ አንቺን ለማየት ቢጓጓ አይፈረድበትም ። ምናልባትም ሰሞኑን ሁሉ ስላንቺ ሲያወሩ ይሆናል የከረሙት ። ሙሽራ መሆንሽን አትርሺ ። እስኪያዩሽ ድረስ ምን ትመስል ይሆን? እያሉ ቢወያዩ የተለመደ ነውና እምብዛም ሊደንቅሽ አይገባም ። ሁለው አድረው ማንነትሽን ሲረዱ ፡ ባህሪሽን ሲለምዱ እንደሚወዱሽ እርግጠኛ ነኝ ። ለቤት ውስጥ ጣጣውም ቢሆን ሚስዝ ዳንቨርስ እስካለች ድረስ በእርሷ ላይ መጣል ነው ። ለመጀመሪያ ጊዜ ጠባይዋ ትንሽ ግር ያሰኝሽ ይሆናል ። ያም ቢሆን ፡ እስክትለምጃት ነውና እምብዛም ሊያሳስብሽ አይገባም… ያንን ቁጥቋጦ አየሽው? አበቦቹ ሲፈነዱማ አካባቢውን በውብ ሀብረ—ቀለማቸው ያስጌጡታል ። " አለኝ ።

ሀሣብ እየናጠኝ ምንም መልስ ሳልሰጠው እንደፈዘዝኩ ለይስሙላ አካባቢውን እቃኝ ነበር ። የግቢውን መንገድ ስንያያዘው መንገዱ የገመትኩትን ያህል ካለመስፋቱም በላይ እንደ እባብ ጥምዝምዝ ማለቱ አስገረመኝ ። ግራና ቀኝ የበቀሉት ዛፎች ቅርንጫፎቻቸውን እርስ በርስ በማቆላለፍ የሰሩት ተፈጥሯዊ ቅስት ውብ የአይን ማረፊያ ነው ። አልፎ አልፎ ባጋጠመው ቀዳዳ ሾልኮ የገባው ጨረር መንገዱ ላይ ካሳረፈው ወርቅማ ፈርጥ ሌላ እጅ ለእጅ የተያያዙት ቅጠሎች የወሀይን ብርሃን ላለማስገባት ያደሙ ይመስል መተላለፊያው ሁሉ ደብዘዝ ያለ ነው ። ፀጥ ረጭ ከማለቱም በላይ ከአውራ ጎዳናው ላይ በጥፊ ሲያፏሉኝ የቆየው ነፋስ ዙሪያው ታጥሮበት የመግባት እድል አላገኘም ። ወደ ሽለቆው አሽቆልቁለን በትንሿ ጅረት ላይ የተዘረጋውን ድልድይ ስናልፍ ጫካው

t.me/OLDBOOKSPDF

ይበልጥ ጥቅጥቅ እያለ ሄደ ።

ዙሪያዬን ከከበበኝ ደን ሌላ ምንም አልታይሽ ቢለኝ ሜዳ የሚባል ነገር ፈፅሞ የለም ማለት ነው? ቤቱስ እምኑጋ ይሆን? መናፈሻዎቹስ የት አሉ? የሚሉና መሰል ሌሎች ጥያቄዎች በአእምሮዬ ይጉላሉ ጀመር ።

በዚህ ሀሣብ ተወጥሬ ጥቂት እንደቆዝን ጫካው እየላላ ፡ መንገዱ እየሰፋ፡ አካባቢው እየገለጠ ሲሄድ ታየኝ ። ዙሪያውን በአረንጓዴ መስክና ልብን በሚያሸፍቱ አዐዶች ተከቦ ፡ ውበቱንና ግርማ ሞገሱን እንደተጎናፀፈ ማንደርሌይ ከፊቱ ጉብ አለ ። ከበራፉ እንደቆምን አይኔ ከአንደኛው መስኮት ዘልቆ ሲገባ አዳራሹ በሰው መሞላቱን አየሁ ። ማክሲም ''ምን ማለት ነው ይህች አሮጊት? እንዲህ አይነቱን ግርግር እንደማልወድ እያወቀች?'' ብሎ ሲያጉረመርም ሰማሁት ።

''ምንድነው ነገሩ? ይህ ሁሉ ሰው ምን እያደረገ ነው?'' ስል ጠየቅኩት ።

''ምን ታደርጊዋለሽ? እንግዲህ አንዴ ከሆነ እንደሁኔታው መቀበል ነው'' አለኝ ማክሲም ብስጭትጭት እያለ ''ሚስዝ ዳንቨርስ የቤቱ ፡ የግቢው ሠራተኛ አንድም ሳይቀራት ሰብስባልናለች ። ቢሆንም ያን ያህል የሚያስጨንቅሽ አይደለም ። ማንኛውንም ነገር እኔው እወጣዋለሁና ፈፅሞ አታስቢ ።''

በደመነፍስ እየተመራሁ የመኪናውን በር ለመክፈት ስታገል አንድ ጠና ያሉ ሰው በፍጥነት ደርሰው ከፈቱልኝ ። ሻንጣዬን አውርደው ወደ ማክሲም ሲጠጉ ''እንደምን ከረምክ ፍሪዝ ?'' ሲል ጠየቃቸው ።

''ደህና እግዚአብሔር ይመስገን ። እንኳን በሰላም ገባችሁልን ጌታዬ''

''ከሎንዶን ስንወጣ የጣለው ዝናብ ፡ ዝናብ አይምሰልህ ። እዚህ ጭራሹን አላካፋም ልበል?''

''አረ በጭራሽ ፡ ይኸው ድፍን ወራችን ጠብታም አላየን'' አሉ የእልፍኝ አስከልካዩ ።

''እርስቱስ ይሁን ። ቀዬአችን ሰላም ነው? ሰውስ?''

''ክብሩ ይስፋ ፡ ሁሉም ነገር ሰላም ነው ጌታዬ ። እናንተስ ሰላም ከረማችሁ? እመቤቱስ እንዴት ነዎት?''

''ደህና ነን ። እናመሰግናለን ፍሪዝ ። ብቻ መንገዱ ስላደካከመን ሻይ

t.me/OLDBOOKSPDF

በእስቸኳይ እንዲዘጋጅልን እንድታደርግ… ግን ይህ ሁሉ ትርምስ ለምን አስፈለገ?"

"የሚስዝ ዳንቨርስ ትእዛዝ ነዋ ፡ ጌታዬ"

"መች አላሁት? ይህ እንደሚጠብቀን ቀደም ብዬ መገመት ነበረብኝ" አለና ማክሲም ወደ እኔ ዞር ብሎ" ነይ እንጂ ፡ ብዙም አያቆየንም ። ቶሎ ተገላግለን ሻያችንን እንጠጣለን" አለኝ ።

የእልፍኝ አስከልካዩና ሌላ ሠራተኛ እቃችንን ይዘው እየተከተሉን ከአዳራሹ ገባን ። ያ ሁሉ አይን አንደ ሲያፈጥብኝ በቁም የሚያሚሚኝ ያህል ነው ያስፈራኝ ። ብርክ ያዘኝ ። እንዲት ድፍን ጥቁር የለበሱ ፡ ረጅም፡ አጥንታቸው ያገጠጠ አሮጊት ከሰው መሃል ብቅ ብለው ወደኔ መጡ። በኩሩነታቸውና በራስ የመተማመን ስሚታቸው እየቀናሁ እጇን ዘረጋሁላቸው ። እጃቸውን ስጨብጠው ግን እንደ በድን አካል እጇ ውስጥ ሲዝለፈለፍ ግርም አለኝ ።

"ሚስዝ ዳንቨርስ ይባላሉ" ብሎ ማክሲም አስተዋወቀን ። ሴትዮዋ እጇን እንደጨበጡ ይናገሩ ጀመር ። ትክ ብለው የሚያዩዋቸው ጉድጓዳ አይኖቻቸውን መቋቋም ያቃታቸው አይኖቹን ወዲያ ወዲህ አንከራተትኳቸው ። ያ ፡ በድን ያልኩት እጃቸው ቀስ በቀስ ነፍስ እየዘራ ሲመጣ እንዳች የመረበሽና የሀፍረት ስሜት አጫረብኝ ።

በባልደረቦቻቸውና በራሳቸው ስም የእንኳን ደህና መጣችሁ አጭር ንግግር ማድረጋቸው ትዝ ቢለኝም የተናገሩትን ሁሉ አውን ማስታወስ አልችልም ። ዛሬም ቢሆን የዚያን ወቅቱን ሁኔታ ባስታወስኩ ቁጥር በጆሮዬ እየገባ የሚዘገንነኝ እንደ እጃቸው ሁሉ ቀዝቃዛና በድን የነበረው ድምፃቸው ነው ። ንግግራቸውን እንዳበቁ ምላሽ ያጠብቁ ይመስል እዚያው ቁመው ሲያፈጡብኝ ፊቱ ቀላ ። ጥቂት የምስጋና ቃላት አጉመተመትኩ ። ከመደናገጤ የተነሣ የያዝኳቸውን ጓንቲዎቼን ለቀቅኳቸው ። አሮጊቷ አንስተው ሲሰጡኝ በንቀት ፈገግ ከማለታቸውም ሌላ ሥነ ምግባር የጎደለኝ አድርገው እንደገመቱኝ ከገፅታቸው ይነበብ ነበር ።

ማክሲም ከንዴን ያዝ አድርጎ የምስጋና ንግግሩን ካደረገ በኋላ ወደ ቤተመፃህፍቱ ይዞኝ ገባ ። ሁለት ውሾች ከምድጃው አጠገብ እየሮጡ መጥተው ተቀበሉን ። አንድ አይናዋ እናቲቱ ውሻና ልጇ ጃስፐር ከማክሲም ጋር ተሻሽተው ፡ እግሩ ስር እየተሽለኮለኩ ተጫወቱ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሲያበቁ ለኔም የእንግድነት ድርሻዬን አልነፈጉኝም ።

ባርኔጣዬንና ኮቴን አውልቁ አረፍ ስል ልዩ እፎይታ ተሰማኝ ። አራቱን ግድግዳዎች እስከ ጣሪያው ድረስ ያለበሱት መፃህፍቱን ጨምሮ ቁሳቁሶቹና መስኮቶቹ በእጅጉ አስደሰቱኝ ። የክፍሉ ምቹነትና አጠቃላይ ይዞታ በተለይ ብቸኛ የሆነን ሰው ማርኮ የሚያስቀር ነው ። ካረጁ መፃህፍትና ከሌሎችም ቁሳቁሶች የሚወጣው ሽታ ክፍሉን ወና ወና እንዲሸት ከማድረጉም በላይ የልዩ ልዩ አበቦች መዓዛ ጠረኑን ሊቀይረው አልቻለም ። ያም ሆኖ ሰላምን ለምትሻ ህይወት እይነተኛ ማረፊያ ሆኖ ነው ያገኘሁት ።

ሻይ ቀረበልን ። ማክሲም ፡ በሌለበት ተጠራቅመው የቆዩትን ደብዳቤዎች ማንበብ ያዘ ። አልፎ አልፎ ቀና እያለ ውብ ፈገግታውን ሲጋብዘኝ ለማየት ያህል ልየው እንጂ እኔም ሥራ አልፈታሁም ። ደብዳቤዎች ማንበብ ከእለት ተእለት ተግባራቱ አንዱ እንደሆነ በመገመት የማንደርሉይ ህይወቱ ምን እንደሚመስል ፡ ጠቅላላ ኑሮውን እንዴት እንደሚመራ ከቶውንም እንደማላውቅ ተገነዘብኩ ።

ወደ ኋላ ተመልሼ ግንኙነታችንን ስገመግም ፡ በመጀመሪያው ቀን ያየሁበት ብቸኝነትና ስሜቱን እውስጡ አምቆ እንዴት እራሱን ከአካባቢው አግልሎ ይኖር እንደነበረ ትውስ አለኝ ። ውሎ ሲያድር ምን ያህል እንደተቀራረብን ፡ ለኔ የነበረው ቅን አሳቢነትና ደግነት ይበልጥ እምነት እንድጥልበት ፡ ይበልጥ ሰብአዊነቱን እንድረዳ እንዳደረገኝ አስታወስኩኝ። ከተጋባን በኋላ ደግሞ በፈረንሳይና በጣልያን ምድር ስንንሸራሸር ፈጣዋታው ፡ ሳቁ ፡ እንጉርጉሮውና መላ ድርጊቱ ይበልጥ እንድቀርበው ይበልጥ እንዳፈቅረው ነው ያደረገኝ ።

ይሁን እንጂ ማክሲምን አስካሁን እንደ አንድ የቅርብ ወዳጅ ፡ እንደ አንድ የልብ ጉትረኛ ከመቁጠር ሌላ በእቅድ የተነደፈ ፡ በሥርአት የሚመራ ኑሮ እንደነበረውና ወደፊትም ሊገፋበት እንደሚችል ከቶውንም አስቤ አላውቅም ነበር ።

ሀሳቤ እንዲያ እንዳገኘ ያለ ሀሳብ ቢዋልልም አይኔ ግን ቀደም ሲል ካረፈበት መድረክ አልወረደም—ከማክሲም ላይ ። አንዱን ደብዳቤ ሲያነብ ፊቱ ቅሟም ሲል ፡ ሌላኛውን ሲይዘው ፈገግ ፈካ ሲል አስተዋልኩት ። አንዱን በጥንቃቄና በልዩ አስተያየት ሲያስተናግደው ፡ ሌላውን ደግሞ እምብዛም ሳይጨነቅለት ወርወር ሲያደርገው ማየቱ ለሌላ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሀሣብ ዳረገኝ ። ማክሲም የፍቅር ልቡን ባይከፍትልኝ ፡ ለጋብቻ ባይጠይቀኝ ኖሮ ይሄኔ ከኒውዮርክ የምዕፍለትን ደብዳቤ ቱብ ሳይለው ፡ ከብደት ከነፈጋቸው ደብዳቤዎች ተራ ሲደምረው ፡ እኔ መልሱን በመጠበቅ ልቤ ምን ያህል ስቅል ጥልጥል ይል እንደነበረ ሳሰላስል ዝግንን አለኝ ።

ወዲያው ደግሞ ባልሆነው ከመጨነቅ ስለ ዛራና ነገ ማሰብ እንደሚበጅ ከራሴ ጋር መክሬ ልቤን በኩራትና በጥንካሬ አገነባው ገባሁ። ከእንግዲህ የማንደርሌይ እመቤትነቱ እስከተረጋገጠ ቤቱን እንዴት እንደማስተዳድር ፡ ሠራተኞችን እንዴት እንደምመራ ማሰብ እንደሚገባኝ ተገነዘብኩ ። እኔና ማክሲም በፍቅር ደርጅቱን ፡ በእድሜ በልፅገን በደስታ ስንኖር ከአብራካችን የወጡ ልጆቻችንን እንዴት በሥነ ምግባር እያነፅኩ እንደማሳድጋቸው በምናብ ታየኝ ።

የሻይውን እቃ ለማንሳት ፍሪዝና አሳላፊው በሩን ከፍተው ሲገቡ የእእምሮዬ ጓዳ የተዘጋበት ሀሣቤ ደግሞ ሹልክ ብሎ ወጣ ። "እመቤቱ ክፍልዎን ማየት ይፈልጉ እንደሆን ሚስዝ ዳንቨርስ ጠይቃቸው ብላኝ ነበር" አሉኝ ሽማግሌው ።

ማክሲም ቀና አለና "ለመሆኑ በደንብ ተዘጋጅቷል?" ሲል ጠየቀ ።

"እረ እፀብ ድንቅ ሆኗል ጌታዬ ። ሠራተኞቹ አጀማመራቸው አላምር ቢላት ሚስዝ ዳንቨርስ እድሳቱ ሳያጠናቅቅ ትመጣላችሁ ብላ ሰግታ ነበር ። አሁን ሁሉም ነገር በመሚላቱ አሳምረውታል ። ቀለል ማለቱም ሆነ ምቾቱ እርሱ የሚሻላችሁ ይመስለኛል ጌታዬ"

"ልዩ ለውጥ እንዲደረግ አዘህ ነበር እንዴ?" በማለት ለሰነዘርኩት ጥያቄ ፡—

"አይ ፡ አንዳንድ ነገሮችን ማደስና ቀለም መቀባባት እንጂ ብዙም ለውጥ አልተደረገም ። ፍሪዝ እንዳለው በቂ ብርሃን ስላለውና ከዕጌረዳው አፀድ ትይዩ በመሆኑ መኝታ ክፍላችንን ከዚያው ብናደርግ ይሻላል ። እናቴ እያለች ግን ለእንግዶች ማረፊያ ነበር የምትጠቀምበት" ሲል ከመለሰ በኋላ ደብዳቤዎችን እያገላበጠ "አንድ አፍታ ይሁችን ፈጠርሽ እመጣለሁ ። እስከዚያ አንቺ ሄደሽ ክፍሎቹን እያቸው ። እንዲሁም ከሚስዝ ዳንቨርስ ጋር በደንብ ለመግባባት መልካም አጋጣሚ ይሆንል ሻል" አለኝ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደኔ ፍላጎት ቢሆን ከማክሲም ጋር ብሄድ ደስ ባለኝ ነበር። ፍሪዝን ተከትዬ በአዳራሹ በኩል ማለፍ እንደጀመርኩ ሜማዬ የሚፈጥረው ድምፅ ለገዛ ጆሮዬ ቢተፈኝ ፍሪዝ ይታዘበኝ ይሆን? የሚል ሀሣብ አደረብኝ። ስለ አዳራሹ ስፋት በእድናቆት ስናገር አዳራሹ ከዋንት ጀምሮ ለትላልቅ ግብዣዎች ሲያገለግል እንደቆየ ፍሪዝ ነገሩኝ። ግራ ቀኙን እየተገላመጥኩ የአዳራሹን ስፋትና ግድግዳዎቹን ያስዋቧቸውን ጊጣጊጦች ሳደንቅ እኒያ አስፈሪና ጎድጓዳ አይኖች የተሰኩበት ያ አስደንጋጭ ፊት ድቅን አለብኝ። ዞር ብዬ ፍሪዝን ብፈልግ ብቻዬን ከሚስዝ ዳንቨርስ ጋር ትተውኝ ወደ ኮሪደሩ ሲሄዱ አየኋቸው።

ወደ አሮጊቲ ስጠጋ ትክ ብለው እያዩኝ እጃቸውን አጣምረው ከቆሙበት ሳይንቀሳቀሱ ጠበቁኝ። ፈገግ ብልላቸውም አፀፋውን አልመለሱልኝም። መለስ ብዬ እራሴን ስመረምር ግን ያን ያህል መገልፈጤ ጅልኛ ቢሆንብኝም አሮጊቲን መታዘቤ እግባብ እንዳልሆነ ተረዳሁ። "ብዙ አስጠበቅሆት እንዴ?" ስላቸው፡

"የሚመችዎትን ጊዜ መምረጥ የሚችሉት እርስዎ ነዎት እኮ፡ የኔ እመቤት። ከኔ የሚጠበቀው ትእዛዝዎን ማክበር ብቻ ነው።" አሉኝና ፊታቸውን አዙረው መንቀሳቀስ ያዙ። ተከተልኋቸው። ልዩ ልዩ ኮሪደሮችንና ክፍሎችን አልፈን ደረጃዎችን ወጥተንና ወርደን በተሟላ ቁሳቁስ የተደራጀ ክፍል ውስጥ ገባን። ወደ ውስጥ ስንዘልቅ ደማሞ ሰፊ አልጋ የተዘረጋበትን ሰፊውን የመኝታ ክፍልና ከጎኑ ያለውንም የመፀዳጃ ክፍል ተራ በተራ አስጎበኙኝ።

በመኝታ ክፍሉ መስኮቶች አሻግሬ ሳይ ከስር የተንጣለሉት ለምለሙ መስክና የዕረፍቱ አፀድ እያታዩን ማረኩት። ከዚህ ሆኖ ባህሩን ማየት አለመቻሉ ቅሬታ ቢያሳድርብኝም በአጠቃላይ ክፍሉ ያሳደረብኝን አድናቆት መሸሸግ አልሆነልኝም። ስለ ቤቱ ለሰንዘርኳቸው አንዳንድ ጥያቄዎች ሚስዝ ዳንቨርስ ከመለሱልኝ በኋላ ስፍራው ቀደም ሲል አልፎ አልፎ ለእንግዶች ማረፊያነት ያገለግል እንደነበር ነገሩኝ። "ከዚህ ቀደም የማክሲም መኝታ ክፍል እዚህ አልነበረም ማለት ነው?" በማለት ጠየቅኋቸው።

"አይ፡ በዚህኛው ህንፃ የሚገኙትን አንዳቸውንም ክፍሎች ተጠቅመው አያውቁም" አሉኝ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ነው እንዴ? ማክሲም ግን አልነገረኝም ።" አልኩና ወደ መስታወቱ ተጠግቼ ፀጉሬን ማበጠር ጀመርኩ ።

"እቃዎን አሊስ ታዘጋጅልዎታለች ። ድንገጡርዎ እስክትመጣም ልታገለግሪ ዎት ትችላለች" አሉ ሚስዝ ዳንቨርስ ።

ፍርሀት ከጀርባዬ ። ፀጉሬን ማበጠሩን ትቼ ዞር አልኩና "እረ ደንገጡር የለኝም ። አሊስ ያሳ.ት የዚሁ ቤት ሠራተኛ ከሆነች እርሷው ብታገለግለኝስ?" ስል ጠየቅኳቸው ።

ገርመም አደረጉኝና "በዚህ የሚዘልቅ ግን አይመስለኝም ። እርስዎን የመሰለች እመቤት የማሳ ገረድ ሊኖራት ይገባል" አሉኝ ።

አነጋገራቸው ዝሙጥ መሆኑ ቢገባኝ ፊቴ ቀላ። "ያን ያህል አስፈላጊ ነው የሚሉ ከሆነ ልትሰለጥን የምትችሉ እንዴት ልጅ እግር ብጤ ቢያፈላልጉልኝስ?"

"ካሉም ደግ ፡ ታዛዥ ነኝ ።"

እኔ ከመቼ መቼ ትተውኝ ዘወጡ እያልኩ ስጨነቅ ሚራሽ እጃቸውን አጣምረው ሲያዩኝ ይበልጥ ከበዱኝ ። ይበልጥ ጠሳኋቸው ። ቶሎ የማይወጡ መሆናቸውን ስረዳ ዝምታውን ለማበወጓድ "እዚህ ማንደርሴይ ውስጥ በመኖር አንጋፋዋ እርስዎ ነዎት መሰለኝ?" በማለት ጠየቅኳቸው ።

"አይ ፡ ፍሪዝ ይቀድመኛል ። ጌቶች ግና ልጅ ሳሉ ነው የመጣው ። እኔማ ይህን ግቢ "ሀ" ብዬ የረገጥኩት ጌቶች የመጀመሪያዩቱን ሚስዝ ደዊንተርን ሲያገቡ ነው ።" ሲሉኝ አስካውን በድን የነበረው ድምነቸው ነፍስ እየዘራ ፡ ገፅታቸው እየተቀያየረ ይሄድ ጀመር ።

በዚህ ቅፅበታዊ ለውጥ ከመደነቄ በላይ ተደናገጥኩ ። ግና በጅምሩ በንቀት ሲዳስሱኝ ፡ በእሽሙር ሊጎነትሉኝ በቸልታ ነበር ያለፉኩት ። የአሁኑ አስተያየታቸውና አነጋገራቸው ግን በጣም ቀጠቀጠኝ — ለኔ ያላቸውን ንቀትና ጥላቻ የሚያጎላ ሆኖ ስላገኘሁት ። ጅል ያመስል እንዲያ ተጎልቼ ማበጠሪያውን ከማፍተልተልና ድንጋጤዬንና እርሳቸውን መጠራጠሬን ከማንፀባረቄ ይልቅ አንድ ነገር መናገር እንዳለብኝ ቢሰማኝ ፡—

"አዩ ሚስዝ ዳንቨርስ ፡ እኔና እርስዎ ጥሩ ወዳጅች ልንሆን እንደምንችል ይታየኛል ። ይህ ቤትና ኑሮው ለኔ አንግዳ ስለሆነ

t.me/OLDBOOKSPDF

ድንግርግር ቢሉኝ አያናድዱብኝ ። ከአዲሱ ሁኔታ ጋር እራሴን ለማለማመድና ከሁሉም በላይ ሚስተር ደዊንተርን ለማስደሰት ብርቱ ጥረት አደርጋለሁ ። የቤቱን ውስጥ አስተዳደር እርስዎ ሊወጡት እንደሚችሉ ሚስተር ደዊንተር ስለነገረኝ እንደወትሮው እንዲያካሂዱት ። እኔ የምተንሰውም ሆነ የምጨምረው ነገር የለኝም" አልኳቸው ። ታሌን አንዴ ከተነፈስኩት በኋላ የተናገርኩት ተገቢ መሆን አለመሆኑን በራሴ ለመወሰን ድፍረቱ ከዳኝና ማረጋገጫ ፍለጋ አያናቸውን በአይኔ አስስ ጀመር ።

"እስቲ ያውና ። ፍላጎትዎን ለማሚላት የተቻለኝን አደርጋለሁ ። ቤቱን ሳስተዳድር አውን እንግዲህ አመት አለፈ መሰለኝ ። ታዲያ ጊዜኞች አንድም ቀን ያህ ጎደለ ፣ ያህ ተበላሸ ብለውኝም አያውቁ ። መሬቱ ይቅለላትና ሚዞ ሚስዝ ደዊንተር በህያወት ሳለች ግን የግብፐው አያነት፡ የእንግዳው ብዛት እንዲህ አልነበረም ። ያኔም ቢሆን ጠቅላላ ስራውን የምሰራው እኔ ብሆንም እርሷ አራሷ ነበረች ሁሉንም ነገር የምትቆጣጠረው ።"

"ግድ የለም ፣ አውን ሁሉንም ለእርስዎ ሰጥቼዎታለሁ ።"

"እንዳለ እንግዲህ ፣ ... አውን ግን የሚያስፈልግዎ ነገር አለ?"

"ለጊዜው ምንም አያስፈልገኝም ።" አልኳቸውና በኔ ላይ ይበልጥ እምነት ቢያድርባቸው ብዬ "ከፍሉን እኩ በሚገባ አደራጅተው ነው የጠበቁን" በማለት አከልኩላቸው ።

"እኔ በግሌ ምን አደረግኩ ብለው? ሚስተር ደዊንተር ያዘዙኝን ነው የፈፀምኩት" ብለው ጥቂት ፀጥ ካሉ በኋላ "እንግዲህ እያዩ የጎደለው እንዲሚላ ፣ የተበላሸው እንዲስተካከል ማዘዝ ይችላሉ" አሉኝ ።

"ጥሩ ፣ ግድ የለም ። ችግር ሲኖር አማክርዎታለሁ"

ሲተኙ መውጣት የሚሹ አይነት አይደሉም ። "ሚስተር ደዊንተር ትልቁ ቁምጣጥናቸው ለምን አልመጣም ብለው ከጠየቁ ግን ፣ ሞክረን በሮቹ ጠበው አላስገባ ስላሉን መተዋችንን እንዲነግሩልኝ ። እነዚህኞቹ ከፍሎች እኩ በምስራላቢው ሀንባ ከሚገኙት ከፍሎች በጣም የጠበቡ ናቸው ..." በማለት መዘባዘብ ያዙ ።

"አያጨንቁ አባክዎ ፣ ምንም ቅር እንደማያሰኝ እርግጠኛ ነኝ ። ብቻ እርስዎ ብዙ ተቸግሩ እንጂ ። እንዲህ አዲስ ክፍል እንዲዘጋጅ

t.me/OLDBOOKSPDF

ማቀዱን አስቀድሚ ባውቅ እንዳይቸገር እንግረው አልነበር ። ያኛውም ሀንዛ ቢሆን ምንም አልነበረበት" አልኩኝ ነገሩን በዚሁ ለመቅጨት ።

"እንዴ ፡ ምነው ሚስተር ደዊንተር ይሀኛውን ክፍል እንደመረጡ ነግረውኝ?" ብለው በጎን እያዩኝ ቀጠሉ "በዚያኛው ሀንዛ የሚገኙት ክፍሎች በጣም ሰፋፊዎች ናቸው ። መኝታ ክፍሉም ቢሆን የዚህን ሁለት ይሆናል ። ማማሩስ ቢሆን? እቃዎቹም ቢሆኑ ምርጦች ናቸው ። መስኮቱ ደግሞ ባህሩን ወለል አድርጎ ነው የሚያሳየው ።"

ይህን ሁሉ ከመዘርዘራቸው በላይ ከድምዳቸው የሚወጣው የቱሪት ቃና 'ለምን?' የሚለውን ጥያቄ ሳያሟርብኝ አልተረፈም ። አልፎ ተርፎ ያለሁበት ክፍል በደረጃ ዝቅ ያለ መሆኑን ለመግለፅ ይሀን ያህል መጨነቁ ለምን አስፈለገ? አሰኘኝ ። አውንም ነገሩን ለማሳጠር በማሰብ "ምናልባት ሚስተር ደዊንተር ጥሩ ጥሩ ክፍሎች ለእንግዶች መስተናገጃ እንዲውሉ ብሎ ይሆናላ" ብላቸው "እረ እንግዶች ወደ መኝታ ክፍሎች ዘር ብለውም አያውቁ ። ልዩ ማረፊያ አላቸው ። ያሂ አውን የነገርኩም — ባህሩ ይታይበታል ያልኩም ክፍል የሚስዝ ደዊንተር መኝታ ክፍል ነበር"

ወዲያው ፊታቸው ላይ አንዳች ጥላ ማጥላቱንና ወደ ግድግዳው ማፈግፈጋቸውን ስከታተል ድምፅ ሰማሁ ።

ማክሲም ነበር ። "ታዲያስ? እንዴት ነው? ክፍሉ ተስማማሽ?" በማለት እንደ ሀዛን ልጅ እየፈነደቀ ሁሬያውን ቃኘ ። "ይሀን የመሰለ ቤት እስከዛሬ ለእንግዳ ማረፊያ ማድረጌ የሚያሳዝን ነው ። መቼም በደንብ ነው ያሳመርሽው እኮ ሚስዝ ዳንቨርስ ። ሽልማት ይገባሻል ።" አላቸው አሮጊቷን ።

"ያቆይልኝ ጌታዬ" አሉና ሹልክ ብለው ወጥተው በሩን ዘጉት ።

ማክሲም ወደ መስኮቱ ተጠግቶ ቁልቁል እየተመለከተ "ይህ የፅጌረዳ አዐድ እንዴት መሰለሽ የሚያስደስተኝ ። ይገርምሻል ፡ ሀዛን ሆኜ እናቴ አበቦችን ስትቆርጥ የቀሚሷን ጫፍ ይዝ አብራሕት ድክ ድክ እል እንደነበረ ትዝ ይለኛል ። ይሀን ክፍል እኮ በጣም ነው የምወደው ። አጅግ ፀጥ ከማለቱ የተነሣ እዚህ አፍንጫችን ስር ያለው ባህር ሞገዱ በጭራሽ አይሰማም ።" አለኝ ።

"አዎን ሚስዝ ዳንቨርስም አጫውተውኛል" አልኩት ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

"ለመሆኑ ከአሮጊቷ ጋር ተግባባችሁ?" ሲል ጠየቀኝ ።

"እኔ እንጃ ፡ በዚህ አስተዳደር ውስጥ ጣልቃ የምገባ መስሏቸው ነው መሰለኝ ትንሽ ግትርትር አሉብኝ"

"ይሄ ያንቺ ጉዳይ ስለሆነ ምንም አይመለከታትም ። እንደነገርኩሽ አንዳንድ ጣር የሚያሰኝ ጠባይ አላት ። በተለይ ከሌላ ሴት ጋር የመግባባት ትልቅ ችግር አለባት ። ቢሆንም ይህን ያህል አትጨነቂላት ። ጠባይዋን አሳምራ መኖር ነልጅለች እጣዋ መባረር ብቻ ነው ። በሌላ ወገን ደግሞ በዙን ቁጥ አድርጋ ስለያዘችው ከብዙ ሽክም ትገላግልሻለች ና እንደ ጠባይዋ ለመያዝ መሞከር ነው ።"

"በደንብ እያወቁኝ ሲመጡ ይበልጥ እንደምንግባባ ተስፋ አደርጋለሁ ። ለመጀመሪያ ጊዜ በጥላቻ አይን ቢያዩኝም እምብዛም የሚደንቅ አይሆንም"

"ምን ማለትሽ ነው? ምን ቁርጥ አድርጎት ነው የምትጠላሽ ደግሞ?"

"ያለ እኮ ነው ። ወንድ ሲያገለግሉ የሚኖሩ ሠራተኞች ሴት ስትመጣባቸው አይወዱም ። የእስከዛሬውን የበላይነታቸውን የምገፋች ውና የምጫናቸው መስሏቸው ይሆናላ"

"ያንተ ያለህ ... መጫን አልሽኝ? ... ግን ...እኮ ..." አለና ሃሣቡን በጅምር ትቶት ጠጋ ብሎ ግንባሬን ሳመኝ ።

"አሁን እንግዲህ የአሮጊቷ ነገር ይብቃን ። ይልቅ ነይ አንዳንድ ነገሮች ላሳያሽ" አለኝ ።

ከፍሎቹን እየተዘዋወርን ስንመለከትና በየግድግዳዎቹ ላይ የተንጠለጠሉትን ስእሎች ሲያሳየኝ ሚስዝ ዳንቨርስን ከነአካቴው ከአእምሮዬ ፋቅኳቸው ።

ምሽቱን ደስ በሚል ሁኔታ ነው ያሳለፍነው ። በዚያ የመጀመሪያ ምሽት የበላነው የምግብ አይነት ፡ የተጨዋወትናቸውና የተሳሳቅንባቸው ነገሮች ሁሉ ትውስ ይሉኛል ። ገበታው ከፍ ካለ በኋላ ወደ ቤተመፃህፍቱ ነበር የሄድነው ።

ምድጃው ውስጥ ከሚንቦገቦጉት ጉዶዎች የሚወጣው ሙቀት የደጁን ቅዝቃዜ የሚያስረሳ ነበር ። ማክሲም በደመ—ነፍሱ እንደሚመራ አይነት በቀጥታ ወደ ወንበሩ አመራ ። ሲጋራውን አቀጣጥሎ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጋዜጦችን ማገላበጥ ጀመረ ። ከእራት በኋላ የዘወትር ልምዱ ቢሆን ነው አልኩኝ ።

በእንድ እጁ አገፉጩን ደግፈ በሌላኛው ሙሻውን አሻሸለው ። በተቀመጥኩበት መንበር ላይ ከእኔ በፊት ሌላ ሰው ይቀመጥበት እንደነበረ ትዘ ሲለኝ አንዳች ነገር መላ ኣካሌን ነዘረው ። ለካስ በርብቃ መንበር ላይ ነው የተቀመጥኩት ... ለካስ የርብቃን መከዳ ነው የተንተራስኩት ... ለካስ ...ለካስ ...

እየቀረበኝ የነበረ የሀሴና እረፍት ሸ ... ሸ ....ኝ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ ሰባት

በማግስቱ ከእንቅልፌ ስነቃ የማክሲም እንዲያ ማልዶ መነሣት ሳይደንቀኝ አልቀረም ። ሦስት ሰአት ግድም ወደ ምድር ቤት ስወርድ ብርቱካን ሲልጥ አገኘሁት ። ከነጋ በኋላ የፃፉቸው በርካታ ደብዳቤዎች ጠረጴዛው ላይ ተደርድረዋል ። እንዲህ ያሉትን ተግባራት ዘወትር በዚህ ጊዜ እንደሚያከናውን ፡ እርሱ ቁርሱን እንደበላና እኔም ተዘጋጅቶ ጠረጴዛው ላይ ከተደረደረው የምግብ አይነት መርጨ እንደበላ ከነገረኝ በኋላ "አያዞሽ ግር አይበልሽ" ይህ የቤታችን ባህል ነውና ውለሽ አድረሽ ትለምጂዋለሽ" አለኝ ።

ማር ..ቅቤ ... እንቁላል ቁጭቁጭ ... አሳ ... እንቁላል ፍርፍር ... ማርመላታ ... እንቁላል ቂጣ ...ገንፎ ... ቅቅል እንቁላል ... ፍራፍሬ በየዓይነቱ ... ሻይ ... ወተት...ቡና...ሞርታዴላ ... ወዘተ·

ሳልበላ ጠገብኩ ። ምንም ያህል ብንበላ ሁለታችን ብቻ ይህን ሁሉ ምግብ እንደማንፈጨርስ እየታወቀ እንዲህ ተትረፍርፎ መዘጋጀቱ አስገረመኝ ። ግቢው ውስጥ ተስፈኞች ይኖሩ ይሆን? ወይስ ተመላሽ ምግብ ሁሉ ሊጣል? የሚል ሀሣብ ቢጎበኘኝም እንዴት ብዬ ልጠይቅ?

"ከዚህ ቀደም እንደነገርኩሽ ያሉኝ ብቸኛ ዘመዶቼ አሮጊት አያቴና እህቴ ቢያትሪስ ብቻ ናቸው ። ቢያትሪስ ዛሬ ለምሣ እመጣለሁ ብላ ልካለች ከአንቺ ጋር ለመተዋወቅ" አለኝ ማክሲም ። ድንግጥ አልኩና መብላቱን አቋርጬ "ዛሬ?" ስል ጠየቅኩት ። "አዎን ፡ በደብዳቤዋ እንደገለፀችው ከሆነ ብዙ ለመቆየት የምትሻ አይመስለኝም ። መቼም ቢያትሪስን ቀረብ ብለሽ ስታውቂያት እንደምትወጂት ተስፋ አደርጋ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለሁ። እንዴት ያለች ግልፅ ሰው መሰለችኝ ። እርሷ ዘንድ ነገር መሸፋፈን ብሎ ነገር የለም ። ሁኔታሽን ካልወደድኩት ፣ ነገረ ስራሽ ካላማረት እዚሁ እፊትሽ ነው የምትነግሪሽ”

ነገሩን ሙንትላቱ ውስጥ ማጉላላት ስጀምር ማነሰም ብድግ ብሎ “በይ እንግዲህ ብዙ ሥራ ስለሚጠብቀኝ መሄዴ ነውና እንዳትቦዝኚ ። ግቢውን አዚዙሬ አሳይሻለሁ ብዬ ነበር ። ግን ምን ላድርግ ? ወነሰሉን ከርውሉይን ለስራ ጉዳይ ስለምፈልገው ነው ። በነገራችን ላይ እርሱም ለምሣ ቢመጣ ምን ይ፟ስልሻል ? እንዲያው ቅር ይልሽ እንደሆነ ብዬ ነው” ሲለኝ ።

“እረ ግድ የለም ። ለምን ቅር ይለኛል ?” አልኩት

ተሰናብቶ ከወጣ በኋላ ቁጭ ብዬ ፣ ከምግብ ጋር ሠላብ አከዬ እመነኛክ ጀመር ። ፍሪዝ ገብተው ትክ ብለው ሲያዩኝ ፣ ዝም አልኩ ። አራት ሰዓት መሙላቱን ላይ ፈንጠር ብዬ ተነስቼ ይሀን ያህል ማእድ ላይ በመቆየቴ ይቅርታ ጠየቅኳቸው ። ምንም ላይናገሩ በትህትና እጅ ቢነሱኝም አስተያየታቸው ግን አላማረኝም ። መናገር የማይገባኝን ነገር ተናግሬ ይሆን ? በማለት እራሴን በራሴ ጠረጠርኩት ።እንደ አሮጊቷም ሁሉ ሽማግሌውም በራሴ ላይ እምነት የሌለኝ ዋላ ቢስ አድርገው ቆጥረውኝ ይሆናል የሚል ግምትም አደረብኝ ።

ክፍሉን ለቅቄ ለመውጣት ስንቀሳቀስ እግሮቼ ተወላከፉብኝ ። መንገዳችንን ያዩት ፍሪዝ ደገፍ አድርገውኝ ከእጄ የወደቀውን መሀረብ አንስተው ሰጡኝ ። ልጅ እግሩ አሳላፊ ሮበርት ደግሞ ሁኔታውን ሁሉ ከበሩ በስተጀርባ ሆኖ ያስተውል ኖሮ ይስቅብኝ እንደነበረ እንዳላውቅ በት ፊቱን ሲያዞር አየሁት ።

አዳራሹን አልፌ ስሄድ ሲንሾኳሽኩብኝና ሲስቁብኝ ሰማኋቸው ። በዚህ ሰአት መግባቴ ተገቢ አይሆን ይሆናል ብዬ በመጠራጠሬ የቆየ የቢቱን ባህል ያፈረስኩ መስሎ ቢታየኝ በሩን ዘግቼ በመጣሁበት ተመለስኩ ። ኮቴዬን አጥፍቼ ድምጼን ውጬ ከቢተ መፃህፍቱ ገብቼ መሸግኩ ።

ማታ መቀቱ እንዲያ ደስ እንዳላለኝ ሁሉ አጥንት ሰርስሮ የሚገባው ብርድ ቢያንዘፈዝፈኝ መስኮቶቹን ዘግቼ እሳት ለማያያዝ ክብረት ፍለጋ ገባሁ ። አልቀናኝም ። መኝታ ክፍላችን ውስጥ ክብሪት እንደነበረ ትዝ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቢለኝም እነኛ ሠራተኞች ደግሞ እንዳይሳለቁብኝ ፈርቼ ሄዶ ማምጣቱን ተውኩት ። እነ ፍሪዝ ምግብ ቤቱን አዕድተው ሲወጡ ከዚያ ሄጂ ለማምጣት ወሰንኩ ። ወላ ብዬ ሳዳምጥ የእቃዎች ግጭግጭታና የሰው ድምፅ ስሰማ ተመለስኩ ። ጥቂት ቆይቶ ሁሉም ነገር ወጥ ሲልልኝ ኮሽታ ሳላሰማ ቀስ ብዬ ሄድኩ ። ከክፍሉ ገብቼ ክብራቱን ሳንሳና ፍሪዝ በሩን ከፍተው ሲገቡ አንድ ሆነ ። ክብራቱን ኪሴ ውስጥ ለመደበቅ ብጣጣርም እጅ እጄን የሚያየው አይናቸው ቀድሞኝ ጥረቱን መና አደረገብኝ ።

"ምን ፈልገው ነው የኔ እመቤት ?" ሲሉ ጠየቁኝ ።

"ክብራት አጥቼ እኮ ነው" ስላቸው ክብራት ሲጋራ ሞምር ሲሰጡኝ እጠዬ ዴብ አለ ።

"እረ አላጨስም ። ቤተ መዛህፍቱ ውስጥ ብርዱ አላስቀምጥ ቢለኝ እሳት ለማቀጣጠል ፈልጌ ነው ።"

"እዩ ፡ ቤተ መዛህፍቱ ውስጥ እኮ ከሰአት በፊት እሳት አናነድም ። እሁን እሳት የሚኖረው ከእልፍኙ ነው ። ጠዋት ጠዋት ሚስዝ ደዊንተር እዚያ ነበር የሚያርፉት ። የቤተ መዛህፍቱ እሳት እንዲቀጣጠል ከፈለጉም ሠራተኞቹን ማዘዝ እችላለሁ፡"

"ግድ የለም ፡ ግድ የለም ፡ መደዚያው ወደ እልፍኙ እሄዳለሁ"

"እመቤቱ ፡ ምናልባት ከፈለጉም መረቀት ፡ ብእርና ቀለም እዚያው እልፍኙ ውስጥ አለልዎት ። ሚስዝ ደዊንተር ደብዳቤያቸውን የሚፅፉትና ስልክ የሚደውሉት እዚሁ ነበር ። ሚስዝ ዳንቨርስን ማነጋገር ካሻዎትም ውስጥ ለውስጥ ለሚደረጉ ግንኙነቶች የሚያገለግል ስልክም አለ ።"

"አመሰግናለሁ ፍሪዝ" አልኳቸው ።

እልፍኙን አላውቀውም ማለቱ ሞት መስሎ ታየኝ ። ማነሰምም እስካሁን እንዳላሳየኝ መሳለፁ አሳፈረኝ ። ሳያውቅ አዋቂ ያደረግኩትን እኔነቱን ኮሸሸ ፡ በአስመሳይነት ጥላ ተከልዬ አዳራሹን ሳቋርጥ የልብ ልብ እንዲሰጠኝ እያንጎራጎርኩ ነበር ። እግሬ እንደመራኝ ሄጄ በይሆናል በከፈትኩት ክፍል ውስጥ ያየሁት ነገር ግራ አጋባኝ ። በጠረጴዛው ላይ የተደረደሩትን በርካታ አበቦችና እዚህም እዚያም የተሰገሰጉትን ቅራቅምቦዎች ሳይ በሩን ዘግቼ ተመለስኩ ።

ከነበሩበት ሳይንቀሳቀሱ እንቅስቃሴዎቼን ሁሉ ይከታተሉ የነበሩት ፍሪዝ "አይ የኔ እመቤት ፡ እልፍኙ እኮ ወዲህ ነው ያለው ። ያኛው

t.me/OLDBOOKSPDF

በስተቀኝ ያለው በር ይታይዎት የለ ? በዚያ አድርገው ፡ በእንግዳ ማረፊያው በኩል ሲያልፉ በስቱግራ ያገኙታል ።" ሲሉኝ በትህትና "አመሰግናለሁ" ከማለት ሌላ አማራጭ አልነበረኝም ፡ለዳግም አስመሳ ያነት የሚዳዳኝ ድፍረቱ ተሟጠ አልቆ ነበርና ።

በተሰጠኝ መመሪያ መሠረት ከእንግዳ ማረፊያው ስገባ የነፍሱ ስፋት ከመሰጠኝ በላይ የስእሎቹና የቁሳቁሶቹ ውበት ነበር በእጅጉ የሳበኝ። በነፍሱ ውበት ብማረክም አረፍ ብዬ አድናቆቴን መፈጸሪስ ግን አልፈለግኩም ። ፊት ለፊቱ ባገኘሁት በር ወጥቼ ፡ ግራዬን ታጥፌ ከአልፍኙ ገባሁ ።

ውሾቹ ከእሳቱ አጠገብ ቁጭ ብለው ማየቱ በጣም አስደሰተኝ ። ከሰአት በፊት እሳት የሚገኘው አዚህኛው ክፍል ውስጥ መሆኑን ማወቃቸው ምን ያህል ቢገሩ ነው ? የሚል ጥያቄ ቢደቅንብኝ ሥልጡንነ ታቸውን እንዳያጋት የማድ አለኝ ። በአልፍኙ ድምቀትና ብሩህነት የሸፈተው ልቤ ገፋፍቶኝ ወደ መስኮቱ አመራሁ ። ያ ትናንት ማምሻውን እንዲያ ውበቱ የሳበኝ በደማት ተደ አበቦች የታጀበው ሀረግ መናፈሻው ላይ ተንጣለሎ ማየቱ ስሜቴን ቀሰቀሰው ። ይኸው ቆንጆ ሀረግ ሚዳውን ከማሳመር አልፎ በመስኮት ዘልቆ እንዲገባ ስለተፈቀደለት ለአልፍኙ ተጨማሪ ውበት በመቸር ረገድ ድርሻዉ እንዳይዘነጋ ያለ ይመስላል ።

በቆንጆው ሀረግና በልዩ ልዩ አበቦች ባጌጠው መናፈሻ ውስጥ በአረንጓዴ ወፍራም የሳር ምንጣፍ የተሸፈነ ትንሽ መስኮ ይታየል ። ከፊል የሰው ፡ ከፊል የፍየል አካል ያለው ቅርፅ መስኩ ላይ አየሁ ። አቋቋሙ ቁንጠኛ ነው ። አፉ ላይ ዋሽንት ይማኗል ። የመስኩ አጨዋወት ደግሞ ምስሉ ሽንጥ ባለው ቁጥር ዳንኪራውን እንዲረግጥበት ሆኖ ተብሎ የተዘጋጀ መድረክ ያስመስለዋል ።

ፊቴን ወደ ክፍሉ ውስጣዊ ይዘትና ቅርፅ ስመልስ መቆጣጠር እስኪሳነኝ ድረስ ነበር አድናቆቴ እየበረታ የሄደው ። የነፍሱ አደያዝ ፡ የእቃዎቹ አመራረጥና አቀማመጥ ፡ ውስንተናዊ ይዘታው ልዩ ግምት የሚሰጠው ሆኖ ነው ያገኘሁት ። ከዚህም በላይ ከመንበሮቹ እስከ ትናንሽ ቁሳቁሶቹ ፡ ጥቅጥ ጊጣጊጠቹ ጭምር በቅርፅም ሆነ በቀለም እንዲጣ ጣሙ ትልቅ ጥንቃቄ መደረጉን ልብ ብሎ የተመለከተ ሁሉ መገንዘብ ይችላል። ለውበትና ለጥራት እንዲሁም ለሀብር ልዩ አድናቆት ባሳት ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ለቤት አያያዝ በእጅጉ በምትጠበብ እንስት እንክብካቤ የተጠበቀ ለመሆኑ ከአጠቃላይ አደረጃጀቱ መገመት አላዳገተንም።

አልፍኙ ለእረፍትና ለመዝናኛ ከማገልገል ባሻገር ለዕሀፈት ተማሪ ራት ያጠቀመበት እንደነበር ያስገነዘበኝ በአንደኛው ጥግ የሚታዩት የዕሀፈት ጠረጴዛና መንበር ነበሩ። በእያንዳንዱ መሳቢያ ላይ "መልስ የሚሹ ደብዳቤዎች" "የምላብ ዘርዝሮች" "የቤት ውስጥ ጉዳዮች" "ልዩ ልዩ ጉዳዮች" "አድራሻዎች" ወዘተ. ተፅፈው በማንበብ ሲትዮዲ የሞዛ እንዳልነበረች ገመትኩኝ። የቀለም አሳማሉ ደማም ከዚህ ተደም ገጥሞኝ ዳማም እንዳላየው ለእሰት ከዳረኩት ጋር አንድ መሆኑ ስሜቱን ውሉ ረበሸው።

ሀማቤን ወደ ሌላ አቅጣጫ ቢመራልኝ ብዬ አንዱን መሳቢያ ስነሳተው ያ ሲሸሸት የማያውቀው የእጅ ዕሀፈት አፈጠጠብኝ። በጭዳ በተለበጠው ወፍራም መዝገብ ላይ "የማንደርሰይ እንግዲች" የሚል ጠርእሰ ጎላ ተደርጎ ተፅፏል። ገፆቹን ገላልጬ ስመረምር በአጠቃቀሙ ውስጥ ማንደርሰይን የሳበኝ እንግዲች ስም፣ ቁጥ፣ ሰአቱ፣ ያረፉበት ክፍል፣ የተመገቡት የምላብ አይነት -እያንዳንዱ ጉዳችን ንጥብ በዝርዝር መስፈሩ ጉድ አሰኝቶ አፈኝ አስያዘኝ።

ማስታወሻዎቹን መመርመሬን ተጠልኩ። ባለቤቷ በቱም የደረሰች ብኝና ያጋለጠችኝ እየመሰለኝ ሀሊናዬ ሲረበሽብኝ ድንገት ደንግጭኩ። ወዲያው አጠገቤ የነበረው ቴሌቭን አንዴ እረ አለ። ተልቢ ያበልጥ ተገፈፈ። እጄ እየተንቀጠቀጠ አነሳውት። "ማን ልበል ? ማንን ነው የሚፈልጉት ?" አልኩ በተርበፕበተ ድምፅ። የወንድ ይውን የሴት መለየት ያልቻልኩት የሚንተት ሻካራ ድምፅ "ሚስዝ ጄሚንተር ? ሚስዝ ጄሚንተር ነዎት ?" ሲል ጠየተኝ።

"ያቅርታ፣ ተሳስተዋል መሰለኝ። ሚስዝ ጄሚንተር ከሞቱ አመት አልፏቸዋል።" ብዬ አጠገቤ ባገኘውት መንበር ላይ ዘና አልኩበት። እንደ ቲል መንገሪያውን አትኩሬ እየተመለከትው መልስ ስጠብት ድምፅ ሰማው ተደጋጋሚ። ድምው እየጠራልኝ ቢሄድም፣ ማንነቱንም ብገነዘብም፣ በፈፀምኩት ስህተት ከመሸማቀቅ ሌላ እንዴ ያወጣውትን ቃል እንዴት ልዋጠው ? "ሚስዝ ዳንበርስ እኮ ነኝ እመቤቱ፣ ከዚህ ከዚት ውስጥ ነው የደወልኩት" የሚለውን ድምፅ ሰሰማማ የማደርገው

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠፋኝ ።

መተንፈስ እስኪሳነኝ ፡ አፌ እስርስር ብሎ "እ ... ይቅርታ ... ሚስዝ ዳንቨርስ ፡ ቴሌፎኑ ... እ ... እስደነገጠኝ ። ለእኔ ... መደወሉ አልገባኝ ... ያሞኛ ... በውስጥ ሳልክ ... እ ... እ... መናገሬ...ሜሪሽ... አልመሰለኝም ..."አልኩ ።

"ውይ ፡ ለካስ እንዲህ ረብሼዎታለሁና ፡ ይቅርታ የኔ እመቤት ። እኔማ ይፈልጉኛ እንደሆነ ብዬ መጠየቁ ነበር ። በዚያውም ዛሬ ስለሚዘጋጁው የምግብ አይነት ተስማምተው እንደሆነ ለማወቅ ብዬ ነበር የደወልኩት።"

"ነው እንዴ ? ግድ የለም አስማማለሁ ። እርስዎ እንደመሰልዎት ማድረግ ይችላሉ ። እኔንም መጠየቅ አያስፈልግም ።"

"የለም ፡ የለም ። እንዴት ይሆናል ? ዝርዝሩን እንብበው ሀሳብዎን መስጠት አለብዎት እንጂ ። ዝርዝሩ እዚያው ፊት ለፊትዎ ጠረጴዛው ላይ ነው ያለልዎት ።"

እየተበሳጨሁ ጠረጴዛው ላይ ስፈልግ እንድ ወረቀት አገኘሁ ። ለይስሙላ ገረፍ ገረፍ አደረግኩትና "ቆንጆ ነው ፡ በጣም ተስማምቶኛል" አልኳቸው ።

"ይለወጥ የሚሉት ነገር ካለ ማዘዝ ይችላሉ ። ሱጎውን በሚመለከት ደግሞ የግል ምርጫዎን እንዲያስፍሩበት ባዶ ስፍራ ትቼልዎታለሁ ። ሚስዝ ደዊንተር ለሱጎ ልዩ ግምት ትሰጠው ስለነበር ዘወትር በእርሷ ትእዛዝ ነበር የሚሰራው."

"አዩ ፡ ... ሚስዝ ዳንቨርስ ፡ ምኑን አወቅኩት ብለው ? እንደ ድሮው ቢዘጋጅ ፡ ማለቴ ሚስዝ ደዊንተር ትፈቅደው ነበር የሚሉትን ማንኛውንም ነገር ቢያዘጋጁ ግድ የለኝም ።"

"ደግ እንግዲያው ፡ ብቻ እየፃፉ ሳለ ስለረበሽኩዎት ይቅርታ የኔ እመቤት"

"ግድ የለም ፡ ምንም አልረበሹኝም" ብዬ የተገላገልኩ ሲመስለኝ፡ ደብዳቤዎችን ዕፈ ሳበቃ ሮበርትን እንድጠራውና ወደ ፖስታ ቤት እንደሚያስልክልኝ ነገሩኝ ። አመስግኛቸው ጥቂት እንደጠበቅኩ ቴሌፎኑ ተዘጋ — ትልቅ የእፎይታ ብስራት ።

ወዲያው ወደ ማስታወሻዎቼ ስመለስ የኒህ ሁሉ መዛግብትና

t.me/OLDBOOKSPDF

ማስታወሻዎች አዛዥ የነበረችው ሲትዮ ምን ያህል እራሷን በሥራ ትጠምድ እንደነበረ ስገነዘብ በአንዳሩ ደግሞ በራሴ ሥራ ፈትነት በእጅጉ ተማረርኩ ። ሚስዝ ዳንቨርስ ደግሞ ወሐፊ አድርገውኝ ፡ ደብዳቤዎች ሽን ለሮበርት ስፊሊው ፡ ምንትስ ያላቸዉ ። ድንቂም ባለች አቲ ! አንድም የተድሞዋ እመቤታቸው ምን ያህል ብዙ እንደምትባባሩ ስለሚያውቁ እንደ እርሷ ቆጥረውኝ ፡ አሊያም በእሽሙር ሲነኩኝ ይሠሩል ።

ያም ሁነ ያህ እነ እንደዚያችኛዉ ዘመድ ብዙ እደደለውም ። ልባሩ ብልስ ከእኒያ ከሚስዝ ሻን ውጥር ሌላ የማውቀውም የለኝ ። እስቲ ምን ይባላል ? እንድ የምዕፍለት ሰው አጥቼ ለእኒያ እንዲያ ለምጠላቸው አሮጊት ልባሩ ? ምን ይደረግ ?

በሠላብ ዋልዩ በደመ ነፍስ እሞነጫጭር ጀመረ "ውድ ሚስዝ ሻን ውጥር ..." ብዬ ። ጥቂት ጫረ ጫረ አድርጉ የባፍኩትን ስመረምር የእጅ ዕሀፈቱ በጣም አስጠላኝ የደረ መጭርጭር ቢመስለኝ ። ተዳድጂ ልባለው ?

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ — ሰምንት

የመኪና ድምፅ ስሰማ በድንጋጤ ፈንጠር ብዬ ተነሳሁ ። በያትሬስና ባለዜታቸው መሆናቸው ቢገባኝም ሰዓቱ ገና ከሰድስት ትንሽ ፈቅ ማለቱ ነበረና ችኩልው መምጣታቸውን አልወደድኩትም ። ማክሲም በሌለበት ደግሞ ብቻዬን ምን ላደርጋቸው ነው ? የሚሰው ሐሳብ ነበር ከፋኝ የተሜንኝ ። በመስኮት በልዬ ወጥቼ ለመደበቅ አሰብኩ ። ገብተው ሲያጡኝ ፍሪዘ "እመቤቱ ወጣ ሳይሉ አይተሩም" ስለሚሏቸው ምንም ሳይጠራጠሩ ቁጭ ብለው ይጠብቃሉ ብዬ ውሳኔዬን በገቢር ለመተርጎም ወደ መስኮቱ ተጣደፍኩ ።

ኩቴዬን የሰው ውሽቼ ሚንቀሳቃቸውን አጮንተው እሱን አይኔን አዬኝ ። በተለይ ጀስፐር ሙሬውን እየወዘወዘ ሲከተለኝ በጣም ጠላሁት ። በልዬ ወጣሁ ። ድምጼን አጥፍቼ ጥገጣን መሬውድ እንደጀመርኩ እየቀረበ የሚመጣ ድምፅ ስሰማ ወደ ኋላዬ — እግሬ አውጭኝ ። በትልቁ የእንግዳ ማረፊያ በኩል አልፈ ወደ ግሩ ስታጠፍ ፈቅ ለፈቱ ያገኘሁትን በር ከፍቼ ገባሁ ። በፈሲ ላይ የፈጠርኩት ሚንቀት ከአካባቢው ይበልጥ እንድርቅ እየገፋፋኝ ፡ በአንዱ በር ገብቼ በሌላው ስወጣ ፡ በአንዱ ደረጃ አሻቅቤ በሌላው ሳቆለቁል ሙሬውን አይቼው ከማላውቀው አካባቢ ደረስኩ ።

ቀደም ሲል ያላየኋት እንዲት ሥራተኛ መወልወያዋንና ባልዲዋን እንደያዘች እንደ ጉድ ስታየኝ ድንጋጤዬን ለመሸፈን ድንገት እንደመጣ ልኝ "እንደምን አደርሽ ?" አልኳት ። ምላሷ ተባስሮ "እንደምን አደሩ እሜቴ?" ስትለኝ ቀና ብዬ እንኳን አላየኋትም ። እንበረችበት ደርቃ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደተረች ጥያት ሄድኩ ደረጃውን ለመውጣት ። ወደ መኝታ ክፍሉ ያመራሽል ያልኩት መንገድ ወጥ ካለ ኮሪደር ላይ ጣለኝ ። የማደርገው ሁሉ ጠፋኝ ። ልቤ ተረበሸ ። አንዱን በር ስከፍተው አልም ያለ ፈለማ ተቀበለኝ ። ከመስኮቶቹ በትንሹ በሚገባው ሜላንሞል በመታገዝ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች አየሁ ። አልጋ ፡ ቁንጅ ቁንጅ የቤት ቁሳቁሶችና ልዩ ልዩ የቤት ማጌጫዎች በአዳራ መከላከያ ተሸፍነዋል። የዕቃዎቹ አቀማመጥ ፡ የክፍሉ መጨለምና ወና ወና ማለት በአካባቢው ሰው ዝር ካለበት ከረምረም ማለቱን ይጠቁማሉ ።

ይህንን ትቼ በኮሪደሩ መጨረሻ ወደሚገኘው ክፍል ገባሁ ትንሽ ብሩህ ክፍል ። ወደ መስኮቱ ተጠግቼ ቁልቁል የላኩት አይኔ በረጅሙ የተዘረጋውን ለምለሙን መስክ ሲያሳየኝ ባሻገር የሚታየውንም ባሕር እያታ አልነፈገኝም ። ሚስዝ ዳንበርስ ከነገሩኝ ምዕራባዊው ሕንፃ ውስጥ መሆናችንን አእምሮዬ ተገንዝቦ ሊያስገነዝበኝ ሲኮንድም አልጠየቀው ።

በሞገዱ ኮርኳሪነት ገባ ወጣ ፡ ሄድ መለስ በሚለው ውሃ ተመሰጥኩ። ፀሐይ የባሕሩን ወለል በውብ ጨረሯ አድምቃዋለች ። አንፀባራቂ መልክ ለግሳዋለች ። በድርጊቷ የተኩራራች አይነት ተነፍሳ ትንሳማለላ ለች ብዙም አልዘለቀችበትም እንጂ ። ደመናው ጥረቷን መና ለማድረግ ይጣደፍ ይመስል ፅልሙን ዘረጋው ። ባሀሩ ጠቆረ ፡ አካባቢው ጨለገገ ፡ ፀሐይ ከደመናው ወፍራም ካባ ውስጥ ሰጠመች ። ምስኪን ፀሐይ አሳዘነችኝ ። በዚህ ተፈራራቂ የተፈጥሮ ክስተት እየተደነቅሁ ወደ መጣሁበት ስመለስ በአድናቆት ሽንግዬ ደስታ የዘራሁበትን ልቤን የሚያውክ ነገር ገጠመኝ ።

ከበስተጀርባዬ በር ሲከፈት ሰማሁ ። ድምፁ ተልቤን ከገፈፈው በላይ አይኔ ያረፈበት አካል ሀሊናዬን ለማሳት የሚፈታተነን ነበር ። ሁለታችንም ቃል ሳንተነፍስ ለጥቂት ሰኮንዶች እንደተፋጠጥን ቆየን ። ከሰው ማጀት አድፍጬ ገብቼ እጅ ከፍንጅ የተያዝኩ ያህል ሀፍረት አሸማቀቀኝ። ከአፌ ተድሞ ድርጊቱን ለማሳበቅ ይሽተዳደም የመሰለኝ ፊቱ ቅያርያር ማለቱ ቢሰማኝ "ወደ...ክፍሉ እሄዳለሁ ብዬ..ሙ.. መንገዱ ጠፍቶኝ...ነው ።" አልኩኝ የሞት ሞቴን ፡ ስሜቴን ለመቆጣጠር እየሞከርኩ ።

"እንዴ ? ወደ ተውራኒው አቅጣጫ እኮ ነው የመጡት ። ይህ'ውማ ምዕራባዊው ሕንፃ ነው ።" አሉኝ አሮጊቷ ሚስዝ ዳንበርስ በማርምም

t.me/OLDBOOKSPDF

አይሉት በቁጣ አይን እያስተዋሉኝ ።

“አሁንማ የት እንዳለሁ አውቁሞለሁ”

“ለመሆኑ ከፍሎቹን ገብተው አይተዋቸዋል እንዴ ?”

“እረ በፍፁም ። አንዱን በር ስከፍተው ጨለማ ቢሆንብኝ ወዲያው ዘግቼው ተመለስኩ ። እበሩ ላይ ሆኜ እንጂ ወደ ውስጥ እንኳን አልገባሁም። ይቅርታ ፡ ሰው እንዳይከፍተው መከልከሉ አልገባኝም ። ደግሞ ሆን ብዬ ለማጥፋት ያደረግኩት እንዳይመስልዎ”

“እመቤቱ ከፍሎቹን ገብተው ለማየት ከፈለጉም ላስከፍትልዎ እችላለሁ ። በሙሉ የተሟላ ቁሳቁስ ስላላቸው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ናቸው።”

“እረ እኔ እንደዚያ ማለቱ አይደለም ።”

“ምናልባት እዚህ አካባቢ ያሉትን ክፍሎች ሁሉ እንዳስጎበኝዎ ይፈልጉ እንደሆነ ብዬ ነዋ ።”

“አይ ፡ አይ” በማለት ሞንቅላቱን ነቀነቅኩት “እንዲያውም ወደ ምድር ቤት እየሄድኩ ነበር ።” ብዬ ደረጃውን መውረድ ስጀምር ከጎን ጎኔ ሰክ ሰክ ይላሉ ። በገረዷ የታጀበች እመቤት ሳይሆን በዋርዲያ የምትጠበቅ እስረኛ አድርጌ ነበር እራሴን የቆጠርኩት ።

“ለወደፊቱም ቢሆን ሥራ በሌልዎት ጊዜ ቢያስታውሱኝ በዚህ በምዕራባዊው ሀንግ ውስጥ የሚገኙትን ክፍሎች አንድ በአንድ ላሳይዎ እችላለሁ ።” አሉኝ ።

እንደገና እንዲህ አጥበቀው መወትወታቸው ለምን እንደሆነ ባይገባኝም የሕሊና ዕረፍት ነበር የነሳኝ ። ድርጊታቸው የቆየ የልጅነት ትዝታዬን ቀስቅሶብኝ የጊዜን ሰሌዳ ወደኋላ መለስ ብዬ እንድቃኝ ገፋፋኝ። አንድ ቀን ኃይኖዬ ቤት ሄጄ ስንጫወት ሳለ ጠጋ ብላኝ ከንዴን ያዝ አድርጋ “አንድ ነገር ላሳይሽ ? ምን መሰለሽ ? መጽሐፍ። ከእናቴ መኝታ ክፍል ቁምሳጥን ውስጥ ቆልፈው አስቀምጠውታል። ነይ እንሂድ ላሳይሽ ።” ብላ ስታንሾካሹክልኝ አይኗ እንዴት ይቁለጨለጭ ፡ ፊቷ እንዴት በራ ፈካ ይል እንደነበር ትዝ አለኝ ። እንዴት ጎንተል አድርጋኝ እንደነበር ሲታወሰኝ ደግሞ አውን ያደረገችው መሰለኝ። ከንዴን በእጇ ዳሰስ ማድረጌ ሊያስቀኝ ነበር ። አሮጊቷ እንዳያዩኝ በመፍራት ስሜቱን ቆንጠጥ አደረግኩት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ለስነዘሩት ሀሳብ እንዳችም አስተያየት አለመሰንዘራን ሲረዱ አሮጊቷ ተጠሉ ። "በሮቹንና መስኮቶቹን በሙሉ አስከፍቼ ፡ ፅዮምቼም በቀድሞ መልካቸው እንዲስተካከሉ አደርጋለሁ ። ዛሬ ጠዋትም ላስንዘ ኝም እችል ነበር እኮ ፡ ደብዳቤ እየጻፉ ስለነበረ የሚመችም አልመሰለ ኝም እንጂ"

ደረጃውን ወርደን ስንጨርስ በሩን ከፍተው የማለፍ ቅድሚያውን ሰጥተውኝ ፈንጠር አሉ ። በእኒያ አስፈሪ ጥቂቱ እያናጅቸው ጠልተው መረመሩኝ ።

"ስለ ቅን አመለካከትም አመሰግናለሁ ፡ ሚስዝ ዳንቨርስ ። ከፍሎቹን ለማየት ስፈልግ በሌላ ጊዜ እንጠይቃለሁ ።" ብያቸው ተከታትለን ወጣን ።

"ግን እኮ ያሀቸው መተላለፊያ ወደ ምዕራባዊ ሕንፃ ከሚመስደው ዱጨም የተለየ መሆኑን እያዩ መንገዱ እንዲት እንደጠፉም ሊገባኝ አልቻለም ።" አሉ ሚስዝ ዳንቨርስ ተንከላቸውን እያደስ ።

"በዚህ በኩል እኮ አደጋለም የመጣሁት" ስላቸው

"አሃ ፡ በንሮ በኩል ነዋ የሄዱት ?" አሉኝ ቅክ ብለው እያዩኝ ። አስተያየታቸው ቢያስጠላኝ ከአያናቸው እየሸሸሁ "አምን" አልኳቸው ነገሩን በአጭሩ ለመቅጨት ። አሮጊቷ ግን የሚተውኝ አይነት አልነበሩም ። ከአሁን አሁን ለምን በንሮ በኩል እንደሄድኩ ትንጣረኛለች ብለው ነው መስለኝ አፋቸውን ከፍተው አያናቸውን እንደተከለከብኝ ቀሩ ። በመስኮት ዘልዬ ስወጣ አድብተው ሳያዩኝ ፡ ምናልባትም በምዕራባዊ ሕንፃ ውስጥ ስንከላወስ ከአንዴ ግማ ተለጥፈው ሳይከታተሉኝ አልቀሩም የሚል ጥርጣሬ አደረብኝ ። "ሚስዝ ቢያትሪስ፣ ባለቤታቸው ሳያመጡ ይቀራሉ ብለው ነው ? የመኪናቸውን ድምጽ የሰማው መስ ለኝ" ማለታቸው ደግሞ ጥርጣሬዬን ይበልጥ አጠናከረልኝ ።

"እውነት ?" አልኩ ሞራሽ ለንነሩ እንግዳ በመምሰል "በፍፁም አልሰማውም ።"

"ፍሪዝ ወደ አልፍኙ ይዟቸው ሳያዜድ አይቀርም ። ከእንግዲህም መንገዱ ይጠፋዎት ይሆን ?" ሲሉኝ ከእርሳቸው ምኔ በተገላገልኩ ያለው አእምሮዬ ምላሴን አጣድፎ "ግድየለም ፡ ግድ የለም አውቀዋለሁ" አሰኘው ። እየተቅበዘበዝኩ ወደፊቱ ስገሰግስ ዞር ብዬ ባላያቸውም ቁመው

t.me/OLDBOOKSPDF

በእያናቸው እንደሚከተሉኝ መገመቱ አልተሳነኝም ። ጥቂት ከተራመድኩ በኋላ አንተን በዘደ መለስ ሳደርገው አሮጊቷ ከላይ እስከታች ጥቁር ቀለም የተነከረ ሐውልት መሰለው ተገትረው አየኋቸው ።

ከእልፍኙ በር ላይ ቆም ብዬ ሳዳምጥ የማክሲምን ድምፅ ሰማሁ ። የተለያየ ድምሰ መስማቱ ደግሞ ክፍሉ በእንግዶች የተመላ ስለመሰለኝ ሽብሩ አናለብኝ ። ሐዋን ሆኜ እንግዶችን እንድጨብጥ ስጠራ ይሰማኝ የነበረው የፎንቀት ስሜት አይነት አንዴ መረረኝ ። የማላመልጠው ዕዳ ሆኖብኝ እንጂ ለዚያው ተሰውሬ በቀረሁ ምንኛ ደስ ባለኝ ነበር ። የሞት ሞቱን በሩን ክፍቼ ስገባ ክፍሉ ረሜ አለ ። ያን ሁሉ አፍጣጭ አይን የጠፒን ያህል ፈራሁት ።

''እሜቱ መጡ!'' አለ ማክሲም ድምፁን አጉልቶ ''የት ተደብቀሽ ኖሯል አስነአሁን? ፍለጋ ለመውጣት ምንም አልቀረንም ። በይ ነይ ፡ ከእንግዶቹ ጋር ላስተዋውቅሽ ። ይህች ቢያትሪስ ናት...'' እንዳለኝ ወደ ሊትዮኑቱ ሳዘግም ''...እንዴ ምን ነካሽ? ውሻውን ጨፈለቅሽው እኮ...'' አለኝ ማስተዋወቱን አቋረጠ ።

እሀትየው ይስሙኛል ብዬ ስጠብቅ ጠንከር ባለ የእጅ ሰላምታ ገላገለኝ ። አፍጠው ካዩኝ በኋላ ወደ ማክሲም ዞር ብለው ''ካንተ ገለፃ ተነስቼ እኔ ሌላ ሰው ነበር አእምሮዬ ውስጥ የቀረፅኩት ። በፍፁም እንደነገርከኝ አይደለችም'' አሉ ።

ስቀውልኝም ይሁን ስቀውብኝ ሳይገባኝ ሌሎች ሲስቁ ብቻ አብረዬያቸው ሳቅሁ ። ስለኔ የነበራቸው ግምት ምን ነበር? ማክሲምስ ምን ብሏቸው ይሆን? የሚሉት ጥያቄዎች ከንከን አደረጉኝ ።

''ባለቤቷ ደግሞ ይዝናልሽ ፡ ጂልስ ይባላል'' ብሎ ማክሲም እጇን ይዞ ሲያስጠጋኝ ሰውዬው በጠንካራ መዳፋቸው ለቀም አደረጉኝ ። ኮስማና ጣቶቹን ጨማመቂቸው ። ሽምቅቅ ማለቱን አይተው ልዝብ ፈገግታቸውን ጋበዙኝ ። በመነፅራቸው ተከልለው በሚንከባለሉት አይኖቻቸው በርህራሄ ዳሰሱኝ ።

''እዚህ ደግሞ ወኪሉ ፍራንክ ከሮውሌይ አለልሽ'' አለ ማክሲም ማስተዋወቱን በመቀጠል ። ሰውዬው ምስኪን ብጤ ነው ። እንደ ሰጎን እንገት በተመዘዘው ከሲታ አንገቱ ላይ ማንቁርቱ ነው ጎልቶ የሚታየው። ቀና ብሎ ሲያየኝ ልረዳው ባልቻልኩት ምክንያት አይኖቹ ልዩ የእርይታ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስሚት ለገሱኝ ።

ቢያትሪስን ሰረቅ አድርጌ አየኋቸው ። ረዘም ፡ ሞላ ያሉ ፡ መልክ መልካም ሴት ወይዘሮ ናቸው ። አይናቸውና አገጫቸው አካባቢ ከማክሰኞ ጋር ያመሳስላሉ ። አቋማቸው ግን በምናቤ የተረዕኩላቸውን ባሕሪያት የሚያላብሳቸው ሆኖ አላገኘውትም ። ከአጠቃላይ ውጨታቸው ቀኬ የያዛቸው ውሾችን በመንከባከብ የተካኑ ፡ ስለፈረስ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ያላቸውና አተኳኮስ ጠንቅቀው የሚያውቁ መስለው ታዩኝ ።

አረፍ ከማለቱ ''ማክሰኞ እንደነገረኝ ትናንት ማታ መጣታችሁ ነው መሰለኝ ። ታዲያ ማንደርሉይ ምን መስሎ ታየሽ?'' አሉኝ ሚስዝ ቢያትሪስ ።

''ግና ምኑን አየሁት ብለው? ብቻ በጣም ቆንጆ ነው'' አልኋቸው ። ከላይ እስከታች ቢቃኙኝም አስተያየታቸው የሚስዝ ዳንቨርስ አይነት ተንኮል ያዘለ አልነበረም ። ምራቱ እስከሆኑ ድረስ ደግሞ ቢገመግሙኝም ይገባቸዋል ። ማክሰኞ እጄን በእጁቱ ማሻሸት ሲጀምር ልቤ በኩራት ተከፈለ ። ድፍረት ድፍረት አለኝ ።

ሚስዝ ቢያትሪስ ወደ ማክሰኞ ዞር በማለት ''ሽማግሌው ተስማም ቶት የለ እንዴ? ውይ! ብቻ ከዚያ አጥልቶብህ ከነበረ አዚም ለገላገለህ አምላክ ምስጋና ይግባው ። '' ብለው ከተናገሩ በኋላ ሞንትላኮቹን ወደኔ ዘንበል አድርገው ''ለዚህ ያበቃሽው አንቺም ብትሆኚ የምቢነኝው ተካፋይ ነሽ'' አሉኝ ።

ማክሰኞ ፈጠን ብሎ ''እኔ ምኔም እንዳማረብኝ ነው ። በሕይወቱ እንድም ቀን ተለውጬ አላውቅም ። አንቺ ችጣርሽ ምን እንደሆነ ይገባሻል? ሰው ሁሉ እንደ ባለዚትሽ ካልተድበለበለ በሽተኛ ነው የሚመስልሽ'' አለ ።

''ሂድ አባክህ! ከመንፈቅ በፊት እንዴት ሙልትልትህ ሠርቶ እንደነበረ አንተ እራስህ ጠፍቶህ ነው? ጂልስ ፡ ያኔ ማክሰኞ ጣረ ሞት አይመስልም ነበር? ይሄ ሰው መንኮኮቱ ነው ብዬ ላንተስ ነግሬህ አልነበረም?'' አሉ ሚስዝ ቢያትሪስ ።

''በእርግጥ በጣም አቦ ነው የተለወጥከው ማክሰኞ ። ምን ትላለህ ከሮውሌይ? ሰውዬው በጣም አልተስማማውም እንዴ?'' አሉ ሚስተር ጂልስ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰምቹ ይሠን ያህል ስለ ማክሲም ጨንነት ፡ ስለ መልኩ መመለስ መደጋገማቸው ሊገባኝ አልቻለም ። በተለይ እህቱ ለነገሩ ከሚገባው በላይ ግምት ሰጥተው እንዲህ ሙጭጭ ማለታቸው አንዳች ቢኖር ነው የሚል ጥርጣሬ አሳደረብኝ ። የማክሲም ግንፍል ግንፍል ማለትና የፊቱ መቀያየር ደግሞ ምክንያቱን የማወቅ ጉጉቴን ይበልጥ አጠናከረው ።

"ማክሲም እንዲህ የጠቆረው ወሐይ በገቡበት እኩ ነው ። በተለይ ቬኒስ በነበርንበት ወቅት ጠቆር ማለቱ ይበእጥ ያሳምረው ይመስል ይሠንኝ ብሎ በወሐይ ሲንቃቃ ይውል ነበር ።" አልኩ — ካደረብኝ ሐፍረት ጋር እየታገልኩ ።

ከነገሩ ያሠንን ከአንጋፊ ሊገባኝ ባይችልም ሁሉም ሳቁ ። ወዲያው ሚስተር ክሮውሌይ "መቼም በእሠኑ ወቅት የቬኒስ የአየር ሁኔታ በጣም ቆንጆ ሳይሆን ይቀራል?" በማለት ላቀረበልኝ ጥያቄ አምንታዊ ምላሼን ሰጠሁት ። በዚሁ ሞውሙታቸን እቅጣጫውን በመቀየሩ በመካከላችን ሰፍኖ የነበረውን ውጥረት አረገበው ። የተለያዩ ርዕሶችን እያነሳን ስንጨዋወት ቆይተን ቢያትሪስ ውሻውን በእግራችው እየጎነታተሉ "እረ ይሄ ጀስፐር አለቅጥ እየወፈረ ነው ። ገና ሁለት ዓመት ሳይሞላው እንዲህ መዘርጠጡ ምንድነው? በደንብ እንቀሳቅሱት እንጂ ፡ ለመሆኑ ምን እየመገብከው ነው ማክሲም?" አሉ ።

"የኔ እህት ፡ እንዲያው ስለ እንስሳት ካንተ የበለጠ ዕውቀት አለኝ ለማለት እየጓጓሽ እንደሆነ እንጂ ውሻዬ ካንቺ ውሾች የተለየ ነገር አይደለም የሚመገበው" ሲል መለሰ ማክሲም ።

"ኤዲያ ፡ እንዴት ጥሩ አድርገህ አወቅህ በል! ለሁለት ወራት ተለይተኸው ምን ይበላ እንደነበረ አውቅ ነበር ነው የምትለኝ? በቀን ሁለት ጊዜ ፉሪዝ አስከትሎት እስከ ዋናው በር መሄዱ በቂ ነው እንዳትለኝና በሳት እንዳልፈርስ ። ጂምናስቲክ በደንብ የሚሰራና የማይሰራ ውሻ በወጉ ነው የማውቀው ።" አሉ ቢያትሪስ ።

"ተይ እባክሽ ፡ እንዳንቺው ጅላጅል ውሻ መስፋታም ከሚሆን መንዘርጠጡን እመርጣለሁ ።"

"ኡኡቱ! ባለፈው የካቲት በተደረጉት ውድድሮች ሁለቱ ያሸነፈው የኔው እንበሰ አያደለም እንዴ? መች ጠፍቶህ? እንዲሁ ለማጥላላት ያልከው እንጂ" በማለት ተቁነጠነጡ ቢያትሪስ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ማክሲምና እህቱ ዘወትር እንዲህ ይነታረኩ እንደሆነ ባላውቅም እውን ግን በመካከላችን የጭቅጭቅ ድባብ መርበቡን አልወደድኩትም ። ፍሪዝ መጥተው ምሳ መዘጋጀቱን በነገሩንና በገላገሉን አሰኘኝ ። እስከዚያው ሀሳባቸውን ለማስቀየር ቢረዳ ብዬ "ለመሆኑ ቢታችሁ ከዚህ ብዙ ይርቃል እንዴ? በጊዜ መሄድ አለብን ትሉ እንደሆን ብዬ ነው" የሚለውን ጥያቄ ለቢያትሪስ አቀረብኩላቸው ።

"ስማኒያ ኪሎ ሜትር ቢሆን ነው ። ከዚህ ቀጥሎ ካለው ወረዳ ውስጥ ነው ። የኛ አካባቢ ለአደን እንዴት የሰጠ መሰለሽ ። ማክሲም ሲፈቅድልሽ አንዴ መጥተሽ ልትጎበኝን ይገባል ። እንዳሻሽ እንድትገለገ ይበት ጂልስ ፈረሱን ያፈቅድልሻል ።" ሲሉ ቢያትሪስ መለሱ ።

"ውይ ፡ ፈረስ መጋለቡን የት አውቅበታለሁ ብለው? በልጅነቱ ትንሽ ትንሽ እሞክር ነበር ። እውን ግን እስከነአካቴው ሳልረሳው እቀራለሁ?" አልኳቸው እፊቴ ፈረስ አቁመው የግድ ካልወጣሽ ብለው ያስገደዱኝ ይመስል በእጄም በአይኔም እየተለማመጥኩ ።

"እይ ፡ ገጠር ተቀምጠሽ አልጋልብም ማለት አይገባም ። የግድ መለማመድ አለብሽ ። ማክሲም ስዕል መሳል ትወጂያለሽ ነው ያለኝ! በእርግጥ ጥሩ የጊዜ ማሳለፊያ ነው ። ሆኖም ያን ያህል ልምምድ የሚያሻው አይመስለኝም ። እንዲያው አንዳንዴ ደጅ ሲጨተይ ፡ አየሩ ሲቀዘቅዝ ብትሰሪው ነው።"

"ስሚ ቢያትሪስ ፡ እኛ እንዳንቺ የንፁህ አየር ድሆች አይደለንም" አለ ማክሲም ጣልቃ ገብቶ ።

"የኔ ወንድም እኔ ካንተ ጋር አይደለም የምነጋገረው ። የማንደር ሌይ መናፈሻዎች እያሉልህ አየር ፍለጋ እላይ ታች መዳከር እንዴሉለብህ ለመናገር ከሆነ ሁላችንም እናውቅልሃለንና በከንቱ አትድከም ።"

እንደገና ነገር እንዳይደፈርስ ሰግቼ "እኔም በእግር መንሸራሸር በጣም ነው የምወደው ። ማንደርሌይ ውስጥ ቀኑን ሙሉ ስንሸራሸር ብውል ጭራሽ የሚሰለቸኝ አይመስለኝም ። አንዳንዴ አየሩ ሞቅ ሲል ደግሞ ወደ ባህሩ ወረድ ብዬ መታጠብ ደስ ይለኛል ።" አልኩ እየተጣደፍኩ ።

"ልጄ አንቺ ሁሉንም ነገር በቅን ልቦና እያየሽው ነው ። ቅዝቃዜውን ባየሽው ። የባሕሩ ዳር ጠጠርስ በየት በኩል ያሳጥባል

t.me/OLDBOOKSPDF

ብለሽ?'' አሉኝ ቢያትሪስ ።

''ምናልባት ሞንዴ እያየለ ያውክ እንደሆነ እንጂ ይሄ እንኳን ችግር አያፈጥርም ። ከባሀሩ ወሽመጥስ መታጠብ አያመችም እንዴ ?'' ስል ለሰንዘርኩት ጥያቄ ከማንኛውም አቅጣጫ የሚመልስልኝ አጣሁ ። ምን እንደተናገርኩ ትውስ ሲለኝ ሰውነቴ ፈረሰ ። ድንጋጤዬን ለመሸፈን፡ ሀፍረቴን ለመደበቅ አንገብሽ የጀስፐርን ጅሮ ማሻሸት ጀመርኩ ።

''ያልቲንስ ይህን የከበደውን ሥጣ ለማራገፍ መዋኘቱ የሚጠቅመው ለጀስፐር ነበር ። እንዴት ነው ጀስፐር ፡ ባሕሩ ውስጥ መዋኘት ትንሽ አያከብድም ብለህ ነው?'' አሉ ቢያትሪስ ውሻውን ከኔው ጋር እያሻሹ ። የእርሳቸው ድምፅ ፈጥኖ ባያደርስልኝ ኖሮ ክፍሉ ውስጥ ሰፍኖ የነበረው ዐየር ከመታብር ይበልጥ የሚያስፈራ ነበር ።

ማክሲም ''ኧረ እናንተ ስምች ምንድነው የምንጠብቀው? እኔ በጠኔ መሞቴ ነው'' ሲል ሚስተር ክሮውሌይ ተቀበለውና ''የሚድግዴው ሰዓት እንደሚያመለክተው ገና ሰባት ሰዓት መሆኑ እኮ ነው ።'' አለ ።

''ይሀን ሰዓት ተወው እባክህ ። ጥድፊያው የት ለመድረስ እንደሆነ እንጂ ሁሉ እንደጋለበ ነው ።'' አሉ ቢያትሪስ ።

''ከተስተካከለ ስንት ጊዜው'' ሲል መለሰ ማክሲም ።

በዚህ መሐል ፍሪዝ ብት ብለው ምሳ መዘንጀቱን ሲነግሩን ተያይዘን ወጣን ። እኔና ቢያትሪስ ወደፊት ተድመን ስለነበር ''እኔ የዚህ የፍሪዝ ነገር ነው ግርም የሚለኝ ። ሁሉ እንድ ፍሬ ልጅ እንደመሰለ? አትታዘቢኝና እኔማ እርሱን ባየው ቁጥር የኮረዳነት ዘመኔ የተመለሰ ይመስለኛል ። አንቺም እነ ከጣትኩሽ በላይ ልጅ ነው የምትመስዪው ። ማክሲም እንኳን ዕድሚሽን ነግሮኝ ነበር ። ከዚያም የምታንሽ ለማላጋ ነሽ ።'' አሉኝና አያይዘውም ''በነገራችን ላይ ማክሲምን በጣም ትወጂዋለሽ?'' በማለት ጠየቁኝ ።

ዱብ ዕዳ ጥያቄ! እንደተደናገጥኩ ከውኔታዬ መረዳታቸው አልቀረም ። ከንዴን ጠበቅ አድርገው ይዘው መፈገግ ቃጣቸውና ''ግድ የለም ፡ ከምላስሽ ምን አለኝ ብለሽ? ፈትሽ በደንብ ይናገራል ። በሰው ጉዳይ ጣልቃ መግባቱን አበሳው ብሽ መሰለኝ ። ብቻ እንደማትቀየሚኝ ተስፋ አደርጋለሁ ። እንዲህ የሚያደርገኝ ምን መሰለሽ? ለማክሲም ከሚገባ በላይ መጨነቄ እኮ ነው ። እንዲህ እንደ አይጥና ድመት መፈላለጋችንን

t.me/OLDBOOKSPDF

አትዪ ። አምና ይህን ጊዜ ምን ይመስል እንደነበር ባየሽው ። ዕድሜ ላንቺ ፣ እንዲህ በአንድ ጊዜ መልኩን ሁሉ ለዋወጥሽው ። ጠቅላላ ታሪኩን እንኳን እንደምታውቂው…'' ብለው ሀሳባቸውን ሳይቋጩት ከምግብ አዳራሹ ገባን ።

ስላለፉት ዓመታት የማንደርሌይ ሕይወት ፡ ስለተፈፀመው አሳዛኝ ድርጊት ቅንጣት ፍንጭ እንደሌለኝና ማክሲምም እውስጡ አምቆት ብቻውን ከመብሰልሰል ሌላ ምንም እንዳልነገረኝ ቢረዱ ቢያትሪስ ምን ይሰማቸው ይሆን እያልኩ ብቻዬን ማሰብ ጀመርኩ ።

ሰላማችንን የሚያደፈርስ አንዳችም ነገር ሳይፈጠር ምሳው በመልካም መግባባት መገባደዱ ትልቅ የእእምሮ ዕረፍት ነበር የሰጠኝ ። የማንንም ሕሊና የማይጎተጉቱ ነጥቦች እየተነሱ ስንነጋገር ከቆየን በኋላ የሚስዝ ዳንቨርስ ስም ሲነሳ ''የምትገርም አሮጊት ናት'' አሉ ጂልስ ። ወደ እኔ ዞር ብለው ደግሞ ''አይመስልሽም?'' ሲሉ ጠየቁኝ ።

''ማን? ሚስዝ ዳንቨርስ? በጣም ግሩም ሰው ይመስላሉ ።'' ስል መለስኩላቸው ።

''እምን …ብቻ… አንዳንድ ቆርፋዳ ባሕሪዋን ማለሳለሱ በጣም ይከብድ ይመስለኛል እንጂ…'' ብለው ክፍሉን አንደ በሳት ሞሉት ።

የአሁኑ ጨዋታ እንደረበሸኝ ከገፅታዬ የተረዳው ክሮውሌይ ከተነሳው ነጥብ ጋር ምንም ተዛምዶ የሌለው ነገር አንስቶ የውይይቱን አቅጣጫ በመቀየሩ በጣም ወደድኩት ። በዚሁ መሠረት እንደየጨዋታው መልክ ከባቢው አየር አንዴ ወጠር እንደገና ረገብ ባለ ቁጥር ልቤም አብሮ መወዛወዙ ብቻ ሳይሆን የማክሲምም ስሜት መናጋቱ ይበልጥ አሳሰበኝ ።

ግራ ቀኙን ስማትር ማክሲም ፊቱ ቅይርይር ብሎ ሲኮነጠጥ አየሁት ። እርሱም አይቶኝ ኖሮ ወደ በሩ እያመለከተ እንድወጣ ጠቀሰኝ ።

ብድግ ስል ጠረጴዛውን ነቀነቅኩት ። የብርጭቆው መጠጥ ተደፋ ። በጣም ከመደናገጤ የተነሳ በተሳሰረ ምላስ ይቅርታ እየጠየቅሁ ቦታውን ለማፅዳት አጎነበስኩ ። ማክሲም ''ተይው ፡ ተይው ፡ ፍሪዝ ያፀዳዋል ፡ ይልቅ ሌላ ትርምስ እንዳትፈጥሪ'' አለኝና ''እባክሽን ቢያትሪስ ግቢውን አዟዙሪሽ አሳያት'' ሲል እሁቱን ጠየቃቸው ።

ወደ መስኩ ወርደን መንሸራሸር እንደጀመርን ቢያትሪስ ጨዋታ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጀመሩ ''እንዲያው እዚያው ላልያን አንድ ሦስት አራት ወር ቆይታችሁ ብትመጡ ይሻል ነበር ። በጋው አጋማሽ ላይ ነው ማንደርሉይ በጣም ደስ የሚለው'' አሉኝ ።

''አውንም ቢሆን በጣም ደስ ይላል ። ጥቂት ስቆይ ደግሞ ይበልጥ እንደምወደው እርግጠኛ ነኝ'' አልኳቸው ።

''በነገራችን ላይ ፡ እዚያ ፈረንሳይ ውስጥ ከአንዲት ነዝናዛ አሮጊት ጋር ትኖሪ ነበር ነው ያለኝ ማክሲም?''

ስለ ሚስዝ ቫን ሁፐርና ከእርሳቸው ጋር ስለነበረኝ ግንኙነት ስነግራቸው ያዘኑልኝ ቢመስሉም በሙሉ ልባቸው አያዳምጡኝም ነበር።

''ያገርምሻል ፡ ማክሲም ደብዳቤ ዕር ደቡባዊ ፈረንሳይ ውስጥ እንደተገናኛችሁ ፡ በጣም ልጅ እግርና በጣም ውብ እንደሆንሽ ሲነግረኝ እውነቱን ነው የምልሽ ትንሽ ግር አሰኝቶኝ ነበር ። ሁላችንም እጅግ ዘመናዊ ፡ የጊዜውን ፋሽን የምትከተል ፡ ከሰውና ከአካባቢው ጋር በቀላሉ የምትግባባ ልጅ ነበር በአእምሯችን ቀርፀን የነበረ ። ቅድም ግን ገና ወደ አልፍኙ ብት ስትደ የራሴን አደን እንድጠራጠር ነው ያደረግሽኝ ።'' ብለው ሲስቁ አብረዷቸው ልሳት እንጂ ይህ አስተያየታቸው ሁኔታዬን በመውደድ ይሁን ወይም በመንቀፍ በሚራሽ ሊገባኝ አልቻለም ።

ቢያትሪስ ንግግራቸውን በማራዘም ማክሲም በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ ላይ እንደነበርና ከኔ ጋር በመገናኘቱ ያንን ጨለማ ጊዜ እያስረሳው መሆኑን ሲነግሩኝ ልቤ ለሁለት ተከፈለ ። አንዱ ልቤ እንዲሁ እንደጀመራት ስለ ጥንቱ ማንደርሉይና ስለ ማክሲም ሕይወት ለመስማት ሲጓጓ ሌላኛው ደግሞ ምናምንም ቀርቶብኝ ሰላም ብቻ ባልተነፈግኩ ባይ ነበር ።

''እኔና ማክሲም በዐባይ በዓፀዱም አንገናኝም ። እኔ ለማንኛውም ነገር በጣም ግልፅ ነኝ ። ለሰው ያልኝን ፍቅርም ሆነ ጥላቻ መደበቅ አላውቅበትም ። በአንድ ነገር ላይ ደስታም ይሁን ሐዘን ካደረብኝ አውሎ ማሳደር የለችም ። ወዲያውኑ ገፅታዬ ላይ ይነበባል ። ማክሲም ሁሉን ሆዴ ውስጥ ተብሮ ነው የሚኖረው ። እኔ በረባ ባልረባው ሁሉ ድንጉት ቱግ እልና ወዲያው ይበርድልኛል ። ማክሲም አንጥፊው ቢረጋጠት እንኳን በትእግስት ማሳለፍ ነው ። ግን ትእግስቱ ተሟጦ የገነፈለ ዕለት ግን እፊቱ ሊቆም? ሰማይና መሬቱን ያደበላልቀዋል ። እያድርስብሽ ። ብቻ እንቺም በቀላሉ የምትበገሪ አይነት አትመስይም ።'' አሉና ቢያትሪስ ፈገግ ብለው ንግግር አደረጉኝ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ይህንን እዚህ ላይ ትተው ወደ ዐጥሬ ተሸጋገሩ ። እንደ ወዲህ መልሺው ፣ እንደ ወዲያ ቀልብሺው ሲሉኝ ፍቃዳቸውን ሞላሁላቸው ። ስለ ገዛኋቸው ልብሶች አይነት ስለ ሌላው ሁሉ ጠየቁኝ ። ሆን ብለው ተዘጋጅተውበትም ይሁን ወይም እንደመጣላቸው ባላውቅም ያልዳሰሱት ነጥብ አልነበረም ። ''ለመሆኑ ከሚስዝ ዳንቨርስ ጋርስ ተስማማች ሁ?'' ብለው ድንገት ለሰነዘሩት ጥያቄ ወዲያው መልስ ከመስጠቱ በፊት አጎንብሼ እየተከተለን የነበረውን ጃስፐርን ማሻሸት ጀመርኩ።'' ''ጠለቅ ብዬ ባላውቃቸውም ትንሽ የሚያስፈሩ ብጤ ናቸው'' አልኩ ።

''ምኗ ያስፈራል ደግሞ! እኔ እምብዛም ልበ ባያፈቅዳትም እርሷ ግን አንድም ቀን ከበሬታ ነፍጋኝ አታውቅም ። አብዝተሽም ፈት አትስጫያት ።''

''እኔ ምን አገባኝና? ቤቱን ቀጥ አድርገው ስለያዙት በስራቸው ጣልቃ...''

''እርሱን እንኳን ተዪው ፡ የቤቱ እመቤት አንቺ እንጂ እርሷ አይደለችም ።'' ሲሉኝ አባባላቸው ትናንት ማታ ማክሲም ከነገረኝ ጋር መመሳሰሉ ገረመኝ ። ''ልብ አድርጊ ፡ ለጊዜው ልትረብሽሽ ስለምትችል ድርጊቷን ሁሉ በጥንቃቄ መከታተል ነው ። ሌላው ደግሞ ቅናት አይኗን አሳውሯታልና ጠንቀቅ ማለቱ ይበጃል ።''

''እንዴ?'' አልኩ በድንጋጤ ''በማን ነው የሚቀኑት? በእኔ?'' ብዬ አይን አይናቸውን ሳያቸው ''ኋላሳ ፡ በእኔ ኖሯል?'' ሲሉ እንደማፌዝ ብለው ገረመመኝ ።

''እኔ ነገሩ በፍፁም አልገባኝም ፡ ከማክሲም ጋር የተለየ ግንኙነት ነበራቸው ማለት ነው?''

''ወቸው ጉድ! ወዴት ሄደሽብኝ? ጉዳዩ ከእርሱ ጋር የተያያዘ መች ሆነና? እንዲያውም እርሱን በጣም የምታከብረው ፡ ቀጥ ብላ የምትታዘዘው ነው የሚመስለኝ ። ሴትዮዋ የእንቺን መምጣት አልፈተደችውም ፡ አልወደደችሽም ነው የምልሽ ።''

''እንዴ ፡ እኔ ምን በደልኳቸውና ነው የሚጠሉኝ? አያውቁኝ አላውቃቸው ።''

''የገባሽ መስሎኝ እኮ እንዲህ የምደርቀው ፡ ማክሲም አልነገረሽም ማለት ነው? አሮጊቷ ለርብቃ የተለየ ፍቅር ስለነበራት...''

t.me/OLDBOOKSPDF

"አሃ!በቃ ይተዉት ፡ አሁን በደንብ ነው የገባኝ" አልኩ ንግግራቸውን አጨርፈው ።

በምክር ያደረግነው ይመስል ሁለታችንም ጀስፐርን መታ መታ እያደረግን ማሻሸቱን ቀጠልን ። ውሻው ደግሞ እንዲህ አይነት ክብካቤ እንግዳ ሆነበት መሰለኝ ከደስታ ብዛት በጀርባው ተንጋሎ ይንከባለል ጀመር ።

ቢያትሪስ "በይ እንግዲህ ፡ እሾውልሽ ወንዶቹም እየመጡ ነው ። መንበር አስወጥተን እዚሁ ጥሳው ላይ አረፍ ብለን ብንጨዋወት ይሻል መሰለኝ ።" በማለት ጀምረው ወዲያውኑ የሀሳባቸውን አቅጣጫ አዙረው "እረግ ፡ አንቺዬ ጂልስ አንዴት ነው የተዘረጠጠው እባክሽ? በተለይማ ከማክሲም ጋር ሲታዩ ሚራሹን ጎተራ ያህል የለም እንዴ?… ደግሞ ይሄ ፍራንኑ የሚሉት ጉድ! ምን ዓይነቱ ሞዛዛው ነው? እረ ወዲያ ወደ ቢሮው ሂዶ ብገላገለኝ ። ሰው እንዲያው አንድ ጊዜ እንኳ ጣእም ያለው ንግግር አያናገርም? …" እንዳሉኝ መንዶቹ ደርሰው ከእሾው ጋር ተቀላቀሉ ።

ሚስተር ክሮውሌይ ሰአቱን አየና "አሁን እንኳን ይፈቀድልኝና አሰናብቱኝ ። መቼም ሚስዝ ደዊንተር ስለ ምሳው ግብዣ ከልብ አመሰግናለሁ።" ሲል እጄን እየጨበጥኩ "እንግዲህ ይልመድብህ እየተመላለስክ ጠይቀን" አልኩት ።

እነ ቢያትሪስም ሂደው ከማክሲም ጋር ብቻችንን እንድንሆን ነበር ፍላጎቱ ። ሮበርት መንበሮችና ምንጣፎች ይዞ መጣ ። ሚስተር ጂልስ ምንጣፉ ላይ በጀርባቸው ተንጋለው ባርኔጣቸውን ወደ አፍንጫቸው ዝቅ አደረጉት ። ጀርባቸው ግና መሬት ከመንካቱ አፋቸውን ከፍተው ሲያንኮራፉብን "እረ እንተ ሰው አፍህን ዝጋው" አሉ ቢያትሪስ "ወቼ ጉዴ! አልተኛሁም እኮ" ብለው እየተገመተመቱ አይናቸውን ከፈት አድርገው እንደገና ዘጉት ጂልስ ።

በባልና ሚስት አኳኋን እየተገረምኩ ሀሳቤ መበታተን ሲጀምር "አሮጊቲን ሂደን መጠየቅ አለብን እኮ" የሚለው የማክሲም ንግግር ከሀሳበ መንጎዬ መለሰኝ ።

"አሁንስ በጣም ጅጅት ነው ያለችው ። ምስኪን! ምግብ መብላት ሁሉ ተስኗት ከአፏ ሲንጠባጠብ እንዴት ነው የምታሳዝነኝ" አሉ ቢያትሪስ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁለቱ ስለ አያታቸው ሲነጋገሩ እኔ ማክሲም ትከሻ ላይ ደገፍ ብዬ በእገዛው እያሻሸሁት አዳምጣቸው ነበር ። ማክሲምም አፉ ከቢያትሪስ ጋር ሲያወራ ፡ እጁ እጄን በዝግታ ሲያሻሽ ፡ ዐሳቡ ግን ከእርሱ ጋር አልነበረም ።

"ጀስፐርን ሆንኩ አያደለም እንዴ ? ልክ እኔ ጀስፐርን እንደማደገው እኩ ነው ማክሲም እያደረገኝ ያለው ። መታ መታ ሲያደርገኝና ሲያሻሽኝ ደስ ደስ እያለኝ ወደ እርሱ እጠጋለሁ ። ጀስፐርን እንደምወደው ነው ማክሲምም የሚወደኝ ?" አልኩ በልቤ ።

ንፋሱ ጋብ ሲል አካባቢው ሁሉ ወጥ ረሜቴ አለ ። ጀልስ ሞንትላኑ ቸው ላይ የሚያንዣብበውን ንብ በባርኔጣቸው አባረው መደነባረብት ተመለሱ ። ጀስፐር ደግሞ ምላሱን ማራና ቀኝ እያወላወለ ከጎኔ ኩርምት ብሎ ተቀመጠ ። ጎንና ጎኑን በምላሱ እያበሰ አልፎ አልፎ ቀና ብሎ ሲያየኝ ትላልቅ አይኖቹ ይተረጉሙ የሚጠይቁ ይመስሉ ነበር ።

ወጭው ፡ የአረንጓዴው መስክ ልምላሜ ፡ የእዕዋቱ ሀብረ ተለምና የአበቦች መዓዛ ዙሪያውን ነደመቀው የወሐይ ብርሃን ጋር ተጫምረው መንፈስን የሚያሸፍቱ ነበሩ ። በሐይለኛ ሞገድ ሲናጥ የቆየውም ባሕር ወጭ ሰፈነበት ። እዚህም እዚያም አበቦችን የሚቀስሙት ንቦች ከአንዱ አበባ ወደሌላው ሲበሩ ይቆዩና ሞንትላኑቸን ላይ ያንዣብባሉ ። ለትእይንቱ ተጨማሪ ውበት ለመስጠት ይሁን ብለው ያደረጉት ይመስል ነበር ።

ቃል ሳልተነፍስ ለሌሎችም ጆሮዬን ሳልሰጥ እንዲሁ እንደተቀመጥኩ ያሀንን ውድና ድንቅ ትዕይንትና ጊዜ ለዘላለም ማጅየት ብችል ምንኛ በታደልኩ ነበር ። ያሀ ሁላችንንም የከበበ ወጭ ፡ በሁላችንም አእምሮ ውስጥ የሰረፀው ፍስሐ ነገ ሊገኝ አለመቻሉ በጣም አሳሰበኝ ። ዛሬ ዝሙን ጠቅልሎ ስፍራውን ለነገ ሲለት በርካታ ውጥንቅጥ ሁኔታዎች ሊከሰቱ ይችላሉ ። የነገዎቹ እኛ የዛሬዎቹን ሆነን አንቀርብ ይሆናል ። መለያየት አለ ፡ ለበሽታ መጨነፍ ፡ ለሀልፊት መንበርከክም ሊኖር ይችላል። ነገ የኛ አይደለም ። እንዳቀድነው ፡ እንዳሰብነው ሊሆንልን የማይችል የራሱን ኩነቶችና ክስተቶች ይዞ ብቅ የሚል የማይዳሰስ የማይጨበጥ የረጅሙ የጊዜ ሰንሰለት አንዱ ምናባዊ ተለበት ነው ።

ማክሲምም እንደኔው ትኖንትን ለታሪክ መዘከርነት አስተምጠ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ነገን ከሀሳቡ አውልቆ ጥሎ እንዲህ እጅ ለእጅ እንደተቆላለፍን ፡ እንዲህ በደስታ እንደተዋጥን ፡ እንዲህ እንዳማረብን እስከወዲያኛው በኖርን አሰኘኝ ። ግና ያሄ መከረኛ ልቤ አይሆሽ እያለ እያስጋለበኝ እንጂ ምኞቱ ውሉ ከንቱ እንደሆነ ሳይገባኝ ተርቶ አይደለም ። ምንም ብመኝ ፡ ምንም ያህል ብንጓ ተፈጥሯዊውን ሕግ ልጥስ ፡ የጊዜን ጉዞ ልገታ እንደማልችል አልጠፋኝም ።

ማክሲም እንኳን ያህን ውስጣዊ ስሜቱን የሚያውቅልኝ አይመስለኝም ። ቢያትሪስም የኔ ሞንቀት ደንታቸው አይደለም ። ከማክሲም ጋር እያወጉ ሳሩን እየነፈሱ እተጋደሙት ባላቸው ላይ ያርከፈክፉታል ። ለእነርሱ ያህ ወቅት ከሌሎች ቀናት የተለየ አይደለም ። ስለ ትናንቱ ማንሳት እንደሚያስፈራኝ እነርሱን የሚያስፈራቸው ፡ ስለ ነገው ማሰብ እንደሚከብደኝ የሚከብዳቸው አይደሉም ።

"እረ ሳያመሽብን እንሂድ" የሚለው የቢያትሪስ ድምፅ ርቂ ከነንድኩበት መለሰኝ ። ቢያትሪስንና ባለቤታቸውን ለመሸኘት እንቅስ ቃሴ እንደጀመርን ማክሲም ምስራታዊውን ሕንፃ እንድናስጎበኛቸው ጠያቂቸው ተያይዘን ወደዚያው አመራን ። እንግዶቹ በህንፃው ዕድሳትና በክፍሎቹ አደረጃጀት ያደረባቸውን አድናቆት ገልፀው ሲወጡ ቢያትሪስ ማበጠሪያዬን አንስተው ካስፈቀዱኝ በኋላ ፀጉራቸውን ለማበጠር ከመስታወቱ ፊት ለፊት ቆሙ ። ማበጠሪያውን እያደነቁ ለሠርጌ የተሰጠኝ ገፀ በረከት እንደሆነ ጠየቁኝ ። የማክሲም ስጦታ መሆኑን ስነግራቸው "በጣም ቆንጆ ስጦታ ነው ። እኛም እኮ ስጦታ ልንሰጥሽ ይገባል ። እስቲ ንገሪኝ ምን ብንሰጥሽ ይሻላል ?" አሉኝ ።

"እኔ እንጃ ፡ እረ ግድ የለም አትጨነቁ"

"ምን ማለትሽ ነው ? ምንም እንኳን ለሠርጋችሁ ባትጋብዙንም ስጦታሽን ግን በምንም አይነት አላስቀርብሽም ።"

"ወይኔ ፡ መቼም በዚህ እንዳልተቀየማችሁ ተስፋ አደርጋለሁ ። ማክሲም ግርግሩን ስላልፈለገ ነው ሠርጋችን ከሐገር ውጭ እንዲሆን የወሰነው ።"

"እረ አልተቀየምንም ፡ እንዲያውም ጥሩ አድርጋችኋል ። ለዚያውም ቢሆን ያን ያህል ..." ብለው ጅምራቸውን አንጠልጥለው ተውት ። ቦርሳቸው ወደቀ ። "ኤዜ ፡ ምን አይነት ጣጣ ነው? ማንጠልጠያውን

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰበርኩት መሰለኝ ። አይ ፡ ምንም አልሠነም...ምን ነበር የጀመርኩት ልጂ? ረሳሁት እኮ ፡ አዎን ስለ ሠርግ ስጠታ ። የሚድ አንድ ነገር መስጠት አለብን ። ጌጣጌጥ ቢሠንልሽ ምን ይመስልሻል ?" ሲለ ጠየቁኝ ። መልስ አልሰጠኋቸውም ። የሠነ ያልሠነውን ሁለ እንደመጣላቸው እየዘባረቁ ሲመጡ "እንግዲህ ደስ ባላችሁ ጊዜ ብቅ ብላችሁ ጠይቁን ። እኔ ሰዎች በራሳቸው አነሳሽነት ሲጠይቁኝ እንጂ መጋበዝ አልወድም ።" ሲሉኝ "በጣም አመሰግናለሁ" አልኳቸው ።

ሚሲዝ ቢያትሪስ እጂን ይዘው ወደ እርሳቸው ነስጠጉኝ በኋላ ጉንጩን ቆንጠጥ አድርገው "ፀይ እንግዲህ ይሀና ሁኚ ። በረባ ባልረባው ጥያቄ ስላዳረቅኩሽ ይቅርታ አድርጊልኝ ። እኔ ዘዴ የሚሉት ነገር አላውቅበት ፡ እንዳገኘሁ ነው የምናገረው ፡ ስለዚህ ጠባዬ ማነሰም በደንብ ሊነግርሽ ይችላል ። ቀደም ብዬ እንደነገርኩሽ ደግሞ እንደገመት ኩሽ አይደለም ያገኘሁሽ ።" አሉና ትክ ብለው እያስተዋሉኝ ሲንራቹ ውን አቀጣጠሉ ።

የምለውን ለመስማት የቸኮሉ አይነት አፍ አፈኝ ቢጠብቱም ፡ ሁልም አልተነፈስኩላቸው ። በመጨረሻም "አንቺ እኮ ከበብታ በጣም የተለየሽ ነሽ" የሚለውን መርዛቸውን ነስንስው ብኝ ነው የሄዱት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ — ዘጠኝ

የእንግዶቻችን መኪና ከአይታችን እንደተሰወረ ማክሲም እጇን ያዝ አድርጎ "ተመስገን ፡ ግልግል ነው" ብሎ በረጅሙ ተነፈሰና "በይ እንግዲህ አንድ ነገር ደርቢና ትንሽ እንንሸራሸር ። እዚህ መጎለቱ ድብት ነው ያደረገኝ" አለኝ ። በእርግጥም የመልኩ መለዋወጥና ድክምክም ማለቱ በደንብ ይታወቅበታል ። እህቱንና ባለቤታቸውን ማስተናገዱ ለምን ይሆን ያህል እንደከበደው ባይገባኝም ምክንያቱን ከመጠየቅ ታቅቤ "እሺ አንዴ ሮጥ ብዬ ኮቴን ለብሼ ልምጣ" ስለው ፡—

"እዚያ ዕቃ ቤቱ ውስጥ ብዙ የዝናብ ልብሶች አሉልሽ አንዱን ብድግ አድርገሽ ኑይ ።" አለኝና ሀሳቤንም ሆነ እንቅስቃሴዬን ሳይጠብቅ "ሴቶች አንዴ መኝታ ክፍላቸው ከገቡ ቢጎተቱም አይወጡ ። እባክህን ሮበርት ለሚስዝ ደዊንተር አንድ የዝናብ ልብስ ታመጣላት ?" በማለት ሠራተኛውን አዘዘው ። ትዕግስት ከማጣቱ መቁነጥነጡ ጭራሽ እንቆቅልሽ ሆነብኝ ። ከመቼው እንደደረሰ ላላየው ወዲያ ማዶ ቁሞ ጃስፐርን እየጠራው "ና አንተ ደደብ የሆንክ ጉድ ። ዛሬ ይህን የስብ ከረጢትህን ነድዮ ሽክምህን ካላራገፍኩልህ ..." ሲል ሰማሁት ። ጃስፐር በደስታ እየፈነደቀ በጌታው ዙሪያ እየተሽከረከረ ሲጮህ "ዝም በል ፡ የምን ማላዘን ነው?!" በማለት አምባረቀበት ። ወዲያው ፊቱን ወደ ቤቱ መልሶ "ይሄ ሮበርት ደግሞ ጭብቶ ተቀበረ" አለ በመበሳጨት ።

ሮበርት እየሮጠ ያመጣልኝን የዝናብ ልብስ እየተጣደፍኩ ለበስኩት ። ኮቴ እንደበዛብኝ ባውቅም ፡ መቀየሩ የማይመከር ነውና እየተንከራፈፍኩ ማክሲምን ከመከተል ሌላ ምርጫ አልነበረኝም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ከቢያትሪስ ጋር ተግባባችሁ ? ትንሽ ግን ሳታደናግርሽ አትቀርም። እንደ እውነቱ ከሆነ በዚህች ምድር ላይ አሉ ከሚባሉ ድንቅ ሰዎች አንዷ ብትሆንም አንዳንዴ የምትናገረውን አታውቅም ።" አለ ማክሲም ጉዟችንን እንደጀመርን

ግንባቤዬ እስካስጨበጠኝ ድረስ የቢያትሪስ ጥፋት ሊሰተዋለኝ ባይችልም ከመጠየቅ ዝምታን መረጥኩ ። "እንቺስ እንዴት አገኘሻት ?" በማለት አያይዞ ሲጠይቀኝ ግን "በጣም ነው የወደድኳቸው ፡ በደንብ ነው ያጫወቱኝ" አልኩት ።

"እደጅ ወጥታችሁ ምን ምን ነበር የምትልሽ ?"

"እኔ እንጃ ፡ ምን አሉኝ ? እኔ ነበርኩ አብዛኛውን ስለፈልኩ የቆየሁት ። ስለሚስዝ ቫን ሁፐር ፡ እኔና እንተ እንዴት እንደተገናኘንና የመሳሰሉትን ነገሮች እያነሳሁ ሳጫውታቸው ነበር ። እርሳቸው ደግሞ እንደጠበቁኝ እንዳልሆንኩባቸው ነው የነገሩኝ"

"እንዴት ነበር የጠበቀችሽ ደግሞ ?"

"አለ አይደል ፡ ይበልጥ ቀልጣፋ ፡ ይበልጥ ሥልጡን ሴት ትሆናለች ብለው ይሆናላ ። ከሰው ጋር በጣም የመግባባት ችሎታ ይኖርሻል ብዬ ነምቼ ነበርም ብለውኛል።"

ማክሲም ለአፍታ ፀጥ ካለ በኋላ ጀስፐርን ለማጫወት እያጎነበሰ "እንዳንዴ ቢያትሪስ ትጀጃላለች ልበል ?" አለ ።

ምንም ሳንነጋገር መስኩን አቋርጠን ፡ ቁጥቋጦዎችን አልፈን በዛፎቹ መሐል ገባን ። ከማክሲም ጎን ሽጉጥ ብዬ ከንዴን በእጅቼ ጥርቅም አድርጌ ያዝኩና "ማክሲምዬ ፀጉሬን ትወደዋለህ?" ስል ጠየቅኩት ።

ጥያቄዬ ዱብ ዕዳ ሆነበት መሰለኝ በግርምታ አትኩሮ እየተመለከተኝ "አዎን እወደዋለሁ ። ግን ምን ዓይነት ጥያቄ ነው የምትጠይቂኝ ? ፀጉርሽ ደግሞ ምን ሆነ ?" አለኝ ።

"አይ ፡ ዝም ብዬ ነው ለማወቅ ስለፈለግኩ" ስለው

"በጣም የምትገርሚ ነሽ" በማለት ጭንቅላቱን ነቀነቀ

ገላጣው በፍራ ስንደርስ ጸሰፐር ወደ ግራ የሚታጠፈውን የእግር መንገድ ትቶ ወደ ቀኙ ታጠፈ ። ይሄኔ ማክሲም "ና ወዲህ ፡ በዚያ አይደለም መንገዳችን" አለው ። ውሻው የማክሲምን ድምፅ ሲሰማ ዞር ብሎ አየን ። እነበረበት ቆሞ ጭራውን ከመወዝወዝ ሌላ የጌታ ውን

t.me/OLDBOOKSPDF

ትዕዛዝ ለማክበር የተዘጋጀ አያመስልም ነበር ። ትዕይንቱ ቢገርመኝ "ለምንድነው በዚያ አቅጣጫ ለመሄድ የፈለገው ?" ስል ጠየቅኩት ።

"እዚያ አካባቢ የምናቅማት አንዲት ጀልባ ስለነበረችን አዘውትረን እንመጣ ነበር ። ምናልባት ያ ሁኔታ ትዝ ብሎት ይሆናል" አለና በአጭሩ መልሶልኝ ጃስፐር እንዲመለስ በድጋሚ ጠራው ።

ትኩነው መሄዳችንን አይቶ ጃስፐርም ተከተለን ። የደስታ ስሜት ይዳስሰኝ ጀመር ። ማክሲምን ቀና ብዬ ሳየው ተደም ሲል አጥልቶበት የነበረ የብስጭትና የንዴት ስሜት እየለቀቀው ፊቱ ፈካ ማለቱንና እርሱንቱ በደስታ ስሜት መታጀቡ ደስታዬን ይበልጥ አጎላው ።"በደንብ እዩው ይህን አካባቢ ።" አለኝ ማክሲም ድንገት እንትስቃሴውን አቋረጠ።

ቱጥጂጠውን ስንጥቆ ፡ ጅረቱን ተከትሎ የሚጥመለመለውን ቀጭን መንገድ ያስያዝኩት አይኔ ከአንድ ሽልቆ ላይ አረፈ ። ልዩ ልዩ ሀብረ ቀለማት የተላበሱት አበቦች ክፉኛ ልብን ይሰርቃሉ ፡ መዓዛቸው ስሜትን ያሽፍቃል።እላያቸው ላይ ይርከፈከፍ የነበረው ዝናብ ጭንቅላታቸውን ቢያስንበሰውም ውበታቸውንና ግርማ ሞገሳቸውን አልገፈፈውም ። የአበቦቹ ውበት፡ አየሩ ላይ የተናኘው መዓዛቸው ከዝናቡ ድምፅና ከጅረቱ ሽውሽውታ ጋር ተቀናጅተው የፈጠሩት ሀብር ለተፈጥሮ የውበት ምንጭነት በተምሳሌትነት የሚቆም ነው ። ማክሲም ይህን የመሰለ ወጥ ማያናረሰ የከበደው ይመስል "ይህንን ነው እንግዲህ የፍስሐ ሽለቆ የምንለው" በማለት በሽክሽክታ ነገረኝ ። የኔም ፍራቻ ከእርሱ ብሶ እንቱቱን እየነቀነትኩ አድናቆቴን ቀጠልኩ ። አንዲት አበባ ከመሬት አንስቶ ሰጠኝ ። ከመጠውለጓም በላይ የሰው እግር አጎሳቁሏታል። በእጇ ጠራረግኳት ። መዓዛዋ በታደስብኝ ሕይወት የዘራች መሰለኝ ። አገላብፌ አየኋት ።

ይህ ውበት ፡ ይህ እይታ ያላደረብኝን ልዩ አድናቆት አጣጥሜ ሳላበቃ አእዋፍ የትብብሎሽ ዝማሬያቸውን ጀመሩ ። ደስታው ቢያይል ብኝ ናላዬን እንዳልስት ሰጋሁ ። የጣራው ስለው የቀኙ ፡ የላዩ ስለው የታቹ ሁሉም አይን አዋጅ ሆነብኝ ። ውበታቸውን ተላብሼ ፡ መዓዛውን ተጋርቼ ከአበቦቹ ጋር እየተሻሸሁ መንዙ አንሶኝ በአእዋፍ ዋውም ዜማ መታጀቤ ሞራሹን አሰከረኝ ። እውነትም የፍስሐ ሽለቆ !

t.me/OLDBOOKSPDF

የማንደርሌይ ውብ ሕይወት የሚቀጸበት ምንጭ— አሰኘኝ ።

ከባሕሩ ዳርቻ ስንደርስ ሁኔታዬን በአንክሮ ሲከታተል የቆየው ማክሲም "ግሩም አየደል ? መቼም እንደወደድሽው ተስፋ አደርጋለሁ ።" ሲለኝ "ግሩም ብቻ ? ድንቅ ፡ እውብ እንጂ— ዝንተዓለም ኑሩብኝ የሚያሰኝ ስፍራ" ማለቱን እንጂ ያኔ በዚያ ስካር ታላቱ ፡ አገላለፁ እንዴት እንደመጣልኝ ዛሬም አላውቀው ።

እዚያው አረፍ እንዳልን አንዴ የባሕሩን ሞገድ እያደነቅን ፡ አንዴም ከጀስፐር ጋር እየተጫወትን ጊዜያችንን ገፋን ። የጀስፐር ድምፅ ጥፍት ሲልብን ቡራያችንን ታኘን ። ደብዛው ጠፋብን ፡ ብንፈሙ ፡ ብንጣራ ፡ ብቅም አልል አለ ። "ባሕሩ ውስጥ ሰጥሞ እንደሆነ" ብለው "ቢሆን እናየው ነበር" በማለት ማክሲም ሀሳቤን አልተቀበለውም ። "ወደ ፍስሐ ሸለቆ ተመልሶስ እንደሆነ ?" የሚለው መላ ምቴንም አፍርሶ ፌክ ብሎ መጣራቱን ቀጠለ ።

ወደ ሸለቆው ተመለስን ። ድምፅ ሰማሁና "ፈጅሽቱን ሰማኸው፡ በዚህ በኩል አቆራርጦ ሄዷል ማለት ነው ?" ብዬ ድምፁን ወደሰማሁበት አቅጣጫ መጣራት ስጀምር "ተይው እባክሽ የራስ ጉዳይ ። አውን ለእርሱ ብለን በዚህ በኩል ልንሄድለት ነው" አለኝ ማክሲም ድምፁን ረገጥ አድርጎ።

"ውይ ፡ ተው እንጂ ማክሲምዬ ። ምስኪን ፡ ወድቶ ተጎድቶም ሊሆን ይችላል። ሄጄ ልፈልገው እንጂ ። ትሰማለህ? አውንም እየፌሽ ነው እኮ" ስለው "አንቺ ደግሞ ዝም ብለሽ ነው ። ምንም አይሆንም አልኩሽ። መንገዱን ስለሚያውቀው ተመልሶ ይመጣል ።" አለ ማክሲም እንደመሳሳጨት ብሎ ።

ምንም ያልሰማው መስዬ ቋጥኙን እየቧጠጥኩ ወደ ጀስፐር አመራሁ ። ወድቂ እየተንሳፈፉ እንደምንም ጥርሴን ነክሼ አቀበቱን ተያያዝኩት። ማክሲም በጀስፐር ላይ ይሆን ያሀል መጨከኑ ከፉውኑ ሊገባኝ አልቻለም ። ጥቂት ከፍ እንዳልኩ ቀደም ሲል ያየሁትን የሚመስል ባህረ—ሰላጤ አየሁ ። ውሀውን ለመከላከል የተገነባው ግንብም ይታየኛል ። በቁጥቋጦዎቹ መሐል ደግሞ አንድ ጎጆ ብጤ ነበረ ።

ጀስፐርን አየሁት ። ከባሀሩ ዳርቻ አጎንብሶ አሸዋውን በሚጭረው ሰው ዙሪያ እየተሽከረከረ ይጮሃል ። የተጫማው ቦትና የደፋው ቆብ እሳ

t.me/OLDBOOKSPDF

አጥማጅ የሚያስመስለው ሰውዬ ግን የጃስፐርን ጨኽት ቁብም አላለው። "ጃስፐር ፡ ና ወዲህ ጃስፐር" እያልኩ ብጣራም ጃስፐር ቀና ብሎ አይቶኝ ጭራውን እየወዘወዘ ጨኽቱን ቀጠለ ።

ቀና ብዬ ግራ ቀኙን ብቃኝ ማነሰም አልታይሽ ሲለኝ ወደ ባሕሩ አዘገምኩ ። ሰውዬው ኮቴዬን ተከትሎ አንገቱን ሲመልስ ጨልጨል አያኖቹና እርጥብ ቀይ አፉ አንዳች ስሚት አጫሩብኝ ። ፈገግ እንደማለት ሲቃጣ ከጥርስ ይልቅ ድዱን ነበር ያሳየኝ ። ነካ የሚያደርገው ዓይነት ነው።

"እንደምን ዋሉ ? በጣም ያስጠላል አይደል ?" አለኝ ሰውዬው

"ደህና ዋሉ? አምን ዛሬ አየሩ ጥሩ አይመስለኝም" አልኩት

አትኩሮቱን ከኔ ላይ ሳይነቅል ይበልጥ እየፈገገልኝ "ዛጎል አገኝ ብዬ ነው የምለፋው ። ከሰዓት በፊት ነው መቆፈር የጀመርኩት ። አንድም አላገኘሁ" አለ ።

"ኧረ ? ምንም ሳያገኙ ብዙ ደክመኣ"

"አምን ፡ አምን — ምንም ዛጎል የለም"

ሰውዬውን ትቼ አይኔን ወደ ጃስፐር ወረወርኩትና " ኧረ አንተ ጃስፐር ና እንሂድ ፡ እየመሸ እኮ ነው" አልኩት ። ጃስፐር ግን በቁጣ እየተቅበጠበጠ እላይ ታች ሲሮጥና ሲፈሁ ሳየው በጅ የሚለኝ አልመሰለኝም ። አስሬ እንዳልወስደው ደግሞ ማሰሪያ አልያዝኩ ። ወደ ሰውዬው ዞር ስል አንገብሶ ከንቱ ድካሙን ተያይዞታል ። "ገመድ ይኖርዎት ይሆን?" ብዬ ስጠይቀው

ጭንቅላቱን እየነቀነቀ "ምንም ዛጎል የለም ፡ ቀኑን ሙሉ ስቆፍር ነው የዋልኩት እያልኩዎት ?" ብሎኝ ሰማያዊ አይኖቹን ያሻሽ ገባ ።

"ውሻው አልሄድ ስላለኝ ማሰሪያ እኮ ነው የጠየቅሁዎት ።"

"እሀ ?" ብሎ ያን ጅላጅል ፈገግታውን እንደገና ቢጋብዘኝ "ግድ የለም ይተውት" አልኩት ። ብድግ ብሎ ደረቱን በጣቱ ገፋ አደረገና "ይህን ውሻ እኮ አውቀዋለሁ ። የዚያ ግቢ ውሻ ነው" አለኝና አፈጠጠብኝ ።

"አምን ፡ ይገርው ለመሄድ ፈልጌ ነው ።"

"ለምን ? የእርስዎ ውሻ አይደለም"

"የሚስተር ደዊንተር ነው ። ወደ ቤት ልወስደው ነው" ስለው

t.me/OLDBOOKSPDF

"እሀ ?" አለኝና ፀጥ ።

ጀስፐርን ደጋግሜ ጠራሁት ። እኔን ችላ ብሎ ንፋስ ከሚያርገበግ በው ሳባ ጋር ያሯሯጣል ። ጎጆው ውስጥ ማሰሪያ ለመፈለግ መደዚያው አመራሁ ። የቤቱ ዙሪያ በዳዋ ቢሞጥም በእንድ መቶት እንከብከቢ ያልተለየው መናፈሻ እንደ፣በረ ከአሻራው መረዳት ይቻላል ። የተዘጋውን በር ከፍቼ ገባሁ ። ቁሻሻ ነው ፡ አቧራ ነው ። የጀልባ ማሳረፊያ አስከሠነ ድረስ ገመድ ብጠ አሳጣም የሚለው ተስፋዬ ሚሸሸ ። የአደኑን ብሌን ተጠራጠርኩት ። በተሚላ ዕቃ ያጌጠ ክፍል ነው የገጠመኝ ። የጠረጴዛው፡ የወንበሮቹ ፡ የመፃሕፍት መደርደሪያው ፡ የአልጋው ፡ የዕቃ መደርደሪያ ከነ ኩባያዎቹና ሳህኖቹ ምን ተረፈ ?

የዚያ እባሀሩ ዳርቻ ያየሁት ምስኪን መኖሪያ ይሠኝ? የሚል ጥርጣሬ አደረብኝ ። የአቧራው እንዲያ መቆለል ፡ የቤቱ ወና ጠና ማለት ፡ የቁሳቁሶቹ በሸረራት ድር መሸፈን ግምቴን ገሰሰው ። ጎርሀት ጉርሀት አለኝ ። ዙሪያዬን የከበበኝ ጭለማ ፡ ርጥበቱና ቅዝዛዜው ተጫጫነኝ ። ካፊያው ጣሪያው ላይ ፡ኢያርፍ የሚፈጥረው ድምፅ ዘገነነኝ ።

ያም ሆኖ እራት ለፊቱ ያየሁትን በር እግራ እየተምታታ ሄጀ ከፈትኩት ። ልቤ ምቱን ጨመረ ። ትኩሳቱ አየለ ። አንድ ልዩ ግዙፍ ሐይል ጨምድዶ የሚያስቀረኝ እየመሰለኝ እየተሸማቀቅሁ ማራ ሁኑን ገልመጥ አደረግሁት ። እዚህም እዚያም በጨረፍታ የታዘንኋቸው ዕቃዎች ለጀልባዎች ማሳረፊያ የተዘጋጀው ክፍል መሆኑን ነገሩኝ ። ገመድ አገኘሁ ። በእቅራቢያዬ ባገኘሁት ቢላ የምፈልገውን ያህል ቆርጬ ከልዬ ስወጣ ከራሴ ጭምር የምሸሽ እመስል ነበር ።

ሰውዬው ቁፋሮውን አቋርጦ ፡ ጀስፐርም ጨኸቱን አቁሞ ፡ ሰላም ፈጥረው ጎን ለጎን ቆመው ላያቸው ገረመኝ ። ጀስፐርን እያባበልኩ ልያዘው ሳጎንብስ እንደ በፊቱ አልሸሸኝም ። "እጎጆው ውስጥ አነ ገመድ አገኘሁ" ብለው ሰውዬው መልስም አልሰጠኝ ። ገመዱን ጀስፐር አንገት ላይ አጥልቼ እንዳበቃሁ "ያበሉ እንግዲህ ደህና ይሁኑ" ሰለው ግን አንገቱን ዘንበል አድርጎ በእኒያ ጠባብ ጅላጅል አይኖቹ እየመረመረኝ ። "መደዚያ አልፈው ሲሄዱ እየሁምት እኮ" አለኝ ።

"እምን በመሃዲ ሚስተር ደዊንተርም ቅር አይለንም" አልኩት ።
"ግን እኮ አሁን እርፏ መደዚያ አትሄድም"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እምን አትሄድም"

"ባህሩ ውስጥ ግብት ብላለች አይደል ? ከእንግዲህ ተመልሳ አትመጣም"

"እምን አትመጣም" ስለው ድንግጥ እንደማለት አለና "እኔ ግን ምንም አልተናገርኩም አይደል ? ተናግሬያለው እንዴ ?" ብሎኝ ተቁለጨለጨ ።

"በፍፁም ምንም አላሉም ።" ስለው እያልጎመጎመ ወደ ቁሩፎው አንገበሰ ። ጀስፐርን እየጎተትኩ ጥቂት ፈቅ እንዳልኩ ማክሲም እጀቼን ኪሶቼ ውስጥ ከቶ ሽጥኝ ላይ ቆሞ ሲጠብቀኝ አገኘሁት ።

"ያትርታ ፡ ያሄ ጀስፐር አልመጣ ብሎኝ ገመድ ስፈልግ እኮ ነው" አልኩት አይን አይኑን እያየሁት ። ምንም ሳይናገር ፊቱን አዙሮ መንገዱን ተጠሰ ።

"በቃዮን በኩል አንመለስም እንዴ ?" ስለው

"የያዝነውም መንገድ ይመልስናል" አለኝ ።

ጎጇውን ወደጎን ትተን ወደ ሣኪነው የሚያመራውን መንገድ እንደያዝን "ያትርታ ፡ ጀስፐር አስቸግሮኝ ነው የዘገየሁት ። ሰውዬው ላይ እየፎሸሽ እንሂድ ብለው በየት ሰምቶኝ ።" በማለት ያትርታዬን በድጋሚ አትረበ. "ሰውዬው ግን ማን ነው ?" ስል ጠየቅኩት ።

"ቢን የሚባል የዋሀ ምስኪን ነው ። ሽማግሌ አባቱ የጥንት ጠባቂ ነበሩ ። አዚው እማሳው አጠገብ ነው የሚኖሩት" ካለ በኋላ "ለመሆኑ ይህን ገመድ ከየት አገኘሽው ?" ሲል ጠየቀኝ ።

"ጎጇው ውስጥ"

"በሩ ክፍት ነበር እንዴ ?"

"ገርበብ ብሎ ስለነበር ገፋ ሳደርገው ተከፈተ ። የጀልባ ፅዮምችና እንዴት ትንሽ ጀልባ ኖሊችበት የውስጠኛው ክፍል ነው ገመዱን ያገኘሁት"

"እሠ" አለና ጥቂት ዐጥ ካለ በኋላ "ተተርትሮ የነበረውን በር ማን እንደከፈተው ነው ያልገባኝ" ሲለኝ በማላውቀው ጉዳይ ከመቀባጠር ዝምታን መረጥኩ ። ወዲያው "በሩ ክፍት መሆኑን ቢን ነው እንዴ የነገረሽ ?" ሲል ጠየቀኝ ።

"እረ እርሱ ምን ያነግረኛል? እንኳንስ ሊነግረኝ የምጠይቀው ሁሉ

t.me/OLDBOOKSPDF

አልገባ እያለው ሲያነጋገር ነበር”

“ሲያስመስል ነው እባክሽ ። ያለው ቀን ምንም ሳያምታታ ቀጥ ብሎ ነው የሚናገረው ። አንቺ እንዳታውቂበት ብሎ ነው እንጂ ይሄኔ ጎጆውን መዝናኛው አድርጎት ይሆናል ።”

“እያ አይመስለኝም ማክሲም ። ቤቱ እኮ ሰው ድርሽ ብሎበት የሚያውቅ አይመስልም ። በአቧራና በእርጥበት መዓዛና፡ አይበላሹም ትላለህ? አይጥም ሳይኖር አይቀርም ። የሰፋምቹ ጨርቆች ተቦጫጭቀው የለም እንዴ?”

ምክንያቱ ባይገባኝም ማክሲም ጥያቄዬን ወደ ጎን ገሸሽ አድርጎ እርምጃውን አፋጠነው ። ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ነው ። የመንገዱ ወጣ ገባነትና የዝናቡ ማየል ሁለመናዬን አዛለው ። እግሬን እንትት ጀመር ። በዚህ ላይ ከንቱ ሲዳክር ጉልበቱን የጨረሰው ጃስፐር መንቀሳቀስ እስኪሳነው አለከለከ ።

“እረ አንተ ጃስፐር ለእግዚአብሔር ብለህ ተንቀሳቀስ ? ምነው ብትጎትችው ? ወይም አንድ ነገር ብታደርጊው? ያች ቢያትሪስን እንዲሁ ነው የተቃወምኳት ። እውነትም ይህ ውሻ ጭራሽ ሥጋውን መሸከም አቅቶት የለም እንዴ ?” አለ ማክሲም አይኑን በእኔና በጃስፐር ላይ እያፈራረቀ ።

“ያንተ እኮ ነው ጥፋቱ ፡ እንዲህ እየተራመድክ እንዴት እንድረስ ብህ?” ስለው ።

“እንደዚያ ተሽቀዳድመሽ እዚያ ቋጥኝ ላይ ከመውጣት ይልቅ ያልኩሽን ሰምተሽ ቢሆን ኖሮ ይህን ጊዜ ቢታችን ገብተን ነበር ። ጃስፐር እንደሆን መንገዱን አልሳተውም ። ለምን ልትከተዪው እንደፈለግሽ ነው ግልፅ አልሆንልህ ያለኝ” አለኝ ።

“እንዴ ፡ ተሰብሮ ወድቆ ቢሆንስ? በዚያ ላይ ማዕበሉ ጠርጎ እንዳይወስደው ሰግቼ ነዋ”

“ማዕበሉ ያን ያህል የሚያሰጋ ቢሆን እኔ ዝም ብዬ የማይ ይመስልሻል! እንዳትሄጂ እያልኩ ስወተውት ሀሳቤን ጥሰሽ ሄደሽ አውን ደግሞ ይከመኝ ብለሽ ታጉረመርሚያለሽ ።”

“ማጉረምረሜ እኮ አይደለም ። ብረት ካልሆነ በስተቀር ሥጋ ለበስ ፍጡር እንዲህ እየተራመደ ላይደክመው ኖሯል እንዴ? እኔ ጃስፐርን

t.me/OLDBOOKSPDF

ለመከተል ስሄድ ተከትለሽኝ ትመጣለህ አልኩኝ እንጂ ብቻዬን ለቀሽኝ የምትቀር አልመሰለኝም ነበር ።"

"ከዚህ ደደብ ውሻ ጋር ስንመላለስ ለምን ብዬ እራሴን ላድክም አባክሽ?"

"ጅስፐርን መከተሉ ካሁኑ ድካም አደብስም ነበር ። እንዲያው ዝም ብለህ ሉላ ምክንያት ብታመጣ ነው እንዲህ ማለትህ"

"የምን ምክንያት?"

"እኔ ምን አውቄ?" አልኩት በመሰላቸት መልክ "ምን አለ ወሬ ብንቀይር?"

"የማደርገውን ። እንዴ እንደጀመርሽው ሳትጨርሺው አንላቀቅ ትም ። ምክንያት ፍለጋ የሚያስጨንቀኝ ምንድነው? ምንስ የሚሉት ምክንያት?"

"እኔን ተከትለህ ያልመጣህበት ምክንያት ይሆናላ"

"መልካም ፡ ግን አንቺን ተከትዬ ወደ ባሕሩ ዳርቻ መሄድ ያልፈለግኩት ለምን ይመስልሻል?"

"እባክህን ማክሰም? ምነው ብትተወኝ? እኔ ውስጣዊ ምክንያትህን በምን ማወቅ እችልና? ጠንቋይ አልተልብ ። ላለመሄድ መፈለግህን ከገፅታህ ማንበብ ግን ያን ያህል የሚያዳግት አይመስለኝም ።"

"ከገፅታዬ ደግሞ ምንን ነው ያነበብሽው?"

"ስንት ጊዜ ልንገርህ? ጨዋታ እንቀይር ፡ በቃን እባክህ ፡ ምን ያህል እንዳንገሽገሽኝ ባወቅክልኝ ።"

"ይሽው እነ ነው ሴቶች ስትባሉ ወሳያችሁ ። ክርክር ትጀምሩና ማሳፈያው ሲያጥራችሁ እንዲህ ነው የምትሉት ። እሺ ወደዚያኛው የባህር ዳር ለመሄድ ስላልፈለግክ ነው ብልሽሳ? ትረኪያለሽ? እዚያ ርኩስ ጎጆ አጠገብ ድርሽ ማለትም አልፈልግም ። አንቺም በኔ የደረሰ ደርሶብሽ ቢሆን ኖሮ ከአጠገቡም ባልሆርሽ ። ግና ያልተነካ ግልግል ያውቅል አይደል የሚባለው? እንኳን በአውንሽ በሕልምሽም ስፍራውን ባልረገጥ ሽው ። ሞራሽ ስሙን ሲያነሱብሽ ባንገፈገፈሽ ነበር ። እንግዲህ የሚዋጥልሽ ከሆነ ሀቁ ይኸው ነው" አለኝ ።

ፊቱ ገርጥቶ አይኖቹ እንዲያ ቡዝዝ ብለው ሳያቸው እጅጉን በእጅጉ ጥርቅም አድርጌ ይዤ "ምነው ማክሰምዬ ብትተወው?" ስለው

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምኑን?" በማለት ጠየቀኝ

"መልክህ እንዲህ ልውጥውጥ ሲል በጣም ነው የሚጨንቀኝ ። እስካውን ያደረግነውን ምልልስ ሁሉ ረስተን ሌላ ደስ ደስ የሚል ነገር እንጨዋወት ። እባክህን የኔ ፍቅር ፡ ለኔ ስትል እርሳው ።"

"ምን ሲያንተገትገኝ እዚህ ማንደርሉይ እንዳመጣሁሽ በፍፁም ሊገባኝ አልቻለም ። እዚያው ጣልያን ውስጥ በደስታ መኖር ስንችል ምን አመጣን?" ብሎ ጥሎኝ እየተፈናጠረ ሄደ ። እርምጃውን ከበፊቱ ስላፋጠነው ልቤ እስኪወልቅ እሮጥ ጀመር ። በዚያ ላይ ደግሞ ያንን ጀስፕር መጎተቱ ይበልጥ አዝለፈለፈኝ ። እንባ ተናነቀኝ ።

መድረስ አይቀርምና ደረስን ። ማክሲም ምንም ሳይናገር ወደ አዳራሹ ገብቶ በቀጥታ ወደ ቤተ መጻህፍቱ አመራ ። አዳራሹ በር ላይ ለነበሩት ሽማግሌው ፍሪዝ "ሻይ በአስቸኳይ እንዲቀርብልን" ብሎ ቸው የቤተመጻህፍቱን በር ዘጋው ።

እንባዬ ሲፈስ ፍሪዝ እንዳያዩብኝ ክፉኛ ታገልኩ ። "እረ አመቤቲቱ ምን እንደነካቸው እንጃ ያዘንቡታል ። ከጌቶች ጋር ሳይላሉ አይቀርም።" ብለው ለሠራተኞች በሙሉ ቢናገሩብኝስ ፡ ብዬ ባልፈራ አንብቼው ትንሽ ተንፈስ ብል ምንኛ ደስ ባለኝ ።

የዝናብ ልብሴን ሲቀበሉኝ ከመሬት ላይ እንድ ነገር አንስተው "መሐረብዎን ጥለዋል" ብለው አቀበሉኝ ። አመስግኜ ኪሴ ውስጥ አኖርኩት ። ፎቅ ልውጣ ወይስ ማክሲምን ልግባ? እያልኩ ከራሴ ጋር ሙግት ጀመርኩ ። መወሰን ተስኖኝ ጥፍሬን በጥርሴ እየከረከምኩ ፈዘዝ ቀረሁ ።

"ቤተመጻሕፍቱ ውስጥ እሳቱ ሻ ብሎ ሲነድ እንዲህ መሰልዎት እሜቴ" አሉኝ ፍሪዝ ተከዝ ቢያዩኝ እንደመደናገጥ ብለው ።

"እረ? እመሰግናለሁ" አልኩና ወደዚያው አዘገምኩ ። በሩን ከፍቼ ገባሁ ። ማክሲም የተዘጋጁለትን ጋዜጦች ቸል ብሎ በሀሳብ ተውጧል ። እግሩ ስር የተኛው ጀስፕርም የጌታው ትካዜ የገባው ይመስል አያኖቹ ቡዝዝ ብለው ሳያቸው አሳዘነኝ ። በቀጥታ ወደ ማክሲም ሄድኩ ። ከጎኑ ተንበርክኬ "እባክህን የኔ ጌታ ሁለተኛ አትቆጣኝ" ስል በለሆሳስ ተማፀንኩት ።

ፊቴን እያሻሸ "እኔ አንቺን አልተቆጣሁም" አለኝ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንደ ፡ ብትቆጣም ይገባሃል ። ደስታህን እንዳደፈረስኩብህ ይሰማኛል ። ሙስጣፍ ስሚትህ እንዲህ ሲቆስል ልብህ በወዘን ሲብሰከሰክ ማየቱን በፍፁም ለቂቂመው አልችልም እኮ የኔ ፍቅር ። ጌትዬ ፡ እወድሃለሁ እኮ ።"

"እውነት?" አለና እቅፍ አደረገኝ ። "ትወጂኛለሽ?" ብሎ አትኩሮ ሲመለከተኝ አይኖቹ ሙስጣፍ ህሞሳቱን የሚመረምሩ መሰለኝ ። እኒያ ድንገት ጥቁርቁር ያሉትና ጥርጣሬ የሚንበለበላቸው አይኖቹ ብሽታ ያስታየው ፡ ፍርሃት ያጠለቱው ሕፃን ልጅ አይኖች መሰሉኝ ።

"ምነው የኔ ፍቅር! ለምንድነው እንዲህ የምታየኝ?" ስል ጠየቅ ኩት። መልሱን ሳያሰጠኝ ድንገት በሩ ተከፈተ ። ስብስብ ብዬ እንጨት እሳቱ ውስጥ ለመጨመር የፈለግኩ አስመስዬ እጄን ዘረጋሁት ።

ፍሪዝና ሮበርት ተከታትለው ገቡ ። መከሰሳችንን አዘንጅተው እስኪመጡ አምስት ደቂቃ ፈጅባቸው ።

ማክሲም ፊቱ ወለል ብሎ ፡ ብስጭቱ የለቀቀው መስሎ ሳየው በጣም ደስ አለኝ።

"ያን ሁሉ ሥዴዊት ምሳ መጋበዟ ነው ጥፋቱ" በማለት ጀመረ ማክሲም ንግግሩን "ያኒት ቢያትረስ እኮ ዕድሜ ልኳን ነው የምታበሳ ጨኝ ። ልጅት ሳለንማ ሠርክ እንደ ውሻ መባላት ነበር ሥራችን ። ጥሎብኝ ደግሞ በጣም ነው የምወዳት ። በእቅፌ ቢያችን አለመኖሬቸው ግን እንዴት ያለ ግልግል ነው ። በነገራችን ላይ አንድ ጊዜ ብት ብለን አየቱን እንጠያየታለን ... እሰቲ ሻዩን ቅጂልኝ ... ጭንቅ አደረኩሽ አይደል የኔ ፍቅር? ይትረታ አድርጊልኝ" ብሎ ሻዩን ለመቅዳት የዘረጋውትን እጄን ሰተም አድርጎ ሲሰመው አንዳች ስሜት ወረረኝ ። ሲሰመኝ የመጀመሪያ ጊዜው ባይሆንም ያ ሞቃት ትንፋሹ እጄ ላይ ሲንሰራፋ ልዩ ወበት ልዩ ደስታ ተሰማኝ ።

ኩርፊያ ደሀና ሰንብት! የሰላም አየር ነፈሰ ።

ማክሲም ሻዩን ፉት እያለ ፈገግ አለልኝ ። ፈገግታው አዲስ ሕይወት ዘራብኝ ። ከዚህ በላይ ምን አፈልግና! የእርሱ ፈገግታ ለኔ ቀለቤ ነው ፡ ጌጤ ሽልማቴ ። ከናቱሩ እጄን የዳበሰ አንሶ አይንና ጥርሱ ሲስቅልኝ ሳልበላ ጠገብኩ ። ለመጥረስ ያንሳውትን ጥብቅ ቆሪርሼ ለውሾቹ አከፋፈልኳቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ማክሲም ሁሉንም ነገር የረሳ ይመስላል ። በቅባት የወዛውትን እጆቹን ለመጥረግ መሐረቤን እያወጣሁ ሳለ ሰረት አድርጌ ሳየው ጋዜጣው ላይ ተመስሎ ነበር ። መሐረቤን እውጥቼ ስዘረጋጋው መልኩም እሠራራም እንግዳ ሆነብኝ ። የኔ ላለመሆኑ እርግጠኛ ነበርኩ ። ፍሪዝ ያገኙት ከዝናብ ልብሱ ወድቆ እንደሆነ ገባኝ ። አገላብጬው አየሁት ። አራቱንም ጠርዞች ያካለለው ጥልፍ እያታዬን ቅንጥስ ሲያዘው በእንደ ኛው ማዕዘን ላይ ያየሁት ያ መዘዘኛ ጥምልምሉ 'ር' ደግሞ ርብሽብሽ አደረገኝ ።

አእምሮዬ ከመሐረቡ መያ ዝናብ ልብሱ ፡ ከዝናብ ልብሱ መያ ባለ ንብረቷ ይሽከረከር ገባ ። ከዝናቡ ልብስ መጠን በመነሳት ባለ ንብረቷ ከፍ ተጠን ፡ ዘለግ ከወያ ትከሻዋ ሰፋ ትል እንደነበር ገመትኩ ። የተበጠሱትን እንዳንድ ቁልፎች ሳትተክላቸው መቅረቷ ምናልባትም የዝናብ ልብሱን ሜንቅላቷ ላይ መይም ትከሻዋ ላይ ጣል ማድረጉን ትመያ ነበር የሚል መላ ምት አሳደረብኝ ።

ወያ መሐረቡ መለስ ስል ደግሞ ከንፈሯን ስትጠርግ አሻራውን ትቶ ያለፈው ሀምራዊው የከንፈር ቀለሚ ታየኝ ። መሐረቡን ፈተሽኩት ። አንድ ልዩ መዓዛ ሰርኔን ሰርስሮ አእምሮዬን ሲኮረኩረው ሰመመን መሰል ስሜት አያኖቼን አስከደነኝ ። የት·ውስታ ሀሞሳቱን ዕርዳታ እንደሚወን አስገደደኝ ። ሽታው ለኔ እንግዳ እንዳልሆነ ብረዳም የት·ውሎታዎችንን መቼት በውል መጥቀሱ ተሰኖኝ ለጥቂት ጊዜ እንደራዘዘኩ ተረዳ ።

የሀሳብ ጉሀ ጀመርኩ ። ከፍስሐ ሽለቆ ገባው ከማክሲም ጋር ። ማክሲም አትንበሰ ። አንዲት ጎስቋላ አበባ አነሳ ፡ ሰጠኝ ፡ ፈተግኒት ፡ መዓዛዋ አወደኝ ልክ የመሐረቡ ሽታ ያወደኝን ያህል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ — አሥር

በሚቀጥለው ሳምንት አየሩ ቀዝቃዛና እርጥብ ሆኖ በመቆየቱ ወጣ ማለት የሚያስደፍር አልነበረም ። በመሆኑም ወደ ባሀሩ ዳርቻ ከመሄድ ስላገደን በጣም ነው ደስ ያለኝ ። አንዳንዴ ከሰገነቱ ላይ ሆኜ ቁልቁል ወደ ባሀሩ ስመለከት ውስጥ አካሌን ያንዘረዝረኛል ። ድምፁንማ ስሰማ ፈዩሂ ፈዩሂ ነው የሚለኝ ። አንዳንድ ሰዎች የባሕር ሽውሽውታ ለምን እንደሚያስጠላቸው ቀስ በቀስ ይገባኝ ጀመር ። ስሜት የሚቆጠቁጥ ሙሾ መሰል አስፈሪ ድምፁን ቢጠሉ አያፈረድባቸውም ።

ባሀሩን ማየት ቢያስጠላኝም አልፎ አልፎ ግን በምናቤ ሳልጎበኘው አልቀርም ። ስለ ባሀሩ ባሰብኩ ቁጥር ያ ወና ጎጆ ከነቁሳቁሱ ድቅን ይልብኛል ። ያ ምስኪን ቢንም ትውስ ይለኛል ። የዚያን ዕለት ያየኋቸው ትዕይንቶች ሁሉ የማነሰም ሁኔታና ብስጭቱ ውል ውል አያለብኝ ናላዬን ይበጠብጠዋል ። ማነሰም አትሂጂ እንዳለኝ ወደ ዳርቻው ባልሄድ ኖሮ ይህ ሁሉ የአእምሮ እውነታ ሊያርስብኝ እንደማይችል እየተሰማኝ ይበልጥ ያበሳጨኛል ።

ከዚያ ቀን በኋላ ማነሰም ሁሉንም ነገር እርግፍ አድርጎ ትቶ ሰላማዊ ኑሯችንን ብንጀምርም በጋራ ሕይወታችን ላይ ጥቁር ነጥብ የጣለውን የያን ጊዜውን ድርጊቱን በፍፁም ልረሳው አልቻልኩም ። ማነሰም ለእንዲም ለሁሉም እንዳይተሰቀስበት ወደሚሻው ወደ ቀድሞው አስነሪ ትዝታው እንዲገባ ማስገደዴ ያሳደረብኝ የህሊና ዐፀት ፋታ ነሳኝ ። ስለ ባሀሩና ከባሀሩ ጋር ስለተያያዙ ጉዳዮች በተወሰኑ ቁጥር በፍርሃትና በድንጋጤ መሸማቀቁ ላውንቱን ከፈጠረሰው በላይ ሞንቅላቱን

t.me/OLDBOOKSPDF

እናንተው ።

እየዋለ እያደር ተጨማሪ እራስ ምታት የሆነብኝ ነጋ ጠባ የሚነርፉትን እንግዶች ማነጋገሩ ነበር ። ውል ያለው ሀሳብ መሰንዘር ተርፎ እንዲት ቃል መተንፈስ እየተሳነኝ ምላሴ መተሳሰሩና ስውነቴ በላብ መዘፈቁ ይበልጥ ያነጫንጨኛል ። አብዛኞቹ እንግዶች ደግሞ በምክር ይመጡ ይመስል በጨዋታቸው ጣልቃ ስለ ርዕሶ ተነስለ ስውነት፡ ስለ ተወዳጅነቷ ፡ ውሎን አወት ስለመሆኗ ሲያነሳብኝ እነቲያቸው እነቲያቸው ያስኘኛል ።

አንዳንዴ ደግሞ በእንግድነት እየተጋበዝን ወደ ሌሎች ሰዎች ቤት መሄድ የግድ ነበር ። እቤታችንም ውስጥ ሆነ እሌሎች ዘንድ ማነሲም አብሮኝ ካለ ብዙ ከመናገር ስለሚያድነኝ ትንሽ ተሰል ያለኘል ። አብዛኛውን ጊዜ ግን እርሱ በሥራ ስለሚጠመድ ብቻዬን መጋፈጥ ነው ።

አንድ ጊዜ በአቅራቢያችን ወደሚገኘው ካቲድራል ሂጀ አስተድሽ ስመለስ የአቡኑ ባለቤት ጋብዘውኝ ወደ ቤታቸው ጎራ አልኩ ።

"ማንደርሴይ ውስጥ በየዓመቱ የሚዘጋጅ ልዩ የሳንስ ሥሽት ነበር። አውንማ አመት አለፈው መሰለኝ ከተደረገ ። ዘንድሮስ እንዴት ነው? አታዘጋጁም እንዴ?" ሲሉ ጠየቁኝ የአቡኑ ባለቤት ።

ነገሩ ሁሉ የገባኝ ይመስል ፈገግ ብዬ "አሁን እንኳን በብዙ ነገሮች ስለተወጠርን ገና አልወሰንም" አልኳቸው ።

"የለም የለም ፡ አዘጋጂ እንጂ ። እንደምንም ባለቤትሽን ማሳመን አለብሽ ። የባሬ ሁለት ዓመት የነበረው በጎል እንዲህ እንዲመስልሽ! እኔና ባለቤቴም ተጋብዘን ነበር ። መቼም ያንን የመሰለ ተልት ዝግጅት ያላደነቀ አልነበረም"

"ግድ የለም ፡ እስቲ ማክሰሙን አስታውሰዋለሁ"

"ምን እሱ ብቻ ፡ እሬ ተይኝ" ብለው ቀጠሉ ሲትዮጲ። "እንዴ እንዲህ የመናፈሻ ግብዣ ተዘጋጅቶ ተጋብዞ ሁሉ ተሮ ነው ያሳው ። በሁሉ ነገሩ እንዲያ የተዋጣለት ግብዣ አይቼም አላውቅ ። ሲትዮጲ የዋህ ሴት ባለመሆኗ ..."

አላግባብ በሰንዘሩት ሀሳብ እንደመደንገጥ ብለው ሀሳባቸውን ዘጅምሩ እንጠልጥለውት ቢቀሩ እንዳላሳፍራቸው ብማሰብ "መቼም ርዝመ ልዩ ፍጡር ነበረች" አልኳቸው ።

ሳላስበው ይህንን ስም እንዴት ከአፌ እንዳመጣሁት አላንብኝም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ብቻ ጓሙን ሬክክ ብዬ ጠራሁት ። ከአንዳች ከባድ ሀሙም የተገላገልኩ ያህል ነው ትልቅ እፎይታ የተሰማኝ — ርብቃ ብዬ በመጥራቴ ።

ፊቱ እንዲያ ሲቀላና እንዲያ ጭንቅ ጥብጥ ሲለኝ አሮጊቷ አስተውለው እንደሆነ ለማወቅ ሰረቅ አድርጌ አየኋቸው ። ሁኔኮን ጉዳዬ ሳያሰቱት ሟውሙታቸውን ተጥለው "ፍፁም አይተሻት እታውቂም መሰለኝ?" ብለው ጠየቁኝ ። ጭንቅላቴን በመነቅነቅ የሰጠኋቸውን ምላሽ ተከተለው "እኛም ብንሆን እዚህ አካባቢ ከመጣን ገና አራት ዓመታችን በመሆኑ ብዙም አንተዋወቅም ። በጓንሱና በመናፈሻው ግብግ ወቅት መቼም ጥሩ አድርጎ ነው ያስተናገድኸን ። አልፎ አልፎም እንዲሁ ለምላ ስንጋበዝ መስተንግዶዋ ሁሉ ልዩ ነበር ። እንዲህ ያለች ፍልቅልቅ ፡ ሰው አክባሪ ፡ ሁሉን አሟልቶ የሰጣት ነበረች ። ምን ያደርጋል? ሞት አይቀር ስም አይተበር ። የእርሷንም ገላ እኮ ምስጥ ይበላው ይሆናል?" አሉ አሮጊቷ በሐዘን ተመሰጠው ።

"ሁሉንም ነገር ታውቅበት ነበር ነው የሚባለው ። መቼም ውበቱን ብልህነቱን ፡ የስፖርቱንም ችሎታና ፍቅር ሁሉ አሟልቶ የሚይዝ ሰው ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ነው የሚመስለኝ ።" አልኳቸው ስለ እርሷ በጥልቀት መረዳት መፈለጌን እንዳያውቁብኝ ዘና ብዬ ንግግሩን እያፍታታ ተልዙ ።

"ነዪት መጥቶ!" አሉ አሮጊቷ በአድናቆታቸው እየገፉ "በሁሉም ነገር የታደለች ነበረች ስልሽ? አውን ያኔ የግብግቡ ዕለት እደረጀው ላይ ሁና እንግዶቿን አንድ ባንድ እየጨበጠች በፈገግታ ስትቀበል ያ ፡ ጥቁሩ ሀር ፀጉሯ ትከሻዋ ላይ ተዘናፍሎ ልክ እንደ ቀን ጀምበር መልል ብሎ ይታየኛል ። ያ በረዶ የመሰለው ልብሷስ? አይ ውበት! አይ አለባበስ! ጨረቃ ነበር የምትመስለው!"

"የቤት ውስጥ ሥራውንም መምራቷ ጊዜዋንና ሀሳቧን ሳይሻማት አልቀረም ። እኔ ግን ጠቅላላ ሥራውን በሥራተኛዬቱ ላይ ነው ወላልኩት።"

"ምንም አይደለም ። ማንም ሰው ቢሆን ሁሉንም ነገር አካቶ መሥራት አይችልም ። አንቺ ደግሞ ገና አንድ ፍሬ ልጅ ስለሆንሽ ቀስ በቀስ ስትረጋጊ ትደርሺበታለሽ ። በዚህ ላይ ለጊዜ ማላለፊያ ስዕል ትምህርታያለሽ አሉ ። ግን ነበር የነገረኝ ልጄ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ያሄ እንኳን ያን ያህል ትልቅ ግምት የሚሰጠው አያደለም"

"ቢሆንም መች አነሰ ልጇ ። ትንሽም ቢሆን የሚናቅ ተሰጥኦ አያደለም ። በሩዙም እንዳትተያው ፡ ማንደርሌደ ደግሞ ለስእል የሚሆኑ ብዙ ቆንጆ ቆንጆ ቦታዎች አሉት ።"

"ትንሽም ብትሆን" የምትለዋ የንቀት ሐረጋቸው ውስጥ ውሰጡን ብታበግንም "እርሱስ እውነትዎን ነው ። ያሁን እሰቲ" አልኳቸው ።

ከዚያም ሰልቸት እስኪለኝ ድረስ የቆየ የላውን እየተላጠሩልኝ ቆይተው አስር ሰዓት ሲሆን ለመሄድ ተነሳሁ ። ማነሰዎንን ሰላም እንድልላቸውና ስለ ግብግቡም እንዳስታውሰው በድንጣ አሳሰብኩኝ ።

መኪናው ውስጥ ቁጭ ብዬ አይቼው የማላውተውን የዳንስ ግብግ በምናቤ ቀርፁ ብቻዬን እብሰለሰል ገባሁ ። ማንደርሌደ በተጋባዦች ተጨናንቆ ፡ አዳራሹ ደምቆና አሸብርቆ ታየኝ ። ርብታ ልዩ ውበት ተጎናፅፋ ፡ ግርማ ሞገስ ተላብሳ ሽብ ረብ ስትልና የመላ እንግዶች ላት ያለ አድናቆት በአደሌው ሲያስነሳሳት ፡ በአይኔ ሽው አለችብኝ ። ዳንስ መድረኩ ላይ መጥታ ያንን ሠማ ወጉሯን ግራና ቀኝ ስትንሰንሰው አየሩን የሚሞላው ሽቱዋ አፍንጫዬን ዳሰሰው ።

ያሠን ወደ ጎን ተመት አደረግኩ ስል ደግሞ ሌላ ሀሳብ መጥቶ ድቅን አለብኝ ። እኒያ "እንደ" ነው? ለመድሽ?" በሚል አፍ ማሚሻ ተርበው ለአሽሙርና ለሽሙጥ የሚያደፁት ሴቶች ትውበ ሰለኝ ፡ እርር ድብን አልኩኝ ። የሚመጡት አዝነው ሳይሆን ውኔታዬን ሊያጠኑ ፡ ከርብታ ጋር ሊያወዳድሩኝ በአጠቃላይ ሥነዬን በሠሚት ሊዘነጣጥሉት እንደሆነ ይገባኛል ። ከእንግዲህ እደጇ ዝር እንዳያሉ ማነሰዎ እንዲያግድልኝ አነግረዋለሁ ብዬ ወሰንኩ ። ግፋ ቢል "ድርውንሰ መች አጣናትና ፡ እናታን ጠርታ አባታን የማትደግም ድራሽ ቢስ ። ዕድሜ ለማነሰዎ ትበል ፡ ከመንገድ አንሰቶ ለዚህ ያበቃት..." ይሉኝ እንደሆነ እንጂ ምን ሊያመጡብኝ? ያው በለመደው ባለጌ አፋቸው ያሰለትሠኛል እንጂ አያቆርሱኝ አያፈልጡኝ በማለት በእርምጃዬ መጣፋት እንዳለብኝ ተሰማኝ ።

በዚህ ሀሳብ ተውጬ ጥቂት ከቆየሁ በኋላ ሚስተር ሩፈንስ ከሮውሌይን ከራት አያቼው ሽፈሩ መኪናውን እንዲያቆም አዘዝኩት ። ከመኪናው ወርጄ ከእርሱ ጋር ለመንሸራሸር እንደፈለግኩ ነገርኩት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ለመግቢያ ያሆነኝ ዘንድ አቡኑ ቤት እንደነበርኩና ከባለቤታቸው ጋር ስጫወት ማርፈዴን ገልፁለት ስለ አመታዊው የማንደርሌይ የዳንስ ግብዣ እንዲነግረኝ ጠየቅኩት ። ጠቅለል ባለ መልኩ አስረዳኝ ።

"መቼም ብዙ ዝግጅት የሚጠይቅ ሥራ ይመስለኛል" ስለው

"አዎን" በማለት በአጭሩ መለሰልኝ ።

"ርብቃ ነበረች አብዛኛውን ዝግጅት የምታከናውነው?"

"ሁላችንም የአቅማችንን እንጣጣራለን" አለኝ ለስለስ ብሎ ። ከመለሳለሱም በላይ ማፈር ሲጀምረው ምን ነካው አሰኘኝ ። ከርብቃ ጋር ፍቅር ይዞት ነበር እንዴ? ብዬም ጠረጠርኩት ። የመጀመሪያ ቀን ካየሁበት ዝምተኝነት በተፈጨማረ አዩኝ ። አፋርነትም ተጸናብኝ ባህሪዩ ሊሆንም ይችላል በማለት ሞውመውተን ተዋየ "አሁን እንዲህ አይነቱ የዳንስ ግብዣ ቢዘጋጅ እኔ ምናምኑንም አላውቅበትም እኮ" አልኩት ።

"ምን ችግር አለውና? ትንሽ በአለባበሱ ፡ በጊጣጊው አማምረሽ ለመገኘት መሞከር ነው እንጂ ይህን ያህል ምንም የምትሰሪው አይኖርም"

"ስለ ማያፋፈርህ በጣም አመሰግናለሁ ፍራንክ ። ግን እኮ እርሱንስ ቢሆን የት አባቱ አውቅበትና?"

"እረ አሳምረሽ ታውቂበታለሽ" ሲለኝ ልቤን ነካው ። ለማስመሰል ሳይሆን ከአንጀቱ እንደነበር ነው የተሰማኝ ።

"ታዲያ ፡ ማክሰኞም የዳንሱን ግብዣ እንዲያዘጋጅ ትጠይቀዋለህ እንዴ?" ሰል ጠየቅኩት ።

"ለምን አንቺው አትጠይቂውም?" አለኝ

"እኔ እንኳን አልጠይቀውም"

ሁለታችንም ለጥቂት ጊዜ ያህል ወጥ ብለን ከተነጋን በኋላ ትኩረቴን መያሰጠሁት ነጥብ ለማምራት ያረዳኝ ዘንድ ባለፈው ጊዜ ጀስፐርን ተከትዩ መደባሕሩ ዳርቻ ስሄድ አንድ ለየት ያለ ሰው ማየቴን አነሳሁለት ። ሰውዬው ቢን እንደሚባል ፡ እንኳን ሰው ሊነካ እላዩ ላይ ያረፈውን ዝንብ እሽ የማያል የዋህ የአእምሮ ሕሙም መሆኑን ገለፀልኝ ። ከዚያም ስለ ጎጆውና ስለ ዕቃዎቹ በገርገር ጠየቅኩት ። ቤቱ ቀደም ሲል ለጀልባዎች ማረፊያነት አንደተዘጋጀና በኋላም የውስጥ ዕቃዎቹን በማደራጀት ለመዝናኛ እንዲውል ያደረገችው ርብቃ መሆኗን

t.me/OLDBOOKSPDF

አስረዳኝ ።

"ለመሆኑ ጎጆውን አዘውትራ ትጠቀምበት ነበር እንዴ?"

"አዎን ፡ አልፎ አልፎ ፈጣሪው ሙሉ ሆኖ ሰብዐበራ በምትንሸራሸርበት ጊዜና እንዳንዴም በተለያዩ አጋጣሚዎች ትጠቀምበት ነበር ።

"መቼም በሙሉ ፈጣሪው መንሸራሸር እጅጣ በጣም የሚያስደስት ይመስለኛል ። አንተ በእንዲህ ያለ ጊዜ ተንሸራሽረህ ታውቃለህ?"

"እንድ ሁለቴ ተንሸራሽሬአለሁ መሰለኝ" አለኝ ። አንጋፋና አጠቃላይ ሁኔታው ይህን መሰልና ተጣማጅ ሌሎች ጉዳዮች እንዲ ነሱበት የማይፈልግ አይነት ነበር ።

እኔ ግን ውትወታዬን ባለማቋረጥ "እዚያ አካባቢ ደግሞ መልህቅ ብጤ ያየሁ መሰለኝ ። ወደቡ መሆኑ ነው?" ስል ጠየቅኩት ።

"አዎና ፡ ጀልባው እዚያ አልነበረም እንዴ የሚያረፈው?"

"የምን ጀልባ?"

"የእርፏ ጀልባ ነሞ" አለኝ ። ከመጀመሪያው ጀምሮ ርብቃ ወይም ሚስዝ ደዊንተር ማለት ሲችል ለምን እየደጋገመ "እርፏ" እንደሚላት አልገባኝም ።

"ጀልባዋ ሰጥሞ ነው የሞተችው የሚባለው እውነት ነው እንዴ?"

"ነው እንጂ ፡ ጀልባዋ ሲገለበጥ እርፏን ማዕበሉ ይዟት ሄደ"

"ምን ዓይነት ጀልባ ነበር?"

"ሦስት ሙዶ ቱን የሚመዝን አንዲት አነስተኛ ክፍል የነበረው ጀልባ ነበር"

"ግን ምን እንደገለበጠው የታወቀ ነገር አለ?"

"ያው ሐያለኛ ሞገድ ሳይሆን አይቀርም ተብሎ ነው የተገመተው"

"እንዲያው አንድም ሊያድናት የሞከረ ሰው አልነበረም ማለት ነው?"

"እንዴት ብሎ? እደጋው መከሰቱን ማን አየና? ሜሪሽ በጀልባዋ መንዟን ማን አወቀና?"

እንዲህ ብቻዋን እንደነበረች አላውቅም ነበርና አዙን ሰሰማው በጣም ነው የደነቀኝ ። ፍራንክ እንዳያውቅብኝ ስሜቴን ተቆጣጥሬ ጥያቄዬን ቀጠልኩ ። "የቤቱም ሰዎች ለሽርሽር መውጣቷን አያውቁም ነበር ማለት ነው?" አልኩት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

“አዩ ፡ አብዛኛውን ጊዜ ብቻዋን ትሄድና ሌሊት ባሻት ጊዜ ተመልሳ እዚያው ጎጆው ውስጥ ነበር የምታድረው ።”

“ራሳዋ የተገኘው ከስንት ጊዜ በኋላ ነበር?”

“ከሦስት ወራት በኋላ”

ሦስት ወር በጣም ረጅም ጊዜ ነው ። እኔ እስከማውቀው የሰጠሙ ሰዎችን በሦስት ቀን ውስጥ ማዕበል እየጠረገ አምጥቶ ከዳርቻው ያስተፋቸዋል ። ያህ ታሪክ ግን ከጅምሩ እንስቶ በጠቅላላው ጥርጣሬ የሚያሳድርብኝ ሆነ ።

ቀጠል አድርጌም የት እንደተገኘች ስጠይቀው ከሰርጡ ስልሳ ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ አጅኩምብ ከሚባል ስፍራ አቅራቢያ መሆኑን ነገረኝ። ከሦስት ወራት በኋላ ራሳው የእርሷ ለመሆኑ በምን እንደተረጋገጠ ለስነዘርኩት ጥያቄ ደግሞ የሰጠኝ ምላሽ ማክሲም እስኩራው ድረስ ሄዶ እንዳያት የሚገልጽ ነበር ።

ፍራንክ ለማተርብለት ጥያቄዎች ሁሉ መልሱን ሲሰጠኝ ሜንቅ ጥብብ ሲለውና ንግግሩን ቁርጥ ቁርጥ ሲያደርገው በጣም አሳዘነኝ። ለጊዜው ጥያቄዬን ለመግታት አሰብኩና ያልኝን ይበለኝ ፡ እንዳሻው ይታዘበኝ በማለት ሀሳቤን ከዳር ማዘለት እንዳለብኝ ተሰማኝ ።

“በእርግጥ የያን ጊዜው ሁኔታ ሁላችሁንም በእጅጉ የነካ እንደነበረና ስለ እርሱ እንዲነሳባችሁ እንደማትሹ ይሰማኛል ። እንዲያው ያ የተዘጋው ጎጆ እቃዎቹ እንዲያ ሲበለሻሹ ምነው አስታዋሽ አጣ? ለማለት ያነሳሁት ሀሳብ ሳላስበው እየተንለጎለ ሄዶ እንጂ ይህን ያህል ለመግፋት እንኳ ፈልጌ አያደለም” ስለው መልስ አልሰጠኝም ። ከዝምታው ብዙ ሳያሠጋ ከአኳኋኑ ይህን ሁሉ ያናዘዘኝ የጎጆው ሀሳብ እንዳልሆነ መጠራጠሩ ተብቶኛል ።

ስለሠነም ከእርሱ ጋር የነበረኝን የእስካሁኑን መልካም ወዳጅነት በገዛ እጄ እያደፈረስኩት መሆኑ እየተሰማኝ የተሟችን መንገድ መርዘሙን አስታነከኩ. ስለሌሎች ጉዳዮች በማውራት የጭውውታችንን አቅጣጫ ለመጠምዘዝ ሞከርኩ ። ጥርጣሬውን ለመፋት ግን አልቻልኩም ።

መጥቶሌው ንገሩን ሁሉ አፍረጥርጠ ማውጣት መሆኑ ድንጉት ብልጭ ሲልብኝ ። “ያንዘውልህ ፍራንክ ፡ ምን እያሰብክ እንደሆነ ይገባኛል ። ይህን ሁሉ የምጠይቀው ለምን እንደሆነ ላይገባህ ይችላል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምንም ስብእዊ ርህራሄ የሌለኝ ፡ አረመኔ ፡ የወረ ሱሰኛ እድገህም ትግሎኝ ይሆናል ። በፍፁም አያደለም ፡ ልታምነኝ ይገባል ፍራንክ ። ይህን ሁሉ የሚያስለፈልፈኝ የራሴ በሽታ ፡ የገዛ ቲስሌ ነው ።

"ልብ ብለህ አዳምጠኝ እንግዲህ ። እዚህ ማንደርሌይ ከመጣው ጀምሮ ነገር አለሙ ሁሉ እንግዳ ነው የሆነብኝ ። ከባሕር የወጣ አሣ ነው የሆንኩት ። ያልለመድኩት ዓይነት ፡ ያልተወለድኩበት ፡ ያላደግኩበት አዲስ ኑሮ ነው የገጠመኝ ። በተለይ የሰዉ ሹክሹክታና ሐሜታ ሥራሽ ጨርቄን ሊያስጥለኝ ነው ። በሆነ ባልሆነው ከርብታ ጋር ያጋፅፉኛል ። ለማክሲም እንደማልገባ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ይነግሩኛል ። ሳልወድ የማዬን በራሴ እንዳናር ፡ የበታችነት ስሜት እንዲያድርብኝ እየተገፋፋው ነው ። ታድያ ይህን ሁሉ ሳመዛዝነው ምነው ማክሲምን ያገባውበት ቀን የተረገመ በሆነ ያሰኘኛል ። ምን ልሁን? ምን ላድርግ! ቢጨንቀኝ እንጂ ..."

ሀሳቤን መቋጨት ተስኖኝ እንባ ተናነቀኝ ። ትንፋሽ አጠረኝ ። በአንድ በኩል ምስጢራን ዘክዝኬ ማውጣቱ ቢያሳፍረኝም በሌላ በኩል ደግሞ እንዴ ካወጣሁት ወደ ኋላ ማፈግፈግ እንደማልችል መረዳቱ አፅናናኝ ።

ፍራንክ ስሜቱ ተለዋውጦ ትኩር ብሎ እያየኝ "የለም አይገባም ፡ እንዲህ ያለውን ሀሳብ ከአእምሮሽ ፍቀሽ ማውጣት አለብሽ ። እንደኔ ከሆነ የውስጥችሁ ጋብቻ በጣም ነው ያስደሰተኝ ። ማክሲምም እንቺን ባማግባቱ የወደፊት ሕይወቱ እንደሚቃናለት እርግጠኛ ነኝ ። ለማንደር ኤይ ኑሮ እንግዳ መሆንሽ ደግሞ ሐጢአት የለውም ። እንዲያውም እኛ እንቺን የመሰለ ሰው በመካከላችን ማግኘታችንን እንደ ታላቅና አዲስ ለውጥ ነው የምንቆጥረው ። እንደ እውነቱ እንቺን የሚተቹ ቢኖሩ የሠሚት ሱስ ያለባቸው ወረኞች ብቻ ናቸው ። እስከአሁን ግን ማንም ሲተችሽ አላየሁም ፡ አልሰማሁም ። ሰምቼ ቢሆንማ ቀንድ ቀንዳቸውን እያልኩ አፋቸውን አስይዛቸው አልነበር" አለኝ ።

"በጣም አመሰግናለሁ ፍራንክ ። ንግግርህ በጣም ነው ስሜቴን የነካው ። እየሁ ፡ ችግሬ ምን መሰለህ? እኔ ከሰው ጋር መላላትን አላውቅበትም ። ከዚህም በላይ የእርሷን ችሎታ ፡ በራስ መተማመኟን ፡ ግርማ ሞገሷን ፡ ውበቷንና ተጫዋችነቷን እያሰላሰልኩኝ እኔ ሥፍር እንደማልደርስ ሲታወቀኝ መንፈሴ ሁሉ ይታመካል ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

ፍራንክ የመረበሸ ስሜት እንደተሰማኘው ነው "እረ እንደዚህ አትበይ" ከማለቱ በፊት መሐረቡን ከኪሱ አውጥቶ ተናፈጠ ።

"እንዴ ፡ ለምን አልልም? ሀቁን እኮ ነው የነገርኩህ" አልኩት

"የማይተናነሱ ፡ እንዲያውም የተሻሉ ባሕሪያት አሉሽ እኮ ። በእርግጥ ገና ብዙ ሳንተዋወቅ ይህን ማለቱ የሽርደዳ ያመስልብኝ ይሆናል። ግን አያደለም ። ምንም እንኳን ወንደላጤ ብሆንና ስለሴቶች ጠለቅ ያለ ዕውቀት ባይኖረኝም ከሴት ልጅ ውበትና ተሰጥዎችነት በላይ ባሏን የሚገዛው ርህራሄነቷ ፡ ቅንነቷና ትሁትነቷ ይመስለኛል" አለኝ ፍራንክ ። ይበልጥ በተረበሸ ቁጥር አፍንጫውን በመሐረቡ ይለዋል ።

"እኔ እንኳን ያን ያህል ርህራሀና ቅን የሆንኩ አይመስለኝም ። ትሁት እንኳን ላልከው የኖርኩበት ሁኔታ የግድ እንድሆን ስላስገደደኝ ሳይሆን አይቀርም ። በሌላ ወገን ደግሞ ማክሲምን ሞንቴ ካርሎ እንዳገኘሁት ወዲያውኑ ለጋብቻ መስማማቱ ትዝብት ላይ የጣለኝ መሰለኝ ። አይመስልህም?"

"እረ በፈጠረሽ ተይኝ? ፈፅሞ የማይታለመውን? ሌላው ቢቀር እኔ እንዲያ የደከመ ሐሳብ የማስተናግድ ይመስልሻል?"

"እይ ፡ እይ እንዲያ ማለቱ እንኳን አልነበረም ..."

"ይህንን ሀሳብሽን ቢሰማ ማክሲም ምን ያህል እንደሚጨነቅ ፡ ምን ያህል እንደሚበሳጭ ይታየኛል"

"ታድያ አንተ ልትነግረው ነው እንዴ?"

"ምን ብዬ? እንዴት እንደዚያ ትገምቺኛለሽ ሚስዝ ደዊንተር? ስሚኝ እስቲ ፡ አንድ ነገር ልንገርሽ ፡ ማክሲምን ጠለቅ ብዬ አውቀዋለሁ። አንቺ ስላለፈው ሁኔታ እያሰብሽ መጨነቅሽን ቢያውቅ ጭራሽ የሚያዝ የሚጨነቀውን ነው የሚያጣው ። ካንቺ ጋር ከተጋባ በኋላ ትንሽ እየለተለተው ስሙነቱ መለስ እያለ ነው ። አምና ይህን ጊዜ የነበረበትን ሁኔታ ብታይ ጭንቅላትሽን ይዘሽ ትጮኺ ነበር ። አንቺ ገና ለማላጋ ወጣት በመሆንሽ ስላለፈው መጨነቅ ሳይሆን የወደፊቱን ነው ማየት ያለብሽ ። እርሺው ሚስዝ ደዊንተር ። ከእንግዲህ ማክሲምንም ሆነ ሁላችንንም ከዚያ አስፈሪ ያለፈው ትዝታ መንጭቶ አውጥቶ በወደፊቱ ብሩህ ጎዳና ላይ እንድንንቀሳቀስ የማድረጉ ሀላፊነት በትከሻሽ ላይ ወድቋልና አስቢበት ። ከማጡ አውጪው ፡ መንገዱን አሳያው" አለኝ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠንከር ብሎ

"ኡፋ ! ምን አለ ይሀን ሀሳቤን ቀደም ብዬ አካፍሁህ ቢሆን? አሁን እንዴት ነው የቀለለኝ ። እንድ ጥሩ ጓደኛ ነው ያገኘሁት ። እደመስልህ ፍራንክ?" አልኩና እይን እያኑን ሳየው እርሱ አቀርቅሮ መራት መራቱን በአይኑ እየዳሰሰ "እምን ፡ በሚገባ እንጂ" አለኝ ።

ጥቅጥቅ ካለው ጫካ ወጥተን ከጎላማው መስክ ስንደርስ እኒያ ሙላ አበባች ተቀበሉን ። አይ እኒህ አበባች ፡ ውበታቸውን እንዲህ የሚያጎላው የሕይወት ዘመናቸው እጅግ አጭር መሆኑ ይሆን? የሚል ሀሳብ አደረ ብኝ።

"ፍራንክ" አልኩት ድንገት ወደርሱ ዞር ብዬ "ያሀንን ሟሙሙታችንን ከማብቃታችን በፊት አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ?"

"የምን ጥያቄ?" አለ እንደ መደናገጥ እያለው

"ምን ችገረህ? ስጠይቅህ ትሰማው የለ? ብቻ እንተ እውነቱን ልትነግረኝ ቃል ግባልኝ"

"እንዴት እንዲያ ይሆናል? እኔ ..."

"ምንድነው ይሀን ያህል ያስፈራህ? ለምጠይቅህ ጥያቄ የሚመስልሀን መመለስ ነው ። የሚመስልህን ብቻ ሳይሆን እትብቴን ፡ ሥሩን ነው የምፈልገው"

ፍራንክ ይብስ ተረበሸብኝ ። የሚናገረው ጠፍቶት እይኑን አጉረጥርጦ አፉን ከፍቶ ቀረ ። "በል እንጂ ፡ ምን ነካህ? እሺ በለኝ" ስለው እየተርበተበተና እየተንተባተበ "ተይ እንጂ ሚስዝ ደዊንተር ፡ ያማም እይደል ። በፍፁም ፡ ልመልሰው የማልችለው ዓይነት ቢሆንስ? ... እንዴ ..." አለኝ እንዴ እኔን ፡ እንዴ ሙሪያውን ቃኘት ቃኘት እያደረገ ።

"እረ ግድ የለህም ። ያን ያህል የከበደ አይደለም ። የግል ህይወትንም የሚመለከት እንዳይመስልህ"

"እስቲ እንግዲህ ጥያቄው ይቅረብና እሞክረዋለሁ"

ይሀን ሲለኝ ወደ ማንደርሌይ እየተጠጋን ነበር ። ቁና ብዬ ማንደርሌይን ሳየው እንደ መትሮው ሁሉ ውበቱ ፡ ግርማ ሞገሱ አስፈራኝ። ከምን ጊዜውም ይበልጥ ግውዝነቱን እውልቅ ጥሎ የሕያውነት ሥጋ የተላበሰ ፍጡር መሰለኝ ። ሙሪያውን በተደረደሩት የመስኩት አይኖቹ የሚያስፈራራኝ አይነት ። ከቤተመጻህፍቱ ሚስ ሠወጫ

t.me/OLDBOOKSPDF

በቀጭኑ እየወጣ ወደ አየሩ ከሚምዘገዘገው ጢስ ጋር ሀሳቤን ላክሁት ። ሽቅብ ነጎደ ። ልጓሙ እንደ ላላለት ፈረስ መጭ ማለት ሲያዝ ቆንጠጥ አደረግኩት ።

ቀስ ብዬ አይኔን መደንን ስለው ፍራንክ እጮኔ ነው ያለው ። አይናገር አያጋገር በትካዜ ሰጥሞ ። "ፍራንክ" ስለው እንደመባነን አለና "እመት" አለኝ ።

"ጥያቄዬን ላትርብልሃ?" አልኩት — ውስጡን በሚመረምር አይነት እያየሁት

"እ ... እ... ሺ ... እሺ ብያለሁ ... እኮ"

"እንዴት ነው? ርቧት በጣም ቆንጆ ነበረች?"

ፍራንክ፡ ዐጥ አለ ። አይኑን በአሻገር ልኮ እቤቱ ላይ ተከለው ። ቀስ በቀስ "እ·ም·ን" ማለት ጀመረ "አምን ፡ በሕይወቴ — እንደ እርሷ ውብ ቆንጆ አያቸም አላውቅ ..."

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አስራ አንድ

ከሚስዝ ዳንቨርስ ጋር አዘውትሬ ባለመገናኘቴ ደስ ነው ያለኝ ። እንደተለመደው ቂት ቂት እየደወሉ ስለ አለቱ የምግብ ዝግጅት ያነጋግሩኛል ። በአሊስ ምትክ ከላሪስ የምትባል የግል አገልጋይ መድበውልኛል ። ከላሪስ የዚያው የማንደርሌይ ገበሬ ልጅ ስትሆን እጅግ ግሩም ፀባይ ያላት ነበረች ። ቀደም ሲል ራት ካለ ስፍራ ከአክስቲ ጋር ትኖር ስለነበር እርሷም እንደኔው ሁሉ ለማንደርሌይ እንግዳ ናት። የሌሎች አለባልታ ስላልተጠናወታትም በጣም ነበር የምንስማማው ። ለቀድሞዬቱ እመቤት ስላላደረች ከዚቱ ውስጥ እርሷ ብቻ ነበረች እመቤትነቴን የምታውቅልኝ ፡ እርሷ ብቻ ነበረች ከአንጀቷ በቅን ልቦና ሚስዝ ደዊንተር ብላ የምትጠራኝ ።

ያች አሊስማ እብሪቷም የሚቻል አልነበር ። ስፈታቸው የለቀቁ ልብሶቼን እኔው እጠቅማቸው እንደሆነ እንጂ ለእርሷ ደፍሬ አልሰጣትም ነበር ። አንድ ቀን የውስጥ ልብሴን አገላብጣ እያየች የጨርቁን ጥራት ፡ የዳንቴሉን አሠራር ስትመረምር ፊቷ እንዴት ኩምትርትር እንዳለ አይዘነጋኝም ። የጨርቁ ርካሽነትና የዳንቴሉ መናኛነት የራሷን ክብር የነካው ይመስል እንዲያ ስትሸማቀቅ ሳይ ልቤ ነበር የተሸማቀቀው።

የውስጥ ልብሶቼ ንፁህ ይሁኑ እንጂ ስለ ሙቧታቸውና ስለ ጥራታቸው እምብዛም ደንታ አልነበረኝም ። የከላሪስ ሁኔታ ትምህርት ሆነኝና ሎንዶን የሚገኘው ልብስ ሰፊ የውስጥ ልብሶች ካታሎግ እንዲልክልኝ ወዲያውኑ ዓዘዝኩለት ። ካታሎጉ ደርሶኝ ምርጫዬን እንዳስተካከልኩ አሊስን ተክታ ከላሪስ ስለመጣች ሐሳቡን ሰረዝኩት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ልብሱን ልገዛው ያሰብኩት ለኔ ሳይሆን ለአሊስ እንደነበረ ሲታወቀኝ እራሴን ብታዘበውም ከላሪስ ደግሞ እንደዚያችኛይቱ ቺንኖ አውሬ ስላልመሰለችኝ ወጪ ማውጣቱ አልታየኝም ።

ሚስዝ ዳንቨርስ ከላሪስን የመደብልኝ እንደምንስማማ አውቀው ሆን ብለው መሰለኝ ። የአሮጊቲ እንዲያ ቆጣ ቆጣ ፡ ግንፍል ግንፍል ማለት ለምን እንደሆነ ውስ አድሮ ነው የገባኝ ። በ.ያትሪስ እንደነገሩኝ እኔም እንዳስተዋልኩት ለርብቃ ላቅ ያለ ፍቅርና አክብሮት ነበራቸው ። እኔን ስብእናዬን ሳይሆን የጠሉት የርብቃ ምትክነቴን እንደሆነ ተረዳሁላቸው ።

ምን ያድርጉ? አልፈርድባቸውም ። የእኔ እዚያ መገኘት ያስፈ ትዝታቸውን እየቀሰቀሰባቸው ልባቸው በሐዘን ሲሞጥ እየተሰማኝ ይበልጥ አዝንላቸው ጀመር ። እርሳቸው ለዘመናት አብረዋት ስለኖሩ ከመልኳ አንስቶ ባህሪዋ ፡ መላ ድርጊቷ እየተደቀንባቸው ቢያዝኑ፡ ቢተክዙ አውነት አላቸው ። የእኔ አይብስም እንዴ? አንዲት ቀን እንኳን ያላየኋትን ሴትዮ በምናቤ እየቀረፅኩ ኑጋ ጠባ እንዲያ ብስልስል ፡ እንዲያ ትክንክን እል የለም?

ፍራንክ ደግሞ ምን ነበር ያለኝ? ያለፈውን እርሺው አሉኝ? እንዳለኝ ሁሉ መሞከሬ አልቀረም ነበር ። ግን እንዴት አድርጌ ልርሳው፡ እርሱ ምን ችገረው? እኔ በምውልበት አይውል ፡ በማድርበት አያድር ፡ በኔ የደረሰው አልደረሰበት ። እርሱ እንደኔ በተቀመጠችበት መንበር አያቀመጥ ፡ በተኛችበት አልጋ አይተኛ ፡ እርሷ የያዘቻቸውን ቁሳቁሶች አይነካቸው ፡ የእርሷን የዝናብ ልብስ አይደርብ ፡ ከሷ ውስጥ የረሳቸውን መሐረብ አላየው ። አይ ምስኪን ፍራንክ! እርሺው አሉኝ? ሌላው ቀርቶ ያች ያረጀች ውሻ እንኳን ወደ ቤተ መጸሀፍቱ በገባው ቁጥር ኩቴዋን አውታ ማለቱ የሴት ኩቴ መሆኑን አንተቷን ቀና አድርጋ ታየኝና ገርመም አድርጋኝ ወደ ማንሳላጀቷ መመለሷ የጠበቀችው ልዩ ሰው ፡ ያኖችው ግን ሌላ ቢሆንባት አይደለም ? ይህን ሁሉ እያየ መርሳት ተላል ነው እንዴ ? ያልተነካ ነው ግልግል የሚያውቅ !!

እንደኔማ ምኞት ቢሆን ኖሮ ሁሉንም ነገር እርግፍ አድርጌ ትቼ እራሴ ተደስቼ ማክሲምንም ባስደሰትኩት ነበር ። ኑሯችንን በፍቅር ፡ በሰላምና በደስታ ከመምራት የተለየ ፍላጐት ፈፅሞ የለኝም ። ግን

t.me/OLDBOOKSPDF

ዙሪያዬን የከበበኝ ፡ ስመጣ ስገባ የሚገጥመኝ ሁሉ እርሷን እያስታወሰኝ ስላም ሊኖረኝ አልቻለም ።

በእውኑም በሕልሜ እየመጣችብኝ ዕረፍት ትነሳኛለች ። አንዳንዱም በገዛ ቤቱ ባያቸዋርኑት እየተሰማኝ ከአውን አውን መጥታ "እዚህ ምን ያሳልትሻል?" ብላ አንገቱን ጠምዝዛ ስትገፈትረኝ ይታየኛል ።

አንዳንድ ጊዜ በራሴ አነሳሽነት አንዳንድ ጥቃቅን ነገሮችን ለማድረግ ስነሳ "ሚስዝ ደዊንተር እንዲህ ነበር የምታደርገው" "ሚስዝ ደዊንተር እንዲህ ነበር የምትሰራው" "ይህንን ዕቃ እዚህ ነበር የምታስቀምጠው" ሲሉኝ ይበልጥ ተስፋ እቆርጥና እጄን አጣጥፌ መቀመጡን እመርጣለሁ ።

አንድ ቀን ሲት ከማረፊያው ክፍል እንደተቀመጥኩ ቢያትሪስ የላኩልኝ የጋብቻ ስጦታ ደረሰኝ ። ባለ አራት ትላልቅ ቅጾች የስእል መጻህፍት ነበሩ ። ቢያትሪስን በቁም ነገረኛነታቸውና የእኔን ስሜት ለማርካት ሰንደዉን ድረስ ሂደው መፃህፍቱን በመግዛታቸው ከልቤ አድናቆቱን ለገስኳቸው ። እኔ ይልቁኝና ተደላድዬ ስእል መለማመዴን የጀመርኩ ይመስላቸው ይሆናል የሚለው ሀሳብ ሲያድርብኝ ማልቀስ ቀረኝ ።

መፃህፍቱን አንስቼ ከዕሀፈት ጠረጴዛው ላይ በቁመት ደረደርኳቸውና አቀማመጣቸውን ለማየት ሀር እንዳልኩ ተከታትለው ወደቁ ። ጠረጴዛው ላይ የነበረ አንድ ትንሽ የአበባ ማስቀመጫ ከወለሉ ላይ ወርዶ ሲከሰከስ የሆነውን አጣሁ ። ጥፋቱ እንዳይታወቅበት እንደሰጋ ሕፃን አይኔን ወደ በሩ መረመርኩት ። ስብርባሪውን ልቅም አድርጌ በአንድ ኤንቬሎፕ ውስጥ ከከተትኩት በኋላ ከጠረጴዛው ጀርባ ደበቅኩት ።

መፃህፍቱን ይዝ ወጣውና ቤተ መፃህፍቱ ውስጥ ደረደርኳቸው ። ለማክሲም ሳሳየው ፈገግ ብሎ "አይ ቢያትሪስ ፡ እንዴት ፍቅር ብትጥይባት ነው እባክሽ? መፅሀፍ የሚሉት ነገር በአይኗ ማየት እንኳ ይቀፋታል እኮ" አለኝ ።

"በነገራችን ላይ" አልኩ አንድ የከነከነኝ ነገር ስለነበር ዕድሉን ለመጠቀም ፈልጌ "ስለ እኔ ምንም ነግረውህ አያውቁም?"

"እዚህ እኛ መጥታ ሳለ? ምንም አልነገረችኝም"

"አይ ከዚያም በኋላ ቢሆን ፡ ወይ በደብዳቤ..."

t.me/OLDBOOKSPDF

''እኔና ቢያትሪስ እኮ ተግፅፈንም አናውቅ ። እንዲያው አንዳንዴ ቢተሰባችንን የሚመለከት የጎላ ጉዳይ ካልገጠመን በስተቀር ደብዳቤ መግባቱ ምን ዋጋ አለው ብለሽ፣ በከንቱ ጊዜ ማጥፋት ነው ።''

አሃ! አልኩኝ በልቤ እኔ ትልቅ ጉዳይ አያደለሁም ማለት ነው፣ የሚል ጥርጣሬ አድሮብኝ ። ቢያትሪስ ቢጠሉኝ ወይም ለወንድማቸው የማልገባ አድርገው ቢገምቱኝ ይሆናል እንጂ ሰለ ወንድማቸው ሚስት እንደኔት አንድ ሁለት ቃላት መሰንዘሩ ይሳናቸዋል አሰኝኝም ። መለስ ብዬ ደግሞ የማይወዱኝ ከሆነ ለንደን ድረስ ሄደው ምርጫዬን ፈልገው መግሀፋቱን እንዲገዙ ማን አስገደዳቸው? በማለት እኔው ያመጣሁትን ጥርጣሬ እኔው አነሳሁት ።

በማግስቱ ፍሪዝ የሰዓት ቡናችንን ከአተረጉሙልን በኋላ ወደ ማክሰም ጠጋ ብለው ''ጌታዬ ፡ መልካም ዕድልም ከሆነ አንዴ ባንጋገርምት?'' አሉት ። የማክሰምን ስምምነት ካገኙ በኋላ ሽማግሌው ተጠል አድርገው ''ሚስዝ ዳንቨርስና ሮበርት ትንሽ ግጭት ፈጥረዋል መሰለኝ'' አሉ ።

''ምን አጋጫቸው ይግሞ?'' በማለት ማክሰም ሲጠይት እኔ ደግሞ እንዲህ አይነቱ ሁኔታ ሲፈጠር እንደማደርገው ሁሉ ጀስፐርን ለማሻሸት እጄን ሰደድ አደረግኩት ።

''ይኸውልዎት ጌታዬ ፡ ነገሩ እንደዚህ ነው ። ማሪፊያ ክፍሉ ውስጥ የነበረው አንድ ውድ የአበባ ማስቀመጫ ስለጠፋ ሚስዝ ዳንቨርስ ሮበርትን ሰርቀሃል ወይም ሰብረህ ደብቀሃል ትለዋለች ። ሮበርት ደግሞ ፊዕሞ ባልዋልኩበት ነው የተጠረጠርኩት ብሎ ዕብድ ሆኗል ። ሲነግረኝ እንባ እየተናነቀው ነበር ። ጌታዬና እመቤቱ ልብ አላሉት እንደሆነ እንጂ በምላ ሰዓትም እኮ በጣም ልውጥውጥ ብሎ ነበር ።''

''አዎን ፡ ልክ ነህ እባክህ ። ጥብሱን ሳያቀርብልኝ ባዶ ሳህን ለምን አሳቀፈኝ ብዬ ገርሞኝ ነበር ። እንግዲያው እርሱ ይሀን ያህል ከተከራከረ ጥፋተኞቹ ሌሎች ሠራተኞች ይሆናሉ ።''

''አይደለም ጌታዬ ፡ ሚስዝ ዳንቨርስ የአበባው ማስቀመጫ አለመኖሩን ያየችው ክላሪስ ገብታ ክፍሉን ከማደራጀቷ በፊት ነው ። ከዚያ በፊት ደግሞ ከእመቤቱና ከሮበርት ሌላ ዝርም ያለ የለም ። ግራ የገባው ነገር እኮ ነው ጌታዬ''

''እስቲ ሚስዝ ዳንቨርስን ጥራልኝና ነገሩን ከሥሩ ልስማው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የሠነበ ሠነና ዕቃው የቅሟው ነው?''

''እዚያ ዕህፈት ጠረጴዛው ላይ የሚቀመጠው መርቅማው የአበባ ማስቀመጫ እነ ነው ጊታዩ''

''መልእክ ገብርኤል! እንያ ፣ ያማ አሉን ከምንላቸው ውድ ንብረቶቻችን አንዱ እነ ነው ። አያያረግም ፣ አያያረግም ። በል ሚስዝ ዳንቨርስን በአስቸኳይ ጥራልኝ ።''

''እሽ ጊታዩ'' ብለው ፍሪዝ ሲወጡ ማክሲም ወደኔ ዞር ብሎ ''ምን አያነት ጉድ ነው? እንያት ያለ ውድ ዕቃ መሰለሽ? እንዲህ አያነቱን ነገር እኔ ዘንድ አንጠልጥለው መምጣታቸው ምን ይባላል ? ይሄ እነ ያንቺ ድርሻ ነው የኔ ፍቅር'' አለኝ በለዘብታ ።

እውሰጠ በሚሰማኝ ግለት ፊቱ ምን ያህል እንደቀላ ይታወቀኝ ነበር። ''ያቅርታ የኔ ጊታ ፣ እኔ እንኳን አስቀድሚ እንግርሃለሁ ብዬ ነበር። ረሳሁት ። ዕቃውን እኔ ነኝ ትናንት የሰበርኩት ።'' አልኩት ፈራ ተባ እያልኩ ።

''እኔ ነኝ የሰበርኩት? ታድያ ፍሪዝ እያለ ለምንድነው ያልተናገር ሺው?''

''እኔ እንጃ ፣ ድስ አላለኝም ። ከጅል ይቆጥሩኛል ብዬ ፈርቼ ነው።''

''ይልቅስ አሁን ነው ከጅልም ጅል አድርጎ የሚቆጥርሽ ። በይ አሁን ፍሪዝና ሚስዝ ዳንቨርስ ሲመጡ እንድትነግሪያቸው ።''

''አይ እኔ አልናገርም ። እባክህን ማክሲምዬ እኔ ወደፎቅ ልውጣና አንተ ንገራቸው ።''

''ምን ነካሽ አንቺ ሴትዮ? እንዲህ ስትሆኚ ቢያዩሽ የፈራሻቸው እየመሰላቸው ሁሉም ናቅ አድርገው ነው የሚጥሉሽ ።''

''አዎና አፈራቸዋለሁ ። ማለቴ መፍራት ሳይሆን...ብቻ...''

በሩ ተከፈተ ። ሚስዝ ዳንቨርስና ፍሪዝ ገቡ ። ''ነገሩ ሁሉ ስህተት ነው ፣ ሚስዝ ዳንቨርስ ። የአበባ ማስቀመጫውን የሰበረችው ሚስዝ ደዊንተር ባለማወቅ ነው ። አለመናገሯ ደግሞ ስለረሳችው ነው ።'' አለ ማክሲም ።

ሁሉም አይናቸውን ሲተክሉብኝ ይበልጥ በሀፍረት ሽምቅቅ አልኩኝና የሚስዝ ዳንቨርስን አይኖች እያየሁ ''ይቅርታ ፣ እኔ ነኝ ጥፋተኛዋ ። ሮበርት እንዲህ ችግር ውስጥ ይገባል ብዬ አላሰብኩም''

t.me/OLDBOOKSPDF

አልኳቸው ።

"ለመሆኑ ሰባራውን መጠገን ይቻል ይመስልዎታል እሜቴ?" በማለት ሚስዝ ዳንቨርስ ጠየቁኝ ።

"አይ አይመስለኝም ። ድቅቅ ብሎ ነው የተሰባበረው" ይህን እንዳልኩ ማክሲም ጣልቃ ገባና "ስብርባሪዎችንስ የት አደረግሻቸው?" ሲል ጠየቀኝ ። ቃሉን እንደሚሰጥ እስረኛ ሁኔታዬ ለራሴ እየነገረመኝ "ኤንቬሎፕ ውስጥ" በማለት መልስ ሰጠሁ ።

"ኤንቬሎፑንስ?" ለሚለው የማክሲም ድጋሚ ጥያቄ ያስተመጥኩበትን ቦታ ተናገርኩ ። ማክሲም ጥያቄዎችን ሲሰነዝር የመገረም ምልክት ይነበብበት ነበር ። አሁንም ፈገግ ብሎ "አየሽ ሚስዝ ዳንቨርስ ፡ ሚስዝ ደዊንተር እኮ ዘብጢያ የምታወርጃት መስሏታል ። እንግዲህ ስብርባሪዎችን እያቸውና የሚጠገኑ ከሆኑ ሎንዶን ላኪያቸው ፡ ተስፋ ከሌላቸውም መላል ነው ። በል አንተም ፍሪዝ ሮበርትን ሂደህ አይህ በለው" ብማለት አሰናበታቸው ።

ፍሪዝ ሲወጡ ሚስዝ ዳንቨርስ መደኃላ ቀረት ብለው "እኔ እራሴ አውኑኑ ሮበርትን ይቅርታ መጠየቅ አለብኝ ። እንዴት ብዬ ሚስዝ ደዊንተር ሰበሩት ብዬ ልጠርጥር? ወደፊት ግን እንዲህ ዓይነቱ ነገር ሲፈፀም እመቤቴ ለኔው በቀጥታ ቢነግሩኝ ብዙ አስመላሳቶችን ሊያስወግድልን ይችላል ።" አሉና የማክሲምን የማረጋገጫ ሀሳብ ይጠብቁ ይመስል እዚያው ቁመው አይናቸውን እንደተከለቡት ቀሩ ።

"ልክ ነሽ ሚስዝ ዳንቨርስ ። ትላንትናውኑ መናገር ነበረባት ። ይህንኑ እየነገርኳት ነበር እናንተ የመጣችሁት" አለ ማክሲም

ሚስዝ ዳንቨርስ አይናቸውን ወደኔ አዙረው "ምናልባት እመቤቴ ዕቃው ምን ያህል ውድ እንደሆነ ባያውቁ ይሆናል" አሉ

"አይ እርሱን እንኳን አውቁአለሁ ። ለዚህ አያደለም እንዴ ስብርባሪዎችን በጥንቃቄ የሰበሰብኳቸው?" አልኩ ሳውንቱ እየተሸማቀቀ ።

"ከዚያም ማንም እንዳያያቸው ከጠረጴዛ ጀርባ ደበቅሻቸው ፡ አይደል?" አለ ማክሲም ፈገግ ብሎና ትከሻውን እየነቀነቀ ። "ልክ አንዳንድ አገልጋዮች እንደሚያደርጉት እኮ ነው ፡ አይደለም እንዴ ሚስዝ ዳንቨርስ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

“ይቅርታ ያድርግልኝና የኔ ጌታ ፡ የእንግዳ ቤቱን ልዩ ልዩ ውድ ዕቃዎች እንድትነካ ለየትኛዉም አገልጋይ በፍፁም ተፈቅዶላት አታውቅም” አሉ ሚስዝ ዳንቨርስ አንገታቸውን አየሰበቁ ።

“አምን ይገባኛል ፡ አንቺ ድርሽ እንደማታደርጊያቸው መች አጣሁት” አለ ማክሲም

“እንዲያው መጥፎ አጋጣሚ ሆነና እንጂ እንዲህ ያሉ ውድ ዕቃዎች መች ተሰብረው ያውቃሉ? መሬቱ ይቅለላትና ሚስዝ ደዊንተር በነበረችበት ወቅት አብረን ነበር የምናዉጻቸው ። ከዚያም በኋላ ከእኔ ሌላ ማንም ነክቷቸው አያውቅም” በማለት ሀሳባቸውን አጠናከሩ አሮጊቷ ።

“አሁን እንኳን አንደ ሆኗል ። ምንም ማድረግ አይቻልም” አለና ማክሲም ሚስዝ ዳንቨርስን አሰናበታቸው ።

ሴትዮዋ ሲመጡ ማክሲምም ወደ ጋዜጣው ተመለሰ ። ፀጥ ፡ ፀጥ ሆነ። ጥቂት ቆይቼ “ይቅርታ የኔ ፍቅር ፡ መፃህፍቱን እደረድራለሁ ብዬ እኮ ነው ዕቃው የተሰበረው ። በጥንቃቄ አድርጌው…” እንዳልኩ ማክሲም አቋረጠኝና ።

“በቃ እኮ አርሺው ፡ ወለላዬ ። ይህን ያህል ምን ያሳስባል?” አለኝ ።

“ያሳስባል እንጂ ፡ መጠንቀቅ ነበረብኝ ። መቼም ሚስዝ ዳንቨርስ እንደተናደዱብኝ ይሰማኛል ።”

“እርሷ ደግሞ የምን ቤት ነኝ ብላ ነው? ዕቃው ንብረቷ አይደለም”

“ቢሆንም ፡ ዕቃዎቿን በጣም የሚወዷቸው መሰለኝ ። ከዚያም በላይ እስከዛሬ አንድም ዕቃ ሳይሰበር ኖሮ በእኔ መጀመሩ ነው የሚያበሳጨኝ”

“ያ ምስኪን ሮበርት ከሚሰብረው አንቺ መስበርሽ ይሻላል ።”

“እሪ እላክህ እርሱ ቢሆን ይሻላል ። ሚስዝ ዳንቨርስ ምኔም ይቅር የሚሉኝ አይመስለኝም ።”

“ምን ማለትሽ ነው? ሚስዝ ዳንቨርስን ሞራሽ ፈጣሪሽ እደረግሻት እንዴ? እሪ እዚያ እንውርወስ ያውርዳት ። ለመሆኑ ምኗ ነው የሚያስፈራሽ?” ጮኸብኝ ማክሲም ።

“በእርግጥ እፈራቸዋለሁ ስል… ፍርሐት ማለቱ ሳይሆን …ብቻ እኔ እንጂ ልገልፀው የማልችለው ስሜት ነው የሚሰማኝ ።”

“እንዴት ያለ ግራ የገባው ነገር ነው የምታወሪው? ዕቃው

t.me/OLDBOOKSPDF

ሲሰበርብሽ ጠርተሻት ይኸውልሽ ይህ ዕቃ ተሰብሯልና አስጠግኂው ብትያት ኖሮ ትዕዛዝሽን በሚገባ ማክበር ስትችል እንቺ ግን ቅድም እንዳልኩት ልክ እንደ እንዲት ሠራተኛ ወስደሽ ደበቅሽው ። የቤቱ እመቤት መሆንሽን መዘንጋት የለብሽም ።''

''አይ ፡ እኔ በብዙ ነገሮች እንደ ሠራተኞቹ ነኝ ። ለዚህም ነው ከክላሪስ ጋር በብዙ ነገሮች የምንመሳሰለው ። እርሷም ይህን ያህል የምትወደኝ ለዚህ ይመስለኛል ። ባለፈው ጊዜ እናቷን ልጠይቃቸው ሄጄ 'ለመሆኑ ክላሪስ ከኛ ጋር መኖሩን ወዳዋለችን?' ብዬ ብጠይቃቸው ምን እንዳሉኝ ታውቃለህ? 'እረ በጣም ነው የተስማማት ። እንዲያውም እንደ እመቤቱ ሳይሆን ልክ እንደኛው አድርጓ ነው የማያቸው አለችኝ' አሉኝ ። ታድያ ይህ አባባል ምን ማለት ይመስልሃል?''

''ይህማ እንዴት ይሆናል? አጥንት የሚሰብር ስድብ አይደለም እንዴ? እንቺ በምንሽ ነው እነሱን የምትመስዪው? የናቷን ቤት አይተሽ ላት የለም? እላያቸው ላይ ሊወድቅ ከመቃረቡ በላይ አዛባ አዛባ አይደል የሚሸተው? አንድ ጊዜማ ሴትዮዋ ማቲውን ፈልፍላ እንዴት ሁነው ይኖሩ እንደነበረ እግዚአብሔር ይወቀው? እርሷ እራሷ ሞንቅላቷ ላይ እስቶኪንጎን ጠቅልላ በባዶ እግሯ ማሳው ውስጥ ስትርመጠመጥ እንዴት ነበር የምታስጠላው ። ይህች ክላሪስ ግን እንዴት እንዲህ ንፁህ ልትሆን እንደቻለች ፍፁም አይገባኝም''

''እርሷ እንኳን ከአክስቷ ጋር ነበር የምትኖር'' በማለት በዝግታ ከነገርኩት በኋላ ቀጠል አድርጌ ''በርግጥ ያ ፍላኔል ቀሚሴ ከፊት ለፊቱ የማይለቅ ቁሻሻ ነገር ቢኖርበትም እኔ ግን ሞንቅላቱ ላይ እስቶኪንግ አልጠቀልልም ። በባዶ እግሬም አልሄድ ። በሌላ ወገን ደግሞ የአቡኑ ባለቤት እንዴም የኛ ሰው ነሽ ብለውኝ አያውቁም'' ስለው

''ታድያ ያንን ቁሻሻ ቀሚስ እየለበስሽ እንደሆነ የምትጎበኚያቸው በፍፁም እንዲያ የሚሉሽ አይመስለኝም'' አለኝ ።

''ለነገሩ እንኳን ቆንጆውን ረጅሙን ቀሚሴን ነበር የለበስኩት ። ያም ሆነ ይህ ሰውን በአለባበሱ የሚገምት ሰው ደካማ አስተሳሰብ ያለው ነው ባይ ነኝ ።''

''አሮጊቷ እንኳን በፍፁም በእንዲህ ዓይነቱ አመለካከት የሚጠረጠሩ አይመስሉኝም ። ምናልባት ያኔ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰው ቤት አብረን በሔድንበት ወቅት እንዳደረግሽው ወንበሩ ጠርዝ ላይ ተቀምጠሽ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

አንገትሽን ቀብረሽ ፡ ለምትጠየቂው ሁሉ 'አዎን' 'አይ' ብቻ እያልሽ ስትመልሺ ሴትየዋ ግራ ተጋብተው ይሆናላ''

''አይን አፋርነቱንማ ላስወግደው የማልችለው ጠባዬ መሆኑን እያወቅህ?''

''መቼ አጣሁት? ለማስወገድ ሞራሽን ጥረት አታደርጊም እንጂ''

''እንዲህ ማለትህ እንኳ ተገቢ አይመስለኝም ። የማልጥርበት ጊዜ የለም ። ከእንግዶች ጋር በተገናኘሁ ቁጥር አንድም ቀን ጥረት ሳላደርግ ቀርቼ አላውቅም ። እንተ ያደግክበት ፡ የኖርክበት ስለሆነ እንግዳ ላይሆንብህ ይችላል ። ለኔ ግን ሁሉም ነገር አዲስና ግራ የሚያጋባ ነው የሚሆንብኝ ። ይህንን ነው እንግዲህ ልትረዳልኝ ያልቻልክው ።''

ማክሲም ሳይታወቀው ድምፁ የቁጣ ቃና ተላበሰ ''ምኑን ከምን አገናኘሽው? ይህ ከአስተዳደግ ጋር በፍፁም የሚገናኝ አይደለም ። ሁኔታዎችን በቅጡ ተገንዝቦ ተገቢውን ምላሽ የመስጠት ጥያቄ ነው ። እኔ በየሰው ቤት የምሄደው ወድጄ መሰለሽ? ምን ያህል እንደሚያሰለቸኝ ባወቅሽልኝ ። ሆኖም ግን ከሰዎች ጋር እስክኖርን ድረስ የግዴታ ማድረግ ያለብን ነው።''

''ቁም ነገሩ መች መሰላቸቱ ሆነና? ለመሰላቸቱ ቅንጣትም ደንታ አልነበረኝም ። እኔን ያንገፈገፈኝ ሰው ሁሉ ከአግር ጥፍሬ እስክ አራስ ፀጉሬ መመልከቱ ነው።''

''ማን ነው ደግሞ እንዲህ የሚመለከትሽ?''

''ማን ማን ልበልህ? ሁሉም ነዋ ። ልጅ አዋቂው ፡ ሴት ወንዱ ፡ ሲገመግመኝ አይደል እንዴ የሚውለው? ለሽያጭ እንደቀረበ ፈረስ ከንፈሬን በልጥጠው ጥርሴን ማየት ነው የሚቀራቸው ።''

''ቢያዩሽ ምን አለበት? ለክፋት ያሉት ሳይሆን ደስ ቢላቸው ይሆናል''

''እንዴ? አሻንጉሊት እመስል እኔ ነኝ እንዴ መደሰቻቸው? ለምንስ ሥጋዬን ሲቦጭቁት ይኖራሉ?'' አልኩኝ ቆጣ ብዬ ።

ይህን ጊዜ ማክሲም ቀዝቀዝ አለና ''አየሽ ፡ የዚህ አካባቢ ሰዎች በዚህ በዚህ ካልተገናኑ ሌላ ምን መዝናኛ አላቸው ብለሽ?'' አለኝ ።

''በዚህ አይነት ማ ምኑን መዝናኛ ሆንኳቸው? የአይን በሽታ እንጂ'' አልኩት አንጀቱ እያረረ ጥርሴ ግን በምፀት እየፈገገ ። ማክሲም ግን መልስ ሳይሰጠኝ አይኑን ወደ ጋዜጣው ሲመልስብኝ ''የአይን በሽታ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሆንኩባቸው ነው እኮ የምልህ'' በማለት ተጠልኩ ''አንተም ሆን ብለህ ለዚሁ ሳይሆን አይቀርም ያገባኸኝ ። ፈዛዛ ፡ ዝግ ፡ ምንም ልምድ የሌለኝ መሆኔን ስለምታውቅ በኔ የመጣ ምንም ዓይነት አሉባልታ አይቀሰቀስብ ኝም ብለህ ስለገመትክ ይሆናል ''

ማክሲም ጋዜጣውን ወርውሮ ብድግ አለ ። ''ምን ለማለት ፈልገሽ ነው?'' ሲል አፈጠጠብኝ ። መልኩ ፡ ድምፁ ሁሉ የእርሱ አልመስልሽ አለኝ ።

''እኔ እንጃ'' አልኩት ወደ ኋላ እየተለጠጥኩ ''ይሀን ያህል እንዲህ የሚያደርግ እንግዳ ነገር ተናገርኩ እንዴ?''

''እዚህ አካባቢ ስላለው አሉባልታ ምን የምታውቂው ነገር አለና ነው?'' ሲል በአይኑም በምላሱም አጣደፈኝ ።

''ኧረ እኔ ምኑንም አላውቅም ። እንዲያው እንደመጣልኝ ነው የተናገርኩት ። እባክህን ማክሲም ፊትህን እንዲህ አታጨልምብኝ! እንዴ! ምንድነው ነገሩ!

''ለመሆኑ ምን ምን ብለው አወሩልሽ?''

''ኧረ እባክህ ፡ ማንም ምንም አላወራልኝም''

''ታድያ ይሀን ሀሳብ ከየት አመጣሽው?''

''እየነገርኩህ? ንዴቱ ቢበዛብኝ ዝም ብዬ ተናገርኩ እንጂ ምኑንም አውቂው አይደለም ። የሰው ሁኔታ ቢያበሳጨኝ ፡ አንተ ደግሞ አይን— አፋርነቴን እየጠቀስክ ብትወቅሰኝ እንጂ የተለየ ምክንያት ኖሮኝ አይደለም ማክሲምዬ'' በማለት አለማመጠው ገባሁ ።

''እንግዲያውስ የተናገርሺው ተገቢ ይመስልሻል?''

''አይደለም ፡ እሺ ይቅርታ አድርግልኝ''

እጆቹን ኪሶቹ ውስጥ ክቶ ፡ በተረከዙ ቁሞ ፊትና ኋላ ያወዛወዛል እትኩሮ እየተመለከተኝ ለራሱ ያወራ ይመስል ''ለካስ እራስ መዳድነት ከፉኛ ቢጠናወተኝ ነው አንቺን ያገባሁት ።'' አለኝ ።

ድንገተኛ ሐዘን ልቤን ሰርስሮት ገባ ። ''ምን ማለትህ ነው?'' ብዬ ጠየቅኩት በሰለለ ድምፅ

''አቻሽ አይደለሁማ! በመካከላችን የተጋረጠው ሰፊ የዕድሜ ገደብ አቻነቱን ነፍጎናላ! ግማሹን የዕድሜ ዘመኑን አካቶ ወደ መታብር የሚያሽቆለቁል የኔ ብጤውን ከማግባት ይልቅ እኩያሽን እስክታገኚ

t.me/OLDBOOKSPDF

መቆየት ነበረብሽ ማለቱ ነዋ!''

ድምጼን ከፍ አድርጌ ''በፍፁም ልክ አይደለህም'' ብዬ ብድግ አልኩ ''የዕድሜ ልዩነት በጋብቻ ላይ ምንም ተጽዕኖ እንደሌለው እያወቅክ?'' በማለት እጆቼን በአንገቱ ዙሪያ ጠምጥሜ ። ''ለምንድነው እንዲህ ነፍሴን የምታሰጨንቃት? በዚህ ምድር ላይ ካንተ ይበልጥ የምወደው እንደሌለ ታውቃለህ ። አባቴ ፡ ወንድሜ ፡ ልጄ ፡ ሁሉ ነገሬ አንተው ነህ ። ካንተ ሌላ ምን አለኝና ነው እንዲህ የምትለኝ?'' ስለው ።

ከአንጀቱ ሳያዳምጠኝ ''እየነገርኩሽ? አንቺ ምን አጠፋሽ? ጥፋቱ ያለው እኔ ዘንድ ። ጥቂት የማሰቢያ ጊዜ ሳልሰጥሽ አጣደፍኩሽ'' አለኝ ።

''ምንም የማስበው ነገር አልነበረም ። ሌላ ምርጫ አልነበረኝምና ። እንዴት ብዬ ልግለፅልህ ማክሲምዬ? ፍፁም ልትረዳልኝ አልቻልክም እኮ። ሰው በፍቅር ሲጠመድ ...''

''እዚህ ከመጣሽ ወዲህ አንዳንዴ እንዲህ ከስተሽ ፡ ፊትሽ ገርጥቶ ሳይሽ ኑሮው የተስማማሽ ስለማይመስለኝ እኮ ነው''

''እንዴት አልተስማማሽም ትለኛለህ ማክሲምዬ? አካባቢውን ፡ አየሩን ፡ በአጠቃላይ የማንደርሌይን ኑሮ በጣም ነው የወደድኩት ። ሰውን ስለመጎብኘትም ከሆነ አንተን ደስ ካለህ በየዕለቱ ባደርገውም ግድ የለኝም ። አንድ ነገር ደግሞ ተረዳልኝ ። እኔ አንተን በማግባቴ ቅንጣትም ፀፀት እንዳላደረብኝ ልታምነኝ ይገባል የኔ ፍቅር''

በሀሳብ እንደተመሰጠ ጉንጩን መታ መታ ካደረገ በኋላ ጎንበስ ብሎ ግንባሬ ላይ ሳመኝ ''አይ አንቺ ፡ የምትገርሚ ነሽ ። ከኔ ጋር መኖር በጣም ከባድ ነው አይደል?'' ሲል ጠየቀኝ ።

''በፍፁም'' አልኩት ተቻኩዬ ''ካንተ ጋር መኖር ከገመትኩት በላይ ነው ቀላል ሆኖ ያገኘሁት ። ጋብቻ ሲባል በጣም አክብጄ ነበር የማየው ። ሰካራም ወይም ነገናዛ ወይም ተሳዳቢ በአጠቃላይ ምናምኑም የማይጥም ባል ይገጥመኝ ይሆን? እያልኩ ከፉኛ ነበር የምጨነቀው። ታድያ አንተ ከዚህ ሁሉ መጥፎ በሽታ የፀዳኸው ሰውዬ ምንህ ነው አስቸጋሪ?''

''እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁንና ከዚህስ አድኖኛል'' አለና ፈገግ ሲልልኝ አፀፋውን መልሼለት ሁለቱንም እጆቹን አገላብጬ ሳምኳቸው ። ''እንዲህ እየተፋቀርን ፡ እንዲህ እየተቀራረብን ፡ እቻ አይደለንም

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚለው ጥያቄ መነሳት የሚገባው ነው? ዘወትር እንዲህ በደስታ ሰጥ መን ለሚያየን በፍቅር ያረጀን የብዙ ጊዜ ባለትዳሮች አያደለም እንዴ የምንመስለው? ታዲያ በመጋባታችን ተሳስተናል የምትለው እንዲሁ ለማለት ያህል እንጂ ከአንጀትህ ነው ማክሲምዬ? ከኛ በላይ ደስተኛ አለ? ጋብቻችንስ የሰመረ ጋብቻ አይደል?" አልኩት ከአይኖቹ ዘልቁ ውስጣዊ ስሜቱን እየፈተሽኩ ።

"ካልሽ ደግ" አለኝ ።

"እኔ ብቻ ነኝ እንዴ የምለው? አንተም ልትለው ፡ ልታምንበት ይገባል ። ደስተኞች ነን ፡ በጣም ደስተኞች ነን በለኝ እንጂ ፍቅሬ?" ስል ተማፀንኩት ።

መልስ ነፍጎኝ በመስኮት ደጅ ደጁን እንዳየ ቀረ ። እጆቹን እንደያዝኩ ጥቂት ከታገስኩ በኋላ "ምንድነው ዝምታው? ለምን መልስ አትሰጠኝም?" አልኩት ።

ጉንጮቹን በሁለቱም እጆቹ ይዞ አይን አይኔን እየተመለከተ "ምን ብዬ ነው የምመልሰው? እኔ ምኑንም አላውቀው ። ደስተኞች ነን ካልሽ ደስተኞች ነን ብለን ነገሩን በዚው ብንቀርጠው አይሻልም?" አለኝና እንደገና ስሞኝ ራቅ ብሎ ሄደ ።

"ይህን ሁሉ የምትለው ከአንጀትህ እንዳልሆነ ይገባኛል ። ብስለት የጎደለኝ ፡ ባላገር ብጤ ፡ አለባበሴ ከርፋፋ ፡ አይነ—አፋርነት የሚያጠቃኝ በመሆኔ የአንተንና የማንደርሴይን ክብር የማጎድፍ አድርገህ እንደምትቆጥረኝ አውቃለሁ" አልኩት ።

"ምነው እንዲህ አይነቱን የማይረባ ነገር መዲያ ብትይልኝ ። እኔ ባላገር ነሽ ፡ ከርፋፋ ነሽ ወጣኝ? ዝም ብለሽ አንቺው የፈጠርሽው ቅዠት ነው ። አይነ— አፋርነቱንም ቢሆን ልታስወግጂው እንደምትችይ ቀደም ብዬም ነግሬሻለሁ ።"

"ተሽከርክረን ወደተነሳንበት ነጥብ ተመለስን አይደል? ይህን ሁሉ የቆሰቆሰው ያንን የአበባ ማስቀመጫ መስርፌ ነው ። ማስቀመጫው ባይሰበር ኖሮ ይህን ጊዜ ..."

"ለምን ድምጥማጡ አይጠፋም ። ይህን ያህል የሰው ነፍስ የጠፋ አድርጌ የወሰድኩት መሰለሽ እንዴ?"

"ማን ያን ያህል ውድ ዕቃ ነበር ማለት ነው?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እኔ እንጃ ፡ ይሆናላ ። ብቻ ምን ያህል ዋጋ እንደነበረው እንኳ ረስቼዋለሁ ።" አለ ማክሲም ነገሩን በአጭሩ ለመቅጨት በማሰብ ። እኔ ግን የማይረቡ ጥቃቅን ጥያቄዎችን እያነሳሁ አስጨነቅኩት ። በመጨረሻም ዕቃው ከየት እንደመጣ ስጠይቀው ፦

"የርብቃ የጋብቻ ስጦታ ሳይሆን አይቀርም" አለኝ

ስሚን ሲጠራው መብረቅ የመታኝን ያህል ከው አልኩ ። አቀርቅሬ ጣቶቼን ማፍተልተል ጀመርኩ ። ለአንድ ደቂቃ ያህል ፀጥ ብዬ ከተቀመጥኩ በኋላ ማክሲምን ቀና ብዬ አየሁት ። አይኑን እፊት ለፊቱ ተክሎ በትካዜ ሰጥሟል ። የርብቃ ትዝታ ቢጋረጥበት ነው ብዬ አሰብኩ ። ስለ ስጦታው ዕቃ ፡ ማን እንዳመጣው ፡ ርብቃ ተቀብላ ስታሳየው ፡ የአበባውን ማስቀመጫ በእጅጅቸው መሐል አውለው የፍቅር ፈገግታ ሲለዋወጡ ፡ ልባቸው የደስታ ከበሮ ሲደልቅ በአይነ ህሊናው ቢታየው ነው አልኩኝ ። ከሁሉም በላይ የእኔ የጋብቻ ስጦታ የርብቃ የጋብቻ ስጦታ እንዲሰበር ምክንያት መሆኑ አስደነቀው ወይስ አበሳጨው? አልኩና "ማክሲም ምን እያሰብክ ነው?" በሚለው ጥያቄዬ ፀጥታውን አደፈረስኩት ።

"ምንም ፡ ግን ለምን ጠየቅሺኝ?" በማለት ጥያቄዬን በጥያቄ መለሰው ።

"አይ ፡ ርሳህ ፡ መጥቀህ በሐሳብ ጭልጥ ብለህ የነጎድጓ ስለ መሰለኝ"

"ነው?" አለና ሃይ አምስተኛውን ሲጋራ አቀጣጠለ—በማግሽ ቀን መሆኑ ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አሥራ ሁለት

ሰኔ መጨረሻ ላይ ማክሲም ለስራ ጉዳይ ወደ ሎንዶን ሄደ ። እደጅ ድረስ ወጥቼ ስሸኘው ከሁለት ቀናት በኋላ ተመልሶ የሚመጣ ሳይሆን ለዘላለሙ ተለይቶኝ የሄደ ነው የመሰለኝ ። ፍርሐት ገባኝ ፤ ጭንቅ አለኝ ። ጭራሽ በሰላም ይመለሳል አላልኩም ። አደጋ የሚገጥመው ፡ ሞቱን የሚያረዱኝ እየመሰለኝ ክፉኛ ተረበሽኩ ።

እንዲያው ለስሙ ገበታ ልቅረብ እንጂ ምሳዬን ፍፁም ሳልነካው ተነሳሁ። ከቅትር በኋላ መናፈሻው ውስጥ ከአንድ ዛፍ ስር ቁጭ ብዬ መፅሐፌን ዘረጋሁ ። መፅሐፉ ይገለጥ ፡ አይኔም ያፍጥ እንጂ አንዲት ገጽ እንኳን ማንበብ አልቻልኩም ። ጥቂት ቆይቶ ሮበርት እየገሰገሰ ወደኔ ሲመጣ "ወይኔ አምላኬ ፡ ምን ልታሰማኝ ይሆን?" እያልኩ አይኔን ተከልኩበት ። ልቤ ደረቴን ፈንቅሎ ለመውጣት ሲጣደፍ "እሜቴ ፡ ጌቶች ከአስር ደቂቃ በፊት ገብተዋል ብለው አንድ ሰውዬ ደውለው ነገሩኝ" አለኝ ሮበርት ።

ከደስታ ብዛት መፅሐፉን እንዴት እንደዘጋሁት ፡ እንዴት እንደዘለልኩ አላውቀውም ። ብቻ "አመሰግናለሁ ሮበርት ፡ ማክሲም እንዴት እንዲህ ቶሎ ደረሰ?" ማለቴ ትውስ ይለኛል ። ጥሪው ማክሲም በሰላም መግባቱን ለማብሰር እንደሆነና ምንም የተለየ መልዕክት እንደሌለ ሮበርት ከነገረኝ በኋላ አመሰግኜ አሰናበትኩት ።

እፎይ አለ ሁለመናዬ ። ወዲያው ወደ ምግብ ቤት ገብቼ ጥቂት ብስኩቶችንና አንድ ፖም ይዤ ወጣሁ ። እቤት ውስጥ የተዘጋጀው ምግብ ባይጥማት ብስኩት ትበላለች ብለው ሠራተኞቹ ለወጥ ቤቷና ለሚስዝ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዳንቨርስ እንዳይነግሩብኝ ሠግቼ ዛሬቼ ውስጥ ተደብቄ በላሁ ።

የማክሲምን በሰላም መድረስ ከሰማሁና ብስኩቶቼን ከበላሁ በኋላ ልዩ የደስታና የነፃነት ስሜት ነው የተሰማኝ ። ትናንሽ ልጆች በሰንበት ትምህርት ፡ የቤት ሥራ የሚሉት ጣጣ በሌለበት ሰፊ ጊርቱና ሲፈነጥዙ ሲውሉ የሚሰማቸው ዓይነት ደስታና ነፃነት ነው የተሰማኝ ። ማክሲም ለአፍታ እንኳ እንዲለየኝ የማልፈልገዋ ሴትዮ ዛሬ ከአጠገቤ ሲርቅ እንዲህ መፃረቄ ሊገባኝ አልቻለም ።

እራሴን ልታዘበው ፈለግኩና 'በምን ምክንያት" ? የሚለው ሀሳብ ገታኝ። ምንነቱን ሳላውቀው አንዳች ልዩ ስሜት ወረረኝ ። በእዝነ ልቦናዬ አንሾካሾከብኝ ....

ጃስፐርን አስከትዬ ወደ ፍሰሐ ሸለቆ ተንደረደርኩ ። በአበቦች ተከብቤ እንዲያ ብቻዬን ተጋድሚ መዝናናቱን በእጅጉ ወደድኩት ። ብቸኝነቱ አስደሰተኝ ። ማንም ፡ ማክሲም እንኳን ቢሆን አጠገቤ እንዲኖር አልፈቅድም ነበር ። ወዲያው ደግሞ እንዴት? ማክሲምን? እልና አይ እርሱን መካዴ ፡ በእርሱ መጨከኔ አይደለም ። ማክሲም ሕይወቴ ፡ አለሜ ፡ ተስፋዬ ነው ፡ በምንም የማልለውጠው በማለት ከተጋደምኩበት ፈንጠር ብዬ ተነሳሁ ።

ወደ ባሕሩ ዳርቻ በመጓዝ ላይ ሳለን ጃስፐር እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ ባልተፈቀደለት መንገድ ሲሄድ "ና አንተ ጃስፐር ፡ መንገዱ ወዲህ ነው" ብዬ ጮህኩ ። ቁብም አላለኝ ። "ምንም ማድረግ አልችልም ።ጥፋቱ የኔ አይደለም ። ማክሲም ደግሞ የለም" አልኩና በሄደበት ተከተልኩት ።

ከጎጆው አጠገብ ስንደርስ ጃስፐር በሩን ተጠግቶ ሲያንፈገፍግ "አይ ፡ አሁንስ አበሳሽው ፡ እዚህስ ተከትዬህ አልገባም ። ና ወዲህ" ብዬ ጮህኩበት ። ባሕሩ ዳር ሆኜ ከውሀው ጋር ጥቂት ከተጫወትኩ በኋላ መለስ ስል ጎጆው እፊት ለፊቱ ተደቅኖ ታየኝ ። በዝግታ አዘገምኩ ። 'ምንድነው የሚያስፈራኝ፣ እንደማንኛውም ጎጆ ጎጆ አይደለም እንዴ? እናማ መግባት አለብኝ' ብዬ ከራሴ ጋር የጀመርኩትን ሙግት አልባት ሰጥቼው ወደ በሩ ተጠጋሁ ።

በሩን ነካ አደረግሁት ። ብርግድ ብሎ ተከፈተ ፡ ከው አልኩ ። ባለፈው ጊዜ በደንብ ዘግቼው መውጣቱ ይታወሰኛል ። ምናልባት ሌላ ሰው ከፍቶ ገብቶ ይሆናል ብዬ ሳስብ ጃስፐር እያጉረመረመ ከበሩ ሥር

t.me/OLDBOOKSPDF

ሲያነፈንፍ አየሁት ። "ተው ጃስፐር" ብዬ ብገስፀውም አፍንጫውን ያፋላይ ተክሎ ማነፍነፉን ቀጠለ ። በሩን ስከፍተው ድድቅ ጨለማ ነው ። የአይኔ ብሌን ጨለማውን ሲላመደው ሁሪያዬን ቃኘት አደረግሁት ። ከወትሮው የተለየ አንዳችም ለውጥ አልነበረም ። የግምጃ ቤቱ በር ከፍቱን ነበር ። ጃስፐር እየሮጠ ወደ ግምጃ ቤቱ ሲገባ ተከተልኩት ። ከማነፍነፍ አልፎ ጨኸቱን ሲለቀው አንድ ኮሽ የሚል ድምፅ ሰማሁ ። አመዴ ቡን አለ ። "እረ እባክህን አንተ ጃስፐር ና እንመለስ" አልኩት በጣር ድምፅ ። እርሱ እንደሆነ ባሰበት ። የጃስፐር እንዲያ መቅበጥበጥ ኮሽታውን የፈጠረው አይጥ ይሆናል የሚለው መላምቱን ወደ ጎን እንድጥለው አስገደደኝ ። ጃስፐርን ደጋግሜ ብጠራውም ሊሰማኝ ስላልፈለገ ወደ በሩ ወጣ ብዬ "ማን ነው እዚህ ያለው?" በማለት በባዶው ጨለማ አፈጠጥኩ ።

መልስ አጣሁ ። የጃስፐርን አንገት ይዤ እየጎተትኩት እበሩ ሥር አጎንብሼ አሰሳ ገባሁ ። አይኔ አንድ ነገር ላይ ሲያርፍ እዚያው ውሀ ሆኜ ቀረሁ ። ሰው ይሁን አውሬ አጣርቼ ማየት ባይሆንልኝም አንድ ኩርምት ብሎ የተቀመጠ ፍጡር ለማየቱ ግን እርግጠኛ ነበርኩ ። ከኔ ይበልጥ ድንጋጤ የሚያንዘፈዝፈው ሰው መሆኑ የተከሰተልኝ ዘግይቶ ነበር ። ከፍርሐቱ ብዛት እራሱን በጅልባ ሸራ ሊሸፍን ሲጣጣር አየሁት ወፈፈው ቢን ።

"ምነው ቢን? እዚህ ምን ትሰራለህ?" ብለው አፉን ከፍቶ እኒያ ጅላጅል አይኖቹን እያቁለጨለጨ ጥቂት ከቆየ በኋላ "ማን? እኔ ምን? ምንም ምንም አልፈልግም" አለኝ ።

ጃስፐር እየጮኸ ቢያውከን አንገቱ ላይ ያጠለቀውን ቀበቶ ጠበቅ አድርጌ ይዤ እንዲያርፍ ፈቀድኩለት ። ወደ ቤን መለስ ስል ልቤም መለስ እያልልኝ ነበርና "ታዲያ እዚህ ምን ታደርጋለህ?" አልኩት ትንሽ ደፈር ብዬ ። እንደ ጅል ፈገግ ከማለት ሌላ መልስ ቢነፍገኝ "እዚህ መሆንህ ላንተም ጥሩ አይደለምና ብትወጣ ነው የሚሻለው ። ሚስተር ደዊንተር ማንም ሰው እንዲገባ አይፈቅድም ፡ ይቆጣሃል" ስለው ቀስ ብሎ ብድግ አለ ። በአንድ እጁ አያበለባ አፍንጫውን እየጠራረገ ይስቃል ። እንዴን እጁን ወደኋላው ሲያብቀው አይቼ "ምንድነው የያዝከው ቢን?" ብዬ ጠየቅኩት ። ልክ እንደ ሕፃን ልጅ እጁን ዘርግቶ አሳየኝ —

t.me/OLDBOOKSPDF

የአሣ ማጥመጃ ገመድ ። "ምንም አይደለም ፡ ምንም አልሰራሁም" አለ ቤን እየተርበተበተ ።

"ገመዱን ከዚሁ ነው ያነሳኸው?"

"እህ?"

"አየህ ቤን ፡ የያዝከውን ገመድ የምትፈልገው ከሆነ ለሣሬው ልትወስደው ትችላለህ ። ሁለተኛ ግን እንዳይለምድህ ። የሰው ንብረት መውሰድ ነውር አይደለም እንዴ?" ምንም ሳይናገር ዓይኑን ብልጭ ድርግም እያደረገ መንቀሳቀስ ሲጀምር አስከትዬው ወጣሁ ። የጎጆውን በር ከዘጋሁ በኋላ "እቤትህ ሂድ እንጂ ቤን" አልኩት

ገመዱን ከደረቱ ለጥፎ ይዞ "እብዶች ሐኪም ቤት አታስገቢኝም አይደል?" አለኝ ። መላ አካሉ ነበር የሚማፀነኝ ። አንጀቴን በላው ። እጆቹ ይንቀጠቀጣሉ ። ከላይ እስከ ታች እየተርገፈገፈ አይን አይኔን ሲያየኝ "በፍፁም አላስገባህም" አልኩት በሚያረጋጋ አባባል

"እኔ ምንም አላደረግሁም ። ደግሞ ለማንም አልተናገርኩ ። ምን አጠፋሁ? እብዶች ሐኪም ቤት መግባት አልፈልግም" እያለ እንባውን ዝርግፍ ዝርግፍ አደረገው ።

"ተው በቃ ቤን ። ግድ የለም ፡ ማንም አያስገባህም ፡ ብቻ ሁለተኛ ወደ ጎጆው እንዳትገባ ፡ እሺ?" ብዬው መንገዴን ስቀጥል ተከትሎኝ እጄን ለቀም ሲያደርገው ደንግጬ ዞር አልኩ ። "ይኸውልሽ ቆይ.. አየሽ .. አንድ ... አንድ ነገር ላሳይሽ" አለና ወደ ዳርቻው ተጣደፈ ። ተከተልኩት ። ከአንድ ቋጥኝ ስር ተንበርክኮ አንዱን ድንጋይ ፈነቀለው ። ከዛኦች ስብስቡ አንዱን አንስቶ "ይሄ ... ይሄ ለአንቺ ... ውሰጂው" ብሎ ሰጠኝ ።

"አመሰግናለሁ ቤን ፡ በጣም ቆንጅዬ ዛጎል ነው" ስለው እንደገና ፈገግ ብሎ ጆሮውን አሻሸ ። ፍርሐቱ እየለቀቀው ነበር ። ትኩር ብሎ እየኝና "እህ ፡ አይኖችሽ ፡ እህ ፡ የመላእክት ... አይን .." ሲለኝ ዝም ብዬ አቀርቅሬ ዛጎሉን መመልከቱን ቀጠልኩ ።

"አንቺ ፡አዎን ... አንቺ ግን ...እህ! እህ እንደርሷ አይደለሽም" ሲለኝ ግን "ምንደነው የምትለው ቤን? እርሷ የምትላት ደግሞ ማን ናት?" ስል ጠየኩት ።

ጭንቅላቱን ሲነቀንቀው የትካዜ አማልክት ይሁኑ ወይም ሰይጣናት

t.me/OLDBOOKSPDF

የተጠጉት አይነት መልኩ ወዲያውኑ ልውጥውጥ አለብኝ ። ጣቱን አፍንጫው ላይ አጋድሞ "እንዴ ፣ ረጅም ነበረች እኮ ... ደግሞ ጠይም" ብሎ ጀመረ "እባብ ነው የምትመስልሽ እኮ ፣ አዎን ... እዚህ ነው ያየኋት፣ በአይኔ ። ማታ ማታ ትመጣ ነበር እኮ ፣ አይቻታለሁ .. እኔ ምን ቸገረኝ?" አለና ፀጥ ። ቀና ብሎ አየኝና ቀጠለ "እንዴ ደግሞ እዚህ ውስጥ ሳያት አየችኝ አይደል? አይቻታለሁ ። 'ታውቀኛለህ? እኔን ታውቀኛለህ? ከዚህ ቀደም በፍፁም አይተኸኝ አታውቅም' አይደለም ያለችኝ? 'ከእንግዲህ እህ..ወ ወደፊትም አታየኝም ። ሁለተኛ በመስኮት ብታየኝ እብዶች ...እህ.. እብዶች ሐኪም ቤት ነው የምወረውርህ ። እዚያ ሐኪም ቤት ውስጥ ምን ዓይነት ጨካኝ ሰዎች እንዳሉ ታውቅ የለም? አለችኝ ።' አዎን በደንብ ብላኛለች ደግሞ ...'በኋላ ...በኋላ .. እኔ.. እኔ የኔ እመቤት እባክሽን ምንም አልናገርም' አልኳትና አየሽ ... አየሽ እንደዚህ ባርኔጣዬን አወለቅኩት ። አሁን ግን እርሷ አትመጣም ። ሄዳለች አይደለም? ሄዳለች ... ሄዳለች ... አትመጣም ... አትመጣም አይደል?" ሲል እየተቁለጨለጨ ጠየቀኝ ።

"እኔ እንጃ ፣ ስለ ማን እንደምታወራ አልገባኝም ቤን ። ሐኪም ቤት ግንም አያስገባህምና አይዞህ ። በል ደህና ዋል" ብዬው ፊቴን አዞርኩ ።

ጃስፐርን አስከትዬ ጉዞዬን ቀጠልኩ ። ምስኪን ቤን ፣ በጣም አሳዘነኝ ። ይሄኔ ፍራቻውን እራሱ የቀረፀው ይሆናል ። ምናልባትም ዘመዶቹ ስለ እርሱ ሲናገሩ ሰምቶ አልፎ አልፎ ብልጭ እያለበትም ይሆናል ብዬ ገመትኩ ። አስተሳሰቡ ሁሉ እንደ ሕፃን ስለሆነ ዛሬ ያፈቀረውን ነገ ያለ ምክንያት ሊጠላው ይችላል ። ዛሬ የአሣ ማጥመጃውን እንዲወስድ ስለፈቀድኩለት ለኔ ቀና አስተሳሰብ አለው ። ነገ ቢያየኝ ግን ከነመፈጠሬም ሊረሳ እንደሚችል በማሰብ ለእርሱና ለእርሱ መሰሎች ሁሉ አዘንኩላቸው ።

ይህን እያሰላሰልኩ አይኔን ባሻገር ስወረውረው ቤን በቋጥኞች መሐል እየተሹለከለከ ሲገሰግስ አየሁት ። ወደ ኋላዬ መለስ ብዬ ጎጆውን በርቀት ሳየው ድንገተኛ ፍርሀት ደርሶ በልቤ ተዘፈዘፈ ። አንዳች አስፈሪ አካል አንገቴን ጨምድዶ የሚጥለኝ እየመሰለኝ በጣም ፈራሁ ። መሮጥ መሮጥ አለኝ ። ተዝቆ የማያልቅ ሀብት ይሰጥሻል ብባል ዳግመኛ ወደዚህ አካባቢ ዝር ላለማለት ቁርጠኛ ውሳኔ አድርጌ ሩጫዬን ቀጠልኩ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጃስፐርም አዲስ አይነት ጨዋታ የማጫወተው እየመሰለው እየፈገገ አብሮኝ ይሮጥ ጀመር ።

ትንፋሼ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ከቤታችን አካባቢ ደረስኩ ። ወደ ሰገነቱ ስመለከት አንድ የሚያብረቀርቅ ነገር አይኔን ወደ ሌላ አቅጣጫ እንዳዞረው አስገደደኝ ። ምንነቱን ለማጣራት እንዲረዳኝ አይኔን ከወሐዩ ጨረር ለመከላከል እጄን ከግንባሬ ላይ አዋልኩት ። ተጠጋሁ ። ያየሁት መኪና መሰለኝ ። ይበልጥ ተጠግቼ መኪናነቱን ሳረጋግጥ የማን መኪና ሊሆን እንደሚችል ግራ ገባኝ ። እንግዳ መጥቶ ይሆን? የሚለው ሐሳብ የዋልኩበትን ደስታ ሊያደፈርስብኝ ተናነቀኝ ። የእንግዳ መኪና ደግሞ አለ ወትሮው ይህን ያህል ርቆ ፡ ለዚያውም እቱጥጂጠው ውስጥ ተደብቆ ለምን ይቆማል? የእንግዶች መኪና የት እንደሚቆም የሚያውቁ ሠራተኞች እያሉ ፡ ይህ ለምን ይሆናል ? በዚያ አለባበሴ እንግዶች ፊት መቅረብ አልፈለኩም ። ከማረፊያው ቤት መስኮት በኩል አያቸውኝ እንደሁ ብዬም ተሸማቀቅሁ።

አይኔን ሳቀና ከምዕራባዊው ሕንፃ መስኮቶች መሐል አንደኛው መከፈቱን አየሁ ። አንድ ሰውዬ እኔን አይቶ ነው መሰለኝ ወደ ጎን ሲሸሽ አየሁት ። ወዲያው ሌላ ሰው መስኮቱን ዘጋው ። መስኮቱን የዘጋው የማን እጅ እንደሆነ መለየቱ አላዳገተኝም ። ያ ጥቁር የቀሚስ እጅጌ የሚስዝ ዳንቨርስ መሆኑን ጠንቅቄ አውቅ ነበርና ። ቤቱን የሚጎበኙ ሰዎች ናቸው እንዳልል ምዕራባዊውን ሕንፃ ማንም ጎብኝቶት አያውቅም ። በማክሰኞ ደግሞ እንዲህ ዓይነቱ ጉብኝት ተደርጎም አያታወቅ ። የጥገና ሠራተኛ እንዴይባል አይቶኝ መሸሹ ምን አመጣው? እንግዲያው የሚስዝ ዳንቨርስ የግል እንግዳ ይሆናል ፡ ምን አገባኝ ብዬ ወደ ቤት ገባሁ ።

ከሰው ጋር መንገድ ላይ እንዳልገናኝ በመስጋት ግራና ቀኙን እየመረመርኩ እጄን ታጥቤ ወደ እልፍኜ አመራሁ ። የእጅ ሥራዬ ጠዋት ትቼው ከሄድኩበት ሥፍራ ተነስቶ ወደ ጥግ ተደርጉአል ። ሌላ ሰው ገብቶ እንደነበረ የወንበሮቹና የጠረጴዛው አቀማመጥ ይናገራል ። ምናልባት ሚስዝ ዳንቨርስ እኔና ማክሲም ወጣ ስንልላቸው እንግዶቻቸውን የሚያስተናግዱት እዚህ ሳይሆን አይቀርም ብዬ ገመትኩ ። ምን ችግረኝ? እኔን አይመለከትም አልኩና የእጅ ሥራዬን ይዤ ለመውጣት ስዘጋጅ ባልደረባዬ ጃስፐር ዙሪያውን ሲያነፈንፍ አየሁት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በሩን ከፍቼ ስወጣ ድምፅ ሰማሁና ወደ ኋላ አፈገፈግኩ ። ያቺ ጃስፐር ደግሞ ምላሱን ጮልጦሎ ፣ ጭራውን እየወዘወዘ ፣ እበሩ ላይ ቆሞ ወደ ውስጥ ያየኛል ። እንዳያጋፍጠኝ ሠግቼ ትንፋሼን ውጬ ደርቄ ቀረሁ።

የሚስዝ ዳንቨርስን ድምፅ ነበር "እንደ'ት ቶሎ እንደተመለሰች እንጃ ፣ ወደ ቢተመጻሕፍቱ ሳትሄድ አትቀርም ። እዚያ ከሆነች በአዳራሹ በኩል ሹልክ ብለህ ትወጣለህ ። እዚህ ቆይ እስቲ ፣ ሄጂ ልይልህ" ሲል የሰማሁት ።

ስለኔ እያወሩ መሆናቸው ገባኝ ። ጃስፐር ትቶኝ ሲሄድ እፎይ አልኩኝ ። "አ ፣ ቦቢ" ሲል ሰማሁት ሰውዬው ። ጃስፐር ከፉኛ ጮኸ ። የእግር ኮቴ ስሰማ የት አባቴ እንደምደበቅ መላ ቅጡ ጠፋኝ ። የማሰቢያ ጊዜም ሳላገኝ ሰውዬው ዘው ብሎ ከነበርኩበት ክፍል ገባ ። ከበሩ ጀርባ ተለጥፌ ስለነበር አላየኝም ። ያ መአተኛ ጃስፐር እየፈነጠዘ እላዬ ላይ ዘለለ ። አለቀልኝ ። እንደዚያ ደንግጬም አላውቅም ። ለስርቆት ሰው ቤት ገብቼ ባለቤቱ ድንገት የደረሰብኝ ዓይነት ነበር የሆንኩት ።

አይኑን ከላይ እታች እያመላለሰብኝ "ይቅርታ" አለኝ ሰውዬው ። ግዙፍ መልክ መልካም ነው ። ፊቱ ፀሐይ የመታው ሲመስል የአይኖቹ ቅላት ድልህ ያስንቃል ። ፀጉሩ እንደመልኩ ሁሉ ቀላ ያለ ፣ እብጥ ያለው አንገቱ በአሥሮር ጊዜ ውስጥ የስብ ጋን ሊመስል የሚያስችል ፈጣን ዕድገት የሚታይበት አይነት ነው ።

በውስኪ የታጀበው ትንፋሹ እቅምኩበት ዘልቆ አፍንጫዬን ገረፈው ። በዓይኑ ሥር ውል ላለች እንስት ሁሉ የሚለግሰውን ዓይነት ፈገግታ አሳይቶኝ ፣ —

"አስደነገጥኩሽ እንዴ?" ሲለኝ ከበሩ ሥር እየተንተባተብኩ ወጣሁና "አይ አላስደነገጡኝም ። ድምፅ እንኳን ሰምቼ ነበር ፣ ማን እንደሆነ አላወቅኩም እንጂ ። ዛሬ ደግሞ እንግዳ ይመጣል ብዬ በጥፀም አልገመትኩም ነበር" አልኩት ።

"ጥፋተኛው እኔ ነኝ ። እንዲህ ዘው ብዬ በመግባቴ ይቅርታ እንደምታደርጊልኝ ተስፋ አደርጋለሁ ። ዳኒ የጥንት ወዳጄ ስለሆኑ እርሳቸውን ለመጠየቅ እግረ — መንገዴን ብቅ ብዬ እኮ ነው ።"

"ግድ የለም ፣ ምንም አይደለም ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

“አይ ዳኒ ፡ ልዩ ፍጡር እኮ ናቸው ። ሰውን ማስከፋት በፍፁም አይሹም ። አንቺንም ላለማስጨነቅ ብለው ነው ያልነገሩሽ ።”

“እረ ምንም ችግር የለም”

ጃስፐር እየዘለለ ሰውዬው ላይ ሲንጠለጠልበት “ይህ ምስኪን ደግሞ አልረሳኝም ማለት ነው? በጣም ተስማምቶት የለም እንዴ? ያኔ ሳየው በጣም ትንሽ ነበር ። አሁን በጣም ወፍሯል ። ልምምድ የሚያሻው ይመስለኛል ።”

“አዎን ፡ አሁንም አንሸራሽሬው ነው የመጣሁት ።”

“እውነት? ስፖርተኛ ነሽና?” አለና ጃስፐርን ሲያሻሽ ከቆየ በኋላ የሲጋራ ፓኬቱን አውጥቶ ጋበዘኝ ። እንደማላጤስ ስነግረው የራሱን ሲጋራ አቀጣጥሎ በጢሱ መሃል ያየኝ ጀመር ። ሲጋራ ለሚያጨሱ ሰዎች የተለየ አስተያየት ባይኖረኝም እሰው ቤት ገብቶ እንዲያ በመሆኑ ግን ታዘብኩት ።

“ማክስ እንዴት ነው እባክሽ?” ሲለኝ ሳይገርመኝ አልቀረም ። ማክስ ብሎ መጥራቱ ፡ ድምፀቱ ሁሉ በደንብ የሚተዋወቁ ያስመስለዋል።

“በጣም ደህና ነው ፡ ሎንዶን ሄዶ ነው ።” አልኩት ።

“እንዴ? ሙሽራዪቱን ብቻዋን ትታት? አይገባም ። አንዱ ጭልፊት ቢጠልፍበትስ?” አለና ከትከት ብሎ ሳቀ ። ገና ከጅምሩ ውቃቢዬ አልወደደው ፡ ሲስቅማ ይበልጡን አስጠላኝ ።

ይህን ጊዜ ሚስዝ ዳንቨርስ ገቡ ። ሲያፈጡብኝ ደነገጥኩ ። ምን ያህል እንደሚጠሉኝ አስተያየታቸው ይገልፅ ነበር ።

“አ ፡ መጡ እንዴ ዳኒ? ጥንቃቄዎ ሁሉ አልሰራም ። እመቤቲቱን በሩ ሥር ስትደበቅ አገኘኋት እኮ” አለና እንደገና ይስቅ ጀመር ። ሚስዝ ዳንቨርስ ግን ፀጥ ብለው አይናቸውን እኔ ላይ እንደተከሉት ቀሩ ። “ምንድነው ዝምታው? አያስተዋውቁኝም እንዴ?” ሲላቸው “ተዋወቁ እመቤቴ ፡ ሚስተር ፌቭል ይባላል” አሉ ሚስዝ ዳንቨርስ አየቀፈ ፋቸው ።

“እመሰግናለሁ” አልኩ “ታዲያ አረፍ ብለው ሻይ ይምጣልዎታ” ግብግቡ ከአንገት በላይ ነበር ፡ እንዲያው ትህትና ለማሳየት ያህል ።

“ምን ይመስልዎታል ሚስዝ ዳንቨርስ? ትልቅ ግብግ ነው” አለ እንግዳው ወደ ሚስዝ ዳንቨርስ ዞር ብሎ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እርሳቸው ግን በአፋቸው ሳይሆን በአይናቸው መለሱለት ። ገረመሙት ። "ግብግቡን ብቀበል ምንኛ ደስ ባለኝ ፣ ግን ስለምቸኩል ብሔድ ይሻላል ። ይልቅ እስቲ ብቅ በይና መኪናዬን እዪልኝ" አለኝ ። ወጥቼ ማየቱን አልፈቀድኩም ነበር ። መልሴን ሳይጠብቅ ለጠቅ አደረገና "ነይ እንጂ ፣ እንዴት ያለች ቆንጆ መኪና መሰለችሽ ። ማክስ እንዲህ ያለ ፈጣን መኪና በሕይወቱ ይዞ አያውቅም" አለኝ ።

ማምለጫ ምክንያት አልነበረኝምና "የት ነው መኪናዎ ያለ ችው?" ስል ቀዝቀዝ ብዬ ጠየቅኩት ።

"ኩርባው ላይ ነው ያቆምኳት ። ምናልባት የሰዓት እንቅልፍ ለምደሽ እንደሆን እንዳልረብሽሽ ነው እደጅ ድረስ ያላመጣኋት ።"

ተከታተለን ስንወጣ ሰውዬው ሚስዝ ዳንቨርስን ጠቀስ ሲያደርጋቸው በጨረፍታ አየሁት ። እርሳቸው ግን አፀፋውን አልመለሱም ። አሮጊቷም አላረውን ይሂዱ እንደሆነ ቢጠይቃቸው በአሉታ መልሰውለት ሊለዩን ሲዘጋጁ እጃቸውን ጠበቅ አድርጎ እየነቀነቀ "ይበሉ ደህና ይሁኑ ። በጣም ጥሩ ጊዜ ነው ያሳለፍኩት ። በሌላ ጊዜ ብቅ እላለሁ ።" አለና ተሰናበታቸው ።

የቤቱን መስኩቶች ቀና ብሎ እየተመለከተ "ማንደርሌይ እኮ እንዳለ ነው ያለው ። መቼም እኒሁ አሮጊት ናቸው እየተንከባከቡት ያሉ ። የዋሣ አይደሉም ።" ሲል

"አዎን ጥንቁቅ የሥራ ሰው ናቸው" አልኩት

"እዚህ ውስጥ ታፍኖ መኖሩን እንዴት ነው የምታይው?"

"ምንም መታፈን አይደለም ። በጣም ነው የምወደው ።"

"ከማክስ ጋር የተገናኛችሁት ሞንቴ ካርሎ ነው መሰለኝ? ሞንቴን እኮ አብጠርጥሬ ነው የማውቃት"

ሞንቴ ካርሎ እኖር እንደነበር ሳረጋግጥለት ከመኪናው አጠገብ ደረስን ። መኪናዋም ባለቤቷን ነው የምትመስለው ።

"ታድያስ መኪናዬ እንዴት ናት?" ሲል እየተንበላጠጠ ጠየቀኝ

"በጣም ቆንጆ ናት" አልኩት በትህትና ።

"እንዴት ነው ታድያ ፣ እስከ ዋናው መግቢያ ድረስ ትንሽ ትንሸራሸሪባት?"

"ውይ ፣ በጣም አመሰግናለሁ ። ስለደከመኝ ነው ።" በማለት

t.me/OLDBOOKSPDF

ይቅርታ ጠየቅኩት ።

"ወይስ የማንደርሌዋ እመቤት ከኔ ብጤው ጋር መሄዴ ክብሯን ይነካል ብለሽ?" አለኝ እየሳቀ — የሽሙጥ ሳቅ ።

"እረ በፍፁም ፡ ደክሞኛል እያልክዎት"

ጅንን ብሎ በእኒያ አስጠሊታ ሰማያዊ አይኖቹ ከላይ እስከታች አየኝ ። ጭራሽ የመሸታ ቤት አሻሻጭ መሰልኩት እንዴ? ብዬ ሳስብ ፊቱን ወደ ጃስፐር አዙሮ "ስማ ጃስፐር ፡ ሙሽራዪቱን የማዬታ ማሳሳት የለብንም ። አይመስልህም?" አለና ከመኪናው ውስጥ ቆቡንና ጓንቶቹን አወጣ ።

"በይ ደህና ሁኚ እንግዲህ" ሲል እጁን ዘረጋልኝ ።

"ደህና ይሁኑ" አልኩት በአጭሩ — ቶሎ መገላገሉን ፈልጌ

"በነገራችን ላይ" ሲል እንደ ቀልድ ጀመረና "መምጣቱን ለማክስ እንደማትነግሪው ተስፋ አደርጋለሁ ። ለምን እንደሆነ ባይገባኝም እጅግም አይፈቅደኝም ። ከሁሉ በላይ በሚስዝ ዳንቨርስ ላይ ችግር እንዳይፈጥር ሠግቼ ነው" በማለት አጠቃለለ ሀሳቡን ።

"ምን ብዬ ይህን እናገራለሁ" አልኩት ግራ በተጋባ አንጋገር

"በጣም ጥሩ ። አሁንም ሀሳብሽን አልቀየርሽም? ማለቴ አብረሺኝ ትንሽ ለመንሸራሸሩ?"

"ይቅርታ ያድርጉልኝና ቢቀርብኝ ይሻላል" በማለት በድጋሚ ለመንኩት

"እንዳልሽ ፡ እንግዲህ ደህና ሁኚ ። አንድ ቀን ብቅ ብዬ አይሽ ይሆናል ።" ካለ በኋላ ሀሳቡን ወደ ጃስፐር መልሶ "ና እባክህ ውረድ አንተ ጃስፐር ፡ የመኪናዬን ቀለም ትልጥብኛለህ ።" አለው ። አያይዞም "እኔ እኮ እስካሁን ከአእምሮዬ ያልተፋቀልኝ ማክስ ብቻሽን ትዮሽ ሎንዶን የመሄዴ ጉዳይ ነው" ሲለኝ ፡—

"እኔ ግድ የለኝም ። ብቻዬን መሆኑ ደስ ይለኛል" አልኩት

"ደስ ይለኛል? ዛሬ ደግሞ ይህ ጅሮዬ የምን ጉድ ነው የሚያሰማኝ? ጭራሽ እንግዳ የሆነ ነገር? ከተጋባችሁ ገና ሦስት ወራችሁ አይደለም እንዴ?"

"ወደዚያው ግድም ነው"

"ወይኔ ሰውዬው ! እኔ እቤት ውስጥ ቁጭ ብላ የምትጠብቀኝ

t.me/OLDBOOKSPDF

የሦስት ወር ሙሽራ ብትኖረኝ ምንኛ በታደልኩ ! ደስታውንም አልችለው ! ብቸኝነት ያጠቃኝ ምስኪን ላጤ እኮ ነኝ" አለና እየገለፈጠ ቆቡን ወደ አናጺዉ ሳበው ። በድጋሚ ተሰናብቶኝ መኪናውን አስነስቶ በረረ ። ቡልቅ እያለ ወደኋላ የሚወረወረው ጠስ የሰውዬውን ንጭትና ቁጣ የሚገልፅ ይመስል ነበር ።

ጃስፐር ጆሮቹን አንከርፍፎ ፡ ጭራውን እግሮቹ መሐል ሸጉጦ ፡ አይኑን መኪናው ላይ ተክሎ ፡ በትካዜ ሰጥሞ ሳየው በጣም ገረመኝ ። ከሌላ ሰው ጋር እንዲህ ሲሆን ሳየው የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር ። ከፈዘዘበት አንቅቼ ፡ ይዣው ወደ ቤት አዘገምኩ ።

ሚስዝ ዳንቨርስ በአቅራቢያውም አልነበሩ ። አዳራሽ ገብቼ ደወሉን ብደውል እንድም ድርሽ የሚል ሰው ጠፋ ። ከአምስት ደቂቃ በኋላ ነበር አሊስ ብቅ ብላ ሮበርትን ሚስዝ ዳንቨርስ ልከውት እንደሄደና ሽማግሌው ፍሪዝም ዕረፍት ላይ መሆናቸውን የነገረችኝ ።

ለካስ ማክሲም ወላ ሲል የቤቱ ሥነ ሥርዓት ሁሉ እንዲህ ብልሽትሽት ይላል? የሚል ሀሳብ አደረብኝ ። የሽማግሌው እንኳን ይሁን ፡ የዕረፍት ቀናቸው መሆኑን አውቃለሁ ። አሮጊቲ ሮበርትን የላኩት ሆን ብለው ሳይሆን እንደማያቀር ገመትኩ ። እኔም ራቅ ብዬ ለሽርሽር መውጣቴን ስለሚያውቁ የእንግዳው በዚያን ወቅት መምጣት በጥናት የተደረገ ለመሆኑ የሚያጠራጥር አልነበረም ።

ግን ይህ ፈቭል የሚሉት እንግዳ ማን ነው? ምንስ ፍለጋ መጣ? መምጣቱን ማክሲም እንዳያውቅበትስ የፈለገው ለምንድነው? በእርግጥ በጠየቀኝ መሠረት ላለመናገር ቃል ገብቻለሁና ቃሌን እጠብቃለሁ ። ሚስዝ ዳንቨርስ ችግር ላይ እንዲወድቁ አልሻም ። ማክሲምስ ለምን ይጨነቅ? ግን ይህ ሁሉ ጥንቃቄ ለምን አስፈለገ? እኒህና መሰል ጥያቄዎች በአእምሮዬ እየተመላለሱ ዕረፍት ነሱኝ ።

በሌላ ወገን ደግሞ ይህ ሰው ማክሲምን እንዴት "ማክስ" ብሎ ሊጠራው ቻለ? የሚለው ጥያቄ ተጨማሪ እረፍ ምታት ነው የሆነብኝ ። ማንም ማክስ ብሎ ሲጠራው አልሰማሁም ። አንድ ጊዜ ግን በአንድ መፅሀፍ የመጀመሪያ ገፅ ላይ ተፅፎ ማየቴ ትዝ ሲለኝ ፡ ያ ጥምልምልና ቅልማማ የእጅ ዕሀፊት ውልብ አለብኝ አጥወለወለኝ ።

አእምሮዬ መለስ ሲልልኝ እንግዳውና ሚስዝ ዳንቨርስ ምን ሲሰሩ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው የቆየት ለሚለው እንቆቅልሽ ምላሽ እንዲፈልግ ሥራ ሰጠሁት ። እኛ የሌለንበት ፡ ሴቶች አገልጋዮችም በሥራ የተወጠሩበት ይህ አጋጣሚ የተመረጠበት ምክንያት ምን አይነት ምስጢራዊ ተግባር ለመፈፀም ይሆን? ብዬ እራሴን ብጠይቅ መልስ አጣሁለት ። የምን ድብብቆሽ እንደሆነ ቄራሹን ሊከሰትልኝ አልቻለም ። አእምሮዬን ወደ ሌላ አቅጣጫ ስጠመዝዘው ደግሞ ሚስዝ ዳንቨርስ ከፌቭል ጋር በመመሳጠር በምዕራባዊው ሕንፃ ውስጥ የተከማቹትን ውድና ክቡር ዕቃዎች ለመስረቅ ማሴራቸው ይሆን? የሚለውን ጥርጣሬ አሜረብኝ ። ወደ ሕንፃው ሄጄ ማጣራት አለብኝ የሚል ድንገተኛና ቁርጠኛ ሀሳብ አደረብኝ ። ልቤ እየዘለለ ፡ እግሮቼ እየተንቀጠቀጡ ወደዚያው አመራሁ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አሥራ ሦስት

ፎቅ ወጥቼ ኮሪደሩ ላይ ቆም አልኩ ። ወደምፈልገው ክፍል ያስገባኛል ብዬ የገመትኩትን በር ከፈትኩት ። መስኮቶቹ በሙሉ በመዘጋታቸው ጨለማው ተቀበለኝ ። ማብሪያ ማጥፊያውን በዳሰሳ ፈልጌ መብራቱን አበራሁት ። ክፍሉ አነስ ያለ ሲሆን ዙሪያውን የቆሙት ቁምሳጥኖች የመልበሻ ክፍል መሆኑን ጠቆሙኝ ። ፊት ለፊት ያገኘሁትን በር ከፍቼ ገባሁ ። መብራቱን ሳበራው ያየሁትን ማመን ተሳነኝ ። ሰፊው ክፍል በተሟላ ቁሳቁስ የተደራጀ ነበር ። አልጋው እንደተነጠፈ መሆኑ ወንበሮቹና ጠረጴዛዎቹ በሥርዓት መሆናቸው ገረመኝ ። ምንም እንኳን ወና ወና ቢልም የዕቃዎቹ አቀማመጥና አንዳችም አቧሯ አለመታየቱ ክፍሉ ግልጋሎት ያላቋረጠ ያስመስለው ነበር ።

የፀጉር ማበጠሪያዎች ፡ ፒጃማ ፡ ነጠላ ጫማዎችና መሰል መገልገያ ዎች በየሥፍራቸው በሥርዓት ከመቀመጣቸውም በላይ ያልጠወለጉ አበቦች እዚህም እዚያ ማየቱ ግራ አጋባኝ ። ልዩ ቅዕበታዊ ስሜት ወረረኝ። ሀሳቤን ወደ ኋላ እያንደረደረ ከህልም አለም አስገባኝ ። ርብቃ በነፍስ በሥጋዋ ከፊቱ ተደቀነችብኝ ። እያንጎራጎረች ወደ መስታወቱ ተጠጋች ። ማበጠሪያዋን አንስታ ፀጉሯን ማበጠር ጀመረች ። በመስታ ወቱ ውስጥ እኔ የእርሷን ፡ እርሷ የእኔን ምስል ስናይ ተፋጠጥን ። እንጉርጉሮዋ ቆመ ፡ ማበጠሩን አቋረጠች ፡ ትንፍስ ልውስ የሚል ጠፋ ። ተግባሮቻቸውን ያልዘነጉት ግን ተጎልቶለው ለመውጣት የተቃረቡት አፍጣጭ አይኖቻችን ብቻ ነበሩ ።

ከቅዠት መንፈቅ ወደ ገሃዱ አለም የመለሰኝ ለፀጥታው ድባብ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያልተበገረው የግድግዳው ሰዓት ነበር ። እራሴን ነቀነቅኩት ። እንደገና ዙሪያዬን ቃኘሁ ። ሁሉም ነገር ለማስመሰል የተደረገ እንጂ እውነትነት እንደሌለው በመተማመን እራሴን ማፅናናት ያዝኩ ። 'ርብቃ አክትሞላ ታል መቃብር ውሏታል ። እስካሁን ምስጡ አፅሟን እንኳ አያስተርፈውም ። ይህ ሁሉ የሚስዝ ዳንቨርስ ቅዠት ነው' በማለት ሞንቀቴን አስወግጄ ወደ መስኮቱ ተጠጋሁ ።

መጋረጃውን ከፍቼ ቁልቁል ስመለከት ቀደም ሲል ፈቭልና ሚስዝ ዳንቨርስ ሲመለከቱኝ ከነበሩበት መስኮት ላይ መሆኔን ከአትጣጫው ተገንዘብኩ ። በመስኮቱ የገባው የፀሐይ ብርሃን በመብራቱ ብርሃን ላይ ገነነ ። ይሁንና ተፈጥሯዊውም ብርሃን ክፍሉን ይበልጥ ሕይወት ይስጠው እንጂ ሞንቀቴንና ፍርሀቴን ለማስወገድ ስላልረዳኝ በእጅጉ ጠላሁት ። ሚስዝ ዳንቨርስ ርብቃን ከሙታን አለም የመመለስ ከንቱ ምኞታቸውን እንዲያንላላቸው መብራቱን በእውቅ ባለሙያ ያሰሩት መስሎኝ ነበር ። የፀሐይ ብርሃን ደግሞ ለዚህ መሰሪ አላማ ግንባር ቀደም ተባባሪ ሆኖ በመገኘቱ እንደ አሮጊቷ ሁሉ ኮነንኩት ። እንደ እርሳቸው ሁሉ ታዘብኩት ።

አጥወለወለኝ ፡ እግሮቼ እንደ ቁጠማ ተጥመለመሉ ፡ ሰውነቴ ከዳኝ። በአቅራቢያዬ ባገኘሁት በርጩማ ላይ አረፍ አልኩ ። ልቤ ከሥፍራው ሲገባ የክፍሉን ውበት ፡ የቁሳቁሶቹን ጥራትና አደረጃጀት ማድነቅ ጀመርኩ ። ሁሉም የኔ ቢሆን ኖሮ የሚል ከፍተኛ ጉጉት አደረብኝ። በደመነፍስ እየተንተባተብኩ ማበጠሪያዎቿን ፡ ሻማዎቿን ፡ የሌሊት ልብሶቿን ጠቅላላ ዕቃዎቿን አንድ በአንድ እያነሳሁ መረመርኳቸው። አልጋዋ ላይ ጋደም ብዬ እላይ ታች አናጠርኩበት ።

ድንገት ከአልጋው ላይ ተፈናጥሬ ወርጄ ወደ መልበሻ ክፍሏ ገባሁ። መሳቢያዎቹን ተራ በተራ እየከፈትኩ ፍተሻዬን ቀጠልኩ ። ልዩ ልዩ ልብሶቿን እያነሳሁ ጥራታቸውንና ልስላሴያቸውን በእጄቼ መመርመሩ አላረካ ቢለኝ በጉንጮቼ ዳሰስኳቸው ።

ያየሁት ሁሉ ናላዬን ቢበጠበጠው የማደርገውን አሳጣኝ ። እንደገና እየተቻኮልኩ ወደ መኝታ ክፍሉ ገባሁ ። አይኔን አልጋ ልብሱ ላይ ተክዬ እንደፈዘዝኩ ትከሻዬን ከበደኝ ። የእግር ኮቴ ሰምቼ ዞር አልኩ ። መሬት ተሰንጥቃ ብትውጠኝ ፍቃዴ ነበር ።

t.me/OLDBOOKSPDF

“ምን ሆኑ የእኔ እመቤት?” አሉኝ ሚስዝ ዳንቨርስ በዚያ መብረቅ ድምፃቸው ። ወጉኝ በእኒያ ጦር አይኖቻቸው ።

መልስ መስጠቱ የማይሞከር ቢሆንብኝም ፈገግታ እንኳ ራቀኝ ። “ምነው ደህና አይደሉም እንዴ?” ብለው እጆቻቸውን ዘርግተው ሲጠጉኝ ሊያሳፍረኝ የሚያነሳሳኝ መልአከ ሞት መሰሉኝ ። ሲቀርቡኝ ስርቃቸው ፡ ሲቀርቡኝ ስርቃቸው ከጀርባዬ የነበረው ጠረጴዛ እርምጃዬን ገታው ። የኋላ ኋላ “አዩ ... ሚስዝ ዳንቨርስ ... እታች ሆኜ መስኮቱ መከፈቱን ... እህ ... ስላየሁ ... አዩ ልዝ ... ልዘጋው ነው የመጣሁት” አልኳቸው የሞት ሞቱን ።

“እኔ እዘገዋለሁ” ብለውኝ ከዘጉት በኋላ ወደኔ ቀረብ ብለው “መስኮቱን እንኳ ዘግቼው ነበር የሄድኩት ። እርስዎ እራስዎ ነዎት የከፈቱት ። ቀጥታውን ከፍሉን ላይ ነው የመጣሁት አይሉኝም? እኔ እኮ የማያገባኝ አስጎብኚኝ ቢሉኝ አንድ በአንድ የማሳይዎትን ድብብቆሹ ምን አመጣው? ”ሲሉኝ ቃል መተንፈስ አልቻልኩም ። አይን አይናቸውን ሳይ “ይምጡ አሁንም ፡ ከመጡ አይቀር ላስጎብኝዎ” በማለት ከንዴን ይዘው ወደ አልጋው ወሰዱኝ ።

እያንዳንዱን ነገር እያሳዩኝ ዘርዘር አድርገው ሲያስረዱኝ ከመቼው ተገላግዬ መኝታ ክፍሉ በገባው ነበር ያሰኘኝ ። ዝርዝር መግለጫቸው በጣም ከማሰላቸቱም በላይ እንዳንዱን ዕቃ እያነሱ “እስቲ ይህን ይዘው ይዩት ...ልዩ እነ ነው ። እቃዎቹ ሁሉ ምርጥ ናቸው ። መቼም እንደ እርሷ ምርጫ የሚያውቅ ማንም የለም ። አለባበስ ቢሉ ፡ ያ ለግላጋ ቁመናዋ ላይ የጣለችው ፈጠርቅ ሁሉ አብሯት የተሰራ ነበር የሚመስለው ...” በማለት ቀጠሉ ። እጇን ጠበቅ አድርገው ይዘው “እስካሁን መቼም ዕቃዎቹን ሁሉ እያነሱ ሲያዩ ነዛር ። አይደለም? እንዴት ነው ታዲያ ፡ አልወደዱትም?” እያሉ በአይናቸው ቂጥ እያዩኝ ያንን የውሸት ፈገግታቸውን ጋበዙኝ ። መልስ አልሰጠኋቸውም ። አጠንክረው የያዙት እጇ ደነዘዘኝ ። ለማስለቀቅ ድፍረቱ አነሰኝ ። ቢረዱልኝ ብዬ በአይኔ ብማፀናቸውም ቸል ብለውኝ ገለፃቸውን ቀጠሉ ።

“...አይ ይህ አልጋ ፡ ዛሬ እንዲህ ተገትሮ ይቅር? ያን ረጅሙን ፀጉሯን ዘንፈል አድርጋ ጋደም ያለች እንደሆነ አቤት ውበት! አቤት

t.me/OLDBOOKSPDF

ግርማ ሞገስ!... ማታ ማታ ወጉሯን እኔ ነበርኩ እኮ የማበጥርላት ። አንዳንዴ ጌቶችም ሽንጥ ያላቸው ዕለት ያበጥሩላት ነበር ። እኔ እንኳን ከአንዴም ሁለት ሦስቱ እዚሁ ወንበር ላይ አስቀምጠው ወጉሯን ሲያበጥሩ በዚሁ በአይኔ በብረቱ አይቻቸዋለሁ ። አቤት ያኔ እንዴት ነበር ደስ የሚላት! እየተፍለቀለቀች 'ማክስ በደንብ አበጥርልኝ እንጂ' ስትላቸው ትዕዛዟን ሁሉ ይሞሉላት ነበር ። በጣም ነበር የሚያስቀኑት ። ያኔ ጌቶች ሁልጊዜ መሳቅ ፣ ሁልጊዜ መደሰት ነበር ።" አሉኝ ።

ከዚያም ወደ መሞቷ አቅራቢያ ርብቃ ወጉሯን ስታሳጥረው ሰው ሁሉ እንዴት እንደተቃወማት ነገሩኝ ። ስለ ውስጥ ልብሶቿም ማብራሪያ ተሰጠኝ — ስትሞት ለብሳው የነበረ የልብስ አይነት ሳይቀር ። እያይዘውም "መቼም የፈሰሰ ውሃ አይታፈስም እንጂ የዚያን ዕለት ለሽርሽር ከመውጣቷ በፊት አግኝቻት ቢሆን ኖሮ አትሞትም ነበር..." በማለት ስለ አሟሟቷ በዝርዝር ይነግሩኝ ጀመር ።

"... ቀኑን እኔ ፍቃድ ወስጂ ወጣ ብዬ ነበር ። እርሷም ሎንዶን ሂዳ ስለነበር በጊዜ ትመለሳለች ብዬ ስላልገመትኩ አመሻሽቼ እመለሳለሁ ። እርሷ ግን ቀድማኝ ትመጣለችና እራቷን በልታ ወደ ባሕሩ ወረደች ሲሉኝ በጣም አሳሰበኝ ። ሐይለኛ ንፋስ ስለነበር ሞገዱን ነበር የፈራሁት። ይቅርብሽ ፣ ዛሬ አደገኛ ነው ብላት እሺ ነበር የምትለኝ ። እግዚአብሔር ያክብራትና የሥላትን ሁሉ ትሰማኝ ነበር ። ሞኝ ያደርገል? ያን የመሰለ ገላ ውሃ በልቶት ቀረ ።

"ይኸውልዎ ታድያ ሚስተር ደዊንተር ሚስተር ከሮውሌይ ዘንድ እራት ሲበሉ ያመሹና እስከ ምሽቱ አምስት ሰዓት ድረስ ሳይመለሱ ይቀሩልዎታል ። እንዲሁ ጭንቅ ጥብብ ሲለኝ ቆይቼ ሲመጡልኝ አለመመለሷን ነገርኳቸው ። 'እንደተለመደው እዚያው ጎጆው ውስጥ ብታድር ይሆናላ ።' ብለው አሰናበቱኝ ። እንቅልፍ በዓይኔ ሳይዞር ሌሊቱ ወገግ አለልኝ ። ልብሴን ደራርቤ ስገሰግስ ወደ ባሕሩ ወረድኩ ። እርሷ የለች ፣ ጀልባዋ የለ... ከዚያም ውሎ ሲያድር የጀልባዋ ስብርባሪ በየቦታው ይታይ ጀመር ።" አሉና ይዘውት የነበረ እጄን ሲለቁልኝ አፈትልከሽ ውጪ ውጪ ነበር ያለኝ ። አሮጊቷ ይቅበጠበጡ ጀመር ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በእጆቻቸው አንዳንድ ዕቃዎች እያነሱ ለማስተካከል የሚጥሩ ይምሰሉ እንጂ ሀሳባቸው ከእርሳቸው ጋር እንዳልነበረ ይነበብባቸው ነበር ።

በዚህ ሁኔታ ጥቂት ከቆዩ በኋላ "እንግዲህ ሚስተር ደዊንተር ይህን ክፍል ለምን እንደማይወዱት ገባዎት አይደል? ባሕሩን ይሰሙታል?" ብለው የረሳሁትን ሀሳብ ቀሰቀሱብኝ ። የባህሩ ሞገድ እነበርኩበት ዘልቆ የሚያጥለቀልቀኝ እስኪመስለኝ ድረስ ሽውሽውታው ተሰማኝ ።

"ከዚያ ቀን በኋላ" በማለት ቀጠሉ ሚስዝ ዳንቨርስ "ጌቶች ይህ ክፍል እርም ይሁንብኝ አሉ ። ክፍላቸው ወዲያውኑ እንዲቀየርላቸው አዘዙ ። ከዚያም ለብዙ ቀናት አልተኛ ብለው ወንበር ላይ ተቀምጠው ሲጋራውን በቂጥ በቂጡ ነበር የሚያቦኑት ። መቼም ወለሉ በሙሉ በአመድ ብልሽትሽት ነበር የሚለው ። ቀን ቀንም እንዲሁ እቤተ—መፃህፍቱ ውስጥ ላይ ታች ሲንጎራደዱ መዋል ነበር ።" ሲሉኝ የማከሲም የያኔ ሁኔታ ሁሉ ድንገት በአይነ—ሕሊናዬ መጣብኝና በሀሳብ ሰጠምኩ።

የመተላለፊያውን በር ዘግተውት "ይበሉ እንግዲህ…" ሲሉኝ ከሀሳቤ ባነንኩ ። "ለዛሬው ያዩት ይበቃዎታል ። በሌላ ጊዜ ፀጥታ ሲያንስዎ እዚህ እየመጡ ማረፍ ይችላሉ ።" ብለውኝ ስንወጣ "መቼም ክፍሉን እንደወደዱት እርግጠኛ ነኝ ። እኔማ በየቀኑ ክፍሉን እየጠረግሁ ዕቃዎቹን እያፀዳሁ ስወጣ ልክ እርሷ በሕይወት ያለች ነው የሚመስለኝ ። እዚህ ብቻ መሰለዎት እንዴ ? የትም ብሄድ እንዳለች አድርጌ ነው የምቆጥረው ። ቁመናዋ ፡ ድምጿ ፡ ጠረኗ ሁሉ ነው የሚመጣብኝ ። ምን ዓይነት መድሐኒት እንዳስነካችኝ እንጃ ። አንድም ቀን ሙታለች ብዬ አላውቅም ። አሆሆ! እርስዎስ በሕይወት ያለች መስሎ አይታይዎትም?" በማለት ትኩር ብለው ሲያዩኝ ይበልጡን ፈራኋቸው ።

"አሁን እንኳን" አሉ "አሁን እንኳን እኔና እርስዎ እዚህ ቁመን ስናወራ የምታየን ፡ የምትሰማን ነው የሚመስለኝ ። በሞቱ አይደብቁኝና እርስዎስ አይመስልዎትም?"

"እኔ እንጃ ፡ እኔ እንጃ" አልኳቸው በተሰባበረ ድምፅ

"የኔስ የብቻ ነው ። አንዳንዴ እዚህ ብቅ ብላ እርስዎና ሚስተር ደዊንተርን አንድ ላይ ብታያቸው ምን ይሰማት ነበር? እያልኩኝ

t.me/OLDBOOKSPDF

አስባለሁ” ብለውኝ ውልቅ ።

እኔም ወደ መኝታ ክፍሌ ጥድፍ — ሕመሜን ላስታምም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አሥራ አራት

በማግሥቱ ቁርስ እየበላሁ ሳለ ስልኩ አቃጨለ ። ብድግ ብዬ ተነሳሁ ። ጥሪው የማክሲም እንደሆነ ገምቼ ነበር ። ሽማግሌው ፍሪዝ ሲገቡ እንደዚያው እንዳኮበኮብኩ ከአሁን አሁን ይጠሩኛል ብዬ ስቁለጨለጭ "ጌቶች ደውለው ዛሬ ማምሻውን በአንድ ሰዓት ግድም እገባለሁ ብለዋል" ሲሉኝ ተስፋ ቆርጬ ወደ ወንበሬ ተመለስኩ ። ፍሪዝ እንዲህ እንደ ሕፃን ስስገበገብ ምንኛ ታዝበውኝ ይሆን በማለት ሐፍረት ተሰማኝ።

ምግቡ አልበላ ብሎኝ አፌ ውስጥ ሳንገዋልለው ሀሳብ አብሬ እያመነገርኩ ነበር ። ቀኑን እንዴት ልገፋው ነው የሚለው ጭንቀቴ ወደ ትላንቱ እንቅልፍ አልባው ሌሊት መሰደኝ ። እንቅልፍ አጥቼ እንዴት ስወራጭ እንዳደርኩ ሳስታውስ አልፎ አልፎ ሽለብ ሲያደርገኝ ትዝ ይመላለስብኝ እንደነበረ ትዝ አለኝ ። እኔና ማክሲም ሆነን ሳጓካው ውስጥ የምንንሸራሸር ይመስለኛል ። እርሱ እፊት ፊቱ ሲገሰግስ የጣርኩትን ያህል ብጣጣር የማልደርስበት ሆነ ። ጅርባውን እንጂ እንዴም ፊቱን ማየት ባለመቻሌ ብስጭትጭት አደረገኝ ። ጠዋት ስነሳ ትራሴ ረጥቦ አይኖቼ አባብጠው ሳያቸው ሌሊት ሳላለቅስ እንዳልቀረሁ ገመትኩ ።

እንዴት ሊመሽ ይሆን? በሚለው ጥያቄ እንደተወጠርኩ ስልኩ ጮኸ ። ቢያትሪስ ነበሩ ። እኛው አካባቢ ምሳ ተጋብዘው እንደመጡና ከሰዓት በኋላ ግን አያታቸውን ለማየት ስለሚሄዱ አብሬያቸው እሄድ እንደሆነ ለመጠየቅ ነበር የደወሉት ። ጥያቄያቸውን በደስታ ተቀበልኩት። ተዘጋጅቼ እንድጠብቃቸው ነግረውኝ ስልኩን ዘጉት ።

ገና ከጠዋቱ አራት ሰዓት ነበር ። ጊዜውን ለመግፋት መናፈሻው

t.me/OLDBOOKSPDF

ውስጥ ተቀምጬ እንዴ መፅሐፍ አንዴ ጋዜጣ ለማንበብ ብሞክርም ሀሳቤ ሊሰበሰብልኝ አልቻለም ። ማንበቡ ሲሰለቸኝ ደግሞ የእጅ ሥራዬን አንስቼ ልሳራህ ብለው ፍላጎቱ ራቀኝ ። እንዲሁ ስቅበጠበጥ የምሳ ሰዓት ደረሰልኝ ። ገበታ የቀረብኩት የምግብ ፍላጎት ኖሮኝ ሳይሆን እንዲያው ጊዜውን ለመግደል ቢረዳኝ ብዬ ነበር ።

ልክ ዘጠኝ ተኩል ሲሆን የመኪና ድምፅ ሰምቼ ወጣሁ ። መኪናው የቢያትሪስ መሆኑን ሳረጋግጥ በቀጠሮ አክባሪነታቸው አደነቅኳቸው ። እስኪቀርቡልኝ ቸኩዬ ልቀበላቸው ሮጥኩ ። ከመኪናቸው ወርደው ተቃቅፈን ተሳሳምን ። ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ "ምነው ልጄ? ምን ሆነሻል?" ብለው እላይ ታች እያዩኝ "ፊትሽን ምን መጠጠው? ደግሞም ገርጥተሻል" አሉኝ ።

"እረ ምንም አልሆንኩም" አልኩ የሆዴን በሆዴ ይዤ "ፊቴ እንደሁ ልማዱ ነው"

"እረ ተዪኝ ፡ ያኔ ሳይሽ እንዲህ ነበርሽ እንዴ ?"

"እንግዲያው ከጣልያን ይዤው የመጣሁት መልኬ እየገፈፈ ቢሆን ነዋ"

"ድንቄም! አንቺም የባልሽ ብጤ ነሽ ልበል? ስለ ጤንነታችሁ ሲጠይቋችሁ አትወዱም" ብለው መኪናውን አስነስተው መንገድ እንደ ጀመርን "ምናምን ቋጥረሽ ይሆን እንዴ?" ሲሉ ጠየቁኝ ።

"ምን? ልጅ? እረ በፍፁም ፡ ወሬውም የለ ።" አልኳቸው ።

"ጠዋት ጠዋት እንደማቅለሽለሽ ፡ እንደ መቆራረጥ አያደርግሽም?"

"ምንም አይሰማኝም"

"አንዳንድ ሴቶች እንደዚህ ናቸው ። እኔ የመጀመሪያውን ልጄን ሮጀርን ስወልድ አንድ ቀን ቆረጠኝ ፡ ፈለጠኝ ሳልል ነው በደህና የተገላገልኩት ። እንዲያውም እንደነገ ልገላገል በዋዜማው ጎልፍ እጫወት ነበር ። ታዲያ የሰው ሁሉ ፍጥረት የተለያየ ነውና የምትጠራጠሪው ነገር ካለ ብትነግሪኝ ጥሩ ነው"

"ምን ነካዎት ቢያትሪስ? እረ እኔ ከእርስዎ የምደብቀው ምንም ነገር የለኝም ።"

"ማክሲም ወራሽ የሚሆነው ወንድ ልጅ ቶሎ ብትወልጂለት

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዴት በፈቀደ ። መቼም መከላከያ እንኳን የምትጠቀሚ አይመስለ ኝም።"

ጭውውቱ ወደ ሌላ አቅጣጫ ማምራቱ ቢያስደነግጠኝ "እኔ እቴ፣ ስሙንም አላውቀው ።" አልኳቸው እየተቻኮልኩ ።

"ምነው ይህን ያህል መደንገጥሽ? እኔ ለከፋት ያልኩት አይደለም ። የዘመኑ ሙሽሮች የማያውቁት የለም ። በተለይማ እንደ አደን ፣ ፈረስ መጋለብ አይነት የሚወዱ ከሆነ እንደተዳሩ መውለዱን አይፈቅዱትም ። ያንቺ ስእል መሳል ግን ልጅ ወልዶ ከማሳደጉ ጋር እምብዛም ስለማይጋጭ ችግር አይፈጥርብሽም ።" ካሉ በኋላ "በነገራችን ላይ ፣ የስእል ስራሽን ከምን አደረስሽው?" በማለት ጠየቁኝ ።

"አይ እባክዎ ብዙም አልለማመድ" ስል መለስኩላቸው ።

ከዚያም ስለ ላኩልኝ መፃህፍት ጠይቀውኝ በጣም እንደወደድኳ ቸው ከምስጋና ጋር ገለፅኩላቸው ።

መኪናቸውን በፍጥነት እያሽከረከሩ ፣ መንገድ ላይ የሚያጋጥሙ ንን ተሽከርካሪዎች እየቀደሙ ፣ መተላለፊያ የሚዘጉብንን በጥሩንባ እያስደነገጡ ከማስለቀቃቸውም በላይ ሲገላምጧቸውና ሲሰድቧቸው ሳይ አስደነገጡኝ ። በጉዟችን ላይ አንዳንድ ነጥቦችን እያነሱ ሲጠይቁኝ እጥር ምጥን ያሉ መልሶች እሰጣቸው ነበር ። ካርታ እጫወት እንደሆነ ጠየቁኝ ። በቂ ችሎታ እንደሌለኝ ስነግራቸው ፣

"ስለ እርሱ ግድ የለሽም ። ትንሽ ካወቅሽበት ሌላውን ትማሪያለሽ። እኔ በሽታዬ የመማር ፍላጐት የሌለው ሰው ብቻ ነው ። አሊያማ ይህ ክረምት እንዲሁ ዝም ብሎ ተጎልቶ ወሬ በመሰልቀጥ ብቻ መቼ ይገፋል ብለሽ" አሉኝ ።

መልስ አልነበረኝም ። ቀጠል አደረጉና "ያለፈው ገና ከእኛ ጋር ብትኖሪ እንዴት በተደሰትሽ ። ጥቂት እንግዶች ጋብዘን ስለነበረ ስንደሰት ነው ያመሸነው ። ጂልስንማ ብታይው በሳቅ ትፈርሺ ነበር ። በእንዲህ ዓይነቱ አጋጣሚ ልዩ ልዩ ልብሶች ለብሶ ሰውን ማሳቅ ነፍሱ ነው ። አንድ ሁለት መለኪያ ሻምፓኝ ከተጎነጨማ ጨዋታው ሁሉ ከየት እንደሚመጣለትም አላውቅ ። ልዩ ሰው ነው የሚሆነው ። እንዲህ ሲሆን ያየው ሁሉ ቲያትረኛ ቢሆን እንዴት ባማረበት ነው የሚለው ። እናልሽ

t.me/OLDBOOKSPDF

በዚያን ዕለት ዲኪ ማርሽ ከሚባለው ወዳጃችን ጋር ሆኖ የሴት ቀሚስ ለብሰው ሲዘፍኑ በሽንታችን ነው የታጠብነው ።" ሲሉኝ ፈገግ ብዬ ፦

"ለካስ እንዲህ ኮሚክ ኖረዋል!" አልኳቸው ። ቢያትሪስም ያለፈ ትዝታቸውን እያስታወሱ ከትከት ብለው ሳቁ ። እርሳቸው እንዲያ ሲንተከተኩ እኔ ደግሞ 'ለሚመጣው ገና በዚህ አይነቱ ግብግብ ላይ ተገኝ እንዳይሉኝ ብቻ ፡ ምን ችገረኝ? ጊዜው ይድረስና የዚያኔ እንደምንም ብዬ እንፍሉዌንዛ እንዲይዘኝ ማድረግ ነው' ብዬ ብቻዬን አብሰለሰል ነበር ። አፈ—መንገዳቸውንም ስለ ማንደርሌይ ዓመታዊ ግብግብ ሲያነሱብኝ በሽታዬ ተቀሰቀሰ ። እዝማሚያዬ ባያምራቸውና የመንደሩ ውስጥ ጠመዝማዛ መንገድ ትኩረታቸውን ቢስበው ሀሳባቸውን በአጭሩ ቀጩ ልኝ — ግልግል ።

ስለ ሚስዝ ዳንቨርስና ፈቭል ስለሚባለው ሰውዬ ልንገራቸው ! አልንገራቸው? እያልኩኝ ከሕሊናዬ ጋር ስሟገት ቆይቼ "ቢያትሪስ" አልኳቸው ስማቸውን ለውሳኔዬ ማብሰሪያ ተጠቅሜ "ጃክ ፈቭል የሚባል ሰው ያውቃሉ?"

"ጃክ ፈቭል አልሽኝ ? ቆይ እስቲ ፡ ይሀን ስም የሰማሁ ይመስለኛል። አምን ልጄ ፡ ቆየት ብሏል እንጂ አንዴ ሳላየው አልቀርም ። የሆነ ማጋጣ ብጤ እኮ ነው ።"

"ሚስዝ ዳንቨርስን ለመጠየቅ ትናንት ማንደርሌይ መጥቶ ነበር ።"

"እውነት? ይመጣ ይሆናል..."

"እንዴት? ይመጣ ይሆናል ሲሉ ምን ማለትዎ ነው?"

"የርብቃ የአጎቷ ልጅ ነው መሰለኝ ።"

ደነገጥኩ ። ርብቃ ይሀን ዓይነት የአጎት ልጅ ይኖራታል ብዬ ፈፅሞ አልሜም አላውቅ ። ድንጋጤዬን በአድናቆት ለመሸፈን እየተጣጣርኩ "ነው እንዴ ?" ስላቸው ፡

"አምን ፡ እርሷ እያለች አዘውትሮ ማንደርሌይ ይመጣል ነበር መሰለኝ" ከአስተያየታቸውና ከአነጋገራቸው በነገሩ ለመግፋት የፈለጉ አይመስሉም ነበር ።

"እኔ ሰውዬውን ገና ሳየው ለምን እንደሆነ እንጃ ቅሩር አለኝ" ብዬ

t.me/OLDBOOKSPDF

አፍ አፋቸውን ስጠብቅ "ቢልሽም አይፈረድብሽም" ብለው በአጭሩ መለሱልኝ ። ፈቭል ፡ መምጣቱን ምስጢር አድርገሽ ያዢው እንዳለኝ ብነግራቸው ያልታሰበ ችግር ሊፈጥር ይችላል ብዬ በመስጋት ተውኩት ።

ጥቂት እንደተጓዝን ከአንድ ትልቅ ግቢ ስንደርስ በሩ ተከፈተልንና ገባን ። "አሮጊቷ ብርሃኗ እየደከመ ነው ። ከሰሞኑ ደግሞ ትንሽ ወሰድ ስለሚያደርጋት ግር እንዳይልሽ" ሲሉ አስጠነቀቁኝ ቢያትሪስ ። ከመኪናው እንደ ወረድን "እንደምንመጣ ለሞግዚቷ ደውዬ ስለነገርኳት ምንም ችግር አይኖርም" አሉኝ በማያያዝ — ሲያረጋጉኝ ።

ቢያትሪስ በመጀመሪያ ከተቀበለችን ኖራ ከምትባለዋ ሠራተኛ ጋር ካስተዋወቁኝ በኋላ ስለ አሮጊቷ ጤንነት ሲጠይቋት "ምንም አይሉም ። እንዲሁ ወሰድ መለስ እያደረጋቸው ነው ። እስቲ ግቡ እናንተን ሲያዩ በጣም ደስ ይላቸዋል ።" ብላ ወደ አዳራሹ መራችን ።

አዳራሹንና ጥቅጥቅ ባሉ ቁሳቁሶች የተመላውን እልፍኝ አልፈን ወደ በረንዳው አመራን ። በበረንዳው ጠርዝ ላይ የቢያትሪስን አያት በተሽከርካሪ ወንበር ላይ ተቀምጠው አየኋቸው ። ግራና ቀኝ በትራስ ተከበው በቡልኮ ታጅለዋል ። ቀረብ እንዳልኩ ከማክሲም ጋር እንደሚመሳሰሉ መገንዘቡ ቅፅበትም አልጠየቀኝ ። በተለይ ማክሲም ሲያረጅና ሲደክም ቁርጥ እርሳቸውን እንደሚመስል ከወዲሁ ታየኝ ።

እኛን ስታይ ሞግዚታቸው ለአሮጊቷ ታነብላቸው የነበረውን መፅሐፍ አጥፋ ብድግ ብላ ተቀበለችን ። ቢያትሪስ "ወቸው ጉድ! አሮጊቷ በርትታ የለም እንዴ! በዚህ በሰማኒያ ስድስት አመታ እንዲህ መሆኗ መች አነሳት ። ተአምር እኮ ነው ።" ብለው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው "እምዬ ይሽውልሽ በሰላም ገብተናል" አሏቸው ።

"ውይ በሞትኩት ፡ ቢያትሪስዬ መጣሽ እንዴ? ነይልኝ እስቲ ልሳምሽ የኔ እመቤት" አሉ አሮጊቷ ፈታቸውን ወደኛ አዙረው ።

ቢያትሪስ ጎንበስ ብለው እየሳሟቸው "የማክሲምም ባለቤት ልይሽ ብላ ይጮት መጥቻለሁ ። ሥራ በዝቶ አልመች ብሏቸው እንጂ ቀድም ብለው ሁሉ ከማክሲም ጋር ሊመጡ አስበው ነበር" አሏቸውና ቀና ብለው ጎንተል አድርገውኝ "ሳሚያት እንጂ" ሲሉ በሹክሹክታ ነገሩኝ ። ጎንበስ ብዬ ሳምኳቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

አሮጊቷ ፊቴን እየዳሰሱ "ጎሽ የኔ ድምቡሽቡሽ ፡ እንኳን መጣ
ልኝ። ምነው ታዲያ ማክሲምን ይዘሽው አልመጣሽ?" ሲሉኝ

"ማክሲም እኮ ሎንዶን ነው ያለው ። ዛሬ ማታ ነው የሚገባው
አልኳቸው ።

"በሚቀጥለው ጊዜ ግን ይዘሽው እንድትመጪ ። ነይ እስቲ በደን
እንዳይሽ ፊት ለፊቴ ቁሚ በይ" ካሉኝ በኋላ ወደ ቢያትሪስ ዞር ብለው
"ቢያትሪስዬ አንቺም በዚህ በኩል ተቀመጪ ። ለመሆኑ ሮጀር ደህ
ነው ? ቆይ ፡ ይሄ ወስላታ መጥቶ አይጠይቀኝም ማለት ነው ?" አሏቸው ።

"ነሐሴ ግድም ይመጣል ። አክስፎርድ ሊገባ እኮ ነው" ሲሉ
ቢያትሪስ ጮክ ብለው ነገሯቸው ።

"እውነትሽን ነው? መቼም ባየውም አላውቀው ፡ ትልቅ ጎረምሳ
ሳይሆን አይቀርም"

"አዎን ከአባቱ የበለጠ ቀውላላ ሆኗል"

ቢያትሪስ ስለ ቤተሰባቸውና ስለ ኑሯቸው ዘርዘር አድርገው
ለአሮጊቷ እየነገሯቸው ሳለ ሞግዚቷ ጅምር ሹራቧን ለመሥራት አንስታ
ታጫውተኝ ጀመር ። የማንደርሌይ ኑሮን ለምጀው እንደሆነ ላቀረበችልኝ
ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ ከሰጠኋት በኋላ "ማንደርሌይን በጣም ነበር
የምንወደው እኮ ። አሁን እርሳቸው ከተዳከሙ ወዲህ ብቅ ማለቱንም
ትተነዋል ።" አለችኝ ። ሌሎች ሌሎች ጥያቄዎችንም እያነሳች ስንጨዋ
ወት በንግግሯ ጣልቃ "እኛ" "እኛ" ማለቷ በነጋሲያን ዘይቤ መጠቀሟ
ይሁን ወይም እርሷንና አሮጊቷን እንደ አንድ ሰው ቆጥራ እንደሆነ
ሊገባኝ አልቻለም ።

አደን እወድ እንደሆነ ጠየቀችኝ ። ልምድ እንደሌለኝ ነገርኳት ።
አደን የማንደርሌይ ባሕል በመሆኑ መለማመድ እንደሚገባኝ ስትነግረኝ
ቢያትሪስ ጣልቃ ገቡና ስእል የመሳል ልምድ እንዳለኝ ነገሯት ። አያቷ
ጆሯቸውን አቁመው ፊታቸውን ወደኛ ማለታቸውን ሲያዩ የሚወራው
ስለኔ ሰዓሊነት መሆኑን አስረዷቸው ።

"እቤታችን ውስጥ ሰአሊ ከየት መጣ ደግሞ?" አሉ አሮጊቷ ።

"አዲሷ ልጅሽ ናታ! እስቲ ለሰርጓ ምን ዓይነት ስጦታ እንደሰጠኋት
ጠይቂያት"

t.me/OLDBOOKSPDF

“ቢያትሪስ ምን እንደምታወራ አይገባኝም” አሉና አሮጊቷ ወደኔ መለስ ብለው “ሰዓሊ መሆንሽን መቼ አውቅና? እቤታችን ውስጥ ሰዓሊ ኑሮም አያውቅ” አሉኝ ።

“ዝም ይበሏቸው እማማ ፡ ቢያትሪስ ሲቀልዱ ነው ። ለጊዜ ማሳለፊያ እሞነጫጭራለሁ እንጂ ሰዓሊ አይደለሁም ። በእርግጥ ቢያትሪስ ለሰርጌ መፃህፍት ሰጥተውኛል” አልኩ ።

“መፃህፍት ሰጠችኝ? የማንደርሌይን ቤተመፃህፍት ያጣበቡት መፃህፍት የት ገቡና? አሆሆ! ወደ ማንደርሌይ መፃህፍት ማምጣት ፡ አሶች በውሀ እጦት እንዳያልቁ አንድ ባልዲ ውሃ ባህር ውስጥ እንደመጨመር እኮ ነው እናንተዬ” ብለው ከአንጀታቸው ሲስቁ ሁላችንም ከሳቁ አገዝናቸው ።

መፃህፍቱ ለየት ያሉ የስእል መፃህፍት መሆናቸውን ቢያትሪስ ቢያስረዷቸውም አሮጊቷ ሊዋጥላቸው አልቻለም ። እንዲያውም “ምን አይሰማ ጆሮ! መፅሀፍ እንደ ጋብቻ ስጦታ ሲሰጥ ገና ዛሬ መስማቴ ነው። እኔ ስዳር ማንም ሰው መፅሐፍ አልሰጠኝም ። እረ ወዲያ ፡ ቢሰጡኝስ? ስጦታ ብዬ ልቀበል ? ስራም አላጣሁ ። ንክች አላደርገውም ነበር ። አላነበውም ነበር” አሉና ሳቃቸውን ሲቀጥሉ ቢያትሪስ ብሽቅ አሉ ።

ወዲያው አሮጊቷ “ይህች ኖራ ምን ነካት? ሻዬን አትሰጠኝም እንዴ?” ብለው ሲጮሁ “ምነው እማማ? አሁን አይደለም እንዴ የጠጣነው? አሁን አሰኙቶዎት ነው?” በማለት ሞግዚቷ ትራሳቸውን ልታስተካክልላቸው ብድግ አለች ።

ሁሉም ነገር ስልችት አለኝ ። ዕድሜ የተጫናቸውን ሰዎች መንከባከብ ምንኛ አስቸጋሪ እንደሆነ ተሰማኝ ። ሕፃናትን ወይም ቡችሎችን መንከባከቡ በስንት ጣዕሙ! ሽማግሌዎችንና አሮጊቶችን ማስታመሙ ይበልጥ የሚከብደው ፡ የሚበረክትላቸው ግልጋሎት ሁሉ ምን ያህል አክብሮት የታከለበት መሆን አለመሆኑን አጥብቀው መቆጣጠራቸው ነው ። ህፃናት ይህን አያውቁም ። ህፃናት ምን እንደሚያስፈራራቸውና ምን እንደሚያስፈነድቃቸው ፡ እወቁልን እንጂ ስገዱልን ተሽቆጥቁጡልን መች ይወጣቸውና ።

የማክሰኞ አያት እንዲያ ብርሃናቸው ፈዞ ፡ አቅሙ ከድቷቸው ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ኩርምት ብለው ሲቀመጡ ምን ይሰማቸው ይሆን? የጥንቱ የጥዋቱ የልጅነት ጊዜያቸው እፊታቸው ድቅን ይል ይሆን? የኮረዳነት ዘመናቸው ላይመለስ ማለፉስ ምን ያህል ይፀፅታቸው ይሆን? ወይስ የዕድሚ ጫና ያለፈ የሕይወት አሻራቸውን ሞራሹን ከአእምሯቸው ፍቆ ከቆዳ መሸብ ሸብ ፡ ከቁርጥማት ፡ ከጉልበት መፍሰስና ከመሰል የእርጅና አስከፊ ገፅታዎች ጋር ብቻ ነው ያቆራኛቸው?

ከዚህ የሀሳብ ጉዞዬ የመለሰኝ የአሮጊቷ እንደገና 'የሻይ ያለህ' ብሎ ማጉረምረም ነበር ። ሞግዚቷ በለዘብታ አረጋጋቻቸው ። ይህን ጊዜ "መጥኔውን ይስጥሽ እቴ! ምን ዓይነት ወፍራም ቆዳ ነው ያለሽ?" አሉ ቢያትሪስ ወደ ሞግዚቷ ጆሮ ተጠግተው ።

"እኔ እንደው ለምጄዋለሁ" አለች ሞግዚቷ በፈገግታ "አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር እማማ ያን ያህልም የሚያስቸግሩ አይደሉም ። በዚህ ላይ ደግሞ ሠራተኞች ሁሉ ቅኖች ስለሆኑ እምብዛም አይከብደኝም"

ኖራ ሻይ ይዛ ብቅ አለች ። አሮጊቷ "ምነው ይህን ያህል ዘገየሽ?" ብለው ሲጮሁባት በእርጋታ ስትመልስላቸው በጣም ገረመኝ ።

ፊዴዋታው ሌላ መስመር ይዞ እያወጋን የማክሲምን ስም ሲሰሙ አሮጊቷ "ለመሆኑ ማክሲም ለምን አልመጣም?" የሚል ጥያቄ ሰነዘሩ ።

"ግብግ ተጠርቶ ሎንዶን ሂዷል ብለን ነግረንሽ የለም እንዴ? ጂልስም እኮ እዚያው ነው" አሉ ቢያትሪስ በመሰላቸት መልክ

"ነው እንዴ?" በማለት ተጠሉ ሲትዮዋ "ጣልያን ሂዶ ነበር የምትሉት ደግሞ ፡ እዚያ ምን ሊያደርግ?"

እኔና ማክሲም በሚያዚያ ወር ጣልያን እንደነበርንና አሁን ግን ወደ ማንደርሌይ መመለሳችንን ቢያትሪስና ሞግዚቷ በየተራ ነገሯቸው ። እኔም ላክልበት ብዬ "በአሁኑ ወቅት ማንደርሌይን ቢያዩት እንዴት ያስደስት መሰልዎት ። ዕጬረዳው በየሜዳው ፈክቶ ሲታይ ውበቱ ሌላ ነው። ረስቼው ነው እንጂ ጥቂት ዕጬረዳ ይዤልዎት ብመጣ ጥሩ ነበር" አልኳቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

አሮጊቷ "ጥሩ ነበር ፡ ዕጌረዳ በጣም ነው የምወደው" አሉና በእኒያ ቡዝዝ ባሉት አይኖቻቸው ትክ ብለው እያዩኝ "አንቺም ማንደርሌይ ውስጥ ነው የምትኖሪው እንዴ?" ሲሉ ጠየቁኝ ።

ምን ልመልስላቸው? ቢያትሪስ "ምን ማለትሽ ነው እምዬ? የማክሲም አዲሷ ሙሽራ ናት ብለን ስንት ጊዜ ነግረንሽ?" ብለው ባይገላግሉኝ ኖሮ ምን ይውጠኝ እንደነበር አልገባኝም ።

"ሁላችሁም ትለፈልፋላችሁ እንጂ ምን እንደምታወሩም አይገባኝም።" አሉ አሮጊቷ ፊታቸውን አጨፋግደው እየተመለከቱኝ "እንቺ ደግሞ ማንነሽ? ከዚህ ቀደም አይቼሽም አላውቅ ። ማንደርሌይ ውስጥ እኖር ነበር ነው የምትዪኝ? በፍፁም ትዝ አትዪኝም ። አንቺ ቢያትሪስ ፡ ይህች ልጅ ማን እንደሆነች ለምን አትነግሩኝም? ቆዩኝ እንጂ ፡ ደግሞ ይሄ ማክሲም ርብቃን ለምን ይዟት አልመጣም? ርብቃን እኮ ነፍሴ እስኪወጣ ነው የምወዳት ። የት እንዳለች አትነግሩኝም?" ብለው ዙሪያቸውን በግልምጫ ቃኝተ ከመካከላችን ፈልቅቀው ያወጧት ይመስል ።

ፀጥታ ። የአሮጊቷ አነጋገር ሁላችንንም ቢያስደነግጥም የእኔው ግን የብቻ ነበር ። ሞግዚቷ ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ ወደ አሮጊቷ ስትጠጋ "እናንተ ሰዎች አትሰሙኝም ማለት ነው? ርብቃን አምጡልኝ እኮ ነው የምላችሁ።" አሉ አሮጊቷ ድምፃቸውን ረገጥ አድርገው ።

ቢያትሪስ በጣም እንደተናደዱ የገባት ሞግዚቷ "ሚስዝ ሌሲ ፡ ብትሄዱ ይሻላል ። አንዳንድ ጊዜ እንዲህ እንደመቃዠት ያደርጋቸዋል ። መቼም በዛሬ ቀን መሆኑ መጥፎ አጋጣሚ ነው ። ሚስዝ ደዊንተር እንደማይከፋዎት ተስፋ አደርጋለሁ" አለች ።

"በፍፁም ፡ እንዳልሺውም ብንሔድ ይሻላል" አልኩ

እኔና ቢያትሪስ ለመሄድ ስንዘጋጅ አሁንም አሮጊቷ "ርብቃ የት ነው ያለችው? ማክሲም ለምን ይዟት አልመጣም?" በማለት ጥያቄያቸውን ሲደግሙ ሰምተን እንዳልሰማ ዝም ብለናቸው ወጣን ።

ሁለታችንም በሀሳብ ሰጥመን ዝም ዝም ብቻ ሆነ ። ብዙ ከተጓዝን በኋላ ነበር ቢያትሪስ "እኔ እኮ ምን አባቱ እንደምል መላው ጥፍት አለኝ ። በጣም ነው የማዝነው ። እባክሽን አትቀየሚኝ" አሉኝ ።

"ምን ማለትዎ ነው ቢያትሪስ? ምንድነው የሚያስቀይመኝ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

አልኳቸው ።

“እንዲህ እንደምትሆን በፍፁም አላውቅም ። አውቄ ቢሆንማ መቼ ይዤሽ እመጣ ነበር?”

“አሁን ይህን ሁሉ ምን አመጣው? እርስዎ ምን አጠፉና ነው እንዲህ የሚሉት? እኔ ነገሩ ሁሉ ይገባኛልና ሁለተኛ ስለዚህ እንዳያነሱ ብኝ።”

“ግራ ግብት ነው ያለኝ ። ስላንቺ ደብዳቤ ፅፌላታለሁ ። እኔም ማከሲምም በቃላችን ስንቴ ነግረናታል ። ጋብቻችሁ የተፈፀመው ከአገር ውጭ መሆኑን ሰምታ እንኳ እንዴት ነበር ደስ ያላት ። ታድያ ምንድነው እንዲህ የሚያደርጋት?”

“እንዴ ፣ ምን ማለትዎ ነው? የፅድሜውም ነገር አለ እኮ ። እንዴት ብለው ሊያስታውሱ ይችላሉ? የእርሳቸው አእምሮ መዝግቦ የያዘው ማከሲምንና እኔን ሳይሆን ማከሲምንና ርብቃን ነው።”

“ለርብቃ ልዩ ፍቅር እንደነበራት ረስቼው እኮ ነው ። በአደጋ መሞቷ ሲነገራት እንኳን አልተዋጠላትም ነበር ። ይህን ሁሉ እንዴት እንደረሳሁት እኮ ነው ጭራሽ አልገባ ያለኝ ። መቼም በዛሬ ጥፋቴ ሁለተኛ ሰው አታደርጊኝም” አሉ ቢያትሪስ ግፍግፍ ብለው ።

“ምነው ቢያትሪስ ቢተውት? ምንም አልመሰለኝ እያልኩዎት?”

“ርብቃም እኮ አሮጊቷን በደንብ ነበር የምትንከባከባት ። በየጊዜው ማንደርሌይ እያስመጣቻት ታዝናናት ነበር ። ታዲያ እማማም ርብቃን ያገኘች ዕለት ስትፈነድቅ መዋል ነበር ። ርብቃ ደግሞ ከተጫዋችነቷም በላይ ሰውኚየማግባባት ልዩ ችሎታ ነበራት ። ከሴት ፣ ከወንዱ ፣ ከህፃን ፣ ከሽማግሌው ከእንስሳት ሳይቀር መግባባት ታውቅበት ነበር ። አሮጊቷ ይህ ሁሉ ትውስ እያላት ይሆናል።”

“ይገባኛል ፣ ይገባኛል” አልኳቸው ቢያትሪስን እንደመሰላቸት ብዬ ‘ምንድነው ይህን ያህል? ምነው ጨዋታውን ቢቀይሩት?’ ብዬ ለራሴ በውስጤ እየተናገርኩ ሳለ “መቼም ጂልስ ሲሰማ እንዴት እንደሚጮህ ብኝ እኔ እንጃ” አሉ ቢያትሪስ በመቀጠል ።

“ለምን ይነግሯቸዋል? ለእርሳቸው መንገሩ ነገሩ እንዲባዛና እንዲጋ ነን ከማድረግ ሌላ ምን ፋይዳ ይኖረዋል ብለው?”

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንድ ነገር እንዳስከፋኝ ከፊቱ ተረድቶ መጠየቁ አይቀርም ፡ በመሃከላችን ምንም መደባበቅ ስለሌለ መንገሬ የግድ ነው" አሉኝ ።

የባሰ አታምጣ! የአሁኑ ነገር ደግሞ ይበልጥ የሚረብሸኝ ሆነ ። እንዲያውም ምን አማኝቹ ያለ ምድረ—ወሬኛ ሁሉ ይህንን ሰምቶ እንዴት እንደሚጠቃቀስብኝ ፡ እንዴት እንደሚያሽሟጠጠኝ በምናቤ ቢታየኝ ተረበሽኩ ።

ቢያትሪስ ባለቤታቸውን ለመቀበል እንደሚሄዱ ነግረውኝ ተሳስመን ተለያየን ። እቤታችን በር ላይ የማክሲምን መኪና በማየቱ እስካየውቸኩልኩ ። ደረጃውን እንዴት እንደወጣሁትም አላውቀው ።

ከቤተ መፃህፍቱ በር ስደርስ ከማን ጋር እንደሆነ ባይገባኝም ማክሲም ፈክ ብሎ ሲናገር ሰማሁት ። "ለወደፊቱ ማንደርሌይ ድርሽ እንዳትል ብለሃል ብለሽ እንድትፅፊለት ። ገባሽ?… ያ አይደለም ቁም ነገሩ ። ማንም ይንገረኝ ማን ትናንትና መኪናው እዚህ እንደነበረ ሰምቼአለሁ ። ከእርሱ ጋር የግድ መገናኘት አለብኝ የምትዪም ከሆነ ከቅጥር ግቢዬ ውጭ እንዳሻችሁ ። ደጃፌን ብቻ አይርገጥብኝ ብዬሻለሁ አይርገጥብኝ ። ትዕዛዜን የምታከብሪ ከሆነ ይህ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያዬ እንደሆነ ይግባሽ ።" አለ ማክሲም ምርር ብሎ ።

ቀስ ብዬ ወደኋላዬ ተመለስኩ ። የቤተ መፃህፍቱ በር ሲከፈት ወደ አንዱ ጥግ ዞር አልኩ ። ሚስዝ ዳንቨርስ በሩን ከፍተው ሲወጡ እንዳያዩኝ በመስጋት ከግድግዳው ጋር ልጥፍ ብዬ በጨረፍታ አየኋቸው ። በጣም የተናደዱ ይመስላሉ ።

ጥቂት ቆይቼ የቤተ መፃህፍቱን በር ከፍቼ ገባሁ ። ማክሲም ጭንቅላቱን አንድ ደብዳቤ ላይ ደፍቶ ጀርባውን ሰጥቶኝ ቆሞ አገኘሁት ። እንቅስቃሴዬን ሰምቶ ዞሮ "ማነው ደግሞ?" ብሎ ሲዞር ፊቴን በፈገግታ አድምቄ እጁን ለሰላምታ ዘርግቼ ተጠጋሁት ።

"አሃ ፡ አንቺ ነሽ እንዴ?" ብሎ ተቀበለኝ ። ፊቱ ጠቁሯል ። የንዴት መልክ ይነበብበታል ። ግንባሬ ላይ ስሞኝ እጁን ትከሻዬ ላይ ጣል አድርጎ የት እንደነበርኩ ጠየቀኝ ። ነገርኩት ።

"አሮጊቷ እንዴት ናት?"

"ደህና ናቸው"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ቢያትሪስ ለምን አልገባችም?"

"ባለቤታቸውን ለመቀበል ችኩለው ሄዱ ።" ካልኩት በኋላ እጆቹን በእጆቼ እየዳሰስኩ "አቤት ፡ ዓመት የተለያየን ነው የመሰለኝ ፡ እንዴት ነው የናፈቅከኝ?" ስለው "እውነት?" አለና ፈገግ አለ ።

"ሎንዶን እንዴት ነው? ይሞቃል እንዴ?" ስል ጠየቅኩት

"በጣም እንጂ ፡ እኔ እኮ በጣም ነው የምጠላው" አለኝ

ከሚስዝ ዳንቨርስ ጋር በምን ሲጨቃጨቁ እንደቆዩ ፡ ስለፌቭል ደግሞ ማን እንደነገረው እንዲነግረኝ በምን ልኮርኩረው ብዬ ሳስብ ቀየሁና "ምን ነው ? ይህናም አይደለህም እንዴ ? የከፋህ ትመስላለህ" ስለው

"በጣም ስለደከመኝ ነው ። በቀን ሁለት ጊዜ ያን ያህል ርቀት መመላለሱ ማንንም አያደክምም እንዴ?" አለኝ ።

እንዳልሰመረልኝ ተረድቼ "እረ በጣም ያደክማል ። እኔም ሙትት ነው ያልኩት" ብዬው ለኩርከራዬ ልጓም አበጀሁለት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አሥራ አምስት

ሳንበት ። እኔና ማክሲም ከፍራንክ ከሮውሌይ ጋር ሆነን እለቱን በሰላም እናሳልፋለን ነበር እቅዳችን — የእንግዶች ተግተልትሎ መምጣት ሰላማችንን አደፈረሰብን እንጂ ።

የመጀመሪያዎቹን እንግዶች የያዘው መኪና በገባ በግማሽ ሰዓት ውስጥ ሌላው መኪና ተከተለ ። ጥቂት ቆይቶ ደግሞ ሶስት እግረኛ እንግዶች ከተፍ አሉ ። ሳንወድ የግዳችንን ማስተናገዱን ተያያዝነው ። እንደተለመደው በየመናፈሻው ፡ በየመስኩ ስናንሸራሸራቸው ቆየን—የፍሰሐ ሽለቆ ጉብኝትም ሳይዘነጋ ።

ለመክሰስ ወደ ቤት ተመለስን ። እንግዶቻችንን በሻይና በኬክ እያስተናገድን ሳለ እመት ክሮዋን የሚባሉት እንግዳችን "እህ ፡ አዩ ሚስተር ደዊንተር ፡ አንድ ነገር እጠይቅዎታለሁ ብዬ እስቤ ከዛሬ ነገ ስል ስንት ጊዜዬ መሰልዎት ። እንዴት ነው ፡ ያንን የማንደርሌይን የልዩ አልባሳት በአል ማዘጋጀቱን ተዋችሁት ወይስ?" ብለው ጥርሳቸውን ብልጭ አደረጉት ።

እኔ አቀርቅሬ ሻዩን መጠጣት ብቻ ሆነ ። ማክሲምም መልስ ከመስጠቱ በፊት ጥቂት ፀጥ ካለ በኋላ ለዘብ ብሎ "እኔ እንጃ ፡ ትዝ ብሎኝም አያውቅ ። ሌላ ያሰበበት ሰውም ያለ አይመስለኝም ።" አለ ።

"እንዴ? ኧረ እኛ ሁላችን ዘወትር እንዳስታወስነው ነው ። ምን ያህል ያስደሰተን እንደነበረ ልነግርዎት አልችልም ። እንዲያው እንደ ምንም ብለው ያስቡበት እባክዎትን" አሉ እመት ክሮዋን ልመናቸውን

t.me/OLDBOOKSPDF

በማጠናከር ።

“እኔ እንጃ” አለ ማክሲም “የማቀነባበር ጉዳይ ስለሆነ እስቲ ፍራንክን ጠይቂት ። እርሱ ነው የሚያውቅበት ።”

እሙት ክሮዋን ወደ ሚስተር ክሮውሌይ ዞር ብለው ··አባክህን” ሲሉት ሌሎችም ተያርበው ይጠይቂት ገቡ ።

“እኔ ምን ችገረኝ ፡ ማክሲም የሚስማማ ከሆነ ማዘጋጀቱ ችግር አይሆንም ። ወሳኞቹ እርሱና ሚስዝ ደዊንተር እንጂ እኔ አይደለሁም” አለ ሚስተር ክሮውሌይ ።

ዓይኖች ሁሉ አንዴ ወደኔ ዞሩ ። “እንግዲህ አቢቱታችን ወዳንቺ ሳይመጣ አይቀርም” አሉ እመት ክሮዋን “ባለቤትሽን ማሳመን የምትቺ ዱው አንቺ ነሽ ። እንዴ ፡ ሌላው ቢቀር በአሉ ለሙሽራነትሽ ክብር ሊዘጋጅ ይገባል እኮ”

ሌላው ሌላውም ሁሉ በእርሳቸው ሀሳብ ላይ ሲያክል አንዱ እንግዳ ብድግ ብሎ “ሠርጋችሁን አለመብላታችን ሲቆጨን ይህን በአል ልትነፍጉን አይገባም ። እስቲ በአሉ ይዘጋጅ የምትሉ እጃችሁን አውጡ ። አያችሁ··· አንድም ተቃዋሚ የሌለበት?” ሲል ጭብጨባና ሳቅ አስተጋባ።

ይህን ጊዜ ማክሲም ወደኔ ዞር ብሎ “ታዲያ ምን ይመስልሻል?” ሲል ጠየቀኝ ።

“እኔ እንጃ ፡ ቢዘጋጅ ግድ የለኝም” አልኩት ።

ከዚያም የበአሉን መዘጋጀት የሚደግፉ ልዩ ልዩ ሀሳቦች ሲሰነዘሩ ማክሲም ትክ ብሎ ያየኝ ነበር ። በኔ አይናፋርነት በእንዲህ አይነቱ በአል ላይ መገኘቱ አይሆንላትም ብሎ ገምቶ ይሆን? ታሳፍረኛለች ብሎም ይሆናል የሚል ሀሳብ ቢቀሰቀስብኝ ሁሉንም እንዳመጣጡ ተቋቁሚ በሚገባ መወጣት እንዳለብኝ ሲሰማኝ “መቼም ልዩ በአል እንደሚሆን ይታየኛል” አልኩ ።

በዚሁ እንዲዘጋጅ በመወሰኑ ማክሲም ኃላፊነቱን ለሚስተር ክሮውሌይ ሰጠው ። ሚስዝ ዳንቨርስም በደንብ ሊረዱት እንደሚችሉ በመጥቀስ ተባብረው እንዲያዘጋጁት ነገረው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ብዙም ሳይቆይ እንግዶቹ ለቀውን ሲሄዱ ትልቅ እፎይታ ተሰማን ። ማክሰ ም ከጀስፐር ጋር መጫወት ሲይዝ እኔና ፍራንክ ብቻችንን ቀርተን ነበር ። ሻዩን እየጠጣሁ ይህ የተባለው በአል ምን ሊመስል እንደሚችል በአእምሮዬ ሳጣ-ላላው ቆየሁ ። የተለያዩ ሰዎች ልዩ ልዩ ያልተለመዱና አስቂኝ ልብሶችን ለብሰው ወዲያ ወዲህ ሲንጎራደዱ ፡ ተመልካቹ በሳቅ ሲፈርስ ታየኝ ። ማክሰ ምስ ምን ዓይነት ልብስ ይለብስ ይሆን? እኔስ? ምን ለብሼ ፡ ምን መስዬ እቀርብ ይሆን? የሚለው ሀሳብ ሲመላለስብኝ ቆየና በመጨረሻም ቢሆን ፍንጭ ለማግኘት ይረዳኛል ብዬ በመገመት "የዚህ በአል ነገር ምን ይመስልሃል ፍራንክ ?" ስል ጠየቅኩት ።

"እኔ እንጃ ፡ እንግዲህ እንደሚሆን ይሆናላ ። ማክሰ ምም ስምምነቱን የገለፀ ስለሆነ መዘጋጀቱ አይቀርም" አለ ፍራንክ መስኩ ላይ ከጀስፐር ጋር ይጫወት የነበረው ማክሰ ምን በመስኮት እያስተዋለ ።

"ምን ያድርግ? እኒያ እመት ክሮዋን የሚባሉት ሴትዮ ውጥር አድርገው ሲያዙት እያየህ? ለመሆኑ እውነት ሌሎችም ሰዎች የእርሳቸውን ያህል ይህ በአል ይህን ያህል ያጓጓቸዋልና ነው እንዲህ የሚሆኑት?

"እንዴታ!" አለ ክሮውሌይ "አየሽ የዚህ አካባቢ ሰዎች ወግ አጥባቂዎች መሆናቸው ብቻ ሳይሆን የመዝናኛ ምንጫቸው ውሱን በመሆኑ በአሉን በጣም ነው የሚወዱት ። እመት ክሮዋን ደግሞ ላንቺ ክብር ሲባል እንኳን መዘጋጀት አለበት ሲሉ ከአንገት በላይ እንዳይመስልሽ ። አንቺም እኮ ሙሽራ መሆንሽን አትርሺ"።

"እርሱን ተወው እባክህ ፍራንክ ፡ ለእኔ የሙሽራነት ወግ ማዕረግ ማን ሰጠኝና? መልክ ላለው ሰርግ እንኳ መች ታደልኩና? ቪሎ የለ ፡ ሚዜ የለ ፡ አጃቢ የለ ፡ አበባ እንኳን በሌለበት አይደለም እንዴ ያገባሁት? ለእኔ ተብሎ የሚዘጋጅ ይህ ዓይነቱ የቢልት ዳንስ በአፍንጫዬ ይውጣ"

"የለም ፡ የለም እንዲህ አትበዪ ። እንዴት ያለ ቆንጆ በአል መሰለሽ። እንደምትደሰችበት ደግሞ ተስፋ አደርጋለሁ ። ይህን ያህልም ብዙ የሚያስጨንቅሽ አይደለም ። ግፋ ቢል እንግዶቹን ተቀብሎ ማስተናገድ ነው ። ብቻ አንድ ጊዜ ከኔ ጋር እንድትደንሺ አስቸግርሽ ይሆናል" ሲለኝ ሳቅ እፍን አደረገኝ ። ቅንነት የተሞላበት ድፍረቱ ደነቀኝ።

t.me/OLDBOOKSPDF

“እንድ ጊዜ ብቻ ? የፈለግከውን ያህል አጫውትሃለሁ ። እንዲያ ውም ካንተና ከማክሲም ጋር እንጂ ከማንም ጋር አልደንስም” አልኩት ።

“አይ ፤ ይህ እንኳን እንዴት ይሆናል ።” አለ ፍራንክ ኮስተር ብሎ “እንግዶች ሊቀየሙ ይችላሉ ። ከሚጠይቁሽ ሁሉ መደነስ አለብሽ”

ምስኪን ፍራንክ ። ባሾፍበትም ምንም ሊገባው አልቻለም ። ቅንነቱን ይበልጥ ተረዳሁለት ። ሳቁ እንዳይፈነዳ እየተጨነቅኩ ጨዋታ ውን ወደ ሌላ መራሁት “ስማ እንጂ ፤ ቅድም እኒያ እመት ክሮዋን ደግሞ አንደ ድሬስደን እረኛ መልበስ አለብሽ ሲሉ ሰማኋቸው? አንተስ በዚህ ሃሳብ ትስማማለህ ?” ስለው ፡—

“አዎን ፡ እስማማለሁ ። በደንብ የሚያምርብሽ ነው የሚመ ስለኝ ።” አለኝ ።

መቋቋም ቢሳነኝ ሳቄን ለቀቅሁት ። “ወይኔ ፍራንክ ፡ በጣም ደስ የምትል ሰው እኮ ነህ ። በጣም ነው የወደድኩህ” ስለው ደነገጠ ፡ ፊቱ በርበሬ መሰለ ። በመሳቄ ደግሞ ቅር ያለው መሰለኝ ።

“ይህን ያህል የሚያስቀ ነገር የተናገርኩ አልመሰለኝም” አለኝ። በዚህ መሃል ማክሲም ብቅ አለና “እንዲህ የሚያስፈነድቃችሁ ምን ብታገኙ ነው እባካችሁ?” ሲል ጠየቀን ።

“እረ ፍራንክህ ቀልደኛ ወጥቶታል ። እመት ክሮዋን እንዳሉት እንደ ድሬስደን እረኛ ብትለብሺ ያምርብሻል እኮ ነው የሚለኝ” አልኩት ሳቄን ሳላባራ

“እርሷን ተያት እባክሽ ፡ አስቸጋሪ ሴት ናት ። አሁን ግን ወጣም ወረደ በአሉን ለማዘጋጀት ማሰባችንን ሰዉ ሲሰማ አሰፍስፎ ነው የሚጠብቀን ። አንድም ሰው ሳይቀር መጥራት ያለብን መሰለኝ ። በአሉ የተሳካ እንዲሆንም ከአሁኑ ልናስብበት ይገባል ።” አለ ማክሲም ።

ፍራንክ “አይ ፡ ችግር የለውም ። የስም ዝርዝሩ ፡ የሌሎችም ፋይል ቢሮዬ ውስጥ ስላለ ቀላል ነው ። በፖስታዎቹ ላይ ቴምብር መለጠፉ ጊዜ ይፈጅ እንደሆነ እንጂ ሌላው እንኳን ...” ሲል ማክሲም ፈገግ ብሎ አቋረጠውና “ይህንን ሥራ እንኳን ላንቺ ነው የምንሰጥሽ” አለኝ ።

“እረ ግድ የለም ፡ እዚያው ቢሮ ውስጥ እንሰራዋለን ። ሚስዝ ደዊንተርን በምንም ነገር አናስቸግራትም” አለ ፍራንክ

t.me/OLDBOOKSPDF

ምንም ዓይነት ኃላፊነት ውስጥ እንዳልገባ ስለተዶረግኩ በእጅጉ ደስ ቢለኝም በሌላ ወገን ደግሞ ቱምብር ለመለጠፍ እንኳን ብቃት እንደሌለኝ መቆጠሬ ሳያሳፍረኝ አልቀረም ።

"ማክሲም ፡ አንተ ግን ምንድነው የምትለብሰው?" ስለው

"እኔ አያስፈልገኝም ። ደንቡ እንደዚያ አይደል እንዴ ፍራንክ?" ሲል መለሰ ማክሲም ወደ ፍራንክ ዞር ብሎ ።

"እኔ ግን የድፌስያኗን እረና ልብስ ብሞት አለብስም ። ልብስ መምረጥ ስለማላውቅበት ግን ምን አባቱ እንደሚበጀኝ እንጃ" አልኩ ።

"ወንርሽን በሪቫን ሽብ አድርገሽው <u>የወንደርላንዷን አሊስ</u> መምሰል ነዋ! እንዲያውም ጣትሽን ስትጠቢ ሳይሽ እርሷን ነው የምትመስይኝ" አለ ማክሲም ።

"ሉው እንጂ አትሳደብ ማክሲም ። ታየኛለህ ደግሞ ፡ 'ማን ናት ይህች ሴት?' እስክትሉ ድረስ አንተንና ፍራንክን ባላስደነግጣችሁ እኔ አይደለሁም"

"ፊትሽን ጥላሸት ተለቅልቀሽ ጠጣ አትምሰይ እንጂ የፈለግሽውን ብታደርጊ ደንታ የለኝም ።"

"እሺ ብቻ እንተያያታለን ። ምን እንደምለብስ ደግሞ እስከመጨረሻይቱ ደቂቃ ድረስ በምስጢር ስለምይዘው ማንም አያውቀውም ።" አልኩና "ና ጃስፐርዬ እነርሱ ያሻቸውን ይበሉ" በማለት ጃስፐርን አስከትዬ ስወጣ ማክሲም ይስቅብኝ ነበር ። ያሉትን ማዳመጥ ባልችልም ሲንሾኳሾኩ ግን ሰማኋቸው ።

ሰገነቱ ላይ በትካዜ ፈዝዤ ቀረሁ ። ጃስፐር እግሬ ስር እያነፈነፈ ቢኮረኩረኝም ቱቢም አላልኩት ። ጥፍሬን በጥርሴ ስበረክም ሀሳብ በአእምሮዬ አመነሻሽክ ነበር ። ማክሲም እስከ መቼ እንዲህ እንደ ህፃን ፡ ኃላፊነት እንደማያሰማኝ ፡ ደካማና ብልሹ ፍጡር እንደሚቆጥረኝ ሊገባኝ አልቻለም ። ሲሻው እንደ አንድ ፍሬ ህፃን ልጅ ወጉን እያሻሸ ያጫውተኛል ። ያላለው እለት ደግሞ አጠገቡ ቁጭ ብዬ እስከነአካቴው መፈጠሬን ረስቶ በራሱ ሀሳብ ይዋኛል ። እኮ እስከ መቼ ነው የእርሱን ዱካ ብቻ ተከትዬ ኋላ ኋላው ሱክ ሱክ የምለው? እንደ ባልና ሚስት ጎን ለጎን ቆመን ትከሻ ለትከሻ ተካክን ፡ እጅ ለእጅ ተቆላልፈን የምንታየው

t.me/OLDBOOKSPDF

መቼ ነው? ከእንግዲህ ልጅነት ይብቃኝ ። ሚስቱ ብቻ ሳልሆን እናቱ ጭምር መሆን አለብኝ አልኩ ።

ልቤ ከሰጠመበት የትካዜ ባህር እየተንቦጫረቀ አይኔን ወደ ማንደርሌይ ባህር ሰደድኩት ። ደመ ነፍሴ እያንደረደረ ደረጃውን ሲያስቆጥረኝ "ና ጃስፐር ፡ ና እንሩጥ ፡ እንብረር" ብዬ ፎከሀኩ ። እግሬ የመስኩን ሳር እየጠረገ ሲጣደፍ መሬር እንባ ደግሞ ካልገንፈልኩ እያለ ውስጣዊ ህዋሳቴን ሲፍቅ ይሰማኝ ነበር ።

— 0 —

እንደ ገመትኩት ሁሉ የበአሉ ወሬ ዳር እስከ ዳር ተናኝቶ ነበር ። የቤት ውስጥ ሠራተኞች ሁሉ በእጅጉ እንደተደሰቱና በአሉን በጉጉት እየጠበቁ መሆናቸውን ከክላሪስ ሰማሁ ። ክላሪስ በአለቱ ምን አይነት ልብስ እንደምለብስ ብትጠይቀኝ ገና እንዳልወሰንኩና ጊዜው ሲደርስ ግን ለእርሷ ብቻ እንደማሳውቃት ስነግራት ልዩ ደስታ አስነበበችኝ ።

አንድ ቀን የእራት ልብሴን እየለበስኩ ሳለ በሩ ተንኳኳ ። "ይግቡ" ስል ያልገመትኩት ሰው ገብቶ በማየቴ ደነገጥኩ— ሚስዝ ዳንቨርስ ።

ከሚስዝ ዳንቨርስ ጋር ከተለያየን ሰንበት ብሎ ስለነበረ መምጣታቸው ገረመኝ ። ያ ፌቭል የሚሉት ሰውዬ ከመጣ ወዲህ ከእርሳቸው ጋር ተገናኝተንም አናውቅ ። እንዲያውም በየእለቱ ያገናኘን የነበረ የቤት ውስጥ የቴሌፎን ግንኙነት በፍሪዝ በኩል ይካሄድ ስለነበር ከድምፃቸው ጭምር መለያየቴ ደስ ብሎኝ ነበር ። አንዳንዴ ግን ማክሲም ስለ ፌቭል የሰማው ከኔ ይሆናል ብለው በመገመት አሮጊቲ ተቀያመውኝ ይሆን? ብዬ ማሰቤ አልቀረም ።

ሚስዝ ዳንቨርስ ቁርጥራጭ ወረቀቶች የያዙ እጆቻቸውን እየዘረጉ "ስለ ረበሽኩዎት ይቅርታ ያድርጉልኝ የኔ እመቤት ።" በማለት ጀመሩና "በየእለቱ ከየክፍሉ የሚወጡ ቆሻሻ ወረቀቶችን መመርመር ተግባሬ እንደመሆኑ መጠን እነዚህን ስዕሎች ከቤተ መፃህፍቱ የቲሻሻ ቅርጫት ውስጥ ስላገኘኋቸው ምናልባት ሳያስቡ ጥለዋቸው እንደሆነ ብዬ ለማጣራት ነው ።" ሲሉ አጠቃለሉ ።

"አይ አልፈለጋቸውም ሚስዝ ዳንቨርስ ። እንዲያውም ዝም ብዬ የነደፍኳቸው ናቸው" አልኳቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በእርግጥ ስእሎቹ እንኳን የተሳሉበት ምክንያት ነበር ። የልዩ አልባሳት በአል እንዲዘጋጅ ከተወሰነ ወዲህ እኔ በምንም ቦታ እንደማላስ ፈልግ ቢነገረኝም "ምን ልልበስ?" የሚለው ጥያቄ ግን ነጋ ጠባ አእምሮዬን ቆንጠጥ ያደርገዋል ። ታዲያ አንድ ቀን ብቻዬን ቁጭ ብዬ ይህንኑ ሀሳብ ሳሰላስል አንድ ነገር ብልጭ አለብኝ ። ቢያትሪስ የሰጡኝን የስዕል መፃሕፍት አንድ በአንድ እያገላበጥኩ የልብስ አይነቶች አማርጥ ገባሁ ። ይሁንና ለዓይኔ የሞሉት ሁሉ ለልቤ አልገባ እያሉ በጣም ተቸገርኩ ። ይሻላሉ ያልኳቸውን አንድ ሁለቱን ሳጠና ቆየሁና በወረቀት ገልብጬው ስመረምራቸው ጭራሽ አላረካ አሉኝ ። ጨመዳድጄ ለቅርጫት ዳረግኳቸው ። እኒህን መረቀቶች ነው እንግዲህ ሚስዝ ዳንቨርስ ይዘውልኝ የመጡት ።

እንደማያስፈልጉ ሰነግራቸው "አይ መልካም ፡ ለእርስዎ ሳላሳይ እንዳይጣል ብዬ ነው" አሉኝ ።

"ገባኝ ፡ ጥሩ አድርገዋል" አልኩ በአጭሩ ፡ ቶሎ እንዲሄዱልኝ ፈልጌ

"ስለ በአሉ ልብስ እስካሁን አልወሰኑም ማለት ነው?" ሲሉኝ ግን በጥርጣሬ ተመለከትኳቸው ። ምን አሳሰባቸው? አሰኘኝ ። "ገና አልወሰን ኩም" ነበር መልሴ

"ከስዕል አዳራሹ እኮ ጥሩ ጥሩ ስእሎች አሉ ። አሳሰቡበትም እንዴ? ከእነርሱም መገልበጥ ይቻላል እኮ ።"

የሴትዮዋን አይን ማየቱ ቢያስጠላኝ ተሞርደው የወጣላቸውን ጥፍሮቼን በጥፍር ሞረድ እፈትጋቸው ገባሁ ። "እስቲ አስብበታለሁ" አልኳቸው ።

ስሜቱን እንዳያውቁብኝ ቆጠብ አድርጌው እንጂ ሀሳባቸው ድንቅ ነበር ። እስካሁንም እኔ እንዴት እንዳልታየኝ ገረመኝ ።

በመጨረሻም ጥሩ ጥሩ አለባበሶች የሚያሳዩ በርካታ ስእሎች ከአዳራሹ መኖራቸውን በመድገም "በተለይ በእጁ ባርኔጣ ይዛ ነጭ በነጭ የለበሰችዋ ወጣት ልጅ አለባበስ እኔን በጣም ነው የሚያረካኝ ። መቼም እመቤቱ በምርጫዎ ጣልቃ የመግባት መብት ባይኖረኝም

t.me/OLDBOOKSPDF

ምርጫዎን ሲያስተካክሉ ግን ልብሱ ለማንዱን መሰፋት ያኖርበታል ። እዚህ አካባቢ የረባም ልብስ ሰፊ የለም ። ከለማንዱንም ቦንድ ጉዳና ያለው ቮቹ ልብስ ሰፊ ምርጥ ይመስለኛል ።" አሉኝ

ስለ ሀሳባቸው አመስግኛቸው ሊወጡ ሲሉ ደግሞ ስለዚያች ወጣት ልጅ አለባበስ እንዳስብበት በድጋሚ አሳሰቡኝ ። ጉዳዩን ምስጢር አድርገው እንደሚይዙትም አረጋግጠውልኝ ወጡ ።

ይህን ያህል ምን አሳሰባቸው? አይቼባቸው የማለውቀው ዓይነት ቅንነትና አሳቢነት ዛሬ ከየት ተጠጋቸው? ሊታረቁኝ ይሆን? ስለ ፌቭል አለመናገሬ ሲታወቃቸው ቅሬታቸውን ፍቀው በዚህ ሊክሱኝ ማሰባቸው ይሆ? በቅ ያሁኑ ባህሪያቸው ከምን እንደመነጨ ባያጣጣኝም ለእንዲህ ዓይነቱ ወዳጅነት ያበቃን የዚያ የፌቭል መምጣት ከሆነ አጋጣሚውን አመስግኜ ወደ ሌላ ሀሳብ ነንድኩ ።

እውን ፌቭል የርብቃ የአጎት ልጅ ነውን? ታዲያ ማክሲም ለምን ጠላው? ደጁን አያርገጥ የሚለው ምን ጥፋት ቢታይበት ይሆን? በእርግጥ ቢያትሪስም እምብዛም እንደማያፈቅዱት ነግረውኛል ። እኔም እንዳ የውት ቢሆን ማጋጣ ብጤ ነው ። በሌላ ወገን ደግሞ ማንደርሌይን ጠንቅቆ ለማወቁ የጄስፐር ከእርሱ ጋር እንዲያ መወዳጀት አንድ ምልክት ነው ።

ከርብቃ ጋር ደግሞ በመልክም ሆነ በባህርይ ቅንጣትም መመሳሰል ሳይኖራቸው እንዴት ታስጠጋዋለች ? እርሷ እንኳን አይፈረድባትም ። ስጋዋ አይደለም እንዴ? ቆርጣ አትጥለው ። ምንም እንኳን ማክሲም ባያፈቅደውም ያላት ምርጫ ዘመዷን ሳታስከፋ ትዳሯንም ሳታናጋ በብልሃት አቻችላ መያዝ ነው ። ለዚህ ደግሞ አሳምራ የምታውቅበት ይመስለኛል በማለት ከራሴ ሀሣብ ጋር ስሟገት ቆየሁ ።

ለእራት ስቀርብ ተጭኖኝ የነበረ ሀሣብ አብሮኝ ቀረበ ። እራሴን ሳይሆን ርብቃን የሆንኩ መሰለኝ ። ወንበሩን ወደ ጠረጴዛው ሳስጠጋው ፍሪዝ መጥቶ "እሜቴ ፡ ሚስተር ፌቭል በቴሌፎን ይፈልግዎታል" ሲሉ በእዝነ ልቦናዬ አቃጨለብኝ ። ርብቃ ብድግ ብላ ማክሲምን በአይኗ ገረፍ አድርጋው ስትወጣ ታየችኝ ። ማክሲም አተርትር ይበላል ። ርብቃ ተመልሳ ስትመጣ ማክሲምን እንዴት እያሳሳቀች ስታጣጣባውና ቅሬታ ውን ስታስረሳው ፡ ጨፍንት የነበረ ፊቱ በፈገግታ ተሞልቶ እጇን ጎተት

t.me/OLDBOOKSPDF

አድርጎ ሲስመው ፡ እርሷ ሳቋን ስትለቀው ... እንደ መባነን አደረገኝ ።

"ምን ነካሽ ሴትዮ?" አለኝ ማክሲም "ሎራሽ መብላቱን ትተሽ ሎልጥ ብለሽ ሂደሻል እኮ ። የዛሬው ደግሞ የተለየ ነው ። መጀመሪያ አንድ ነገር የምታዳምጪ መሰልሽና ከንፈርሽ ይነቃነቅ ጀመር ። አይንሽን ወርወር አድርገሽብኝ መለስሽውና አንዴ ሞንቅላትሽን ትነቀን ቲያለሽ ፡ አንዴ ፈገግ ትያለሽ ፡ አንዴ ትከሻሽን ላይ ታች ትይዋለሽ ። ይህ ሁሉ እኮ ከመቅፅበት ነበር የሚሆነው ። ለመሆኑ ለበአሉ ልምምድ እያደረግሽ ነበር ልበል?" እያለ እየሳቀ ያስተውልኝ ጀመር ። እንደገና "ምንድነው የሆንሺው? ፊትሽ እንዴት እንደተቀያየረ ባየሽው?" ሲል ጠየቀኝ ።

"አይ ምንም አልሆንኩ" በማለት መለስኩለት

"እስቲ ስለምን እያሰብሽ እንደነበረ ንገሪኝ "

"ለምን ብዬ? አንተ ስለምን እንደምታስብ ነግረሽኝ ታውቃለህ እንዴ?"

"መች ጠይቀሽኝ ታውቂና?"

"መች ጠይቀሽኝ ታውቂና? አንዴ ብጠይቅህ መች መልስ ሰጠሽ ኝና?"

"ትዝም አይለኝ ። መቼ ነው እኮ የጠየቅሽኝ?"

"እንዲያውም ቤተ መፃህፍት ውስጥ ቁጭ ብለን አልነበረም?"

"እኔ እንጃ ፡ ይሆን ይሆናል ። ታዲያ ምን መልስ ሰጠሁሽ?"

"ምን የረባ መልስ ትሰጠኛለህ ፡ አሾፍክብኝ እንጂ"

"እስቲ እኮ ምን ብዬ?"

"ምን እያሰብክ ነው? ብልህ ስለ ሰሞኑ የሱፌይና የሚድል ሴክስ የእግር ኳስ ፊጁዋታ ነዋ ያልከኝ"

"እንዴ ፡ እንደዚያማ ከሆነ በጣም አስከፋቹኛለሁ ማለት ነው ። ግን አንቺ ስለምን የማስብ መስሎሽ ነበር?" በማለት እንደገና እየሳቀ ጠየቀኝ።

"እኔማ ስለሌላ ነገር የምታስብ ነበር የመሰለኝ ።"

"እኮ ስለሌላ ነገር ስትዪ? ለምሳሌ ስለምን?"

"እባክህን ተወኝ ፡ ምንም አላውቅም ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"አይ አንቺ! ስለ ጨዋታው ነው የማስበው ካልኩሽ ስለ ጨዋታው ነበር ማለት ነው ። በቃ አለቀ ። ሌላ የሚያመራምር ምንም ምስጢር የለውም ። የሴቶች አእምሮ ለምን ቀና ቀናውን እንደማያስብ ብቻ ነው የማይገባኝ ። ወንዶች እንዲህ መጠማዘዙን አያውቁበትም ። ገባሽ ማሚትዬ! አሁንም አእምሮሽ ውስጥ አንዳች እየተጉላላ መሆኑ በደንብ ያስታውቃል ። ፊትሽ እንዴት ነው የተለዋወጠው?"

"እንዴት ሆኖ ተለወጠብህ ደግሞ? ምን መስዬ ታየሁህ?"

"እኔ ምን አውቄ? ብቻ ደስ የማይል ነገር ነው የሚነበብብሽ ። ጭራሽ አሮጊት መሰልሽ" .

"ታዲያ ምን አለበት? አሮጊት እንድመስል አትፈልግም እንዴ?

"በፍጹም"

"ለምን?"

"ስለማያምርብሽ ብቻ"

"አማረብኝ አላማረብኝ እድሜውን ከሰጠኝ አንድ ጊዜ ማርጀቱ አይቀርልኝ ። ወገቤ ጎብጦ ፣ ፊቴ ተጨማዶ ፣ ሽበት ወርሶኝ ማየት አትፈልግም ማለት ነው?"

"ያ ሌላ ይሄ ሌላ ። ያኔማ የተፈጥሮ ግዴታ ስለሆነ የግዴታ መቀበል ይኖርብኛል ። "

"ታዲያ የማትቀበለው ምኑን ነው?"

"አሁን የማይብሽን ልዩ መልክ ። አይንሽ አንድ የተደበቀ ምስጢር እንዳለሽ ይናገራል ።" ከመደነት በላይ የማወቅ ጉጉቱ ቢያይልብኝ "ምን ማለትህ ነው ማክሲም? የምን ምስጢር?" እንዳልኩት ፍሪዝ በሩን ከፍቶው ስለገቡ ሁለታችንም ፀጥ አልን ። ፍሪዝ እንደወጡ ማክሲም ገለፃውን ጀመረ ። "መጀመሪያ ያየሁሽ እለት እፊትሽ ላይ አንድ ነገር አነብ ነበር ። ያ አስተያየትሽ ምን እንደሆነ መግለፅ ባይሆንልኝም አሁንም ስታሳይኝ በጣም ደስ ይለኛል ። እንዳገባሽ ከገፋፉኝ ምክንያቶች ም አንዱ ይኸው አስተያየትሽ ነበር ። አሁን እዚህ ተቀምጠን ሳይሽ ያ ቆንጆው ገፅታሽ ከመቅፅበት ልውጥውጥ ሲልብኝ ግን አልወደድክ ትም"

"ይሄ ተለዋወጥሽብኝ የምተለው ነገር ምን እንደሆነ ፣ እንዴት እንደተለዋወጥኩ ለምን አታስረዳኝም ማክሲም?" በማለት ጎተጎት ኩት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ግንባሩን ሸብሸቦ ፡ ቅንድቦቹን ሰብስቦ ጥቂት ካስተዋለኝ በኋላ "ሰማሽ የኔ ወለላ ፡ ሀፃን ሳለሽ አንዳንድ መፃሀፍት እንዳታነቢ ታግደ ሽም አታውቂ? እነኛን መፃሀፍት ደግሞ አባትሽ ሳጥን ውስጥ አይቆልፉባ ቸውም ነበር?"

"በሚገባ"

"እንግዲያውስ ልብ ብለሽ አዳምጪኝ ። አባትና ባል ከሞላ ጎደል አንድ ናቸው ማለት ይቻላል ። ባል ሚስቱ እንዳታውቃቸው የሚፈልጋቸ ውን ነገሮች አፍኖ መያዝ አለበት ። ይኸው ነው በቃ ። ከእንግዲህ ምንም ልትጠይቂኝ አይገባም" አለኝ ተኮሳትሮ ።

"ተው እንጂ ማክሲም ፡ ጭራሽ ጡጦ እንዳላበቃ ሀፃን አታድርገኝ እንጂ"

"ታዲያ ምን እንዳደርግሽ ነው የምትፈልጊው?"

"ባሎች ሁሉ ሚስቶቻቸውን እንደሚያደርጓቸው ነዋ"

"በፍልጥ እንዳገላብጥሽ?"

"አትቀልድ እንጂ ፡ ፍልጡን ምን አመጣው? ሁሉንም ነገር እንደ ፈዝ ባትቆጥረው ምን አለበት?"

"አይ ፡ ፈዝ አይደለም ፡ የምፈን ነው"

"የምርህን እንዳልሆነ እንኳ ፊትህ ይናገራል ። ዘወትር እንደ አሻንጉሊት የምትጫወትብኝ ሀፃን ማድረጉ ለምደብህ ነው እንጂ"

"እውነትም <u>የወንደርላንዴ አሊስ</u> ። እንዴት ያለ ጥሩ ስም ነው ያወጣህልሽ ። ለመሆኑ ሻሹንና ሪባኑን ገዛሽ እንዴ?"

"ልብ አድርግ ብቻ ማክሲም ፡ የዚያን እለት በእድሜህ ተደንቀህ የማታውቀውን ያህል 'ጉድ !' ካላሰኘሁህ እኔ አይደለሁም ልጅት"

"ይሁን እስቲ ፡ ለማየት ያብቃና ። ይልቅ ትን እንዳይልሽ እየበላሽ አትናገሪ ። ብዙ የምዕራቸው ደብዳቤዎች ስላሉኝ መሄዴ ነው" ብሎኝ መልሴን ሳይጠብቅ ወደ ቤተ መፃህፍቱ አመራ ።

እኔም ጥቂት ብስጭቴን ሳስታምም ከቆየሁ በኋላ ተነስቼ ወደ ስእለ አዳራሽ አመራሁ ። ሚስዝ ዳንቨርስ እንዳየው ከጠየቁኝ ስእል ፊት ለፊት ቆሜ ልብሱንና ለባሿን በአንክሮ ማስተዋሉን ተያያዝኩት ። ቀደም ሲል ከሁሉም በላይ አብልጬ የምወደው ስዕል ሆኖ ሳለ እንዴት ትዝ ሊለኝ እንዳልቻለ እየተገረምኩ እያንዳንዱን ነጥብ በዝርዝር መረመርኩት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ስእሉ የማክሲም ቅድመ አያት እህት የነበሩት የካሮሊን ደዊንተር ምስል ነበር ። በጊዜያቸው አካባቢው ሁሉ አድናቆቱን ያልነፈጋቸው እጅግ ውብ ነበሩ ። ልብሱን ከመጠን በላይ ስለወደድኩት ሠዓቢን በዚሁ ቋጭቼ በማግስቱ ለሎንዶኑ ልብስ ሰፊ ከዝርዝር መግለጫ ጋር የስእሉን ግልባጭ አከዬ ላኩለት ። ልብስ ሰፊው ትእዛዙን ተቀብሎ በተጠየቀው መሠረት በተባለው ቀን እንደሚያደርስ ሲገልፅልኝ ደስታ ፈነቀለኝ ። የበአሉ ነገር ያን ያህል ያልከበደኝን ያህል አሁን በመጠኑ ቀለል ይለኝ ጀመር ።

ቀኑ እየተቃረበ ሲመጣ ዝግጅቱ ተጣደፈ ። ዋናው ሀላፊ ክሮውሌይ ዝግጅቱን አንድ ባንድ እየተከታተለ ሲመራ የማክሲምም ድጋፍ አልተለየውም ነበር ። ማክሲም የሰአት በፊት ስራውን ለዚሁ ነበር ያዋለው ። ሳያሰልስ ከክሮውሌይ ጋር እየተገናኘ ይወያያል ።

ከሁሉ በላይ የገረመኝ ደግሞ እያንዳንዱ የማንደርሌይ ሰራተኛ ምን ያህል ተመስጦ እንደነበረ ማየቱ ነበር ። ፍሪዝ ከዓት እስከ ማታ ደፋ ቀና ሲሉ ፡ ሽር ጉዱን ሲያሳምሩት ዋናው አዘጋጅ ነበር የሚመስሉት። የሮበርት ነገርማ አይነሳ ። ሠዓቡን ሁሉ በአሉ ላይ አውሎት የእለት ተእለት ተግባሩን ረስቶት ነበር ። ምግብ አትርቦ ሳህን ይከለክለናል። ፊንጃሉን ሳይሰጠን የሻዩን ጀበና እንደያዘ እፊታችን ፈዞ ይገተራል ። የእነርሱን በቅርብ ማጤኔ እንጂ ይህ በአል ልቡን ያልሰወረው አንድም ሰው አልነበረም ። የሚስዝ ዳንቨርስን ስሜት ብቻ ነው ማወቅ የተሳ ነኝ ።

እያንዳንዱ ክፍል ከመታደሱና በልዩ ልዩ ጊጣጌጦች ከማጌጡም በላይ ግቢውን በሙሉ የማሸብረቁ ሥራ ይቀላጠፋል ። ከቤቱ ሰራተኞች አልፎ ለዚሁ ተግባር የተቀጠሩት ሙያተኞች ግቢውን አጣበውታል ። ኦኔ የተለየ የሥራ ድርሻ አልነበረኝምና እዚያም እዚህ እየቆምኩ የሚሰራውን ሳደንቅ እቃ ከወዲያ ወዲህ የሚያመላልሱ ሰዎች ‘‘ይቅርታ የኔ እመቤት ፡ አንዴ ያሳልፉኝ?’’ የሚለው ጥያቄ በዛብኝ ። ዝም ብዬ እንደ ጅል ከምገተር አንዳንድ ሠዓብ ጣል ባደርግስ አልኩኝና አንድ ጊዜ ‘‘ወንበሮቹን ወዴት ነው የምትወስዷቸው? ቤተ መዛህፍቱ ውስጥ ቢሆኑ አይሻልም?’’ ስል ፡—

‘‘አይ ፡ ሚስዝ ዳንቨርስ ናቸው ወደ ጓሮ እንድንወስዳቸው ያዘዙን’’

t.me/OLDBOOKSPDF

በማለት አንዱ ሰራተኛ መለሰልኝ ።

"ልክ ነው ልጄ ። ምን ማለቱ ነው ? እዚያው ቢሆኑ ነው የሚሻለው" አልኩና በሥራ የተጠመድኩ ለማስመሰል እርሳስና ወረቀት ይዤ ውል የሌለው ነገር እሞጫሞር ገባሁ ። አንዱ ሰራተኛ ሰረቅ አድርጎ ሲያየኝ አየሁት ። አስመሳይነቱ እንደ ተነቃብኝ የተረዳው ልቤ ሀፍረቱን ፊቱ ላይ አንፀባረቀው ።

ልብሱ በተባለው ቀን ደረሰልኝ ። ደስ አለኝ ። በትእዛዙ መሠረት መሰራቱ ደግሞ ይበልጥ አረካኝ ። የመኝታ ክፍሌን ቆልፌ ሞከርኩት ። ግሩም ድንቅ ። ሁሉም ነገር እንደፍላጎቱ ነበር ። ሁሉም ነገር ተስማምቶኛል ። ፍንድቅድቅ አልኩ ።

የበዓሉ አለት ።

ለጊዜው ከግርግሩ ለመራቅ አስበን እኔና ማክሲም ምሳችንን ፍራንክ ዘንድ ለማድረግ መሰንን ። ፍራንክ በወንደላጤ ቤቱ በሚገባ አስተናገደን ። ከአንዳንድ ጥቃቅን ነገሮች በስተቀር ዝግጅቱ ከሞላ ጎደል ተጠናቆ ነበርና ሙያያችንን በአብዛኛው ያተኮረው በአፈፃፀሙ ላይ ነበር። ጥቂት ስንጫወት ከቆየን በኋላ ስራውን ለመከታተል ወደ ቢታችን አቀናን ። በልብሱ ከመጠን በላይ መደሰቱ ፍራቻዬን የቀነሰው ቢሆንም ወደ ቢታችን እየተቃረብን በሄድን ቁጥር የበለጡ መከፈቻ መቃረቡ እየታወሰኝ ልቤ ደረቱን ይጎሰም ጀመር ።

ሁሉም ነገር በመልክ በመልኩ ተደራጅቷል ። አበቦች በየቦታው እየተቀመጡ ነበር ። ሚስዝ ዳንቨርስ እያንዳንዱን የአበባ ማስቀመጫ እያነሱ በተገቢው ቦታ ሳ ያስቀምጡ ፍዝዝ ብዬ ነበር የማያቸው ። ከአደራደራቸው ስርአት የእጅቻቸው ቅልጥፍና በእጅጉ ደነቀኝ ።

ፀሀይ ዘቅዘቅ ስትል ሁሉም ነገር ተከውኖ የእንግዶች መምጣት ነበር የሚጠበቀው ። ወዲያው ቢያትሪስና ባለቤታቸው መጥተው ዝግጅቱን እየተዘዋወሩ ይመለከቱ ጀመር ። "እንዴ ፡ ሞራሽ ልክ እንደ ድሮው አይደለም እንዴ ያደረጋችሁት?" አሉ ቢያትሪስ "አበቦቹ ደግሞ ልዩ ናቸው ። አንቺ ነሽ እንዲህ ያሳመርሽው?" ሲሉ ጠየቁኝ ።

"አይ ፡ ሚስዝ ዳንቨርስ ናቸው" አልኳቸው ትንሽ እንደማፈር ብዬ። ለእንዲህ አይነቱ ሙያ ባለመታደሉ በራሴ ስበሳጭ በእንባሩ

t.me/OLDBOOKSPDF

በአሮጊቷ ክፉኛ ቀናው ።

ከቢያትሪስና ከባለቤታቸው ጋር በአሉን የሚመለከቱ ልዩ ልዩ ነገሮች እየጠቀስን ስንጫወት የአለባበስ ነገር ተነሣ ። ጂልስ እንደ አረብ ሼክ ለመልበስ ማቀዳቸውና የቢያትሪስም አለባበስ ከባለቤታቸው አለባበስ ጋር እንዲገጥም መደረጉ ተነገረን ። ፍራንክ ግን በስራ ውጥረት የተነሳ ብዙ እንዳላሰበበትና የተለየ ነገር እንዳላዘጋጀ አስታወቀ ። የእኔ አለባበስ በምስጢር መያዙን ደግሞ ማክሲም ተናገሮ ። ቢያትሪስ ምን አይነት ልብስ እንዳዘጋጀው በተለያዩ መስተለኛ ጥያቄዎች ቢያጣድፉኝም ለእርሳቸውም ሞምር ምስጢር ሆኖ እንዲቆይ መወሰኔን እቅጩን ነገርኳቸው ።

ጊዜው እየገፋ ሲሄድ ምነው ቶሎ በደረሰልኝ የሚል ጉጉት ይተናነቀኝ ያዘ ። አንዴ ምነው ባልደረሰ ፡ አንዴ ደግሞ ቶሎ በሆነልኝ የሚያስብል ይህን የመሰለ ዝብርቅርቅ ስሜት እንዲህ ወዲያው ወዲያው ሲፈራረቅብኝ በጣም ገረመኝ ። ጉጉቴን ለመሰወር በመጣጣር በትንሹ እንደማዛጋት ብዬ ''ሰአቱ ስንት ሆነ ግን?'' አልኩ እንደ ቀልድ አስመስዬ። አያይዤም ''ወደ ፎቅ ብንወጣ አይሻልም?'' ስላቸው ሁሉም ስምምነታቸውን ገለፁልኝ ።

ከአዳራሹ ገና ከመድረሳችን ልዩ የደስታ ስሜት ከበበኝ ። ዙሪያዬን የማየው ሁሉ ክፉኛ ልቤን ማረከው ። ማንደርሌይ እንዲህ ያምርበታል በዬ ፍፁም ገምቼ አላውቅም ነበር ። እያንዳንዱ ክፍል ልዩ ውበትና ድምቀት ተላብሶ ነው ያየሁት ። ቅድመ ዝግጅቱ ይህ ተረሽ በማያስኝ መልኩ የተሟላ በመሆኑ አንድ እርምጃ እንኳን ያለ አድናቆት መራመድ አልቻልኩም ።

መኝታ ክፍሌ ስገባ ክላሪስ በደስታ ፈክታ ስትጠብቀኝ አገኘኋት ። በሩን ቀረቀርኩው ። ልብሴን ለመልበስ በጣም ቸኩዬ ። ኩቴያችንን አጥፍተን ፡ እንደ ድመት አድብተን ስንራመድ ፡ ድምፃችንን ቀብረን ስንንሾካሾክ ፡ አንድ ብርቱ ጉዳይ ይዘን የምንመሳጠር እንመስል ነበር ። እኔማ በባዶ እግሬ ወዲያ ወዲህ ስንሯሯድ ፡ በሆነ ባልሆነው ስፍለቀለቅ በነና ዋዜማ በፍስሐ ባህር የሰጠመ ህፃን ነበር የምመስለው ።

ልብሱ በሚገባ ተስማማኝ ። ''እንዴት ነው? አምሮብኛል?'' እላታለሁ ደግሚ ደጋግሚ ክላሪስን ''ምን ይጠየቃል? ልዩ ነው ። በጣም

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው የተስማማምት… የእንግሊዝ ንግስትም እንዲህ አያምርባት … ምንም እንከን አይወጣለትም'' ትለኛለች እርሷ ደግሞ ።

''እዚህስ? … ያዝ አድርጎኛል እንዴ?… ትከሻዬ ላይ? … ሽንጤ?… ዳሌዬንስ …'' አስጨነቅኳት ክላሪስን በጥያቄ ። ''ግራም ነው፡ ድንቅ ነው'' ባለችኝ ቁጥር መስታወቱ ውስጥ ከሚታየኝ ምስሉ ጋር እየተሽከረከርኩ መፈንደቅ ብቻ ።

ቆቤን አድርጌ ጠርዙን አልፎ የወጣውን ፀጉሬን ሳስተካክል በሩ ተንኳኳ ። ''ማን ነው?'' አልኩ በድንጋጤ ''ማንም ሊገባ አይችልም ።''

''እኔ ነኝ'' አሉ ቢያትሪስ ''አላበቃሽም እንዴ? እስቲ ከፊቱ ፡ ልይልሽ ''

''እይ ፡ እይ ፡ አ ይ ቻ ል ም ። ጥቂት ስለቀረኝ ሁሉን ላጠናቅቅ እመጣለሁ ። ማክሲምን እንዳትመጣ ፡ እዚያው ጠብቂኝ ይበሉልኝ'' አልኳቸው ።

''ማክሲም እንኳን አይመጣም ። መዘግየትሽ ግን በጣም አሳስቦ ታል … እህ … እኔ 'ምለው ፡ ምንም የምረዳሽ … ነገር … የለም?''

''ምንም አልፈልግም ። ይሄዱ ፡ ጨርሻለሁ ። እዚያው እመጣለሁ'' በማለት አባረርኳቸው ።

ሉሎችስ? የመረጡት ልብስ ተስማምቷቸው ይሆን? የሚል ሀሣብ ቢደቀንብኝ እስካያቸው ቸኮልኩ ። ወዲያው ደግሞ ይህ ሁሉ የሀሣን አይሉት የእብደት ሥራ ለምን አስፈለገ? አሰኘኝ ። ሆኖም ግን እንዴ ገብቼበታለሁና ልወጣው ብዬ ዝግጅቱን ለማጠናቀቅ ተጣደፍኩ ።

ለብሼ እንዳበቃሁ ምስሉን በመስታወት ስመረምር የኔ አልመ ስልሽ አለኝ ። ሌላ ! ፍፁም ሌላ ። ከክላሪስ ጋር የመጨረሻ ፍንደቃችንን ተለዋውጠን ለመውጣት ተነሳን ። እርሷ ቀደም ብላ መንገዱ ነፃ መሆኑን አጣርታ ከነገረችኝ በኋላ ተከታትለን ወጣን ።

ከአንድ ምሰሶ ጥግ ቆሚ ቁልቁል ስመለከት ሁሉንም አየኋቸው ። ''ሼክ ጂልስ''በነሱ የአረብ አልባሳት ደምቀው ፡ ጎራዴያቸውን እንና ቸው ላይ ሻጥ አድርገው ፡ በሙሉ አረንጓዴ ከተዋቡት ባለቤታቸው ጋር ይሳሳቃሉ ። ጅላጅል አመለካከቱ አሁንም ያልተለየው ፍራንክም እንደነገሩ ለብሶ ከጎናቸው ይታያል ። መደበኛ አለባበሱን እንደጠበቀ የነበረው ማክስ ብቻ ነበር ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ማክሲም "ይህች ሴትዮ ምን ነካት ? ገብታ ቅርት አለች አይደል ? እዚሁ እንደተገተርን እንግዳው ሊያጥለቀልቀን ነው እኮ" በማለት ፍራንክን ሲጠይቀው ሰማሁ ።

አይኔን ወደ አንድ ጎን ስወረውረው የካሮሊን ደዊንተር ስእል በብሩህ ብርሃን ፈክቶ ታየኝ ። ከላይ ወደታች ፡ ከታች ወደ ላይ አየሁት ። እኔንም መረመርኩ ። ምንም ልዩነት የለውም ። ፍፁም አንድ ። በሀይወቱ ልቤ እንዲያ በደስታ ተሞልቶ እንዲያ በኩራት ተወጥሮ አያውቅም ።

የሙዚቃ ድምፅ የሳበው ጆሮዬ አይኔንም ጎተተው ። የሙዚቃ ባንዱ በተጠንቀቅ ቆሟል ። ቫዮሊን ተጫዋቹ ቫዮሊኑን ይታኛል ። ቀና ሲል ወደኔ እንዲመጣ ጠቀስኩት ። ድምፅ አውጥቶ ሲራዬን እንዳያከሽፍ ብኝ በመስጋት "እሽሽ" አልኩት በድምፅ አልባው የጣቶቹና የከናፍሬ ግንኙነት ። መጣ ። "ከበሮ መቺው ከበሮውን እንዲደልቀውና 'እነሆ ወይዘሪት ካሮሊን ደዊንተር መጥተዋል!' ብሎ እንዲያስተዋውቀኝ ንገረው" አልኩት ። እጅ ነስቶ ተመለሰ ።

የከበሮው ድምፅ ሲያስተጋባ ሳቅ ሁካታው ፀጥ አለ ። "እነሆ ወይዘሪት ካሮሊን ደዊንተር..." የሚለው ድምፅ ሲከተል ከሰገነቱ ብቅ አልኩ ። ባርኔጣዬን በአንድ እጄ ይዤ ፡ ጭንቅላቴን በኩራት አቅንቼ ፈገግ ብዬ ተጠጋሁ ። ጭብጨባና አድናቆት ይኖራል ብዬ ስጠብቅ ፀጥታ ነው የተቀበለኝ ። ዝግ ብዬ ደረጃውን ስወርድም ያው ነው ። ሁሉም ፀጥ ረጭ ። ቢያትሪስ መጨሀ ቃጣቸው ። አፋቸውን በእጃቸው ጭምም አድርገው ያዙት ።

ሙሉ ፈገግታዬን እንደጠበቅኩ "ጤና ይስጥልኝ ሚስተር ደዊን ተቺ" አልኩ ድምፄን አጉልቼ ።

ማክሲም ድርቅ ብሎ ቆሟል ። አፍጦ ያየኛል ። ፊቱን አንዴ አመድ መረሰው ። ፍራንክ ጠጋ ብሎ አንዳች ሊነግረው ሲሞክር ገፈተረው ። አንድ እግሬ አንዱን ደረጃ እንደረገጠ ፡ ሌላኛው እግሬ ሌላኛውን እንደረገጠ ቀጥ አልኩ ። ምንድነው ነገሩ? ሰዎቹ ምን ነካቸው? እንዴት ነው የሚያዩኝ? ምን አፈዘዛቸው? እረ ማክሲም ምን ሆነ?

"ምን እየሰራሽ ነው?" ሲል ጮኸብኝ ማክሲም ። አይኑ ፈጀኝ ፡ ፊቱ ገረፈኝ ።

"እንዴ ? ስእሉ ነዋ!" አልኩት እግሬ ከነበረበት ባይለቅም ስሜቱ

t.me/OLDBOOKSPDF

ግን ከአይኑና ከቁጣው ለመሸሽ እየሞከረ "አዳራሹ ውስጥ ያለው ስእል እኮ ነው"

እንደተፋጠጥን ቆምን ። አፌ ደረቀ ። እንዳች አፈነኝ ። ጉሮሮዬን በእጄ ደግፌ "ምንድነው ነገሩ? ምን አጠፋሁ?" ስል ጠየቅኩት ።

"በይ : ይህን ልብስ አውልቀሽ ወዲያ ጣዪው ። ሌላ የፈለግሽውን መልበስ ትችያለሽ ። ብቻ ሰው ሳይመጣ ይህንን ልብስ ቶሎ እንድትቀይሪው" አለኝ ቁጣውን አክርሮ ።

ዝም ብዬ አየሁት ። ያንን በቁጣ የቀላውን አይኑን እያጉረጠረጠብኝ "ምን ቁመሽ ታይኛለሽ? ሂጂ : ልብሱን ቀይሪ አይደለም እንዴ የምልሽ?" ሲለኝ ድምፁ እየሻከረ መጣ — የእርሱ ለመሆኑ እስኪያጠራ ጥረኝ ድረስ።

እምባዬ ግጥም አለ ። የቀሚሴን ጫፍ ቆንጠር አድርጌ ሽቅብ ተንደረደርኩ ። ዙሪያው ጨለማ ሆነብኝ ። ክላሪስን እንኳን አጣኋት ። እግሮቼ እርስ በእርስ እየተላተሙ : ልቤ በሀዘን እንደጨለመ ኮሪደሩ ላይ ስሮጥ ባሻገር ወደ ምዕራባዊው ህንፃ መግቢያ ላይ ያየሁት ነገር ለምኔውም ከአእምሮዬ የሚፋቅ አይደለም ።

ሚስዝ ዳንቨርስ ። የጥላቻ : የንቀት : የድል አድራጊነት ድብልቅ ስሜት ተላብሰው ሲስቁብኝ አየኋቸው ። ምስለ ሰው—ግበረ ሰይጣን !!

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አስራ ስድስት

ያቺኑ ከላሪስን ነበር መኝታ ክፍሌ ውስጥ ያገኘኋት ። አይኖቿ አይኖቼን ሲገጥሙ መንታ መንታውን ያወርዱት ጀመር ። የቀሚሴን ቁልፎች ለማላቀቅ ስጣጣር ልትረዳኝ ስትጠጋ ለቅሶ ባሰባት ። ስቅስቅ ብላ ስታለቅስ "ምነው ከላሪስ? ይብቃሽ እንጂ ፡ እንቺ ምን አጠፋሽና?" ብላትም እንባዋ ሊገታ አልቻለም ። ጉንፉጯን እያጠበ ደረቷን ይዳስሰው ዓባ ። "ወይኔ—ይህን—የመሰለ—ቆንጆ—ቀሚስም—አይ—እሜትዬ" አለች ከላሪስ እንቅ እንቅ እያደረጋት ። "ምንም አይደለም" ብዬ ለማረጋጋት ሞከርኩ ።

በለውጡ ምን እንደምለብስ ምርጫዬን እንዳስታውቃትና ወዲያውኑ ፉትተኩስልኝ እንደምትችል ነገረችኝ። "ማድ የለሽም ፡ አትቸገሪ ከላሪስ" አልኳት ለዘብ ብዬ "ይልቅ ደቅርታ ኦድርጊልኝና ለጥቂት ጊዜ ብቻዬን ተዪኝ ። እንቺ ሂደሽ ተዝናኚ"

"እንዴ? ምን ማለትዎ ነው? እርስዎን ትቼ ነው የምዝናናው?"

"እኔ ምንም አልሆንም ። ሂጂ ማድ የለም ። ብቻ—ከላሪስ—ይህንን ጉድ ለማንም—እንዳትናገሪ—አደራሽን" ስላት እንባዋን እንደገና እያነረፈችው "እረ—ለማንም—አልናገርም" አለችኝ ።

"እረ በቃሽ እንቺ ልጅ ። ይልቅ ሰው ሳያይሽ ሂደሽ ፊትሽን ተጣጠቢና ወደ በአሉ…" እንዳልኩ በሩ ተንኳኳ ። "ማነው?" ለሚለው ጥያቄ በሩን ከፍተው በማንባር ምላሹን የሰጡኝ ቢያትሪስ ነበሩ ። ከላሪስ ሹልክ ብላ ወጣች ።

ቢያትሪስ ሊያዕናኑኝ ሞከሩ ። ውሀ በብርጭቆ አምጥተው ሲሰጡኝ

t.me/OLDBOOKSPDF

እርሳቸውን ለማስደሰት ስል ብቻ ፉት አልኩለት ።

"እኔ እኮ ትልቅ ስህተት እንደተፈፀመ ያወቅኩት ወዲያውኑ ነው ። አንቺ ግን አይፈረድብሽም ፣ ምኑንም አታውቂምና" አሉኝ ቢያትሪስ

"ምኑን ነው የማላውቀው?" ስል ጠየቅኋቸው

"ስለ ቀሚስሽ ነዋ ። ባለፈው በአል ርብቃ የለበሰችው ቱርጥ የዚህ ዓይነት ልብስ ነበር እኮ ። አንቺ አዳራሹ ውስጥ ካለው ስእል ገልብጠሽ አይደለም እንዴ? እርሷ እኮ እንዲህ ነበር ያደረገችው ። መቼም ገና ሰገነቱ ላይ ብቅ ስትዪ እኔ..." አሉና ጅምር ሀሣባቸውን በእንጥልጥል ትተው ትከሻዬን መታ መታ ካደረጉ በኋላ "ምስኪን ፣ መጥፎ አጋጣሚ ነው ። በምን ልታውቂ ኖሯል?" አሉኝ ።

"አይ ፣ በቃ ይተውት ፣ አሁን ገባኝ ፣ ማወቅ ነበረብኝ" አልኳቸው ትኩር ብዬ እያየኋቸው ።

"በምን ተአምር? የማንም አእምሮ ሊገምተው የሚችል ነገር አይደለም ። እኛም ብንሆን ይህ ይሆናል ብለን በፍፁም አልጠረጠርንም ። ማክሲም..."

"ማክሲም? ማክሲም ምን አለ?"

"እርሱማ ሆን ብለሽ ያደረግሽው ነው የመሰለው ። ያልጠበቅሽው ነገር ነው የማሳይህ ብለሽ ስትዝቺበት ስለከረምሽ እርሱን ለማበሳጨት ያደረግሽው ቢመስለው አውነት አለው ።"

"እኔ ነኝ የማልረባ ደደብ ፣ ማወቅ ነበረብኝ ። ቢያንስ ቢያንስ መጠርጠር እንኳን እንዴት ተሳነኝ? " ብዬ ቁጭቴን ስገልፅላቸው

"አሁን እርሱን ተይው ፣ እርሺው ። ሁኔታውን ግልፅልፅ አድርገሽ ስታስረጂው ሁሉም ነገር ይስተካከላል ። እንግዶች እየገቡ ስለሆነ የት ቀረች ብለው ጥያቄ እንዳያበዙ ልብሷ ስላልተስተካከለላት ትንሽ ተበሳጭታ ነው በማለት እንዲያስረዱ ለጂልስና ለፍራንክ ነግሬያቸው ነው የመጣሁት" አሉኝ ።

መልስ ሳልሰጣቸው አገጩን በእጆቼ ደግፌ እተተመጥኩበት ፈዝዤ ቀረሁ ። "በይ እንጂ ፈጠን በይ ፣ የትኛው ልብስ ይሻልሻል? " በማለት ቢያትሪስ ከቁምሣጥኔ ውስጥ ረጅሙን ሰማያዊውን ቀሚሴን አመጡልኝ ። "በጣም ቆንጆ ቀሚስ ነው ። በይ አስቲ ልበሺውና ቶሎ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንሂድ''

''በፍፁም ፡ እኔ አልሄድም''

''እንዴ ፡ ምን ማለትሽ ነው? ኧረ ነውር ነው ።''

''ይተውኝ እባክም ቢያትሪስ ፡ እንዴት ብዬ ነው የሰዉን ፊት የማየው?''

''የተፈጠረውን ማን ያውቅና? ልብስ ሰፊው ለበአሉ ያቀድሽውን ልብስ ትኖ ፡ በስህተት ሌላ ስለላከልሽ ፡ የወትሮ ልብስሽን እየለበስሽ ነው ተብሎ ስለተነገረ ማንም የሚጠራጠር አይመስለኝም ።''

''እኔ የልብሱ ነገር መቼ አስጨነቀኝና ። በገዛ እጇ የሰራሁት ነገር አእምሮዬን እየጎገጠው እንዴት ብዬ? ምን አለበት ቢያትሪስ ቢተውኝ ?

''እስቲ ነገሩን ቀስ ብለሽ አብሰልስዪው ። ጂልስም ሆነ ፍራንክ ይገባቸዋል ። ማክሲምም ቢሆን በቀላሉ ሊረዳ ይችላል ። እኔ ደግሞ ወደ ዳር ወጣ አድርጌ ዘርዘር አድርጌ አስረዳዋለሁ··· እንዴ? እንግዶቹስ ምን ይላሉ? በምን ምክንያት ቀረሽ ልንላቸው ነው?''

''የፈለጋችሁትን ምክንያት ፈጥራችሁ ልትናገሩ ትችላላችሁ ። ደግሞ እኔ መጣሁ ቀረሁ ምን ልዩነት ያመጣና? ማንም አያውቀኝ ። '' አልኩ ተቃውሞዬን በማጠናከር

''ኧረ በፈጠረሽ አንቺ ልጅ? እስቲ እንደምንም እራስሽን ለማሸነፍ ሞክሪ ፡ ሌላው ቀርቶ ለማክሲም ስትዪ ። ለእርሱ አታስቢም ማለት ነው?''

''ለዚያ ለዚያማ የዘወትር ሀሣቤ ስለማን ሆነና?''

እኛ እየተነታረክን ሳለ በር ተቀበቀበ ። ቢያትሪስ ከፍተው ከዚያው ቆሙ ። ''ምን ሆናችኋል? ሰው ሁሉ ተሰብስቦ የለም እንዴ? ማክሲም 'እስቲ ጠይቃቸው' ቢለኝ ነው የመጣሁት '' ሲሉ ሰማኋቸው ጂልስ በሩ ላይ እንደቆሙ ።

''እስቲ ትሰማህ እንደሆነ አንተ ጠይቃት ። አልወጣም ነው የምትለው ፡ እኔ ብላት ብሰራት አንተቴ ይታረድ አለችኝ ።'' አሉ ቢያትሪስ

ዝግ ባለ ድምፅ የሚናገሩት ሁሉ ባይያዝልኝም ''አይ ፡ አይ'' የሚለው ቃል ግን አላመለጠኝም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

“ትንሽ ድክምክም ስላላት ነው ፡ ሻል ሲላት ለመምጣት ትሞክራ ለች፡ ብለህ ለማክሲም ንገረው ። ለእራት እንዳትጠብቁን ። ትንሽ ቆይቼ እመጣለሁ ። ” በማለት ቢያትሪስ ባለቤታቸውን ሸኟቸው ።

ለጊዜው ጭንቀቱን ለማስወገድ ቢረዳኝ ብለው “ብራንዴ ልስ ጥሽ?” ሲሉኝ ምንም እንደማልፈልግ ነገርኳቸው ።

“እንግዲህ እምቢ ካልሽ ምን አደርጋለሁ ። ለእራት እየጠበቁኝ ስለሆነ ብቻሽን ትቼሽ ልሂድ እንዴ?”

“ግድ የለም ይሂዱ ፡ አመሰግናለሁ ቢያትሪስ”

“ምኑን አመሰገንሽኝ ። ምንም አልረዳሁሽ” ብለው ለመውጣት ወደ በሩ ሲያዘግሙ የቁምሣጥኑ መስተዋት ‘እንዴ’ ሲል ግብግቡን አቀረበላቸው ። አላሳፈሩትም— “በስመ–አብ ፡ ምን መስያለሁ? ጭራቅ፣ ወጮራንስ ምን እንዲህ አንጨፋረረው?” በማለት ለሰነዘሩት ጥያቄ ከመስተዋቱ ምላሽ ቢያጡ ፀጉራቸውን አስተካክለው ፡ ፊታቸውን በፓውደር አብሰው ወጡ ።

ቀናሁባቸው ። ልባቸውን ወኔ ሞልቶት ገንፍሎ የለም እንዴ! እርሳቸው የእኔ እጣ ቢደርሳቸው ኖሮ ይህን ጊዜ ምንም ሳይመስላቸው ልብሳቸውን ቀያይረው ከች ይሉ ነበር ። የእርሳቸው ዘመነኞች ሁሉ እንዲህ ያለ ባህሪይ ነው ያላቸው ። እኔ ታዲያ እንደሳቸው መሆን አላውቅበት ። አስተዳደጌም አይፈቅድልኝ ። ምነው እርሳቸውን ባደረገኝ፣ ማለቱ አልቀረም ። ግና ማን ማንን ይሆንና?!

አልጋዬ ላይ ስተክዝ ከቆየሁ በኋላ ተነስቼ ወደ መስኮቱ ተጠጋሁ ። እይታዬ የፈቀደልኝን ያህል ዙሪያ ገባውን ቃኘሁት ። አካባቢው በሙሉ አሸብርቋል ። ጥቂት ሠራተኞች ውር ውር ይላሉ ። አንዳንድ ያልተሟሉ ነገሮችን ለማሟላት ይሯሯጣሉ ። አንደኛው ፡ አምፖሎቹ በትክክል መስራታቸውን እየፈተሸ ያንጎራጉራል ። ደስ የሚል ዜማ ነበርና አስቀናኝ ። ምነው ዛሬ እርሱን ባደረገኝ አሰኘኝ ።

እኔና እርሱን ጎን ለጎን አስቀምጬው ማነፀፀር ያዝኩ ። የኔ ልብ በሀዘንና በቅሬታ ቅኝት ሲራገብ ፡ የእርሱ ልብ ግን የደስታ ከበሮ ይደልቃል ። እኔ የሀሳብ ቁራኛነት አንገቱን ሲያስደፋኝ ፡ እርሱ ግን ከሀሣብ ነፃ ነውና ደረቱን ነፍቷል ። እኔ የማክሲምን ሶብ ባለማወቅ

t.me/OLDBOOKSPDF

በማድማቱ የሀሊና ወቀሳ ሲንጠኝ ፡ እርሱ ግን የፈፀመው ጥፋት ስለሌለ ሀሊናውን የሚኮሰኩሰው ነገር የለም ። የኔ አይን ፡ የእንግዶችን አይን እንዴት ብዬ አያለሁ? የሚል ፍራቻ ሲፈታተነው ፡ የእርሱ አይን ግን መቼ መጥተው ባየኋቸው በሚል ጉጉት ይርገበገባል ። እኔ ምነው ይህ በአል ባልኖረ? እያልኩ ከዚህ ጭንቀትና ጥበት የሚገላግለኝ አንዳች ተአምር ዱብ እንዲያደርግልኝ ፡ የዕድል አማልክቱን ስማፀን ፡ እርሱ ግን ለበአሉ መጀመር በመቻኮል በስሜት ይንሳፈፋል ።

ይህን ሳጠናጥን ቆይቼ ሌላ የሀሳብ ገመድ አፈትል ጀመር ። እንግዶች ከተሰበሰቡ በኋላ በምናብ ከመሃከላቸው ዘው ብዬ ገባሁ ።

— ለመሆኑ ሲትዮዋ ብት ብላ እንግዶቿን አታስተናግድም እንዴ?

— አንቺ ስለ ማስተናገዱ ነው የተቸገርሽው? ከነአካቴው በበአሉም ላይ አትገኝም ይባላል ።

— ምን ነካኝ ብላ?

— የነካትን ምን አውቁ?

— ልብሷ ስላልተስማማት አኩርፋለች ነው የሚባለው መሰለኝ ።

— አሆሆ! እንዴት ተቀለደ እናንተዬ? እንዲህ ነው አንጂ እመቤት ነት ።

— ኧረ ተዉ አታስቁኝ ። ልብሷ ካልተስማማት በማን ላይ ነው ኩርፊያው? ቀድም ብላ አታስብበትም ነበር?

— ዝም አትያት ም ፡ ምን አይነቷ እንከፍ ናት ።

— ይሄኔ ያቺ ርብቃ ብትሆን ምድሩ ይጠባት ነበር ። እዚህ ናት ሲሏት እዚያ ፡ እዚያ አየናት ሲሉ እዚህ… እንግዶቿን ስታሟዉት … ስታሳስት…

— ምንና ምኑን ነው የምታወዳድሪው?

— ኧረ ነገሩ ሌላ ነው የሚባለው ። እዚያ ማዶ ሲያወሩ አልሰማህም?

— ምንድነው የሰማኸው?

— ልብሷ አልተስማማትም … እራሷን አሟታል … የሚባለው እንዲያው ለሽሩን ነው እንጂ ባልና ሚስቱ ብጥብጣቸው ወጥቷል ነው መሰለኝ የሚሉት ።

— እንዲያውም ከተጋቡ ጀምሮ አንድም ቀን በመሃላቸው ሰላም

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰፍኖ አያውቅም አሉ ። ሰውዬው ካገባት በኋላ በጣም ነው የፀፀተው ።

— እኮ! ቀድሞውንስ? የእርሱ ነው እንጂ ስህተቱ ። በፍፁም እቸው አያደለችም ። እርሱን የመሰለ ጨዋ ፡ መሠረተ ጨዋ ፡ እዚህ ግቢ ከማትባል ከማንም የመንደር ልጅ ጋር ምን ብሎ ይጣመራል?

ሰማኋቸው እንዲህ እየተቀባበሉ ሲሰለቅጡኝ ፡ ሲስቁብኝ ፡ ሲሳለቁብኝ ። እየኋቸው ሲጠቃቀሱብኝ ፡ ከንፈር ሲያጣምሙብኝ ።

መብሰክሰኩን ትቼ ወደ ነበርኩበት ተመለስኩ ። አዲሱ ልብሴን አጣጥፌ አስቀመጥኩት ። ቢያትሪስ መርጠውልኝ የነበረውን ሰማያዊውን ቀሚስ ተኮስኩት ፡ ለበስኩትም ። ከቀሚሱ ጋር የሚስማማ ጫማ ተጫማሁ ፡ ፀጉሬን አበጣጠርኩ ፡ ፊቴን አሳበስኩት ።

ወጣሁ ። ልውስ ትንፍሽ የሚል የለም ። እየተጠጋሁ ስሄድ ከወደ አዳራሹ የሰማሁት ጫጫታ የእራት ግብዣው በመካሄድ ላይ መሆኑን ጠቆመኝ ። በስእል አዳራሹ በኩል ሳልፍ የካሮሊን ስእል ቁልጭ ብሎ ታየኝ ። ስታፈጥብኝ አፈጠጥኩባት ። ወዲያው አንድ ነገር የትውስታ ሀዋሴን ኮረኮረው ። ከዚህ ቀደም የአቡኑ ባለቤት "... ያ ጥቁሩ ፀጉሯ እትከሻዋ ላይ ተዘናፍሎ ፡ ... ያ በረዶ የመሰለው ልብሷስ? አይ ውበት! አይ አለባበስ ! ጨረቃ ነበር የምትመስለው" ያሉኝ ትውስ አለኝ ። ስለ አለባበሴ ከመወሰኔ በፊት ምነው ይህ አባባል ትዝ አላለኝ? ምነውላ ነገሩን አብጠርጥሬ አለማጥናቴ? በማለት በራሴ ችኩልነትና ጅልነት በእጅጉ ተናደድኩ ።

ይህን በዚህ ትቼው አባባቢውን ወደ መቃኘቱ ተመለስኩ ። የሙዚቃ መሣሪያዎቹ ወደነበሩበት አይኔን ስወረውር ሙዚቀኞችን አጣኋቸው ። መሣሪያዎቹን እረፍት የሰጣቸው የሙዚቀኞቹ ከማእዱ ለመቋደስ ወደ ግብሩ አዳራሽ መግባት እንደሆነ ገባኝ ።

ኮሪደሩ ላይ እንዳለሁ ከወደታች የነበረውን ሳስተውል ጥቂት ከቆየሁ በኋላ እያደገ የሄደው ጫጫታ አይኔን ወደ ግብሩ አዳራሽ ሳበው ። በሩ ሲከፈት ተጋባዦች እየተከታተሉ ወጡ ። ጠርቀምቀም እስኪሉ ጠብቄ ልቀላቀላቸው ወሰንኩ ። ደረጃውን አንድ ፡ ሁለት ቆጠርኩት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጥቂት የማውቃቸው ፣ በርካታ የማላውቃቸው ሰዎች ። ቁጥራቸው ለአይን የሚታክት ሰዎች ። እንደ መልካቸው ሁሉ አለባበሳቸውም የተለያየ ሰዎች ። የዚህ ሁሉ አይን አንዴ ሲያርፍብኝ ተዝለፍልፌ ባለመውደቁ ጥንካሬዬን አደነቅኩት ። ዕልመት ያጠለቀውን እውነተኛ ስሜቱን ከልቤ ቀብሬ በሀሰት ፈገግታ የተኳለውን ፊቴን እያስመታሁ ዳር ዳሩን ያዝኩ ።

ከበሮው ተደለቀ ፣ ዋሽንቱ እሪ አለ ፣ ቫዮሊኑ ተንሰጠሰጠ ፣ ሳክስፎኑ አምባረቀ ... ። ሳቅ ሁካታ ጎነነ ። ሰዉ ጥንድ ለጥንድ እየተቆላለፈ ዳንኪራውን ያቀልጠው ገባ ። አይኔ እዚህም እዚያም ቢቁለጨለጭም አብይ ተግባሩ ግን ማክሲምን መፈለግ ነበር ። ከአንዱ ጥግ አየሁት ። እንግዶችን ያጫውታል ። የኔው አይነት በግዴታ የተፈጠረ ደረቅ ፈገግታ እፊቱ ላይ አየሁበት ። ቀስ ብዬ ወደ እርሱ አዘገምኩ ። ስጠጋው ይርቀኛል ፣ ስቀርበው ይሸሸኛል ። አይኑን ስከተል አይኑን ያሸሽብኛል ። ድምፁን ስከተል ልሳኑን ይቀብርብኛል ። አልፎ አልፎ መሸሽ በማይችልበት ሁኔታ ሲወጠር ከጎኔ ለመቆም ቢገደድም ቃል አይተነፍስም ነበር ።

ቢያትሪስ እየደነሱ ሳለ ባሻገር አዩኝና ሙሉ ፈገግታቸውን ሲለግሱኝ አፀፋውን መለስኩላቸው ። ባለቤታቸውም ከሰው መሀል ፈልገውኝ ለዳንስ ጠየቁኝ ። እየተጫወትን "እንዴት ያለ ቆንጆ ልብስ ነው የለበስሽው? እዚህ ያለውን ሁሉ የሚያስንቅ ነው" ያሉኝ አይረሳኝም። በተፈጠረው ችግር የተከፋሁ ስለመሰላቸውና እኔን ለማፅናናት መሆኑ ስለገባኝ ቅንነታቸውን ከልብ አደነቅኩላቸው ።

ከሁሉም በላይ ስሜቱን የነካው ግን የፍራንክ ሁኔታ ነበር ። በሄድኩበት እየተከታተለ የሚበላ የሚጠጣ ነገር እያመጣ የግድ ይለኛል። ለምኑም ወሰፋቱ ዝግጁ ባይሆንም እርሱን ለማስደሰት ስል ብቻ ቀመስ እያደረግኩ እተወው ነበር ። ፍራንክ የሀላፊነት ግዴታ ተጭኖት እንግዶችን ለማስተናገድ ወዲያ ወዲህ ይበል እንጂ ልቡ ለመከፋቱ ከፊቱ ይታየኝ ነበር ። "ምን ላምጣልሽ? ሻምፓኝ? ሳንድዊች?" "ለምን አትደንሺም?" "ዝም ብሎ መቆሙ እኮ ያደክምሻል ፣ ለምን አረፍ አትይም?" ይለኛል እየመላለሰ ። ለኔ እንዳይጨነቅና በተቻለው እንዲዝ

t.me/OLDBOOKSPDF

ናና ብነግረውም ልቡ ሊያርፍ እንዳልቻለ ስረዳ ልዩ ፍቅር አሳደረብኝ ።

ከእንግዶቹ መሀል አንዳንዶቹ እየተጠጉኝ የቆጥ የባጡን ሲቀባጥሩ ልኝ ሳልወድ የግዴን ፈገግ እልላቸው ነበር ። ስለ ልብሴም በማያገባቸው እየገቡ ሲቀባዥሩ በአሮር አሮሩ እመልስላቸዋለሁ ። አንዱ አለባበሱ መርከበኛ የሚያስመስለው ቀዥቀዥ ያለ ጉድ እኔና ማክሲም ወደ ቆምንበት ጠጋ ብሎ "እንዴት ነው እባክህ? የባለቤትህን ልብስ እንዲህ ያበላሸው የትኛው ልብስ ሰፊ ነው ? እንዴ ፡ ትልቅ ክብር መዳረር እኮ ነው ። በቀላል መተው የለባችሁም" አለ እየሳቀና ማክሲምን ጎንተል እያደረገው ።

ማክሲም "እርሱስ ነው ፡ ግን ምን ታደርገዋለህ?" ሲል ነገሩን በአሮር ለመቅጨት እንደፈለገ ከአነጋገሩ ግልፅ ነበር ።

"እንዴት ምን ታደርገዋለህ? እኔ ብሆን ከስሼ ፍዳውን ነበር የማስቆጥረው ። የባለቤቱን የአጎት ልጅ አንዴ እንደዚሁ አልተጫወቱ ባት መሰለህ?"

"እባክህን ተዋቸው ፡ ባለጌዎች ናቸው" ነበር የማክሲም መልስ ።

ይኸው መርከበኛ ብጤ ወደኔ ዞር ብሎ "አዲሱ ልብስሽ እንኳንም ቀረብሽ ። ይኸኛው ሰማያዊ ልብስሽ 'አትርሱኝ' የሚባለውን ውብ አበባ ነው ያስመሰለሽ ። አይደለም እንዴ ማክሲም? በእኒያ ሰማያዊ ፡ ውብ ትናንሽ አበቦች ሰየምኳት እኮ ። ከእንግዲህ 'አትርሱኝ' ብላ እራሷን እንድታስተዋውቅ ባለቤትህን ንገራት ። " አለና እየገለፈጠ ሄደ ።

የማየው ሁሉ አልጥም ብሎኝ ያሰለቸኝን አንሶ የጊዜው አለመግፋት ደግሞ ይበልጥ አበሳጨኝ ። ሁኔታዬን በትርብ ሲከታተሉ የቆዩት ቢያትሪስ "ፊትሽ እንዴት ነው ጥቀርሻ የመሰለው? እስቲ ትንሽ አረፍ በይ" ሲሉኝ

"አይ ምንም አልሆንኩ ። ደህና ነኝ ፡ አልደከመኝም" አልኳቸው ። ወዲያው ጂልስ መጡና "ነይ እስቲ ወደ ሰገነቱ ብቅ ብለን ርችቱን እንመልከት" ብለው ይዘውኝ ወጡ ።

ልዩ ልዩ ቅርጾች ያላቸውና በልዩ ልዩ ሀብረቀለማት የተሸለሙ ርችቶች ወደ አየር ተስፈንጥረው ጥቁሩን ሰማይ አለበሱት ። ተፈጥሮ

t.me/OLDBOOKSPDF

የማይጠገብ ውበቱን የለገሳቸው ከዋክብትን የሚፈታተኑ የሚመስሉ ሰው ሰራሽ ብርሃናዊ ጌጦች በየማእዘኑ ተሰራጩ ። እጥፍ ዘርጋ ፡ ስብስብ ፈካ እያሉ አየሩ ላይ ሲምነሸነሹ ፡ አንገቱን አንጋጠ የሚመለከታቸው ሁሉ እንዲያ ሲፈነድቅና ሲያስካካ ሳየው "ምን የሚሉት ፊሊጥ ነው? ሰው እንዴት እንዲህ ይጃጃላል?" አሰኘኝ ።

የርችቱ ስነ ስርዓት እንዳበቃ የበአሉን መጠናቀቅ የሚያበስሩ ልዩ ልዩ የህብረት መዝሙሮች ተዘመሩ ። በዚህ መሀል አንዳንዱ ሰው በተራረፉት ምግቦች ላይ እንዲያ ሲረባረብ ማየት በጣም የሚያሳፍር ነበር። ትዝብቱ በተለይ በአንዲት ሴትዮ ላይ ያመዘነ ነበር ። ሌሊቱን ሙሉ አፍ ከልፍለፋና ከምግብ አልተለየም ። አንዴም ቂጧ መሬት ሳይዝ እንዲሁ እንደተቅበጠበጠችና እንደዘለለች ነጋላት ። አሁን ደግሞ አጠገቧ ያገኘችውን ሁሉ እያነሳች ስታግበሰብስ "መጥኔ እቱ" አልኳት በሆዴ ።

ሰዉ ተራ በተራ እየቀረበ አድናቆቱንና ምስጋናውን በመግለፅ ይሰናበተኝ ጀመር ። ማክሰኞም ፈንጠር ብሎ በሚሰናበቱት እንግዶች ተከቦ አየሁት ።

"ወይኔ ! አልቂአለሁ ።" አሉ ቢያትሪስ ዝልፍልፍ ብለው ወደኔ እየቀረቡ ። "ሙትት እኮ ነው ያልኩልሽ ። መቼም እግሬ እንዴት እንደዛለ ባየሽልኝ ። ጭራሽ የኔ እግርም አይመስለኝ ። አንቺዬ ፡ አሁን ሳስበው ግርም ይለኛል ፡ አንድም ጊዜ እኮ ዳንሱ አላመለጠኝም ። ቢሆንም በጣም ነው ደስ ያለኝ ። ቆንጆ በአል ነበር ።"

"እውነት?" አልኳቸው በስሱ ፈገግ ብዬ

"ሙች ፡ ምንም እንኮን አይወጣለትም ። ይህን ልብስሽን ደግሞ ሰው ሁሉ እንዴት ነው ያደነቀው መሰለሽ ። ማምሻውን ምን እንደተፈጠረ ምንም የጠረጠረ ሰው የለም ። በይ እስቲ አንቺም ሌሊቱን ሁሉ ቁመሽ አይደለም እንዴ ያነጋሽው? አሁን ገብተሽ ጥቅልል ማለት ነው ።"

"እሺ ፡ ግድ የለም እደርሳለሁ ።"

"ሆዴ ባዶ ስለሆነ እስቲ የሚቀመስ ነገር ልፈልግ ። አንቺም ትንሽ ከኔ ጋር ትቀምሻለሽ" ብለው ለማምጣት ሲዘጋጁ እኔ ምንም እንደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ማልፈልግ ነገርኳቸው ።

"በይ ፡ ሂደሽ አረፍ በይ ። ለማክሲም እነግረዋለሁ" አሉኝ ። ጉንጮቼን ስመው እያሰናበቱኝ ።

ደረጃውን እንዴት እንደወጣሁት ሳላውቅ እንደ ምንም እየተጎተትኩ ከመኝታ ክፍሉ ገባሁ ። ልዩ የእርጅና ፡ የነዳንት ስሜት ከበበኝ ። ከሰው መሃል ሆኜ እንዲያ ብቸኝነት እንዳላስፈሌነቸኝ ፡ ብቻዬን ክፍሉ ውስጥ ስቆም ግን አዲስ ሀያወት የዘራሁ ነው የመሰለኝ ።

የንጋት ጐህ መስተዋቱን ሰንጥቆ አስተናገደኝ ። አእዋፍ የማለዳ ገፀ በረከታቸውን ለገሱኝ—ጥዑም ዜማቸውን ። ልብሴን አወላልቼ ፡ መጋረጃውን ዘርግቼ ፡ አልጋዬ ላይ ተዘረጋሁ ። ሰውነቴን አዝናንቼ እይኔን ቀለስ ባደርገውም እእምሮዬ ግን የሌሊቱን ትያእንት በምልሰት እየተጫወተ አላርፍ አለኝ ። አይኖቼ ያለ ፍላጎቴ እየተገለጡ ቢያስቸግሩኝ በእጆቼ ጥርቅም አድርጌ ይዠአቸው "አደብ" ብላቸውም የአእምሮዬ መዋለል እየገፋፋቸው ከመዳፎቼ ስር ሲንከባለሉ ይሰማኝ ነበር ።

የማክሲም መዘግየት ቢያሳስበኝ ቀና ብዬ አልጋው ላይ ፈለግኩት ። አልነበረም ። አልጋው ብርዱን ለማስተናገድ የተነጠፈ ቢመስለኝ በጣም ጠላሁት ። ኮሞዲኖው ላይ የነበረው ሰአት 'ቲክ ፡ ቲክ ፡ ቲክ' እያለ 'ሀሳብሽን አንዳፍታ' አለኝ—የጊዜን አያቋርጡ እንቅስቃሴ ሲያስገነዝበኝ ። በጎኔ ጋደም ብዬ አይኔን ሰአቱ ላይ ተክልኩት ። የሴኮንድ ቆጣሪው አንድ ፡ ሁለት ፡ እያለ ያዘግማል — ደቂቃ ይሞላል ። የደቂቃ ቆጣሪው አንድ ሁለት ይቆጥራል— ሰአት ይደውላል ። ሌላ ሴኮንድ ፡ ሌላ ደቂቃ ፡ ሌላ ሰአት — ማክሲም ግን አልመጣም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምእራፍ አስራ ሰባት

ከእንቅልፌ ሳነቃ ከቀኑ አምስት ሰአት ሆኖ ነበር ። እንደ ነገሩ የተውኳቸው ልብሶቹ በስርአት መቀመጣቸውና የሻይ በራድ አጠገቤ መኖሩን ሳይ ክላሪስ ገብታ እንደነበረ ተገነዘብኩ ። ቀዝቃዛውን ሻይ እየጠጣሁ እንቅልፍ ባልጠገቡት አይኖቹ ግራ ቀኙን አሰስኩት ። የማክሲም አልጋ እንደዚያው ባዶውን ሆኖ ማየቱ ሀሣቤ ወደትናንቱ ምሽት ትእይንት ይጎትተኝ ጀመር — አእምሮዬን ሊረብሽ ።

የክላሪስ ገብቶ መውጣት ሲታወሰኝ ደግሞ መላ አካሌ ይበልጥ ተናወጠ ። አልጋው እንደተነጠፈ መሆኑን ስታይ ማክሲም ወደ መኝታ ክፍሉ እንዳልገባ ሳትጠረጥር አትቀርም ። ያየችውን አይታ ግርምቃዋ ንም ሆነ ጥርጣሬዋን ለእራሷ ብቻ አድርጋው ብትቀር መልካም ። ግና ለሌሎች የስራ ባልደረቦቿ ማካፈሏ አይቀርም ። ወሬው ከመቅፅበት እንደ ሰደድ እሳት ሲዛመት ታየኝ ። 'ምን ልበል?' አፎችና 'ምንአሉ?' ጆሮዎች በበረከቱበት በኛ ቀዬ ይህ ተገኝቶ?!

ይሁንና ለሠራተኞች ሹክሹክታ ፡ ለወሬ ሱሰኞች አሉባልታ ይህን ያህል መሸበሬ ለምንድነው? ትናንትና ማታስ ቢሆን ከዚያ ድርጊት በኋላ ከፍሉ ገብቼ መቅረት ስችል ሰማያዊውን ልብሴን ለብሼ በክብረ በአሉ ላይ የተገኘሁት ይህች ትንሿ ጭንቅላቱ ሀሜትን ፡ አሉባልታን እንደ አንድ ነገር አክብዳ በማየቷ አይደለም እንዴ? በበአሉ ላይ የተገኘሁት ለማክሲም ብዬ? ለቢያትሪስ? ወይስ ለማንደርሌይ? በፍፁም ። ለራሴ ስል ነው ። ግለ ክብሬን ለማስጠበቅ ብቻ ። ተጋባዦች "... ከማክሲም ጋር ተጣልታለች ። ምንጊዜም ደህና ሁነው አያውቁም ... " እያሉ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዳይዘባበቱብኝ ተዳዳውን ለመድፈን ስል ብቻ ነው ።

አጠቃላይ ሁኔታዬን ስመረምረው አዝማሚያዬ የጤና አልመሰለኝም ። የውጭው አለም እስካላወቀብን ድረስ እኔና ማክሲም በየግል አለማችን ተፈጥመን ብንኖር ምንም አይሰማኝም ማለት ነው ። ለራሴ ሳይሆን ለሌሎች ስል መኖሬ የምን ፈሊጥ እንደሆነ እንቆቅልሽ ሆነብኝ ።

አይኔ እንደገና ያረፈበት የማክሲም ባዶ አልጋ የእኔን ህይወት ባዶነት የማያስታውሰኝ መሰለኝ ። ሰው የትዳር ህይወቱ ከመጨናገፍ በላይ የሚያሳፍረው ፡ እንጉቱን የሚያስደፋው ነገር ይኖር ይሆን? በተለይ እንደኔ ትዳሩ ገና ከጥንስሱ ፡ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ብትንትን ሲልበት የሞት ሞት አይደለም እንዴ? ለካስ ሰው የሚለው አውነቱን ኖሯል? "ያላቻ ጋብቻ" እያለ ሲንሾካሾክ 'ያጣ ወፌ' ብዬ ጆሮ ዳባ ማለቱ ምንኛ ብሳሳት ነው! ማክሲምን እንደ አንድ ታማኝ ውሻ ከአንጀቱ ፡ ከልቤ ማፍቀሬ ለካስ ረብም የለው ። እርሱ ለኔ ፍቅር ደንታ የለውም ። ብዙ ነየው ፡ ብዙ ለለመደው ማክሲም ደስታ አንናዕፈዋለሁ የሚለው የኔ ውርውርታ የስሜት ቅርፊቱን እንኳን ሊዳስሰው እንደማይችል ታወቀኝ።

እኒያ ሚስዝ ቫን ሁፐር "ይህ የዛፌው ስህተትሽ ነገ ትልቅ ዐፀት የምታተርፊበት እንዳይሆን ... አፍቅሮኛል ብለሽ እንዳትመዓጂቂ ። የልብ ልብ አይሰማሽ ..." ሲሉኝ በምቀኝነት ኮነንኳቸው ፡ በጨካኝነት ወነጀልኳቸው ። ዛሬ ግን አወቅኩት ። ማክሲም ለኔ ቅንጣት ፍቅር አልነበረውም ፡ አሁንም የለውም ። ነገም ያፈቅረኛል ብዬ በከንቱ ልቤን አላንጠለጥለውም ። ለእርሱ ፍቅሩም ህይወቱም ርብቃ ናት ። ትናንት መላ ፍቅሩን ሰጥታለች ። ዛሬ ርብቃ በአካል ብትለየውም የትናንት ፍቅሩን ፡ የትናንት አሳቢነቱን ሊነፍጋት አልቻለም ። ሚስዝ ዳንቨርስ እንዳሉት ሁሉ ርብቃ ሞታ አልሞተችም ። በመላ ማንደርሌይ ዛፌም አለች ። በየክፍሉ ፡ በየመኖፈሻው የርብቃ መንፈስ ይንቀሳቀሳል ። ልብሶቿ ፡ ጌጣጌጦቿ ፡ መገልገያ ቁሳቁሶቿ ሁሉ እንዳሉ ናቸው ። እያንዳንዱ የማንደርሌይ ህይወት የሚንቀሳቀሰው በእርሷ መመሪያ ነው። ሠራተኞች ሁሉ የሚመሩት በእርሷው ትእዛዝ ነው ። የቤት ውስኖ ድርጅትም ሆነ የየእለት ምግባችን የሚዘጋጀው በእርሷው ንድፍ ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የማክሲም አያት እንኳን "አንቺን አላውቅሽም ። ርብቃ የት አለች? ርብቃን አምጡልኝ" እያሉ ሲወተውቱ አልነበረም እንዴ? ቢያትሪስም ቢሆኑ መጀመሪያ የተገናኘን እለት "ከርብቃ በጣም የተለየሽ ነሽ" ብለውኝ የለ? ያ የዋሁና ቅኑ ፍራንክም "በህይወቱ እርሷን መሰል ውብ አይቼ አላውቅም" እኮ ነው ያለኝ ። ሳር ቅጠሉ ሁሉ 'ርብቃ' 'ርብቃ' ። ታዲያ የኔ ባዶ ህልውና ትርጉሙ ምንድነው?

የሰውን አፍና አስተሳሰብ እንደሆንኩት ሆኜ ልቋቋመው ብጣጣ ርም ከእርሷ ጋር መጋፈጡን ነው ያልቻልኩት ። ስበላ ስጠጣ ፡ ስቀመጥ ስነሳ ፡ በሀሣቤም ሆነ በህልሜ እየመጣችብኝ እረፍት ነሳችኝ ። ከህያዋን ጋር የቻልኩትን ያህል ለመታገል እሞክር ይሆናል ፡ ከሙት ጋር ግን ፡ የመፋለም አቅም የለኝም ። ሎንዶን ውስጥ ማክሲም ቅምጥ ቢያስቀምጥ እንኳን በኔ በኩል ችግር አልነበረም ። በቅናት ብበግንም ጣውንቴን ታግዬ ለመጣል ግን የምሰንፍ አልነበርኩም ። ያም ባይሆን ቁጣና ቅናት ፈልተው ገንፍለው መብረዳቸው አይቀርም ። አንድ ቀን ይህችው ጣውንቴ እርጅና ይጫጫናትና ፡ አቅሙ ይከዳትና ፡ ውበቷ ይረግፍና ፡ ወዟ ይሚጠጥና ማክሲም እርግፍ አድርጎ ሊተዋት ይችላል ። ርብቃ ግን ምኔም የምታረጅ አይደለችም ። ምኔም አትደክምም ። ታዲያ እኔ እርሷን የምፋለምበት አቅሙንስ ሆነ ችሎታውን ከየት አባቴ አምጥቼው?

አንሶላውንና የአልጋ ልብሱን ወደ ጎን ብዬ ተነሳሁ ። የመስኮቱን መጋረጃ ሰብሰብ አድርጌ ዙሪያውን ማተርኩ ። እቃዎች ሁሉ ወደየስፍራቸው ተመልሰው አካባቢው የወትሮ መልኩን ይዟል ። ወደ በሩ መለስ ስል ደግሞ ወለሉ ላይ አንድ ማስታወሻ አየሁ ። ከብእር አጣጣሉ የቢያትሪስ ፅሁፍ መሆኑን ለማወቅ ጊዜም አልጠየቀኝ ።

"አንኳኩቼ ምላሽ ሳጣ በምክፊ መሰረት ለጥ ማለትሽን ተረዳሁ ። እኔ እንኳን ጥቂት እንድንቆይ ፈልጌ ነበር ። ነገር ግን በዛሬው እለት በሚካሄደው የክሪኬት ውድድር አንድ ተጫዋች ተከቶ እንዲወዳደር ለጂልስ መልእክት ስለደረሰው መሄዳችን ነው ። ውድድሩ በስምንት ሰአት ስለሚጀምር መቆየት አልቻልንም ። ጂልስ ያንን ሁሉ ሻምፓኝ ሲለጋ አድሮ ኳሱን እንዴት እንደሚያይም እንጃለት ። ማክሲምን ልንሰናበተው ፈልገን ልናገኘው አልቻልንም ። ማለዳ ለቁርስ ብቅ ብሎ እንደነበር ፍሪዝ ነገሩን ። ስለዚህ ሰላምታችንን እንድታደርሽልን ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በማታው በአል ከሚገባ በላይ ረክተንበታልና ለሁለታችሁም ላቅ ያለ ምስጋናችንን እናቀርባለን ። የልብሱን ነገር ከአእምሮሽ ፍቀሽ አውጪው። ምን ጊዜም ያንቺው — ቢ”

ነበር የሚለው የቢያትሪስ ማስታወሻ ።

የቢያትሪስን ማስታወሻ አንብቤ ሳበቃ ስለ ሁለቱ የትዳር ጓደኞች የደስታ ኑሮ ፣ ሀያ አመታት ስላለፈው የጋብቻ ዘመናቸው አሰብኩና ቀናሁባቸው — በሦስት ወራት ፍርክስክስ ካለው ከኔ ትዳር ጋር በማነፃፀር።

ወደ ውጪ ከመውጣቴ በፊት የማክሲምን አልጋ የተኙትበት ለማስመሰል ብትንትን አደረግኩት ። እንዲያው ያቺን ክላሪስ አንዳች ይዞልኝ ካልነገረቻቸው ሌሎች ሠራተኞች እንዳያዩት ብዬ ነበር ።

ገላዬን ከታጠብኩ በኋላ ልብሴን ቀይሬ ወጣሁ ። ሮበርት ጠረጴዛዋችን ሲያፀዳ አገኘሁትና ስለማክሲም ጠየቅኩት ። ቁርሱን ቀማምሶ መውጣቱን እንጂ ወዴት እንደሄደ እንደማያውቅ ነገረኝ ። ወደ ዋናው ፅህፈት ቤት ደውዬ ስጠይቅ እዚያም እንዳልነበረ ከፀሀፊው ተረዳሁ ።

“እመቤቱ ሊያነጋግሯቸው ከፈለጉ ግን ሚስተር ክሮውሌይ አሉ” አለኝ ፀሐፊው ። በዚያን ወቅት ማንንም ለማነጋገር ፍቃደኛ አልነበርኩም ። ፀሐፊው ግን ሀሣቤን የመግለፅ ፋታ ሳይሰጠኝ “ምን ችግር አለ?” የሚለውን የፍራንክን ድምፅ ሰማሁ ። ገረመኝ ። ‘እንደምን አደርሽ?’ ብሎ የእግዚአብሄር ሰላምታ እንደማቅረብ ‘ምን ችግር አለ?’ ብሎ መጀመሩ ቢገርመኝም፡—

“እንዴት አደርክ ፍራንክ? ማክሲም የት ነው የሄደው?” ስል ጠየቅኩት ።

“እኔ እንጃ ፣ አላየሁትም ።”

“ወደ ፅህፈት ቤት አልመጣም ማለት ነው ?”

“ከነጋ አልመጣም”

“እሀ ፣ እሺ ፣ በቃ ተወው”

“በቁርስ ሰአት አላየሽውም እንዴ ?”

t.me/OLDBOOKSPDF

“ተኝቼ ስለነበር አልተገናኘንም ”

“እርሱስ እንዴት … የት ነበር የተኛው?” ብሎ ሲጠይቀኝ ግን ጥቂት ባመነታም ከእርሱ በላይ የማምነው ሰው ባለመኖሩ ልደብቀው አልፈለግኩም ።

“እንዲያውም ወደ መኝታ ክፍል ብቅም አላለ” አልኩት ።

ፍራንክ ጥቂት ፀጥ ብሎ ከቆየ በኋላ “እህ ፣ ነው? … እ … እኔም ጠርጥሬ ነበር” አለኝ ።

“ስማ እንጂ ፍራንክ” አልኩት ተቻኩዬ ‘ ለመሆኑ ሰዉ ከተበተነ በኋላ ማክሲም የተናገረው ነገር ነበር እንዴ? እናንተስ ምን ስትሰሩ ቆያችሁ?”

“እኔ ከጂልስና ከቢያትሪስ ጋር ሳንድዊች ስበላ ቆየሁ ። ማክሲም ግን ይቅርታ ጠይቆን ወደ ቤተ መፃህፍቱ ገባ ። ከዚያ እኔም ብዙ ሳልቆይ ወደ ቤቴ ስለተመለስኩ ምን እንደተፈጠረም አላውቅ ። ምናልባት ሚስዝ ሌሲ ሳታውቅ አትቀርም ።”

“እርሳቸውማ ሂደው የለም እንዴ? ማክሲምን እንዳላዩትም ማስታወሻ ትተውልኛል”

ፍራንክ “እህ” ብሎ ፀጥ ማለቱን አልወደድኩለትም ።

“የት የሄደ ይመስልሃል ታዲያ?” ስል ጠየቅኩት

“ምን ይታወቃል? ምናልባት ለሽርሽር ወጣ ብሎ ይሆናላ”

“ማክሲምን የጣድ አግኝቼው ስለ ትናንትናው ሁኔታ ማስረዳት አለብኝ ። ሆን ብዬ ያደረግኩት መስሎት ቂም — ሳይዝብኝ — አልቀረም … ” ድምጼ ድንገት ቁርጥርጥ አለብኝ ። ሌሊቱን ሁሉ አምቄ የያዝኩት እንባዬ ገንፍሎ ጉንጮቼን ያጥብ ጀመር ። “ሆን ብዬ በእርሱ ለማሾፍ ያደረግኩት መስሎታል እኮ” አልኩት ፍራንክን

“አይ ፡ እንደዚያ እንኳን አይደለም ”

“አሆሆ ! ነው እንጂ ፍራንክ! አንተ አላየኸውም ፣ አይኑ እንዴት ደፍርሶ እንደነበረ ። ሌሊቱን ሙሉ አንዴ ሶር ብሎ አላየኝም ብልህ ፣ አንዲት ቃል አላናገረኝም ብልህ ታምነኛለህ?”

“ያ እንኳን በቂ ምክንያት አይደለም ። በእንግዶች ተከቦ እያየሽው? ደግሞ ማክሲምን እስክማውቀው እን… ”

t.me/OLDBOOKSPDF

"እኔ እኮ እንዲያ ቢመስለውም እውነት አለው ነው የምለው ። እይኔን ለማየት ቢጠየፍ ፡ ንግግር ቢነፍገኝ አልፈርድበትም ።"

"የለም ፡ እንዲህ እንኳን ማለት አይገባም ። አስቲ ብቅ እልና እንጨዋወታለን"

"መጥተህ ምንም የምታደርገው ነገር የለም ። አንዱ ከሆነ ወዲያ ላይቀና ነገሩን እየደጋገሙ ማንሳቱ ምን ፋይዳ አለው ብለህ? ይልቅ እኔ ትልቅ ትምህርት ነው ያገኘሁበት ። እንዲያው ጅብ ከሄደ ውሻ ፈሪ እይነት ሆነብኝ እንጂ"

"ምንድነው የምታወራው?"

"ማክሲምን ከማግባቱ በፊት ይህን አስቢና ጠርጥሬ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ለዚህ ባልበቃው ነበር ።

"ምን እንደምትይ ሊገባኝ አልቻለም"

"ስለ ማክሲምና ስለ ርብቃ ነዋ" ስለው በረጅሙ ተነፈሰና ወጥ አለብኝ ። ጥቂት ከቆየ በኋላ "ምንድነው የምትይው?" ሲል ደጋግሞ ጠየቀኝ ።

"አውን ይሄ ጠፍቶህ ነው? እንዲህ ልታስለፈልፈኝ ፈልገህ እንጂ ። ማክሲም በፍፁም እንደማያወደኝ አውቂዋለሁ ። እርሱ አሁንም ቢሆን ፍቅሩ ያለው ርብቃ ዘንድ ነው ። ኑጋ ጠባ ሠማዩ ርብቃ ፡ ርብቃ ፡ ርብቃ ፡ ብቻ ናት ።" አልኩት ።

ፍራንክ በድንጋጤ ሲጮህ ሰማሁት ። "እንግዲህ ምን ያህል እንጂቱ እንደበገነ አውን የገባህ ይመስለኛል" አልኩት ።

"መጣሁ ፡ መጣሁ ። ይሄ ነገር እንዲህ በቀላሉ በቴሌፎን የምናወራው አይደለም ። መጣሁ" አለኝ ። ቴሌፎኑን ለመዝጋት ወረድ ሳደርገው "ሚስዝ ደዊንተር? ሚስዝ ደዊንተር?" በማለት እየጮኸ ሲጣራ ሰማሁት ።

ከፍሉን ለቅቄ ወጣሁ ። ወዴት እንደምሄድ ባላውቅም ቤቱ ስላስጠላኝና ሂጂ ሂጂ ስላለኝ ብቻ ወደመናፈሻው ገባሁ ። ጆስፐር ተከተለኝ ። ወደ ሽለቆው የሚያመራውን መንገድ ስያያዘው ገም አንድ ጊዜ መጣና አካባቢውን አለበሰው ። አይኔን ወደቤቱ ስመልሰው አንድ ጥላ መሰል ነገር ከአንደኛው መስኮት ተጠግቶ ቁልቁል ሲመለከት አየሁ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በጣም ደንግጥኩ ። ማክሲም መሰለኝ ። አለመሆኑን ያወቅኩት ግን ጥቂት ቆይቶ ጉሙ ትንሽ ለቀቅ ሲያደርግና የቆመው አካል መንቀሳቀስ ሲጀምር ነበር ።

ሚስዝ ዳንቨርስ ።

አሮጊቷ ከዚያ ላይ እንቅስቃሴዬን ሁሉ ሲቆጣጠሩ ነበር ማለት ነው። ቀደም ብለውም እዚያው መሽገው ከነበር በቴሌፎን ከፍራንክ የተጫወትነውን ሁሉ ሳያሰሙ አልቀረም ። ሀዘን የተቀላቀለበት ድምጼንና ልቅሶዬን ሲሰሙ ምን ያህል እንደሚፈነድቁ ሲታወሰኝ ብግን አልኩ። ለዚህ ሁሉ ያበቁኝ እርሳቸው በመሆናቸው ቢፈነድቁም ይገባቸዋል ። ድሉ የእርሳቸው ነው ። የርብቃም ሟምር ።

በቀጥታ ስክንፍ ወደቤት ተመለስኩ ። ደረጃውን እየሮጥኩ ወጣሁና የርብቃን ክፍል ከፍቼ ገባሁ ። ሚስዝ ዳንቨርስ እዚያው መስኮቱ አጠገብ እንደቆሙ ነበር ።

"ሚስዝ ዳንቨርስ ፡ ሚስዝ ዳንቨርስ" ብዬ ሁለቱ ከተጣራው በኋላ ዞር ብለው አዩኝ ። አይኖቻቸው ቀልተዋል ፡ አባብጠዋልም ። ፊታቸውም ጥቀርሻ ለብሷል ።

"ምንው?" አሉኝ በንረነን ድምፅ

እንደትናንቱ ማታ የፈዝ ፈገግታቸውን ያሳዩኛል ብዬ ነበር የጠበቅሁት ። እንኳን ሊፈግጉ ፊታቸው ጨፍጎት ፡ ጉስቁል ፡ ድክም ብለው ሳያቸው ግራ ተጋባሁ ። ምን ማለት እንደሚገባኝ ሳሰላስል በእኒያ ለቅሶ ባቀላቸውና ባሳበጣቸው አይኖቻቸው ትኩር ብለው ሲያዩኝ ከቆዩ በኋላ "የምጣቡን ዝርዝር እተለመደው ቦታ ላይ አትፈልዎታለሁ ። እንዲለወጥ የሚፈልጉት ነገር አለ?" ሲሉ ጠየቁኝ ።

"ሰሙ ሚስዝ ዳንቨርስ ?" በማለት ጀመርኩ ። ለንግግር መንዴን ስለከፈቱልኝ የልብ ልብ ተሰማኝ ። ይገርው የቆየሁትን የበሩን እጀታ ለቅቄ ወደ እርሳቸው ተጠጋሁ ። "ሰሙ ሚስዝ ዳንቨርስ ? ስለ ምግቡ ዝርዝር ለመነጋገር እንዳልመጣሁ ልቦናዎ እያወቀ ለምን ሊያሳስቱኝ ይሞክራሉ ?" አልኳቸው ። መልስም አልሰጡኝ "ሲያልሙት የነበረውን ስለፈፀሙ ልብዎ ቅቤ ነው የጠጣው ። አይደለም እንዴ?" ስል ጠየቅኳቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ፈታቸውን አሠሩት ። በመስኩት ውጭ ውጨን እያዩ "ምነው እዚህ ማንደርሌይ ባልመጡብን ? በእርስዎ መምጣት ማንም እንዳልተደሰተ አያውቁም? ያን የመሰለ ሰላማዊ ኑሯችንን ከሚያደፈርሱብን እዚያው ፈረንሳይዎ ውስጥ አርፈው ቢቀመጡ እንዴት ያለ አረፍት በሆነልን"

"እዚህ ያመጣኝ የሚስተር ደዊንተር ፍትር መሆኑን ዘንተት ልበል ወይስ...?"

"እውነት ለእርሳቸ ው ፍትር ቢኖርዎ ኖሮ በፍፁም ባላገቡዋቸው ነበር" ሲሉኝ የምናገረው ጠፋኝ ። አሮጊቷ አይናቸውን ከመስኮቱ ባሻገር እንደተከሉ እንት እንት በሚለው ድምፃቸው ቀጠሉ ። "በመጀመሪያ ጥልት ነበር ያደረግሁዎት ። አሁን ግን ይህን ሀሳቤን ትቼዋለሁ ።"

"እንዴ ፡ በምን ምክንያት ነው የሚጠሉኝ? ምን በደልኩዎት ?"

"የሚስዝ ደዊንተርን ስፍራ ለመንጠት በመሞከርዎ ነዋ"

"የማንደርሌይን የእለት ተእለት እንቅስቃሴ በሚመለከት እንድም ያደረግኩት ለውጥ እንደሌለ እያወቁ? ሁሉንም ነገር እንዳሻዎት ብዬ ለእርስዎ ትቼው የለም እንዴ? ሀ ብዬ ይህን ግቢ ከረገጥኩበት ቀን አንስቶ ፊትዎን ያጠቆሩብኝ እርስዎ ነዎት እንጂ እኔ ከእርስዎ ጋር መልካም ግንኙነት ለመፍጠር ያልጣርኩበት ጊዜ የለም ።" አልኳቸው ። መልስ የለም ። "ለሁለተኛ ጊዜ መጋባት በኔና በማክሲም ነው እንዴ የተጀመረው ? ሰው የመጀመሪያ ጋብቻው በልዩ ልዩ ምክንያቶች ሲፈርስበት ዳግም ማግባቱ እንግዳ አይደለም ። ታዲያ እኔ ማክሲምን ማግባቴ እንደ ወንጀል ፡ በሚችል ላይ እንደፈፀምኩት በደል አድርገው የሚያወሩት ለምንድነው ? እኔና ማክሲም እንደ ማንኛውም ሰው ደስተኞች ሆነን የመኖር መብት የለንም ማለት ነው?"

ይህን ስላቸው ዞር ብለው አዩኝና "ሚስተር ደዊንተር ናቸው እንዴ ደስተኛው፣ ማንም ደንቆሮ አይናቸውን በማየት ብቻ የሚናገረውን ? ደስታ ከራቃቸው ዘመንም የለው ። እርሷ ከሞተች በኋላ አንድም ቀን ተደስተው አያውቁም" አሉኝ ።

"ሀሰት ፡ ሀሰት ። ፈረንሳይ በነበርንበት ወቅት እንዴት ደስተኛ እንደነበረ ሳውቀው? ፈጣዎታው ፡ ሳቁ ። እንዲያውም ከደስታ ብዛት ጭራሽ ጉረምሳ ነበር የሚመስለው ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ለዚያ ለዚያማ ወንድ መሆናችው ቀረ እንጂ፣ ሙሽራ ማቀፍ ልቡን የማይተረክከው ወንድ ከቶውንስ ይኖራል?" በማለት ትከሻቸውን እየወጣጠሩ የፈዝ ጥርሳቸውን ብልጭ አድርገው "ምንም ቢሆን ሚስተር ደዊንተር እኮ አርባ ስድስት አመታቸው ነው ።" አሉ ።

ንድድ አለኝ ። "ምን ያህል ቢያፍሩኝ ነው እንዲህ የሚሉት ?" አልኳቸው ። ፍራቻዬ ተገፈፈልኝና ቀጥ ብዬ ወደ እርሳቸው ሄጄ እጃቸውን ይዤ እየወዘወዝኩት "እድሜ ለእርስዎ ፣ ትናንት ማታ ያንን ቀሚስ እንድለብስ ያደረጉት ሆን ብለው አይደል? የማክሲምን ስሜት ለማድማት፣ እንዲበሳጭ ብለው እንደሆነ ኃላ ነው የገባኝ ። እስከ ዛሬ የተበሳጨው ፣ እስከ ዛሬ የተሰቃየው አንሶት ነው ይህን የጠነሰሱለት ? ለመሆኑ የማክሲም መሰቃየት ሚስዝ ደዊንተርን ከመቃብር የሚመልስ ይመስልዎታል?"

"ተዪኝ እባክሽ?" ብለው እጃቸውን ሞንጭቀው አስለቀቁኝ ። "በሰቃይ ባይሰቀይ ደንታዬ መሰለሽ ። እርሱስ ስለኔ ስቃይ መቼ አስቦ ያውቅና ? እንጂ? ምን ማለትሽ ነው? አንቺ በእርሷ እግር ተተክተሽ እዚህ መኖርሽን ሀሊናዬ በፀጋ ሊቀበለው የሚችል ይመስልሻል? በእርሷ ከቡርና ምርጥ እቃዎች ስትጠቀሚ አይኔ ማየቱን የሚፈቅድ ይመስል ሻል? አፈሩን ገለባ ያድርግላትና እውነተኛዋ ሚስዝ ደዊንተር ፣ ሀቀኛዋ እመቤቱ መቃብር ተጭኗት እነ ሮበርት ፣ እነ ፍሪዝ 'ሚስዝ ደዊንተር ይህን አለች ፣ ሚስዝ ደዊንተር ይህን አደረገች' እያሉ ያለ ስምሽ በስሟ ሲጠሩሽ ልቡ ምን ያህል ጭስስ ፣ ብሶን እንደሚል ባወቅሽልኝ ። ታዲያ ሚስተር ደዊንተር 'ተሰቃየ ፣ ተሰቃየ' የምትዪው ሲያንሰው ነው ። በገዛ እጁ ያመጣው ስለሆነ እንደገባበት ይወጣው ። ቀን በሀሣብ ፣ ሌሊት በህልም እየመጣችበት የቁም ስቅሉን እያሳየችው ነው ። 'ገሀነም ሲመርዱ ይታየኛል ። ብተዋቸው አይተወኝ' እያለች ዘወትር በሀሣብ ትመላለስብ ኛለች ። አይ ሰው አለማወቅ! የኔዪቱ ሚስዝ ደዊንተር እኮ የወንድ ልብና ወኔ ነበር የነበራት ። 'ምነው ወንድ አድርጎ በፈጠረሽ' ነበር የምላት" አሉ አይናቸውን እያጉረጠረጡ ። እጅግ መናደዳቸውን የተረዳሁት ከኔ አልፈው ማክሲምን ጭምር ከበፊቱ በመንፈጋቸው ነበር ።

"ምነው ቢበቃት ሚስዝ ዳንቨርስ? ይህን ሁሉ ምን አመጣው? እንደ እርስዎ ሁሉ የሚነካ ስሜት ያለኝ ሰብአዊ ፍጡር ነኝ እኮ ። እፊትዎ

t.me/OLDBOOKSPDF

አቁመውኝ ይህን ሁሉ ስለ እርሷ ሲያዥጎደጉዱልኝ ምን እንደሚሰማኝ አይሰማዎትም?"

ተማፅኖዬን ቁብም ሳይሉት ቀጠሉ ። "የልጅነት ውበቷስ? ስእል ነበር የምትመስለው ። ገና የአስራ ሁለት አመት ልጅ ሳለች ውበቷ ሱሪ ያጠለቀውን ሁሉ የሚያማልል ነበር ። 'ዳኒ ፡ ከፍ ስል ይበልጥ ቆንጆ ነው የምሆነው' ትለኝ ነበር ። በዚያ እድሜዋ ከአዋቂዎች ጋር ስትጫወት ፡ ስትከራከር አስተሳሰቧንና እውቀቷን የማያደንቅ አልነበረም ። አባቷ ንጣ በትንሿ ጣቷ ነበር የምታሽከረክራቸው ። ከአንቷ ልጅ ከሚስተር ጃክ ጋር ደግሞ ገና ከልጅነታቸው ጀምሮ ሲግባቡ እንዲህ አል ነበረም! እርሱም እንደ እመቤቴ ወኔያም ነበር ። የባህር ሀይል ስልጠና ውን ረግጦ የወጣው ጥብቅ ስነስርአቱ አልዋጥ ቢለው ፡ ይኸው 'ማን ደፍሮኝ' የሚለው ወኔው ቢያይልበት ነው..." አሉኝ ።

አፌን ከፍቼ ፡ በድንጋጤ ተውጬ አዳምጣቸው ነበር ። አያይዘውም ስለ ሀይለኛነቷ ፡ ስለ እውቅ ፈረስ ጋላቢነቷ ፡ ስለ አጠቃላይ የአካልና የመንፈስ ጥንካሬዋ ሲያወሩልኝ ከቆዩ በኋላ "...ለማንም የማትበገር አንበሳ ነበረች ። ምን ያደርጋል? የማታ ማታ መረታት አይቀርምና ተረታች ። ታዲያ የረታት መች ሰው ሆነና! ባህሩ አየለባት ፡ ውሀ በላት እንጂ ።" አሉና ፀጥ አሉ ። ፊታቸው ቅይርይር አለ ። እረታቸውን ያቀልጡት ጀመር ።

ደነገጥኩ ። "ሚስዝ ዳንቨርስ ፡ እባክዎን ወደ ነፍስዎ ሂደው ይረፉ" አልኳቸው ። በግልምጫ አነሱኝ ። "ምን ነው ብትተዪኝ? እኔ ሀዘኔን በገለፅኩ አንቺ ምንሽ ተነካ? ስለማላፍርበት በራን ዘግቼ አይደለም የማለቅሰው ። እኔ እንደ ሚስተር ደዊንተር በራን ጠርቅሚ አላይ ታች ፡ እታች አላይ አልንቆራጠጥም ።"

"ምን ማለትዎ ነው? ሚስተር ደዊንተር በፍፁም እንዲህ አያደር ግም ።"

"በያ ፡ ዋሸሽ በዪኝ ደግሞ ። እኔ ነኝ የቤተ መፃህፍቱን በር ዘግቼ ወጥመድ ውስጥ እንደገባ አውሬ የምንቆራጠጠው? ስንት ቀን በበሩ ቀዳዳ ያየሁትን!"

"እሺ ይብቃዎት ። እንዲህ ያለውን ነገር ባልሰማ ነው የሚሻለኝ"

t.me/OLDBOOKSPDF

“ላትዘልቂበት ለምን ትሞግቺኛለሽ ታዲያ? አሁን እንግዲህ አንቺ ነሽ በሰርጉ ሰሞን ደስተኛ አድርጌው ነበር የምትዪ? ልጁ ልትሆኚ የምትችዪ አንቺ ሙርቃ ልጅ ነሽ ፡ እርሱን የምታስደስቺ ? ስለ ህይወት ፡ ስለ ወንዶች ባህርያት ምን የምታውቂው ነገር አለና? አሁን አንቺ ነሽ እመቤቱን የምትተኪ? ሠራተኞች እንኳን እንዴት እንደሚያሽሟጥጡሽ ባየሽ...”

“ይብቃዎት አልኩኝ እኮ ሚስዝ ዳንቨርስ ። ይልቅ ወደ ክፍልዎ ይሂዱ”

“ልሂድ እንዴ? ጉድ እኮ ነው ! ቀጭኗ እመቤት እንድሄድ አዘዙ ። ከዚያስ ምን ሊኮን? እኔ ስሄድልሽ ሮጠሽ ለሚስተር ደዊንተር ሰደበችኝ ብለሽ ልትነግሪው? ያኔ ስለ ሚስተር ጃክ መምጣት እንደነገርሽው አሁን ደግሞ እንዲህ አለችኝ ፡ እንዲህ አደረገችኝ ፡ ልትዪው እንደሆነ መቺ ጠፍቶኝ ።”

“እኔ ይህንን በፍፁም አልነገርኩትም”

“ኧረ? አልነገርሺውም ? አንቺ ካልነገርሺው ጣራው ነው ወይስ ግድግዳው የነገረው ? ፍሪዝ አልነበረ ፡ ሮበርት አልነበረ ። ወፍ እንኳን ዝር እንዳላለ እያወኩት አልነገርኩትም ትይኛለሽ? ከዚያ ወዲህ ነው ላንቺም ለእርሱም የማትረሱት ትምህርት ልሰጣችሁ ቆርጬ የተነሳሁት። እኔ እንደተሰቃየሁት ሁሉ እርሱም መሰቃየት አለበት ። የእርሱ መሰቃየት አለመሰቃየት ደንታዬ መሰለሽ?! በይ ንገሪኝ እስቲ? ከሚስተር ጃክ ጋር እንዳልገናኝ የምታገድበት ምንድነው ምክንያቱ? የእመቤቱን አይን የማይበት አንድ እርሱ ቢቀረኝ እንዳንተያይ መታወጁ፡ ምን በበደልኩ? ምን በበደለ? ‘ሁለተኛ ደጃፌን አይርገጥብኝ ብየሻለሁ ፡ አይርገጥብኝ ። ይህ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ እንደሆነ ይግባሽ’ ተባልኩኛ ። ቀናተኛነቱ አሁንም ባይለቀው አይደል እንዲህ ማለቱ?” አሉኝ አሮጊቷ ሰውነታቸው እየተንዘፈዘፈ ።

ውግዘታቸው በዚሁ አበቃ ብዬ ተገላገልኩ ስል ቀጠሉ ። “በህይወት ሳለችም መቅናት ፡ ከሞተችም በኋላ መቅናት ። ምን ማለት ነው? ሚስተር ጃክን እኮ ዛሬ ብቻ ሳይሆን ያኔም አትድረስብኝ ነበር የሚለው ። ይህ ሁሉ መብከንከን ዛሬም ከአእምሮው እንዳልፋቃት

t.me/OLDBOOKSPDF

አይደለም የሚያመለክተው፣ በእርግጥ ቢቀናም አይፈረድበትም ። እኔም ሆንኩ የሚያውቃት ሁሉ እንደቀናባት ነበር ። ታዲያ እርሷ ደንታዋ መሰለሽ ። ማንንም ከመጠፍ አትቆጥርም ነበር ። 'ተያቸው እባክሽ ዳኒ ። ይንጨርጨሩ ። እንዳሻኝ ከመኖር ማንም ሊያግደኝ አይችልም ።' ትለኝ ነበር ። ትስቅባቸው ነበር ። አንዴ አይቷት ጨርቱን ጥሎ የማይከንፍ እኔ ነኝ ያለ ሱሪ ያጠለቀ ወንድ አልነበረም ። ይገባታል ደግሞ ። ስንቱን ወንድ ስታተራምሰው እንደነበረ ያየሁት አይደል? ሎንዶን ውስጥ የተዋወቀቻቸውን ሰዎች እዚህ ድረስ እየጋበዘች ፣ ባህሩ ድረስ ይዛቸው ስትሄድ ፣ እዚያው ጎጆዋ ውስጥ እራት ስትጋብዛቸው ደስ ካላትም ትተኛቸው ነበር ። ደግሞ እርሷን አግኝቶ ! ማን አልተኛም ሊል ። በማግስቱ ስትመለስ ደግሞ ምን እንደተደረገ ፣ ምን እንደተነገረ እንዲንም ሳታስቀር በዝርዝር ትነግረኝ ነበር ። ጉዳይዋ አልነበረም ። እንደ ፌዝ ፣ እንደ ጨዋታ ነበር የምትቆጥረው ። ታዲያ ሰው ሁሉ ትክን ድብን ቢል ሲያንሰው ነው ። ሚስተር ደዊንተር ብትዪ ፣ ሚስተር ጃክ ፣ ሚስተር ክሮውሌ ብትዪ ። እረ ወዲያ ፣ ሁሉ ፣ ሁሉ ነበር አልኩሽ በቅናት እብድ የሚለው ።"

"በቃዎት እባክዎ ። እኔ ይህን ሁሉ መስማት አልፈልግም" ስላቸው ይበልጥ ተጠግተውኝ ሌባ ጣታቸውን እየቀሰሩብኝ ፣ "እኮ ለአንቺማ ምን ሊረባሽ? ልክሽን ታውቂ የለ? ብትወጪ ብትፈርጪ ከርሷ እንደማት ስተካከዪ መች አጣሺው? አሁንም ቢሆን እውነተኛዪቱ የማንደርሌይ እመቤት እርሷ እንጂ አንቺ አይደለሽም ። ሀያወት አለኝ አትበዪ ። በድንሽ ነው ያለው ። ተንቀሽ ፣ ተረስተሽ እንደ ጥላ እንደ መንፈስ ተቆጥረሽ ነው ያለሽው ። ምነው ታዲያ ከዚህ ሁሉ ውርደት ማንደር ሌይን ለርሷ ለቀሽላት ብትሄጂ?" አሉኝ ።

ፈራኋቸው ። ስሸሻቸው እየተከተሉ ክንዴን ጥርቅም አድርገው ያዙት ። "ማንም ሳይፈልግሽ መቀመጡ የምን ሙዝዝ ማለት ነው? እርሱም አይፈልግሽም ። አይፈልግሽም ። ከእርሷ ጋር ነው መኖር የሚፈልገውና ምነው ቤቱን ለቀሽላቸው ብትሄጂ ። እርሷ ሳትሆን አንቺ ነበርሽ መሞት የሚገባሽ ። በዚያ በርሷ ከቡር ገላ ምትክ ያንቺን ሬሳ ነበር እዚያ ቤተ ክርስቲያን ወስዶ መወርወር" እያሉ እየገፈታተሩ ወደ መስኩቱ ወሰዱኝ ። "እስቲ ቁልቁል ተመልከቺ ። ይልቅ አሁን በደንብ

t.me/OLDBOOKSPDF

አዳምፊኢ ። ለዘላለም የሚረባሽ ምክር ልስጥሽ ። ከዚህ ዘለሽ ለምን አትገላገዪም ? አይዞሽ… ዝለዪ ፡ አይጐዳሽም… የዘላለም እረፍት ነው ። በይ እንጂ ሞክሪው ። ባህር ውስጥ መስጠምን ያህል የሚጐዳ አይደለም…”

መስኮቱ ክፍት ነበር ። ጉሙ ድንገት መጥቶ አካባቢውን አለበሰው። አይኔን ጋረደው ። አፍንጫዬን ሰርስሮት ገባ ። የመስኮቱን ጠርዝ እንደያዝኩ ፈዘዝ ቀረሁ ።

“አትፍሪ እንጂ ። ከፈለግሽ ፡ ትገፋኛለች ብለሽ ከፈራሽ ፡ እኔ ልራቅልሽ አልነካሽም ። አንችው እራስሽ ዝለዪ ። የሚስተር ደዊንተርን ድጋፍ አጥተሽ ፡ ፍቅሩን ነፍጎሽ ፡ ደስታ ርቆሽ እንዲህ የስቃይ ኑሮ ከምትኖሪ መገላገሉ አይሻልም ?” የሚለው የሚስዝ ዳንቨርስ ዲያቢሎሳዊ ማደናፈሪያ እንደ ሀልም ይሰማኝ ነበር ። አይኔን ቁልቁል እንደተከልኩት ሰገነቱ ላይ የነበሩት አበቦች ከነማስቀመጫቸው ይታዩኝ ነበር። ድንጋይ ንጥፉ የሰገነቱ ወለል አባጣ ጎርባጣ የሌለበት ለስላሳ ምንጣፍ መስሎ ታየኝ ። ጉሙ ሩቅ ያስመስለው እንጂ ወለሉ ያን ያህል የራቀ አልነበረም ።

“ምነው የማትዘዪው? በይ ሞክሪው እንጂ” ይሉኛል አሮጊቷ

ጉሙ እየከበደ መጣና እይታዬን ሁሉ አጨለመው ። ሁሉ ነገር ደበዘዘብኝ ። ልዩ አለም ውስጥ የገባሁ መሰለኝ ። የመስኮቱን ጠርዝ የተደገፍኩባቸው እጆቼና ሚስዝ ዳንቨርስ አጥብቀው የያዙት የግራ ክንዴ ብቻ ነበሩ በእውኑ አለም ውስጥ መኖሬን የሚያዘክሩኝ ። አሮጊቷ እንዳሉኝ ብዘል ሀይለኛ ሀመም ቢሰማኝም ወዲያው ጭጭ እንደምል ተሰማኝ ። ግን ስወድቅ ከታች የሚቀበሉኝ ድንጋዮች አይታዩኝም ። ጭጋጉ ይጋርዳቸዋልና ። እንዴት…?

“በይ አትፍሪ” ይሉኛል ሚስዝ ዳንቨርስ ከጆሮዬ ተጠግተው ።

አይኖቼን ከደንኳቸው ። አጥወለወለኝ ። እጆቼ ዝለዋል ። አፍንጫዬን ሰርስሮ የሚገባው ጉም ያደነዝዘኝ ገባ ። ከእንግዲህ ስለ ደስታ ፡ ስለማክሲም ፍትር ማሰቡ ይብቃኝ አልኩኝ ። ርብቃንም ልርሳት አልኩ ። ሁሉንም ነገር ልረሳው አይደለም? በቃ…በቃ…

እጆቼን ቀስ በቀስ አላቀቅኳቸውና በረጅሙ ተነፈስኩ ። መንቀሳ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀስ ልጀምር ስል ዙሪያ ገባውን ያናወጠ ፍንዳታ ተሰማ ። ጉሙ ተናጋ ። ፀጥታው ደፈረሰ ። አይኖቼን ገለጥኳቸው—የግድ ። ሚስዝ ዳንቨርስ ላይ አፈጠጥኩባቸው ። ሌላ ፍንዳታ— ሌላም— ሌላም ተከታተለ ። የፍንዳታው ድምፅ ያወካቸው አእዋፍ ከየመሸጉበት እየወጡ ቱር ቱር ይሉ ጀመር ። የአከናፋቸው ርግብግቢት እየሩን እየሰነጠቀ አስተጋባ ።

“ምንድነው? ምንድነው ነገሩ?” አልኩ

ሚስዝ ዳንቨርስ ለቀቁኝ ። አካባቢውን ቃኘት ቃኘት አደረጉና “ሮኬት እየተተኮሰ ነው ። ችግር የገጠመው መርከብ መኖሩን የሚያመለክት ተኩስ ነው ።” አሉ ።

አይናችንን ተከለን ማዳመጥ ያዝን ። ወዲያው ግም ግም የሚል ድምፅ ሰማን—ሰገነቱ ላይ ይንቀሳቀስ የነበረ የሰው ኮቴ....

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አስራ ስምንት

የማክሲምን ድምፅ ሰማሁ ። ፍሪዝን ጠርቶ "መርከቧ እደጋ ላይ ሳትወድቅ አልቀረችም ። ከዚያ አካባቢ ነው የመጣሁት ። እስቲ ሰዎቹ ምናምን ይፈልጉ እንደሆነ ምግብና መጠጥ እንዲዘጋጅላቸው አድርግ ። ለሚስተር ክሮውሌይ ደግሞ ደውልና ንገረው ፡ እኔ ወደዚያው ተመልሼ መሄዴ ነው" አላቸው ። እኔና ሚስዝ ዳንቨርስ ከነበርንበት ቁልቁል ስንመለከት ማክሲምና ፍሪዝ በጭጋጉ ተሸፍነው ሲራመዱ አየናቸው ።

ሚስዝ ዳንቨርስ ካቀረቀሩበት ቀና አሉና "ይበሉ እንሂድ ። ምግቡን እንዳዘጋጅለት ፍሪዝ ይፈልገኝ ይሆናልና ልሂድለት ። መስኮቱን ልዘጋው ነውና ጣትዎን እንዳልቀረጥፍዎ" አሉኝ ። የስድቡ ቅጣት ተነሳልኝ መሰለኝ ወደ ከበሬታው መለሱኝ ።

የማየው ፡ የምሰማው ሁሉ እውነት አልመስልሽ አለኝ ። አሮጊቷ መስኮቱን እየዘጋጉ "...ደግነቱ ማእበል አለመኖሩ ነው ። ሰውም አይተርፍ ነበር ። መርከቧ እንኳን ልትንዳ ትችላለች" አሉኝና ወደ በሩ አምርተው እያስቀደሙኝ "እንግዲህ ለእርስዎም ቀዝቀዝ ያለ ምግብ እንዲዘጋጅልዎ አደርጋለሁ ። ባሻዎት ጊዜ መብላት ይችላሉ ። ሚስተር ደዊንተርም እንዲህ ተወጥረው አሁን ምላ የሚፈልጉ አይመስለኝም" ሲሉኝ ምን እንደምመልስላቸው ግራ ገብቶኝ ዝም ብዬ አትኩሬ አያቸው ነበር ።

"እንግዲህ እመቤቱ ፡ ሚስተር ደዊንተርን ካገኟቸው የመርከቡን እንግዶች ይዘው ቢመጡ ምግብ እንደሚዘጋጅ እንዲነግሯቸው" ባሉኝ

t.me/OLDBOOKSPDF

"እሺ ሚስዝ ዳንቨርስ ፡ እነግረዋለሁ" አልኳቸው በተለዋዋጩ ባህርያቸው እየተደነቅኩ ።

ቀሚሳቸው ወለሉን እየጠረገ ድክ ድክ እያሉ ሄዱ ። ከዓይኔ እስኪሰወሩ ድረስ በግርምታ አይቻቸው ተከትያቸው ሄድኩ ። ከምግቡ አዳራሽ ፍሪዝን አገኘኋቸው ። ማክሲም መጥቶ እንደነበረና አንዲት መርከብ እደጋ እንደገጠማት ነገሩኝ — ያልሰማሁ ቢመስላቸው ። ማክሲምን ማግኘት ከፈለግኩ ብዙ ሳይርቅ ልደርስበት እንደምችል ሲነግሩኝ አመስግኜ ተለየኋቸው ።

ወደ ሰገነቱ ሄድኩ ። ጉሙ እንደ ጢስ እየተጥመለመለ ፡ እየሳሳ ፡ እየሳሳ ሲሄድ አካባቢው ገለጥለጥ ይል ጀመር ። ከአምስት ደቂቃ በፊት የነበርኩበትን መስኮት አንጋጥጬ ስመለከተው እጅግ በጣም ርቆ ታየኝ ። ከእግሬ ሥር የተንጣለለው የሰገነቱ ወለል ከመጠን በላይ ጠጣርና ጠንካራ ሆኖ ተሰማኝ ። ዓይኔን ከወለሉ ወደ መስኮቱ ፡ ከመስኮቱ ወደ ወለሉ ሳንከራትተው አንዳች ልዩ ስሜት ወረረኝ ። ከማጅራቱ የተነሳው ላብ ሀብለ–ሰረሰሬን ይዞ ቁልቁል ወረደ ። ጥቂቱር ነቁጦች ዓይኔ ሥር ዳንኪራ ይረግጣሉ ። ግድግዳውን እየታከክኩ እንደምንም ከአዳራሹ ገብቼ ወንበሩ ላይ ዘፍ አልኩበት ።

ፍሪዝን ጠራሁና "አይታዘቡኝና በአንዲት ትንሽ ብርጭቆ ብራንዲ ያምጡልኝ" አልኳቸው ።

"እንዴት ነው? ደህናም አይደሉ እንዴ እመቤቱ? ክላራስን ልጥራ ልዎ?" አሉኝ ፍሪዝ ብራንዲውን እያቀረቡልኝ ። ጉንጨት አደረግኩለትና አጣጣምኩት — ጭልጥ አደረግኩትም ። ጥቂት ወበቅ ስላስቸገረኝ እንጂ ደህና መሆኔን ነገርኳቸው ። ጥቂት አረፍ እንድል ሲጠይቁኝ "ግድ የለም አይጨነቁ ፡ ትንሽ ቆይቼ ወጣ ማለቱ አይቀርም" አልኳቸው ።

ፍሪዝ ትተውኝ ሲወጡ እዚያው እንደተቀመጥኩ ቆየሁ ። በረድ ሲልልኝ ተነስቼ ወጣሁ ። ወደ ባህሩ ለመሄድ ፈልጌ ጃስፐርን ብጠራ ሳያመጣልኝ ቢቀር ማክሲምን ተከትሎ ቢሄድ ነው ብዬ መንገዴን ብቻዬን ተያያዝኩት ።

ወደ ባህሩ እንደተጠጋሁ አደጋ የደረሰባትን መርከብ ከርቀት

t.me/OLDBOOKSPDF

አየኋት ። ለእርዳታ በደረሱ በርካታ ጀልባዎች ተከባለች ። ዳር ዳሩን ስሽሎኮለክ ቆይቼ ወደ አንድ ጉብታ ከፍ ብዬ ዙሪያውን ብቃኝ በባሀሩ ዳር ከተሰበሰበው ሕዝብ መሀል ማክሲምን ላየው አልቻልኩም ። ፍራንክን ሳየው ግን ሀፍረት ተሰማኝ ። ከአንድ ሰዓት በፊት በቴሌፎን እንዲያ መንፈቅፈቱ ነበር ያሳፈረኝ ። ልሸሸው ስሞክር ቀደመኝና እጁን አውለበለበልኝ ። ከመሄድ ሌላ አማራጭ አልነበረኝም ።

ከፍራንክ ጋር ቆሞ የነበረው የወደብ ጠባቂ የሚዳ መነጽሩን ሰጥቶኝ ዘንበል ብላ የቆመችውን መርከብና በዙሪያዋ የሚካሄደውን ውርውርታ በደንብ ተመለከትኩ ። በነበረው ከባድ ጉም ሳቢያ መርከበኛው አቅጣጫውን በሚገባ ለመለየት ባለመቻሉ መርከቧ በቋጥኞቹ መካከል መሻቢን ሰውዬው ነገረኝ ። ስሯ ተነድሎ ውሀ ማስገባት ጀምራ እንደሆነ ለመመርመር ባህር –ጠለቅ ዋናተኛ ለመላክ በዝግጅት ላይ እንደሆኑም አስረዳኝ ።

“ሮኪቱ ሲተኮስ ከሸለቆው በታች ካለው የመጀመሪያ ባህረ – ሰላጤ አካባቢ ነበርኩ ። የጉሙ ብዛት ከሦስት ሜትር ርቀት የነበረውን ነገር በቅጡ ለመለየት የሚያስችል አልነበረም” አለ ፍራንክ ።

የጋራ የሆነ ነገር ሲገጥማቸው ሰዎች ሁሉ የጋራ ባህሪይ መያዛቸው በጣም ገረመኝ ። ፍራንክ ልክ እንደ ፍሪዝ ስለተፈጠረው ነገር በዝርዝር ይነግረኝ ጀመር ። ወደ ባህሩ ዳር የሄደው ማክሲምን ፍለጋ እንደነበረ ፡ እንደኔው ሁሉ እርሱም በጣም ተደናግጦ እንደነበረ እያወቅኩ አሁን መድረኩን ለሌላ ሀሳብ መዳረጋችን እስደነቀኝ ። በቴሌፎን ያደረግነው ጭውውት ፡ ያ ሁሉ ሚንቀታችን ፡ አሁኑኑ ካልተገናኘን እያለ ፍራንክ ይወተውት የነበረው ሁሉ ተዘንግቶ መላው ትኩረታችን ጉም ወዳሰናከላት መርከብ መሳቡ ገረመኝ ።

የወደቡ ጠባቂ ካንድ ልጅ ጋር ሲዳረቅ እኔ ማክሲም ወዴት እንደደረሰ ፍራንክን ጠየቅኩት ። እንድ የተጎዳ የመርከቡን ሠራተኛ ለማሳከም ወደ ኬሪዝ በጀልባ መሄዱን ነገረኝ “አሁን እኮ ነው ከመምጣትሽ አምስት ደቂቃም አይሆን ከሄደ ።” አለ ፍራንክ ። “...ማክሲም እኮ በእንዲህ ዓይነቱ ጊዜ የተቻለውን እርዳታ ከመለገስ ወደኋላ አይልም ። አሁን ታያለሽ ፡ የመርከቡን ሰዎች ሁሉ አብልቶ አጠጥቶ

t.me/OLDBOOKSPDF

አሳድሮ ነው የሚሸኛቸው ።”

“ልክ ነው ። ለወገናቸው ተቆርቋሪ ከርሳቸው በላይ ማን አለና? የለበሱትን አውልቀው ይሰጡ የለም እንዴ? በዚህ በቀያቸው የእርሳቸው ዓይነት አንድ ሁለት በተፈጠረ የሚያሰኝ ነው ።” አለ የወደብ ጠባቂው ።

ከዚያም ፍራንክና ሰውዬው ለመርከቧ ስለሚደረገው የእርዳታ ዓይነት ሲጨዋወቱ የማዳምጣቸው ብመስልም ሀሳቤ ከእነርሱ ጋር አልነበረም ። ጥቂት ቆይቶ ፍራንክ “ከእንግዲህ የኛ እዚህ መቆየት ምንም ፋይዳ የለውም ። ምንም የምናደርግላቸው ነገር የለም ። ረሀቡም እየቆነጠጠኝ ነው” ሲል ብሰማም መልስ አልሰጠሁትም ።

“አንቺ ከእንግዲህ ምን ታደርጊያለሽ?” ብሎ ጠየቀኝ ።

“ትንሽ እዚሁ እሆናለሁ ። ስላልራበኝ ምሳዬን ቀስ ብዬ እበላ ለሁ ። እስቲ ያ ባህር–ጠለቅ ዋናተኛው የሚያደርገውን ልየው” አልኩት ።

“ምንም የሚታይ ነገር እኮ የለም ። ይልቅ አብረን ሂደን ምሳ ብንበላ ይሻላል ።

“አይ ፡ ግድ የለም…እኔ አሁን አልበላም”

“እንግዲያው እምቢ ካልሽ ምን ይደረጋል? ከፈለግሽኝ ከሰዓት በኋላ በሙሉ ቢሮዬ ውስጥ ነው የምሆነው”

“እሺ አመሰግናለሁ” አልኩትና ተሰናብቶኝ ሄደ ። አስቀይሜው ይሆን የሚል ሀሳብ ቢያድርብኝም ምንም ላደርግ እንደማልችል ታወቀኝ። ወቅቱን ጠብቆ አንድ ቀን ሁሉንም ነገር በዝርዝር አስረዳው ይሆናል ብዬ ተዕናናሁ ።

“ሚስተር ከሮውሌይ እኮ ግሩም ሰው ነው ። መቼም ለሚስተር ደዊንተር ደግሞ ቀኝ እጃቸው ነው ።” አለኝ የወደብ ጠባቂው ።

“እምን ፡ በጣም ትልቅ ሰው ነው” አልኩት ።

ከዚያው ሳልንቀሳቀስ በእካባቢው የሚደረገውን ትርምስ ሳስተውል ቆየሁ ። ለወሬ የሚሰባሰበው ሰው እላይ በላይ እየተደራረበ የባህሩን ዳርቻ አጣበበው ። ዋናተኛው አንድ ሁለቴ ብቅ ጥልቅ ሲል ባየውም አንድም ለየት ያለ እንቅስቃሴ ባለመጀመሩ ስልችት አለኝ ። ለመሄድ አስቤ የእጅ ሰዓቴን ሳየው ዘጠኝ ማለፉን ነገረኝ ። ከመጣሁ ከሁለት ሰዓት

t.me/OLDBOOKSPDF

በላይ እንደሆን አልታወቀኝም ነበር ።

በኮረብታው አቆልቁዬ ወደ ባሀረ ሠላጤው ሰጠጋ እንደወትሮው ሁሉ አካባቢው ረጭ ብሏል ። አመልማሎ ደመና ሰማዩን ዳር እስከዳር አልብሶታል—ፀሐይንም ጋርዶ ። ጥቂት እንደተራመድኩ ቤንን አየሁት። በሁለት ቋጥኞች መካከል ካለች ትንሽ ኩሬ አጠገብ አጉንብሷል ። ቀንድ አውጣዎችን ይጠራርጋል ። ደመናው ግርዶሹን ያነሳላት ፀሐይ ብርሃኗን ረጭታብኝ ኖሮ ውሀው ላይ ያረፈውን ጥላዬን አየና ቤን ዞር አለ። በስሱ ፈገግ ብሎ "ጤና ይስጥልኝ ፥ ደህና ዋልሽ?" አለኝ ።

"እንደምን ዋልክ ቤን ?" አልኩት ።

እየተንገዳገደ ተነሳና በእንድ አዳፋ መሀረብ የሰበሰባቸውን ቀንድ አውጣዎች እያሳየኝ "ቀንድ አውጣ ትበያለሽ ?" ሲል ጠየቀኝ ።

ስሜቱን ላለመንካት ብዬ "እሺ ፥ እመሰግናለሁ" አልኩት ።

አስር ያህል ቀንድ አውጣዎችን እጁ ላይ ሲያኖርልኝ በቀሚሴ ኪሶች አስገባኋቸው ። "በዳቦና በቅቤ ስበላው በጣም ነው የሚጣፍጠው። ሁሉንም ...እ... እንድትበያቸው ። ለ... ሴላ ... ሰው እንዳያይብሽ... ደግሞ በደንብ ...እ...እ... ቀቅዪው" አለኝ ።

"እሺ"

ፈገግ እንዳለ እያስተዋለኝ "መርኳቧን አየሻት አይደል?" አለኝ

"አዎን ፥ ተሰናክላ እኮ ነው" ስለው

"ምን?" ሲል በጥርጣሬ መልክ አየኝ ።

"ተበላሽታ ነው ፥ ስሯ ሳይበላ አይቀርም ።"

ፊቱን ድንገት ቅሙም አደረገና "እንዴ...በቃ... እዚያው ተቀርቅራ ቀረች እኮ" አለ ።

"አይ ምንም አትሆንም ፥ ውሀው ሲሸሽ ጐትተው ያወጧት ይሆናል።" ስለው መልስ ሳይሰጠኝ ቀረ ። ዓይኑን በዓይኔ ስከተል ከተበላሸችው መርከብ ላይ አረፍኩ ። አውንም በርካታ ሰዎች ዙሪያዋን ከበው የማዳን ዘመቻውን አጧጡፈውታል ።

ቤን እየፈገገና አፍንጫውን በእይበሉባው እየጠራረገ አንዳንድ ጥያቄዎችን ጣል ማድረግ ጀመረ ። ቀጠለ አደረገናም "ያው ትንሽ እየተበጣጠሰች ነው የምትልቀው ፥ እንደ ድንጋይ እኮ ጭው ብላ

t.me/OLDBOOKSPDF

እትሰጥምም” አለና ብቻውን ተፍነከነከ ። ዝም ብዬ አየሁት “እስካሁን አሶቹ ብልት አድርገው ጨርሰዋታል አይደል?” በማለት ጠየቀኝ ።

“ስለ ማን ነው የምታወራው ?” ስለው በአውራ ጣቱ ወደ ባህሩ እያመለከተ “እርሷን ነዋ ፡ ያቺኛዪቱን” አለ ።

“አሶች እኮ መርከብ አይበሉም” አልኩት ።

“እህ ?” አለና በዚያ ጅላጅል ዓይኑ ትኩር ብሎ አየኝ ።

“በል እንግዲህ ደህና ዋል ፡ መሄዴ ነው ።” ብዬው ወደ ቤት ተመለስኩ ። ምግብ ቤት ውስጥ ስገባ ምሳዬ ተዘጋጅቶ ተቀምጦልኝ ነበር። የማክሲም ሥፍራ ባዶ መሆኑን ሳይ ሮበርትን ጠርቼ

“ሚስተር ዩዊንተር መጥቶ ነበር እንዴ ?” ስል ጠየቅኩት ።

“አምን እመቤቴ ፡ ስምንት ሰዓት ግድም ብት ብለው ምሳቸውን በችኮላ ቀማመሱና ተመልሰው ወጡ ። እርስዎንም ሲጠይቁ ፍሪዝ መርከቡን ለማየት ወደ ባህሩ ሳይወርዱ አይቀሩም ብለው ነገሯቸው” አለኝ ሮበርት ።

“በዚህ ሰዓት እመለሳለሁ ብሏል እንዴ ?”

“አይ ፡ ምንም አልተናገሩም እመቤቴ”

“ምናልባት ወደ ባህሩ ይሆናል የሄደው ። በተለያየ አትጣጫ ሆነን ሳንተያይ ቀርተናል ማለት ነው ።”

“ቢሆን ነዋ እሜቴ”

የተዘጋጀልኝን ምግብ በዓይኔ ታኝት አደረግኩት ። የምግብ ፍላጐቴ በመዘጋቱ ነው መሰለኝ ምግቡ ከነመልኩ በላም አስጠላኝ ። ዳዩ በቅቤ ከሻይ ጋር ወደ ቤተ—መዛሕፍቱ እንዲያመጣልኝ ለሮበርት ነግሬው ወደዚያው አመራሁ ።

ከመስኮቱ አጠገብ ከነበረው ወንበር ላይ አረፍ አልኩ ። ጀስፐርን እስካሁን አለማየቱ ቅር ቅር አለኝ ። አሮጊቲ ውሻ ግን ቅርጫቲ ውስጥ እንቅልፏን ትለጥጠዋለች ። ጋዜጣ ብድግ አደረግኩና አገላብጠው ጀመር። እንዲያው የልምድ ነገር ሆነና እንጂ እንዴት መስመር ማንበብ እንደማልችል አውቀው ነበር ። የጠዋቱ ረብሻና የመርከቧ ብልሽት ምሳ ካለመብላቱ ጋር ተዳምረው ልዩ ስሜት አጫሩብኝ ። ያለፈውን ሁሉ የሚሽር አዲስ የሕይወት ምእራፍ የጀመርኩ መሰሎ ተሰማኝ ። ትናንት

t.me/OLDBOOKSPDF

ማታ ያንን ቀሚስ የለበስኩት እኔ ሳልሆን ሌላ ሴት እንደሆነች ፡ ድርጊቱም እጅግ ራቅ ባለ ጊዜ የተፈፀመ እድርጌ ቆጠርኩት ። እራሴን እንደ አዲስ ፍጡር ፡ ፍፁም ከወትሮው የተለየሁ አስመሰልኩት ።

ሮበርት ፡ እንድም ጸቦ በቅቤ ብቻ ማቅረቡ አሳፍሮት ፡ አሊያም ቤቱ ያልለመደበትን 'እንዴት ብዬ?' ነው መሰለኝ ከሻይው ጋር ጥቂት ኬክና ሳንድዊች ይዞልኝ መጣ ። ቁርሱን እንከት ፡ ሻይውን ግጥም አደረግኩት ።

ሮበርት ተመልሶ መጣና "እሜቴ ፡ ጌቶች ገብተዋል እንዴ ?" አለኝ

"አይ አልገባም ። ምነው ? ማን ነው የፈለገው ?"

"የኬሪዝ ወይብ ሀላፊ ካኖቴን ሲርል ቴሌፎን ደውለው ሚስተር ደዊንተርን በማንባር ላነጋግራቸው እፈልጋለሁ ይላሉ ። አለመኖራቸውን ስነግራቸው እርስዎን ለማነጋገር ይፈልጋሉ" አለኝ ።

መጥተው እንዲያነጋግሩኝ ተስማማሁ ። ለአስቸኳይ ጉዳይ ነው ስላሉ ነው እንጂ ምን ቢሉ ምን እንደምመልስ ገብቶኝ እንኳን አልነበረም። ሀሳቤን ሳላበቃ ነበር ካኖቴን ሲርል የገቡት... ስለ ተበላሸችው መርከብ ይነግሩኝ ጀመር...

"...መርከቧን እንዲመረምር አንድ ጠላቂ ልከን ነበር ። ስሯ እንደተበሳ ነረጋገጠ በኋላ ሌላ ብልሽት ይኖር እንደሆነ ለማየት በዙሪያዋ ሲሽከረከር አንድ አስገራሚ ነገር ነው የገጠመው ። እንዲት በጐኗ የተጭች ትንሽ ጀልባ ያገኛል ። የአካባቢው ነዋሪ በመሆኑ ጀልባዋን ለይቶ ያውቃታል ። ምን መሰልዎት ... እህ ... አፈሩን ገለባ ያድርግላትና የሚችቷት የሚስዝ ደዊንተር ጀልባ ነበረች ።" አሉ ካኖቴን እያቅማሙ ። ጀልባዋን ለማንሳትም ጥረት እንደሚያረግ አስረዱኝ ።

ይህ ወሬ ሲወራ ማክሲም አለመኖሩ በጣም ደስ ሲለኝ ከትናንት ምሽቱ ድርጊት ማግስት ሁኔታው መከሰቱ ደግሞ የገረመኝን ያህል አስደነገጠኝ ።

"ምን ዓይነት ጉድ ነው ጆሮዬ የሚያሰማኝ ፣ ማክሲም ነገሩን መስማት አለበት ያላሉ ? ማለቱ ጀልባዋ እዚያው እንዳለች ብትኖር ምን የሚያመጣው ችግር ይኖራል ?" ስል ካኖቴኑን ጠየቅኳቸው ።

"በመሠረቱ እንደኔ ፍላጐት ቢሆን ጀልባዋን እንዳለች መተዉን እመርጥ ነበር ። የሚስተር ደዊንተርን ስሜት የሚረብሽ ማንኛውም ነገር እንዲደረግ እንደማልሻ ቀደም ሲል የነገርኩዎት ይመስለኛል ። ችግሩ

t.me/OLDBOOKSPDF

መቼ ይህ ሆነና ። ያኸው ዋና፡ኛ ጀልባዋን በደንብ ሲመረምር እንዳችም ጉዳት ሳያደርስባት ሁሪያሞ በሙሉ ጥርትም ብሎ እንደተዘጋ ያገኛታል ። ከባህሩ ወለል ድንጋይ አንስቶ አንዱን መስኮት ሰብሮ ሲመለከት ውስጧ በውሀ ተሞልቷል ። ከሥር ተሸንቱራ ይሆናል በማለት ሲያሰላስል ድንገት አንድ ነገር ያይና መላ አካሉን ያንዘረዝረዋል…" አሉና ካፕቴን ሲርል ንግግራቸውን አቋርጠው ማራ ተኛቸውን ገልመጥ ገልመጥ አደረጉት — አንዱ ሠራተኛ ይሰማ እንደሁ ብለው የሰጉ ዓይነት። "ጀልባዋ ውስጥ አንድ የተጋደመ የሰው አካል ነው ያየው" አሉ ካፕቴን ድምፃቸውን ዝቅ አድርገው ። "ስጋው ያለቀ ቢሆንም በሚንቀሳቀስ ፡ በእጅና በእግሮቹ ቅርፅ የሰው አዕም መሆኑን መለየት አላዳገተውም ። ደንግጦ ከባህሩ ይወጣና ቀስ ብሎ ለኔ ይነግረኛል ። እንግዲህ ያኸውልዎት ሚስዝ ደዊንተር ፡ ባለቤትዎን ለምን ማነጋገር እንደፈለግኩ የተረዱልኝ ይመስለኛል ።"

እንደ መደንገጥ ፡ እንደ መፍራት እያለች ትክ ብዬ አየኋቸው "እስከ ዛሬ ሲነገር እንደምሰማው ጀልባዋ ላይ ብቻዋን ነበረች አልነበረም እንዴ ሲባል የነበረው ? ሌላ ሰው አብሯት ነበር ማለት ነው?" ስል ጠየቅኋቸው።

"እንደዚያ ነው የሚመስለው"

"ከሆነ ደግሞ ማን ነበር አብሯት የነበረው ? ወራው በጋዜጣ ሳይቀር ያን ያህል ተራብቶ ፡ ሰው ጠፍቶኛል የሚል አንድ ዘመድ እንኳን የሌለው ሰው ሊሆን ? ከሁሉ በላይ ግራ የሚያጋባው ደግሞ አንድ ሰው ጀልባዋ ውስጥ ሲገኝ የሚስዝ ደዊንተር ራሳ ከብዙ ወራት በኋላ ራቅ ካለ ሥፍራ መገኘቱ እኮ ነው ።"

"እኔም ከእርስዎ የተለየ ሀሳብ የለኝም ። ወራው በየሰዉ አፍ መሸከርከሩን እንዴት መግታት እንደምንችል ነው ሀሳብ የሆነብኝ ። በእርግጥ እርስዎና ባለቤትዎ ኑሯችሁን በሰላምና በደስታ ለመምራት በምትጣጣሩበት በአሁኑ ወቅት ይህ እንቅፋት መደንቀሩ ምንኛ ከባድ እንደሆነ ይሰማኛል ።"

"በተቻለ መጠን ማከሲም እንዳይሰማ ማድረግ አይቻልም ?" አልኳቸው በዓይኔ ፡ በእጅቼ ፡ በሚንቀሳቀሱ እየተማፀንኳቸው ።

"የሚቻል ቢሆን ኖሮ ምንም ወደኋላ እንደማልል ንገርክምት እኮ ሚስዝ ደዊንተር ። የእኔንም ሁኔታ ለረዱልኝ ይገባል ። ስለ ተገኘው

t.me/OLDBOOKSPDF

አካል ለሚመለከተው ክፍል ማስታወቅ የሙያ ግዴታዬ ነውና ምንም ማድረግ አልችልም ።" እንዳሉ በሩ ተንኳኳ ። ተከፈተ ። አንድ ሰው ብቅ አለ ።

"ጤና ይስጥልኝ ፡ ካፕቴን እዚህ መኖርህን አላወቅኩም ነበር ። ምነው ? ችግር አለ እንዴ?" አለ ማክሲም ።

የፈራሁት አልተረፈኝም ። እውነታን መጋፈጥ አልሆን ያለው ሰብእናዬ በደመ ነፍስ ጉትቶ አስወጣኝ ። የማክሲምን ዓይን ቀና ብሎ ማየቱ አልሆን ብሎኝ ሽልክ ብዬ ወጣሁ ። ወደ አዳራሹ ነበር የሄድኩት ። ጀስፐር ገበቱው ላይ አቀርቅሮ ሲጠጣ አየሁት ። ቀና ብሎ አየኝና ሜራውን ግራ ቀኝ ካማታ በኋላ ወደ ሥራው ተመለሰ ። ሲበታው ነው መሰለኝ እየቦጠ መጥቶ በሁለት እግሮቹ ቆሞ ተሚሲ ላይ ተንጠለጠለ ። ሜንትላቱን ሳምኩትና ወደ ሰገነቱ ወጥቼ ቁጭ አልኩ ። ይህን ከፊቱ የተጋረጠውን ተውጠ ሁኔታ መጋፈጥ እንደሚገባኝ ተሰማኝ ። የእስከ ዛፈውን ፍርሃት ፡ በራስ ያለመተማመንና ፡ የበታችነት ስሜት አሽቀንጥሬ መጣልና ፡ ድል መንሳት አለብኝ አልኩ ። ከአሁን የተሻለ እድል ከቶውንም አላገኝምና መሸነፍ የለብኝም ። ዛሬ የሽንፈት ዕዋ ተመስኩ ማለት ዝንተዓለም ከሽንፈት ማጥ አልወጣም ማለት ነው ብዬ ላለመረታት ቁርጠኛ ሀሳብ አደረብኝ ። ድፍረቱን እንዲሰጠኝ ፡ ጥረቴን እንዲያሳካልኝ አምላኬን ዓይኔን ጨፍኜ ለመንኩት ። በዚሁ መልክ ለአምስት ደቂቃ ያህል ስብሰለሰል ከቆየሁ በኋላ የመኪና ድምፅ ሰማሁ ። ካፕቴን ሲርል ማክሲምን አርድተው መሄዳቸው እንደሆነ ገባኝ ።

ወደ ቤተ መፃሕፍቱ ስሄድ ማክሲም ፊቴን ለመስኮቱ ፡ ጀርባውን ለእኔ ሰጥቶ ቆሟል ። እጄን ከኪሴ ከትቼ ቤን የሰጠኝን ቀንድ አውጣዎች አፍተለትላቸው ጀመር ። ማክሲም ጀርባውን እንደሰጠኝ ነበር ። ቀስ ብዬ ተጠጋሁት ። እጄን በእጄ አንስቼ ከጉንጩ ላይ አዋልኩት ።

"አዝናለሁ ማክሲምዬ ። በጣም ፡ በጣም ነው የማዝነው" አልኩት በለሆሳስ ። ልውስ ትንፍሽ የለም ። እንደ በረዶ የቀዘቀዘ እጁን ሳምኩት ጣቶቹንም እንዲሁ አንድ በአንድ በከናፍሬ ዳሰስኳቸው ። "ስማኝ እንጂ ማክሲምዬ ፡ ከእንግዲህ የኔ ልጅነት አከትሟል ። በሀያ አራት ሰዓት ውስጥ በሳል ሰው ሆኜልሃለሁ ። ይህንን ዱብ እዳ ብቻህን አትሸከመው

t.me/OLDBOOKSPDF

ምና በማንኛውም መልኩ ልጋራሀ ዝግጁ ነኝ" አልኩት ።

ምንም ሳይመልስልኝ ሳብ አድርጐ ከደረቱ ለጠፈኝ ። ፍርሀቱ ሲለቀኝ ፡ ዓይን አፋርነቱ ሲነሳልኝ ተሰማኝ ። "በቃ ፡ ይቅርታ አደረግክልኝ አይደል ? አይደል ጌትዬ ?" ስለው

"ይቅርታ አደረክልኝ ? ለምኑ ነው ይቅርታው ?" አለኝ

"ስለ ትናንትናው ማታ ነገር ነዋ — ሆን ብዬ ያደረግኩት ስለመሰለህ"

"እሱን ነው እንዴ የምታወራው ? እኔ ረስቼዋለሁ አላክሽ ። ግን ማታ በጣም ነው የተቆጣሁሽ አይደል ?"

"በጣም እንጂ"

ደረቱ ላይ እንደለጠፈኝ ዝም ብሎ ሲቀር "ማክሲምዬ ፡ ከእንግዲህ ሁሉንም ነገር ሀ—ብለን እንጀምረውም ? የመጣውን ሁሉ ክፉም ሆነ ደግ—አብረን እንወጣውም ? ፍቅርህን ስጠኝ እያልኩ ፡ የማይሆን ነገር እየጠየቅኩ አላስቸግርህም ። እንደ ወንድ ንደኛህ ፡ እንደ ወዳጅህ ብትቆጥረኝ ለኔ በቂዬ ነው ። ሌላ ምንም አልፈልግም ።" አልኩት ።

ፊቴን በመዳፎቹ መሀከል ይዞ ትክ ብሎ ካየኝ በኋላ "እስቲ ምን ያህል ነው የምትወጂኝ ?" በማለት ጠየቀኝ ። እንዴያ መክሳቱን ፡ መገርጣቱንና ቆዳው መሸብሸቡን ሳይ በጣም አዘንኩለት ። የምመልሰው ጠፍቶኝ ዓይን ዓይኑን ሳየው "አየሽ ፍቅርዬ ፡ እድል ፊቷን ካዞረችብን በኋላ ምን ዋጋ አለው ብለሽ ? ከእንግዲህ እኔና አንቺ ለሀዘን እንጂ ለደስታ አልታደልንም" አለኝ ።

"ተው እንጂ ማክሲም ፡ ልክ አይደለህም"

"ምን ልክ አይደለህም ትይኛለሽ ? ነገሩ ሆኖ እያየሁት?"

"የምኑ ነገር?"

"ዘወትር ያሳስበኝ የነበረው ነገር ነዋ ። የሀሊና እረፍት ነስቶ ነጋ ጠባ ስሜቴን ሲቆጠቁጠው የነበረ ነገር ነዋ ። ተይው እላክሽ ፡ እኔው እንደሆንኩት ላልሆን አንቺን ከማታውቂው ስታይ ውስጥ አስገብቼ የልጅነት አበባሽን ማቅ ማልበስ ፡ አፍላ የደስታ ጊዜሽን በሀዘን መለወጤ ብቻ ነው የሚቆጨኝ ።" አለና ትቶኝ መስኮቱ ጠርዝ ላይ አረፍ አለ ።

እጆቼን ትከሻው ላይ አሳርፌ ፡ እፊት ለፊቱ ተንበርክኬ "ምንድ ነው የምታወራው ማክሲምዬ ?" ስል ጠየቅኩት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እጅቼን በእጅቹ እየዳበሰ ፡ ዓይኖቼን በዓይኖቹ እያሰሰ "ርብቃ ድል አደረገች ነው የምልሽ" አለኝ ።

የልቤ ምት ፍጥነቱን ጨመረ ፡ እጅቼን ድንገተኛ ቅዝቃዜ መረራቸው።

"እኔና አንቺ" በማለት ቀጠለ ማክሲም "እኔና አንቺ ልብ ለልብ እንዳንገናኝ ዘወትር ጥላዋ እየጋረደን ፡ መሀላችን እየተጋረጠ ፡ ሲያውከን ነው የኖረ ። አንድ ቀን ያህ ሊሆን እንደሚችል በመጠራጠር ልቤ በስጋት እየተራገበ አውን እንደያዝኩሽ እንኳን ልያዝሽ አልችልም ነበር ። እንደምን ብዬ የኔ ፍቅር ? ጣር ላይ እያለች እኔ ላይ ስታንከባልለው የነበረ ዓይኗን እያየው ? ያ መሰረ ፈገግታዋ በዓይኔ ሥር ውል እያለብኝ ? እንዴት ብዬ የኔ ገላ ? ያኔም ልትሞት እያጣጣረች ሳለ ያህ ሊሆን እንደሚችል ፡ አንድ ቀን እንደምትረታ በታወቃት ነው እንጂ..."

"አረ በፈጠረህ ማክሲምዬ ? ምንድነው የምትለኝ ? እኔ ሟራሽ እንቆቅልሽ ነው የሆነብኝ ።"

"ጆልባዋን እነ አገኟት"

"ሰምቻለሁ ፡ ካፕቴን ሲርል ነግረውኛል ። ውስጡ የተገኘው አፅም ነው ያሳሰበህ አያድል ?"

"ነው እንጂ ፡ ሌላማ ..."

"እነ ፡ ያስፈልጎትህ ከርብቃ ጋር የነበረው ሰው ማን እንደሆነ ማወቁ አያድል ?

"ተዪኝ እባክሽ ፡ አንቺ ምንም አልገባሽም ።"

"እባክህን የኔ ወለላ ንገረኝና ልወቀዋ ። ሀሳብህን ፡ ሟንቀትህን ልካፈል እያልኩ ?"

"ርብቃ ከማንም ጋር አልነበረችም ፡ ብቻዋን ነበረች" ዐጥ ብዬ አፍ አፉን ፡ ዓይን ዓይኑን እየሁት ። "ጆልባዋ ውስጥ የተገኘው የርብቃ አፅም ነው ።" ሲለኝ

"እንዴት ተደረጎ ?" ስል ጮህኩ ።

"መታበሩ ውስጥ የተቀበረው የርብቃ ፊሳ አልነበረም" በማለት ቀጠለ ማክሲም ልዝብ ዝማ ብሎ "የአንዲት ማንኒት የማይታወቅ ሴትዮ ፊሳ ነበር ። እንደ እውነቱማ ከሆነ እደጋም አልተፈጠረ ፡ ርብቃም አልሰጠመችም ። እኔ ነኝ የገደልኳት —በጥይት—እዚያ ጎጆው ውስጥ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከዚያም ራሳዋን ተሸክሚ ጀልባዋ ውስጥ አኖርኩት ፡ ጀልባዋንም አሰጠምኩት— ዛሬ በተገኘችበት ሥፍራ ። ጀልባዋ ውስጥ የተገኘችው ርቢቅ ናት ። ይኸው ነው—ይኸው ነው እንግዲህ ምስጢሩ — የሟንቲ የጣሩ ምክንያት ሁሉ ። በይ እንግዲህ—አሁን ዓይኔን ትክ ብለሽ እያየሽ አፈቅርሃለሁ ትይኛለሽ? — በያ — እህ — እይኝ እንጂ የምትይውን በይኝ እንጂ ...እህ”

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ

ቤተ መዓሕፍቱ ውስጥ ወጥታ ሰፍኗል ። ጀስፐር እግሩን ያላልሳል ። እሾህ ወግዶታል መሰለኝ አንዱ በጥርሶቹ ሲፈለፍል ፡ አንዱ በምላሱ ያልሰ ዋል። የማነሲም የእጅ ሰዓት ደማሞ ። እኒህ ሁለት ድምጾች ብቻ ነበሩ የሚሰሙኝ ጀስፐር እግሩን ሲልስና የማነሲም ሰዓት ቲክ ፡ ቲክ ሲል ።

ሰንፍ ሲያላግጥ እንደመሰራት ታማኙ ፡
ጊዜ ረጅ ያላል በቱሙ ተኝቶ

የሚለው ግጥም ድንገት ከትውስታ ሰሌዳዬ ላይ ድቅን ሲል ወደ ጥንቱ የትምህርት ቤት ዘመኔ መሰደኝ ። ግጥሙ ደግሞ ደጋግሞ በጆሮዬ አቃጨለ ። "ጊዜና ማዕበል ማንንም አይጠብቁም" የሚለው አባባል ምን ያህል ትክክል መሆኑ ያኔ ነው የተከሰተልኝ ።

የሰው ልጅ ሞትን ያህል ትልቅ አደጋ ሲገጥመውና ድንገት እጁ ወይም እግሩ ሲቆረጥ ወዲያውኑ አይታወቀውም ። ለምሳሌ አንድ ሰው በድንገት አንድ እጁ ቢቆረጥ ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል መቆረጡን አይገነዘብም ። እጁ ከራሱ ጋር ያለ እየመሰለው ጣቶቹን አንድ ባንድ ለማንቃንት ይሞክራል እጅ በሌለበት ፡ ጣቶች በሌለበት ። እኔንም የገጠመኝ ይኸው ነው ። ከማነሲም ፊት ለፊት ተንበርክኬ ፡ እጆቼን ትከሻዉ ላይ ጣል አድርጌ ፡ ገላዬ ከገላው እየተነካካ ፡ ሞንቀትም ሆነ ፍርሀት በልቤ አለማደሩ ፡ ምንም ሊሰማኝ አለመቻሉ ገረመኝ ። ደረቱ ከደረቱ ተለጥፎ ሙቀቱን ቢሻማም ልቤ የልቡን አለመጋራቱ ደነቀኝ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ይባስ ብሎ ጃስፐር እግር ውስጥ የተሰካውን እሾህ እንዴት ነው የማወጣለት ? ሮበርት መጥቶ ይህንን የሻይ እቃ አያነሳምን ? የሚሉትን ሀሳቦች ማስተናገዴ ምን ይባላል ? ወቅቱ ስለ ጃስፐር እሾህ ፡ ስለ ማክሰም ሰዓት ፡ ስለ ሮበርትና የሻይ ዕቃዎች የማስብበት ጊዜ ጥሯል ? እንዲህ ስሜት አልባ በመሆኔ እራሴን ታዘብኩት ። ቀስ በቀስ ግን ነገሮች ሁሉ ተጠራቅመው እንደገና ከጭንቅላቱ ሲገቡ ሁሉንም ነገር እንደምገነዘብ ታወቀኝ ። ለጊዜው ግን ይህን ልብ አልባ ፡ አእምሮ የለሽ ፡ ስሜት —ቢስ በድኔን ለማክሰም እንዳሳቀፍኩት ፈዝዝ ቀረሁ ።

በዚህ ሁሉ መሀል ከአገሩ ቀና አድርጎ ሲስመኝ የምሠነው ጠፋኝ — ስልምልም እንዲያው ቅልጥልጥ ። እጅቹን በአንገቱ ዙሪያ ጠምጥሚ አይኖቹን ጨፈንኳቸው ። እልም አልኩኝ— ወደ ልዩ አለም ። እንዲህ አድርጎ ስሞኝም አያውቅ ። "በጣም ...በጣም እወድሻለሁ" አለኝ በለሆሳስ ።

እንዲህ ነው እንጂ ! ዘወትር የምጠብቀው ይህንኑ አልነበር ? አወጣሞ ! ከሞንቱ ካርሎ ጀምሮ አልመው የነበረ ፡ አመኘው የነበረ እኮ ነው ። ዛሬ ተንፈሰልኝ ! ቀና ብዬ አየሁት ። እንደገና ስግብግብ ብሎ ሲስመኝ እንደገና ወደ ሌላ አለም አንሳፈፈኝ ። ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር ማክሰም እንደሚወደኝ ሲነግረኝ ።

ድንገት ከናፍሩን ከከናፍሬ አላቀቀና ገፍተር አድርጎኝ ብድግ አለ ። "አየሽ ፡ ከእንግዲህ ልትወጂኝ እትችዪም ማለቱ ትክክል እንደሆነ ? ለምን በዪኛ ? ጊዜው አልፎብናል ! ተደምነው ስንል ተደመና !" አለኝ ።

ይህ አንገገሩ ወደ እውነታው አለም ሲመልሰኝ ልቤ ደረቱን ፈንቅሎ ለመውጣት ይታገል ጀመር ። "ለምኑ ነው ጊዜው የሚያልፍ ብን?" አልኩና ፈንጠር ብዬ ጠጋ አልኩት ። ከንዴን ያገ አድርጌ "እንዲህ ልትል አትችልም ። እኔ በዚህ ምድር ላይ ካላንተ ሌላ የማፈቅረው ምን አለኝና ? አውን ስትስመኝ ግን ምድር ጎለሙ ዞሮብኝ ፡ ልቤን ቢሰውረኝ ፡ የምናገረው ጠፍቶኝ እንጂ ላንተ ፍትር ሳይኖረኝ ቀርቶ ነው ብለህ ?" አልኩት ።

"ተይ እባክሽ ፡ ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ ነው ። አትወጅኝም እንጂ ብትወጂኝማ ኖሮ ... ደግሞ እኔም ለጥያቄው ዘግይቶሁና አይፈረድብሽም"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዴት አልወድህም ?

"ይህ የሣፈው ሁኔታችን ከአራት ወራት በፊት ቢሆን ኖሮ ውጤቱ ሌላ ነበር ። ሰዎች እንደ ወንዶች አለመሆናቸውን እያወቅሁ እኔ ነኝ የተዘናጋሁት ።"

"ማክሲምዬ · እስቲ እንደገና አንዴ ሳመኝ!"

"አይ : አይ : አይ : አሁን ምን ዋጋ አለው ብለሽ ?"

"እባክህ የኔ ፍቅር እሺ በለኝ ። ከእንግዲህ እኔና አንተን የሚከልል አንዳችም ግርዶሽ በመካከላችን ሳይደነቀር : የሚያራርቀን ምንም ምስጢር ሳይኖር አብረን መኖር እንችላለን እኮ ።"

"አብረን የምንኖርበት ምን ጊዜ አለና ብለሽ ? የጋራ ሕይወታችን በሰአታት : ግፋ ቢል በጥቂት ቀናት የሚቆጠር ነው ። ይህ ሁሉ ነገር ተፈጥሮ ምኑን አብረን ኖርነው ? ጀልባዋ ተገኝ እያልኩሽ ? ርቀን አገኟት እያልኩሽ ?"

የሚለኝ ሁሉ አልገባሽ ብሎኝ እንደ ጅል አይን አይኑን እያየሁ "ታዲያ ምንድነው የሚያደርጉት ?" ስል ጠየኩት ።

"እርሷ ነቲን በሚገባ ለይተው ያውቃሉአ ። የለበሰችው ልብስ : ያጠለቀችው ሜካፕና ጌጣጌጧ : ሁሉም ነገር ስላለላቸው አጽሙ የርቀት መሆኑን ለመለየት ምንም አይቸግራቸውም ። ከዚያ በኋላ ደግሞ የሚቀጥለው ጥያቄ የተቀበረችው ሴትዮ ማን ናት ? የሚለው መሆኑ ነው ።"

"ታዲያ አንተ ምንድነው ማድረግ ያለብህ?" ስል በዝግታ ጠየኩት።

"እኔ እንጃ ምን አባቱ አውቂው ።"

ያ ቅድም ሽሽቶኝ የነበረ ስሜት ቀስ በቀስ ይዳስሰኝ ገባ ። እጆቼ እየሞቁ : መላ አካሌ እየጋለ ሲሄድ ተሰማኝ ። ካኖቱን ሲርል : ባህር ጠለቁ ዋናተኛ : እኒያ በመርከቧ ዙሪያ አሰፍስፈው የነበሩ ሰዎች ሁሉ በአይነ ህሊናዬ ድቅን አሉ ። የከራዝ ባለመያዘሮች : የመንደር ልጆች በየመንገዱ ሲያሻፉ : አባ ከቤተመቅደስ ሲወጡ : እመት ከሮዋን ከመናፈሻቸው ሙስጥ ዕጌራዳ ሲቀጥፉ... እኒህና እኒያ ... ሌሎችም ሁሉንም ነገር ማወቃቸው አይደል ? ነገ ወፍ ሳይንጫጫ ሁሉም መፈጠን ሲያራግባው "ርቀት ከጀልባዋ ተገኘች : ማክሲም ርቀቱን ገደላት ..."

t.me/OLDBOOKSPDF

እያለ ሲያናፍሰው በእዝነ ልቦናዬ ሲያቃጭል ዝግንን አለኝና ሚንትላቱን ግራ ቀኝ ወዘወዝኩት ። ይሽው ሀሳብ የአሁኑን ከቅድሙ ፡ የዛፈውን ከትናንቱ ፡ የትናንቱን ከትናንት በስቲያው ፡ የትናንት በስቲያውን ከዚያ ወዲያው ፡ የዚያ ወዲያውን ከዚያኛው እያቅራኘ ነጠላ ዜንጦችን እያዛመደ ፡ የደነዘውን እየሳለ ፡ የደበዘዘውን እያበራ ፡ የደከመውን እያጐለበተ ፡ የሰለለውን እያደነደነ ሁሉንም ከምናብ ሰሌዳዬ ላይ ገጣጥሞ አቀረበልኝ ።

"እንግዲያውስ ምንድነው ማድረግ ያለብን? ምን ማለት ነው የምንችለው?" አልኩት ። መልስ አልሰጠኝም ። ጢስ መውጫውን ተደግፎ አይኑ በባዶው እንዳፈጠጠ ፀጥ ብሎ ሲቀርበኝ "ስለ ሁኔታው ሌላ የሚያውቅ ሰው አለ እንዴ?" ብዬ ጠየቅኩት ። ሚንትላቱን እየነቀነቀ "ማንም አያውቅም" አለኝ ።

ከኔና ከእርሱ በስተቀር ማንም እንደማያውቅ በድጋሚ ሲያረጋግጥልኝ "ፍራንክም? እርሱም እንደማያውቅ እርግጠኛ ነህ?" ስለው

"ፍራንክ? እርሱ እንዴት ሊያውቅ ይችላል? ብቻዬን ነበርኩ ። ደግሞ ጨለማ ስለነበር..." አለና ሀሳቡን ገታው ። ወንበሩ ላይ አረፍ አለ—ግንባሩን በእጁ እያሻሸ ። ሄጀ አጠገቡ ተንበረከክኩ ። እጁን ከግንባሩ አላቅቄ አይኖቹን አይኖቹ ላይ እያንከባለልኩ "እወድሃለሁ ፡ ወለላዬ" አልኩት በለሆሳስ ። "እወድሃለሁ ፡ እወድሃለሁ ። አሁንስ አታምኝኝም?" ስለው ግንባሬ ላይ ሳመኝ — እጆቼንም እያገላበጠ ሳማቸው ። ልቡ ውስጥ ሀይለኛ ፍርሀት ተዘፍዝፎ ከለላ ወይም እርዳታ እንደሚሻ ሕፃን እጆቼን ጥርቅም አድርጎ ያዛቸው ።

"ከአሁን አሁን ምን ይፈጠራል ብዬ እየጠበቅሁ እዚሁ እንደ ጅል መቀመጤ...ጨርቄን ጥዬ ማበድ ነበረብኝ ። የልቤን ልቤ እያወቀው በየእለቱ ይጐርፉልኝ የነበሩትን ደብዳቤዎች ሳስተናግድ ፡ ምንም ያልደረሰብኝ ይመስል እንደ ማንኛውም ጤነኛ ሰው ስበላ ስጠጣ ፡ መሉ አቅል እንዳለኝ ሳስመስል...ፍሪዝ ፡ ሌሎችም ሠራተኞች ፡ ሚስዝ ዳንቨርስ—በተለይ ሚስዝ ዳንቨርስ — እንዳላባረራት ከርብቃ ጋር በነበራት የቀረበ ግንኙነት ሳቢያ ልትጠረጥር ትችላለች ብዬ እየፈራሁ.... ደግሞ የፍራንክ ነገር እንጂ — ምኔም ከጎኔ ያልተለየኝ ፍራንክ — ዘወትር ሀዘን ችግሬን የሚጋራኝ ፍራንክ ፡ ውልጊዜ 'ምነው ከዚህ አካባቢ ራቅ

t.me/OLDBOOKSPDF

ብትል? እዚህ ያለውን ሥራ እኔ እቆጣጠራለሁ ። መሄድ አለብህ ሲለኝ ። ጂልስና ቢያትሪሰስ ቢሆኑ — ያቺ ምስኪን ፡ ተንኮል የሚባል ፡ ዘዴ የሚሉት ነገር የማታውቀው ‘ውይ ፡ የዓመት በሽተኛ ትመስል የለም እንዴ? ምነው ሀኪም ዘንድ ሄደህ ብትመረመር’ ስትለኝ…እያንዳንዷ የምትነፍሳት ታል በሀሰት የተሞሸረች መሆኗን እያወቅኩ ነበር የእኒህን ሁሉ ሰዎች ፊት አይኔን አፍጥጬ የማየው…”

እጆቹን በእጆቹ ጠበቅ አድርጌ እንደያዝኩ ገላውን ከገላዬ ይበልጥ እያስጠጋሁ ጸጥ ብዬ ማዳመጤን ቀጠልኩ ። “ያኔ ጄስፐር ወደ ባሕሩ መሽመጥ ሄዶብሽ አንቺ ማሰሪያ ፍለጋ ጎጆው ውስጥ የገባሽ እለት እዚሁ ልክ እንዳሁኑ ቁጭ ብለን ይህን ሁሉ ምስጢር ላጫወትሽ ነበር ። ድንገት ፍሪዝና ሮበርት ሻይ ይዘው መጥተው አቋረጡን እንጂ” አለኝ ።

“አምን ትዝ አለኝ ። ግን ከዚያ በኋላስ ቢሆን ለምን አልነገርከኝም? ነግረኸኝ ቢሆን ኖሮ ይህን ሁሉ ጊዜ በሰላምና በደስታ ማሳለፍ ስንችል ?”

“አንቺ በየት ተገኝተሽ? ሁሌ ሙሾሽ መናፈሻ ውስጥ ነው ፡ ሁሌ ከጄስፐር ጋር —በራስሽ አለም ተፈጥመሽ ስትሽከረከሪ ። እንደ ዛሬ መች ቀረብሺኝና?!”

“ምነው ነግረኸኝ ቢሆን ኖሮ?” በማለት በጆሮው ሳንሾካሾክለት

“ደስታ የራቀሽ ፡ የተሰላቸሽ እየመሰልሺኝ እንዴት ብዬ? እኔ ደግሞ በእድሜ ካንቺ በጣም የገፋሁ ስለሆነ ነው መሰለኝ ከኔ ይልቅ ለፍራንክ ነበር ግልጽነትሽ ። ለኔማ ከነአይናፋርነትሽ ፡ ከነንጭንጭሽ ልዩ ፍጡር ነበር የምትሆኚብኝ ።” አለኝ ።

“የእኔንስ ችግር ለምን አታይልኝም? አንተ ርብቃን ከአእምሮህ እንዳልፋቅካት ፡ ፍቅሯ ከልብህ እንዳልተሰረዘ እያወቅሁ እንዴት ልቅረብህ ? እንዴትስ እንድታፈቅረኝ ልጠይቅህ?”

ይበልጥ ወደራሱ እያስጠጋኝና አይኖቼን እየፈለገ “ምን ድንው የምትዪው? ምን ማለትሽ ነው?” ሲል ጠየቀኝ ።

እዚያው እተንበረከክኩበት እየተመቻቸሁ “እጆችህ በዳሰሱኝ ቁጥር ከርብቃ ጋር የምታነፃፅረኝ እየመሰለኝ መላ አካሌ ሽምቅቅ ነበር የሚለው። ስታናግረኝ ፡ ትክ ብለህ ስታየኝ ፡ መናፈሻው ውስጥ ስንንሸራሸር፡ ማእድ አብረን ስንቀርብ ሁሉ በሀሳብ ሞልተ ስትልብኝ ‘ጨዋታ ዱሮ ቀረ — ከርብቃ ጋር ! መብላት መጠጣት — ከርብቃ ጋር !

t.me/OLDBOOKSPDF

መንሸራሸር—ከርብቃ ጋር ነበር' እያልክ የምታሰላስል እየመሰለኝ ምን ያህል ነበር ልቤ የሚሸማቀቀው" ስለው ምኑም እንዳልገባው አይነት በግርምታ ትክ ብሎ ያየኝ ነበር ።

"ምነው? እውነት አይደለም እንዴ?"

ወለሉ ላይ ኩርምት ብዬ እንደተቀመጥኩ ተሽከርክሮ አየኝና "ርብቃን ይወዳታል ብለሽ ታስቢ ነበር ማለት ነው? ብወዳት ነው የገደልኳት? ይመስልሻል? ምንኛ እጠላት እንደነበረ ባወቅሽልኝ ። ትዳራችን ከጥንስሱ ጀምሮ አንድ ቀን ሰላም ያልሰፈነበት ፡ አንድም ደስታ ያልነገሰበት የልብ መቁሰያ ቤተ—ሙከራ ነበር ። ርብቃ ፍቅር የሚባል ነገር ስሙን እንኳ የምታውቀው አልነበረችም ። ትንንት ሲያልፍ አልነካትም ። ልቧ በክፋት የታጨቀ ፡ ድሯም ማንም ተንኮል ብቻ ። በርግማን የተለታለቀች ፍጡር ። ከነአካቴው የአእምሮዋን ጠንንት እጠራጠር ነበር ።" ሲለኝ ጉልበቱን አጣጥፌ ትኩር ብዬ አየሁት ።

"በእርግጥ ብልህ እንደነበረች ግን ልክድ አልችልም ። ክፋቱ ብልህነቷም የሚውለው ለተንኮል ብቻ ነበር እንጂ ። ላይ ላይዋን ያየ ሁሉ በምድር ላይ ተወዳዳሪ የሌላት አዋቂ ፡ ደግሞ ፡ ርህሩህ ፡ ቸር አድራጎ ነበር የሚቆጥራት ። ሰውን እንደየስሜቱ የማግባባትና የማቅረብ ተሰጥኦዋ ልዩ ነበር ። አሁን ካንቺ ጋር ብትገናኝ ኖሮ እጅሽን ይዛ መናፈሻው ውስጥ እያንሸራሸረችሽ ስለ አበቦች ፡ ስለ ሙዚቃ ፡ ስለ ስእል —ብቻ ፍላጎትሽን ኮርኩራ አውጥታ ደስ ስለሚልሽ ነገር ሁሉ ታወራልሽ ነበር ። በሰዎች ልብ ውስጥ ሰርስራ ገብታ ከእግሯ ስር ተንጥፈው እስኪያመልኳት ድረስ የማድረግ ችሎታዋ ፍጹም ሌላ ነበር ።"

ማክሰኞ እላይ ታች መንጎራደዴን ሳይተው ትረካውን ቀጠለ "ያኔ ሳገባት ምንኛ የታደልክ ነህ ያላለኝ አልነበረም ። በውበት ፡ በቁመና በአንጋገር ለዛ አሚልቱ የሰራት ነበረች ። አያቴ እንኳን ሰው ማድነቅ የሚለት ነገር ሞራሹን ከአፉ የማያጠጣው አያቴ እንኳን ግና ስታያት ነበር የወደደቻት ። ለአንዲት የቤት እመቤት የሚያስፈልጉ ሦስቱን መሠረታዊ ነገሮች መልካም አስተዳደግ ፡ ብሩህ አእምሮና ቀና መልክ አካታ የያዘች ልጅ ናት ነበር ያለችኝ ። ያኔ ባምናትም ፡ ወይም ደግሞ እንዲያምን እራሴን ባታልለውም ሁልጊዜ ሀሊናዬን የሚጎረብጠው ነገር ነበር ። አይኖቿን ሳያቸው አንዳች ስሜት ያሞራብኝ ነበር..."

t.me/OLDBOOKSPDF

እኒያ የተበታተኑ ምስሎች እንደገና እየተሰባሰቡ ሲገጥሙ ታየኝ ። ርዕሱ ከተሸሸገችበት ስውር አለም ብቅ ብላ እውነተኛው ገፅታዋ፡ ውስጣዊ እሳቤዟን የተላበሰው ሰውነቷ ታየኝ ። ሕይወትን በሁለት እጅጅ ጨብጣ ፡ አለምን እንደ ፈረስ እየጋለበች ቹ! ስትለው በድል አድራጊነት ፍንድቅ ፈታ ስትል ድቅን አለችብኝ ።

የተለያዩ ሰዎች ሚስዝ ቫንሁፐር ፡ ቢያትሪስ ፡ ማክሲም እራሱ ፡ ፍራንክ ፡ ሚስዝ ዳንቨርስ ፡ ያ ጅላጅሉ ቤን ሳይቀር — በተለያዩ ጊዜያት ስለ ርዕሱ ያወጉኝ ክፉ ደጉ ፡ የነገሩኝ ፀአዳም ሆነ ጨለማ ጎኗ ሁሉ በአእምሮዬ ተመላለሰ ።

ማክሲም ብሶቱን ተጠለ "...ግን ወዲያው ነው ምንነቷን እብጠር ጥሬ ያወቅኩት በተጋባን በአምስተኛው ቀን ። ያኔ እኔና እንቺ ሞንቴ ካርሎ በነበርንበት ጊዜ ለሽርሽር የሄድንበትን ቦታ ሳታስታውሺው የምትቀሪ አይመስለኝም ። ድንገት በሀሳብ ሟልጥ ብዬ መንኳኴ ማሪ አጋብቶሽም ነበር ። ከእርሷ ጋር እዚያው ቦታ ሄደን በነበረበት ወቅት መሬቱ ላይ ተዝናንታ ተቀምጣ ፡ ንፋስ የሚያጫውተው ወጉሯን በጣቶቿ እያፍተለተለች ስለ ራሷ ትነግረኝ ጀመር ። ኩርከራ በተቀላቀለበት ሳቋ እያጀበች የነገረችኝ ነገር የማንም ሰብአዊ ፍጡር ጆሮ ሊሰማው የሚገባ አይደለም ። ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ነው ምን እያነት ሴት እንዳገባሁ የተከሰተልኝ ። መልከ ቀና ፡ አእምሮ ብሩህ ፡ አስተዳደግ መልካም — አለች አያቱ! አያ ፈጣሪዬ!..." አለና ንግግሩን አቋርጦ ከትከት ብሎ ይስቅ ጀመር ። የመሳቱ ነገር ካደናገረኝ በላይ የመልኩ ልውጥውጥ ማለት ሟርሱን አስደነገጠኝ ። አንጀቱ ተላወሰ ። እንዲህ ሲሆን ዝም ብሎ ማየቱ አልሆን ቢለኝ "ማክሲም! ማክሲም!" ብዬ ጮህኩ ።

ሰጋሪውን ለኩሶ በልቅ በልቅ እያለ ካፉ የሚወጣውን ጢስ በትካዜ ሲያስተውለው ከዙያ በኋላ ፊቱን መለስ አድርጎ ወዲያ ወዲህ ማለት ያዘ ። "በዚያን ወቅት ግደላት ፡ ጨርሳት ነበር ያሰኘኝ ። ምነው አድርጌው በነበር? ትልቅ ግልግል ነበር ። በዚያ ሞው ባለው ገደል ትንሽ ገፍተር ማድረግ ብቻ ነበር እኮ ። ያ እንደ ግድግዳ ቁጥ ያለውን ገደል ታስታውሺው የለ? እንዲያውም አስፈራርቼሻለሁ እንጂ ። ታዲያ እንደ እብድ ሳትጮሂራኝ አልተረሽም ። በእርግጥም ያኔ አላበድኩም ነበር ብለሽ? ምን ያኔ ብቻ አውንስ መች ጤነኛ ሆንኩና!...ከዲያብሎስ ጋር

t.me/OLDBOOKSPDF

እየተኖረ ሙሉ ጤንነት በየት ይገኝና?"

ወዲያ ወዲህ ፡ ወዲህ ወዲያ ሲንጎማለል ቁጭ ብዬ በእይኔ እከተለዋለሁ ።

"...እዚያ ገደሉ አፋፍ ላይ ቁጭ ብላ የተንኮል ድርሳኗን ስታነበንብ ልልኝ እንደ ጅል አፈጠጠ ከፍቼ ነበር የማዳምጣት ። እበትሀን አሳምሬ እይዝልሃለሁ ። ከፈለክ ደግሞ ውበትና ድንቁ ማንደርሉይን በሚገባ ከመንከባከቢም በላይ በመላ አገሪቱ እጅግ የተደነቀ መስሀብ ላደርግልህ እችላለሁ ። ሊጎበኘን የሚጎርፈው ህዝብ ብዛት ይታየኛል ። ሳር ቅጠሉ ስለ እኛ ሲያወራ ፡ ሲቀናብን ፡ በምድረ እንግሊዝ እንደኛ ትዳር ያማረ ፡ የታደለ ፡ ደስታ የሰፈነበት ሊኖር እንደማይችል አገር ሁሉ ሲመሰክር ልን። አሾፍኩብህ አይደል ፡ ማክስ? አለችና እየተጎነጎነች ይሣው የነበረውን አበባ ብጥስጥስ አድርጋ ጣለችው ።" አለ ማክሲም ራቡን ያህል ያጨሰለትን ሲጋራ ወደ ምድጃው እየወረወረ ።

"ይህን ሁሉ ስታወራልኝ ዝም ብዬ ነበር የማዳምጣት።" በማለት ቀጠለ ማክሲም "እንዳሻት ስትንከተከት ዝም ብዬ አየኋት እንጂ አልገደልኳትም ። ተያይዘን መኪናችን ውስጥ ገባንና ወደ መጣንበት አመራን ። የነገረችኝን ሁሉ እንደማያርግላት ፡ ያሰበችውን ሁሉ እንድትፈጽም እድሉን እንደማልነፍጋት ፡ ሁኔታዎችን እንደማመቻች ላት ሙሉ እምነት ነበራት ። ስለ ራሷ የነገረችኝን በጋብቻችን ማግስት ተነስቼ አገር ስማኝ ብዬ ከመለፍለፍ ይልቅ ስሜን ፡ ክብሬን ፡ ማላዊ ስሜቴን — ማንኛውንም ነገር መስዋእት ከማድረግ እንደማልመለስ እርግ ጠኛ ነበረች ። የፍች ጥያቄ አንጠልጥዬ ችሎት እንደማልቆም ፡ እርሷን አሳልፌ እንደማልሰጣት ፡ የማንም ጣት እንዲቀሰርብን ፡ ማንም እየተነጣ በየጋዜጣው የጭቃ ጅራፉን እንዲያሳርፍብን ፡ የመንደር ወሬኛ አፍ ማሟሻ እንዳንሆን ፡ 'ይሄ ነው ማንደርሉይ ማለት ፡ እዚህ ነው እንግዲህ ጉዱን በጋዜጣ ያነበብንለት ሰውዬ የሚኖረው ፡ ዳኛው ስለሚስቱ ምን እንዳለ ትዝ ይላችኋል ... ?' እያሉ ሰዎች እንዲዘባበቱብኝ እንደማልሻ አሳምሬ ታውቅ ነበር ።"

ወዲኔ መጥቶ ፊት ለፊቴ ቆመ ። እጅቹን ዘርግቶ "ታዘብሽኝ አይደል? ምን ታደርጊ? እኔ ውስጥ የሰረፀ ሀፍረት ፡ ጥላቻና ቅሬታ አልዳሰሰሽ..." ሲለኝ ምንም መልስ ሳልሰጠው የዘረጋቸውን እጅቹን

t.me/OLDBOOKSPDF

በእጅቹ እየመራው ደረቱ ላይ ሰበሰብኳቸው ። ይሀን ሁሉ ሲዘከዝክልኝ በወጥ ልስማው እንጂ የሚለውን ሁሉ ልብ አላልኩለትም ። ስለ እርሱ ሀፍረት ፡ ስለሌላውም ስሜቱ ትንሣትም ደንታ አልነበረኝም ። በእጅጉ ትኩረቱን የሳበውና ደማሚ ደጋማ አሰላስለው የነበረ አንድ አቢይ ቁም ነገር ቢኖር "ማክሲም ርብቃን እይወዳትም ነበር ፡ ወዷትም እያውቅ ፡ ለእንዲት ሲኾንድ እንኳን ደስታ ተጋርተውም አያውቁ?" የሚለው ሠፃብ ብቻ ነበር ።

"በዚህች ምድር ላይ ከማንደርሉይ የማስቀድመው እንዳችም ነገር አልነበረም ። ዳሩ ምን ዋጋ አለው? ማን ሊረዳልኝ? ማን ሊያምነኝ? በሰዉ እንኳን አልፈርድበትም ። ለእንዲህ አይነት ፍቅር ባይተዋር ነዋ..." እያለ ሲያማርር አቋረጥኩትና

"የኔ ገላ ማክሲምዬ ፡ ፍቅሬ ፡ መለሳዬ" አልኩና እጆቹን ከፊቱ ላይ አኖርኳቸው ። አገላብጦ ሳምኳቸውም ።

"ለመሆኑ የምለው ሁሉ ይገባሻል? በደንብ ይገባሻል? እህ?"

"አምን የኔ ፍቅር ፡ በደንብ ነው የሚገባኝ" አልኩት ። ፊቴ ይናገርብኝ እንደሁ ብዬ በመስጋት አይኑን ማየት አልደፈርኩም ። ገባኝ ፡ አልገባኝ ምን ለውጥ ሊኖረው? እኔ እንደሆንኩ ርብቃን እንደማያፍቅራት ካወቅሁ ወዲህ ልዩ ስሜት እየተሰማኝ ነበር ። ልቤ ደረቴን ፈንቅሎ መውጣቱ አዳገተው እንጂ አየር ላይ እንደሚንሳፈፍ ላባ ነበር የሆነው ።

"ያለፉትን አመታት መራራ ትዝታ እንደገና ማንሳት አልሻም" ሲል ዝግ ባለ ድምፅ ጀመረና "ላንቺ እንኳን መንገሩ ደስ አይለኝም ። ምን የሚነገር ነገር አለውና? የሀፍረት ፡ የውሸት ኑሮ? እኔና እርሷ የድብብቆሽ ፡ የማስመሰል ኑሮ ነው ያሳለፍነው ። በዘመድ አዝማድ ፡ በወዳጆቻችን ፡ በሰራተኞቻችን ፊት ፡ ፍሪዝን በመሰሉ ቅንና ታማኝ ፍጡራን ፊት ተስማምተንና ተፋቅረን የምንኖር ነበር የምንመስለው ። በዚያ ጤፍ በሚቆላ ምላሷ ስትሸረድደው የማይወዳት ፡ የማያምናት ፡ አድኖቹን የማይቸራት ከቶም አልነበረ ። ጥርሷን ብልጭ እያደረገች ስትሸነግላቸው ያለ እርሷ ሰው የለም ነበር የሚሉት ። ከበስተጀርባቸው እንዴት እንደምታሾፍባቸው ግን የት አዩትና? አፈ ቅቤ ፡ ልበ ጨቤ ማለት እርሷን ነበር ። ሀሣቱስ ሲወጂት! ስለታምነቷን ስለምታርከፈክፍላቸው ባለፈች ባገደመች ቁጥር እየፈነደቁ እጅ እጇን ነበር የሚያዩት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"የዚህን አካባቢ ሀገሀብ እንዲህ አድርጋ ስለገዛችው የሰራችውን ብትሰራ ማንም አያጠረጥራት ። እርሷስ ምኗ ሞኝ! ምስጥ አያያለች : ሎንዶን ትሄድና አራት አምስት ቀናት ሰንብታ የልቧን አድርሳ መመለስ ነው ። እኔ ሁለንም ነገር ልዋናዬ እያወቀ ዝም ነው ። የገባውትን ታል ማጠፍ የለብኝማ ። ማንደርሌይን ልዩ አደርገሞለሁ ባለችው መሠረት በእርግጥም ይሸው ዛሬ እንደሚታየው የምድር ላይ ገነት አስመስላዋ ለች። ለዚህ ለማንደርሌይ ባለኝ ፍቅር : በዚህ ደካማ ጎኔ ገብታ አያያል እንዲያ ያነሠለለችኝ ። በአባቱ ጊዜ ማንደርሌይ እራሱን የቻለ የተፈጥሮ ውበት ቢኖረውም ጥቅጥቅ ያለ ሜካ ነበር ። "የሰው ያለህ : የአሞቲ ያለህ : የባለሙያ ያለህ ብሎ ሲጮህ ከተርሞ ከች አለችለታ ። መኖሪሻዎችን ብትዩ : ፍስሐ ሸለቆን ሳያቀር እንዲህ ያለ ውበት ያጎናፀፈቻቸው ርዛታ ። ክፍሎቹን : የእቃዎቹ አደረጃጀት ሁሉ ዛሬ የያዙትን ውበትና ግርማ ያለበሰቻቸው ርዛታ ። የቤት ውስጥ ቲሳቲሶቹ : ስእሎቹ : ልዩ ልዩ ማጌጫዎች የእርሷ ጥበበኛ እጅ ያልዳሰሰው የለም ።"

የዘመናት ብስጭቱን እንዲተነፍስውና ትንሽ እንኳን እርጋታ እንዲሰማው ፈልጌ ሳላቋርጠው ዝም ብዬ አዳምጠው ነበር ።

"እንዲህና እንዲህ ሆነን ወራት አለፉ : አመታት ተቆጠሩ ። ለማንደርሌይ ሰል ታውሬ : ለማንደርሌይ ስል ሀሊናዬን ተሰልቢ ኖርኳታ። ሎንዶን ውስጥ እንዳሻት ብትሆን ደንታም አልነበረኝ የማንደርሌይ ክብር እስካልተነካ ድረስ ። በመጀመሪያዎቹ አመታት በጣም ጥንቁቅ ስለነበረች ጣጣ ፈንጣጣዋን እዚያው ሎንዶን ከውና ትመጣ ነበር ። ውላ ስታድር ግን ቸል ማለት አመጣች ። አንድ ሰው እንደሷት የመጠጥ ሱሰኛ እንደሚሆን ታውቀያለሽ: እንደ ዘበት ይጀምረ ዋል ። እየተራፈፈው እንዲያው አንዳንዴ በአራት ወያም በአምስት ወር አንድ ጊዜ ይተማምላል ። ከዚያ የእረፍት ጊዜውን እያሳጠረ እያሳጠረ ይሄድና በየሁለት ወር : በየወሩ በየአስራ አምስት ቀኑ : በየሣምንቱ ... እያለ መሄድ ነው ። ከዚያማ ምኑ ቅው : እንዳሉት : ኪስ እንደፈቀደ : ጋባሻ እንደተገኘ : ሀሊናም በእጅጉ ከተደፈ አፍ አውጥቶ ለምኖ መጠጣት ነው ። ርዛታም እንዲሁ ነው የሆነችው ። ቀስ በቀስ ወዳጅ : ጓደኛ እያለች ሰምችን እዚው ድረስ እየጋበዘች አሸሸ ገዳሜዋን ተያያዘ ችው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"አንድ ጊዜ ለአደን ስኮትላንድ ከርሜ ስመለስ ባሀሩ ዳርቻ ካለው ጎጆ ውስጥ ፈጽሞ አይቻቸው ከማላውቅ ሰዎች ጋር ስትምነሸነሽ አየኋት ። 'ይሄ ነገር ደግም አይደል' ብዬ ማሳሰቢያ ብጤ ብሰጣት አፍንጫዋን ነፋችብኝ ፡ ትከሻዋን ኮረሰችብኝ ። 'ምን ያገባህና ?' ብትለኝ ፡ ሎንዶን ውስጥ ካሻት ሰው መሆን ፡ እንዳሻት መፈንጠዝ እንደምትችልና ማንደርሉይ ግን የግሉ ነውና እንድትተውልኝ ፡ ስምምነታችን መጣስ እንደሌለበት ብነግራት የምወት ፈገግታዋን አሳያታኝ ወጥ አለች ።

"ጥቂት ቆይታ የአይን አውጣነቷ ብዛት ፍራንክን አላስቆም አላስተምሞ ብላ አበሳውን ብታሳየው ስሞታ ነገረኝ ። በመጀመሪያ ግን ምስጢሩን በሆዱ ተብሮ ሌላ ስራ ስላገኘ እንዳሰናብተው ጠየቀኝ ። አብደሃል ወይ? አልኩት ። ነገሩን እያድበሰበሰ ሁሪያ ጥምጥሙን ሲሄድ ለውሶ ፡ ስአታት ያህል ተከራከርን ። ውጥር አድርጌ ስያዘው ርብቃ በየጊዜው እቤቱ ድረስ እየሄደች አብሯት ወደ ጎጆው እንዲሄድ ትጠይ ተው እንደነበረና አንተልኝ ትገፋፋው እንደነበረ ዘረዘረልኝ ።

"ይህስ ለምን ይሆናል? ብዬ ብጠይቃት ግስላ ሆነችብኝ ። ካሻ ያልወጣ ወያኖ ስድብ አልነበረም ። ብጥብጣችን ወጣ ። ከዚያም ተነስታ ሎንዶን ትሄድና ወር ያህል ትተመጣለች ። ተመልሳ ስትመጣ ዝም ዝም ብትልብኝ ቢሰግት ነው አደብ የገዛችው አልኩና ተውኳት ። አንድ ቀን ቢያትሪስና ባለቤቷ ሊጎበኙን ይመጣሉ ። እኔና ቢ እመስኩ ላይ እየተንሸራሸርን ሳለ ርብቃና ጂልስ በጀልባ ሲንሸራሸሩ ቆዩ ። ሲመለሱ ጂልስ ፊቱ ተልጦል ፡ እንደ ሀሣን መፈንደት ነበር የቀረው ። ርብቃም ሌላ ስርቆት እንደ ጀመረች አደኗ ያሳብቅባት ነበር ። ገበታ ቀርበን ቢያትሪስ የሁለቱንም ሁኔታ በዕሞና ስትከታተል መገንዘቤ እንቅልሽ ሆኖብኝ ለነበረው የቢያትሪስ ርብቃን እንደዚያ መጥላት ፍች እንዳገኝለት ረዳኝ ።"

እያዳመጥኩ ነገሮችንና ድርጊቶችን በአእምሮዬ እየገላለጥኩ እገረም ነበር ። የርብቃ ስም በተንኮለ ቋጥር የፍራንክ መቅበጥበጥ ለካስ ለዚህ ኖሯል? የቢያትሪስ ለለ ርብቃ ቀና አስተያየት ማጣት ለዚህ ኖሯል? እያልኩኝ በማርምታ ተሞጥኩ ። ከወዘኔታ ፡ ከትን ልቦና የመነጨ ይመስለኝ የነበረ የሰዉ ዝምታ ለካስ ሀፍረት የወለደው ፡ ጥላቻ ያሳደገው የውስጥ ስሜት ነውብራት ኖሯልና? በአይናፋርነት ካባ ስር ተከልዬ ይህን

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁሉ መገንዘብ ባለመቻሉ እራሴን ክፉኛ ገመትኩት — ወቀስኩትም ።

ይህች ምድር እንደኔው ሁሉ ከተበተባቸው የአይናፋርነትና የቁጥብ ነት ድር መላቀቅ የተሳናቸው ፡ አስተሳሰባቸውን አደንዘው ልቦናቸውን ያሳወሩ ፡ በገዛ እጃቸው በዙሪያቸው ያቆሙትን ሀቲን የጋረዳቸውን ግድግዳ ገንድሰው መጣል አቅቷቸው ፡ በድንቁርና ባህር ውስጥ የሰጠሙ ስንቶችን አፍርታ ይሆን? እኔስ? አንዴ እንኳን አይናፋርነቴን ገፍፈ ፡ ማክሲምን ጠይቄው ቢሆን ኖሮ ከአራት ከአምስት ወራት በፊት ይህን ሁሉ ይነግረኝ አልነበር?

"ከዚያን ቀን ዝኳላ ቢያትሪስና ጂልስ የእረፍት ጊዜያቸውን በማንደርሌይ ማሳለፉን እርግፍ አድርገው ተውት ። ለምን ብዬ ጠይቄአቸውም አላውቅ" አለ ማክሲም በማያያዝ "እንዳንዴ ሰፈ ግብግ ስናደርግ እንደማንኛውም ተጋባዥ መምጣታቸው ግን አልቀረም ። ቢ ምንም አንስታብኝ ባታውቅም ኑሮዬ ያሳስባት እንደነበረ ከሁኔታዋ መረዳት አላዳገተኝም ። እንግዲህ ርብቃም ያንኑ ምስጣ ምስጥ የአስመሳ ይነት ተግባሯን ትቀጥልልሻለች ። እኔ ከዚህ ወጣ ስል ምን ታደርግ እንደነበረ እግዜር ይወቀው ። ፍራንክንና ጂልስን እንዳባበለች ሁሉ የምታማግጠው አታጣም ። ሠራተኞች ሞልተውላታል…ከኬሪዝም አንዱን ልትጎትት ትችላለች…ብቻ እኔ እንጂ ። እኔን ዘወትር ያስጨንቀኝ የነበረው አንድ ቀን ይህ ምስጢር ወጥ ይሞቀውና…የሰው ሹክሹክታ… ሀሜቱ…የወረኛ አላማ መሆኑ…"

እዚያው እንደተቀመጥኩ ሀሳብ ሟልጥ አድርጎ መሰደኝ ባህሩ ዳር ወዳለው ጎጆ ። ዝናቡ ጣራው ላይ ሲያርፍ ተሰማኝ ። አባሪ የለበሰች ቁሳቁሶች…ያ ምስኪን ቢን እኒያ ጅላጅል አይኖቹን እያቁለጨለጨብኝ "…እብዶች ሀኪም ቤት አታስገቢኝም አይደል?" ሲል ተሰማኝ ሌሎች ሀሣቦችም ።

"አንድ ደግሞ የአጎቷ ልጅ ነበረ ፡ ጃክ ፈቭል የሚሉት ። እግሬን ጠብቆ የሚመላለስ…" አለ ማክሲም ድምፁን አለሰልሶ ።

ቀበል አደረግኩና "አውቀዋለሁ ፡ ያኔ ሎንዶን ሂደህ በነበረበት ጊዜ መጥቶ ነበር እኮ" አልኩት ።

"አንቺም አይተሽው ነበራ? ለምን አልነገርሽኝም ታዲያ? ፍራንክ እኮ ነው የነገረኝ ፡ ሙኪናውን አይቶ ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እኔ መንገሩ ደስ አላለኝም ። ርብቃን ያስታውስሀና ትረበሻለህ ብዬ ነው"

"ያስታውስሀና? እንዴት አስታወስኳት እላክሽ?" አለና ታሪኩን ለጊዜው አቋርጦ በሳቁ አፍጦ ቀረ ።

ከእንቅልፍ የባነነ አይነት ሞንቅላቱን ነቀነቀና ቀጠለ ። "ከዚው ከፈቭል ጋር አዘውትራ ወደ ጎጆው ትሄድ ነበር ። ለሠራተኞች ሌሊቱን በጀልባ እንሽራሸራለሁ ትልና እዚያው ከእርሱ ጋር አድራ ትመጣለች ። እንዴት ይሆናል? ብዬ በድጋሚ ማስጠንቀቂያዬን ሰነዘርኩ ። ሌላው ቀርቶ ማንደርሌይ ክልል ውስጥ ባገኘው በጥይት እንደምጠብሰው ነገርኳት ። እንደተለመደው ትከሻዋን ትኮፍስብኝ እንጂ መአቱ አልመረደብኝም ። ፊቷ ድንገት ሲገረጣ ፡ ልውጥውጥ ሲል ታየኝ ። እርጅና አሻራውን ሲጥልባት ምን ልትመስል እንደምትችል ለመጀመሪያ ጊዜ የገመትኩት ያኔ ነው ። ያሄ ፈቭል የሚሉት ወስላታ ፡ ሰው እንዳይመስልሽ ፡ ስሙ ብክልክል ያለ ብልሹ....

"...አንድ ቀን ለንደን መሄዴ ነው ብላ ትወጣና የዚያኑ እለት ማምሻውን ትመለሳለች — አድርጋው የማታውቀውን ። እኔ ደግሞ እለቱን ትመለሳለች ብዬ ስላልገመትኩ ከፍራንክ ጋር ስንሰራ አመሸንና እራቴን ከእርሱ ዘንድ እበላለሁ ። አመሻሽቼ ወደ አራት ሰዓት ተኩል ግድም እቤት ስገባ የእንግት ልብሷንና ጓንቲዋን አዳራሹ ውስጥ መንበር ላይ ሳይ ግራ ገባኝ ። በየክፍሉ ፈልጌ ሳጣት ወደ ጎጆው ሄዳ ነው ብዬ ገመትኩ ። ይህን ብጥልጥል የድብብቆሽ ኑሮ ፡ ይህን በሸፍጥ ላይ የተመሰረተ ትዳር ላንዴም ለሁሌም ማፍረስ አለብኝ የሚል ቁርጠኛ ፍላጐት አደረብኝ ። ሁለተኛ እንዳያሞክሩት እርሷንም ሰውዬዋንም ማስፈራራት ነው ብዬ ሽጉጤን ይዤ ወጣሁ — ሹልክ ብዬ እንደገባሁ ሹልክ ብዬ ።

"የጎጆውን በር በርግጂ ስገባ ያልጠበቅኩትን ነው የገጠመኝ ። ርብቃ ብቻዋን ሶፋው ላይ ተንጋላ አገኘኋት ። አጠገቧ የነበረው መኮስተሪያ በኩስታራና በአመድ ተሞልቷል ። መልኳ ተቀያይሯል ። በሽተኛ ትመስላለች ። ሌላ ነገር ሳላነሳ በቀጥታ 'እኔና አንቺ እስካሁን ያሳላፍነው አሳፋሪ ኑሮ የበቃን መሰለኝ ። ይገባሻል ? ከፈቭልም ጋር ሆነ ከፈለግሽው ሰው ጋር እዚያው ለንደንሽ ውስጥ እንዳሻሽ ልትሆኚ

t.me/OLDBOOKSPDF

ትችያለሽ — ኑሮሽንም መመስረት ብትፈልጊ ። እዚህ ማንደርሱይ ሙሽዋ ግን እያታለምም ብዬ ደጋግሚ ነግሬሻለሁ' ስላት ዝም ብላ ስታዳምጠኝ ቆየችና ትክ ብላ እያየችኝ የውሽት ጥርሷን ብልጭ አድርጋ ' ፍላጐቱ እዚህ መኖር ከሆነስ?'አለችኝ ።

"በብልጣብልጥ ምላስሽ ሸብበሽኝ ፡ እስክ ዛሬ ስታጭበረብሪኝ የኖርሽው ይበቃሻል ። ቤቱን እንዳሻሽ የምትፈነጪበት በረት ልታደር ጊው የምትችዪ መስሎሽ ይሆናል ። አትችይም ፡ አትችይም ፡ በቃ ። ርብቃ፡ ይገባሽ እንደሆነ ፡ እግዚአብሔር በሚያውቅብኝ ከሚገባ በላይ ነው የታገስኩሽ ። ዛሬ ግን የመጨረሻ እድልሽ ነው' አልኳት ።

"ሲጋራዋን መኮስተሪያው ላይ ጣል አድርጋ ብድግ አለች ። እጆቿን ዘርግታ ተንጠራራችና 'እውነትህን ነው ማክስ ፡ አዲስ ህይወት የምጀምርበት ጊዜ ተቃርቧል'አለችኝ ። እጆቿን ሱሪዋ ኪስ ውስጥ አድርጋ ስትንጎራደድ ደሜን አፈላችው ።'ለመሆኑ ፍች ፈልገህ በፍርድ ቤት ብትከሰኝ ምንም ማስረጃ ልታቀርብብኝ እንደማትችል አስበህበት ታውቃለህ? ጓደኞችህ ሁሉ ፡ ሠራተኞቻችን ሳይቀሩ ትዳራችን ምንም እንከን የሌለበት አድርገው እንደሚያዩት ሳያገባህ የሚቀር አይመስለኝም ።" አለችኝ ።

"ፍራንክም የሚለው የለውም ? ቢያትሪስስ ? ስል ጠየቅኳት ።

"ከትከት ብላ ሳቀችና 'ፍራንክ? ምን ብሎ ሊመስክርብኝ? እኔ ነኝና ልጅት! የፈለገውን ቢል እኔ እርሱን መጻፏም ሊያቅተኝ? አይ የሰው ልክ አለማወቅ? ቢያትሪስስ ብትሆን የምትናገርበት ምን አፍ አላትና? ባሉ ተጀጅሎ ሀሊናውን ሲስት ስለተቀማሁ በቅናት በማኾለሁ ብላ አፍን ሞልታ ችሎት ልትቀርብ? ተው አትሳሳት ማክሲም ። በፍለጋ ብቻ እድሚህን ትጨርስ እንደሆነ እንጂ አንድም ምስክር ልታገኝ አትችልም። ካለችኝ በኋላ ቁማ ታስተውለኝ ጀመር ። እጇን ከኪሷ ሳታወጣ ፡ እቆመችበት እየተወራገረገች ትስቃለች ።

"'ለመሆኑ' ብላ ቀጠለች 'ዳኒን የኔ ምስክር አድርጌ ባቀርባት በየትኛውም ችሎት ላይ እኔ የጠየቅኳትን ሁሉ ልትመስክርልኝ እንደምትችል አታውቅም? ሌሎች ሠራተኞች ሁሉ እርሷን በሚፍን እንደሚከተሉና እንደሚመሰክሩልኝስ?'"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ጠረጴዛው ላይ ተቀምጣ እግሮቿን እያወዛወዘች 'አገር ሁሉ በፍቅር የተሳሰርን ባልና ሚስት መሆናችንን እየመሰከረ አንተ እንዴት አድርገህ ነው የምታስተባብለው? ማንም ሊያምንህ እንደማይችል እያወቅሽው? ይልቅስ እኔና ዳኒ መሳቂያ መሳለቂያ እንዳናደርግህ።' አለችና ከጠረጴዛው ላይ ፈንጠር ብላ ወርዳ ከፊቴ ተገተረች። 'አየህ ማክስ፡ ልጅ ብወልድ እንኳን ያንተ አይደለም ብሎ ማሳመን የሚችል አንድም ሰው እንደሌለ፡ አንተም ብትሆን እንደማትችል አታውቅም? በስምህ እየተጠራ እዚሁ ማንደርሌይ ሲኖር አመንክም አላመንክ ከመቀበል ሌላ አማራጭ የለህም። ስትሞትም ማንደርሌይን የሚረከብ ወራሽ ነው የሚሆነው። ምንም ማድረግ አትችልም። እንዲህ ከመጠን በላይ ለምትወደው ማንደርሌይ ወራሽ ማግኘቱ እድሜ ልክህን የምታልመው ነገር ስለነበረ በጣም ደስ እንደሚልህ እርግጠኛ ነኝ። ታየኝ፡ ልጇ በህፃን ተሽከርካሪው ሆኖ መናፈሻው ውስጥ ሲጫወት ስታየው ምን ያህል እንደምትደሰት። እያደገ ሲሄድ፡ መስኩ ላይ ሲፈነጭ፡ ፍስሐ ሸለቆ ውስጥ ከቢራቢሮዎች ጋር ሲሯሯጥ። ስማኝ እንጂ ማክስ? ልጇ ቀን በቀን እያደገ ሲሄድ ማየት፡ ስትሞት ደግሞ ወራሽህ እንደሚሆን ማወቅ የህይወትህ አብይ ደስታ አይደለም እንዴ?' አለችኝና ንግግሯን አቋርጣ ጥቂት ከተውረገረገችብኝ በኋላ ሲጋራዋን አቀጣጥላ ወደ መስኩ ሄደች። ከትከት ብላ ትስቃለች። ማቆሚያም የሌለው ሳቅ እያልኩ ሳስብ ድንገት ሳቋን ገታችውና 'ጉድ እኮ ነው! ከጉድም ጉድ ድንቅ እንጂ! አዲስ ህይወት የምጀምርበት ጊዜ ተቃርቧል ያልኩበት ምክንያት ምን እንደሆነ አውን ሳትገነዘብ የቀረህ አይመስለኝም። መቼም የአካባቢው ነዋሪ ሁሉ ምን ያህል እንደሚደሰት ይታየኛል "እንኳን ደስ ያልዎት ሚስዝ ደዊንተር፡ ይህን ቀን ስንጠብቀው ነበር እኮ" እንደሚሉኝ እርግጠኛ ነኝ። ጥሩ የቤት እመቤት እድርገው እንደሚያዩኝ ሁሉ እንደ ጥሩ እናት እንደሚቆጥሩኝ አልጠራጠርም አሊች።

"ብጣን አልኩኝ። ውስጥ አንጀቱ አረረ። ከመርዛማ ምላስ ተንኳሽ አይኖቿ፡ ከአይኖቿ አሽሚጣጭ ጥርሶቿ፡ ከጥርሶቿ አሿፊ የአካል ንቅናቄዋ — ሁሉም አታወጡኝ። አንድ እጇን ከኪሷ ሳታወጣ በሌላው እጇ ሲጋራዋን እንደያዘች ሆር ብላ አይታኝ ስትገለፍጥ ትእግስቱ ተሟጠጠ። ሽጉጤን አነሳው፡ ለልባ አለምኩ። ልትደነግጥ ነው? ወይ

t.me/OLDBOOKSPDF

ፍንክች ! ወይ ንቅንቅ! ቃሉውን ሳብኩት ። ጥይቱ ልቧን ነድሎ ቢወጣም ወዲያው አልወደቀችም ። እንደቆመች…እንደሳቀች … አይኗን እንዳጉረጠረጠች…"

የማክሲም ድምፅ እየደከመ ሄዶ ሞራሽ ሹክሹክታ ሆነ ። እጆቹ ቀዘቀዙብኝ ። አይኑን ማየት ፈርቼ አይኔን ወደ ሌላ ስለው ከጎኔ ተጋድሞ ያንጉላጅ ከነበረው ጃስፐር ላይ አረፈ ።

"ሰው በጥይት ሲመታ ብዙ ደም እንደሚፈሰው ረስቼ ነበር ። እንደጎርፍ የወረደውን ደሟን ለማጠብ ውሀ ፍለጋ ወደ ባህሩ ወረድኩ ። የተበከለውን አካባቢ ሁሉ በደንብ እስካወዳ ውሀ ማመላለሱ ብቻ ጊዜ ፈጀብኝ ። ምንም አይነት የደም ምልክት አለመኖሩን ካረጋገጥኩ በኋላ ሬሳዋን ተሸክሜ ጀልባዋ ውስጥ አኖርኩት ። ጊዜው ወደ ምሽቱ ስድስት ሰአት ከመቃረቡም በላይ ድፍን ያለ ጨለማ ነበር ። ንፋሱ ፡ ሞገዱ አይነሳ…" በማለት ማክሲም ሁሉንም ነገር በዝርዝር አስረዳኝ ። የርብቃን ሬሳ ከጀልባዋ ማረፊያ ክፍል እንዴት እንዳሳረፈው… ጀልባዋን ራቅ አድርጎ እንደወሰዳት … የውሀ መቆጣጠሪያውን ከፍቶ ውሀ ወደ ውስጥ እንዲገባ እንዳደረገ … ጀልባዋ ቀስ በቀስ በቋጥኞች መሃል ሰጥማ እንደቀረች … ሁሉን ፈፅሞ ወደ ጎጆው ተመልሶ ምንም አይነት አሻራ እንደሌለ እንዳረጋገጠ… ጎጆው ሲያርስ ዝናብ መጣል እንደጀመረ… ሁሉንም ነገረኝ ።

"… ይኸው ነው እንግዲህ ፡ እስከ ዛሬ አምቼ ይዠው ስብሰለሰል በት የነበረ ምስጢር" አለ ማክሲም ትረካውን እያጠቃለለ ። "…ወይቤቱ ገብቼ ልብሴን ሳወላልቅ ሀይለኛ ነፋስ ይነፍስ ነበር ። ዝናቡም እያየለ ሄደ። አልጋዬ ላይ እንደተቀመጥኩ ሚስዝ ዳንቨርስ መጣችና የርብቃ ነገር እንዳሳሰባት ነገረችኝ ። ምንም እንዳታስብና ሂዳ እንድትተኛ ነገርኳት …"

በመካከላችን ፀጥታ ሰፈነ ። የቀዘቀዙ እጆቹን እንደያዝኩ በትካዜ ተዋጥኩ ። "አየሽ" አለኝ ማክሲም "ጀልባዋን እኩ ራቅ አድርጌ ላሰጥማት ነበረ ፡ አልቻልኩም እንጂ ። ወዲህ ቀረብ በማለቷ ነው እንጂ ማንም አያገኛትም ነበር ።"

"ይሄ የተረገመ መርከብ ሲንቀዠቀዥ መጥቶ እዚህ ባይሰናከል ኖሮ ጀልባዋ በፍፁም አትገኝም ነበር" አልኩት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ወዲህ ቀረብ ማለታ ነው..." ሲል ደገመ ማክሲም

ለጥቂት ሲኮንዶች ዝም ዝም ካልን በኋላ "እንድ ቀኝ ግን ይህ ሁኔታ ሊፈፀም እንደሚችል ይታየኝ ነበር" አለ ማክሲም "ኤጅኮምብ ሄጂ ያ ራሳ የርሷ ነው ብዬ ካረጋገጥኩ በኋላ እንኳን ምንም የህሊና እረፍት አልነበረኝም ። ርብቃ አንድ ቀን ድል እንደምታደርግ አውቅ ነበር ። እየሳቀች መሞቷ አንድ ቀን እንደምትረታ ቢታወቃት አይደል? አንቺን ግግኙቱ ፡ አንቺን ማፍቀሬ ምንም አልጠቀመኝ — ከዚህ ሞንቀት መች ገላገለኝና?!"

"ርብቃ እኮ ሙታለች ። ከእንግዲህ እርሷ ልትናገር አትችልም ። ልትመሰክርብህ አትችልም ። ይህንን ነው መግንዘብ ያለብን" አልኩት ።

"እርሷ ባትናገር ራሳዋ ይናገራል ። ጀልባዋ ውስጥ እንዳተጋደመ ዋናተኛው አያቶት የለም እንዴ?"

"ሌላ ዘዴ መቀየስ አለብና ። ራሳው የእርሷ ሳይሆን ፊዕሞ አይተኸው የማታውቀው የሌላ ሰው ራሳ ነው ብትልስ?"

"አይ ያንቺ ነገር ። ልብሷ ተበጣጥሶ አልቂል ብንል እንኳን ጌጣጌጦቿ ቁልጭ ብለው ይታዩ የለም እንዴ? ራሳዋስ ቢሆን እስከዛሬ ማንም ስላልያረሰበት እንዳስቀመጥኩት ሊገኝ ይችላል"

"ማንም ባያያርስበትስ ራሳ ይህን ያህል ጊዜ ሳያፈራርስ ውሀ ውስጥ ይቆያል እንዴ?"

"እኔ እንጃ ፡ እኔ እንጃ" አለ ማክሲም ሞንቅላቱን እየነቀነቀ ።

"ታዲያ እንዴት ነው የምታጣራው?"

"እንግዲህ ነገ ማለዳ በአስራ አንድ ከሰላሳ ባህር ጠለቁ ዋናተኛ ጀልባዋን ለማንቀሳቀስ ስለሚሞክር ካፕቴን ሲርል አብረን እንሄዳለን ብሎኛል ።"

"ጀልባዋንስ ያንሷት ፡ ከዚያስ?"

"ካፕቴን ሲርል እንደነገረኝ ከሆነ የጀልባዋ እንጨት ካልፈራረሰ ቀስ አድርገው አውጥተዋት በሌላ ተሽካሚ ጀልባ ሞነው ወደ ኬሪዝ ሊወስዷት አስበዋል ። ከዚያም በኋላ ራሳውን ዶክተር ይመረምረዋል ብሎኛል ።"

"የዶክተሩ ውጤት ምን የሚሆን ይመስልሃል?"

"ምን አባቱ አውቂ"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንግዲያው ይኸውልህ ፡ ይህ ራሳ የርብቃ መሆኑን ካረጋገጡ ያኛው ራሳ የርብቃ ነው ያልከው በስህተት እንደሆነ ማስረዳት አለብህ ። ያኔ ኤጅኮምብ በሄድክበት ጊዜ ክፉኛ በመታመምህ ሚንቅላትህ ትክክል እንዳልነበረ ፡ ምኑንም ማስታወስ እንደማትችልና በዚያን ወቅትም ቢሆን እርግጠኛ እንዳልነበርክ ማሳመን ነው ያለብህ ። በቃ ፡ በስህተት ነው በላቸው ። አሁን እንዳልኩህ ትነግራቸዋለህ አይደል?"

"እስቲ ፡ መናገሩ ከጠቀመ እናገራለሁ"

"ታዲያ ምንድነው ሚንቲ? የዚያኔ ማንም ስላላየህ አንድም ሰው ሊመሰክርብህ አይችልም ። ከእኔና ካንተ ሌላ ምስጢሩን የሚያውቅ ማን አለና? ፍራንክ እንኳን አያውቅም ። ስማኝ እንጂ ማክሲምዬ እኔና አንተ ብቻ ነን እኮ የምናውቀው ።"

"አዎን"

"ሰዎቹ ሊሉት የሚችሉት ርብቃ የሰጠሟቸው ጅልባዋ ሞገድ አናግቶት በመገልበጡ ነው እንጂ ሌላ ምን ሊሉ? አይደለም እንዴ ማክሲም?"

"እኔ እንጂ" አለ ማክሲም "እኔ እንጂ"

ወዲያው ከዚተ መሣሀፍቱ በስተጀርባ ከሚገኘው ክፍል ውስጥ ቴሌፎኑ ጮኸ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ ሀያ

ማክሲም ታሪኩን እያወራልኝ አጠገቡ ቁጭ ብዬ ሳዳምጠው ሁለት ስሜቶች ያፈራረቁብኝ ነበር ። በአንድ ወገን ለማክሲም የነበረኝ ፍቅር ሀዘኑን እንዳዝን ፡ ብስጭቱን እንድበሳጭ እየገፋፋኝ በርቀታ ሚድያ ጀልባዋን በማስጠመሙ የኔም እጅ የነበረበት መስሎ ታየኝ ። በእያንዳንዱ እንቅስቃሴ እራሴን ከጎኑ አሰልፈ የቅጠሉ ኮሽታ ፡ የንፋሱ ሽውሽውታ ፡ የሞገዱ ድንፋታ ፡ የሉሎችም ድርጊቶች ሁኔታ ያሰማኝ ነበር ። በሌላ ወገን ደግሞ ምንጣፍ ላይ ኩርምት እንዳልኩ አእምሮዬን ያጎነትለውና ደጋግሚ አሰላስለው የነበረ አንድ ሀሣብ ነበር ‘‘ማክሲም ርብቃን እያወዳትም’’ የሚለውን ።

የቱሉዚኑ ድምፅ ግን እነዚህን ሁለት ስሜቶች ፈጽፍሎ አንድ አረጋቸው ። ወደ ቀድሞው እኔነቱ መለሰኝ ። ያውንና ከዚህ ቀደም የማያውቀኝ ፡ የማላውቀው ስሜት አደረብኝ ። ከእንግዲህ ርብቃን አልፈራትም ፡ አልጠላትም ያሰኘኝ ጅመር ። እንዲህ ርኩስ ፡ መሰሪና ከንቱ መሆኗን እያወቅኩ እርሷን የምፈራበት ፡ እርሷን የምጠላበት ምክንያት አይኖርም ። ከእንግዲህ ልትጎዳኝ አትችልም ። በእንቅልፍ እያላነጋችኝ ፡ በቱም እያታገቸኝ ፡ ስቆም እየቆመች ፡ ስተመጥ እየተተመጠች ፡ ስሄድ እየተከተለችኝ የቱም ስቅሉን ስታሳየኝ መኖሯ አበቃ ። የእስከዛሬው መሸማቀቁ ፡ በስጋት መዋጡ አክትሚልና ከእንግዲህ የእርሷ በነበሩ ቁሳቁሶችና መገልገያዎቿ ነፃ ሆኜ መጠቀም እችላለሁ ። ራሳዋ ታታያቶ ፡ ትንቢት እንድትናገር ሆን ተብሎ የታተደ ይመስል ‘ዝ— ረቪያ’ (እመለሳለሁ) በማለት በፈረንሳይኛ የተሰየመችው

t.me/OLDBOOKSPDF

ጀልባዋ ተገኝታ ልፈራት አይገባም ።

ከእንግዲህ ከማክሲም ጋር ሆኜ እጅጉን ለመያዝ ፣ ገላውን በገላዬ ለመዳሰስ ፣ ፍቅሬን ሰጥቼው ፍቅሩን ለመቀበል ሙሉ ነፃነት አለኝ ። እኔ ማለት አብቅቷል ። በእኛ ተተክቷልና ። አንድ አካል ፣ አንድ እምሳልነታችንን ገሀድ የሚያወጣ አዲስ ዘመን ተወልዷልና ። ይህንን አንድነታችን ካጥፋን ሲርልም ሆኑ ዋናተኛው ፣ ፍራንክም ሆነ ሚስዝ ዳንቨርስ ፣ ቢያትሪስም ሆኑ ማንኛውም ፍጡር ሊያናጋው አይችልም ። ዛሬ ልጅነቱን ጨርሻለው ። ከአያናፋርነት ፀድቻለሁ ፣ ከፍርሀት ነፅቻለሁ። ከማክሲም ጎን ቆሚ እስከመሆኔ ረሻው እፋለምለታለሁ ። ምዬም ሆነ ተገዝቼ ፣ ክጀም ሆነ ቀጥፌ ነፃ ላወጣው ቆርጫለሁ ። ታዲያ ማክሲም እንዳለኝ ርብታ በምኗ ነው ድል የምታደርገው? ሽንፈቷ ነው የሚሸተኝ ፣ ውድቀቷ ነው የሚታየኝ ። የሚል በቱርጠኝነት ላይ የተመሰረተ ፣ በፅኑ እምነት የታነፀ ብርቱ ስሜት አደረብኝ ።

ይህን ሀሣብ በሞንቅላቱ ውስጥ ሳወጣና ሳወርድ ማክሲም ተመልሶ መጥቶ ቱሌርኑን የደወሉት የኬሪዝ አጥቢያ ዳኛ እንደነበሩና በማግስቱ የጀልባዋን ሁኔታ ለመመልከት አብረዋቸው እንደሚሄዱ ነገረኝ ። ዳኛው ባቀረቡለት ጥያቄ መሠረት የተገኘው ራሳ የማን እንደሆነ እንደማያውቅ ፣ ሁሉም እስከሚያውቀው ድረስ ርብታ ጀልባዋ ውስጥ ብቻዋን እንደነበረች ሲነግራቸው "ታዲያ የኤጅኮምቡ የማረጋገጫ ታልም በስህተት የተደረገ ነዋ?" ብለው እንደጠየቁት ነገረኝ ። "ዳኛው እንዲህ አለህ? እንዲህ ብለው ጠየቁህ?" አልኩት ።

"አዎን" አለኝ ማክሲም ቀዘቀዝ ብሎ

"ታዲያ እንተስ ምን አልካቸው?"

"እኔ እንጃ ፣ ሊሆን ይችላል አልኳቸው"

"እንግዲያው ነገ ጠዋት የምትሄዱት አንተ ፣ ዳኛው ፣ ካፕቴን ሲርልና አንድ ዶክተር መሆናችሁ ነዋ?"

"የፖሊስ መኮንኑ ፣ እንስፔክተር ዊልችም ይኖራል።"

"እንስፔክተር ዊልች? እርሱ ደግሞ ምን ያደርጋል?"

"ራሣ ሲመረመር አንድ የፖሊስ መኮንን እንዲገኝ ደንቡ ስለሚያዝ ነው " ዝም አልኩ ። አይን ለአይን ተያየን ። ሆዴን ባር ባር አለው ። ጀልባዋን ለማንሣት እንደማይችሉ ከተነጋገርን በኋላ ማክሲም በመስኮቱ

t.me/OLDBOOKSPDF

በኩል ድጅ ደጅን እያየ ‘‘ጥቂት ቀደም ሲል ንፋሱ ከደቡባዊ ምዕራብ አቅጣጫ ይነፍሳል ብዬ ነበር። ሜሪሽን ወጥ፣ አረሜ አለ እኮ’’ አለኝ ።

‘‘አምን ልጄ’’ ስለው

‘‘ታዲያ እኮ ጥሩ አይደለም ። ነገ ዋናተኛው ምንም ችግር አይገጥመውም ማለት ነው’’ እንዳለኝ ቱሴርኑ በድጋሚ ጮኸና ማክሲም ትኩኝ ወጣ ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ተመለሰና ‘‘አላልኩሽም? የፈራውት ደረሰ’’ አለኝ ።

ድንገተኛ ቅዝቃዜ መላ አካሉን ወረረው ‘‘ምነው? ምን ተፈጠረ?’’ አልኩት ።

‘‘አንድ ‘የካውንቲ ከሮኒክል’ ጋዜጣ ጋዜጠኛ ነው ። ‘የሚስዝ ዩዊንተር ጀልባ ተገንቺ የሚባለው እውነት ነው ወይ?’ ሲል ጠየቀኝ’’

‘‘እና? ምን አልከው?’’

‘‘ጀልባ መገንቱን ተገንዝቧል ። እስካውን ግን የማን ጀልባ እንደሆነ በውል ያወቅነው ነገር የለም ። የእርሷ ጀልባ ላይሆንም ይችላል አልኩት’’

‘‘በቃ ፡ ይህን ብቻ ነው የጠየቀህ?’’

‘‘አይ ፡ አንድ ፈሳ ተገንዝቧል ስለሚለው መፈ አስተያየት እንዳለኝ ጠየቀኝ’’

‘‘ኧረ እባክህ!’’

‘‘እውነቱን ነው ። አንዴ ተንሳሶ ሊሆን ይችላል ። ሲርል እንደማያሆን ግን እርግጠኛ ነኝ ። ያን ዋናተኛ ወይም ዋኒኛቹን ነው የምጠረጥረው ። ያህ ህዝብ እኮ ሰው እንዳይመስልሽ ። በፍፁም ልትቆጣጠሪው አትችዪም ። ታያለሽ እንግዲህ ፡ ነገ ገና በማለዳው መፈው አገር ምድሩን ነው የሚያጥለቀለቀው ።’’

‘‘የሆነስ ሆነና ስለ ፈሳው ምን ስትል መለስክለት?’’

‘‘የማወቀው ነገር የለምና ምንም አስተያየት የለኝም ብዬው ያህን በሚመለከት በድጋሚ ያውለው ባያጠያቀኝ ደስ እንደሚለኝ ነገርኩት ።’’

‘‘ይበልጥ አበሳጭተሃቸው ይሆም እልህ ውስጥ እንዳታስገባቸው።’’

‘‘ምንም ምርጫ የለኝማ ። የማንም ጋዜጠኛ እየደወለ በነዘነዘኝ ቁጥር ከእርሱ ጋር አፍ ልካፈት ነው እንዴ?’’

‘‘እንደዚህ አይደለም እኮ ማክሲምዬ ። ልንጠቀምባቸው እንችል ይሆናል እኮ’’

t.me/OLDBOOKSPDF

"መታገል ካለብኝ ብቻዬን አወጣዋለሁ እንጂ የማንንም ጋዜጠኛ ድጋፍ አልሻም"

"ጋዜጠኛው ኮሎኔል ጁሊያንን ወይም ካፕቴን ሲርልን ይሁሉ ቢጠይቅስ?"

"ይጠይቃ ፡ ከዚህ የተለየ ምንም መልስ ሊያገኝ አይችልም ።"

"ይህን ያህል ረጅም ጊዜ እያለን እስከ ነገ ዝም ብለን እጃችንን አጣምረን ልንቀመጥ ነው? ምንም የምናደርገው ሙከራ የለም ማለት ነው?" በማለት ጠየቅኩት ።

"ምንም ማድረግ አንችልም ፡ እባክሽ" አለኝ ማክሲም ተስፋ በቆረጠ አነጋገር ።

እዚያው ቤተ መፃህፍቱ ውስጥ እንደተቀመጥን ቆየን ። ማክሲም መፅሀፍ አንስቶ ያገላብጣል ። እንደማያነበው ግን እርግጠኛ ነበርኩ ። ቴሌፎኑ የተደወለ እየመሰለው ድጋግሞ ጆሮውን ጣል እያደረገ ያዳም ጣል። የእራት ሰአት ሲደርስ ምግብ ቤት ሄደን እንደ ነገሩ ተማመስንና ወደ ቤተ መፃህፍቱ ተመለስን ።

ማክሲም ወንበር ላይ ሲቀመጥ እኔ እግሩ ስር ሆኜ ጭንቅላቱን ጉልበቱ ላይ አሳረፍኩት ። ፀጉሬን ሲያሻሸኝ አንዳች ልዩ ስሜት አጫረብኝ ። ጣቶቹ ፀጉሬን እየፈለፈሉ የራስ ቅሌን ሲነካኩ እንደ አንድ ነገር ነዘረኝ ። ከዚህ ቀደም እንዲህ ባሻሸኝ ቁጥር እራሴን እንደ ጀስፐር እቆጥረው እንዳልነበረ የዛሬው የማክሲም ዳሰሳ ግን እኔነቴን አስገነዘበኝ። አልፎ አልፎ ሲስመኝና አንዳንድ ቃላት ጣል ሲያደርግልኝ በደስታ አሰከረኝ ። እፊት ለፊታችን ጨለማ የሞጠው ዓለም ተደቅኖብን እያለ እንዲያ ለመደሰት መቻሌ በእጅጉ ገረመኝ ።

ሉሊቱ በሰላም አለፈ ።

በማግስቱ ብንን ስል ማክሲም ከጎኔ የለም ። ከንጋቱ አንድ ሰአት ሆኗል ። ማክሲም ሳይቀሰቅሰኝ ሹልክ ብሎ ሄዷል ብዬ ገመትኩ ። ጀልባዋን ለማውጣት የሚያረገውን ጥረት በአይነ ህሊናዬ ሳሰላስል ቆየሁ።

ከአልጋዬ ወርጄ ፡ ገላዬን ተጣጥቤ ለቁርስ ቀረብኩ — በተለመደው ሰአት — በሦስት ። ጠረጴዛው ላይ በርካታ ደብዳቤዎች ተቀምጠዋል ። አድርገነው ለነበረ ግብግ ተጋባዦች ምስጋናቸውን ያቀረቡባቸው ነበሩ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ገረፍ ገረፍ አደረግኳቸው ። ፍሪዝ መጡና ለማክሲም ቁርስ ይዘጋጅለት እንደሆነ ሲጠይቁኝ ለስራ ጉዳይ ማልዶ እንደወጣና የመመለሻው ጊዜም እንደማይታወቅ ነገርኳቸው ። የፍሪዝ ቅዝቀዝ ማለትና መኮሳተር የሚያውቁት ነገር ይኖር ይሆን? የሚል ጥርጣሬ አሳደረብኝ ።

ከቁርስ በኋላ ወደ እንግዳ ማረፊያው ሄድኩ ። ክፍሉ ወና ወና ይላል። የተዘጉትን መስኮቶች ከፈትኳቸው ። አበቦቹ ጠውልገዋል ፣ ወለሉ ቆሽሿል ። መጥሪያውን ነካሁና ሞውድ የምትባለዋ ሠራተኛ ስትመጣ ''ምንድነው እንቺ? ዛሬ ይህንን ክፍል ሼራሽን ዞር ብላችሁም አላያችሁት? ቤቱ አልተጠረገ ፣ መስኮቶቹ አልተከፈቱ ፣ ምንድነው ይህ ሁሉ መዝረክረክ?'' አልኳት ።

ድንግጥ አለች ። ''ይቅርታ እሜትዬ'' ብላ እየተርበተበተች የአበቦችን ማስቀመጫዎች አነሳቻቸው ።

''እንዲህ አይነቱን መዝረክረክ ሁለተኛ እንዳላይ'' ስላት ''እሺ የኔ እመቤት'' ብላኝ ወጣች ።

ለካስ ሀይለኛ መሆን እንዲህ ቀላል ሆኖ ሳለ ነው እስከዛሬ ይህን ያህል የተጨነቅኩት? ብዬ አሰብኩ ። የእለቱን የምግብ ዝርዝር ጠረጴዛው ላይ ሳየው ለግብጣው ተዘጋጅቶ ከነበረው ጋር መመሳሰሉን ተገነዘብኩ ። ሮበርትን ጠርቼ ''ሚስዝ ዳንቨርስን የሰሞኑ ምግብ አላልቅ ብሎዎት ከሆነ የሚያደርጉትን ያድርጉ እንጂ ይህንን ዝርዝር አልተቀበልኩትም ብላለች በላቸው'' አልኩት ።

ሮበርት ትእዛዜን ተቀብሎ ሲወጣ ተከትዬው ወጣሁ ። ወደ መኖሪያው ሄጄ ዕጌራዎች እየቆረጥኩ ሳለ ማክሲም እንዴት ሆኖ ይሆን? የሚለው ሀሳብ በአእምሮዬ ተጉላላ ። የሆነውን ሁሉ ቶሎ መጥቶ እንዲነግረኝ ቸኮልኩ ። አበቦችን ይዤ ስመለስ የእንግዳ ማረፊያ ክፍሉ በሚገባ ፀድቶ ጠበቀኝ ። አበቦችን በመልክ በመልካቸው አደራጅቼ እንደጨረስኩ በሩ ተንኳኳ ።

''ይግቡ'' አልኩ ።

ሚስዝ ዳንቨርስ የምግቡን ዝርዝር ይዘው ገቡ ። ገርጥተዋል ፣ ድካም የተጫጫናቸው ይመስላሉ ። ''ምነው የምግቡን ዝርዝርና መልእክቱን በሮበርት የላኩልኝ?'' ብለው ሲጠይቁኝ በእጄ የያዝኩትን ዕጌራዎ እያፍተለተልኩ ባይኔ ቲጥ አየኋቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምግብ ጠፍቶ ነው እንዴ ይህን እየደጋገሙ የሚያሰለቹን? ዛሬ ለውጥ ያስፈልገናል ። ይህንን ሠራተኞቹ አልበላም ብሎምት እንደሆነ ወዲያ አይወረውሩትም እንዴ? እዚህ ቤት ውስጥ ዘወትር የሚባክነውን የምናውቀው ነውና የዛሬው እምብዛም አይጎዳም" አልኳቸው ።

መልስ ሳይሰጡኝ ትኩር ብለው ያዩኛል ። "ሌላ የማዘጋጀው ነገር የለም እንዳይሉኝ ብቻ ። ሁሉ ነገር ሞልቶ ተትረፍርፎ ? ምን ጠፋና ?" ስላቸው "በእድሜዬ ገጥሞኝ የማያውቀው በሮበርት በኩል መልእክት ሲላክብኝ ገርሞኝ ነው ። ሚስዝ ደዊንተር በነበረችበት ወቅት የምትፈልገውን ነገር ሁሉ በውስጥ ለውስጥ ቴሌፎን ነበር የምታንጋግረኝ።" አሉ ።

"እኔ እርሷን አይደለሁምና እርሷ ታደርገው ለነበረ ሁሉ ደንታዬም አይደል ። ባለንበት ወቅት ሚስዝ ደዊንተር ማለት እኔ እንደሆንኩ ሊዘነጉት አይገባም ። መልእክቱን በሮበርት በኩል ማስተላለፍ ከፈለግኩ ምንም የሚያግደኝ ነገር የለም ።" እንዳልኩ ሮበርት ገባና "ቴሌፎን እሜቴ ፡ ከካውንቲ ክሮኒክል ጋዜጣ" አለ ።

"የለችም በል" ብዬ ሮበርትን ሸኘሁት ።

ወደ ሚስዝ ዳንቨርስ መለስ አልኩና "እሺ ? ሚስዝ ዳንቨርስ ፡ ሌላ የሚሉት ነገር አለዎት ?" በማለት ብጠይቃቸው ዝም ብለው አይን አይኔን ሲያዩ "እንግዲያው ብዙ ስራ ስለሚጠብቀኝ ሂደው ወጥ ቤት ልዩ ምግብ እንድታዘጋጅ ይንገሯት" አልኳቸው ።

"ለመሆኑ የጋዜጣው ክፍል ለምንድነው የሚፈልግዎ ?" ሲሉ ድንገተኛ ጥያቄ አቀረቡልኝ ።

"ምንም የማውቀው ነገር የለም"

"የሚስዝ ደዊንተር ጀልባ ተገኘች የሚለው ወሬ እውነት ነው እንዴ ? ፍሪዝ ከኬሪዝ ሰማሁ ብሎ ነው ያጫወተኝ ።"

"እንዲህም የሚል ወሬ አለ ? እኔ በጭራሽ አልሰማሁም"

"ካፕቴን ሲርል ትናንት እዚህ መጥተው ነበር ብሎ ሮበርት ነገረኝ። ፍሪዝ እንደሚለው ደግሞ የኬሪዝ ህዝብ የሚያወራው የሚስዝ ደዊንተርን ጀልባ ያገኘው አንድ ባህር ጠለቅ ዋናተኛ ነው እያለ ነው ።"

"እኔ እንጃ ፡ ይሆን ይሆናል ። ሚስተር ደዊንተር ሲመጣ ቢጠይቁት ይሻላል"

"እንዲያውም ስማቸውን ሲያነሱ የረሳሁት ነገር ትዝ አለኝ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ለመሆኑ ጌቶች ምን ቢገጥማቸው ነው እንዲህ በማለዳ የወጡት ?"

"እኔ ምን አውቄ ? ስራ ቢኖረው ይሆናላ"

አሮጊቷ አይናቸውን ከአይኔ ሳይነቅሉ ጥያቄያቸውን አከታተሉ ብኝ ።

"እረ ሰው የሚያወራው ሌላ ነው ። ጀልባዋ ውስጥ የሰው ሬሳ ተገኝቷልም ይባላል ። ሚስዝ ደዊንተር ብቻዋን እንደነበረች ሁሉም እያወቀው የተገኘው የማን ሬሳ እንደሆነ ሊገባኝ አልቻለም"

"ይሰሙኛል ሚስዝ ዳንቨርስ ? እኔ ከእርስዎ የበለጠ ምንም የማውቀው ነገር ስለሌለ ምነው ባያያርቁኝ ?" አልኳቸው ።

ሚስዝ ዳንቨርስ ዝግ ባለ ድምፅ "እውነት አያውቁም ?" ብለው እንዳፈጠጡብኝ ሲቀሩ አይናቸውን እየሸሸሁ አበቦችን የማስተካከል መስዬ አንዱን የአበባ ማስቀመጫ አንስቼ መስኮቱ ላይ አኖርኩት ።

"ይበሉ እንግዲህ ስለ ምሳው ዝግጅት ትእዛዙን ላስተላልፍ" ብለው ጥቂት ከቆሙ በኋላ ከኔ ምላሽ ሲያጡ ትተውኝ ወጡ ። የወጡበትን በር በቁጣ እየተመለከትኩ ከእንግዲህ ይህችን ነገረኛ አሮጊት አልፈራትም ብዬ አሰብኩ ። በእስከዛሬው መሽቆጥቆጤ እራሴን ረገምኩት ። የእሷ ሀይል ከርብቃ ጋር አክትሞለታልና ከእንግዲህ ምንም አታስፈራኝም ። ምንም ያህል ብታውቅ ፡ ያለችውን ብትል ምንም ልትጎዳኝ እንደማትችል ተረዳሁ ። አበቦችን ማሰማመሩን ትቼ ፡ መቀሱን ጠረጴዛ ላይ አስቀምጬ ወንበር ላይ አረፍ አልኩ ። ስራ የሚባል ነገር አስጠላኝ ። እጄ ስራ ቢፈታም አእምሮዬ ግን የሚሰራውን አላጣም ። ስለ ማክሲም ያሰላስላል ። ስለ ካውንቲ ክሮኒክል ጋዜጠኛ የቴሌፎን ጥሪ ያጠነጥናል ። መስኮቱን ያገፍ ብዬ ወደ ውጭ ስመለከት ሀሣቤን ለጊዜው የሚያዘናጋ እይታ ገጠመኝ ። አትክልተኞቹ ሳሩን ሲያጭዱ ተመለከትኳቸው ። አንዱ አትክልተኛ የማጨጃ መሣሪያውን ይዞ መስኩ ላይ እላይ ታች ሲመላለስ አይኔ ለጥቂት ደቂቃዎች ከእርሱ ጋር ሲንከራተት ቆየ ።

መቀመጡ ስልችት ሲለኝ ወደ ሰገነቱ ወጣሁ ። እየሩ ሞቅ ከማለቱም በላይ ነጎድጓዱ ሰማዩን ሲራገጥ ይሰማል ። እንደ መቅበዝበዙ ቢያያርገኝ ወዲያ ወዲህ መንጎራደዱን ተያያዝኩት ። ለሽርሽር ይዤው ባለመውጣቴ ቅሬታ ያደረበት የሚመስለው ጃስፐር ከጎን ጎኔ ሱክ ሱክ ይላል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

አምስት ሰአት ተኩል ግድም ማክሲም በቴሌፎን እንደሚፈልገኝ ፍሪዝ ነገሩኝ ። እጇ እየተንቀጠቀጠ የቴሌፎኑን እጀታ ሳነሳው "ማን ...? አንቺ ነሽ እንዴ ? ... ማክሲም ነኝ ... ቢሮ ነው ያለሁት ... ከፍራንክ ጋር ..." አለኝ ማክሲም ። አያይዛም ጀልባዋን እንዳነሳት ፡ ካኖቱን ሲርል ፡ ኮሎኔል ጄልያንና ፍራንክ አብረውት እንደነበሩ በአጭሩ ከገለፀልኝ በኋላ ኮሎኔል ጄልያንንና ፍራንክን በሰባት ሰአት ለምሣ ይዟቸው እንደሚመጣ ነገረኝ ።

ስለ ሁኔታው ዘርዘር አድርጎ ስላልነገረኝ ጭንቀቱ ሊለቀኝ አልቻለም ። ሰአቱ አልገፋ ቢለኝ ስንቆራጠጥ ፡ ስወጣና ስገባ ፡ ስተመጥና ስነጣ እንደምንም አንዱን ሰአት አነሳሁት ። ልብሴን ቀያይሬ ስጠባበቅ ፡ ለሰባት አምስት ጉዳይ ሲሆን ማክሲም ኮሎኔል ጄልያንንና ፍራንክን አስከትሎ ብቅ አለ ።

እኔና እንግዳው ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ማክሲም የወይን ጠጅ እንዲቀርብልን አዞ ለመተጣጠብ ሲገባ ፍራንክም ተከትሎት ገባ ። የወይን ጠጁ እንደተቀዳልን እንግዳው አልጠጣም ቢሉም እኔ ግን የመጠጡ አምሮት ኖሮኝ ሳይሆን እጇን ስራ ላለማስፈታት ብቻ አንዱን መለኪያ አነሳሁ ።

ኮሎኔል ጄልያን ወደነበርኩበት ጠጋ ብለው "አዩ ሚስዝ ደዊን ተር፡ በእርስዎና በባለቤትዎ ላይ የደረሰው መጥፎ አጋጣሚ ከልብ ነው ያሳዘነኝ" አሉኝ ።

"አመሰግናለሁ" አልኩና ከወይን ጠጁ ቀመስ አድርጌ መለኪያውን ከጠረጴዛው ላይ አኖርኩት ። እጅቼ ሲርገፈገፉ እንግዳው አይተው ይሆን? የሚለው ሀሣብ ሽምቅቅ አደረገኝ ።

"ነገሩን ይበልጥ ውስብስብ የሚያደርገው ባለቤትዎ ከአንድ አመት በፊት ያዩት ሬሳ የእርሷ ነው ብለው ማረጋገጫ መስጠታቸው ነው።" አሉ ኮሎኔል ጄልያን

"ስለምን እንደሚያወሩ ሊገባኝ አልቻለም" አልኳቸው ።

"ዛሬ ጠዋት ምን እንዳገኘን አልሰሙም ማለት ነው ?"

"ባህር ጠለት ዋናተኛው አንድ ሬሳ ማግኘቱን ሰምቻለሁ"

"አዎና" አሉ ኮሎኔል ጄልያን ። ወደኋላቸው ገልመጥ ብለው ከተመለከቱ በኋላ ድምፃቸውን ዝቅ አድርገው ቀጠሉ "ሬሳው እኮ የእርሷ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሆኖ ነው የተገኘው ። አሁን ከእርስዎ ጋር ስለ ነገሩ በስፋት ለመነጋገር አመቺ ባይሆንም ባለቤትዎና ዶክተር ፊሊፕስ ሬሳውን አይተው በሚገባ ማረጋገጣቸውን እ...”

የማክሲምና የፍራንክ መመለስ ኮሎኔል ጅምር ሀሣባቸውን በእንጥ ልጥል እንዲተዉት አስገደዳቸው ። ወዲያው ምሳችንን ለመብላት ወደ ምግብ ቤቱ አመራን ።

እየበላን ልዩ ልዩ ነገሮችን እያነሳን እንጫወት ነበር ። ስለ አየሩ ሁኔታ ፡ ስለ ሰሞኑ ግብግ ፡ ስለ ሌሎች ጉዳዮችም ብንጨዋወትም በሁላችንም አእምሮ ውስጥ ይገላላ የነበረው ሀሣብ ግን አንድና አንድ ብቻ እንደነበር ከማናችንም ሀሊና የተሰወረ አልነበረም ። ሮበርት ወጣ ገባ እያለ አስፈላጊውን ሁሉ ሲያቀራርብልን ፍሪዝ እዚያው ቆመው ያበሉን ነበርና የልባችንን አውጥተን እንዳንነጋገር እንደገታን ግልፅ ነበር። በወቅቱ የፍሪዝ ሀሣብ ከእኛ የተለየ እንዳልነበረ እርግጠኛ ነበርኩ። ጥልቅ ጉዳዮችን በሠራተኞች ፊት አለማንሣት የሚለውን የቆየ ወግ ሽረን ሁሉንም ነገር ፍርጥርጥ አድርገን ብንጫወት ፍቃዴ ነበር ።

ሆኖም እንደጀመርነው እዚህም እዚያም ስንረግጥ ቆይተን ኮሎኔል ጁልያን “ለመሆኑ ሚስዝ ዊንተር ፡ ጎልፍ ይጫወታሉ ?” ሲሉ ጠየቁኝ። እንደማልጫወት ከገለፅኩላቸው በኋላ “የለም ፡ የለም ፡ መማር አለብዎት። ይገርምዎታል ፡ የኔዩቱ የበኩር ልጄ ሜንቅላቷ እንዲህ እንዳይመስ ልዎት ። ግን ምን ያደርጋል ? የሚመስላት ጓደኛ አጣች ። ታዲያ ብልሀኒቷን እያየሁ ብጨዋን አጥታ በብቸኝነት እንዳትቸገር በማሰብ ለልደት በአሏ አንዲት ትንሽ መኪና ሰጠኋት ። ከዚያ በኋላ በየቀኑ ወደ ምእራባዊው ጠረፍ ወጣ እያለች ስለምትመለስ ምንም አትል ።” አሉ ኮሎኔል ኩሩስ ብለው ።

“ጥሩ አድርገዋል” አልኳቸው ።

“ምን ያደርጋል ? እግዜር ተሳሳተብኝ ፡ ወንድ አድርጎ ሊፈጥራት በተገባ ነበር ። ወንዱን ልጄ ብታዩት ደግሞ በምኑም አይስተካከላትም እኮ ።ጨዋታ የሚባል ነገር አንድም የማይጥመው ነፈዙን ምን እንደፈጠረብኝ እኔ እንጃ ! እርሱ ታዲያ ግጥም የሚሉት አባዜ ይዞት ነጋ ጠባ ይጫጭርልኛል ። በዚሁ እንዳያድግበት ነው ስጋቱ”

“እሪ ?” አለ ፍራንክ ተበል አድርጎ “እኔ እራሴ በልጅነቴ ልክ እንደ

t.me/OLDBOOKSPDF

እርሱ ግጥም እዕፍ ነበር ። በከንቱ ጊዜ ማባከን ስለመሰለኝ እርግፍ አድርጊ ተውኩት ።”

“እኔስ ከእንዲህ አይነቱ ዝባዝንኬ ፈጣሪዬ ሰውሮኛል” አለ ማክሲም ።

እንደዚው በሌሎች ርእሰ ጉዳዮች ላይ ስንጨዋወት ከቆየን በኋላ ገበታው ከፍ ብሎ ቡናችንን እያጣጣምን ጠጣን ። ሮበርትና ፍሪዛ እቃዎችን አነሳስተው ፡ ጠረጴዛውን አፀዳድተው ወጡ ።

ኮሎኔል ጄልያን ከመቼው ተንፍሸ በተገላገልኩ ያሉ ይመስል “ከዚህ ቀደም የተገኘው ሬሣ የዛፈውን ሁኔታ እጅግ እንዳወሳሰበው ለባለቤትዎ እየነገርኳቸው ነበር እኮ” አሉ ወደ ማክሲም ዞር ብለው ።

“ልክ ነዎት ፡ ኮሎኔል” አለ ማክሲም

ይህን ጊዜ ፍራንክ ጣልቃ ገብቶ “በነበረው ሁኔታ ማክሲም ያደረገው ማንም ሊያደርገው የሚችለውን ነው ። ባለሥልጣኖች ማክሲም ቀርቦ ማረጋገጫውን እንዲሰጥ ሲጠሩት ሬሳዋን አግኝተናል የሚለውን ሀሣብ በአእምሯቸው ይዘው ነበር ። ማክሲም ደግሞ በወቅቱ በመልካም ሁኔታ ላይ አልነበረም ። እኔ እንኳን ይህንኑ በማጤን አብሬህ ካልሄድኩ ብዬው ነበር ፡ አይሆንም ብሎ ብቻውን ሄደ እንጂ” አለ ።

“አሁን እንኳን ወደኋላ ተመልሰን ዝርዝር ውስጥ የምንገባበት ጊዜ አያደለም ።” አሉ ኮሎኔል “ይልቅ አሁን ማድረግ ያለብዎት ባለፈው ጊዜ ሬሳው የእርሷ ነው ብለው ማረጋገጫ መስጠትዎ በስህተት መሆኑን ማስረዳት ነው ። ከዚህ የተለየ አማራጭ ይኖር አይመስለኝም”

“ምን አማራጭ አለ ብለው ?” አለ ማክሲም

“እንደኔ ፍላጎት ፍርድ ቤት ቀርበው ቃል ከመስጠት ፡ በዚሁ ሳቢያ ከሚነሣው ወሬ የሚድኑበት መንገድ ቢኖር ምንኛ ደስ ባለኝ ። ይህ ደግሞ በፍፁም የማይታሰብ ነው። ሀሣ ሀሣ ነውና” አሉ ኮሎኔል ።

“እንዴት ተደርጎ ?” አለ ማክሲም

“ደግሞ ያን ያህል ረጅም ጊዜ የሚወስድ አይመስለኝም ። እርስዎ አንድ ጊዜ ቀርበው የማረጋገጫ ቃልዎን ይሰጡና ባለቤትዎ ጀልባዋን ከፈረንሳይ ካስመጡ በኋላ ያስተካከለላቸው ሰውዬ — ስሙን ታብ ነው ? ማን ነው ያሉት ? እርሱ ይቀርብና ጀልባይቱ ለግልጋሎት በሚያበቃት ጥሩ ሁኔታ ላይ ትገኝ እንደነበረ ቃሉን ያስደምጣል ። እንዲያው ደንብ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ደንብ የሚሉት እጉል ጣጣ ሆኖ እንጂ ምንም ባላስፈለገ ። ይልቅ እኔን የሚቆጨኝ በዚህ በማይረባ ነገር የተነሣ ወሬው እንጉል መነዛቱ ብቻ ነው ። እርስዎንና ባለቤትዎን ምን ያህል እንደሚረብሻችሁ ይሰማኛል" አሉ ኮሎኔል ጁልያን ።

"ምንም አይደለም ኮሎኔል ። የመጣውን ሁሉ መቋቋም ነው እንጂ ምን ይደረጋል ?" አለ ማክሲም

"ያች መከረኛ ጀልባ ራቅ ብላ ሰጥማ ቢሆን ኖሮ ይህ ሁሉ መቼ ይፈጠር ነበር ?"

"እህሳ !" ሲል መለሰ ማክሲም

"ከዚህ ቀደም እናስበው እንደነበረ ሚስዝ ደዊንተር ቀስ በቀስ እየሰጠሙ ፡ እየተሰቃዩ ሳይሆን የሞቱት ወዲያው በድንገት ብዙም ስቃይ ሳይደርስባቸው ነው ማለት ነው ። ይህም አንድ መፅናኛ ነው ። ህይወታችውን በዋና ለማትረፍ የማይሞክሩበት ድንገተኛ አደጋ ቢሆን ነው ።" አሉ ኮሎኔል ሞንትላታቸውን እየነቀነቁ ።

"ቢሆን ነዋ" አለ ማክሲም

"ይህኔ እርሳቸው መሪውን ለቀው አንድ ነገር ፍለጋ ወደታች ሲወርዱ ጀልባዋ ከአንድ ነገር ጋር ተጋጭታ በሩ ተዘግቶባቸው መውጫ አጥተው ነው ከዚያው የቀሩት" አሉ ኮሎኔል ጁልያን ። ማክሲም መላ ምታቸውን በአምንታ ሲያረጋግጥላቸው ወደ ፍራንክ ዘወር አሉና ደግሞ "ምን ትላለህ ሚስተር ክሮውሌይ ? ይኸው ነው ሊሆን የሚችለው ፡ አይመስልህም ?" በማለት ጠየቁት ።

"ይኸው ነው እንጂ ። ሌላ ምን ሀሣብ ይኖራል ብለው" አለ ፍራንክ። ፍራንክ ሀሣቡን እየሰነዘረ እይኑን ከማክሲም ላይ ሲያሳርፍ ቀና ብዬ አየሁት ። ፊቱን ወዲያው ቢያዞርብኝም ከአይኖቹ እንዳች ልዩ ስሜት ማንበብ አልተሳነኝም ። ፍራንክ ሁሉንም ነገር እንደሚያውቅ አውቃለሁ። ማክሲም ግን ፍራንክ ማወቁን አያውቅም ።

"መቼም" አሉ ኮሎኔል ጁልያን "መቼም ሰዎች ስንባል እንዳንዴ እንጉል ስህተት ነው የምንሰራው ። የንፋሱ ሀይል በሚበረታበት በሰርጡ አካባቢ ሚስዝ ደዊንተር የጀልባዋን መሪ በፍፁም መልቀቅ አልነበረባቸውም ። ምናልባት ከዚህ ቀደም በዚያ አካባቢ ብዙ ጊዜ ብቻቸውን ተጉዘው ይሆናል ። የአካባቢውን አደገኛነት ሳያረዱት የቀሩ አይመስለ

t.me/OLDBOOKSPDF

ኝም ። እድሌን ልሞክር ብለው ከሞት ጋር መቆመራቸው ይሆናል ለቅስፈት የዳረጋቸው ። ይሄ እንግዲህ ለሁላችንም ትምህርት ሊሆነን ይገባል ።”

“እያጋ እኮ መምጫው አያታወቅም ኮሎኔል ። እኔ ነኝ ያለ ልምድ ያለው ሰው እንኳን ድንገት አያጋ ሊገጥመው ይችል የለም እንዴ ? ለአያን ሄደው እንደወጡ የሚቀሩ በርካታ እውቅ አዳኞች አይደሉም ?” አለ ፍራንክ ።

“ያሌላ ፡ ይሄ ሌላ” አለ ኮሎኔል “አየህ ሚስተር ክሮውሌይ ፡ አደን ላይ እኮ ብዙውን ጊዜ ለአያጋ የሚዳርግህ የተቀመጥክበት ፈረስ ሲወድቅ ነው ። ሚስዝ ድዊንተር የጀልባዋን መሪ ባያለቁ ኖሮ በፍፁም አያጋ ላይ አያወድቁም ነበር ። እኔ በተለያዩ አጋጣሚዎች እንዳየኋቸው ትንሳት ስህተት ሳይሰሩ በደንብ ነበር የሚያሽከረክሩት ። ይሄ ተራ ለማጅ የሚሰራው ስህተት እንጂ ከእርሳቸው የሚጠበቅ አልነበረም ። ያውም በእንዲያ ያለ አደገኛ ስፍራ”

“በዚያን ምሽት ንፋስ የቀላቀለ ሀይለኛ ዝናብ ይጥል ስለነበረ ፡ የጀልባዋ ሞተር አንዳንድ ጥርሶች ነክሰው አልንቀሳቀስ ብለዋት መፍቻ ብጤ ፍለጋ ይሆናል ወደ ታች የወረዱችው” አለ ፍራንክ ።

“ሊሆንም ላይሆንም ይችላል ። በስፍራው ስላልነበርን እርግጠኞች ሆነን መናገር አንችልም ። አጋጣሚው ቢደርስብን ምናልባት እኛም ከዚህ የተሻለ ነገር አናደርግ ይሆናል ።” ካሉ በኋላ ኮሎኔል ጄልያን ይህን ነጥብ ትተው ምርመራው ለነመ·ስ እንዲሆን ለማድረግ ጥረት እንደሚያደርጉ ተናገሩ ።

ሁሉም በፀጥታ ሲዋጥ ከተቀመጥኩበት ብድግ አልኩ ። ወደ መናፈሻው እንሂድ ብያቸው ተከታትለን ወጣን ። ኮሎኔል ጄልያን ከሰአት በኋላ በርካታ ሥራ እንደሚኖራቸው በመግለፅ ይቅርታ ጠይቀው፡ ስለ ምሣው ግብግቸን አመስግነው ፡ ተሰናብተው ሄዱ ። እስክ ቤቱ በመኪናቸው ላድርስህ ስላሉት ፍራንክም አብሯቸው ሄደ ።

ማክሲም ሽኝቷቸው ሲመለስ በቀጥታ ወደኔ መጣና እጄን ያዝ አደረገ ። አይኖቻችንን ለምለሙ መስክ ላይ ተክለን ጥቂት ከቆየን በኋላ “ሁሉም ነገር እንደሚሳካ እርግጠኛ ነኝ ። ዳኞች ፈትም ታል መስጠቱ ምንም ችግር አይኖረውም” አለኝ ማክሲም ። ምንም መልስ ሳልሰጠው

t.me/OLDBOOKSPDF

እጁን ጥርቅም አድርጌ እንደያዝኩ ቆምኩ ።

ማክሲም ቀጠል አደረገና "ሬሳዋ ቁልጭ ብሎ ያስታውቅ የለም እንዴ? እኔም ባልኖር ዶክተር ፊሊፕስ ብቻውን እንኳን መለየት ይችል ነበር ። ዋናው ነገር ጥይቱ አጥንቷን ስላልነካው ምንም የሚያስጠረጥር ምልክት አለመገኘቱ ነው ... ደግሞ ... ኩሎኔልና ፍራንክ ደግሞ ምን ይሉ እንደነበረ በደንብ የሰማሻቸው ይመስለኛል ። ወደታችኛው ክፍል እንደ ወረደች ድንገት በተፈጠረ አደጋ ለመውጣት ሳትችል በዚያው ቀረች ብለው ነው የሚያስቡት ። ዶክተሩም ለዳኞቹ ይህንኑ ቃል ስለሆነ የሚሰጠው በደንብ ያምኑታል" አለ ።

ንግግሩን እጨርሰ አይን አይኔን ቢመለከት አውንም ምንም ሳልተነፍስ ዝም አልኩት ።

"እእምሮዬን ራታ ነስቶ የሚያስጨንቀኝ ነገር ቢኖር ያንቺ ጉዳይ ብቻ ነው ። ባለፈው ጊዜ ለፈፀምኩት ቅንጣት ፀፀት አይሰማኝም ። ሁኔታው ዛሬ ተመልሶ ቢመጣ እንኳን ያኔ ያደረግኩትን ከማድረግ እንዲት ስንገር ወደ ኋላ አልልም ነበር ። ርብቃን ገድያለሁ ። እርሷን በመግደሌ ሰፍሮብኝ የነበረውን አንዳች እርኩስ መንፈስ ከላዬ ላይ አሽቀንጥሬ የጣልኩ ያህል ነው የመንፈስ እረፍት የሚሰማኝ ። ያስደስተኛል እንጂ ከቶውንም አይፀፅተኝም ። የኔ ድርጊት ከማንም በላይ የጎዳው አንቺን መሆኑ ስገነዘብ ግን ልቤ በሀዘን ይደማል ። ማእድ ላይ ይህንን እያሰላሰልኩ ትክ ብዬ ሳይሽ ነበር ። ያ ፍቅሬን የሰዋሁለት ለጋ ሰውነትሽ ሚሸሸብኝ — ... ያ ህሊናዬን ያሳተኝ እምቡጥ ፊትሽ ጠወለገብኝ ... እኒያ በብርሃናቸው ያደመቁኝ ከዋክብት አይኖችሽ ደበዘዙብኝ ...እኒያ ልቤን የሰረቁት ፍልቅልቅ ጥርሶችሽ በለዙብኝ ... ርብቃን ትናንት ገደልኳት ... አዎን ገደልኳት ... ዛሬ ደግሞ አንቺን በቁም ገደልኩሽ ... ፍቅርሽን በረዝኩት ... ላህይሽን መጠጥኩት ...ህይወትሽን አጨለምኩት ..."

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ ሀያ አንድ

ግምሻውን ፍሪዝ በአካባቢያችን የሚታተመውን ጋዜጣ አምጥተው ጠረጴዛው ላይ አኖሩልኝ ። በመጀመሪያው ገፅ ላይ "ባህር ውስጥ ለአንድ አመት የተኛች የማንደርሌይቱ እመቤት" የሚለው ርእስ ጎላ ባሉ ፊደላት ተፅፏል ። አንዳች እንድናገራቸው የፈለጉ ይመስል ፍሪዝ እነበሩበት እንደቆሙ ነበር ። መላ ቤተሰቡን የሚነካ ይህን አይነት አብይ ጉዳይ ተከስቶ ሳለ ዝምታዬ ጅልነት ይሁን እብሪት ሊገባኝ አልቻለም ። ተናገሪ፡ ተንፍሺ የሚል ስሜት ውስጤን ሲጎተጉተው "መቼም ዛሬ የገጠመን ጉድ በጣም የሚዘገንን አይደለም እንዴ ፡ ፍሪዝ ?" ስል ጠየቅኳቸው ።

"እንዴታ እሜትዬ ፡ ሁላችንም በጣም ነው ያዘንነው" አሉ ፍሪዝ

"እኔ በጣም ያሳዘነኝ ፡ ሚስተር ደዊንተር ሰላም አገኘው ሲል አጉል ትውስታ ውስጥ የሚከተው ነገር መከሰቱ ብቻ ነው "

"እረ አያድርስ ነው እመቤቱ ። ጌቶች ስንቱን ክፉ ይቻሉት ? ለመሆኑ ተገኝ የተባለው ሬሳ በእርግጥ የሟች የሚስዝ ደዊንተር መሆኑ ተረጋግጧል ?"

"አዎን ፡ መረጋገጥ እንኳን ተረጋግጧል "

"እኔ እኮ እሜትዬ ፡ ሁላችንንም ግርም ያለን ነገር እርሳቸውን የመሰለ በቂ ልምድ ያለው ሰው እንዴት እንደዚያ እዚያች ጠባብ ክፍል ውስጥ ታፍኖ እስኪሞት ይጠብቃል ?"

"እኛም ይህንኑ ነው የምንለው ፍሪዝ ። አያድርስ ነው እንጂ አደጋ ካጋጠመ መች እገሌን እገሊትን ይላል ብለው ። ብቻ ምን እንደተፈጠረ ግን ያውቃል ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ነው ፡ ነው እሚትዪ ። እንዴት ነው ? ምርመራ ሳያካሂድ ይቀራል ብለው ነው ?"

"እርሱ እንኳን የተለመደ ስለሆነ የሚካሄድ ይመስለኛል ። እንዲያው ለደንቡ ሲባል እንጂ ያን ያህል የሚጠቅም አይደለም ።"

"ልክ ነዎት እሚትዪ ፡ እንዲያው ከእኛ መሃል ለማስረጃነት የሚፈለግ ሰው ይኖር እንደሆን ብዬ ነው"

"አይመስለኝም ፡ ፍሪዝ"

"እኔ አስፈላጊ ከሆነ የቢታችንን ደህንነት ለመጠበቅ ምንም ከማድረግ ወደ ኋላ አልልም ። ደህንነ ደግሞ ጉዞች በሚገባ ያውቁልኛል"

"እሪ አሳምሮ ያውቃል"

"ምን መሰለዎት ፡ እኔ እንኳን ነገሩ በምስጢር ይያዝ ፡ እንዳሻቸው አታውሩ ፡ ብዬ ለሰራተኞች ሁሉ ነግሬ ነበር ። ግን የስንቱ አፍ ተይዞ ይቻላል ። በተለይ ሴቶቹማ አፋቸው ቢያዝ ሌላ ነገራቸው ያናገራል ። ሮበርትን እንኳን መቆጣጠሩ አያስተኝም ነበር ። የሌሎቹ ነገር ነው የቸገረኝ እንጂ ። ሚስዝ ዳንቨርስ ግን ውኔው በጣም የተሰማት ነው የሚመስለኝ"

"ለምን አይሰማቸው? በጣም ይሰማቸዋል እንጂ"

"ከምላ በኋላ ከክፍሏም አልወጣች ። አውን ግድም አሊስ ሻይና ጋዜጣ ይዛላት ሄዳ ነበር ። የአመት በሽተኛ ትመስላለች አለችኝ"

"እንግዲያው ያን ያህል ከታመመ ጉድ ጉድ እላለው ብለው እንዳይነሱ አሊስ ትንገራቸው ። እኔው አስፈላጊውን ትእዛዝ እየሰጠኋት ወጥ ቤት ማንኛውንም ነገር ታሰናዳለች ።"

"አነላዊ ሀሙም እንኳን አይመስለኝም ። ለሚስዝ ደዊንተር ልዩ ከበፈታና ፍቅር ስለነበራት ፈሳቸው ተገኝ መባሉ ክፉኛ ሳያስደነግጣት አይቀርም"

"እውነትዎትን ነው ፡ ይሆናል" ካልኳቸው በኋላ ፍሪዝ ብቻዬን ትተውኝ ወጡ ። ጋዜጣውን እንስቼ ስመለከት ከፅሁፉ በተጨማሪ ደብዘዝ ያለ የማክሲም ፎቶግራፍ ሲያፈጥብኝ ደነገጥኩ ። ከፎቶግራፉ ግርጌ የሰፈረው እኔ የማክሲም ሁለተኛ ሚስት መሆኔና ከሰሞኑ ስለተደረገው ትልቅ ግብዣ የሚገልፀው ፅሁፍ ይበልጥ ረበሸኝ ። ከዚያም ጋዜጣውን ገረፍ አደረግኩት ። የርብቃን ውበት ፡ ብልሀቷን ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ተወዳጅነቷን ካጠሳ በኋላ በሞተች በአሙቱ ማክሰኞ ስለማግባቱ ፡ ስለ ግብግቡ ፡ በግብግቡ ማግስት የርብቃ ፈሳ ስለመገኘቱ ጋዜጣው በዝርዝር ያትታል ።

ማክሰኞ እንዳያየው ጋዜጣውን ደበቅኩት ። ይሁንና በማግስቱ የወጡት የሎንዶንና የሊሎች ከተሞችም ጋዜጦች ዜናውን አስፍረውት ስለነበረ ማክሰኞ ሁሉንም አንድ በአንድ አያቸው ። እጅጉን የሚገርመው ፡ ሆነ ተብሎ የተደረገ ይመስል ጋዜጦቹ ሁሉ የርብቃ ፈሳ የተገኘው በግብግቡ ማግስት መሆኑን ልዩ አፅንኦት መስጠታቸው ነበር። በመሠረቱ ጋዜጦቹ ያሰፈሯቸው ሀሣቦች በጥቅሉ ከእውነት የራቁ ባያሆኑም አንባቢዎቻቸውን ለመሳብ ሲሉ ብቻ በአሸብራቂ ሀይለ ቃላት፡ በተጋነኑ ሀረጎች መታጨቃቸው አልቀረም ።

ማክሰኞ ጋዜጦችን ሲያነብ ፊቱ ልውጥውጥ ሲል ይታየኝ ነበር ። "ይድፋችሁ ፡ ይድፋችሁ" እያለ ሁሉንም ተራ በተራ አነበባቸው ።

ከቱርስ በኋላ ፍራንክ ሲመጣ የመጸከምና የመገርጣት መልክ ይታይበት ነበር ። በርካታ ሰዎች ማክሰኞን በቱሉፎን ለማግኘት እንደሚሹ ፡ ሁሉንም እርሱ እንዳነጋገራቸው ፡ ማክሰኞ ማነጋገር እንደማይፈልግና ወደፊትም የሚመጣውን የቱሉፎን ጥሪ ሁሉ እርሱ እንደሚመልስ ነገረን ። "ሚስዝ ሌሲ ደግሞ በሁለት ሰአት ተኩል ደውላ አሁኑኑ እመጣለሁ አለችኝ" አለ ፍራንክ ።

"ያንተ ያለህ! ምን..." አለ ማክሰኞ ድንገት ሙክ ብሎ

"ግድ የለም ፡ ግድ የለም" አለ ፍራንክ በማረጋጋት "መምጣቱ አስፈላጊ እንዳልሆነ ነግሬአታለሁ ። አንተ ግንኙም ማነጋገር እንደማትፈልግ ስላስረዳኸት አትመጣም ። ምርመራው መቼ እንደሚካሄድ ብትጠይቁኝም ገና አልተወሰነም አልኳት ። ግና ዳሩ ጋዜጦች ላይ ካየች መምጣቷ የሚቀር አይመስለኝም ።"

"አራ! እኒህ መናኛ ጋዜጠኞች! ምን ቢደረጉ ይሻላል?" አለ ማክሰኞ

"ልክ ነህ ማክሰኞ ። ሁላችንም ማንቁርታቸውን ይዘን ብንጨፈልቃቸው ደስ ባለን ነበር ። ግና ነገሩን ከእነርሱ አንፃር ሁነን እንየው ። የእንጀራ ጉዳይ ስለሆነ ይህን መሰል ሥጋ ዜና አግኝተው እንዴት ይለፉት? በየአትጣጫው እያነፈነፉ ጥሩ ጥሩ ዜና ይዘው ካልቀረቡ

t.me/OLDBOOKSPDF

አዘጋጁ እየመነቀረ ያስወጣቸው የለም እንዴ? አዘጋጁ ደግሞ አንባብያ ንን የሚስብ ፡ የጋዜጣውን ሽያጭ የሚያዳብር እትም ካላዘጋጀ የጋዜጣው ባለ ንብረት ያባረረዋል ። ጋዜጣው ካልተሸጠ ደግሞ ባለንብረቱ መክሰሩ ነው። ይህንን ነው ማየት ያለብን ። እየህ ማክሲም ፡ የፈለጉትን ያህል ቢንቋቋ እንተ ከማናቸውም ጋር መጣናኘት የለብህም ። በኔ ላለው ። ይልቅ አንተ ማተኮር ያለብህ ምርመራው ላይ ስለምትሰጠው ቃል መሆን አለበት ።”

“ምን ማለት እንደሚገባኝ እንኳን አውቀሞለሁ” አለ ማክሲም

“መርማሪው ያ ሞባዛ ሆሬጅ መሆኑን አትዘንጋ ። እንዲሁ በማያስፈልጉ ነገሮች ሲጨቃጨቅ ነው የሚውለው ። ለሌላ ሳይሆን ዳኞች በሥራው ትጉህ ነው እንዲሉት ብቻ ነው አንጂ ግራንጂውን የሚያበዛ ። እና ወጥመዱ ውስጥ እንዳያስገባህ መጠንቀቅ ነው ።”

“ምንድነው ይህን ያህል ወጥመዱ ውስጥ የሚያስገባኝ?”

“ሰውዬውን በተለያዩ የምርመራ ወቅቶች እንዳየሁት ሰዎችን ተንኮስ በማድረግ እንዲናደዱና የሆነ ያልሆነውን እንዲቀባጥሩ ስለሚ ያደርጋቸው ጠባዩን እንድታውቀው ለማለት ነው ።”

ይህን ጊዜ እጓለቃ ገባውና “ፍራንክ እኮ እውነቱን ነው ። ሁሉም ነገር ቀና በሆነ መንገድ በሰላም መፈፀሙ ለሁላችንም ጥሩ ነውና ተጠንቀቅ ማለቱ ክፋት የለውም ።” አለኩ ።

ሀማቡ ለጊዜው በዚህ ይቋጭ እንጂ ያ ጣጠኛ የቀጠሮ ቀን ማክሰኞ እስኪደርስ እንዲህ ስናምጥ ቆየን ። እንደማይደርስ የለምና ማክሰኞም ደረሰ ። ሜንቅ ጥብብ ። ምሳ ቢቀርብልንም በግዛ አልገባም ከጉሮሮዬ ጋር ግብግቡን ገጠምኩ ። ፍራንክ መጣና ቢያትሪስ ደውላ “ለመምጣት አልቻልኩም” ብላለች ሲለን አቢት እንደተደሰትኩ ። ቢያትሪስን እኮ ጠልቻቸው አያደለም ። በጣም ቅን ፡ ግልፅ ፡ የሞሀ ስለሆኑ ለመንደግቸው ባላቸው ፍቅር ፡ በቅን ልቦና በሚሰነዝሯቸው ጥያቄዎች ማክሲም እንዳያረበሽ በማሰብ ነው መምጣታቸውን ያልፈለግኩት ። ፍራንክ እንደነገረን የቢያትሪስ ልጅ ሮጀር ኩፍኝ ይዞት መደቤቱ ስለተመለሰ የቤተሰቡ አባላት በሙሉ ከሰው ጋር እንዳይገናኙ ስለታገዱ ነው ቢያትሪስ መምጣት ያልቻሉት ። ይህን ስሰማ ኩፍኝን መረቅኩት ክልቤ

እኔና ማክሲም በመኪናችን ፡ ፍራንክ በመኪናው ተከታትለን

t.me/OLDBOOKSPDF

ምርመራው ወደሚካሄድበት ላንየን ወደሚባለው ከተማ አመራን ። ከማክሲም ጎን ተቀምጬ እጇን ጉልበቱ ላይ ጣል አድርጌው ነበር ። ልቤ ምቱን ከመጨመሩም በላይ ወጋ ወጋ እያደረገ አስቸገረኝ ። እራሴን ፡ ውጤቱ ምን እንደሚሆን ለማይታወቅ የቀይ ጥገና ህክምና ወደ ሆስፒ ታል የሚወሰድ በሽተኛ አድርጌ ቆጠርኩት ። ማክሲም ግን ምንም እያነት የመረበሽ ምልክት አይታይበትም ነበር ።

መንገደኛው ሁሉ እኛን የሚያይ ፡ ሳር ቅጠሉ በእኛ የሚንሾካሾክ መሰለኝ ። አስፋራው ደርሰን መኪናችንን እንዳቆምን አንዲት ሴትዮ ማክሲምን እያየች አብሯት የነበረውን ሰውዬ ጎንተል ስትደርገው ሳይ እርር ድብን አልኩ ።

"እዚሁ ውኜ ብጠብቅህ አይሻልም?" አልኩት ማክሲምን

"እኔ ሙጀመረያውኑ መምጣትሽን አልደገፍኩም ነበር ። እዚያው ማንደርሉይ ብትቀረ ነበር የሚሻለው" አለ ማክሲም

"አይ ፡ መምጣቱንስ እንኳን መጣው ፡ እዚሁ ነው የሚሻለኝ ።"

ፍራንክም መኪናው ውስጥ እንደምጠብቅ ሲነገረው በፀጥታ ተስማምቶ ከማክሲም ጋር ተያይዘው ሄዱ ። ከመኪናው ሳልወጣ መንገዱ ዳር የተገጠገጡትን ሱቆች በአይኔ ማተርኳቸው ። ይህን ሳበቃ ደግሞ ወትሮውኑም አድራጎቱ ሁሉ የማማሽ ልብ ነበረና ሀሣቤን ወደ ማክሲም ሰደድኩት ። ገዢው አልገፋ አለኝ ፡ አቁነጠነጠኝ ። መኪናውን ከፍቼ ወጣው ። ገበያው መሃል እላይ ታች ስንሯራደድ ፡ አንዴ ወደ ሱቆቹ ተጠግቼ መስኮት ላይ የደረደሯቸውን እቃዎች ሳይ ፡ እንደገና እላይና ታች ስመላለስ ቆየሁ ። አንድ ፖሊስ ትኩር ብሎ ሲያየኝ አስተያየቱን አልወደድኩትም ። ከአይኑ ለመሸሽ በአቅራቢያዬ ባገኘሁት መንገድ ታጠፍኩ ።

ሳላስበው ምርመራው ከሚካሄድበት ህንፃ በር ላይ ደረስኩ ። የምርመራው ሰዓት በስፋት ባለመነገሩ ነው መሰለኝ እንደፈራሁት ምንም ትርምስ አልነበረም ። ሰተት ብዬ ገባሁ ። ከየት መጣ ሳልለው አንድ ፖሊስ ብቅ አለና "ምን ይፈልጋሉ?" ሲል ጠየቀኝ ።

"ምንም ፡ ምንም አልፈልግም" አልኩት ።

"እንግዲያው እዚህ መቆም ክልክል ነው"

"ይቅርታ ፡ አላወቅኩም" አልኩና በገባሁበት ወጣሁ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ፖሊሱ ተከትሎኝ መጣና "ይቅርታ የኔ እመቤት ፡ ሚስዝ ደዊንተር አይደሉም እንዴ?" ሲል ጠየቀኝ ።

"ነኝ" አልኩት ።

"ለእርስዎ እንኳን አልተከለከለም ። ከፈለጉ እዚሁ ሊቆዩ ይችላሉ። እዚህኛው ክፍል ውስጥ መንበር አለልዎት" ብሎኝ ክፍሉን አሳየኝ ። አመስግኜው ገባሁ ። እጅቼን እግሮቼ ላይ እንዳስቀመጥኩ ፀጥ ብዬ ተቀምጬ ጣሪውን እቆጥር ጀመር ። አምስቱ ደቂቃ አምስት ሰአት ያህል ረዘመብኝ ። መኪናው ውስጥ መቀመጡ ይሻለኝ ነበር ። ተንስቼ ወጣሁ ። ፖሊሱን ከነበረበት አገኘሁትና "ይቆዩ ይሆን?" ስል ጠየቅኩት ።

"ከፈለጉ ገብቼ ልጠይቅልዎት" ብሎኝ ሄደ ። ወዲያው ተመለሰና "ብዙ የሚቆዩ እንኳን አይመስለኝም ። ሚስተር ደዊንተር ታላቸውን ሰጥተዋል ። ካፕቴን ሲሬል ፡ ዋናተኛውና ዶክተር ፈሊፕስም ጨርሰዋል። አሁን የቀረው ጀልባ ሰሪው ሚስተር ታብ ብቻ ነው" አለኝ ።

"እንዲያ ከሆነስ አልቋል ማለት ነው" ስለው

"መሰለኝ እመቤቴ" አለና ወዲያው ደግሞ "ቀሪውን ክፍል ለማጸዳት ከፈለጉ እዮን ላይ መቀመጫ አለ ። ማንም ሳያይዎት ሊገቡ ይችላሉ" አለኝ ።

ስምምነቱን ገልፄለት አስከትሎኝ ገባ ። እንዳልሰማ የፈለግኩት የማክሲምን ቃል ነበር ። ማክሲም ስለጨረሰ ሌላውን መስማቴ ምንም እንደማያረብሸኝ ስለማውቅ ነበር መግባቴን የፈቀድኩት ። እበሩ ስር በመቀመጫ ማንም ሊያየኝ አይችልም ነበር ። የምናልባቴ ጉራጅ ግን አንገቴን ሙሉ በሙሉ እንዳቀና አላስደፈረኝም ። አልፎ አልፎ ሰረቅ አድርጌ የወረወርኩት አይኔ ማክሲምና ጉራንክ በእንዴ ጥግ ቁጭ ብለው አሳየኝ ። መርማሪውንም አየኋቸው ። ጠና ያሉ ከሲታ ናቸው ። መነፅራቸውን አስር ጊዜ ወደ ላይ ይገፉታል ። ለሎች በርካታ የማላውቃቸው ሰዎችም ነበሩ ። አይኔን በጓለኛው ረድፍ ላይ ሳንከባልለው ያየሁትን ማመን አቃተኝ ። ደንግጬ ። ሚስዝ ዳንቨርስ ገብ ብለዋል ። ጃክ ፈቭልም ከጎናቸው አለ ። የእዚያ የነገረኛ አሮጊት ነገር እንኳን አልገረመኝም ። ፈቭል ይኖራል ብዬ ግን በጭውም አልገመትኩም ነበር ።

"አምን ጊዜዬ ፡ የሚስዝ ደዊንተርን ጀልባ አስተካክየላቸዋለሁ" አለ ሚስተር ጀምስ ታብ ከመርማሪው ለቀረበለት የመጀመሪያ ጥያቄ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሲመልስ "ቀድሞ ጀልባይቱ ለአሳ ማጥመጃ ነበር የምትውለው ። ከፈረንሳይ ገዝተው ካመጧት በኋላ ለሽርሽር እንድትስማማ አድርጌ ሰርቼላቸዋለሁ ።"

"ጀልባዋን አስተካክልኳት ካልክ ለጉዞ ብቁ ነበረች ማለት ነው?" ሲሉ መርማሪው ላቀረቡለት ጥያቄ ሚስተር ታብ አምንታዊ ምላሹን ሰጠ።

"ጀልባዋ ከዚህ ቀደም ሰጥማ ታውቃለች?"

"በፍፁም ጊታዬ ፡ እንዲህ አይነቱ አደጋ ደርሶ ቢሆን ኖሮ ሚስዝ ደዊንተር ያነግሩኝ ነበር ። በጀልባዋ ሙሉ በሙሉ እንደረኩባት ነበር ዘወትር የሚነግሩኝ ።"

"መቼም እንደሚገባኝ ከሆነ ጀልባዋ በጥንቃቄ መያዟ ያለባት ይመስለኛል ። አደጋስ እንዴ ሚስተር ታብ?"

"በመሠረቱ ማንም ሰው ቢሆን በጀልባ ሲጓዝ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል ። የሚስዝ ደዊንተር ጀልባ ግን እንደ አብዛኞቹ እዚህ ኬረዝ እንደምናያቸው ጀልባዎች አይነት አይደለችም ። ብዙ አስከፊ የአየር ሁኔታዎችን መቋቋም እንደምትችል በተለያዩ አጋጣሚዎች አስመስክራለች ። የዚያን ቀን የነበረው ነፋስ ያን ያህል ከብዶ ፡ እንዴት ሊያሰጥማት እንደቻለ ግራ ነው የገባኝ ።"

"ግን እኮ አብዛኛው ሰው እንደገመተው ሚስዝ ደዊንተር መሪውን ለቀው ወደታችኛው ክፍል በወረዱበት ወቅት የነበረው ነፋስ ጀልባዋን ለመገልበጥ አይችልም ትሶለህ?"

"በፍፁም ፡ እኔ ያሰጋን ሀጣብ በፍፁም አልተበልም ።"

"እየነ ሚስተር ታብ ፡ ማናችንም ፡ ሚስተር ደዊንተርም ጭምር ያንተ ስራ እንከን ነበረበት የሚል ሀጣብ አልወጣንም ። ምናልባት ሚስዝ ደዊንተር በጀልባዋ ጥንካሬና በራሳቸው ችሎታ ከመጠን በላይ ተማምነው ለአደጋ ተጋልጠው ይሆናል ነው ግምታችን ። ይሄ ደግሞ በማንም ላይ ሊደርስ የሚችል አጋጣሚ ነው ።"

"ያትርታ ያድርጉልኝና ጌታዬ እኔ ደግሞ ሌላ የምለው ሀጣብ ስላለኝ መልካም ፍቃድዎ ከሆነ..."

"በለው እንጂ" አሉ መርማሪው አቋርጠውት "በለውና እንስማው።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"መልካም ፡ የዛሬ አመት አደጋው እንደተፈጠረ በርካታ ሰዎች የእኔን ስራ እያናናቁ ሲያሙኝ ከረሙ ። ሚስዝ ደዊንተርን ሆን ብዬ በማይረባ ጀልባ ላይ ጥዬ ለህልፈት እንደዳረግኳቸው ተደርጎ ተወራብኝ። በዚህ አንገል ወራ የተነሣ ካንድም ሁለት ሦስት ደንበኞቼ ሸሹኝ ። በወቅቱ የምናገረው አልነበረም ። ከዚያ በኋላማ ሁላችንም እንደምናውቀው በቅርቡ የሚስዝ ደዊንተር ጀልባ ከሰጠመበት ተጎትቶ ወጣ ። ታዲያ ትናንትና ካነቱን ሲርልን አስፈቅጄ ከስራዬ አንዣር መርከቧን መርምሬ ያት ነበር ። እና…"

"እና ምን አገኘህ? መቼም የምርመራ ውጤትህ በስራህ ይበልጥ እንድትተማመን እንዳደረገህ እርግጠኛ ነኝ ።" አሉ መርማሪው በመቻኮል ።

"በሚገባ" አለ ጀልባ ሰሪው ትንሽ እንደ መኮፈስ ብሎ "ጀልባዋን አንድ ሳይቀር ሁለመናዋን በደንብ መረመርኳት ። ጀልባዋ የተገኘችው አሸዋማ በሆነ ስፍራ እንደነበረ ዋናተኛው ነግሮኛል ። እኔም እንዳየኋት ምንም ቋጥኝ እንዳልነካት ፡ አንዳችም ጭረት እንዳልነበራት ለማረጋገጥ ችያለሁ ። እንዲያውም ቋጥኞች የነበሩት ከጀልባዋ ስምንት ኪሎ ሜትር ያህል ርቀው ነበር" አለና ሚስተር ታብ ወጥ አለ ።

መርማሪው በጉጉት ሲያዩት ቆዩና "በታ ፡ ይህንኑ ነው ልትነግረን የፈለግኸው?" ሲሉ ጠየቁት ።

"አይደለም ጌታዬ" አለ ታብ ፍርጥም ብሎ "ጀልባዋ በተገኘችበት አካባቢ ምንም አይነት ድንጋይ ወይም ቋጥኝ የለም ብያለሁ ። ታዲያ እዚህ ላይ ነው እንግዲህ ትልቁ ነጥብ ። የጀልባዋን ወለል ማን ነው የበሳው? በአካባቢው ቋጥኝ ነበረ እንኳን ብንል ቀዳዳቹ በቋጥኝ የተበሱ አይነት አይደሉም ። በሾለ ነገር ነው የተበሱት"

ቀና ብዬ ማየት ተሳነኝ ። አንገቴን ደፍቼ ወለል ወለሉን አይ ገባሁ ። ሁሉም ወጥ ረጭ አለብኝ ። መርማሪውም ያን ያህል በዝምታ መዋጣቸው ገረመኝ ። ጉሮሯቸውን መጠራረግ ሲጀምሩ ድምፃቸው ከሩቅ የሚመጣ ነበር የመሰለኝ ።

"የምን ቀዳዳ ነው ሚስተር ታብ?" ሲሉ ጠየቁ በመደነቅ

"የጀልባዋ ወለል ሦስት ቦታዎች ላይ ነው የተበሳው" በማለት የቀዳዳቹን አቅጣጫ ካስረዳ በኋላ "የጀልባዋን ሚዛን ለመጠበቅ

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚያገለግለው ክብደት ያለው ነገር ከስፍራው ተሸጋሽጓል ። ፉካም ችም ተከፍተዋል ።”

“ፉካሞቹ ደግሞ ምን የሚሰሩ ናቸው?”

“የመዐጀና የመታጠቢያ ክፍሎችን ቁሻሻ የሚያስወግዱ ተባዮች ናቸው ። ሚስዝ ደዊንተር በጠየቁት መሠረት ሰርቼላቸው ነበረ ። እነዚህ ተባዮች ምንጊዜም በሚገባ መዘጋት ይገባቸዋል ። አሊያ ውሀ ሰተት ብሎ ነው የሚገባው” አለ ሚስተር ታብ ።

ምን አይነት ሙቀት ነው? ምነው መስኮቱን ቢከፍቱት? ይህ ሁሉ ህዝብ እንዲህ ታሞቹ ታፍኖ መሞቱ አይደለም እንዴ? ነበር ያሰኘኝ ።

“ታዲያ” በማለት ቀጠለ ባለሙያው “ታዲያ ጌታዬ ፡ ይህ ሁሉ ክፍተት ባለበት እንዲህ ያለች ትንሽ ጀልባ ወዴያው ነው የምትሰጥመው — ግፋ ቢል አስር ደቂቃም አትቆይ ። ጀልባዋ ከኔ ድርጅት ስትወጣ ምንም ቀዳዳ እንዳልነበረባት እርግጠኛ ነኝ ። እንደኔ አስተሳሰብ ጀልባይቱ ሆን ተብሎ ነው እንድትሰጥም የተደረገችው ባይ ነኝ ።”

እየሩ አነሰኝ ፡ ክፍሉ ጠበበኝ ። ከጎኔ የተቀመጠው ሰው እየተጠጋ፡ እየተጠጋ··· ሁሉም ነገር የሚያፍነኝ መሰለኝ ። ተነስቼ ለመውጣት ፈለግኩ ። ሀያሉ ከየት መጥቶ! ብሎ አለብኝ ፡ ሜጫታ ነገሰ ። መርማሪው ሰዉ ፀጥ እንዲል ከጠየቁ በኋላ “ሚስተር ደዊንተር” ሲሉ ሰማኋቸው ። ማየት አልቻልኩም ። ቢቻለኝም እንኳ ማከሲምን ማየት አልፈለግኩም ። ወበቁ ይበልጥ ይወረኝ ጀመር ። ከግራ አልፎ ቀስ በቀስ ወደ ላይኛው አካሉ እየዘለቀ ፡ ፊቱን አንገቱን ሲወረኝ ይሰማኝ ነበር ።

“ሚስተር ደዊንተር ፡ ጀምስ ታብ የሰጠውን ማብራሪያ የሰሙ ይመስለኛል ። ጀልባዋ ወለል ላይ ተገኙ ስለሚባሉት ቀዳዳዎች የሚያውቁት ነገር አለ?” ሲሉ መርማሪው ።

“ምንም የማውቀው ነገር የለም”

“ጀልባዋን ምን ነደላት ብለው ይገምታሉ?”

“እኔ ምን አውቄ?”።

“ይህን ነገር ሲሰሙ የመጀመሪያ ጊዜዎ ነው?”

“አዎን”

t.me/OLDBOOKSPDF

"መቼም እንዳስደነገጠዎት እርግጠኛ ነኝ"

"እስካሁንስ የሚያስደነግጥ ነገር መች አነሰኝና? ካንድ አመት በፊት የባለቤቱ ብዬ ያስተዋወኩት ሬሳ የሌላ ሰው መሆኑ ያስደነገጠኝ ሳያንስ ዛሬ ደግሞ ባለቤቱ የሞተችው ጀልባዋ እንዲሰጥም ሆን ተብሎ ተነድሎ ነው ተባልኩኝ ። ታዲያ ይህ ቢያስደነግጠኝ ይህን ያህል የሚያስገርም ነው?"

ተው እንጂ ሚክሲም ። ምነው ፍራንክ ያለህን ብትሰማ ማክሲምዬ? ተው ሰውዬውን አታናዳቸው እንጂ ። እባክህን ማክሲምዬ አትቆጣ ፡ ሰውዬውን ተቆጥተህ አታስቆጣቸው ። እባክህን የኔ ፍትር ተዘቀዝ በል ። ምነው አምላኬ ትእግስቱን ብትሰጠው? ምነው ትእግስቱን ብትሰጠው?

"አዩ ሚስተር ደዊንተር ፡ በተፈጠረው አጋጣሚ ሁላችንም ከልብ ነው ያዘንነው ። ይህን ምርመራ የማካሂደው ለእርስዎ ስል እንጂ እራሴን ለማዝናናት እንዳልሆነ ሊረዱልኝ ይገባል ። ባለቤትዎም እንዴት ና ለምን እንደሞቱ መታወቅ አለበት የምለው ለእርስዎ ብዬ ነው ።"

"ይህማ ግልፅ አይደለም እንዴ?"

"መልካም ፡ እንግዲያው ወደ ዋናው ነጥብ እንመለስና ጄምስ ታብ የሰጠውን ቃል ይቀበላሉ አይቀበሉም? ማለቴ ስለ ተዳዮቹ ፡ ስለ ፋኒዎቹ መከፈት"

"እንዴት አልተበልም? የሚናገረውን የሚያውቅ ባለሙያ አይደለም እንዴ?"

"የሚስዝ ደዊንተርን ጀልባ ማን ነበር የሚንከባከበው?"

"ማንም አልነበረም ፡ እራሷ እንጂ"

"ምንም ቅጥረኛ ሠራተኛ አልነበራትውም ማለት ነው ?"

"አልነበረም"

"ጀልባዋ ትቆም የነበረው በማንዶርሌይ የግል መደብ ነበር?"

"አዎን"

"ወደ ወደቡ የሚያስገባ ሌላ መንገድኛ የሚመላለስበት የእግር መንገድ አለ?"

"የለም"

"ወደቡ በጫካ የተከበበ ወጥ ያለ አይደለም እንዴ?"

"ነው"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንድ ሰው ሽልክ ብሎ ቢገባ ላይታይ ይችላል ማለት ነው?"

"እምን ፡ ላይታይ ይችላል ።"

"አሁን ጁምስ ታብ እንደነገረን ደግሞ እንዲህ የተበላላች ጀልባ ግፋ ቢል በአስርና በአስራ አምስት ደቂቃዎች ውስጥ ትሰጥማለች ነው ያለን ። አይደለም እንዴ?"

"እህ?" አለ ማክሲም ጭንቅላቱን በመነቅነቅ ።

"ስለዚህ ጀልባዋ ላይ ደባ የተሠራው ወደቡ ላይ ቁማ በነበረች በት ጊዜ እንዳልሆነ እርግጠኞች እንሆናለን ማለት ነው ። ምክንያቱም ገና ከመንቀሳቀሷ በፊት ተበሳስታና ፉካዎቿ ተከፍተው ቢሆን ኖሮ ብዙ ሳትርቅ እዚያው አካባቢ በሰጠመች ነበር ።"

"ትክክል"

"እንግዲያው ወለሏን የበሳውና ፉካዎቹን የከፈተው ጀልባው ላይ የነበረ ሰው ነው ማለት ነው"

"ሊሆን ይችላል"

"ተጅም ሲል እርስዎም ሆኑ ዶክተር ፊሊፕስና ካፕቴን ሲሪል እንደነገራችሁኝ የታችኛው ክፍል በር ፡ መስኮቶቹ ሁሉ ተዘግተው ነበር ፡ አይደለም እንዴ?"

"ነው"

"ታዲያ የጀልባዋ ወለል በሹል ነገር ተበስቷል ፡ ፉካዎቹ ተከፍተዋል ፡ መባለ በጣም የሚገርም ነገር አይደለም እንዴ?"

"በጣም እንጂ"

"መልካም ፡ የሚያቀርቡት የተለየ አስተያየት አለዎት?"

"ምንም አስተያየት የለኝም"

"እሺ ሚስተር ዲዊንተር ፡ መቼም ስሜትዎን ክፉኛ ቢነካም የስራ ግዴታዬ ነውና የግል ሀሳብዎን የሚመለከት ጥያቄ ልጠይቅዎት እገዳለሁ ።"

"ጥሩ ፡ ይጠይቁኝ"

"በእርስዎና በሚቺ በሚስዝ ዲዊንተር መካከል የነበረው ግንኙ ነት ደስታ የሰፈነበት ነበር?"

እንግዲህ ጀማመሩኝ ። እኒያ ጥቋቁር ነጠብጣብ ፡ አይኖቼ ላይ ድቅን አሉ ። አየሩ ላይ ውርውር እያሉ ያጥበረብሩኝ ጀመር ። ያ ሁሉ

t.me/OLDBOOKSPDF

የሰው ሥጋንቅላት እያበጠ ፡ እያበጠ ሄዶ እላዬ ላይ የሚፈነዳ ፡ ያ ሁሉ አይን እየሾለ ፡ እየሾለ እላዬ ላይ የሚሰካ ፡ ሁሉም ነገር የሚበላኝ ፡ የሚያሚሚኝ... መሰለኝ ። ጣሪያው እየተረበኝ ፡ እየተረበኝ ሲመጣ ወለሉ ደግሞ ከፍ ፡ ከፍ እያለ ሊያጣብቀኝ ...

"እረ ጎበዝ እ ም እርዱኝ የ ባለቤቱ ቅ

ቅልጥ አለች — የሚለው የማከሲም ድምፅ ከሰመመን መለሰኝ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ ሀያ ሁለት

አእምሮዬ ትንሽ መለስ ሲልልኝ የት እንደነበርኩ ቀስ በቀስ መገንዘብ ቻልኩ ። ቀድም ሲል እነበርኩበት ትንሽ ክፍል ውስጥ ወለሉ ላይ ቁጭ ብዬ ነበር ። ፖሊሱ በብርጭቆው ውሃ ሲያቀብለኝ የአንድ ሰው እጅ ትከሻዬ ላይ አረፍ ብሎ ነበር ። የፍራንክ እጅ ።

የጣራው ፣ የግድግዳው ፣ የሰዉ ምስል ጥርት ብሎ ሲታየኝ "ይቅርታ ፣ መቼም እንደረበሽኳችሁ ይሰማኛል ። ግን ምን ላድርግ ? በጣም ነው የሚሞቀው ። መቋቋም አልቻልኩም" አልኩ ።

"ልክ ነሽ ፣ በጣም ይሞቃል ። ሕዝቡ ዘወትር እሮሮ ቢያሰማም ክፍሉ ምንም ሊሻሻል አልቻለም ። በመሞቱ የተነሳ ብዙ መደዛዘርት ናቸው ተዝለፍልፈው የሚወድቁ" አለ ፖሊሱ ።

"እንዴት ነሽ አሁን ?" ሲል ፍራንክ ጠየቀኝ

"በጣም ደህና ነኝ ። ግድ የለም ፣ እየተሻለኝ ስለሆነ ልትጠብቀኝ አይገባም" አልኩት

"ትንሽ ማንደርሉይ ልወስድሽ እኮ ነው"

"እይ አልሄድም"

"ማክሲም እኮ ነው ውሰዳት ያለኝ"

"የለም ፣ አንተ ከእርሱ ጋር መቆየት አለብህ" ብለውም ማክሲም ይዞኝ እንዲሄድ እንደነገረው ደጋግሞ ሲያስረዳኝ ሳልወድ የግዴን ለመሄድ ተነሳሁ ። "መሬመድ ካልቻልሽ መኪናውን ላስጠጋው" ቢለኝ እንደምችል ከነገርኩት በኋላ እንደገና የመሄዱ ሀሣብ ሲከነክነኝ "ግን እኮ ማክሲምን እዚሁ ብጠብቀው ይሻል ነበር" አልኩት

"ማክሲም ሊቆይ ይችላል" አለኝ ፍራንክ

t.me/OLDBOOKSPDF

ፍራንክ ከንዱን ይህ ወደ መኪናው ሲመለሰኝ አእምሮዬን ያስፈራን ቀው የነበረ "ማነሲም ሊቆይ ይችላል" የሚለው አባባሉ ነበር ። ለምን ? ምን ማለቱ ነው ? እያልኩ አሰላስል ነበር ።

መኪናው ውስጥ ገብተን ገሀ እንደጀመርን "ማነሲም ለምንድነው የሚቆየው ?"በማለት ጠየቅኩት ።

ፍራንክ አይኑን መንገዱ ላይ እንደተከለ "ምናልባት ምርመራውን እንደጉና ይጀምሩ ይሆናል" አለኝ ።

"የሁለንም ታ ተቀብለው የለም እንዴ ? ድንገተኛ ምርመራ ለምን ያስፈልጋል ?"

"ምን ያታወቅል ? ታብ በስተመጨረሻ ያቀረበውን መረጃ ተንተርሶ መርማሪው ነገሩን ከተለየ አቅጣጫ በማየት አዳዲስ ጥያቄም ችን ያቀርብ ይሆናል "

"ምን ማለትህ ነው ? ምን ነው የተለየ አቅጣጫ ?"

"ታብ የሰጠውን ታል ስምተሽ የለ ? ከእንግዲህ ጀልባዋ የሰጠመ ችው በአደጋ ነው የሚለውን አስተሳሰብ ማንም አይቀበለውም ማለት ነው"

"ምን እያሉት እዳ ነው ፍራንክ ? የልጅ ፌዋታ አይደለም እንዴ ? ይሆን ያህል ጊዜ ቆይቶ ጀልባዋ የተንደለችው በዚህ በዚህ ነው የሚለውን የታብን ሀሣብ እንዴት አድርገው ይቀበላሉ ?"

"እኔ ምን አውቂላቸው?"

"ታዲያ ምን ያብጀል ትላለህ ፍራንክ ? ያ ንዝናባ መርማሪ የሆነ ያልሆነውን እየፈለፈለ የማነሲምን ትእግስት አስፈራርሶ ገደል እንዳይከ ተው ነው ፍራቻዬ ።"

ፍራንክ ምንም መልስ ሳያሰጠኝ መኪናውን በፍጥነት ያሽከረክር ነበር ። ፍራንክን አስከማውቀው ድረስ በሣም ጥንቁት አሽከርካሪ ከመሆኑ የተነሳ አስፈ ግራ ቀኙን እየተገላመጠ ፡ አስፈ ጥሩንባውን እያስጮኽ ነበር የሚያሽከረክረው ። ለሚጠየቀው ማንኛውም ጥያቄ መልም ለሚተርብለት ማንኛውም አስተያየት መልስ መልም ሀሣብ አያጣም ነበር ። እና የዛሬው ለውጡ ጭንቀት ቢበዛበት አይደል ? ምስኪን ፍራንክ ።

"ያን ሰውዬ ያ እንኳን አንዴ ማንደርሰይ መጥቶ የነበረውን ሰውዬ ምርመራው ክፍል ውስጥ አየሁት እኮ" አልኩት ፍራንክን አይን አይኑን እያየሁት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ፈቃዱን ማለትሽ አያደል ? እኔም አይቸዋለሁ" አለኝ ።

"የሚገርመው ደግሞ ከሚስዝ ዳንዘርስ ጋር ነበር የተቀመጠው ። እኔ 'ምለው ግን እንዴት ሊመጣ ቻለ ? ምርመራው ላይ የመገኘት መብት ለእርሱ ማነው የሰጠው ?"

"የእንቲ ልጅ እኮ ነው" አለ ፍራንክ

"ቢሆንሳ : እርሱና ሚስዝ ዳንዘርስ በፍጹም መገኘት አልነበረባቸውም : እኔ በምንም አያኑት አላምናቸውም ። እንዳች ተንኮል የሚሸርቡ ነው የሚመስለኝ ።"

ፍራንክ አውንም መልስ ሳይሰጠኝ ወዮ እንዴሶ ቀረ ። ለማክሰም ያለው ታማኝነት ምን ያህል ዕኑ መሆኑን የተረዳሁት ከኔ ጋር እንኳን የልቡን ለመጫወት በመቆጠቡ ነበር ። ሁለታችንም ዝም ዝም እንዳልን ማንደርሱያ ደረስን ። ግራና ቀኝ ፈነቀው ያየኋቸው አበቦች እኛን በሰልፍ ለመቀበል የተዘጋጁ መሰለው ታዩኝ ። አበቦቹ ምንም ያህል ውበት በላበሱም የዕልመት ደባብ ተጫዋቾቻቸዋል የሬሣ : የመቃብር : የቀብር ሥነ ሥርዓት ደባብ ።

እቤት እንደደረስን ፍራንክ ካስገባኝ በኋላ "በደ እንግዲህ አረፍ በደ፡ እኔ ማክሰም ደፈልገኝ ይሠናልና መደዚያው ተመልሼ ልሂድ" ብሎኝ በመጣበት ተመለሰ ።

አልጋዩ ላይ ጋደም እንዳልኩ ሀሳቤን ወደ ማክሰም አሻገርኩት ። በምርመራው ነፍስ ውስዋ ምን እንደሚካሄድ በውል አለመረዳቱ በምናብ ከመሸከርከር አልታደንም ። "ምርመራ የማካሂደው ለራሴ መዝናኛ ብዬ አደደለም" የሚለው አባባሉ በእዝነ ልቦናዬ ሲደመደል ደንን ተመላለሱ መርማሪ እነቲው እንቲው አሰኘኝ ።

መርማሪው እንደነና ማክሰምን ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ሲጠይቀው —የአደጋው አለት ምሽት የት እንደነበረ —ከዚያ በኋላ ጊዜውን እንዴት እንዳሳለፈ ሁሉንም ነገር በዝርዝር እየጠየቀ ሲያፋጥጠው የቢሮች ንም ሠራተኞች እንድ ባንድ ቀርበው ታላቸውን ይስሙ ሲባል —ያች ርኩስ አሮጊት አለሁ ብላ ማክሰም ላይ ልድፍ አድረን ስትመስክርበት —ማክሰም ዙሪያው ገደል ሆኖበት : እንቱን ደፍቶ እንደቆመ ያህ ሁሉ በአእምሮዬ እየተመላለሰ አስጨነቀኝ ።

ማክሰም እንድ ወንጀለኛ ተቆጥሮ ዘብጠያ ሊወርድ ነው ማለት ነው ? እኔን ብቻዬን ትቶኝ ? ያሀን አስከፊ ሁኔታ እንዴት ልወጣው ነው ? እኔ እንጃልኝ : ፈጽሞ ልቋቋመው የምችለው አይደለም ።

መሰል ሁኔታ የደረሰባቸው አረጋውያት አስረኞችን ለማስፈታት

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለሚያደርጉት ጥረት በተለያዩ ጊዜያት በጋዜጦች አንብቤያለሁ ። ሲኖቹ ተከሳሾችን እንዲፈታላቸው ለአገር መሪዎ አቤተዳደር ምኒስትሩ ማመልከቻቸውን ፡ የእሥረኞች ወዳጆችም አቤቱታቸውን ሲያቀርቡ ፡ ምኒስትሩ ደግሞ ሕግ በማንም ላይ ተፈፃሚነት እንዳለው በመግለፅ ተከሣሾችን ስራቸው ያውጣቸው ከማለት ሌላ ምንም ሊያደርግ እንደማይችል ይነግራቸዋል ። ይሆን በየጋዜጦቹ የሚያነበው ተራው ሰው ደግሞ "ለምን ተብሎ ? ሚስቱን ገድሎ በነፃ ሊፈታ ? ሀያውት አያደለም እንዴ ያጠፋው? ምህረት ይደረግለት ማለት ማንም ተነስቶ እንዳሻው እንዲጨፈጭፍ፡ ማደፋፈር አይደል ? ግለሰቡ ወንጀሉን ከመፈጸሙ አስቀድሞ ማሰብ ነበረበት ። ሥልጣንና ክብር የወንጀለኛ መከለያ መሆን የለበትም ። ማንም ቢሆን ፡ ሹም ሆነ ባለፀጋ ከገደለ እንደማንኛውም ነፍስ—ገዳይ መገደል አለበት ። መሰቀል አለበት—ለሁሉም መተጣጫ እንዲሆን" እያለ ቁጣውን ይገልፃል ።

አንዴ ደግሞ አንድ ጋዜጣ ላይ ያየሁት ትዝ ይለኛል ። የስቅላት ፍርድ ሲፈጸም ለማየት የተኮለኮሉ የበርካታ ሰዎችን ፎቶግራፍ ይዞ የወጣው ጋዜጣ የየሰውንም የተለያየ አስተያየት አስፍሮ ነበር ። አንዳንዱ ስቅላት ወዲያው ነው ዐጥ የሚያደርገው ፡ አንገት ሰብሮ ወዲያው ጭጭ ነው ሲል ፡ አንዳንዱ ደግሞ እረ ሁልጊዜ እንዲህ ቀላል አይደለም ፡ ነፍሱ አልወጣ እያለ ስንቱ ሲሰቃይ ሁሉ የምናየው አይደለም እንዴ ? ይላል ። ከፊሉ ፡ ይመት—በቃ የተበየነበት እስረኛ ከሚታሰርበት ክፍል ተነስቶ ፡ መሰቀያው ሥፍራ ደርሶ ፡ ፍርዱ እስኪፈጸምበት ሦስት ደቂቃ ይፈጃል ሲል ፡ ከፊሉ ደግሞ የለም ከሃምሳ ሴኮንዶች አይበልጥም ይላል ። አንዱ የወህኒ ቤት አዛዡ አጎቱ እንደነገረኝ ፍርደኛው እጁ የፊጥኝ እንደታሰረ ከተዘጋጀለት መድረክ ላይ ይወጣና ሽምቀቆው አንገቱ ላይ እንደገባ የቆመበትን ሲያሽሹበትና ተንጠልጥሎ ህይወቱ ስታልፍ፡ ከዚያ በላይ ይፈጃል ባይ ነው ። ሌላው ደግሞ የወህኒ ቤት ዶክተር የሆነ ወንድም አለኝ በማለት እርሱን በዋቢነት በመጥቀስ የግሉን ዝርዝር ሀሣብ ለማስደመጥ ይሞክራል ።

ወይኔ አምላኬ ? አሁን ይህን ሁሉ ምን አሳሰበኝ ? አልኩኝና ጭንቅላቴን በእጆቼ ጥርቅም አድርጌ ያዝኩት ። ጩኸት ፡ እሪታ ቃጣኝ ። ወደ ሌላ አቅጣጫ ልምራሀ ያልኩት ሀሳቤ እያንሳፈፈ ወስዶ ከምድረ—አሜሪካ ጣለኝ—ከሚስስ ቫን ሁፐር ዘንድ ። ሚስዝ ቫን ሁፐር ከልጃቸው ጋር እንዴት ያለ መልካም ጊዜ እንደሚያሳልፉ ሳሰላስል

t.me/OLDBOOKSPDF

ከፉኛ ቀናዑባቸው — አድርጊው የማላውቀውን ። መናፈሻ ውስጥ ቁጭ ብለው ጋዜጣ ሲያገላብጡ ቅያሉው "አንቺ ሄለን ፡ ነይማ አንድ ጊዜ" ብለው ልጃቸውን ጠርተው "አየሽልኝ ይህን ጉድ ! ማክስ ደሞንተር የመጀመሪያ ባለቤቱን ገድሏል ነው እኮ የሚሉት ። እኔ ሁልጊዜ የሰውዬው ሁኔታ እንዳጠራጠረኝ ነበር ። ያቺን ጅል ተዩ አትሳሳች ብዩ ብመክራት አሻፈረኝ ብላኝ ዋጋዋን አገኘች ። አሁንማ ሳታስበው ከሰማያ መና ወረደላት ። ጋዜጦች ፎቶግራፏን ለማውጣት በርከት አድርገን እንክፈልሽ በማለት ሳያረባረቡባት አይቀሩም" በማለት ስጋዬን ሲበጭቱት ተሰማኝ...

የአልጋውን ጠርዝ አልፎ ተንጠልጥሎ የነበረውን እጇን እንድ ነገር ሲነካኝ ከተንሳፈፍኩበት የሀሳብ አለም መለሰኝ ። ጃስፐር ነበር በቀዝቃዛ አፍንጫው የዳሰሰኝ ።የውሾች ነገር በጣም ነው ግርም የሚለኝ። የሰውን ሞንቀት ፡ ሀዘን እንዴት እንደሚረዱ ፡እንዴት እንደሚሰማቸው፡ እንዴት የሀሳብ ተካፋይ ለመሆን እንደሚጥሩ በጣም ይደንቀኛል ። ጃስፐርም ብስጭት እንደተሰማኝ ፡ ሀዘን እንዳደረብኝ ተገንዝቦ ሊያፅናና ናኝ መሞከሩ እንደሆነ ገባኝ ።

እንዲሁ በሀሳብ ስንገዋለል ቆይቼ እንቅልፍ ይዞኝ ሄዶልጥ አለ ። ስንቃ አስራ አንድ ሰዓት ሆኖ ነበር ። ወደ ሰገነቱ መጣሁ ። ሰማዩ የፅልመት ካባውን ከመከናነቡም በላይ አልፎ አልፎ የሚያንራው ነንድንድ ሽብር ይነሳል ። ሁሪያ ገባው እጅግ ከመጨለሙና ወጥ ከማለቱ የተነሳ በጣም ያስፈራል ። እንዲሁ ከሚያስገመግም ዘንቦ ቢወጣለት ይሻል ነበር ።

ወደ ክፍሉ ስገባ ሮበርትን አግኝቼ እነ ማክሲም ተመልሰው እንደሆነ ጠየቅኩት ። አለመመለሳቸውን ነግሮኝ ሻይ እፈልግ እንደሆነ ጠየቀኝ ። ምንም እንዳላሰኘኝ ስነግረው ከትካዜዬ ጋር ትቶኝ ወጣ ። ጥቂት ቆይቶ— አስራ አንድ ተኩል ላይ ሮበርት ተመልሶ መጣና

"መኪናው ልክ አሁን ወደ ግቢ ገባ ፡ እመቤቱ" አለኝ

"የትኛው መኪና?" ስል ጠየቅኩት—መላ አካሉ በድንጋጤ ተውጦ

"የጌቶች መኪና ነዋ እመቤቱ" አለ ሮበርት እየተጣደፈ

"እራሱ እየነዳ ነው የመጣው?"

"አዎን ! እመቤቱ"

እነሳለሁ ብል እግሮቼ ከዱኝ—እንደ ቁጠማ እየተጥመለመሉ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደምንም ሶፋውን ተደግፌ ቆምኩ ። ንብሮዬ ደረቀ ። ዓይኔ ፈጦ እንደቆምኩ ማክሲም ብቅ አለ ። ከእግር ጥፍሬ እስከ ራስ ወጉ ተንዘፈዘፈ ። ማክሲም በሩን ከፍቶ ገባና እዚያው እንደቆመ አትኩሮ ይመለከተኝ ነበር ። ከመጠን በላይ የተጻከመ ከመምሰሉም በላይ በጣም አረጀብኝ ። ፊቱ ከምትርትር ፡ ሰውነቱ ሁሉ ዝልፍልፍ ብሏል ።

"ቢቀ ፡ ሁሉንም ነገር ተገላገልነው" ሲለኝ መናገር ተርቶ መንቀሳቀስ ተሳነኝ ።

ለጠቅ አድርጎም "እራሷን አጠፋች ብለው ውሳኔ አሳለፉ" አለ ማክሲም

ሳፋው ላይ አረፍ አልኩና "እራሷን ገደለች ብለው ወሰኑ ነው የምትለኝ ? ለዚህ ያበቃትንስ ምክንያት ምንድነው አሉ ?" ስል ጠየቅሁት።

"እሱን ለእግዚር ትቸውታለ ። ምክንያቱን ለማወቅ እምብዛም የተጨነቁ አልመሰለኝም ። ያ ሠሪጅ የምትዪው ሽማግሌው መርማሪ 'ሚቹ የገንዘብ ችግር ነበረባት ወይ ?' ብሎ አልጠየቀኝ መሰለሽ?" አለ ማክሲም ጥያቄውን በማስታወስ አውንም እየተገረመ ።

ወደ መስኮቱ ሄዶ ዓይኑን በአረንጓዴው መስክ ላይ አሳረፈና "አውንስ እግዚአብሔር ሊገላግለን ነው መሰለኝ የሚዘንብ ይመስላል ። ከሳንየን እስከዚህ ያመናው እንዲቹ እንደከዳኝ ነው የመሰላት" አለ ።

የእርሱን ሀሳብ ወደ ጉን ብዬ "እኔ 'ምለው" ስል ጀመርኩና "ለመሆኑ መርማሪው ምን አለ ? እስካሁንስ ስምን ቆየህ ?" በማለት ጠየቅኩት ።

"ምን የረባ ነገር ያነሳል ብለሽ ? ምርመራውን እንደ አዲስ ከስሩ ጀምሮ ማንም ጉዳዩ የሚያላቸውን ጥቅጥን ነገሮች እየፈለፈለ ሲያጉላላኝ ላብድ ምንም አልቀረኝም ነበር ። እንደምንም ሁሉንም ሞጥ አድርጌ በትእግሥት አሳለፍኩት ። እዚያ በሩ ሥር ዝልፍልፍ ብሬ ፣ ካየሁሽ በኋላ ነበር ነገሮችን ሁሉ በፅሞና ፡ በትእግሥት ማሳለፍ እንደሚገባኝ የተገነዘብኩት ። ዓይኔን አንድ ጊዜ እንኳ ከዚያ ከሠረጅ ላይ ሳልነቅል ነው የዋልኩት ። መቼም ያ ፊት ፡ ያ አስተያየት እስከ ሕይወቱ ጥግሚ አያረሳኝም ። አፋ ፡ እንዴት ሙት ብዬልሻለሁ መሰለሽ" ብሎኝ አረፍ አለ ።

ብዙም ሳንቆይ ሻይ ቀርቦልን እየጠጣን ሳለ ፍራንክ የት እንደሄደ ስጠይቀው "ቁሱን ለማንገር ሄዷል ። እኔም ያንቺ ነገር አሳስቦኝ ስርጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

መጣሁ እንጂ አብሬው መሄድ ነበረብኝ" አለኝ ።

"ቱሱን ለምንድነው የሚያነጋግራቸው ?" ስል ጠየቅኩት

"ማምሻውን ቤተ---ክርስቲያን ውስጥ አንድ የሚሠራ ሥራ ስላለ ነው"

ርብቃን ለመቅበር እንደሆነ ገባኝ ። ማክሰምም እንደገባኝ አወቀና "አስራ ሁለት ተኩል እንዲሆን ነው የተስማማነው ። ከኔ ፡ ከናራንክ ፡ ከኮሎኔል ጀልያንና ከቱሱ በስተቀር ማንም ሰው አያውቅም" አለኝ ።

"ተመልሰህ ባትወጣ እንዴት ደስ ባለኝ" አልኩት ።

ጥቂት ዝም ፡ ብሎ ቆየና "ደርሼ ስመለስ ሁሉንም ነገር በስፋት እንፈላሰጥለን ። ሀ ብለን አዲስ ሕይወት ለመጀመር መዘጋጀት ያለብን ይመስለኛል ። መቼም መጥፎ ባል እንደሆንኩብሽ ይሰማኛል" አለ ።

"በፍጹም ፡ እንዲህ ብለህ መናገር የለብህም"

"ግድ የለም ፡ ይህንን ፈተና ከተወጣነው ትዳራችንን እናድሰዋለን። ከእንግዲህ አንቺም ሆንሽ እኔ በየግል ሕይወታችን ተከልለን መኖሩን አብቅተን የጋራ ሕይወት እንጀምራለን ። ልጆችም እንወልዳለን" ካለ በኋላ ሰዓቱን አይቶ "በደ እንግዲህ እንዳልዘገይ ልሂድ" ብሎኝ ተነሳ ።

ለመውጣት ሲንቀሳቀስ እጁን ይዤ "እኔም አብሬህ እመጣለሁ" ስለው

"አደ ምን ታደርጊያለሽ ? ያንቺ መሄድ አያስፈልግም" ብሎኝ ወጣ።

ማክሰኞም ከሄደ በኋላ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ምን እንደሚያደርጉ ሳስላስል ቆየሁ ። ከዚያ የሚገኘውን የንግክሰምን የቤተሰብ መቃብር አይቼው ባላውቅም እናቱ አባቱና ሌሎች የሞቱ ዘመዶቻቸው ሸሳጥኖቻቸው እንደተኙ ይገኙ ይሆን ? አሁን ደግሞ የርብቃን ፈላ ሲያስቀምጡ የዚያችን በስህተት የተቀመጠችውን ምስኪን ሴትዮ ፈላ ምን ሊያደርጉት ነው ? አወጥተው ሊወረውሩት ? እኔ እንጃ...

"...ሰው ሆዩ አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ ..." የሚለው የቱሱ ፍትሐት በጀርባዬ ሲንሾካሾክብኝ ቀስ በቀስ መጣል የጀመረው ዝናብ ገላንሲኝ ። በፍጥነት ሄድኩና መስኩን ከናቹ የዝናቡን አወራረድ እመለከት ጀመር ። ዝናቡ እያየለ ሄዶ ፈቱን እየገረፈ ወደ ቤት ውስጥ ሲዘልቅ ከመጠን በላይ ደስ አለኝ ። በዝናቡ እጅግ ከመመሰጤ የተነሳ ማን እንደገባ ሳላውቅ "ይቅርታ የኔ አመቤት" የሚለውን ድምፅ ሰምቼ ዞር

t.me/OLDBOOKSPDF

ስል ፍሪዝ አጠገቤ ቁመው አየኋቸው ። "ይቅርታ የኔ እመቤት ፡ ጌቶች ይቆዩ ይሆን ?" በማለት ሲጠይቁኝ

"ብዙ የሚቆይ እንኳን አይመስለኝም ፡ ምነው ? ደህና ?" አልኳቸው

"እንግዳ መጥቶ ነው ። ጌቶችን አገናኝኝ ፡ በጣም አስቸኳይ ነው ስላሉኝ ነው"

"ማንነው ? የሚያውቁት ሰው ነው ?"

ፍሪዝ ፊታቸውን እንደማኮሳተር አሉና "አምን እመቤቱ ፡ ሚቺ በሕያውት በነበሩበት ጊዜ አዘውትረው ይመጡ ነበር ። ሚስተር ፊሽል የሚባሉ ሰው ናቸው"

መስኮቱን ዘጋሁት ። ወደ ፍሪዝ ዞር ብዬ "እንግዲያውስ እኔ አነጋግረዋለሁ" በማለት እንግዳውን እንዲያስገቡ ነገርኳቸው ። ሰውዬውን ለማነጋገር የፈለግኩት ከማክሲም ጋር ሳይገናኝ ቶሎ ለመሸኘት እንጂ ምን ብዬ እንደማነጋግረው እንኳን አላውቅም ነበር ።

ፍሪዝ እንግዳውን አስገብተው ወጡ ። ሰውዬው ባለፈው ጊዜ ካየሁት አንዳንድ ለውጦች ይታዩበታል ። አለባበሱ ትንሽ ቆሸሸ ከማለቱም ሌላ ፡ ፀጉሩ በትጉ አልተበጠረም ። ፊቱ ወሐይ ክፉኛ ያጠቃው ይመስላል ። መጠጥ ተሜጭኖት እንደሆንም አላውቅ ዓይኖቹ በርበሬ መስለዋል ።

ከመያናጠጌ የተነሳ የእግዜር ሰላምታ ማቅረቡን እንኳን ረስቼ "ማክሲም እነ እቤት የለም ። ጥዋት ጽሕፈት ቤቱ ውስጥ እንድታነጋግረው ተጠሮ ብትደዝ አይሻልም ?" አልኩት ።

"መቆየቱ እንኳን አያገደኝም ። ደግሞም ወደዚህ ስመጣ ምግብ ቤቱ ውስጥ የማክሲም ቦታ ተዘጋጅቶ ስላየሁ ብዙም የሚያቆየኝ አይመስለኝም" አለ እንደመዘባነን ብሎ

"ለእራት ይመለሳል ብለን ነበር ። አሁን ግን ቶሎ የሚመለስ አይመስለኝም ። በጣም ሳያመሽ አይቀርም" አልኩት ።

"ፈርጥዒል በይኛ?" አለ ፊሽል በነፉል ፈግታ ። "በእርግጥ አሁን በተፈጠረው ሁኔታ ማድረግ የሚገባውን ነው ያደረገው ። አየሽ ፡ አንዳንድ ሰዎች አለባልታን በጣም ስለሚፈሩ በተቻላቸው መጠን ይሸሹታል ።"

"ምን ማለትህ እንደሆነ አልገባኝም"

"እውነት ? አልገባሽም እንዴ ? ዓይኔን አታስቲው ? ይልቅ እሱን

t.me/OLDBOOKSPDF

ተያና አሁን ሻል አለሽ ?ቀን በምርመራው ውጥ አጥወልውሎሽ ስትወድቂ ሳይ በጣም ነበር ያዘንኩት ። መጥቼ ልረዳሽ አስቤ የክብር ዘብሽ መኖሩን ሳይ መለስ አልኩ ። መቼም ፍራንክ ከርውሌይ በደስታ ሳይናውዝ አልቀረም ። እንዴት ነው ? እቤት ድረስ ይሆሽ መጣ አይደለም? እኔ ትንሽ ላንሸራሽርሽ ብል አምስት ሚትር እንኳን አብሬህ አልሄድም አላልሺኝም ? እ...''

አቋረጥኩትና ''ማነሰምን ለምንድነው የፈለግከው?'' ስለው

ጠረጴዛው ላይ ከነበረው ጋኬት አንድ ሲጋራ አወጣና ''በማጨስ እንደማትቀየሚኝ ተስፋ አደርጋለሁ ። ምናልባት አይስማማሽ እንደሆን ብዬ ነው ። ምን ይታወቃል ? እናንት ሙሽሮች እኮ ጠባየ—ቅብጥብጦች ናችሁ'' አለ ሲጋራውን እያቀጣጠለና በነበልባሉ ውስጥ ሰረቅ አድርጐ እየተመለከተኝ ። ''ባለፈው ጊዜ ካየሁሽ ወዲህ ያደግሽ ትመስያለሽ ። ለመሆኑ ምን እያደረግሽ ነበር ? ከፍራንክ ጋር እየተንሸራሸርሽ ?'' አለኝ ጢሱን በአፉ በቀስት እያደረገ ። ''በነገራችን ላይ ውስኪና ሶዳ ልታገርልኝ ትችያለሽ ?''

ምንም ሳልናገር መጥሪያውን ነካሁት ። ፈቭል በሶፋው ጠርዝ ላይ ተቀምጦ እግሩን ያወዛውዛል ። ያ የአሽሙር ፈገግታው አሁንም አልተለየውም ። ሮበርት ደወሉን ስምቶ ሲመጣ ''ለሚስተር ፈቭል ውስኪና ሶዳ አምጣ'' አልኩት ።

''ታዲያስ ሮበርት'' አለ ፈቭል እየተቁነጠነጠ ''ከተያየን ረጅም ጊዜ ሆነን እኮ ጃል ፡ አሁንም የኬሪዝን ኮረዶች እያሳበድካቸው ነው ?''

የሮበርት ፊት ከመቅጽበት ቀላ ። ቀና ብሎ እኛን ''ጎድ የለም አላሳጣህም ፡ የታዘዝከውን ቶሎ አምጣልኝ'' አለው ፈቭል ያገሙና ።

ሮበርት ሲወጣ ፈቭል እየተንቁተቁተ ይስቅ ጀመር ። የሲጋራው አመድ ወለሉን በሙሉ ለሰበሰው ።

''ያገርምሻል ፡ አንቺ ሮበርትን በአረፍት ጊዜው ከኔ ጋር አዝናናዋለሁ ብል ርብቅ በሩዋም አታደርገውም ብላ በአምስት ጋውንድ ተወራረደች፡፡ና ረታኋት አልሻለሁ ። ታዲያ ያንለት በሕይወቱ አልረሳውም ። እንዴው ስንቁተቁት ነው ያመሸሁት ። ሆ ! ሆ ! አሁንም ያስቀኛል ሳስበው ፡ ይሄ ሮበርት የሞላ ሰው እንዳይመስልሽ ። ካየናቸው ሁሉ ምርጥ የተባለችዋን ነው ይዞ ያመሸው''

ሮበርት የታዘዘውን ይዞ ሲመለስ ፊቱ እንደቀላ ነበር ። ውስኪውን ሲቀዳለት ፈቭል ፈገግ ብሎ ሲያስተውለው ቆየና በሳቅ ተንከተከተ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ወዲያው ማሻሸት ጀመረና "ዘማው ይሄ ነበር አይደል?" አለው ዓይኑን ከሮበርት ላይ ሳይነቅል "እንዴት ነው ሮበርት ፡ አውንም ወርቅማ ወተር ትወዳለህ እንዴ?"

ሮበርት ቀና ብሎ በስስ ፈገግታ ኮንቶት ሲወጣ ፈቭል እየተንከተከተ ነበር ። "ምስኪን ፡ ከዚያን ጊዜ ወዲህ እድሉን ያገኘ አይመስለኝም ። ሽሚዋ ፍሪዝ ቆንጠጥ አድርጋ ሳትያዘው አልቀረችም ።" አለ ፈቭል ሳቁን ሳያቋርጥ ።

ሙስኪውን እየጠጣ በዓይኑ ዙሪያውን ይኮሻል ። አልፎ አልፎ ፈገግ እያለ ሲያየኝ ከቆየ በኋላ "ማክስ ለእራት ባያመጣ እኮ ደንታም የለኝ ።" አለና "አንቺስ?" ሲል ጠየቀኝ ።

እጇን የኋለት አጣምሬ እንደቆምኩ የሆነ ያልሆነውን ሲቀባጥር ዝም ብዬ ካየሁት በኋላ "ይቅርታ አድርግልኝ ሚስተር ፈቭል ፡ እንደ ነውር አትቁጠርብኝና ማክሲምን ለምን እንደፈለግኩው የማትነግረኝ ከሆነ ዝም ብለህ መቀመጥህ አግባብ አይመስለኝም ። ቀደም ብዬ እንደነገርኩህ ዒት ቢሮው ሂደህ ልታነጋግረው ትችላለህ ። ቀኑን ሙሉ ድክም ብሎኝ ስለዋልኩ ነውና ይቅርታ" አልኩት ።

ከሶፋው ላይ ፈንጠር ብሎ ወርዶ ፡ መለኪያውን እንደጨለጠ ወደኔ መጣና "ተይ አትጨክኚ እንጂ ፡ እኔም ብሆን ደክሞኝ ነው የሞልኩት ። እንዴት ብቻዬን ጥለሽኝ ትሄጃለሽ ? ምነው? የሚባላ አውሬ ነው ፡ አትቅረቢው አሉሽ እንዴ ? መቼም ማክስ ስለኔ የሆነ ያልሆነውን እየፈጠረ ሳይነግርሽ አይቀርምና ብትፈሪኝም አይፈረድብሽም" ሲለኝ ዝም አልኩት ። ፈቭል ልፍለፋውን ቀጠለ "እንደ ትልት አስፈሪ ተኩላ እኮ ነው የምትቆጥሪኝ ። አለመተዋወቃችን ነው እንጂ ርግብኩቱን ባየሽ ነበር ። ለማንኛውም ላሳየሽኝ መልካም መስተንግዶ ከጉልበቱ ሽብረክ ብዬ አድናቆቱን እገልጽልሻለው ።"

አፉ ይተሳሰር ጀመር ። እጀቹን እያወራጨ ፡ ጥቂት ከተንገዳገደ በኋላ መለኪያውን ጠረጴዛው ላይ አስቀምጦ ዲስኩሩን ቀጠለ "መቼም የዛሬው ውኔታ ምንኛ ልቤን እንዳደማው ሳትገነዘቢ የቀረሽ አይመስለኝም ። ርብቃ እኮ የአጐቴ ልጅ ነበረች ። ስወዳት ደማሞ እንዲህ እንዳያመስልሽ" አለኝ ።

"አውቃለሁ ። እኔም በውኔታው በጣም ነው ያዘንኩት" አልኩት

t.me/OLDBOOKSPDF

"ይገርምሻል ፡ አብረን ከማደጋችንና እጅግ ከመቀራረባችን የተነሳ ምርጫዬን ፡ ፍላጐታችን ሁሉ በጣም የተመሳሰለ ነበር ። በዚህ ዓለም ላይ እኔም ከእሷ እሷም ከኔ ሌላ የምንወደው ሰው አልነበረም። ይህ ሁሉ ተደማምሮ ነው ወዘኔን ያከበደው"

"ልክ ነው ፡ ይገባኛል"

አፀፋ ፈገግታው ጠፋ ። ኩስትርትር አለና "ከእንግዲህ የማክስ እርምጃ ምን እንደሚሆን ነው ማወቅ የምፈልገው ። ያ የተልዕ ምርመራ አበቃ ብሎ እጁን አጣምሮ በእርዳታ ሊተመጥ? መስሎታል" አለኝ ከአንገቱ ወደኔ ዘንበል እያለ ። ቀስ በቀስ ድምፁ እየጐላ ሄደ "ርብቃ እውነተኛውን ፍትህ እንድታገኝ ነው የምሻው ። እራሷን ገደለች ነው ያሉት እኒያ ጉቦኛ ዳኞች? እኔና አንቺ ግን ሀቁ ይህ እንዳልሆነ አሳምረን እናውቃለን ። አይደለም እንዴ? ምነው ዝም አልሽ? እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል ነውና መቼም አንድ ቀን ሀቅ መውጣቱ አይቀርም ።" አለና ይበልጥ ወደኔ ዘንበል ብሎ "አይመስልሽም? እ?" ሲለኝ ፡ ፡

በሩ ተከፈተና ማክሲም ገባ ። ፍራንክ ተከትሎታል ። ማክሲም ቀጥ ብሎ ቆሞ "ምን ትፈጥር መጣህ ይሞሞ?" ሲል ፌቭል ላይ አፈጠጠበት ።

ፌቭል ዞር አለና እጅቹን ኪሶቹ ውስጥ ከቶ ቆመ ። ለፍጥሜው አፀፋውን ሲሰጥ ቆየና ፈገግ ብሎ "እንደ እውነቱ ከሆነ ጊታ ማክስ ፡ የምርመራው ውጤት የተሳካ በመሆኑ እንኳን ደስ ያለዎት ለማለት ነው የመጣሁት"

"ቀጥ ብለህ ትወጣለህ? ወይስ እኔና ከሮውሌይ ግፍትረን እንድናስወጣህ ትሻለህ?" አለው ማክሲም ኮስተር ብሎ።

"ይታገሱ ጌታው" አለ ፌቭል ሲጋራውን አቀጣጥሎ ሶፋው መደገፊያ ላይ እየተቀመጠ "ይታገሱ ፡ ይታገሱ እንጂ" በማለት ተዘባነነ።

"የምናገረውን ፍሬነገር እንዲሰማ የሚፈልጉ አይመስለኝምና ፍቃድዎ ቢሆንና በሩን ቢዘጉት?" አለ ፌቭል አይኑን ከማክሲም ላይ ሳይነቅል ።

ማክሲም ከቆመበት ሳይንቀሳቀስ ከሮውሌይ ነበር በሩን የዘጋው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

“እንግዲያው ያዳምጡኝ ጌታ ማክስ ፡ ከዛሬው ጉድዎ ባልጠበቁት መንገድ በመገላገልዎ ደስ ሳይልዎ አልቀረም ። ምርመራው ተጀምሮ እስኪያበቃ እዚያው እንደነበርኩ ሳያዩኝ አልቀሩም ። ምርመራው አሳሳቢ ደረጃ ላይ ሲደርስ ባለቤትዎ ተዝለፍልፈው ሲወድቁም አይቻለሁ ። ዳሩ እሳቸው ምን ያድርጉ? አይፈረድባቸውም ። ምስጢሩ ያለው ከሌላ ዘንድ ። ጌታው እንደተመኙት ተሳክልዎት አይደል? መቼም ዳኞችን ውሀ ብጤ ሳያቀማምሷቸው እንዳልቀሩ እርግጠኛ ነኝ ። በዚ…’’ ብሎ ሳያበቃ ማክሲም ወደ እርሱ ሲጠጋ ንግግሩን አቋረጠና በእጆቹ ምልክት እያሳየው ቀጠለ ‘‘ምነው ጌታዬ ትንሽ ቢታገሱ? ገና፡ ገና መቼ ጨረስኩና? ብዙ በተናገርኩ ቁጥር የማያስደስትዎ ፡ ካለማስደስትም አልፎ አደጋ ላይ ሊጥልዎት የሚችል ነገር እንደሚፈጠር ከወዲሁ ቢከሰትልዎት አይደል እንዲህ የሚያደርግዎት?’’ አለ ፈቭል ዓይኑን እያገላበጠ ።

እግሮቹ ሰውነቱን መሸከም ተስኗቸው እንደመብረክረክ ሲሉብኝ አጠገቤ ባገኘሁት ወንበር ላይ አረፍ አልኩ ። የወንበሩን መደገፊያዎች በእጆቹ ጥርቅም አድርጌ ያዝኳቸው ። ፍራንክ ወዴት መጥቶ ከበስተጀር ባዬ ቆመ። ማክሲም ግን ዓይኑን ፈቭል ላይ እንደተከለ እንበረበት ፈዞ ቆሚል ።

‘‘ይስሙኝ ጌታ ማክስ ፡ በእርስዎና በባለቤትዎ መካከል የሚደበቅ ምስጢር ይኖራል ብዬ አልገምትም ። እንደሚገባኝ ከሆነ ፍራንክም ከናንተ ጋር ባለው ቅርበት ምስጢራችሁን ቢጋራ የሚከፋችሁ አይመስለኝምና ለእናንተ ለምስቱ ደስተኛ ስላሴዎች የማወጋችሁ አለኝና በደንብ አድምጡኝ ። ሁላችሁም እንደምታውቁት እኔና ርብቃ ፍቅረኞች ነበርን። ፍቅረኞች እንደነበርን ድሮም እንደነገራችሁበትና እንዳልካድኩ ሁሉ ዛሬም አፈን ሞልቼ የምናገረው ነው ። አይ አዙሮ አለማየት? እስከዛሬ እንደማንኛውም ጅል ርብቃ የሞተችው አደጋ ገጥሟት ነው የሚለውን አሳሳች አባባል አምኜ ተቀብዬ ነበር ። ይሁን ስሰማ የነፋሁበን ቢሰማኝም የጀግና አሟሟት በመሞቷ ደግሞ ‘ይሁ ነው ለርብቃ የሚስማማት — ስትታገል እንደኖረች ሁሉ ስትታገል ሞተች’ በማለት ከራሁባት።’’ አለና ንግግሩን አቋርጦ እያንዳንዳችንን በዓይኑ ከዳሰሰን በኋላ ቀጠል አደረገና “ባለፈው ሰሞን ደግሞ ጋዜጠኞች ‘የርብቃ ጀልባ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተገኝች ፡ ውስጧ የሰው ፈሳ አለበት' ብለው የጸፉትን ሳነብ ግራ ገባኝ ። ጀልባዋ ውስጥ ከርብቃ ጋር የነበረው ማን ነው? እያልኩኝ ስጨነት ከረምኩ ። ነገሩን ለማጣራት ወደ ኬረዝ ብቅ ብዬ ነበር ። ከሚስዝ ዳንዘርስ ጋር ተገናኘሁና ፈሳው የርብቃ መሆኑን ነገሩኝ ። በወቅቱ ስላሚሚጂ የተሰጠውን መላምት ሁሉ አምኜ ተቀብዬ ቆይቼ በዛፈው ምርመራ ያገኛው ምንም እንኳን ውጤቱ በመርማሪውና በዳኞቹ ተደበስ ብሶ ቢያልፍም ሚስተር ኦብ ያቀረበው መረጃ ትልቅ ፍንጭ ነው የሰጠኝ ። እና ጌታ ማክስ? ጀልባዋ ወለል ላይ ስለተገኙት ቀዳዳች ፡ ስለተከፈቱት ፋኳዎች የሚሰጡን አስተያየት ይኖራል?'' ሲል ማክሲምን ደጋግሞ ጠየቀው ።

ይህን ጊዜ ማክሲም ለመናገር እንደሚሻ ከአጠቃላይ እንቅስቃሴው ቢታወቅበትም አንዳች ያገደው ያህል ''እ...እ...'' ሲል ቆየና ''አሁን ማን ያመት ቀኑን ሙሉ ስዳረቅ የዋልኩ አንሶኝ እንደገና ልናዘዝ? ደግሞስ አንተን ማን ጠያቂ አደረገህና? ማስረጃዎችን ሰምተሃል ፡ ብይኑንም ሰምተሃል ። ሁሉም ፡ መርማሪው ፡ ዳኞች ፎርም የተስማሙበትን ነገር አሁን ምን ይጠበስ ብለህ ነው የምተጠይቀኝ?'' አለ ዝግ ባለ ድምፅ ።

''ሃ!ሃ!ሃ!'' ሳቀ ፈቭል ''የትኛው ብይን? ርብቃ እራሷን ገደለች የሚለው አደናጋሪ ውሳኔ? ርብቃ ናት እራሷን የምትገድል?'' አለና በንዴት እየተወራጨ ከክሱ አንዲት ብጣሽ ወረቀት አውጥቶ ''እርስዎ ግን ጣጣ ፈንጣጣዬ አለቀ በማለት እፎይ ብለው ሊቀመጡ? ከደሙ ንፁህ ነኝ ብለው እጅዎን ሊታጠቡ? እህ? መስሎዎታል! እስቲ ርብቃ ከመሞቷ በፊት ዕፋልኝ የነበረውን ይህን ማስታወሻ ይስሙና ምን እንደሚሉ ልስማዋ'' በማለት ደረቱን እየነፋ ወረቀቱን ገላለጠው ።

ወረቀቱ ላይ የስፈሩትን ቀጫጭን ፡ ጥምልምል ፊደላት ሳይ ልቤ ተሸበረ። ፈቭል ወረቀቱን እያዘናረ ካሳየን በኋላ ያነብልን ጀመር

'እዚሁ ሆኜ በቴሌፎን ላነጋግረህ ብሞክር ላገኝህ አልቻልኩም ። አሁኑኑ ወደ ማንደርሌይ መመለስ ነው ። ዛሬ ማምሻውን ጅምር ጉጀው ውስጥ እሆናለሁና ይህ ማስታወሻ በጊዜ ከደረሰህ በመኪናህ ተከትለህ ድረስብኝ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሴሊቱኝ ሁሉ እዚያው ጉጅው ውስጥ ለማደር ስለፈለግሁ በሩን አልቀረቅረውም ። ከፍተህ መግባት ትችላለህ ። የምንግርህ ጥብቅ ጉዳይ ስላለኝ አደራ እንዳትቀር ። በተቻለ ፍጥነት ለመምጣት ሞክር ።

ርብቃ'

ማስታወሻውን አንብቦ እንዳበቃ ወረቀቱን አጣጥፎ ኪሱ ውስጥ ከተተና ''ታዲያ እራሱን ለመግደል የፈለገ ሰው እንዲህ ብሎ ያጽፋል? ቤቱ ስገባ ማስታወሻውን ባገኘውም ነበሴሊቱ አስር ሰዓት ሞኖ ስለነበር ላልያርስ ምን አደከመኝ በማለት ተውኩት እንጂ ስከንፍ እመጣ ነበር ። ኧረ እንዲያውም የዚያን አለት ርብቃ ለንደን ውስጥ ትኖራለች ብዬ ፈጽሞ አለመገመቴ ነው ለዚህ ያበቃኝ...'' አለና በቁጭት እራሱን ነቀነቀ ። ቁጭ ካለበት ማነሲምን ትከተር ብሎ ያየው ነበር ። ሌሎቹን ግን ዝም ብለን ቀረን ።

''ለመሆኑ'' በማለት ቀጠለ ፈቭል ''ይህንን ማስታወሻ ዛሬ በምርመራው ወቅት መርማሪው አያቶት ቢሆን ኖሮ ምን ይውጠት ነበር ጌታ ማነስ?''

''ታዲያ አ አሁን ወስ ወስደህ ለምን አ·አ· አትሰጠ —ውም። ኖ ኖሎ በል — አን ካሳ ዶር ሳያ — ሳይቀድምህ'' አለ ማነሲም በንዴት ።

''ረጋ ፡ ረጋ በል እንግዲህ ወንድሚ ። ግንፍል ፡ ግንፍል ማለቱ የትም አያደርስህም ። ለኔ ያለህ ጥላቻ ከፍተኛ መሆኑን ባውቅም በዚህ ቂም ይዣ ከፉ እንዲነካህ አልሻም ። ቆንጆ ሚስት ያላቸው ወንዶች ሁሉ በቅናት መብገናቸው ያለ ነው ። አንዳንዶቹ አልፈው ተርፈው የአቴሎን እርምጃ ሲወስዱ የምናየው ነውና አዲስ ነገር አያደለም ። እንዲህ አይነቶቹ ሰዎች መቼም የተፈጥሮ ባህሪያቸው በመሆኑ ለምን እንዲህ ያደርጋሉ ብዬ አልፈርድባቸውም ። እኔ ግን የራሴ የሆነ ሕብረሰባዊ እምነት አለኝ ። ወንዶች ሚስቶቻቸውን መጋራት ሲችሉ ለምን እንደሚገድሏቸው ሊገባኝ አይችልም ። ቆንጆ ሴት እንደ መኪና ትማ አልታ ከአገልግሎት ውጭ የምትሆን አይደለችም ። ይልቁን ብዙ በተጠቀምክባት መጠን ይበልጥ እየበረታች ይበልጥ ልምድ እያገኘች

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው የምትሄደው… እንግዲህ ፡ የኔ ወንድም ሀሳቤን ሁሉ ቁልጭ ፡ ዝርዝር አድርጌ ያስቀመጥኩልህ መሰለኝ… ለምን ከአንድ ሰምምነት ላይ አንደርስም? እንደምታውቅኝ ባለፀጋ አይደለሁም ። በዚህ ላይ የቁማር ሱስ አለብኝ ። ይሀን ሱሴን እንደ ልብ እንዳልወጣ ደግሞ የወረት እጥረት እጅ እግሬን አስሮታል ። እና በየአሙቱ ዕለት ወይም ሦስት ሺህ ፓውንድ የምትሰጠኝ ከሆነ ገላገልከኝ ማለት ነው ። በዚህ የምንስማማ ከሆነ ደግሞ ላላስቸግርህ በእግዚአብሄር ስም እምልልሃለሁ'' አለ ፈቭል አይኖቹ እየተጉረጠረጡ ፡ ትንፋሹ እጥር እጥር እያለ ።

''ምነው ሰውዬ ሰላም ብትሰጠኝ?'' አለ ማክሲም ቁጣው ገንፍሎ ''ውላልኝ ብዬሃለሁ ውላልኝ ''

''ቆይ ፡ ቆይ ማክስ ፡ እንዲህ አይደለም ። እስቲ ግማሽ ደቂቃ ፍቀድልኝ'' አለ ፍራንክ ። ወዲያው ወደ ፈቭል ዞር ብሎ ''ሀሣብህ ወዴት እያመራ እንደሆነ ይገባኛል ። እስቲ ማክሲም ሊከፍልኝ ይገባል የምትለውን አትጨነን ንገረኝ'' አለው ።

ማክሲም ፊቱ ቅይርይር ሲል ፡ ስሮቹ እየተገታተሩ ሄዱና ''ስማ ፍራንክ ፡ ይህ የግል ጉዳዬ ነውና ባልቃ መግባት የለብህም ። ለእንዲህ ዓይነቱ ማስፈራራያ ቀዳዳ መክፈት አልችልም'' አለ ።

''የኔ ወንድም ፡ ባለቤትህ የነፍስ ጓዴ ፡ በስቅላት የተቀጣው ሰውዬ ሚስት እያለ ሰዎች ጣታቸውን እንዲቀስሩባት የምትሻ አይመስለኝም'' አለ ፈቭል ሥነ ብሎ እየሳቀና ወደኔ እየተመለከተ ።

''ስማኝ አንተ ሰው'' አለ ማክሲም እንደዚያው እንደተቆጣ ''ምናልባት አስፈራራሁት ብለህ ልብህ ውልቅ ብሎ ይሆናል ። ለምትሸር በው ሁሉ ቅንጣት ፍራቻ እንደማያድርብኝ ልታውቅ ይገባል ። ኮሎኔል ጄልያንን በቴሌፎን ብጠራቸው ወዲያው ከች እንደሚሉ አታውቅም? እና ወረደት ሳያንሰህ ቶሎ ብትወጣ ይሻልሃል ብዬአለሁ … ዋ በኋላ…''

ፈቭል አይኑን ሰልጥጦ እያየውና በሳቅ እየተንከተከተ ''አታድርገው ም እንጂ ብታደርገውማ መልካም ነበር ። በገዛ እራሷ እባብ ጠመጠመች አሉ ። ኮሎኔል ጄላያንን የሚያሳምን በቂ ሞብዋ እንዳለኝ እያወቅህ አንገትህን ለገመድ ለመስጠት ትጣደፋለህ?'' አለው ።

ማክሲም እያዘገመ ወጥቶ ቴሌፎኑ መደነበረበት ክፍል አመራ ። የቴሌፎኑን ቅጭልጭልታ ሰሰማ ''እባክህን ፍራንክ ፡ ሂደህ ተው

t.me/OLDBOOKSPDF

በለው'' አልኩት ፍራንክን ።

ፍራንክ የተቻለውን ያህል ቢጥርም ማክሲም አሻፈረኝ ብሎ ኮሎኔል ጁልያንን በቱሉፎን አግኝቶ በአስቸኳይ እንዲመጡ ሲጠይቃቸው ሰማሁ ። ጥቂት ቆይቶ ወደ ነበርንበት መጣ ''ጁልያን አሁኑኑ መጣሁ ብለውኛል'' አለና መስኮቶቹን ከፋፍቶ ፡ ጀርባውን ለኛ ሰጥቶን ቆመ ። ዝናቡ እንደዚያው ጠንከር ብሎ እየዘነበ ነበር ።

ፍራንክ ''ማክሲም ፡ ማክሲም'' እያለ ደጋግሞ ቢጣራም ማክሲም መልስ ስለነፈገው አጠገቤ መጥቶ ቆመ ።

''እባክህን ፍራንክ መላ ምታ እንጂ? ውጣና ኮሎኔል ጁልያን ሲመጡ ጠብቀህ ጥሪው በስህተት የተደረገ ነው ብለህ በዚያው ብትመልሳቸውስ?'' አልኩት ፍራንክን ዝግ ባለ ድምፅ ።

ማክሲም እዚያው ጀርባውን ሰጥቶን እንደቆመ ''ፍራንክም ሆነ ማንም ሰው ይህን ክፍል ለቆ ሊወጣ አይችልም ። የግል ጉዳዬ ስለሆነ እኔው እራሴ እወጣዋለሁ ፡ ኮሎኔል ጁልያን ደግሞ አውን ከአሥር ደቂቃ በኋላ ይመጣሉ'' አለ።

ክፍሉን ፀጥታ ዋጠው ። ፌቭል እግሮቹን አጣምሮ ጠረጴዛው ላይ ያገኘውን ጋዜጣ ያገላብጣል ። ምን እንደማደርግ ግራ ገባኝ ። ፍራንክም ቢሆን እንደኔው ነበር ። ልብ ወለድ መፅሐፍ ወይም ቴያትር ቢሆን ኖሮ ሽጉጤን አንስቼ ፡ ፌቭልን ግንባሩ ላይ አጠብሰውና ሬሣውን ቁምሣጥን ውስጥ በደበቅነው ነበር ። ግን ሽጉጡም የለ ፡ ቁምሣጥኑም የለ ። ማክሲም እግር ላይ ወድቄ ፌቭል የጠየቀህን ገንዘብ ስጠው ማለት አልችል —እንዲያው እጅና እግሬን አጣምሬ ተቀምጬ ውሂቤ ውጬን ፡ ዝናቡን በመስኮት በኩል ማየት ብቻ ።

የዝናቡ ኃይል የመኪናቸውን መቃረብ ሊያሰማን ስላልቻለ የክፍሉ በር ሲከፍት ነበር ኮሎኔል ጁልያን መምጣታቸውን ያወቅነው ። ማክሲም ፊቱን መልሶ ለኮሎኔል ጁልያን አስፈላጊውን ሰላምታ ካቀረበ በኋላ ፈጥነው በመምጣታቸው አመሰገናቸው ። እንግዳውም ለእኔና ለፍራንክ ሰላምታ እየሰጡ ''በጣም ብርቱ ፡ አስቸኳይ ጉዳይ ነው ሲሉኝ እኮ ነው ስገሰግስ የመጣሁት'' አሉ ።

''ደግ አድርገዋል ። ጉዳዩ ብርቱ ባይሆንማ ኖሮ በዚህ ዝናብ ከቤትዎ አንቀሳቅሰዉ አወጣዎት ነበር? ይሽውልዎት ፡ ይህ ሰው ጃክ

t.me/OLDBOOKSPDF

ፈቭል ይባላል ። የሚች ባለቤቱ የአጎት ልጅ ነው። ከዚህ ቀደም ያውቁት እንደሆነ ግን እንጃ'' አለ ማክሲም ወደ ኮሎኔል እየተጠጋ ።

ኮሎኔሉ ጭንቅላታቸውን እየነቀነቁ ''መልኩ እንኳን እንግዳ አልሆነብኝም ። ጊዜው ራቅ ይበል እንጂ እዚሁ ያየሁት ይመስለኛል'' አሉ ።

ማክሲም ''ልክ ነዎት'' አለና ወደ ፈቭል ዞር ብሎ ''ቀጥላ ልጅ ፈቭል'' አለው ። ፈቭል ይዞት የነበረውን ጋዜጣ ጠረጴዛው ላይ ወርውሮ ብድግ አለ ። ፈገግታ አይታይበትም ። ሳይንገዳገድ ቀጥ ብሎ ወደ ኮሎኔል ጄልያን ተጠጋ ። የኮሎኔሉን መምጣት እንዳልወደደው ከሁኔታው ይንፀባረቃል ። ''ይስሙኝ ኮሎኔል'' አለ ፈቭል ድምጹን አጉልቶ ''ዙሪያ ጥምጥሙን መሄድ የሚያስፈልግ አይመስለኝም ። በአጭሩ እዚህ የመጣሁበት ዋናው ምክንያት በዛሬው ምርመራ ላይ የተሰጠው ውሣኔ ስላላረካኝ ነው''

''እህ?'' አሉ ኮሎኔል ጄልያን ''ታዲያ ይህ አባባል የሚያምረው በአንተ ነው? በሚስተር ደዊንተር?''

''ጉዳዩ በቀጥታ ይመለከተኛልና መናገር እችላለሁ ። ይህንንም የምለው የርብቃ የአጎት ልጅ በመሆኔ ብቻ ሳይሆን በህይወት ኖራ ቢሆን ባሏ ልሆን እችል ስለነበረ ነው'' አለ ፈቭል ።

ኮሎኔል ጄልያን ድንግጥ አሉና ''ነገሩ ለእኔ እንግዳ ነው ። ይሄ ነገር እውነት ነው እንዴ ሚስተር ደዊንተር?'' ሲሉ ጠየቁ ።

ማክሲም ትከሻውን እየነቀነቀ ''እረ እኔም ለመጀመሪያ ጊዜ ነው የምሰማው'' አለ ።

ኮሎኔል ጄልያን ሁለቱንም ተራ በተራ እያዩ '' ፈቭል እስቲ ችጋርህን ግልፅ አድርገህ ንገረኝ'' አሉ ።

ፈቭል ከሰደረያው ኮት የርብቃን ማስታወሻ አውጥቶ ''... እንግዲህ ይህን ያንብቡና ማስታወሻው እራሷን ለማጥፋት የወሰነች ሴት የምትዕፈው መሆን አለመሆኑን የግልዎን ሕሊናዊ አስተያየት ይስጡበት'' አለ ።

ኮሎኔሉ መነፅራቸውን አድርገው ማስታወሻውን ካነበቡ በኋላ ለፈቭል መለሱለት ''እንዲሁ እንዳነበብኩት እንኳን አይመስልም ። ከበስተጀርባው ያለው ምስጢር ግን ሊገባኝ አልቻለም ። ላንተ ወይም

t.me/OLDBOOKSPDF

ለሚስተር ዩዊንተር ግልፅ ሊሆን ይችላል '' አለ ኮሎኔል ።

ማክሲም መልስ አልሰጠም ። ፈቭል ግን ''ርዝመት ከጎጇው እንድንገናኝ ማለቷ በግልፅ ሰፍሮ የለም እንዴ? የምንግርህ ነገር አለኝ ማለቷም እንዲሁ ግልጽ ነው ። ምን ልትነግረኝ አስባ እንደነበረ ማናችንም ልናውቅ የምንችል አይመስለኝም ። ቁም ነገሩ ይህ ሳይሆን ብቻዬን ልታገኝና አንድ ነገር ልታሞኝ መፈለጓ ነው ። እኔ ርዝመትን አብጠርጥሬ እስክማውቅት ብቻዋን በጀልባዋ ለመንሸራሸር መውጣቷ አይደንቀኝም ። ግን ፡ ግን ፡ እንደ አንድ ጅላጅል ንክ የራሷን ጀልባ በስተ እራሷን ልታሰጥም? አታደርገውም ፡ አላደረገችውም'' አለ ታላቁን ሬገጥ እያደረገ ። ፊቱ ልውጥውጥ ይል ጀመር ። የርዝመትን ማስታወሻ በእጁ ያፍተለትለዋል ።

''ይቅርታ አድርግልኝና የኔ ወንድም'' አለ ኮሎኔል ጂልያን ቅዝቀዝ ብለው ''እንዲህ መበሳጨቱ ምንም ሊጠቅምህ አይችልም ። እኔ የወረዳው አስተዳዳሪ እንጂ መርማሪ ወይም ውሣኔውን ያሳለፈው ችሎት አባል አይደለሁም ። ሥልጣኔ በሚፈቅድልኝ ደረጃ አንተንም ሆነ ሚስተር ዩዊንተርን በተቻለኝ ከመርዳት ወደ ኋላ አልልም ። የአንተህ ልጅ እራሷን ነው የገደለችው የሚለውን ውሣኔ አልተበልም ነው የምትለው? አይደለም? በሌላ ወገን ደግሞ ዛሬ በተከናወነው ምርመራ ጀልባ ሰሪው ስለ ጀልባዋ መበሳትና ስለፉነሎቹ መከፈት ያተረበውን ሀሣብ እንደማናችንም የሰማህ ይመስለኛል ። እንግዲያው የአደጋው መንስዔ ምንድነው ትላለህ?''

ፈቭል አንገቱን አዙሮ አይኑን ማክሲም ላይ አሳረፈው ። ማስታወሻውን በጣቶቹ እያፍተለተለ ''ጀልባዋን የነደለችውና ፉነሎቹን የከፈተችው ርዝመት አይደለችም ። አውንም ቢሆን ርዝመትን ሰው ነው የገደላት ባይ ነኝ ። ገዳይዋንም እንድነግርዎ ከፈለጉ ያውልዎ መስኩቱ አጠገብ ቁሞልዎት ፡ በማን አለብኝ እብሪት ደረቱን ነፍቶ ያየኋቸልዎታል ። የሚገርመው ደግሞ የሚስቱ ሙት ዓመት ከመከበሩ ፡ ሌላ ሚስት ለማግባት መሽቀዳደሙ ። እርሱ ነው የርዝመት ገዳይ ነፍስ ገዳዩ ሚስተር ማክሲሚሊያን ዩዊንተር ። በደንብ ይዩት እንጂ ፡ ፍርዱን ከወዲሁ እንዳወቀ ሁሉ የተሰቀለ ሰው ይመስል የለም እንዴ...?'' አለና ከት ከት ብሎ ይስቅ ጀመር ። አውንም የርዝመትን ማስታወሻ እያፍተለተለ እንደ ሰካራም ፡ እንደ ጅል ድምፁን ከፍ አድርጎ መሳቁን ቀጠለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ ሀያ ሦስት

የፈቭል ዓይኖች በርበሬ መስለዋል ። ፊቱ ደም ለብሷል ። ጣቱን ቀስሮ ፡ እየተንዳገደ እንዲያ ማስካካቱን ኮሎኔል ጁልያን አልወደዱለትም ። "ስውዬው ሰክሯል መሰለኝ ። የሚናገረውንም አያውቅ" አሉ ኮሎኔል ረጋ ብለው ።

"እኔ ነኝ ሰክሬአለሁ?" አለ ፈቭል ድምፁን ከፍ አድርጉ አይሳሳቱ ጌታዬ ፡ የእርስዎ አስተዳዳሪነትና ኮሎኔልነት ደንታም አይሰጠኝ ። ሕግን ተንተርሽ ተንስቻለሁና የምፈራ አይምሰልዎት ። በዚህ ክፍለ ሀገር ውስጥ ሌሎች አስተዳዳሪዎች መኖራቸውንም አይዘንጉ ። የሥራ ብቃት ጐድሏቸው ፡ ከሥራቸው ተባረው ፡ የመመግደቂያ ሚዳሊያቸውን ደረታቸው ላይ አንጠልጥለው በጉራ የሚወጣጠሩ ወታደሮች ሳይሆኑ የአርሶ ማስተዋል ፀጋ የተላበሱ ፡ የፍትሀንም ምንነት ጠንቅቀው የሚያውቁ አስተዳዳሪዎች በርካቶች ናቸው ። ማክስ ደዊንተር ርብቃን ለመግደሉ በቂ መረጃ ስላለኝ በአሸናፊነት እንደምወጣ እርግጠኛ ነኝ ።"

"ስማ ፡ ስማ ሚስተር ፈቭል ፡ በምርመራው ላይ የተሰጠው ብይን ትክክል አይደለም የምትል ከሆነ ለምን በወቅቱ ፡ እዚያው ፍርድ ቤቱ ውስጥ ተቃውሞህን አልገለፅክም? ለምንስ ይህን ደብዳቤህን አታቀርብም ነበር?" አሉ ኮሎኔል ጁልያን አሁንም ረጋ እንዳሉ ።

ፈቭል ኮሎኔሉን ትኩር ብሎ እየተመለከተና እየሳቀ "ለምን አላቀረብኩም? ሳልፈልግስ? ሀሳቤን እፈለግኩበት ቦታ የማቅረብ መብት ስላለኝና ከሚስተር ደዊንተር ጋር በግል እንድንወያይበት ስለፈለግኩ ነው" አለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህን ጊዜ ማክሲም ከቆመበት ተንቀሳቅሶ ወደፊት ቀረበና ቀደም ሲል ፈቭል የሰነዘረውን ማስፈራሪያና ገንዘብ እንዲሰጠው መጠየቁን ተናገረ ። ጉዳዩንም ፍራንክና እኔ መስማታችንን ሲያስረዳ ፍራንክም ሁሉንም ነገር እንደሰማ እማኝነቱን ሰጠ ።

ኩሉኔል ጄልያን ይህን ያህል ገንዘብ ካልተሰጠኝ ፡ ይህ ካልተደረገልኝ ሰም አጠፋለሁ ፡ ምስጢር አወጣለሁ በሚሉ አንዳንድ ተንኮለኞች ሳቢያ የብዙ ንፁሃን ሰዎች ኑሮ እንደሚናጋ ፡ አፈጉበርባሪዎችም ብዙውን ጊዜ ለእስር እንደሚዳረጉ ካስረዱ በኋላ "... ሚስተር ፈቭል? አራስህን በሚገባ የምትቆጣጠር ከሆነ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ ። አውን እንዳዳመጥኸው ሚስተር ደዊንተር ላይ ከበድ ያለ ውንጀላ መሰንዘርህን እንድታውቀው ያሻል ። ለመሆኑ ለዚህ ውንጀላህ የምታቀርበው ማስረጃ አለህ?" በማለት ጠየቁ ።

"የምን ማስረጃ? ከጀልባዋ መበላት በላይ ምን ማስረጃ ያስፈልግና?" አለ ፈቭል ።

"እና እርሳቸው ለመብላታቸው ምን ማረጋገጫ አለህ? ምስክር ማቅረብ ትችላለህ?"

"ምንም ማስረጃ ፡ ምስክር ፍለጋ የሚያስኬድን ነገር የለም ። ሚስተር ደዊንተር ርብቃን ገድሏታል ። ከእርሱ ሌላ ማን ሊገድላት ኖሯል?"

"ይህማ እንዴት ሊሆን ይችላል ? መቼም የኬረዝ ነዋሪዎች እጅግ በርካታ መሆናቸውን ታውቃለህ ። ታዲያ በየቤቱ እየሆርክ ከሰሀን የሚያጠናክርልህ ምስክር ለምን አትፈልግም ?" አሉ ኩሎኔል ጄልያን ።

"ያቺ ናት ጨዋታ ! ሁሪያ ጥምጥሙን ከሚሸከረክሩ በቀጥታ መዳጅዎን ለመርዳት እንደሚሹ አያናግሩምን ? አብራችሁ ማህበር እንደም ትጠጡ የአደባባይ ምስጢር ነው ። የማንደርሌው ጊታ ፡ እኒህ ትልቁ ሰው አይንም እያየ መቀመት ሲጠርዱ እንዴት ሊያስችልዎ ? እንዲህ ነው የሙያን ግዴታ መወጣት! እንዲህ ነው እንጂ የሕዝብን አደራ መጠበቅ ! እንዲህ ነው ስልጣን የማለሰቦች መጠቃቀሚያ ሰትሆን! ጀርባህን ልከክልህ ፡ ጀርባዬን እከክልኝ!"

"ምላስህን ቆንጥጠው ሰውዬ ፡ ሞ" አሉ ኩሎኔል ትንሽ እንደመቆጣት ብለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምላስህን ቆንጥጠው፤ እኮ ፡ ዐቂን ስላወጣ፤ ሊያሩጉት፤ እኔ እንደሆን እሰክ ፍርድ ቤት ያርሺ ተከራከሬ የምረታበት በቂ ማስረጃ እንዳለኝ እንዲያውቁት ። እንዲያውም ያዊንተር ርብቃን የገደለው በኔ ምክንያት ነው ። ፍቅረኛዬ እንደነበረች በሚገባ ያውቅ ስለነበር በግኖ ነው የገደላት ። የዚያን እለት ከኔ ጋር ተጠሮ እንደነበራት ስላወቀ ሆን ብሎ ነው አሰተድሞ የገደላት" አለ ፈቭል ።

"መልካም ፡ አሁን የነገርከንን በጥሩ ተረትነቱ እንቀበለዋለን ። አሁንም ያጋማሚ የማስገንዘብህ ለምትናገረው ሁሉ በቂ ማስረጃ እንዲኖር ርህ ነው ። ያርገጡ ሲፈጸም ያየ የአይን ምስክር ማቅረብ የምትችል ከሆነ የማትታመንበት ምክንያት የለም ። ስለዚህ..."

"ያሉዩ ፡ ያሉዩ" አለ ፈቭል ለስለስ ብሎ "አዎን ይቆዩ...እንዲያውም ያዊንተር ድርጊቱን ሲፈጽም ያየ ምስክር ማቅረብ ከቻልኩሳ?"

ኮሎኔል ጂልያን ትክሻቸውን ነቀነቁ ። ፍራንክ ማክሰሚን በጥር ጣሬ መልክ ሲያስተውለው አየሁት ። ማክሰም ደማሞ ታል ሳይተንፍስ ዓይኑን ፈቭል ላይ ተክሎታል ። የፈቭል የመጨረሻው እንጋገር ሚንቅላቱን ነፋኝ ቢመታው ፍርሀት አደረብኝ ። ልቤ ተረበሸ ። ፈቭል እንደሚለው በእርግጥም ምስክር ሊኖረው ይችላል ብዬ አሰብኩ ። እኒያ በተለያዩ አጋጣሚዎች ሰምቼአቸው እብድ የዘባረቅቸው በማለት ችል ያልኳቸው የተጽፉ ፈረጠ አረፍተ ነገሮች በጅሮዬ ያጭሚሉ ጀመር ። እዚያ ታች ነው ያሉችው አይደል? ከእንግዲህ አትመለስም?' 'ለማንም አልተናገርኩም ።' 'አሶች በልተዋታል አይደል?' ያ ንክ ቢን ይሆን ሁሉ መቀባጠሩ ያለ ምክንያት አለመሆኑ እየገባኝ ሄደ ። ዛሮቹ መሃል ተደብቆ ማክሰም ያደርግ የነበረውን አንድባንድ ቢያይ ነው ። ይሆን ሳሰላስል እንዳች ነገር መላ አካሌን መረረው ።

"እንድ አእምሮው የተንካ ጅላጅል አለ ። አብዛኛውን ጊዜ ከባህሩ ዳርቻ አይጠፋም ። እንዳንዴ የእየሩ ሁኔታ ሞቅ በሚልበት ጊዜ ጫካው ውስጥ ሰለሚያድር ከርብቃ ጋር ባህሩ ዳርቻ አካባቢ ስንዘዋወር ፡ ተያይዘን ወደ ጉጅው ስንገባና ስንወጣ ብዙ ጊዜ አይተናል ። ስለሆነም የዚያን እለቱን ሁኔታ የማየት እድሉ በጣም የሰፋ ነውና ይምጣና ታሱን ይስጠን" አለ ፈቭል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ነገሩ ግራ ያጋባቸው ኮሎኔል ጂልያን ፈቭል ምን ማለቱ እንደሆነ ሲጠይቁ "ቢንን ማለቱ ነው ። ያንዱ ሞሰኛችን ልጅ ነው ። ከልደት ጀምሮ አእምሮው የላሸቀ በመሆኑ የሚናገረውንና የሚሠራውን የሚያ ውቅ ሰው አይደለም" አለ ፍራንክ አልፎ አልፎ ማክሲምን በዓይኑ ገረፍ እያደረገ ።

"ምን ለማለት ፈልገህ ነው የኔ ወንድም ?" አለ ፈቭል እየተቁነጠ ነጠ ። "ሰውዬው አይን ስላለው ያየውን መናገር የሚሳነው አይደለም ። ለሚቀርብለት ጥያቄ አምን ወይም አያደለም ብሎ መመለስ እንደሚችል እየታወቀ የምን ነገር ወዲያ ወዲህ ማምታታት ነው? ይምጣ ብቻ እኔ እንዲናገር አደርገዋለሁ ።"

"ምን ትላላችሁ ጃል?" አለ ኮሎኔል ሦስታችንንም በየተራ እየታኘ "ሰውዬውን አስቀርበን ብንጠይቀውስ?"

ማክሲም "ምን ጥያቄ አለው? ይምጣ እንጂ" አለና ርበርት ሂዶ እንዲያመጣው እንዲያደርግ ፍራንክን አዘዘው ።

ፍራንክ እንደ ማመንታት ሲል ፡

"ምነው ፍራንክ?" አለ ማክሲም እየተጣደፈ "ሂድና አስመጣው እንጂ ፡ ነገሩ ይደር የሚባል አይደለም ። አሁኑኑ መፈጸሩስ አለብን"

ሞንቅ ፡ ጥብብ አለኝ ። ፍራንክ መልእክቱን አድርሶ ተመለሰ ። ሌሎቻችን በዝምታ ተውጠን ሳለ ፈቭል ብቻ ነበር እንደመጣለት የሚቀባጥረው ። በሳት እየታጀበ የሆነ ያልሆነውን ይለፈልፋል ። "...መቼም የዚህች ማንደርሌይ ንብ ነገሥት ነች" አለ ማክሲምን በአይኑ ቂጥ እያየ "ስለሆኑም ማንም እርስዎን አሳልፎ ለመስጠት አይደፍርም—ክቡር የወረዳው አስተዳዳሪ ሞምር ። ክብርት ባለቤትም እንኳን አይፈረድባትም — በባሏ ላይ ምስክርነቷን የምትሰጥ ሴት የለችምና ። የክሮውሌይን ነገር ደግሞ እናውቃለን ። ጊታውን አጋልጠ የት ሊገባ? ይህም ብቻ ሳይሆን እኔ ላይ ቂም ሳይኖረውም አይቀር ። ምን ትላለህ ክሮውሌይ? ከርብቃ ጋር እምብዛም እንዳልተናነህ ሁለታችንም የምናውቅ ይመስለኛል ። ይልቅ የተመቸህ አሁን ነው ። መቼም አዲሷ ሙሽራ ባጥወለወላት ቁጥር ፈጥኖ ለሚደርስላት ተወዳጁ ክንድህ ትልቅ ባለውለተኛ እንደምትሆን አልጠራጠርም ። አይዞህ ፡ ለማንኛውም የተሻለ እድል የሚገጥምህ ቀን ብዙም አይርቅ ። ዳኛው በባለቤቷ ላይ

t.me/OLDBOOKSPDF

ይሙት በቃ ሲፈርድበት ሰምታ ስትዝለፈለፍ ፡ ያኔ በደንብ እቅፍ ፡ ድግፍ ታደርጋታለህ”

ማክሲም እንዴት ተፈናጥሮ እንደሄደ ሳላይ ፈቭል ተንገዳግዶ ፡ ከሶፋው ጋር ከተጋፈጨ በኋላ ወለሉ ላይ ሲዘረር ነበር ከፉኛ እንደመታው የገባኝ ። ማክሲም ፈቭልን በመምታቱ እራሱን ዝቅ ያደረገ መስሎ ተሰማኝ ። የሁኔታዬን መለዋወጥ ተገንዝቤው ነው መሰለኝ ፡ ኮሎኔል ጄልያን ጠጋ አሉኝና “ፎቅ ወጥተሽ አረፍ ብትዪ ይሻላል መሰለኝ” አሉኝ ።

ሞንቅላቱን እየነቀነቅኩ “አይ ፡ ግድ የለም” አልኳቸው በሹክሹክታ ። ፈቭል እንደምንም እየተንተባተበ ተነስቶ ሶፋው ላይ ተቀመጠ ። ፊቱን በመሀረቡ እየጠረገ “የሚጠጣ ነገር ፡ የሚጠጣ ነገር ስጡኝ” አለ ።

ማክሲም ቀና ብሎ ፍራንክን ሲያየው ተነስቶ ወጣ ። ብዙም ሳይቆይ ሙስኪና ሶዳ ይዞ መጥቶ በብርጭቆ ቀላቅሎ ሰጠው ። በእንድ ትንፋሽ ሞልጥ አድርጎ ሲጠጣው ዘገነነኝ ። ማክሲም ጀርባውን ለፈቭል ሰጥቶ እንደ በፊቱ በመስኮት ደጅ ደጁን ሲያይ የኮሎኔል ጄልያን አይኖች ደግሞ ከእርሱ ላይ አልነቀል አሉ ። ኮሎኔሉ እንዲህ አፍጥጠው ማክሲምን መመልከታቸውን አልወደድኩትም ። ለምን? እርሳቸውም ይጠረጥሩት ጀመር እንዴ?

ቤን እስኪመጣ ሁላችንም በፀጥታ ተሙጠን እንጠባበቅ ነበር ። ደቂቃው የአመት ያህል እየረዘመ አልንዝ ያለኝ እንሶ ከደጅ የሚሰማው የዝናቡ ጠብታ ልቤን አሸበረው ። በዚሁ ሁኔታ ከሩብ ሰዓት በላይ ከቆየን በኋላ ፍራንክ ድንገት ብድግ አለና “መጣ መሰለኝ” ብሎ በሩን ከፍቶ ወጣ ። ወዲያው ተመልሶ እየገባ “አይዞህ ቤን ፡ ምንም የሚያስፈራ ነገር የለም ፡ ሚስተር ደዊንተር ሲጋራ ሊሰጡህ ነው ያስጠሩህ” አለው ለዘብ ብሎ ።

ቤን እየተጥመለመለ ገብቶ በሩ አጠገብ ቆመ ። የሰራን ባርኔጣውን በእጁ ይዟል ። ያለ ባርኔጣ ሳየው የመጀመሪያ ጊዜዬ ስለነበር በጣም ያረጀና እርቃኑን የቆመ መስሎ ታየኝ ። ሞንቅላቱ ፀጉር የሚባል ነገር አይታይበትም ። የከፍሉ መብራት ያጥበረበረው ይመስል ዓይኖቹን ከፈት ዘጋ እያደረገ ዙሪያውን ይቃኛል ። ዓይኑ እኔ ላይ ሲያርፍ በመጠኑ

t.me/OLDBOOKSPDF

ፈገግ አልኩለት ። የለየኝ አልመሰለኝም ። ዓይኖቹን እያርገበገበ ወደ ሴላ አትጣጫ መለሳቸው ።

ፈቭል እርምጃዎቹን እየቆጠረ ወደ ቤን ተጠጋና "እንደምን ነህ ጃል ? ለመሆኑ ኑሮ እንዴት እያደረገህ ነው ?" አለው ።

ቤን ግን መልስ ሳይሰጠው ትኩር ብሎ አየው ። "ምነው? አታውቀኝም እንዴ?" ሲል ፈቭል ጥያቄውን ሰነዘረ ። ቤን ባርኔጣውን እያሽከረከረ "እህ?" አለ ። ፈቭል የሲጋራ ፓኬቱን አንስቶ "ሲጋራ ልጋብዝህ?" ሲለው ቤን ዞር ብሎ ፍራንክንና ማክሲምን አያቸው "ሣድ የለም" አለው ማክሲም "የምትፈልገውን ያህል መውሰድ ትችላለህ"

እጁ እየተንቀጠቀጠ አራት ሲጋራዎችን መዘዘ ። ሁለቱን በግራ ጆሮው ጆርባ ሁለቱን በቀኙ አኖራቸው ።

ፈቭል በድጋሚ "ታውቀኛለህ አያደለም እንዴ?" በማለት ጠየቀው ።

ቤን አሁንም መልስ ሳይሰጠው እንደፈዘዘ ሲቆም ኮሎኔል ጂልያን ጠጋ ብለውት "አየህ ቤን ፡ አንድ ሁለት ጥያቄዎች ጠይቀንህ እነ በተጥታ ወደ ቤትህ እንልክሃለን ። ማንም ባንተ ላይ ክፋት የሚያስብ የለምና እመነን ። እሺ ፡ እኔው ልጠይቅህና ፡ ሚስተር ፈቭልን ታውቀው የለ?" ሲሉት ሞንቅላቱን ነቀነቀና ለመጀመሪያ ጊዜ "አላውቅም ፡ አ—ያቺው አ—ላው—ቅም" አለ ።

"እንግዲህ አትጃጃል" አለ ፈቭል ቆጣ ብሎ "ብዙ ጊዜ ከሚስዝ ደዊንተር ጋር ወደ ጐጆው ስሄድ አላየኸኝም? ደጋግመህ እንዳየኸኝ እርግጠኛ ነኝ ። አይቼሃለሁ ፡ አውቅሃለሁ ለማለት ምን አስፈራህ?"

"አይ ፡ አይ ፡" አለ ቤን እየተንገራገረ "ማ ን ን ም አ—ላ—የ—ሁም"

"አንተ ደደብ ቀጣፊ ፡ ሽምጥጥ አድርገህ መካድህ ነው? ከሚስዝ ደዊንተር ጋር ሜካው ውስጥ እየተንሸራሸርን ወደ ጐጆው ስንገባ ስንት ጊዜ አይተኸን አላየሁም ትለኛለህ? እንዲያውም አንዴ በመስኮት ቀዳዳ ስታየን እጅ ከፍንጅ አልያዝንህም?" አለ ፈቭል ቁጣው እያየለ ።

"እህ?" አለ ቤን በድንጋጤ

"እንዴት ያለ ግሩም ምስክር ነው ያቀረብክልን" አሉ ኮሎኔል

t.me/OLDBOOKSPDF

በማሽሚጠጥ ።

ፈቭል ተሽከርክሮ ወደ ኮሎኔሉ ከሠረ በኋላ "ሆን ብሎ የታቀደ ሴራ መሆኑን መች አጣሁት? ብላችሁ ብላችሁ ይሀንንም ጅል ምናምን ጥላችሁለት አፉን ለጎማችሁት? ከአሥር ፡ ከሠያ ፡ ከሰላሳ ጊዜ በላይ እንዳየኝ ፡ በደንብ እንደሚያውቀኝ መቱ በመቱ እርግጠኛ ነኝ ። ቆይ ፡ ቆይ ..." አለና ከኪሱ አንድ ታውንድ አውጥቶ በቤን ዓይን ላይ እያውለበለበው "እሁንሳ? መቼም ይሄ የሰለቡትን የማስታወስ ችሎታህን እንደሚተካለሀ አልጠራጠርም ። እሀሳ? አሁንም አታስታውሰኝም?"

ቤን ከበፈቱ ይበልጥ ተደናግሮና ይበልጥ ጭንቅላቱን እያወዛወዘ "እ—ኔ ፡ እ —ኔ በፍጹም አ—ላ— የ—ሁ—ትም" አለና የፍራንክን እጅ ለቀም አድርጐ "እ—እ ወደ እ—ብ—ዶች ሀኪ—ም ቤ—ት ሊ—መስ —ደኝ ነው የ—መ— ጣ—ው?" እያለ ዓይኑን እያቁለጨለጨ ይማፀን ገባ።

"እያደለም ቤን ። ማንም እይወስድህም" አለው ፍራንክ ለማረጋ ጋት ትከሻውን መታ መታ እያደረገ ።

"እብ— ዶች ሀኪም ቤት አል—ፈ—ልገውም ። እ—ነ—ሱ ከ—ፉ— ናቸው ... እ—ኔ እ—ኔ ቤ—ቱ ይ—ሻለኛል ... ምን ... ም—ንም አ—ላ—ጠ—ፋ—ሁም" አለ ቤን እየተርበተበተ ።

ኮሎኔል ጂልያንም ወደ ሀኪም ቤት እንደማይሄድ እያረጋገጡለት ፈቭልን ያውቀው እንደሆነ ብቻ መልስ እንዲሰጥ በድጋሚ ቢጠይቁት የቤን መልስ ግን ያቺው አላውቀውም ብቻ ሆነ ። "መልካም" አሉ ኮሎኔል በማያያዝ "ሚስዝ ደዊንተርንስ አታስታውሳትም?"

ቤን በመጠራጠር መልክ ዓይኑን እኔ ላይ ጣል ሲያደርግ "የለም ፡ ይህችኛይቱን ማለቱ እይደለም ። ያቺኛይቱ አዘውትራ ወደ ጐጆው ትሄድ የነበረችውን" አሉት ኮሎኔል ረጋ ባለ አንጋገር ።

"እሀ?" አለ ቤን እየተቁለጨለጨ ።

"ጂልባ የንበራትን ሴትዮ አታውቃትም? አታስታውሳትም?"

ቤን ዓይኖቹን በፍጥነት እያርገበገበ "እሷማ ሄ—ዳ— አይደ ለም?" አለ

"ልክ ነህ ። ይሀንን እኛ ሁላችንም እናውቃለን ። መቼም ብዙ ጊዜ በጂልባ ትንሽራሽር እንደነበር ታውቃለህ ። ታዲያ የዚያን እለት ፡ ማለቴ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከአንድ ዓመት በፊት ልትንሸራሸር ወጥታ በዚያው የቀረች ጊዜ ፡ አንተ ባህሩ ዳርቻ ነበርክ እንዴ?" ሲሉ ጠየቁት ኮሎኔሉ ።

ቤን ተቁነጠነጠ ። ባርኔጣውን ያሽከረክረዋል ። ዓይኑ እየተቅበዘበዘ አንዴ ማክሲምን ፡ አንዴ ደግሞ ፍራንክን እየታኘ "እህ? እህ?" አለ በአንድ ፍሬ ሐሣን ድምፅ

ፈቭልም ከቤን ባልተናነሰ ሁኔታ እየተቅበጠበጠ "በል ተናገር እንጂ? ነበርክ አይደል? ሚስዝ ደሚንተር ወደ ጐጆው ስትገባ ፡ ከዚያም ሚስተር ደሚንተር ተከትሏት ሲገባ አይተህ የለም? ከዚያስ? ምን እንደተፈጠረ ንገረን ። በል ፡ በል እንጂ ምንድነው ያየኸው?" በማለት አፋጠጠው ።

ቤን እየተንዘፈዘፈ "ም—ምን አ—ላ—የሁም ። ም—ንም" በማለት እያፈገፈገ ሄደ ከግድግዳው ጋር ተጣበቀ ። "ቤት ፡ ቤ—ቱ ይሻላል ። እብ—ዶች ሀ—ኪ—ም ቤት አ—ል—አል—ሄ—ድም ። ማን—ንም አ—ላ—የሁም ። ሚ—ስ ሙስና አ—ላ—የሁ—ህም ። እ—ሉ—ሳ—ንም አ—ላ—ያት ም ። በ—በ—በፍጹም ፡ በፍ—ጹም" አለ መንተባተቡ እየባሰበት ።

ፈቭል እያዘገመ ወደ ቤን ተጠጋና አንዳች ምስጢር ይነግረው ይመስል "እሀ ፡ አንት አይጠ—መኰና የመሰልክ ጅል ፍጡር ፡ ጅላጅል የጅል መፈጨሪሻ" አለው ።

ቤን መላ አካሉ እየተናጠ ፡ ፊቱ ላይ ችፍ ያለውን ላብ በኩቱ እጅጌ እየጠረገ ፡ ዓይኖቹን ሲያቁለጨልጭ የእርዳታ ያለህ ብሎ የሚማፀን ሐሣን ይመስል ነበር ።

ከዚህ ሁሉ በኋላ ፈቭል ምስክር ብሎ ያመጣው ሰው ቅንጣት ፍንጭ ሊሰጥ እንዳልቻለ በመግለፅ ወደ ቤቱ እንዲመለስ ኮሎኔል ጁልያን ሲናገሩ ፈቭል እንደ ተድሞው ሁሉ "ደለላችሁት ፡ ሽንገላችሁት ፡ ዶለታችሁብኝ ..." እያለ ይራገም ነበር ።

ማክሲም የኮሎኔሉን ኮል ከሰማ በኋላ "አይዞህ ቤን ፡ ሮበርት እቤትህ ያደርስሃል ። ማንም ሀኪም ቤት አይወስድህምና በፍፁም አትፍራ ... እ—እባክህን ፍራንክ ፡ የሚበላው ነገር ስጡት በላቸው" አለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዲህ ነው እንጂ" አለ ፈቭል ሥክ ብሎ "ላበረከተው ግልጋሎት ጉርሻ መሆኑ አያደል? ይገባዋል ። ግዴታውን በሚገባ ተወጥቷልና ... ደግሞ ፡ ደግሞም ከጉድ አውጥቶሃልና የበለጠ ብትከፍለው ም የሚቆጭህ አይመስለኝም ። መስሎሃል ፡ ይህ ጅል ልሳኑን ቢቆልፍልህ የተገላገልክ መስሎሃል ። እኔ ፈቭል ደግሞ ፡ ታየኛለህ" አለና "አክ ፡" ብሎ ምራቁን ወለሉ ላይ ለጥፎ "እንተን መቀመቅ ካላወረድኩህ እንደ ሴት ቁጭ ብዬ እሸናልሃለሁ" በማለት ዘራፍ ይል ገባ።

ቤን ከወጣ በኋላ ፈቭል ዛቻውንና ልፍለፋውን አላቋርጥ በማለቱ ኮሎኔል ጂልያን በጣም ተበሳጨ ። "ምን ይሁን ነው የምትለው? ማስረጃ አትርብ ፡ ምስክር አምጣ ፡ አልንህ እንዴንም ማቅረብ አልቻልክም" አሉት ቆጣ ብለው ።

"አልቻልክም? እንግዲያው አለመቻሌን አሳይዎታለሁ" አለና መጥሪያውን ነካው ።

"ምን ማድረግህ ነው?" አሉ ኮሎኔል ።

"ምን አስቸኮልዎት? የማደርገውን ያዩት የለ?" አለ ፈቭል እየተጀነነ ።

ፍራዝ ደወሉን ሰምቶው ሲመጣ "ሚስዝ ዳንቨርስን ይጥሯቸው" ሲል ፈቭል ትእዛዙን አስተላለፈ ። ሽማግሌው ቀና ብለው ማክሲምን ሲያዩት ጭንቅላቱን በመነቅነቅ መስማማቱን አረጋገጠላቸው ።

"አርጊድ ብዙ የሚያውቁት አለና ይጠየቁልኝ" አለ ፈቭል ።

ጥቂት ቆይተው ሚስዝ ዳንቨርስ ገቡ ። እጃቸውን አማምረው በሩ ላይ እንደቆሙ ሁላችንንም ተራ በተራ ማተሩ ። "እንደምን አመሹ ሚስዝ ዳንቨርስ?" አሉ ኮሎኔል ጂልያን ።

"እግዚአብሔር ይመስገን ጌታዬ" ሲሉ መለሱ ሚስዝ ዳንቨርስ

"በቅድሚያ አንድ ጥያቄ ላቅርብልዎትና በሚጅ በሚስዝ ደዊንተርና በሚስተር ፈቭል መካከል ስለነበረው ግንኙነት የሚያውቁት ነገር አለ?" አሉ ኮሎኔሉ

"አምን ጌታዬ ፡ የወንድማማቾች ልጆች ነበሩ"

"የስጋ ዝምድና ማለቱ አይደለም ፡ ከዚያ የቀረበ ዝምድና እንዳላቸው?"

t.me/OLDBOOKSPDF

“ይቅርታ የኔ ጌታ ፡ ምን ማለትዎ እንደሆነ አልገባኝም ።”

“ምነው ዳኒ ፡ አውቀው እንዳለወቁ ይሆናሉ? ኮሎኔል ጁልያን ምን ለማለት እንደፈለጉ ጠፍቶዎት አይደለም ። እኔና ርብቃ የቆየን ፍቅረኞች እንደነበርን ብነግራቸው ሊያምኑኝ አልቻሉምና ይህንን እንዲያስረዱልኝ ነው ያስጠራሁዎት” አለ ፈቭል ።

ሚስዝ ዳንቨርስ ለጥቂት ሴኮንዶች ፈቭልን በንቀት ዓይን ገርመም ካደረጉት በኋላ “እኔ አላውቅም” አሉ ።

“እንዴት እባክሽ? የዚህች ጠናባ አሮጊት አይብስም? እንዴት ...” ብሎ ፈቭል ሲፎሀ ሚስዝ ዳንቨርስ አቋረጡትና “ርብቃ ካንተ ጋርም ሆነ ከሚስተር ደዊንተር ፍቅር ይዟት አያውቅም ነበር ። ወንድ የተባለ ፍጡር ሁሉ ትጠላ ስለነበር ከማንም ጋር ፍቅር አልነበራትም” አሉ ።

ፈቭል በቁጣ ገንፍሎ “ሴትዮ ምን ማለት ነው? በየጊዜው ጫካውን ሁሉ አቋርጣ ከኔ ትገናኝ የነበረው አንቺ ፊት አልነበረም? ደግሞስ የሳምንቱን መጨረሻ ብዙውን ጊዜ አብራኝ ለንደን ውስጥ ታሳልፍ እንደነበረ አታውቂም?” አለ እየተውረገረገ ።

“እና?” አሉ አሮጊቲ ማሾፍ እየቃጣቸው ። “ይሄ ምን የሚያስደንቅ ነገር ነው? ይህን ስላደረገች ብቻ ፍቅር አድሮባት ነበር ማለት ነው? እርሷ እቴ ፡ ሥራም አላጣች ። የፈለገችውን ማድረግ ደግሞ መብቷ መሰለኝ ። እርሷ ግብረ ሥጋ ግንኙነት ታደርግ የነበረው ለሳቅ ለጨዋታ ፡ በወንዶች ላይ ለመሳለቅ ብላ እንጂ ቅንጣት ፍቅር አድሮባት አልነበረም ። ካንተም ጋር ሆነ ከማንም ጋር ከተገናኘች በኋላ እንዴት ታፌዝባችሁ እንደነበረ ባወቅክ”

ይህ ድንገተኛ ውርጅብኝ ሁላችንንም አስደነገጠን ። የማክሲም ፊት ወዲያውኑ ነው አመድ የለበሰው ። ፈቭል ፈዘ ቀረ ። ኮሎኔል ጁልያን ሪዛቸውን ያፍተለትላሉ ። ክፍሉን ወጥታ ውጠታል ። ትንፍሽ የሚል ጠፋ። ድንገት የተሰማው የሚስዝ ዳንቨርስ ለቅሶ ወጥታውን አደፈረሰው። የሚሰማው የገናቡ ኧኧታና የአሮጊቲ ለቅሶ ብቻ ነበር ። አሮጊቲ ማልቀስ ሲጀምሩ በሩን በርግዶ መውጣት አሰኘኝ ። ፌዝ ፡ ፌዝ አለኝ ።

አሮጊቲን ሀይ የሚል ጠፋ ። ብቻቸውን ሲነፋረቁ ቆይተው ቀስ

t.me/OLDBOOKSPDF

በቀስ ለቅሷቸው ጋብ እያለ ሲሄድ "እንዴ ፡ ያዳምጡኝ እስቲ ሚስዝ ዳንቨርስ?" አሉ ኮሎኔል ጁልያን "ለመሆኑ ሚስዝ ደዊንተር እራሷን እንድታጠፋ የሚገፋፋት ምክንያት ነበረ ብለው ይገምታሉ?"

"በፍጹም ፡ በፍጹም" አሉ ሚስዝ ዳንቨርስ ሞንቅላታቸውን እየነቀነቁ ።

"ይኸውላችኋ ፡ እኔስ ምን ነበር ያልኳችሁ? አልሰማ አላችሁኝ እንጂ" አለ ፈቭል ።

"ምነው ዝም ብትል?" አሉ ኮሎኔል ቆጣ ብለው "እስቲ ሴትዮዋ እንዲያስቡበት ጊዜ ስጣቸው ። ይህ ጥያቄ ሁላችንንም ግራ እንዳጋባን የተስማማን መሰለኝ ። ያንተንም ማስታወሻ ቢሆን ሀሰት ብዬ ውድቅ አላደረግኩትም ። ለእንድ ጉዳይ እንዳንጋርህ እፈልጋለሁ ብላ መፃፏን ሁላችንም አይተነዋል ። እንቆቅልሽ የሆነብን እኮ ይሄ እንድ ጉዳይ የተባለው ምን እንደሆነ መፍታቱ ላይ ነው ። ምናልባት ሚስዝ ዳንቨርስ ማስታወሻውን ሲያነቡ ትውስ የሚላቸው ነገር ይኖር ይሆናልና እስቲ ወረቀቱን ስጣቸው"

ፈቭል ትክሻውን ከነቀነቀ በኋላ ወረቀቱን ከኪሱ አውጥቶ ሚስዝ ዳንቨርስ እግር ላይ ወረወረው ። አሮጊቷ ጉንበስ ብለው ወረቀቱን አንስተው ሲያነቡት የሁላችንም ዓይን እርሳቸው ላይ እንደተተከለ ነበር። "ታዲያ ይሄ ምንድነው?" አሉ ሚስዝ ዳንቨርስ እንብበው ሲያበቁ "ምን ማለቷ እንደሆነ ሊገባኝ አልቻለም ። ለሚስተር ጃክ የምትነግረው ያን ያህል ከበድ ያለ ጉዳይ ቢኖር ኖሮ አስቀድማ እኔን ታዋየኝ ነበር ።"

ይህን አስመልክቶ አሮጊቷ ምንም እንደማያውቁ ደጋግመው በማስታወቃቸው ኮሎኔል ጁልያን ጥያቄውን ወደ ሌላ አቅጣጫ አዞሩት ። የዚያን እለት የርብቃ የሎንዶን ውሎ ምን ይመስል እንደ ነበረ የሚያውቅ ሰው እንዳለ ለሰነዘሩት ጥያቄ ፈቭል ብድግ ብሎ የመሰለውን ቢዘባርቅም ጉዳዩ ያለው አልነበረም ። ሚስዝ ዳንቨርስ ግን ርብቃ ቀደም ሲል በሰጠቻቸው ትእዛዝ መሠረት ከቀኑ ስድስት ሰዓት እስከ ሰባት ሰዓት ተኩል ድረስ ፀጉሯን ለመሠራት ቀጠሮ ይዘውላት እንደነበረ ትዝ እንደሚላቸው አስረዱ ። ከውበት ሳሎኑ ከተጠናቀቀች በኋላ አዘውትራ ታደርገው እንደነበረ ሁሉ ምላዋን ለመብላት ሳትሄድ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዳልቀረች እንደሚገምቱ ገለው ።

"መልካም ፡ ምሳዋን ለመብላት ግማሽ ሰዓት ፈጅባት እንበል ፡ ከዚያስ በኋላ? አውን ሚስተር ፈቭል እንደነገረን ማስታወሻውን የተወች ለት በዘጠኝ ሰዓት እንደነበረና ከዚያም በቀጥታ መደዚህ ነው የመጣችው የሚለውን አባባሉን ብንተበል ከስምንት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ምን ስትሰራ ቆየች?" አሉ ኮሎኔል ጀልያን ።

"መድሃኔዓለም! ያሻትን ብትሠራ ማን የሚያገባው አለና ነው ይህን ጥያቄ የሚሰነዝሩት? ቁም ነገሩን መሳት የለብንም ። እራሷን እንዳልገደለች የሁላችንም ልባና የሚያውቀው ነውና ነገር ማንዛዛቱ ምን ፋይዳ አለው?" ሲል ፈቭል ፈጭ ።

"እስቲ ምናልባት ይጠቅም እንደሆነ" አሉ ሚስዝ ዳንቨርስ "ማስታወሻ ደብተሯ እኔ ዘንድ ስለሚገኝ በእለቱ የነበራትን ቀጠሮዎች ሳታሰፍር አትቀርምና ይምጣ የሚሉ ከሆነ ላመጣው እችላለሁ"

ኮሎኔል ጀልያን ማስታወሻ ደብተሩ እንዲመጣ ማክሲም ፍቃደኛ እንደሆነ ጠየቁት ። ምንም ተቃውሞ እንደሌለው በመግለፁ ሚስዝ ዳንቨርስ ደብተሩን እንዲያመጡ ታዘዙ ።

ሚስዝ ዳንቨርስ ማስታወሻ ደብተሩን አምጥተው ገጾቹን ገላልጠው ለኮሎኔል ጀልያን እያሳዩ "ልክ እንደገመትኩት የዚያን እለት የነበራትን ቀጠሮዎች በሙሉ አስፍራቸዋለች ።" በማለት ቀና አሉ—ወደ ሌሎቻችን ። "እኔ ጠባይዋን መች አጣሁት? እያንዳንዱ ጥቃቅን ነጥብ የማያመልጣት ጥንቁቅ እመቤት ነበረች" አሉ በቁጭት እየገረመሙን ።

ኮሎኔሉ መነፅራቸውን አድርገው ማስታወሻውን ሲመረምሩ ሁላችንም በፀጥታ አኳበተውላቸው ነበር ። ሆዬን ባር ባር አለው ። የገዛ እጅቼን በጥፍር አላስተረፍኳቸውም ። ደረቴን ገምሶ ለመውጣት ይራገጥ የነበረው ልቤ ትርታው ግድግዳውን ጥሶ የሚሰማ ይመስል ነበር ።

"ይኸውና" አሉ ኮሎኔል ጀልያን "ሚስዝ ዳንቨርስ ልክ ናቸው ። ፀጉሯን በስድስት ሰዓት መሰራቷን ፡ ከዚያም ምሳዋን መብላቷን አስፍራለች ። ይሄ ደግሞ ምንድነው የሚለው? አ—አምን ... ቤከር በስምንት ሰዓት ... ቤከር ደግሞ ማነው?" ብለው ማክሲምን ቀና ብለው ቢያዩት 'እንጃ' እንደማለት በጭንቅላት ንቅናቄ መለሰላቸው ። ዓይናቸ

t.me/OLDBOOKSPDF

ውን ወደ ሚስዝ ዳንቨርስ ሲያዞሩት ደግሞ "ቤከር?" አሉ አሮጊቷ በጥርጣሬ መልክ "ቤከር አሉኝ? እርሷ ቤከር የሚባል ሰው አታውቅም ። ኧረ እኔም ይህን ስም ሰምቼውም አላውቅ"

ኮሎኔሉ ማስታወሻ ደብተሩ ላይ የተፃፈውን ለሚስዝ ዳንቨርስ አሳዩአቸው ። ማየት ማመን ነው እንዲሉ አሮጊቷ ቤከር የሚለውን ቃልና ርብቃ ከሰውዬው ጋር መገናኘቷን የሚጠቁም ከቃሉ በስተቀኝ የሰፈረ ውን ምልክት ካዩ በኋላ የትውስታ ሕዋሳቶቻቸውን ለመቀስቀስ እየደጋ ገሙ "ቤከር ፡ ቤከር" ቢሉም ምንም ትዝ ሊላቸው አልቻለም ።

"ይህን ቤከር የሚባለውን ሰው ማንነት ማወቅ ትልቅ ፍንጭ ሊሰጠን እንደሚችል እርግጠኛ ነኝ" አሉ ኮሎኔል ጁልያን ። "ለመሆኑ ሚስዝ ደዊንተር የሰው እዳ ነበረባት?"

"የሰው እዳ? አሆሆ" አሉ ሚስዝ ዳንቨርስ ከኮሎኔሉ አፍ ቀልበው "ምን አይሰማ ጆሮ ?! እርሷ ገንዘብ ችግሯት ብድር ልትገባ?"

"ማለቴ" አሉ ኮሎኔል በለዘብታ ለማስረዳት እየሞከሩ " ... እ—ማለቴ ምናልባት አንዳንድ አሞበርባሪዎች ይህን ያህል ካልከፈልሽን ብለው አስፈራርተዋት እንደሆነ?"

"ኧረ ጌታዬ ወሬ ይቀይሩ" ካሉ በኋላ አሮጊቷ "ቤከር" በማለት አእምሯቸውን በመኮርኮሩ ገፉ ።

"ምንም ዓይነት ባላንጣ አልነበራትም ማለት ነው? ይዝትባት የነበረ ፡ ትፈራው የነበረ ሰው በሞራሽ አልነበረም?"

"ሚስዝ ደዊንተር ናት ደግሞ የምትፈራ? እርሷ በዚህ ምድር ላይ ማንንም ፈርታ አታውቅም ። እድሜ ልኳን ያስጨንቃት የነበረ ነገር ቢኖር ጃጅቶ ፡ በአጉል በሽታ ተለክፎ ፡ የአልጋ ቁራኛ ሆኖ መሞት ብቻ ነበር ። 'መሞቴ ካልቀረ አንድ አፍታ ሞልጥ አድርጉ ቢወስደኝ ፡ እንደ ኩራዝ አልም ድርግም ቢያደርገኝ ነው ምኞቴ' ትለኝ ነበር ዘወትር ። የሚያፅናናኝም ይኸው ነው ። መስጠም ሳያስቃይ ነው የሚገድለው ይባል የለ?"

"ይህ ሁሉ—ፍሬ ከርስኪ ምን ጥቅም አለው?" አለ ፈቭል ወደፊት እየተንደረደረ "በሆነ ባልሆነው ጊዜውን እየገደልን ከዋናው ነጥብ እየሸሸን ነው ። አሁን ይህ ቤከር የሚባለው ሰው ታወቀ አልታወቀ ምን ልዩነት ሊያመጣ ነው? ይሄኔ ይሄ ቤከራችሁ ጥቅም ያላወረው የእስቶኪ

t.me/OLDBOOKSPDF

ንግ ወይም የቅባት ነጋዴ ይሆናል”

ሚስዝ ዳንቨርስ ማስታወሻ ደብተሩን ከኮሎኔሉ ተቀብለው ጥቂት ሲያገላብጡት ከቆዩ በኋላ “እረ እዚህጋ የቱሉፎን ቁጥሮች በሰፈሩበት ቦታ ቢከር ከሚለው ስም አቅጣጫ ቁጥር 0488 ተፅፏል ። የአካባቢው ኮድ ግን የለም” አሉ ማስታወሻውን ለኮሎኔሉ እያሳዩ ።

በመጨረሻም በተለያዩ የአካባቢ ኮዶች ተደውሎ እንዲሞከር በተደረሰው ስምምነት መሠረት ፍራንክ እንዲደውል ተደረገ ። ፍራንክ እያንዳንዱ ሙከራ ባከሸፈ ቁጥር ወደ እኛ መጥቶ ያስረዳንና ምን እንደገጠመው ይነግረናል ። ፌቭል እንደ ጅል እያስካካ “አቢት የኛ መርማሪ ! ... እንግዲህ የማንንም ዳቦ ጋጋሪ ፡ ቅመም ነጋዴ ፡ አረቂ ቸርቻሪ ስልክ ስትቀጠቅጥ እዚህቹ አሳድረን” እያለ ይለፋደዳል ።

እኔ ደግሞ “ምነው ይህ ቢከር ባልተገኘ ? ምነው ሞቶ ተቀብሯል ተብለን በተገላገልን ?” እያልኩኝ በልቤ እዐልይ ነበር ።

ከብዙ ሙከራዎች በኋላ ፍራንክ አንድ ብጣሽ ወረቀት ይዞ መጣ። እጪዬ ዱብ አለ ። “...ሰውዬው ተገኝቷል መሰለኝ ። የግል ክሊኒክ ያለው ዶክተር ነው ። ስራውን ከለቀቀ ከስድስት አመት በላይ ቢሆንም አሁን የሚገኝበትን አድራሻ ተቀብያለሁ ...” ሲል ሰማይ ምድሩ ዞረብኝ ።

ይህን ጊዜ ነበር ማክሲም ለመጀመሪያ ጊዜ ቀና ብሎ ያየኝ ። አይኖቹ ልዩ መልእክት ይነበብባቸዋል — የስንብት አይነት ። እርሱ ለጉዞ በተዘጋጀ መርከብ ላይ ተሳፍሮ እኔ ከበገነቱ ላይ ሆኜ የምንሳጠጥ መስሎ ታየኝ ። መለያየቱ በእጅጉ እንዳስተከዘን የተገነዘበው ከእርሱ ጋር የሚጓዙ መንገደኞች ትከሻውን መታ መታ እያደረጉ ሊያበረታቱት ቢጥሩም ፡ ከኔ ጋር የቆሙ ሽኝዎችም ከንፈራቸውን እየመጠጡ ሊያዕናኑኝ ቢሞክሩም ማናችንም አልተቀበልናቸውም ። ከጎናችን መቆማቸውን እስከንዘነጋ እይን ለአይን እየተያየን መፍዘዝ ፡ መተከዝ ብቻ ። በመካከላችን የነበረው ርቀትና የንፋሱ ፉጨት ከመደማመጥ እንደሚያግዱን ተረድተን ፡ አንናገር ፡ አንጋገር ።

በእኒህ ቅፅበታዊ ሁለት ሴኮንዶች ውስጥ ዙሪያችን የነበሩትን ሁሉ ረሳናቸው ። ይህችን ጊዜ ከሌሎች ጋር ላለመጋራት ሰሰትናት ። የግላችን

t.me/OLDBOOKSPDF

አደረግናት ። የውስጥ ስሜታችንን ተናበብንባት ። በሀሣብ ባህር ሰጠምንባት ። ለብቻችን ተከዝንባት ...ለብቻችን...ለብቻችን...

ርብቃ ዶክተሩን ለምን አነጋገረችው ? የሚለው ጥያቄ ጥቂት አወያየ ። ተጨባጭ ምክንያት ቀርቶ ፍንጭ የሚሰጥ ግምት ሊቀርብ አልቻለም ።

"ምነው እናንተ ሰዎች በዚህ በማይረባ ደደብ ዶክተር ላይ ይህን ያህል ሙጭጭ አላችሁ ?" አለ ፈቭል "የመንደር ቅባት ነጋዴ ፡ የወጉር ቀለም በጥባጭ ፡ የሀሰት ዶክተር ነው ስላችሁ?"

"ተሳስተሃል የኔ ወንድም ።" አለ ፍራንክ ድምፁን ረገጥ አደርጎ "ሰውዬው እንተ እንደምትለው የመንደር አጭበርባሪ አይደለም ። እውቅ የማህፀን ሀኪም እንደሆነ ቅድም ቴሌፎኑን የተቀበለኝ ሰው ነግሮኛል ።"

"አሃ !" አሉ ኮሎኔል ጁልያን ሪዛቸውን እያፍተለተሉ ። "ሚስዝ ደዊንተር ከበድ ያለ የጤና ችግር ነበረባት ማለት ነው ?"

ይህ የኮሎኔል ሀሣብ ከፈቭልም ሆነ ከሚስዝ ዳንቨርስ ውል ያለው ምላሽ ሊሰጥሰው አልቻለም ። ሁኔታውን ለማጣራት ለዶክተሩ በአድራሻው ደብዳቤ መፃፍ እንደሚበጅ ፍራንክ የሰነዘረው ሀሣብ ደግሞ የኮሎኔል ጁልያን ተቃውሞ ገጠመው "... በህክምና ስነ ምግባር የማንኛውም በሽተኛን ጉዳይ ለሌላው አሳልፎ መስጠት በጥብቅ የተወገዘ ነው ። ምናልባት ሚስተር ደዊንተር ዶክተሩን በግንባር አግኝተውት ጉዳዩን በዝርዝር ቢያስረዱት አንድ ጠቃሚ ፍንጭ ሊገኝ ይችል ይሆናል። ምን ይመስልዎታል ፡ ሚስተር ደዊንተር ?" አሉ ኮሎኔል ።

"እኔ ምን ችገረኝ ። ያላችሁትን ሁሉ ለመፈፀም ዝግጁ ነኝ" አለ ማክስ

"እንግዲያውስ ብቻውን መሄድ የለበትም" አለ ፈቭል ሳቅ ሳቅ እያለው "የመታወም መብት የለኝም እንዴ ? ከምርመራ መኮንኑ ከዊልች ጋር የሚሄድ ከሆነ እስማማለሁ ።"

"ነና ከአሁኑ የምርመራ መኮንኑን በዚህ ጉዳይ ላይ ማሳተፉ አስፈላጊ አይመስለኝም" አሉ ኮሎኔል ጁልያን ጠንከር ብለው "እኔ ይገርአቸው ሄጄ ጉዳዩ እስካለቀ አብሬአቸው ቆይቼ ፡ ይገርአቸው ብመለስስ ? በዚህ ትስማማለህ ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

ፈቭል አንዴ ማክሲምን እንደገና ኮሎኔል ጁልያንን ገረፍ አደረጋ ቸው ። አስተያየቱ በጣም ከማስጠላቱም በላይ አንዳች ተንኮል የሚያጠነ ጥን ይመስል ነበር ። "እምን" አለ በድል አድራጊነት ስሜት እየተኩራራ "ግን ለክፉም ለደጉ እኔም አብራአችሁ ብሄድስ ?"

"አይሆንም" አሉ ኮሎኔል ጁልያን "በመሠረቱ የመጠየቅ መብት እንኳን አለህ ። እንዲህ መጠጥ ተጫጭኖህ ግን አብረኸን ልትሄድ አትችልም።"

"እረ ግድ የለምትም ፡ በጣም ጨዋ እሆናለሁ" አለ ፈቭል

ከዚያም ጉዞው በሦስት ሰዓት እንዲጀመር ሰ.ስማሙ "ግን እንዴት ነው የምናደርገው ? ጌታ ማክሲም ሌሊት ተነስቶ ቢጠፋስ ?" አለ ፈቭል ማክሲምን በጥርጣሬ እየገረመመው ።

"በቃሉ የምትተማመኑ ከሆነ አንድ ነገር ማድረግ እንችላለን" አለ ማክሲም ወደ ሚስዝ ዳንቨርስ ዞር ብሎ "እኔና ባለቤቱ ከተኛን በኋላ የመኝታ ቤታችንን በር ከውጭ ቆልፊና ጠዋት አንቺው እራስሽ በአንድ ሰአት ትከፍቺልናለሽ ።"

"እሺ ጌታዬ" አሉ አሮጊቲ

ውይይቱ በዚሁ ተቋጨና እንግዶቹ ለመውጣት ተነሱ ። ኮሎኔል ጁልያን እጁን እየጨበጡ "በይ እንግዲህ ደህና እደሪ ። ስላንቺ ምን ያህል እንደተሰማኝ ሳትረጂ የምትቀሪ አይመስለኝም ። የምትችዪ ከሆነ ባለቤትሽን በጊዜ ብታስተኚው መልካም ነው" ብለው ተሰናብተውን ወጡ።

ከልፍልፉ ፈቭል ደግሞ ከኪሱ ፓኬት አውጥቶ ጠረጴዛ ላይ ከነበረው ሲጋራ እያነሳ ሞላው ። አንዱን ሲጋራ እያቀጣጠለ "መቺም እኔን እራት ትጋብዙኛላችሁ ብዬ ስለማልገምት አፌን ሳላጠፋ ሹልክ ብል ነው የሚሻለው" አለ ፈገግ ብሎ ።

መልስ የሚሰጠው ቢያጣ እየተንጎራደደ መለፍለፉን ቀጠለ "እንግዲያው እንደፈረደብኝ አልቤርጎ ፍለጋ በጊዜ ልሂዳ ! ያች ሸውራራ አልጋ አንጣፊ ደግሞ አሳሬን ልታበላኝ ነው ። ሌሊቱ እንዴት እንደሚነጋልኝ እንጃ ! ሆኖም ግን ያን ያህልም አያሳስበኝም ። በነገው ሁኔታ አንጀቱ እንደሚርስ ስለማውቀው የመጣ ችግር ቢመጣ ደረቱን ነፍቼ ነው

t.me/OLDBOOKSPDF

የምቋቋመው ። ዳኒ ፡ ደህና ይደሩ ። በሩን መቆለፉን እንዳይረሱ ፡ አደራ" ካለ በኋላ ወደኔ ተጠግቶ እጁን ለሰላምታ ቢዘረጋልኝ እንደ ቂላቂል ህፃን እጅቹን ሸሸግኩት ።

"ይገባኛል ፡ ይገባኛል" አለ ፈቭል እየተንከተከተና በፈገግ መልክ እጅ እየነሳኝ ። "ሰላምታ ብትነፍጊኝም እውነት አለሽ ። ይህን የመሰለ መልካም ምሽት ሽን ላበላሸብሽ እንደኔ ላለ አብሣን ሰው እንኳን እጅሽን ሉላም ብትከለክዪው ይገባኛል ። አደሥሽ ፡ ስምሽ ከነህይወት ታሪክሽ በድንት ዜና አብሳሪነታቸው በታወቁ ጋዜጦች ላይ የሚሰፍርበትጊዜ ሩቅ አይደለም ። "ከሞንቱ ካርሎ እስከ ማንደርሌይ ።" "የነፍስ ገዳዩ ሙሽራት ገጠመኞች" የሚሉት ርእሶች በየጋዜጦቹ ላይ ደመቅ ፡ ጎላ ብለው ሲዛፉ ደስ አይሉም ?" አለና እየተጀነነ ወደ በሩ አመራ ። እጁን ለማነሲም እያውለበለበ ደግሞ "ደህና ይሁኑ ጌታው ። መልካም እንቅልፍ፡ እመኝሎታለሁ ። በቁልፍ በተከረቸመች መኝታ ክፍልም ውስጥ የመጨረሻዋን ሌሊት በደንብ ያሣልፋት" እያለ አፉን ለቀቀው። ወደኔ ሦርብሎ ከሳቀብኝ በኋላ ወጥቶ ሄደልን ።

ሁሉም ሲሄዱ እኔና ማነሲም ብቻ ቀረን ። እኔ አይን አይኑን ስፈልግ እርሱ ግን አይኖቹን በመስኮቱ ለቀቃቸው ። የልቡን የሚረዳለት ፡ ሀዘኑን የሚጋራለት ብቸኛ ጓደኛው እርሱ ብቻ ይመስል ጨለማው ላይ እንዳፈጠጠ ቀረ ። ማምሻውን ሁሉ ወደኛ ዝር እንዳይል ታግዶ የቆየው ጃስፐር ደግሞ እየሮጠ መጥቶ እግሬ ስር ይወራጭ ጀመር ። ጭራውን ግራ ቀኝ እየነሰነሰ ፡ ቀሚሴን እየጎተተ ሲቁነጠነጥ ከወትሮው በተለየ መልክ ስሜቱ የተሰማው ፡ ጭንቀቱ የጨነቀው መሰለኝ ።

ማነሲምን "ነገ ጠዋት አብሬህ ነው ወደ ሎንዶን የምሄደው" ስለው ምላሹን ሳይሰጠኝና ግንባሩን ሳያሳየኝ ጥቂት ከቆየ በኋላ "እሞን ፡ ከእንግዲህ አብረን መሆን አለብን" አለኝ ቀዝቀዝ ብሎ ።

ፍራንክ ተመልሶ መጣና እንግዶቹን እንደሸኛቸው ካስታወቀን በኋላ "ለመሆኑ አሁን ምንድነው ማድረግ ያለብኝ ? ደውዬ የማስታውቀው ሰው ካለ ወይም ማንኛውም ማድረግ የሚገባኝ ነገር ካለ ሌሊቱን በሙሉ ያለ እንቅልፍ ባድርም ቅር አይለኝም" አለ ።

"ግድ የለም ፍራንክ ፡ አሁን ምን የሚሰራ ነገር አለ ብለህ ? ምናልባት ከነገ በኋላ ነው በርክት ያለ ሥራ የሚጠብቅህ ። ለማንኛውም

t.me/OLDBOOKSPDF

ጊዜው ሲደርስ እንደርስበታለን ። ይህችን ቀሪዋን ሌሊት ግን እኔና ውዴ ባለቤቴ ብቻ አብረን ብናሳልፋት ደስ ይለናል ። ተግባባን ፍራንክ ?" አለው ማክሲም

ፍራንክም የማክሲምን ሀሣብ ተቀብሎ ተሰናብቶን ወጣ ። ማክሲም እያዘገመ ወደኔ መጣ ። እጆቼን ዘርግቼ ጠበቅኩት ። ልቤን ከፍቼ ተቀበልኩት ። እንደ ህፃን ልጅ እቅፌ ውስጥ ገብቶ ተጠቀለለ ። እርሱ የኔን ፡ እኔ የእርሱን የልብ ትርታ እያዳመጥን ፡ ሙቀቴን ሰጥቼው ሙቀቱን እየወሰድኩ ፡ ለ ለአካል መተቃቀፍ ብቻ ሳይሆን ስሜት ለስሜት እንደተቆላለፍን ፀጥ ብለን ቀረን ።

"ነገ አብረን ነው የምንሄደው" አለኝ ማክሲም በለሆሳስ
"አዎን" አልኩት በእርሱው ቃና
"ጁልያን ቅር የሚላቸው አይመስለኝም"
"በፍፁም"

"የነገውንም ሌሊት አብረን ነው የምንሆነው ። እንዲህ በአስቸኳይ አንዳንድ እርምጃዎች የሚወስዱ አይመስለኝም ። ቢያንስ የሀያ አራት ሰአት እድል አይነፍጉንም ብዬ ነው ።"

አነጋገሩ አንጀቴን በላው ። ሆዴ ቢባባም ይበልጥ እርሱን እንዳላባባው የማዬን ጠንከር አልኩና "እሪ እንዲህ የሚያጣድፍ ነገር የለም ። ደግሞስ ማን ያውቃል ? ..." አልኩት ።

"እርሱን እንኳን ተዪው ። ይልቅ ከቻልኩ የሀማ ሰዎችን ማነጋገር አለብኝ ። ከበርክት ይልቅ ሄስቲንግስ ይሻላል ። ከአባቴ ጋር ደግሞ ትውውቅ ስለነበረው እርሱ ይሻላል ።"

በዚህ መሃል በሩ ተከፈተ ። ፍሪዝ ብቅ ሲሉ ክው አልኩ ። ማክሲምን ገፍተር አድርጌ ተመቻችቼ ቆምኩ ። እራት መዘጋጀቱንና ልብስ መቀየር እንፈልግ እንደሆነ ሲጠይቁን ለዛሬ ልብስ መቀየር እንደማንሻ ነግሬያቸው ወጡ ።

እራታችንን ቀማመስን ። ቤተ መፃህፍቱ ውስጥ ቡና እየጠጣን ሳለ ቴሌፎኑ ጮኸ ። ቢያትሪስ ነበሩ የደወሉት ። ደጋግመው ደውለው መስመሩ እንደተያዘባቸው ነገሩኝ ። በዛሬው አለት ስለ ርብቃ አሟሟት ፍርድ ቤቱ ያሳለፈውን ውሣኔ በምሽት ጋዜጣ ካነበቡ በኋላ እርሳቸውና

t.me/OLDBOOKSPDF

ባለቤታቸው ከመጠን በላይ እንደተበሳጩ ገለውልኝ ። ሙሳኔው ማክሲ ምን ጨምሮ ሁላችንንም እንዳስደነገጠን ነገርኳቸው ።

"በፍጹም ሊታመን የማይችል ነገር ነው ። ርብቃ ናት እራሷን የምትገድል ? እንድ ስውር ተንኮል ቢኖርበት እንጂ እንዲህ ለሰሚው ግራ የሆነ ነገር ሊወሰን አይችልም ። ለመሆኑ ማክሲም ምን አለ ? ለምን እታገናኘኝም ?" አሉኝ ።

ማክሲም ቀኑን ሙሉ እረፍት እንዳላገኘና አሁንም ከኩኔል ጁልያንና ከሌሎች እንግዶች ጋር ሲጫወት ስላመሸ በጣም እንደደከመው፡ ነገም ሙሳኔውን በሚመለከት ወደ ሎንዶን እንደምንሄድ ነገርኳቸው ።

"እንግዲያው ይህንን ነገር በደንብ ማከሸፍ አለባችሁ ። ለማክሲም ለስሙም ቢሆን ጥሩ አይደለም ። እረ የጠቅላላ ቤተሰባችን ስም የሚያጎድፍ ነገር ነው...እንዲህ ያለ መላ የጠፋው ሙሳኔ ሲተላለፍ እንዲያው አንድ የሚታወም ሰው ይጥፋ ? ምን ያደርጋል? እኔ እለመናሬ እንጂ የመጣው ቢመጣ ሽንጤን ገትሬ ነበር የምሟገተው ... ያ ሆሪጅ የምትዪው አሮጌ ቀርበታ ደግሞ ቢጃጅ ነው እንጂ አይኑ እያየ ፡ ጆሮው እየሰማ ይህን ይመስናል ? ...እስቲ ርብቃን የመሰለች ጠንካራ ሴት ምን ሆንክኝ ብላ እራሷን ታጠፋለች ? ... መቼም ኮሎኔል ጁልያን ይህንን ነገር ካላከሸፉ ሰውም አላደርጋቸው ። የእርሳቸው አስተዳዳሪነት ለእንዲህ ያለ ጊዜ ነላገለገለ ምኑን አስተዳዳሪ ሆኑት...? እኔ እንዲያው... ማክሲም ሙሳኤውን ነላስተየረ እኔ እራሴ ዳኛውን ፅፌ እጠይቃለሁ ..."

"አሁን እንኳን ምንም ማድረግ የሚቻል አይመስለኝም ፡ መተው ነው የሚሻለው "

"ለምን ተብሎ ነው የሚተወው ? ርብቃ እራሷን እንዳልገደለች ፡ ሆን ተብሎ በሌላ ሰው የተጠነሰሰባት ተንኮል መሆኑን እያወቅን ? ይሄኔ የነኚ ሙርሙር የሚሉት የጠላቶች ሴራ ይሆናል ። ይቺ ይቺ የነርሱ ሥራ ናት ። መች እጣናት ። ባለቤቴም እንዲሁ ነው ያለው"

"እኔ እንኳን ነው እልልም ። ምናልባት ርብቃ እራሷን ለማጥፋት የሚገፋፋት እኛ የማናውቀው የራሷ የሆነ ምክንያት ይኖራት ይሆናል ። እነርሱም ቢሆን በየወደቡ እያደፈጡ የግለሰቦችን ጀልባ የሚበሱ

t.me/OLDBOOKSPDF

አይመስለኝም ። ምን ሊጠቅማቸው ?" አልኩ ።

ማክሲም ቢያትሪስን ተሰናብቼ ቴሌፎኑን እንድዘጋው ሲነግረኝ "ቢያትሪስ ፡ ለማንኛውም ነገ ከሎንዶን ደውዬ አነጋግርሻለሁ" አልኳቸው ።

"ስሚ እንጂ" አሉ ቢያትሪስ እየተቻኮሉ "ያንን ዲክ ትዶልፊኒን ባነጋግረውስ ? የናንተ የሽንኑ ተወካይ እኮ ነው ። ከማክሲም ይልቅ ከኔ ጋር ወዳጅች ነን ። እስቲ ዲክን ደውዬ ላነጋግረው ወይ ? ብለሽ ጠይቂው"

"እባክዎን ምንም አያስፈልግም ። እንዲያው በከንቱ አይድከሙ እንዳልኳቸው ቴሌፎኑ አንዳች የተለየ ድምፅ አሰማ ። ቢያትሪስ "ሀሎ ፡ ሀሎ ፡ አያቋርጡብን ... አልጨረስንም ..." ሲሉ ስማኝቸው ። ወዲያው መስመሩ ተቋረጠ ። ግልግል ።

ወደ ማክሲም ስሄድ ቴሌፎኑ እንደገና ያሯሯ ጀመር ። 'ሲሯሯ ይደር' ብዬ ዝልፍልፍ አልኩና ማክሲም አጠገብ ቁጭ አልኩ ። ጉልበቶቹን ታቅፌ ድካሜን ሳስታምም የማድግዳው ሰአት ደወለ— ከምሽቱ አራት ሰአት ።

ማክሲም ከተቀመጠበት ተነስቶ ከተቀመጥኩበት አስተዋለኝ ። እጆቹን ሰጠኝ—ተቀበልኩት ። አነሳኝ—ብድግ አልኩለት ። አቀፈኝ —ተጠመጠምኩበት ። ሳመኝ—ሳምኩት ። ከናፍሮቻችንን ሚሙ ። ተሳስመው የማያውቁ ፡ የከንፈርን ምትሀታዊ ንዝረት ለመጀመሪያ ጊዜ የተገነዘቡ አዲስ ፍቅረኞች አይነት የነበርንበትን እስክንዘነጋ በስሜት ሰጥመን ቀረን ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ ሀያ አራት

በማግስቱ ከእንቅልፏ ስንቃ ሰአቱ ከአስራ ሁለት ብዙም ፈቅ አላለም ነበር ። ወደ መስኩ ሄጂ መስኩን ስመለከት አይኔ ሳር ቅጠሉን ካለበሰው ጨዛ ላይ አረፈ ። ተዝለፍልፌ ፡ ረጋ ብሎ የሚንፍሰው ነፋስ ፊቴን ዳሰሰው ።

መስኩ፡ አጠገብ ተንበርክኬ የዕጄረዳ አፀዱን ቃኘሁት ። ሌሊቱን የጣለው ዝናብ የተጫጫናቸው አበቦች አጎንብሰው የሚያንቀላፉ ይመስላሉ ። ልዩ ልዩ አእዋፍ በሀብረ—ዝማሬያቸው ታጅበው ከቅርንጫፍ ወደ ቅርንጫፍ ያበራሉ ። ጥቂት ቆይተው እትክልተኞቹ የእለት ተግባራቸውን ለማከናወን መዲያ መዲሀ ማለታቸው አይቀርም ። እኛ እንዲህ በቁጭት ተቅና በሀሣብ ተወጥረን የማንደርሴይ የእለት ተእለት ከንዋኔዎች እንደ ጠትሮአቸው መካሄዳቸው ገረመኝ ።

የማንደርሌይ ሰላም ፡ ፀጥታና ሳርማ ሞገስ—ከጣራው ስር ማንም ቢኖር ማን ፡ ምንም አይነት ችግርና ጣጭት ቢከሰት ፡ የፈለገው ሰቃይና መከራ ቢፈጠር ፡ እልፍ ልቦች በሀዘን ፍላፃ ተወግተው ቢደሙ ፡ እልፍ አእላፍ አዳኖች ቢያነቡ የማንደርሌይ በጥታና ሰላም ከቶውንም እያደፈረ ስም ፡ ውበቱ ሳድርሱን እይደበዝዝም ።

ሰአቱ ገና በመሆኑ ማክሲምን ልቀሰቅሰው አልፈለግኩም ። ገና ረጅምና አድካሚ ጉዞ ይጠብቀናል ። ከጉዞው ማብቂያ ላይ ደግሞ ምን እንደሚገጥመን አያታወቅም ። እዚያ ስሜናዊ ሎንዶን የሚገኘው ቤከር ክንመፈጠራችንም አያውቅ ። የወደፊት እድላችን በመዳፎቹ ውስጥ እንዳለ ሳያውቅ ይሄኔ ሰላማዊ እንቅልፉን ይለጥጣል ። ይህንን እያሰላሰልኩ ገላዬን ታጥቤ እንዳበቃው ሚስዝ ዳንቨርስ ሌሊት የቆለፉብንን በር

t.me/OLDBOOKSPDF

ሲከፍቱልን ሰማሁ ።

ልብሴን ለባብሼ ማክሲምን ቀሰቀስኩት ። ብንን አለና እንደ እርብትብት ሀሣን አይኖቹን እያቁለጨለጨ ተመለከተኝ ። ወዲያው ጥርሶቹን ብልጭ አደረጋቸውና እጆቹን ዘረጋልኝ ።

ሻይ ከጠጣን በኋላ አርሱ ገላውን ሊታጠብ ሲሄድ እኔ ልብሶችና የሚያስፈልጉንን እቃዎች አዘጋጅ ጀመር ።

ማክሲም ተጣጥቦ ተመለሰ ። ቁርሳችንን በልተን እንደተነሣን የሰማነው የመኪና ድምጽ ሀሣባችንን ሳበው ። ፍራንክ ነበር የመጣው ። ኩሎኔል ጄልያን ዋናው በር ላይ እንደሚጠብቁን ከነገረን በኋ "እንግዲያው ቢሮ ቁጭ ብዬ ነው የምጠብቃችሁ ። ሰውዬውን ካገኛ ት በኋላ የደረሳችሁበትን በቴሌፎን እንድታስታውቁኝ" አለን ።

ወደ መኪናው ለመጣባት ስናዘግም አንዲ መለስ ብዬ ቤታችንን አየሁት ። ምክንያቱ ሳይገባኝ አይኖቹ በእንባ ተሞሉ ።

ኩሎኔል ጄልያን ሲያዩን ድንግጥ አሉና "ምነው አንቺ ደግሞ መምጣትሽ ? በጣም አድካሚና አሰልቺ ጉዞ እኮ ነው ። ባለቤትሽ ለመንከባከብ እኔ አንስኩ ብለሽ ነው ?" አሉኝ ፈገግ እያሉ ።

"አይ ፡ ለዚያ እንኳን ብዬ አይደለም ። እንዲያው መምጣት ስለፈለግኩ ነው እንጂ" አልኳቸው ።

"ይሁን ፡ ይሁን እስቲ ፡" አሉና ወደ ማክሲም ዞር ብለው "ያ ፈቭል ደግሞ ማቂረጫው ላይ እንገናኝ ብሏል ። እዚያ የሉስ እንደሆነ እንጠብቀው እንዳይሉ ። እንዲያው ባይኖር ነው ለኛ የሚበጀን ። ሂዶስ ምን ሊፈይድን ብለው ? ሊበጠብጠን ነው እንጂ ። ምነው እንቅልፍ ሞልጎ አድሮን መስያት በረፈደበት ?" አሉ ።

ከማቂረጫው ስንደርስ ግን ምኞታችን እንዳልያዘልን ያወቅኩት አረንጓዴውን የፈቭል መኪና በቁጥቋጦው ውስጥ ባየሁ ጊዜ ነበር ። ፈቭል ሲጋራውን እያቦነነ መኪናው ውስጥ ተቀምጧል ። ሲያየን ፈገግ አለና እጁን አውለበለበ ልን ። ጉዟችንን ቀጠልን ። አንድ እጄን ማክሲም ጉልበት ላይ አሳርፌ ተመቻችቼ ተቀመጥኩ ። ጊዜው በጎንደ መጠን ኪሎ ሜትር በኪሎ ሜትር እየተደራረበ መንገዳችንም ገፋ ። ኩሎኔል ጄልያንን አልፎ አልፎ ዞር ብዬ ሳያቸው ያዛጋሉ ። ድካም የተጫጫነው

t.me/OLDBOOKSPDF

እንምሯቸው እራሳቸውን መቆጣጠር እየተሳነው ሞንቅላታቸው ይደ
ፋል። አፋቸው ይከፈታል። እንቅልፋቸው ይቀልጣል ። እንደገና
እንደመንቃት ብለው እንደገና ያዛጋሉ ። እንደገናም ያንጎላጀሉ ። ፌቭል
እንዴ ሲከተለን ፡ እንዴ ቀድሞን ሲበር ቆይቶ ለምላ ከአንድ ሆቴል
ስንገባ ግን አብሮን ሳይገባ ቀረ ።

በልተን ስንወጣ ባዶ መኪናውን ከመንገድ ባሻገር ከነበረ አንድ
ቡና ቤት በር ላይ ቆሞ አየሁት ። እንደገና መንገድ በገባን በሦስት ደቂቃ
ውስጥ ሞራችንን ይዞ ይከተለን ጀመር ። ስንወጣ ከአንድ መስኮት ጥግ
እይብቶ ሳያስተውለን እንዳልቀረ ገመትኩ ።

ወደ ሎንዶን ስንቃረብ የሰዉ ግርግር ይብስበት ጀመር ። የመኪናው
ጋጋታ መጨመር ያዘ ። የሱቆቹ ደጆች በሰው ተጨናንቀዋል ። ሀማናት
ልጆቻቸውን በጋሪ የሚገፉ እናቶች በየመስኮቱ የተደረደሩ እቃዎችን
ይቃኛሉ — ጥቂቱ ዕቃ ለማግኘት ፡ አብዛኛው ጊዜ ለማሳለፍ ። ሱቅ
ዘያረቱዎች ያንጫጫሉ ። ገበያተኛው ይተረማመሳል ። ትናንሽ ልጆች
በካሚዮኖች ላይ እየተንጠላጠሉ በየራሳቸው አለም ይዋኛሉ ። ለንጋዴ
ውና ለሸማቹ የዋጋ ውጣ ውረድ ድርድር ደንታ የሌለው ሴላ ሴላው
ደግሞ በየግል ሀሣቡ ተጠምዶ ይንከላወሣል ።

መሀል ከተማውን ስንጥቀን ፡ ሀምፕስቲድን ተሻግረን ፡ ከሎንዶን
ሌላኛው ዳር ስንደርስ ትርምሱና ግርግሩ እየቀነሰ ፡ ፀጥታውና ሰላሙ
እየቀረበ መጣ ። እኒህ ኮሎኔል ደግሞ አስራ ሲያዛጉና ቁና ቁና ሲተነፍሱ
እርር ድብን አደረጉኝ ። የግዴን ከትእግስቱ ጋር እየሞገትኩ ቻልኩት
እንጂ በጥራ ላፎላቸው ፡ አፋቸውን ጥርቅም አድርጌ ልይዘው ምንም
አልቀረኝም ነበር ። ሀምፕስቲድን እንዳለፍን ግን ከኪሳቸው ካርታ
አውጥተው ማነሲምን የባርኔትን አትጣጫ ይመሩት ጀመር ። የመንገዱ
ቁናንትና የየመንገዱ ዳር ምልክቶች አቅጣጫችንን ላለመሳት እንደሚረ
ዱን ግልፅ ቢሆንም ቅሉ ኮሎኔል በየኩርባውና በየመጠምዘዣው ድምፃ
ቸውን ከማሰማት አልታቀቡም ።

ወደ አካባቢው መቃረባችንን እንደተረዳን መኪናችንን እያቆምን ፡
መንገደኛውን እያስቆምን "አባክዎን የዶክተር ቤከር ቤት ወዴት ይሆን ?
ቤቱ ሮዝላንድስ በመባል ነው የሚታወቀው" እያሉ ይጠይቃሉ ኮሎኔል
ጁልያን ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ዶክተር ቤከር ? ዶክተር ቤከር የሚባል ሰው አላውቅም ። ቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ ሮዝ ኮቴጅ ይባል የነበረ ቤት መኖሩን አውቃለሁ ። ግን ሚስዝ ማን ናቸው ? አምን ሚስዝ ዊልሰን የሚባሉ ሴትዮ ናቸው የሚኖሩበት ።" አለ አንዱ መንገደኛ ።

ሀሳን ልጅ በጋሪ የምትገፋ አንዲት ነርስ ስትመልስ ደግሞ "ይቅርታ የኔ ጌታ ፡ ለሰፈሩ እንግዳ ነኝና የሚሉትን ቤት አላውቀውም ... ዶክተር ቤከር ነው ያሉኝ ? ... እኔ የማውቀው ዶክተር ዴቪድሰንን ነው" አለችን ።

አንድ ፖስተኛ ነበር በመጨረሻ ወደ ትክክለኛው ቤት የመራን ። ከቤቱ ደጃፍ ሁለቱ የተመላለስን ቢሆንም በሩ ላይ ስም አለመኖሩ ነበር ያሳሳተን ።

ማክሲም በጣም የተዳከመ ከመምሰሉም በላይ ፊቱ ጥቁርቁር ብሏል። መንገዳችን ላይ ብዙም ሳይናገር ነው የመጣው ።

"...ጥሩ ሰዓት ነው የደረስነው ፡ አስራ አንድ ሰዓት ከአስራ ሁለት ደቂቃ ። የመክሰስ ሻያቸውን ሳይጨርሱ ከምንገባ ጥቂት ብንቆይ ይሻል መሰለኝ " አሉ ኮሎኔል ጄልያን ።

ማክሲም ምላሹን ሳይሰጣቸው ሲጋራውን አውጥቶ ካቀጣጠለ በኋላ እጁን ዘርግቶ እጄን ያዝ አደረገኝ ። መኪናችን ውስጥ እንደተቀመጥን ጥቂት ከቆየን በኋላ ለመጣበት ተስማምተን ወጣን ። ፌቭልም ከመኪናው ወርዶ ወደ እኛ ተጠጋና "ምነው ጃል ? የምን ማመንታት ነው? ፈራችሁ እንዴ ? እንግባ እንጂ" አለን ።

ማናችንም መልስ ሳንሰጠው ወደ በሩ አመራን ። "እረ ? ማን ነው ሰላሳ እኩል ያለው ? አርባ ለአስራ አምስት ነን ። ሌላ ሂደህ የምታመጪበረብረውን ፈልግ ፡ እኔን አያድለም ።" የሚለው የልጅ ድምፅ የሳበው ጆሮዬ አይኔን በአጥሩ ቢልከው ግቢው ውስጥ የቱኒስ ሚዳ መኖሩን አረጋገጠለት ።

ደወሉን ሰምታ አንዲት ለግላጋ ወጣት ሰራተኛ በሩን ከፈተችልን ። ብዛታችን እንዳስደነገጣት ውኃታዋ ነገረባት ። የዶክተር ቤከር መኖሪያ መሆኑን ካረጋገጠችልን በኋላ እንድንገባ ፈቀድችልን ። ከእንግዳ መቀበያው ክፍል ገብተን የዶክተሩን መምጣት ስንጠባበቅ አምስት ደቂቃ አለፈ ። ሁላችንም በየግል ሀሳባችን የሰጠምን እንመስላለን ። ግና ዳሩ

t.me/OLDBOOKSPDF

አረፍት አሳጥቶ ሲያቅበጠበጠን የከረመው ፡ እንቅልፍ ነስቶ ሲያሸብረን የቆየው ፡ እዚህ ድረስ አንጉቶ ያመጣን አብዩ ጉዳይ በየአእምሯችን አልፍኝ በስፋት መንሰራፋቱ ለሁላችንም ግልፅ ነበር ። አይኖቻችን እንዲሁ በደመ ነፍስ በከፍሉ ቁሳቁሶችና ሣጅጣዴው ላይ በተንጠለጠሉት ስእሎች ላይ ያንከባለሉ እንጂ ያዩትን ለማንባቢ ለማብቃት በሚችሉበት ሁኔታ ላይ አልነበሩም ። በተለይ እኔ ለእንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ምዕዋት ለመጠየቅ የመጣሁ መስሎ ነው የተሰማኝ ።

አምስቱ የሚንቀሳቀሱ ደቂቃዎች አለፉ ። በሩ ተከፈተ ። መካከለኛ ቁመት ያላቸው ፡ ፊታቸው ረዘም ያለ ፡ ብጫማ ፀጉራቸው ላይ ሽበት የተርከፋከፈበት ፡ ነጣ ያለ ሸሚዝና ሱሪ የለበሱ ፡ ስፖርታዊ አቋማቸው እድሜያቸውን የሸሸጎላቸው አንድ ጠና ያሉ ሰው ብቅ አሉ ።

"ያቅርታ ፡ ብዙ አስጠበቅኳችሁ መሰለኝ" አሉና ተራ በተራ ቃኙን ። ዓይኖቻን እንደሰራተኛቹ ሁሉ እሳቸውንም ሳያስደነግጣቸው አልቀረ ። "መጥሪያው ሲፈርህ ቲኒስ እየተጫወትኩ ስለነበር እስክጣ ጠብ ነው ያሉየኝ ። ምነው ታዲያ እትቀመጡም እንዴ ?" በማለት መንበር ጋበዙን ።

"ያቅርታ ያክተር ቤከር ፡ ድንገት ቤትዎን ወረን እንዲህ ስለረበሽን ያቅርታ እንዲያደርጉልን በታላቅ ትህትና እጠይቃለሁ ። እኔ ጄልያን እባላለሁ ። ሚስተር ደዊንተር ፡ ሚስዝ ደዊንተርና ሚስተር ፈቭል" በማለት ነሰተዋወቁን በኋላ "በቅርቡ የሚስተር ደዊንተርን ስም በጋዜጦች ላይ ሳያነቡ የቀሩ አይመስለኝም" አሉ ኮሎኔል ።

"አሃ ! አዎን ሳላነብ አልቀረሁም ። ስለ ምርመራ ወይም ተመሳሳይ ነገር ያነበብኩ መሰለኝ ። በደብልዋ ግን ባለቤቱ ነበረች ዝርዝሩን የተከታተለችው" አሉ ያክተር ቤከር ።

"ዳሮቻማ ሚስዝ ደዊንተር እራሷን ነው የገደለችው ሲሉ ውሣኔ አስተላልፈዋል ።" አለ ፈቭል ጣልቃ ገብቶ እየተንቀጠቀጠ ። "እዩ ፡ ሟቿ የአንቱ ልጅ ስለነበረች እብጠርጥሬ አውቃለሁ ። እራሷን የምትገድል ሰው አልነበረችም ። ይህን እርምጃ ለመውሰድ የሚገፋፋትም አንዳች ምክንያት አልነበረም ። ስለዚህ ነው የዳሮችን ውሣኔ አጥብቄ የምቃወመው ። የአውኑ አመጣጣችንም የሞቱች እለት እርስዎ ዘንድ ለምኔ መጥቶ እንደነበረ ለማወቅ ነው ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ይሠንን እንኳን ለጁልያንና ለኔ ብትተውልን መልካም መሰለኝ" አለ ማክሲም ረጋ ብሎ "ሠላብህ ወዲት እንደሚያመራ ዮክተር ቤክር የነገቸው አያመስለኝም ።" አለና ፊቱን ወደ ዮክተሩ መለሰው ። ግንባሩን ሸበሸበው ። የትህትና ፈገግታ ያንፀባረቅባቸው የነበሩ ክናፍሩን ስብስብ አድርጎ ንግግሩን ተጠለ ። "የሚች ባለቤቱ የአንት ልጅ በዳኞቹ ሙግኔ ስላልተስማማና በባለቤቱ ማስታወሻ ላይ ደግሞ ክመሞቷ ቀደም ሲል ክእርስዎ ጋር በስምንት ሰአት ተጠሮ እንደነበራት ሰፍሮ በማግኘቱ ነው ሁኔታውን ለማጣራት የመጣነው ። ስምዎና የቀድሞ የድርጅትዎ ቲሴርን ቲዮር ማስታወሻዋ ላይ ነበር"

ዮክተር ቤክር ሲያዳምጡ ቆይተው ሞንቅላታቸውን እየነቀነቁ "ያችረታ አድርጉልኝና የተሳሳታችሁ መሰለኝ ። ሚስዝ ደዊንተር የምትባል ሴት ፡ እንኳንስ በስራ ዘመኔ በህይወቴም አጋጥማኝ አታውቅም ። ቢሆን ኖሮ በፍጹም የምረሳው ስም አልነበረም" አሉ

ኮሎኤል ጁልያን ከርብታ ማስታወሻ ደብተር ላይ ቀደው ያወጡትን መረጃት ለዮክተሩ እያሳዩ "ያሽውልዎት እነ ዮክተር ፡ ስምዎ ፡ የድርጅትዎ ቲሴርን ቲዮር ፡ የቀጠሮው ቀንና ሰአት ቲልሞ ብለው ተፅፈል እነ ።" አሉ ዮክተሩን አይን አይናቸውን እያዩአቸው ።

ዮክተሩ መረጃቱን ችኩር ብለው እያዩ "በጣም ግራ የሚያጋባ ነገር ነው ። በእርግጥ እርስዎ እንዳሉት የሰፈረው ቲዮር ትክክለኛ ነው" ሲሉ የማረጋገጫ ኮሳቸውን ሰጡ ።

"ምናልባት በሌላ ሰው ስም ተመዝግቦ እንደሆነ ?" ሲሉ ኮሎኤል ጁልያን ፡

"ሊሆን ያችላል ። እኔ እንኳን እንዲህ አይነቱን ነገር ፈፅሞ ደግሜ አላጠቅም ። ነጠሙያችን እንዳር እንዳችም ጠቀሚታ የለውማ" አሉ ዮክተሩ ።

"የታካሚዎችዎ መመዝገቢያ ደኖርዎት እንደሆነ ቢያጣሩልንስ ፤ በእርግጥ ነጠሙያዎ ሥነ ምግባር አኳያ ደህን ጥያቄ መስንዘር እንደማይገባ ይሰማኛል ። ግና የወኢታው ሙስብስብነት ነው ያስገደደን ። ሚጅ እርስዎ ዘንድ የመጣችበት ምክንያት አራቷን ለማጥፋት ምን እንዳንሳሳት ፍንጭ ይሰጥ እንደሆን ብለን ነውና እባክዎን ቢተባበሩን ?" አሉ ኮሎኤል ለስለስ ብለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምን እራሷን ለማጥፋት ይላሉ ? የተገደለችበት ምክንያት ይበሉ እንጂ" አለ ፈቭል ብስጭት ብሎ ።

ዶክተር ቤከር ቅንድባቸውን ሸብሸበው ማክሲምን እየተመለከቱ "ይህም አለ እንዴ ?" አሉና ለጠቅ አድርገው "ለማንኛውም የተቻለኝን ልረዳችሁ ዝግጁ ነኝ ። የእያንዳንዱን በሽተኛ ስምና የበሽታውን ዝርዝር በጥንቃቄ ስለምመዘግብ ከፋይሉ ላይ ላጣራላችሁ እችላለሁ ። እስከዚያው ሲጋራ ተጋብዙ ። የመኝን ጠጅ እንዳልጋብዛችሁ ጊዜው ገና መሰለኝ።" አሉን ።

ኮሎኔል ጀልያንና ማክሲም 'ግድ የለም'ን በሚንቅላታቸው ሲነ ልቡ ፈቭል ግን ለመናገር አፉን ሲያሞጠሙጥ ዶክተሩ እድሉን ላያሰጡት ወጥተው ሄዱ ።

"ምነው ሙስዚና ሶዳ ቢጋብዘን ? ተብትባ ። ይሄኔ ሳጥኑ ውስጥ እሽጎት ያሠኛል ። እኔ ገና ሳየው ነው ውታቢዬ ያልመጀመው ። ምንም የሚረዳን አይመስለኝም" አለ ፈቭል እየተቁነጠነጠ ።

ጥቂት ቆይተው ዶክተር ቤከር እንድ ትልቅ መዝገብና በርካታ ማህደሮች ይዘው ተመለሱ ። "እነዚህ እንግዲህ ያለፈው አመት ሰነዶቻችን ናቸው " ካሉ በኋላ ትልቁን መዝገብ እያገላበጡ "ሰባት ... ስምንት ... አስር" ብለው ለራሳቸው እጉረመረሙ "ቁጭ እስራ ሁለት ነበር ያላችሁኝ ? በስምንት ሰአት ?"

ማናችንም መልስ ሳንሰጥ እይን አይናቸውን ብቻ እናይ ነበር ። "እሥን ፡ እገኘሁት ።" አሉና ቀና ብለው ሁላችንንም ጎረሩ ጎረፍ አድርገውን እንደገና ወደ መዝገባቸው አጎንብሰው "በተባለው ቀንና ሰዓት የመረመርኩት ሚስዝ ዳንቨርስ የሚባሉ ሴትዮን ነው" አሉን ።

ፈቭል "ዳኒን ? ምን ልት..." ብሎ ሲጮሀ ማክሲም አቋረጠውና "ያንዘውልህ፡ ስሚን ቀይራ ነበር ማለት ነው ። አሁንስ ትዝ አለህ ፡ ዶክተር ?" አለ ።

ዶክተር ቤከር መዝገቡን ወደ ጎን አስቀምጠው "ይቅዩ አስቲ ... ይቅዩ" እያሉ ማህደሮቹን ይመረምሩ ገቡ ። 'ሚስዝ ዳንቨርስ' የሚለውን አውጥተው አያቸቸውን በፍጥነት አንሸራተቱበት ። "እሥን ፡ እሥን፡ አሁን ያስታወስኳት ይመስለኛል" አሉ ዶክተሩ በዘገዛ እንደተመሰጡ ።

"ረጅም ፡ ቀጭን ፡ በጣም ቆንጆ" አሉ ኮሎኔል ጀልያን

t.me/OLDBOOKSPDF

ዶክተሩ ለማስታወሳቸው በድንጋጤ አምንታኒ ቃላቸውን ሰጥተው የያዙትን ማሀደር በጥንቃቄ አንበበት። "በመሠረቱ የሙያ ማዴታዬ እንኳን አያፈቅድልኝም ነበር።" አሉና አይናቸውን ማክሲም ላይ አሳረፉት ። "የበሽተኞቻችን ምስጢር በኛና በእነርሱ መሀል ብቻ ተጠብቆ መቅረት ነበረበት ። ይውንና አሁን ባለቤትም በመሞታቸውና ጉዳዩም ለየት ያለ በመሆኑ ችግር የሚፈጥር አይመስለኝም ። እንግዲህ..." ንግግራቸውን እቋርጠው ተና ብለው ተራ በተራ ታኙን ።

"ሚስዝ ዳንቨርስ የተባለች ሴትዮ ከፉ በሽታ ነበር የተጠቃቸት ። ቶዮ ኤሰቲ" ብለው አዩናቸውን እንደገና ማሀደሩ ላይ አሳርፈው "አምን፡ ሴትዮዋ አሁን ከጠቀሳችሁት ቦን አንድ ማምንት ተደም ብላ እኤጋ መጥታ ራጂ ተንስታ ነበር ። በሁለተኛ ጊዜ የራጂውን ሙጢት ለማወት ነበር የመጣችው ። ፊልሙ እዚህ ባይኖርም ዝርዝር ሁኔታው ማሀደሯ ላይ በለ ሰፈረ ችግር አያፈጥርም ። ይገርማችኋል ፡ እየቆየ ሲሄድ የሴትዮዋ አነጋገን ወለል ብሎ ይታየኝ ጀመር ..."

"... አምን ትዝ ይለኛል ፡ ፊት ለፊቱ ቁማ የራጂውን ፊልም እንዳላያት እየጠየቀችኝ ነጣድ የለተም ይክተር ፡ እውነቱን ይንገሩኝ። ከሠን ሆን ነው ። በማይሠን ታላት እንዲሸነግሉኝ አልሻምና እቅጩን ይንገሩኝ፡ ያሏችኝን ምንኒዚም አልረሳውም ..."

ጸር ዳርኔሁ አብቅቶ የሚሉትን ብለው እንዲሸኙን የሁላችንም ምኞት በሠንም ደፍሮ ሠማቱን የሰነዘረ ግን አልነበረም ።

"... መቼም ድፍረቷን በጣም ነው ያደነቅኩት ። እንዳንድ በሽተኞች እንዲህ ናቸው ። ፊልሙ በሀሰት እንድናዕናናቸው አይፈል ጉም ። ይህችም ሴትዮ በድፍረት ንገረኝ አለችኝ ፡ ነገርኳት ። ፍንክች ልትል መስላቸው ? ቅንጣት ፍርሀት አላደረባትም ። 'ሞርማሬው ስለነበረኝ እምብዛም አያስደንግጠኝም' ብላ ሂጣቢን ከፍላ ሄደች" ካለ በኋላ ንግግራቸውን ገትተው ራሶን አጠፉት ።

አሠንሰ እኒህ ሽማግሌ ከማብሀት አልፈው ተንዛዙ አልኩና እኖ አሙጥቼ በሽታው ምን እንደነበረ ልጠያቅ ታጥቶኝ ነበር ።

"... በመሠረቱ ያሀን ያህል ህመም ባያሰማትም በሽታዋ ግን ውስጥ ውስጡን ስሩን እየሰደደ ነበር ። ቶዶ ጥናም ሆን ሌላ ህክምና ፈፅሞ ለያድናት ከማያችልበት ደረጃ ላይ ነበረች ። በህይወት ቆይታ ቢሆን ኖሮ

t.me/OLDBOOKSPDF

በልዩ ልዩ መድሃኒቶች ሀይወቷን ለማርዘም ይሞክር እንደሆነ እንጂ ተስፋም አልነበራት ።"

በመጨረሻው የዶክተሩ ንለፃ ያልተደናገጠ አልነበረም ። ክፍሉ ፀጥ ረጭ ከማለቱ የተንሣ የሚያሳው ሰእት ጎላ ብሎ ከመሰማቱም በላይ የሊጆቹ የደጅ ጨዋታ እንበርንበት ክፍል ውስጥ የሚካሄድ ይመስል ነበር።

ዶክተሩ ንለፃቸውን ቀጠሉ ። "ላይ ላዩን ስትታይ ፍፁም ጤነኛ ነበር የምትመስለው — በጣም ከመክሳቷ በስተቀር ። ከሳት ደግሞ በሴቶች ዘንድ የዘመኑ ፋሽን ስለሆነ የበሽታ ምልክት ላይሆን ይችላል ... በተጨማሪም ራጂውን እንዳየሁት ማነወርም የአተማመጥ ችግር ስለነበረ ረበት ልጅ የመውለድ ተስፋዋ የመነመነ ነበር። በመሠረቱ ይህ እንኳን ከደረባት የካንሰር በሽታ ጋር ምንም ግንኙነት አልነበረውም" በማለት ዶክተሩ ሠማባቸውን አጠቃለሉ።

ኮሎኔል ጀልያን ከመተመጫቸው ብድግ ብለው ዶክተሩን እየጨበ ጪቸው "ለሰጡን ማብራሪያ ከልብ እናመሰግናለን ። የዝርዝር ታሪኩን ቅጂ ቢሰጡን ደግሞ በጣም ሊጠቅመን ይችላል" አሉ ።

"ምን ገዶኝ ፡ እሰጣችኋለሁ" አሉ ዶክተር ቤከር ፈገግ እያሉ ።

ሁላችንም እንድ ላይ ብድግ አልን ። ደስታዬን እውስጤ ቸብሬ ዶክተሩን ጨበጥኋቸው ። ሌሎችም ተራ በተራ ጨብጠዋቸው ለመው ጣት ተዘጋጀን ። እስከ ዋናው በር ከሸኙን በኋላ ወደ ሎንዶን የሚያመራ ውን አቋራጭ መንገድ ጠቆሙን ። አመስግነን ተለየናቸው። እኔማ ከምስጋናም በላይ 'እኔና ማክሲም የእሀን ሰውዬ ውለታ እንደምን እንከፍለዋለን ?' የሚል ሠፃብ እሽሩሩ እያልኩ ነበር ወደ መኪናችን ያመራሁት ።

ወደ ዶክተሩ ቤት የሚያመራውን መንገድ ከዋናው ጎዳና ጋር ከሚያገናኘው ጠርዝ ላይ እንድ እግራም ባለዋሽንት ድልድዩ ላይ ተቀምጦ ያጫወተው የነበረ እንጀት የሚበላ ዜማ ዛሬም ከሀሊናዬ አልጠፋም ።

እንዴት ሆነ ብሎ ከንቱ ያጨንቃል ሰው
እርሱ የንባውን መልሶ ሲያፈርሰው ።
ፈራሽ ሥጋ ለብሶ ብዙን ገላ ይዞ

t.me/OLDBOOKSPDF

አንዱ ላንዱ አይተኛም ቂም በልቡ አርግዞ ።
ለእግሬ ለጠናዬ አልቅሺ አብቅቻለሁ
ጉሮሮዬ ቀርቶ ጢት ማታ አፈሟለሁ ።

ይላል አንድ እግራሙ ፡ በዋሽንቱ ጣልቃ ሲያቀነቅን ። በዚማው ተመስጨው ጆሮዬን የሰጠኋቸው ስንኞች ዜማቸውን እንድጠራጠረው አደረጉኝ ። ማን ፈትቶ ለቀቀብን ? አልኩኝ በልቤ ። መደናገጤ እንዳይታወቅብኝ ፊቴን መደኋላ አዞርኩት ። እንደኔ ሁሉ ሌሎች አጣጥመው እንዳይሰሙ ፡ በተለይ ያ ሰይጣን ፈቲል ግጥሞቹን ሰምቶ ሌላ የነገር ጉንጉን እንዳይሸርብ ቶሎ እንሂድ እያልኩ አጣድፋቸው ነበር ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ ሀያ አምስት

መኪናችን አጠገብ ለጥቂት ደቂቃዎች ዝም ብለን ቆምን ። ከሁላችንም በላይ የፈሪሐል ሁኔታ የተለየ ነበር ። ፈቱ ከመቅፅበት ጥቃርሻ ለብሶ ፡ እፉ ላይ የያዘውን ሲጋራ ማቀጣጠል ተስኖት እጁቹ ይንቀጠቀጣሉ ። ባለ ዋሽንቱ ንጥር ንጥር እያለ ወደኛ መጣ ። ባርኔጣውን አንስቶ እጅ ሲነሳን ማነሲም ሁለት ሺልንነሽ ረጠበው ። ወደነበረበት ተመልሶ ሴላ ዜማ ያንዶረቱር ገባ ።

ፈሪሐል እንገቱን ደፍቶ እይኖቹን በጣቶቹ በሚያፍተለትለው ሲጋራ ላይ ተነበሎ "ለመሆኑ ይሄ ካንሰር የሚሉት ጉድ የሚጋባ ነው ?" አለ ። ጥያቄው ለማን እንደተሰነዘረ ባይገባንም መልስ ከማንኛችንም አላገኘም። ኮሎኔል ጀልያን ብቻ ትከሻቸውን ሲነቀንቁ እየኋቸው ።

"ርብቃ እንዲህ ምስጢሯን ቀብራ ትቀበራለች ብዬ ከቶውንም አልገመትም አላውቅም" በማለት ተጠለ ፈሪሐል እንዳቀረቀረ "የሚገርም እኮ ነው ፡ ለዴኒ እንኳን ሳትነግራት ? አይ ርብቃ ! ካልጠፋ በሽታ እንቺን ካንሰር ይልከፍሽ ? እንቺን ? እህህ" አሰና ቀና ብሎ ካየን በኋላ "እንደ'ት ነው ጀል ? መጠጥ ብጠ አላሰኛችሁም ? እኔ ካለሱ ይህን ካንሰር የምትሉትን መአት ልረሳው አልችልም" አለን ።

መኪናውን ደንፋ ብሎ እይኖቹን በእጆቹ ጋረዳቸው ። ሚንቅላቱን ግራ ቀኝ ወዘወዘው ። መዲያው "ምነው ይህንን ቆሪጣ አፍህን ያዝ ብትሉልኝ ?" አለ ።

"ከዚህ ሁሉ እኛ ለቀንለት ብንሄድ አይበጅም ?" አለ ማክሲም

t.me/OLDBOOKSPDF

“መኪናህን አንተው ትነዳ ወይስ ጂልያን ይያዙልህ ?”

“ምን አለ አንድ አፍታ በሰላም ብትተዉኝ ? ዳሩ ፡ ነገሩ ምን ያህል ውስጤን እንደቦረቦረው እናንተ አይገባችሁ” አለ ፈቭል ድምፁን አጉልቶ ።

“ምንድነው ይህ ሁሉ ያዙኝ ልተቱኝ ? እረ ረጋ በል ፡ መጠጥ ካሻህ ገብተህ ይነጋገሩን ጠይቃቸው” አሉ ኮሎኔል ፍርጥም ብለው ።

“እኮ ፡ እናንተማ ምናችሁ ተነካ ? የአንጀታችሁ ደረሰ እንጂ !” አለ ፈቭል ማክሲምንና ኮሎኔልን እያየ ፡ የፈዝ ፈገግታውን እያሳየ ። “አንተት ለአንተት ተያይዛችሁ ለጤንነታችሁ መጨለጥ ነው ። ኮሎኔል ከእንግዲህ ሠላብ አይግባም ። ለሞለለት ሙለታ ማክሲም የወር ተለብሞን ይሰፍርለታል ።”

“እባክዎን ትተነው እንሂድ ። እርሱ እንደሆነ የያዘው አባዜ ነው የሚያስለፈልፈው ።” አሉ ኮሎኔል ጅሮንቻቸው እየቀሉ አፍንጫቸውም እየተንቀጠቀጠ ።

ሦስታችንም መኪናችን ላይ እንደተሳፈርን ኮሎኔል ጂልያን አንገታቸውን በመስኮት ብቅ አድርገው “ሰውዬው በጊዜ ቢትህ ገብተህ ብትተኛ ይሻልሃል ። በዝግታ መንዳቱን ትተህ እንዳሻኝ አከናንሉህ የምትል ከሆነ ደግሞ ሰው ትገድና ትቀፈዳዳለህ ። ደግሞ ለላ ነገር ፡

ከእንግዲህ በወረዳችን አካባቢ ዝር አላለው ብትል ሀግ በሰጠኝ ስልጣን እግር ተወርች አሳስረህ ፍዳህን ትቆጥራለህ ። ሰውን አስፈራርቶ ገንዘብ ለማግኘት መጣር ሙያ እንዳያመስልህ ፡ ዋጋህን ነው የምታገኘው” በማለት ፈቭልን አስጠነቀቁት ።

ፈቭል ከቆመበት ሳያንቀሳቅስ ጣቱን እየቀሰረ “ማክስ ረትቻለው ብለህ ትዘናና ይሆናል ። እኔ እንደሆን ፍትህን በማጓበት ዘዴ አግኝለው። ከንዴን ሳልንተራስ ፡ አንተን መቀመቅ ሳልክት አርፌ የምቀመጥ እንዳያመስልህ” አለ ።

ማክሲም መኪናውን ካስነሳ በኋላ “እሺ የኔ ወንድም ፡ ለላ የምታከለው ነገር የለህም ? የመጨረሻ እድልህ አውን ነውና ተንፍስህ ቢወጣልህ ይሻላል ብዬ ነው” አለው ።

“ግድ የለም ፡ ሂዱ አላቆማችሁም ። የምለውንና የምልበትን ቦታ

t.me/OLDBOOKSPDF

መች እጣሁት›ና'' አለ ፈቭል ፈገግ እያለ ። መኪናችን ጉዞ ሲጀመር ዞር ብዬ ሳየው እየተንከተከተ እጁን ያውለበልብልን ነበር ።

ምንም ሳንነጋገር ጥቂት ከተጓዝን በኋላ "ምንም ሊያደርግ አይችልም ። ያ ሁሉ ሳት ወዴ መሰላችሁ ? ሽንፈቱን መቀበል መሮት እኮ ነው ። ከእንግዲህ ቅንጣት ማስረጃ ሊያቀርብ ስለማይችል ዝንብዎን እሽ ሊል እይዛፍርም ። ፈሳም ሁላጅ !" አሉ ኮሎኔል መቀመጫቸው ላይ በኩራት ። ኮመንት ።

ተጥ ያለውን መንገድ ይዘን ስንጓዝ መሰላቸቱን ያስወግድልን የነበረው ኮሎኔል ጂልያን አልፎ አልፎ ጣል የሚያደርጓቸው አስተያየቶችና የሚሰነዝሯቸው ጥያቄዎች ነበሩ ።

"እሁን የሚጠብቀን ሥራ ባሬ ከዶክተሩ ያገኘነውን ማስረጃ ህዝቡ እንዲያውቀው ማድረግ ነው ። እየህ ፡ የባሬ ሰው የወሬ ሞራ ይዞ ማራገብ ነወጻል ። አሉባልታ ስንቱ ሆኗል ። ምን እንጠልጥሎ ከምን አትጫኜ እንደሚኑ እያታወቅምና ለክፉም ለደኅ መጠንቀቁ አይከፋም ።" አሉ ኮሎኔል ጂልያን ።

"እምን ልክ ነዎት" ሲል መለሰ ማክሲም

"ይህን ያህል የሚያሰጋ ነገር ይፈጠራል ብዬ ሳይሆን ነገሩን በተሰያየ ሠልኩ ማየቱ መልካም ነው ለማለት ነው ። እርስዎና ከሮውሌይ እዚያ ማንደርሌይ አካባቢ ያለውን ውኔታ ተከታተሉ ። የኬሪዝን በኔ ላይ ። የኔ ልጅ ከብዙዎች ጋር ማንኛንት ስላላት እርሷንም ስለ ነገሩ በደንብ አስረድቼ ብሰዓት በደንብ ልታሳምንልን ትችላለች ። በጋዜጠኞች በኩል ያለው እንኳን ይህን ያህል የሚያስቸግር አይሆንም ።"

"እሺ ፡ እንዳሉት ማድረግ ነው "

ለእይን ያዝ ማድረግ ሲጀምር ቅዱስ ዮሐንስ ጫካ ከሚባል ስፍራ ደረሰን ። ኮሎኔል ጂልያን እሀታቸው ቤት አርፈን እራት እንድንበላ ጠየቁን ። የእርሳቸው ፍላጐት ከሆነ ቢቆይና እኛ ብንሄድ እንደሚሻል አንዳንድ ምክንያቶችን አስደግፎ ማክሲም ነገራቸው ።

በዚሁ ተስማምተን ኮሎኔሉን ከእሀታቸው ቤት አደረስናቸው ። ላደረጉልን ሁሉ ልባዊ ምስጋናችንን አቀረብንላቸው ። እርሳቸው ደግሞ ለወደፊቱም በማንኛውም ረገድ ከጎናችን እንደማይለዩ በማረጋገጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

"... ቅድም እንዳልኳችሁ ያ ውርጋጥ ቀንዱ ስለተመታ አክትሞለታል፤ ወደፊት አላርፍ ብሎ ቢያስቸግራችሁ ወዲያውኑ እንድታስታውቁኝ" አሉ ኮሎኔል እቃቸውን ሰብስበው ከመኪናው እያወረዱ ።

"እስቲ እናንተም ለጊዜው የሰሞኑን ጭንቀታችሁን አራግፋችሁ ለመታደስ ወጣ ብላችሁ እረፍት ብታደርጉ መልካም ነው ። በአሁኑ ጊዜ ስዊዘርላንድ ቆንጆ የአየር ጠባይ ስላላት እዚያ ሳይሻላችሁ አይቀርም፤ ፈቭልን ብንተወው እንኳ አንዳንድ ነገረኞች የሚቆሰቁሱት ነገር አያጣ ይሆናል ። ሌላው ቀርቶ ያ ታብ የሚባለው ሰውዬ መጭጭ ካለ ችግር ሊፈጥር ይችል ይሆናልና ለጊዜው ሰወር ማለቱ ደግ ነው ። ይሄ ወሬኛ ሁሉ እናንተን ካላየ ነገሩንም ይረሳዋል— ከአይን የራቀ ከልብም ይርቃል፡ ይባል የለ ? ከነተረቱ" አሉና ተሰናብተውን ወደ ቤት ገቡ ።

ያ ሁሉ ሀሣብ የተራገፈለትን ፡ ያ ሁሉ ጭንቀት የተወገደለትን ጭንቅላቴን ወደ ኋላ አስደግፌ አይኖቼን ከደንኳቸው ። በመሄጃው ጉዞ ላይ ርብሽብሽ አድርጎኝ ለነበረው የሎንዶን ትርምስና ሁካታ ጆሮዬንም አልሰጠሁት ። እጄ ላይ ያረፈው የማክሲም እጅ ያጭረው የነበረ ሙቀት ብቻ—ይሰማኝ የነበረ ብቸኛ ስሜት ። መከራና ጣር ያጠየመውን፡ ወደ ድቀት ይመራን የነበረውን ህይወት አልፈን አዲስ ብሩህ ህይወት የምንመራበትን አዲሱን ምእራፍ እንዴት እንደ ምከፍተው አሰላስል ነበር ።

የመኪናው መቆም አይኖቼን ገልፈጡ ቀና ብዬ እንድቀመጥ ያድርገኝ እንጂ "የኔ ደካማ" የሚለው የማክሲም የለሆሳስ አገላለፅ ነበር ከሀሣብ አለም የመለሰኝ ። "እጅግ ከመዳከምሽ የተነሣ ልፍስፍስ አልሺብኝ አያደል ? በይ ተነሽ እስቲ ፡ እራታችንን ስንበላ እንደገና እንታደሳለን ። በዚያውም ለፍራንክ ልደውልለት" አለኝ ማክሲም በልዩ ሙዚቃዊ ቃና ።

ጭር ካለው ሆቴል እራታችንን አዘን ስንበላ "እራት በልተን መንገዳችን ላይ መኝታ ፈልገን እናድራለን ። ከዚያ ማለዳ ተነስተን ወደ ማንደርሌይ መንዝ ነው" አለኝ ማክሲም ።

ድካማችንን ለማስወገድና ለመንገዱ እንዲረዳን የጨበጥነውን መለኪያ እየተጎነጨን ጨዋታ ጀመርን ። "ለመሆኑ ጁልያን ስለ ነገሩ

t.me/OLDBOOKSPDF

ምን ያህል ጥርጣሬ እንዳላቸው ታውቂያለሽ?" ሲል ለሰነዘረልኝ ጥያቄ ምላሹን ሳልሰጠው ዝም ብለው "በደንብ ነው የሚያውቁት" አለኝ እርሱ እራሱ መልሶ ።

"ታዲያ ቢያውቁስ ፡ አሳልፈው የሚሰጡህ አይመስለኝም" አልኩት

"አይ ፡ እርሱን እንኳን አያደርጉትም"

ማክሲም መጠጡ እንዲደገምለት አዘዘና እንዴ ከተጎነጨለት በኋላ "አየሽ" አለኝ የተጎነጨውን እያጣጣመ "ያች ምስጥ ሆን ብላ ነበር የዋሸችኝ ማለት ነው ። እድሜዋ አጭር መሆኑን አውቃ ሆን ብላ አበሳጭታኝ እንድገድላት ነበር ማለት ነው ፍላጎቷ ። በሞት አፋፍ ላይ ሁና እንዲያ ከትከት ብላ መሳቋለምን እንደሆነ አሁን ነው የተከሰተልኝ ።"

በዚህ ነጥብ ጥቂት ከተጎጋገርን በኋላ ለፍራንክ ልደውልለት ብሎኝ ሄደ ። ያለፈውንና የወደፊቱን ጉዟችንን በማነፃፀር በሀሳብ ሰሌዳ ላይ እቅዴን ስንድፍ አስሩ ደቂቃዎች እንዴት እንዳለፉ አላወቅኩም ።

"ደውለህ መጣህ እንዴ ?" አልኩት ማክሲምን እንደመባነን እያለኝ ። "ለመሆኑ ፍራንክ እንዴት ነው ?"

"ደህና ነው ። ከቀኑ አስር ሰአት ጀምሮ ቢሮው ውስጥ ቁጭ ብሎ ሲጠብቅ ነበር ። ነገሩን ሁሉ ሳስረዳው ከመጠን ቦላይ ነው የፈነደቀው ።" አለና ንግግሩን ለአፍታ አቋርጦ ባሻገር ይመለከት ጀመር ። ወዲያው ልዩ አስተያየት የሚነበብባቸው አይኖቹን ወደኔ መልሶ "ምን እባክሽ ፡ ያቺ መተተኛ አሮጊት ደግሞ ቤቱን ለታ ጠፉች አሉ" አለኝ ።

"ማን ? ሚስዝ ዳንቨርስ ?" አልኩት በችኮላ

"እሀሳ ! ለማንም ሳትናገር ቀኑን ሙሉ እቃዋን ስታዘጋጅ ውላ ማምሻውን ንዥን ጠቅልላ ሹልክ ብላ ወጣች ነው የሚለኝ ። ከመሄዷ አስቀድማ ማን ምን እንዳላት አይታወቅም እንጂ የሆነ ሰው ራቅ ካለ ስፍራ ቴሌፎን ደውሎላት ነበር ነው የሚባለው ። አገር ምድሩን ቢያስሱ ደብዛዋን ሊያገኙ አልቻሉም ።"

"ታዲያ ምኑ ነው የሚያስጨንቅህ ? ባቂላ አለቀ ቢሉት ፡ ፈስ ቀለለ አለ አሉ ሰውዬው ። እንዲያውም ደህና ገላገለችን እንጂ ። እኛው እራሳችን ማባረራችን ይቀር ነበር እንዴ ? እርሷም ይህንኑ ጠርጥራ ይሆናል ሳይቀድመኝ ልቅደም ያለችው ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"የለም ፡ የለም እኔ አላማረኝም" አለ ማክሲም ጭንቅላቱን እየወዘወዘ

"ምን ልታደርግ ትችላለች ብለህ ? እንደገባኝ ከሆነ ያ ደወለላት የተባለው ሰውዬ ፈቭል መሆን አለበት ። ዶክተሩ የሰጡንን ማስረጃ ፡ ከዚያ በኋላ ኮሎኔል ጄልያን እንዴት እንዳስጠነቀቁት ሳይነግራት አይቀርም ። መቼም ይህን ሁሉ ሰምተው በህይወታቸው ቆርጠው ካልሆነ በቀር እንደገና አስፈራርተው ገንዘብ እናገኛለን ብለው የሚደፋፈሩ አይመስለኝም ።"

"እኔ የማስፈራራቱ ነገር አይደለም ያሳሰበኝ "

"ታዲያ ምኑ ነው የኔ ፍቅር ? ለማንኛውም ጉዳይ ኮሎኔል ጄልያን አስታውቁኝ ብለውናል ። በተረፈ ከዚያ መአት ለሰወረን ጌታ ተንበርክክን ምስጋናችንን ማቅረብ እንጂ ምን የሚያሳስበን ነገር ይኖራል ?"

ማክሲም መልስ ሳይሰጠኝ እንደተከዘ ቀረ ። ታርቆት የነበረ የእፎይታና የእርካታ ስሜት እንዲያ ከመቅፅበት በኖ ፡ ርቆት የነበረ ጭንቀትና ውጥረት እንደገና ይዳስሰው ገባ ። እኔ ከእርሱ በተሻለ ሁኔታ ረጋ ብዬና ተጠናክሬ ስገኝ የእርሱ ድንገት እንደዚያ መሆን ጭርሱን ሊገባኝ አልቻለም ። ለእኔ የሚስዝ ዳንቨርስ መሄድ ትልቅ ግልግል ነው ። በዚያን ወቅት ይታየኝ የነበረ ከዚያ እንደ ጣር መንፈስ አካሌንና አእምሮዬን ገንዞ ሲያንገላታኝ ከነበረው መልኳና ግብሯ ተገላግዬ በራሴ ቤት አዛኟና ፈላጭ ቆራጭ የመሆኔ እድል መከፈቱ ነበር ። ከእንግዲህ በቤቱ ተደላድዬ ስኖር ፡ እኔና ማክሲም ልጆች ወልደን ተንከባከበን እንዴት እንደምናሳድጋቸው ነበር እኔ የማወጣውና የማወርደው ።

ማክሲም ቡና አዞ ከጠጣ በኋላ ሺጣቡን ከፍሎ እንውጣ አለኝ ። እንደኔ ከሆነ ግን ብንቆይ ፍታዬ ነበር ። የከረምንበትን ጭንቀት አራግፈን ፡ የወደፊት ህይወታችንን ለመንደፍ ከዚያ የተሻለ ስፍራ የምናገኝ አልመሰለኝም ። ወጥታውና ምቾቱ ልቤን ከፉኛ ነበር ያሸፈተው ። ግና ዳሩ ሳልወድ የግዴን ተነሳሁ—የማክሲምን ፍታድ ለመሙላት ብቻ ።

ወደ መኪናችን ስንጠጋ "ስሚ እንጂ ፡ የመኪናውን የኋላ መቀመጫ ባስተካክልልሽ መኪናው እየተንቀሳቀሰ መተኛት አይመችሽ

t.me/OLDBOOKSPDF

ይሆን ? ምን ይመስልሻል ?" ሲል ጠየቀኝ ።

"መንገዳችንን ልንቀጥል ? ግን ለምን ? ሦቱል ፈልገን አድረን ጥዋት እንድንነሳ አልነበረም እንዴ የተስማማነው ?"

"እሱማ ነበር ። ግን ልቤ አልረጋ ስላለኝ ሌሊቱን ተጉዘን ቶሎ ቤታችን ለመድረስ ስለፈለግኩ ነው ። የኋላው መቀመጫ ለመኝታ አያመችሽ ይሆን እንዴ ?"

"እኔ እንኳን ግድ አልነበረኝም ። አንተን ይደክምሃል ፡ ይሀን ሁሉ መንገድ ብቻህን እያሽከረከርክ እንዴት ትዘልቀዋለህ ? ማለቴ ነው ።"

"ለኔ አታስቢ ፡ ድካሙን እቋቋመዋለሁ ። አየሽ ፡ አሁን ለሁለት ሩብ ጉዳይ ነው ። በደንብ ከተጓዝን መንገዱም ትራፊክ ስለማይበዛበት ከምሽቱ ስምንት ሰዓት ተኩል ግድም እንገባለን" አለኝ ። ይዘናቸው የነበሩትን ልብሶች ሁሉ እንደሚሆን አመቻችቶ አስተካከለልኝ ። አስተኛኝ ። አለበሰኝ። ብርድ እንዳይነካኝ ዙሪያውን ባገኘው ጨርቅ ወታተፈው ። እግሮቼን ሰብስቢ ፡ ጉልበቶቼን ታቅፌ ጋደም አልኩ ።

"ትራሱ አነሰሽ መሰለኝ ። ቆይ ፡ ይሀን ልጨምርልሽ" ብሎ ሞንትላቱን በእጁ ከፍ አደረገልኝ ። ቀና ብዬ ሳየው እላዩ ላይ ከሸሚዝ ሌላ አልነበረም ። ኮቱን ነበር አጣጥፎ የሰጠኝ ።

"ምነው ማክሲምዬ ? ሽረ አበሳሽው ።" አልኩት ያጣጠፈውን ኮት እየዘረጋጋሁ ። ለኔ ያለ የሌለውን ደራርበህልኝ አንተ ሞራሽን እርቃንህን ልትሄድ ? ይህንንስ አላደርገውም" ብዬ ኮቱን ትከሻው ላይ ጣል አደረግኩለት ። አይሆንም ብሎ ሲሞግተኝ "እንግዲያው እንቢ ካልከኝ አልተኛም ፡ ካንተው ጋር ቁሜ ብዬ እሄዳለሁ" ስለው ነበር በጅ ያለኝ ።

እንደገና ሁሉን አመቻችቶልኝ "እንዴት ነው ? መኝታው ተስማማሽ?" አለኝ

"በጣም ነው የተስማማኝ ። በደንብ ነው የምተኛው ። ያንተ መድከም አሳስቦኝ እንጂ በጊዜ ቤታችን መድረሳችንን ወድጄዋለሁ" አልኩት ከሙሉ ፈገግታ ጋር ።

መንገድ እንደገባን አይኖቼን ከደን አደረግኳቸው ። ሽለብታ ያላማረው አእምሮዬ ደግሞ እዚህም እዚያ እየረገጠ ያለፉ ትዝታዎችን ምስሎች በረቂቁ ሰሌዳው ላይ እየደረደረ ያስነብበኝ ገባ ። ከሞንቴ ካርሎ

t.me/OLDBOOKSPDF

እስከ ማንደርሌይ ፡ ከኬሪዝ እስከ ሎንዶን ፡ ከፍስሐ ሽለቆ እስከ ባሀሩ ዳርቻ እየወሳሰደ ይመልሰኛል ። አንዴ ሚስዝ ቫን ሁፐርን እንደገና ሚስዝ ዳንቨርስን ፡ አንዴ ጃስፐርን እንደገና ቤንን ፡ አንዴ ኮሎኔል ጁልያንን እንደገና ዶክተር ቤከርን ፡ አንዴ ፌቭልን እንደገና ታብን ፡ ሌሎች ሌሎችንም ምስላቸውን ከነግብራቸው እየቀረፀ ያሳየኛል ። እንዲሁ በቅዠት ማእበል እየዋዠቅሁ እያሸለበኝና እያባነነኝ ፡ ስገላበጥ ቆየሁ — በጎኔ በጀርባዬ ።

ቁርጥራጭ ሀልሞች በሚፈራረቁበት በዚህ ሰመመን መሰል እንቅልፌ መሃል እንደገና ሚስዝ ዳንቨርስን አየኋት ። ጥቁር በጥቁር ለብሳ እቤታችን ደረጃ ላይ ቁማለች ። እየሮጥኩ ደረጃውን ስወጣ ተሰወረች ብኝ። የዋጣትን አጣሁ ። ዞር ስል ከአንድ መስኮት በስተጀርባ ቁማ ትገለፍጣለች ። 'ኔይ ውረጂ ፡ አንቺ መተተኛ አሮጊት !' ብዬ ስጮህ እንደገና ተሰወረችብኝ ።

ብንን ብዬ ተነሳሁ ። የት እንደነበርኩ ሲከሰትልኝ "ማክሲም ፡ ስንት ሰአት ሆነ ?" ብዬ ጠየቅኩት ።

ማክሲም ዞር ብሎ ሲያየኝ እጅግ ከመዳከሙ የተነሣ እንዲያ ጠውልጎ ሳየው በጣም አሳዘነኝ ። "አምስት ተኩል ነው ። አይዞሽ ፡ መንገዱን አጋምሰነዋል ። እስቲ ጥቂት ለመተኛት ሞክሪ" አለኝ ለዘብ ባለ አነጋገር ።

"ውሀ ጠማኝ ፡ ማክሲምዬ" ስለው እፊታቱን ከነበረው ከተማ እንደሚያቆምልኝ ነገረኝ ።

ከከተማው ገብተን መኪናችንን ከአንድ ጋራዥ አቆምን ። ውሀ እንዲያፈላልግልን የጠየቅነው ባለ ጋራዡ ባለቤቱ ግና እንዳልተኛችና ሻይ እንደሚያስፈላልን ነገረን ። ከመኪናው እንደወረድን ተኮማትሮ የቆየውን ሰውነቱን ለማፍታታት ጋራዡ ውስጥ ወዲያና ወዲህ እንጎራደድ ገባሁ ። የብርዱ ነገር አይነሳ ። እያሻጨ ይነፍስ የነበረው ሀይለኛ ነፋስ የጋራዡን ቆርቆሮ ክፉኛ ያርገበግበው ነበር ። አጥንቴን ዘልቆ የገባው ብርድ ቢያንዘፈዝፈኝ ኩቴን እስከ አንጉቱ ቆልፌ ከማክሲም ጉያ ገብቼ ተሸጎጥኩ ። በደንብ ተቀበለኝ — እቅፍ ድግፍ አድርጎ ።

እዚያው እንደቆምን ከባለ ጋራዡ ጋር ስለ ወቅቱ የአየር ሁኔታ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስንጨዋወት ሳለ የሰውዬው ባለቤት ሻይውን አፍልታ አመጣችልን ። መሪር ቢልም ስግብግብ ብዬ ጠጣሁት ። ጋባጮቻችንን ከልብ አመስግነን ስንሰናበታቸው መንፈቀ ሌሊት ተቃርቦ ነበር ።

ቀደም ሲል ከነበርኩበት የኋላ መቀመጫ ላይ ተመቻችቼ ጋደም አልኩ ። አይን ስጋዬ ሲከደን አይን ሀሊናዬ ተከፈተ ። እዝነ ልቦናዬም ስራ አልፈታም ። አእምሮዬ ልዩ ልዩ ምስሎችንና ድምፆችን እያስተናገደ ይቀልበኛል ። የማልዳስሰው ሀሣብ ፡ የማልረግጠው ስፍራ አልነበረም ። የፍስሐ ሽለቆን ማየት ፈለግኩና ወደዚያ ብሄድ የሚረብሽ ሁኔታ ነበር የገጠመኝ ። ዙሪያዬን ብቃኝ የወትሮውን ፍስሐ ሽለቆ የሚመስል ነገር አልታይሽ አለኝ ። ስፍራውን ዳሞ ውጦታል። ለዛውና ውበቱ ተገፎ የሚያስጠላ ቁጥቋጦ ለብሷል ። የአስፈሪ አራዊት መፈንጫ ሆኗል ። እኒያ በውበታቸውና በመአዛቸው ልብን ያሸፍቱ የነበሩ የማንደርሌይ መናፈሻዎች ከሰው ቁጠት በላይ በወጡ ልዩ ልዩ ተክሎች ተሸፍነዋል ። ብንን አልኩና እላዬ ላይ የነበረውን ልብስ አሸቀንጥሬ ጥዬው "ማክሲም ! ማክሲም !" ብዬ ጮህኩ ።

"ምነው ? አይዞሽ ፡ አብራሽ እኮ ነው ያለሁት" አላኝ ።

"ሀ ሀ ል ምኦ አይቼ" አልኩት ትንፋሽ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ።

"ምንድነው ያየሽው ?"

"እኔ እ ንጂ ፡ እ ንጂ"

ወዲያው እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ወሰደኝ ። ሀልሙም አልቀረልኝ። ማንደርሌይ ውስጥ ከእንግዳ መቀበያ ክፍል ቁጭ ብዬ ይብዳቤ እፅፋለሁ ። የሣኩትን መለስ ብዬ ስመረምረው አጣጣሉ የኔ አልመስልሽ አለኝ ። ባሰፈርኳቸው ፊደላት ምትክ ወረቀቱን የወረሩት ዘመም ፡ ቆልመም ያሉት ፊደላት ናቸው ። ብድግ ብዬ ወደ መስተዋቱ አመራሁ ። የኔን ምስል ሳይሆን የሌላ ሰውን ምስል ነው ያየሁት ። ጥቁር ሐር ወጉሯ ግማሽ ፊቷን የሸፈናት መልከ መልካም ሴት አፈጠጠችብኝ ። ከናፍሯን ቀስ በቀስ አላቃ ትስትብኝ ጀመር ። እርሷ እዚያው እንደተቀመጠች አንድ ሰው ብቅ ሲል ታየኝ ። ማበጠሪያ ይዞ ወደ እርሷ ሲቀርብ ነበር ማንነቱ የተከሰተልኝ ። 'ማክሲም ? ምን ልትሆን ?' አልኩት ከራሴ አልፎ በማይሰማ ድምፅ ። ትከሻዋ ላይ የተዘናፈለውን ወጉሯን ይዞ ሲያበጥርላት አይኔን ማመን ተሳነኝ ። ማበጠሪያው በወረደበት ቁጥር እንደ እባብ

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚጥመለመለውን ወጉሯን እያሻሸ አይኑም ጥርሱም ሲስቅ ሳየው ልብ ወረደኝ ። እንጂ ስር ተሸጉጦ ወጉሯን መልበስ ሲጀምር ግን የሚከተለውን ለማየት ወኔውን አጣሁ ። ትእግስቱም አይሆንም ብሎኝ አላንኖ አስነሳኝ ።

"የለም ፡ በፍፁም" ብዬ ጨኸቱን ለቀቅኩት "ስዊዘርላንድ መሄድ አለብን ። ኮሎኔል ጁልያንም ስዊዘርላንድ መሄድ አለባችሁ ነው ያሉት"

"ምንድነው ? ምን ሆንሽ የኔ አካል ?" አለኝ ማክሲም ፊቱን እየደባበሰ ። ተነስቼ ተቀመጥኩና "እኔ እንጃ ፡ በፍፁም መተኛት አልቻልኩም" አልኩት ። "እንደ ፡ በደንብ ተኝተሻል እኮ ፡ ቢያንስ ለሁለት ሰአት ያህል ተኝተሻል ። አውን ይኸውልሽ ስምንት ከሩብ ሆኗል። መንገዳችንም እየተገባደደ ነው ።" አለ ማክሲም ።

ማክሲም ለሁለት ሰአት ያህል ተኝተሻል ይበለኝ እንጂ ለሩብ ሰአት እንኳን እንቅልፍ የወሰደኝ አልመሰለኝም ። ህልምና እውን ቅብብሎሽ ሲጫወቱብኝ አይደለ እንዴ የቆየሁት !

ቀሪውን መንገድ ከማክሲም አጠገብ ተቀምጬ መጓዙን መርጬ ወደፊት ሄድኩ ። ብርዱ ብሶበታል ። ድድቅ ጨለማ ነው ። ከዋክብቱ ወዴት እንደገቡ ሊገባኝ አልቻለም ። ሰማዩ ግርማ ሞገሱ ተገፏል ።

"ስንት ሰአት ሆኗል ነበር ያልከኝ?" ስል ጠየቅኩት ማክሲምን ፡ እጄን ጉልበቱ ላይ ጣል አድርጌ ።

"ስምንት ሰዓት ከሀያ" አለኝ ።

"አየኸው ማክሲምዬ ? እዚያ ማዶ ከኮረብታዎች ባሻገር ጎህ እየቀደደ አይመስልም ? በምንም አይነት ሊሆን አይችልም ። ሰአቱ ገና ነዋ" አልኩት ።

"አቅጣጫውን እኮ ተሳስተሻል ። አውን የምታሳዪኝ ወደ ምእራብ ነው ። ጎህ ደግሞ ከመቼ ወዲህ ነው በምእራብ በኩል መቅደድ የጀመረው? አይ ግድ የለሽም ፡ ገና ከእንቅልፍሽ አልነቃሽም" አለኝ ማክሲም ፈገግ ብሎ ።

"አይ...አይደለም ። አቅጣጫውም አልጠፋኝም ። ገርሞኝ ነው እንጂ፡ የሚገርም አይደለም ?"

ማክሲም መልስ አልሰጠኝም ። ፈገግታው ቀስ በቀስ እየሸሸው ፡ ፊቱ ሲቀያየር ታየኝ ። አይኔን እንደገና ወደ ሰማዩ ብሰደው ይበልጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

እየቀላ ፡ የቅላት ክልሉ ያበልጥ እየሰፋ ያሄዳል ። የማክሲም ገፅታ እንዲያ ቀዘቃዛ ፅልመት መልበሱ አስደነገጠኝ ።

"ምነው የኔ ጌታ ? ምን ሆንክ ?" አልኩት ።

ለመስማቱ ባልጠራጠርም ለዝምታው ግን ተጨነቅኩ ። መኪናው ፍጥነቱን ከመጠን በላይ ጨመረ ምድሩን ለቆ አየሩን ለመቅዘፍ የታገለ ያመስል ። ልቤም ትርታውን አሳደገ ቅኝቱን ከመኪናው ፍጥነት ጋር ለማቀናጀት የሚጣጣር አይነት ። አተበቱን ራት ብለነው ሚዳውን ገጠምነው ። የማንያርሉያ መንገድ ከፈታችን ተንጣሏል ። ጨረቃ ብርሃኗን የንፈገችው ጎዳና ጨለማ መሰለ ።

በአካባቢያችን የተዘረጋው ሰማይ እንደ ጠቆረ ነው ። አድማስን ያለበሰው ሰማይ ግን ተልቷል ። ደም የተረጨበት ያመስላል ። እየተረብን በሄድን ቁጥር ሞት ያለው ንፋስ እያነነፈንፈ ያመጣው አመድ አይናችንን ያንርድ ገባ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ይህ ፊቸል የሚሉት አንግዳ ማነው ? ምንስ ፍለጋ መጣ ? መምጣቱን ማክሲም እንዳያውቅበት የፈለገው ለምንድ ነው ? በርግጥ ብጠየቅኝ መሠረት ሳለዉ ናገር ቃል ገብቻለ [illegible] ቃሌን አጠብቃለሁ ። ሚስጊ ትንሽርስ ቻግር ላይ [illegible] አልሻም ። ማክሲምስ ላምን ይጨነቅ ? ግን ይህ [illegible] ሆንቱ ለምን ለስፈለገ ?

[illegible] አንዲ ማክሲም ፡ ድኣሬሽ ጠጦ እንዳላበቀ ህፃና [illegible]
[illegible] ምን እንዳደርገሽ ነው የምትፈልጊው "
[illegible] ሁሉ ሚስተቻግ [illegible] እንደሚያደርጓቸው
[illegible]
[illegible] ጥሺ ?"
[illegible] ፍላጡን [illegible] ጣው [illegible]
[illegible] ሁተቀሳ [illegible] ምን ሽለ [illegible] ?"
[illegible] ደለም [illegible]"
[illegible] እንኳን ..."

[illegible] ነው [illegible] ጥብቀጦ ይሆን [illegible] ደምሮ [illegible] እኮ ነው ። [illegible] ተነለልኝ [illegible] ሰይሁት [illegible] ይገና [illegible] ሰስመኝ [illegible] እንፊፍኝ ...
[illegible] ባፍናፍን [illegible] ላላቆቀና [illegible] ለለ ። [illegible] ለትተይም ማለቱ [illegible] እንደሆ [illegible] ሊዜው [illegible] ቀይምነው ሰንለ [illegible] ?

[illegible]

ዋጋ ብር ፰፡፱፱

t.me/OLDBOOKSPDF